

# ከመጋቢት እስከ መጋቢት

የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ክቡር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ከመጋቢት 24 ቀን 2011 ዓ.ም. እስከ መጋቢት 24 ቀን 2012 ዓ.ም. ያደረጓቸው ንግግሮች እና ያስተላለፏቸው መልእክቶች

# ከመጋቢት እስከ መጋቢት

የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ክቡር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)
ከመጋቢት 24 ቀን 2011 ዓ.ም. እስከ መጋቢት 24 ቀን 2012
ዓ.ም. ያደረጓቸው ንግግሮች እና ያስተላለፏቸው መልእክቶች

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት

የካቲት
፳፻፲፫
ዓ.ም. ታተመ

**ቅፅ ፪ • Vol 2**

**የዚህ መጽሐፍ ገቢ ለበጎ
አድራጎት የሚውል ነው።**

ISBN 978-99944-3-128-1
Copyright © 2020 FDRE Office of the Prime Minister

የካቲት ፳፻፲፫ ዓ.ም. ታተመ

# ማውጫ

**ቀዳሚ ቃል**

**ንግግሮች: አማርኛ**

የአትሌቶች የምስጋና መርሐ ግብር ንግግር 1
የግብርና ግብአት ማሻሻል ስብሰባ ንግግር 10
የሃምሊን ሆስፒታል 60ኛ ዓመት የምሥረታ በዓል ንግግር 18
የሕዝበ ሙስሊሙ አንድነት የተበሠረበት ሥነ ሥርዓት ንግግር 22
የኢኖቬሽን ሳምንት መዝጊያ ንግግር 28
የደሴ ነዋሪዎች ውይይት ንግግር 38
የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የምረቃ በዓል ንግግር 42
የአዲስ አበባ የወንዝ ዳርቻ ልማት ፕሮጀክት ማስጀመሪያ ንግግር 58
የአንድነት ፓርክ ምረቃ ሥነ ሥርዓት ንግግር 63
የ"መደመር" መጽሐፍ ምረቃ ንግግር 70
የ"ሰላም መቶ በመቶ ያሸልማል" መርሐ ግብር ንግግር 87



የብልጽግና ፓርቲን አቋምና ምኞት የሚገልጥ ንግግር 90
የብልጽግና ፓርቲ ውሕደት ሥነ ሥርዓት ንግግር 93
ከኖቤል ሽልማት መልስ የተደረገው አቀባበል ንግግር 100
ከኖቤል ሽልማት መልስ የኢዮቤልዩ ቤተ መንግሥት ንግግር 104
ኢትዮጵያ የመጀመሪያዋን ሳተላይት ያመጠቀችበት ዕለት ንግግር 109
"ለሁላችንም የምትመች ኢትዮጵያን በጋራ እንገንባ" ዝግጅት ንግግር 111
"የጋራ የድል ምዕራፍ ማክበር" የምስጋና መርሐ ግብር ንግግር 123
"የወዳጅነት አደባባይ"ን የሥራ ክንውን ጉብኝት ንግግር 127
የኮንስትራክሽን ዘርፍ የንቅናቄ መድረክ ንግግር 130
የ"በጎነት ወደ ብልጽግና" መድረክ ንግግር 140
የኤሌክትሮኒክስ የአንድ መስኮት አገልግሎት ፕሮጀክት መጀመር ማብሠሪያ ንግግር 155
የገና በዓል ዕለት ለአረጋውያን፣ ለአካል ጉዳተኞች እና ለአዳጊዎች ያደረጉት የምሳ ግብዣ ንግግር 161
በደቡብ አፍሪካ ለሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ያደረጉት ንግግር 163
የጄነራል መኮንኖች ሹመትና ማዕረግ ማልበስ ንግግር 178
የኢትዮጵያ የሕዳሴ ግድብ ጉብኝት ንግግር 184

የፌደራል እና የትራፊክ ፖሊስ የተደረገ የምስጋና ሥነ ሥርዓት ንግግር 188

የሀላባ ዞን ንግግር 195

የተባበሩት ዐረብ ኢሚሬትስ ያደረጉት ንግግር 205


## ንግግሮች: እንግሊዘኛ


Belt and Road Forum for International Cooperation 219

Sudanese Agreement for Peace 224

TICAD7 Special Conference on Peace and Stability in the Horn 230

Russia-Africa Sochi Summit 234

Electronic World Trade Platform Launch 238

Speech during visit to Israel 241

Homegrown Economic Reform Discussion Opening Address 246

13th Ordinary Session of the IGAD Assembly of Heads of State and Government 251

Nobel Peace Prize 2019 Acceptance Lecture 257

Speech at Equatorial Guinea 270

ANC 8th Anniversary Speech 273

Speech for Ethiopian Diaspora in South Africa 280

33rd AU Summit Banquet Dinner 295


## መግለጫዎች እና መልእክቶች: አማርኛ


የጨምበላላ በዓል መልእክት 305

የ1440ኛው ዓመተ ሒጅራ ዒድ አል ፈጥር በዓል መልእክት 308

የብሔራዊ የችግኝ ተከላ ቀን መልእክት 313

ለአረንጓዴ አሻራ ተሳታፊዎች ያስተላለፉት መልእክት 318

የ1440ኛው ዓመተ ሒጅራ የኢድ አል አድሐ በዓል መልእክት 323

የአሸንዳ /ሻደይ/ አሸንድዬ/ ሶለል መልእክት 330

ለከፍተኛ ትምህርት ተማሪዎች ያስተላለፉት መልእክት 334

የመስቀልን በዓል መልእክት 340

የእሬቻን በዓል መልእክት 347

በዜጎች ሕይወት ማለፍ እና በንብረታቸው መውደም በተሰማቸው ሐዘን ያስተላለፉት መልእክት 350

የመውሊድ በዓል መልእክት 353

የብልጽግና ፓርቲን ውሕደት መልእክት 357

የብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በዓል መልእክት 360

የገና በዓል መልእክት 364

የጥምቀት በዓል መልእክት 368

## መግለጫዎች እና መልእክቶች: እንግሊዘኛ

Message to the people and Government of Eritrea on the occasion of Independence Day 375

Message for Christmas 377

## ንግግሮች: ኦሮምኛ

Ergaa Ayaana Irreechaa 381

Ergaa Ayyaana Qillee 383

## ንግግሮች: ትግርኛ

መልእኽቲ መዓልቲ ሰምኣታት ትግራይ 399




# ቀዳሚ ቃል

የሀገር መሪዎች ንግግሮች እና መልእክቶች መሪዎቹ በተለያየ መንገድ እና በልዩ ሁናቴ ስለ ሀገራቸው በሚኖራቸው መረጃ እና ሕልም ላይ የተመረኮዙ ናቸው። ንግግሮቹ እና መልእክቶቹ የሚቀርቡትም በሚያስተዳድሯት ሀገር ውስጥ በሚከሠቱ ዐበይት ሁነቶች አካባቢ ነው። ይህም የየጊዜውን የሀገር መልከ ገልጦ ለማየት ለሚፈልግ ሁሉ ቁልፍ ያቀብላሉ። የመሪዎች መልእክቶች በአንድ ተሰንደው የመገኘት ጠቀሜታ ከመጋቢት እስከ መጋቢት በሚል ታትሞ የነበረው ቀዳሚ ቅጽ በሰጠው አገልግሎት ታይቷል።

ይህን አብነት በመከተልም ከመጋቢት እስከ መጋቢት ሁለተኛው ቅጽ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት ተዘጋጅቷል።

ይህ ቅጽ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ በርእሰ መንግሥትነት ሀገራችንን መምራት ከጀመሩበት ከመጋቢት 2010 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ቀጣዩ መጋቢት 2011 ዓ.ም በተለያዩ ዐበይት ሁነቶች ያደረጉዋቸውን ንግግሮች እና ያስተላለፉዋቸውን መልእክቶች ይዞ የታተመውን ቀዳሚ ቅጽ የተከተለ ነው። በተከታይነቱም ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ በሁለተኛው ዓመት የሥራ ዘመናቸው ከመጋቢት 2011 እስከ መጋቢት 2012 ዓ.ም ያደረጉዋቸውን ዐበይት ንግግሮች እና ያስተላለፉዋቸውን ዋና ዋና መልእክቶች ያካትታል።

የክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ሁለተኛ የሥራ ዘመን ጠቅላይ ሚኒስትሩ በኢትዮጵያ ሀገራችን የመጀመሪያውን የኖቤል የሰላም ሽልማት ያገኙበት፤ ታላላቅ የሀገር ፕሮጀክቶች በአስደናቂ ፍጥነት እና ጥራት የተጠናቀቁበት እና ሌሎች ግዙፍ ሥራዎች የተጀመሩበት፤ የሕዝበ ሙስሊሙ

አንድነት የተበሠረበት፤ የአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ ግብር በአስደናቂ መነሣሣት የተገበረበት፤ ወዘተ ዘመን ነበር። ዘመኑ የተለያዩ ሀገራዊ እና ዓለም አቀፋዊ ጉዳዮችም ለሀገራችን ፈተና ደቅነው እንደየባህሪያቸው ምላሽ የተሰጠበትም ዘመን ነው። በመሆኑም እነዚህን እና ሌሎች ዋና ዋና ሁነቶችን በማስመልከት ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትሩ በዘመኑ ያደረጉዋቸው ንግግሮች እና ያስተላለፉዋቸው መልእክቶች በዚህ ቅጽ ቀርበዋል።

ከመልእክቶቹ እና ንግግሮቹ 46 ያህሉ በአማርኛ፤ 2 በአፋን ኦሮሞ፤ 1 በትግርኛ፤ 15 ያህሉ ደግሞ በእንግሊዝኛ ቋንቋዎች የተላለፉ ናቸው።

**መልካም ንባብ።**



# ከመጋቢት እስከ መጋቢት

ንግግሮች

## አማርኛ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት

የካቲት
፳፻፲፫
ዓ.ም. ታተመ



# የአትሌቶች የምስጋና መርሐ ግብር ንግግር

ሚያዝያ 2/2011 ዓ.ም.

**ክብርት አምባሳደር ሣህለ ወርቅ ዘውዴ የኢፌዴሪ ፕሬዝዳንት፣**
**ክብርት ኮሎኔል ደራርቱ ቱሉ፤ የአትሌቲክስ ፌዴሬሽን ፕሬዝዳንት፣**
**በ43ኛው አገር አቋራጭ ውድድር በመዘጋጀት በመሳተፍ በማሸነፍ ኮርታችሁ ያኮራችሁን አትሌቶች፣**

እንኳን ደስ አላችሁ! ማለት እፈልጋለሁ። በዓለም የአገር አቋራጭ ውድድር ኢትዮጵያ በርካታ ጊዜ አንደኛ፤ ሁለተኛም ወጥታ ታውቃለች። የዘንድሮውን ከእስከአሁኑ ለየት የሚያደርገው፤ ኢትዮጵያ በዓለም መድረክ ላይ ከፍ ብላ እንድትታይ፤ ባንዲራዋ ከፍታውን እንደ ያዘ እንዲቆይ የሚያደርግ ብቸኛው ምስጢር መደመር መሆኑን ያረጋገጥንበት ቀን መሆኑ ነው።

ከዚህ ቀደም የተለያዩ አገራት ሊወርሩን፤ ሉዓላዊነታችንን ሊደፍሩ ሲሞክሩ ተደምረን የማንሸነፍ መሆናችንን አሳይተናል። በአትሌቲክሱም እንደዚሁ ተደምረን ባንዲራችንን ከፍ፣ አገራችንን ከፍ፣ ክብራችንን ከፍ ማድረግ ችለናል። በሰላሙ፣ በልማቱ፣ በዲሞክራሲ ሥርዓት ግንባታውም ብቸኛው የማሸነፊያ መንገድ መደመር ነው። ከዚያ ውጪ ያለው የሰፈር አለቃ፣ የቀበሌ ጀግና ይፈጥር ይሆናል እንጂ ለኢትዮጵያ የተሟላ ዕድል ሊያጎናጽፍ የሚችለው ሁላችን ኢትዮጵያውያን ከጫፍ ጫፍ እንደ አንድ ሰው ሆነን ባለን ዐቅም ሁሉ ተደጋግፈን፣ ተጋግዘን እና ተደምረን ስንቆም ብቻ መሆኑን በድጋሚ ለማረጋገጥ የቻልንበት ድል ስለሆነ እንኳን ደስ አላችሁ! እንኳን ደስ አለን! ማለት እፈልጋለሁ።

ኢትዮጵያውያን ድላቸውን ሲያስመዘግቡ መነሻ እንዳላቸው ሁሉ፤ የእናንተም ድል መነሻ መሠረት አለው። በአገር አቋራጭ ደራርቱን እና ጌጤን፣ ቀነኒሳን እና ገሬን፣ ጥሩነሽን እና ወርቅነሽን ሁሌም እናስታውሳቸዋለን። እነዚህ ሰዎች በሁሉም የውድድር መድረክ ተጋግዘው፣ ተደጋግፈው ኢትዮጵያን በተደጋጋሚ የድል ባለቤት አድርገዋል። እናንተ በእነዚህ ጀግኖች መሠረት እና ውጤት ላይ ቆማችሁ የተፈጠራችሁ ትውልዶች ናችሁ። ድል መሠረት ይፈልጋል። ያንን መሠረት ቀድመው የነበሩ ጀግኖች፣ ቀድሞ የነበሩ አሸናፊዎች እነሱን ለመሆን እና ከእነሱ ለመላቅ የምናደርገው ጥረት ውጤት ስለሆነ ማሸነፋችሁን ብቻ ሳይሆን ለእናንተ ማሸነፍ ፈር ቀዳጅ የነበሩትን ማስታወስ፤ ቀጣይ ትውልድም እናንተን እንዲሁ እያስታወሰ እንዲሄድ ስለሚያደርግ፤ ይሄም የኋላ እና የፊትን የሚያስተሳስር የመደመር ሐሳብ ነውና በድል ላይ ድል እንድንጎናጸፍ ያደረጋችሁን የቀደማችሁትም የዛሬዎቹም አትሌቶች ቀጣይ ትውልድ በጋራ እንድትፈጥሩ አደራ እያልኩ ለድሉ እንኳን ደስ አላችሁ! ማለት እፈልጋለሁ።





ይህ ድል በዋዛ አልመጣም። ማሸነፍ በቀላሉ የሚገኝ ነገር አይደለም። ብዙ ጠዋቶች እንቅልፍ ማጣት ነበረባቸው። ብርድ መጋፈጥ ነበረባቸው። የእንጦጦን ተራራ፣ ሱሉልታን፣ ሌሎችንም መስኮች እንዲሁ አንድ ቀን ማሸነፍ እንደሚመጣ አስባችሁ አበክራችሁ ለሠራችሁ ውጤቱ ይናገራል። የጥረትና የልፋት መጨረሻው መለኪያ የመጨረሻዋን ሲባጎ መበጠስ ነው። ሰው ተምሮ ተምሮ መመረቅ ካልቻለ፤ ሰው ሮጦ ሮጦ የመጨረሻዋን ክር መበጠስ ካልቻለ፤ ኢትዮጵያ ኢትዮጵያ ብለን ኢትዮጵያን ከድህነት ተርታ መገላገል ካልቻልን ድካማችን ከንቱ ስለሚሆን የማሸነፍ ጅማሮ ጥረት፣ ትጋት፣ ድካም ቢሆንም የድል ፍሬ ግን የመጨረሻዋን ክር መበጠስ ነው። ይህንን ማድረግ በመቻላችሁ እና በየዕለቱ ክፉ ዜና በምንሰማበት በዚህ ጊዜ፤ መርዶ በምንሰማበት በዚህ ወቅት ማሸነፍ እንደሚቻል፣ አሁንም ተስፋ እንዳለ፣ ከዋሻው ጫፍ የሚታይ ጭላንጭል ብርሃን እንዳለ፤ ከተደማመጥን፣ ከተሰባሰብን፣ ከተደመርን ማሸነፍ እንደምንችል በማሳየታችሁ፤ እንዲሁም በዚህ ውድድር ለማሸነፍ በሚደረግ ሩጫ ከጅማሮው ሁሉም አሸናፊ በሚመስልበት ልክ፤ ሩጫው ሲጀመር ሁሉም ጉልበታም፤ ሁሉም አሸናፊ፤ ሁሉም ልቆ የሚሄድ የሚያስመስል እና የበረቱ፣ የተጉ፣ የሠሩ፣ የተዘጋጁ ግን እስከ መጨረሻው ሄደው እንደሚያሸንፉ፤ መቶ ሜትር፣ አንድ ኪሎ ሜትር፣ ሁለት ኪሎ ሜትር አሸናፊ የሚመስሉ ግለሰቦች እና ቡድኖች የኋላ ኋላ በውድድሩ መካከለኛ እና ፍፃሜ ላይ እየተንጠባጠቡ እንደሚሄዱ ትምህርት ያገኘንበት እና የአሁኑ ሁሉም ሯጭ ሁሉም አሸናፊ የመሰለበት ሩጫ የማታ ማታ እውነተኞቹ አሸናፊዎች ባለድል እንደሚሆኑ ያስተማረን በመሆኑ ተጨማሪ ተስፋ እንድንሰንቅ አድርጋችሁናልና እንኳን ደስ አላችሁ! ማለት እፈልጋለሁ።

ማሸነፍ ተራራ እንደመውጣት ያታክታል። ተራራ ሲጀምሩት የሚያልቅ አይመስልም። ከፊት የቆመው፣ የሚከልለው፣ የሚጋርደው ስለአለ አርቀን ማየት የማያስችል እና የማያልቅ ስለሚመስል ተራራ ያደክማል። ጥቂቶች የተዘጋጁና የጨከኑ እስከ መጨረሻው ድካማቸውን ተቋቁመው ከተራራው

ጫፍ ላይ ሲደርሱ ከዚያ የማየት አድማስ ከልካይ ባሻገር አርቆ ማየት፣ አርቆ ማሰብ፣ አርቆ ማስተዋል፣ አካባቢያቸውንም በርቀት መቃኘት የሚያስችል የማሽነፍ ብቃት ይጎናጸፋሉ። የጀመርነው የተራራ ጉዞ፣ የጀመርነው ድህነትን የመዋጋት እና አገረ መንግሥት የመገንባት ጉዞ አታካችና አሰልቺ ቢመስልም ኢትዮጵያውያን ጠንክረን፣ ከግራ ከቀኝ የሚጎትቱን ክፉ ዜናዎች አሸንፈን፣ ከተራራው ጫፍ ስንደርስ ልክ በአትሌቲክስ ከዓለም አንደኛ እንደሆንነው ሁሉ በሰላሙም፣ በልማቱም፣ በዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታውም ለእኛም ለአፍሪካም ምሳሌ እንደምንሆን ጥርጥር የለውም። ነገር ግን ይህ ጉዟችን በሩጫው እንዳያችሁት የሚያደክም፣ የሚያታክት፣ በዋዛም የማይገኝ ስለሆነ እናንተን ተከትለን ጉልበት የሚያስጨርሰውንና አድካሚውን ሩጫ ሳናቋርጥ በማሸነፍ ኢትዮጵያን እንደ ስሟ ትልቁን ክብሯን ለመመለስ ለምናደርገው ሩጫ ከዚህ ከዛሬው ድል መማር ይኖርብናል። አንዴ ማሸነፍም በቂ አይደለም። አንዴ ማሸነፍ ሳይሆን የማሸነፍን ምስጢር ማወቅ ነው የሚያስፈልገን። አንዴ ከአሸነፍን በኋላ ሁለተኛ የማንታይ ከሆነ ድሉ ቶሎ ይረሳል። እነ ቀነኒሳን፣ እነ ጥሩነሽን፣ እነ ደራርቱን፣ እነ ገሬን ስናነሣ በተደጋጋሚ እዚያ መድረክ ላይ በመሳተፍ፤ በተደጋጋሚም በማሸነፍ ያው እንደምታውቁት 16 እና 18 ሜዳሊያ ያላቸው ጀግኖች ከዚሁ አገር የበቀሉ ናቸው። ደጋግሞ የማሸነፍ ምስጢር በግለሰብ ደረጃ ትዕግሥት እና ትጋት ይፈልጋል። ሰዎች በትዕግሥት እና በትጋት ከሠሩ፤ ቡድኖች በቅብብሎሽ እና በትብብር ከሠሩ በዘላቂነት ማሸነፍ የድልን ምስጢር ማወቅ ያስችላል። እንደ ሀገር የገጠመንን ፈተና ተሻግረን ዘላቂ እና በቀላሉ የማይፈርስ ድል ለማስመዝገብ ትዕግሥት ያስፈልጋል። ትጋት ያስፈልጋል። ዳተኛ የሆንን ሰዎች መትጋት ይኖርብናል። የምንቸኩል ሰዎች መታገሥ ይኖርብናል። በትብብር፣ በቅብብል እና በድግግፍ በጋራ ማሸነፍ እንደሚቻል ሁላችን ማመን፤ ለዚያም መገዛት ያስፈልጋል።





ዛሬ በዓለም ላይ ስድስት ሺሕ አምስት መቶ ገደማ ቋንቋዎች ይነገራሉ። ስድስት ሺሕ አምስት መቶ ገደማ ቋንቋዎች ቢነገሩም በዓለም ላይ ያሉት 195 አገራት ብቻ ናቸው። 193ቱ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የሚያውቃቸው ሁለቱ ተጠባባቂ ወይም ኦብዘርቨር የሚባሉ ሆነው 195 አገራት አሉ። ለስድስት ሺሕ ቋንቋ ስድስት ሺሕ አገር የለም። የተለያየ ቋንቋ መናገሩ፤ የተለያየ ባህል ያለው ማህበረሰብ በጋራ መኖሩ በኢትዮጵያ አልተጀመረም። በኢትዮጵያም አያበቃም። በዓለም ላይ ያሉ አገራት ባለብዙ ቋንቋ፣ ባለብዙ እምነት፣ ባለብዙ እሳቤ ሆነው በጋራ መኖር እና ማደግ ስለቻሉ፤ እኛ ኢትዮጵያውያን ብዙ ቋንቋ መናገራችን በረባ ባልረባው በትንንሽ ነገር ትልልቁን ፍላጎታችንን በሚያከስም መንገድ ቡድን እየፈጠርን እዚያ እና እዚህ ድንጋይ የምንወራወር እንዳንሆን በማስተዋል ከሩዋንዳ መማር ያስፈልጋል። በሩዋንዳ ብሔርተኝነት ጫፍ ነክቶ ሁቱዎች የቱትሲዎችን በሚሊየን የሚቆጠር ሰው ከገደሉ በኋላ ዛሬ ሩዋንዳ ውስጥ ብሔርህ ምንድነው ብሎ መጠየቅ በሕግ የተከለከለ ነው። ብሔርተኝነት ጫፍ ነክቶ ሕዝብ ከአስጨረሰ በኋላ ያስተማራቸው ትምህርት አንዱ ሌላውን ሩዋንዲዝ መሆኑን እንጂ የየትኛው ብሔር፤ የየትኛው ቋንቋ ተናጋሪ መሆኑን በየትኛውም ሁኔታ መጠየቅ በሕግ ይከለከላል። በፖለቲካ ፓርቲ፣ በግልም በሥራ ቅጥርም። እኛ ከየትኛው ብሔር ነህ? የሚለው ጉዳይ የሚያሸማቅቅ እና የማይጠራ እስኪሆን ድረስ የምንጠላላና የምንገዳደል ከምንሆን ሁሉም አንዱ ለአንዱ ጌጥ፤ አንዱ ለአንዱ ክብር፤ አንዱ ለአንዱ አስፈላጊ መሆኑን አምኖ መኳዝ ያስፈልጋል። ይህ ሲሆን ከመቶ ሚሊዮን በላይ ኢትዮጵያውያን ሁሉም ይሄንን ሐሳብ ይጋራሉ ማለት ግን አይደለም።

ሩዋንዳ ውስጥ በጣም ብሔርተኛ የሚባሉት የሁቱ ተወላጆች ያኔ፤ በ1994 ተሳስተናል ይላሉ። “99 በመቶዎቹ ተሳስተናል። ወንድሞቻችንን መግደል አልነበረብንም” ይላሉ። አንድ በመቶውም “ተሳስተናል፤ ያኔ መጨረስ ነበረብን” ይላል። “ጀምረን ተውናቸው፣ ብንጨርሳቸው ይሄ ሁሉ ጣጣ የለም” ብሎ የሚያስብ ፅንፈኛ ብሔርተኛ ዛሬም አለ። ብዙዎቻችን በጋራ፤

በሰላም መኖር የምንፈልግ ቢሆንም አንዳችንን ከሌላችን በማባላት ትርፍ የሚገኝ የሚመስላቸው ግለሰቦች ዛሬም አሉ፤ ወደፊትም ይኖራሉ። መጥፎው ነገር 99 በመቶው እና ሰላም ወዳዱ ሕዝብ የእነዚያን ሰዎች ፍላጎት ተሸካሚ ሆኖ ከተጓዘ እና ችግሩን ያባባሰ ከሆነ ብቻ ነው።
ኢትዮጵያውያን ከተጠናወተን ሰመመን መንቃት አለብን። ለእኛ ለኢትዮጵያውያን እንደ ዛሬው ድል መደመር እና በጋራ በመሆን ባንዲራችንን ከፍ ማድረግ እንጂ፤ አንዳችን ሌላችንን መጣል በፍፁም የማያስፈልገን፤ ማናችንንም አሸናፊ የማያደርግ፤ ለሁላችንም ውድቀታችንን የሚያፋጥን በመሆኑ መንቃት፣ መማር እና ከተያያዝነው የውድቀት መንገድ ቆም ብለን በማሰብ በተቃራኒው በመደመር ወደ ከፍታ መጓዝ እንዳለብን አጥብቄ መምከር እፈልጋለሁ።

ሁሉንም ነገር በአንዴ ለመፍታት ከሞከርን ሁሉንም እናጣለን። አንድ ሳምንት ተለማምደን በአገር አቋራጭ ውድድር ሁሉም ወርቅ የእኛ ይሁን ብንል አይሆንም። ዘንድሮ አምስት ወርቅ ነው ያገኘነው፤ በ2017 አራት ወርቅ ነው ያገኘነው፤ በ2017 ኬንያ አንደኛ ስትወጣ በአንድ ወርቅ ትበልጠን ነበር። በብርም በነሐስም እኩል ነበርን። አሁን ግን እኛ አምስት ወርቅ ስለአገኘን ሁለተኛ ከወጣችው ኬንያ በሁለት ወርቅ እንበልጣለን። እነሱ ሁለት ወርቅ ስለአገኙ ግን አንደኛ ብንወጣም 7 ወርቅ፤ 9 ወርቅ፤ 10 ወርቅ መመኘታችን አልቀረም። ያ ዛሬ አልሆነም። ያ በአንዴ አይሆንም። ተግተን በመሥራት ወደፊት ልናመጣው እንችላለን። ቅደም ተከተልን የማያውቅ ማንኛውም ሥራ እና ሠራተኛ ሁሉን ጠንቅቆ መጨረስ ስለሚቸግር በሀገር ደረጃ የተከመሩ ችግሮቻችንን በአንድ ጀንበር ለመጨረስ የምናደርገው ሙከራ ሁሉን እንዳያሳጣን በችግሮቻችንን ማስተዋል፣ በምክክር፣ በጊዜ ሂደት፣ በቅደም ተከተል እየፈታን በጋራ የምንጓዝበትን መንገድ እያንዳንዱ ዜጋ ከዚህ ድል ተምሮ መጓዝ እንዳለበት በጽኑ አምናለሁ። ኢትዮጵያ ውስጥ ገለልተኛ እና ብቃት ያለው ተቋም መገንባት፤ የሕግ የበላይነትን ማረጋገጥ፤ የዲሞክራሲ ሥርዓትን አስተማማኝ በሆነ መንገድ መገንባት ለዓመታት የምንይዘው የሀገር አቋራጭ እና የጋራ ሥራ ነው። አንዱ ከአንዱ እየተቀበለ የሚያስቀጥለው መሠረቱን እያጸና እንዳይፈርስ የሚያደርገው ስለሆነ ይህ ለጊዜው እንደተራራ የገዘፈ ችግር መፍትሔው እንደ መርፌ የቀጠነ እና የማይታይ የሚመስለው ሁኔታ ኢትዮጵያውያን ከነቃን ከተደመርን ችግሩን አልፈን ልክ ዛሬ በዓለም አንደኛ የሆንንበትን ውድድር እናንተ እንዳበሠራችሁት አሸናፊ ሆነን የሀገራችንን ስሟን እና ሕዝቦቿን ከፍ ማድረግ እንችላለን። ለዚህ ብቸኛው መንገድ ተደምሮ ተጋግዞ መሥራት ይሆናል። ይህንን ለማሳካት አትሌቶች ፈር ቀዳጅ መሆን ይጠበቅባቸዋል።

በመተጋገዝ እና በመደመር ምን ውጤት እንዳለ ቀነኒሳ፣ ኃይሌ፣ ደራርቱ፣ ስለሺ ስህን በአንድ ወቅት ለሁላችን አስተምረውናል። በመተጋገዝ ውስጥ ያለን ነገር ከእነሱ መማር እንድንችል እናም ያንን እሳቤ በሁሉም መስክ፤ በእርሻውም በትምህርቱም እያበዛን እና እየደመርን ኢትዮጵያን እንድናልቅ እናንተ በማስተማር አርአያ በመሆን ከፊት ሆናችሁ ሕዝቡን እንድታነቁ አደራ ማለት እፈልጋለሁ።

ደራርቱ ላነሣችው ጥያቄ፤ አዲስ አበባን የማስዋብ ፕሮጀክት እንደቀረፅን ሁላችሁም ታውቃላችሁ። ይህ ፕሮጀክት ከአንድ ዓመት በላይ አይወስድብንም። በሚቀጥለው ዓመት ክረምት ኢጋማሽ ላይ አገባድደን በመስከረም አካባቢ ለሕዝብ ክፍት ይሆናል። ለሕዝብ ክፍት የሚሆነው 12 ኪ.ሜ ገደማ እና 40 ሄክታር ተጨማሪ ቦታ የያዘ ነው። ከዚያ በኋላ ፋይናንስ እያፈላለግን እስከ 50 ኪ.ሜ ይሠራል። ይህ ቦታ ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ፤ ለአዲስ አበባ ነዋሪዎች፤ ለቱሪስቶች አስፈላጊ ቢሆንም ከሁሉ በላይ ግን ለእናንተ ያስፈልጋል። ተፈጥሮን ተከትሎ የሚሠራ በመሆኑ፤ የእግር ጉዞ ማድረጊያ መንገዶች የሞሉት በመሆኑ ከፍታንም ዝቅታንም እየሮጣችሁ በውሃ ዳር ከመኪና ስጋት ውጪ ልምምድ ለማድረግ ያስችላችኋል። ከአንድ

ዓመት በኋላ የምንጨርሰው ከ12 እስከ 13 ኪሎ ሜትር ስለሆነ ከእናንተ የበረታ ተለማማጅ ካለ ደርሶ መልስ ከሄደ 26 ኪ.ሜ ይሄዳል ማለት ነው። ከዚያ በላይ በአንድ ቀን እንደማትለማመዱ ደራርቱ ነግራኛለች። ስለዚህ ይህ የወንዞች ዳርቻ ፕሮጀክት የእናንተን የልምምድ ፍላጎት የሚያሳካ ስለ ሆነ ሥራውን በሐሳብ፣ በገንዘብ፣ በጉልበት በመደገፍ ከጎናችን እንድትቆሙ በዚህ አጋጣሚ ጥሪዬን ማቅረብ እፈልጋለሁ። በተጨማሪም በሁሉም ክፍለ ከተማ የስፖርት ማዘውተሪያዎች ተለይተው እየተዘጋጁ ሲሆን፤ ትላልቅ ግንባታ እና በውጭ የምታዩትን ማዘውተሪያ ስፍራ ለመሥራት ለጊዜው የዐቅም ውስንነት ቢኖርም፤ ክፍት ቦታዎች እያዘጋጀን ሰው አካላዊ ልቀቱ እንዲጎለብት፤ ጤንነቱ እንዲጠበቅ ከፌደሬሽኑ ጋር በቅርበት የምንሠራ መሆኑን በዚህ አጋጣሚ ልገልጽላችሁ እፈልጋለሁ።

በመጨረሻም እዚህ ለተሳተፋችሁ አትሌቶች እና አሠልጣኞች፣ የፌደሬሽኑ ሐላፊዎች፣ እንዲሁም ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ከአንድ ሳምንት እስከ ሁለት ሳምንት ሙሉውን ጊዜ መልካም ዜና ሰምተን መሻገር የምንችገርበት ሁኔታ ነው ያለው። በሰሞኑ ያጋጠመንን ችግር ሁላችሁም ታውቃላችሁ። እንደዚህ አንገት የሚያስደፉ፤ የሚያሳምሙ ጉዳዮች በኢትዮጵያ ውስጥ እየተደጋገሙ ይገኛሉ። ችግሩ እንዳይባባስ፤ ከጥፋት እንድንማር፤ ባለበት እንዲቆም ቀና ቀናውን ማሰብ ስለሚያስፈልግ በመጪው እሑድ ጠዋት ከ12፡30 እስከ 1 ሰዓት ባለው ጊዜ ውስጥ ወጥተን፤ ከ1 ሰዓት እስከ 2 ሰዓት ባለው ጊዜ  የመኪና እንቅስቃሴ በማቆም በሁሉም ስፍራ ነዋሪዎቿ አዲስ አበባን እንዲያጸዱ፣ በየክልሉ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ዩኒቨርሲቲያቸውን እና ከተማቸውን እንዲያጸዱ፣ እሑድን ቆሻሻ በማስወገድ፣ ቆሻሻን በመጠየፍ፣ ቆሻሻን በመጥላት፣ አሉታዊ እሳቤን በማራቅ፣ አዎንታዊ እሳቤን በመደመር መጽዳት፣ ማጽዳት እንደሚቻል ከአካባቢያችን በመማር፤ ከአእምሮአችን ውስጥም ጥላቻን፣ ቂምን፣ መጥፎ ሐሳብን እንዲሁ በማጽዳት፣





ከዚያኛው ሳምንት ሰኞ እስከዚህኛው ሳምንት ሰኞ ክፉ ዜና ሳንሰማ፣ መልካም መልካሙን እየሰማን እና መልካም እያደረግን እንድንቆይ፤ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ባለበት ስፍራ፣ ትንሽ ትልቅ፣ ሴት ወንድ፤ ተማሪ አስተማሪ ሳይል፣ በሰፈሩ አካባቢውን እያጸዳ፣ የቆሻሻን ክፋት እያጸዳ ከዚያም ከጭንቅላቱ ክፉ ሐሳብን በማውጣት፣ መልካም በማሰብ፣ እሑድ እንድንጀምር በዚህ ጽዳት የመንግሥት የሥራ ሐላፊዎች፤ በየደረጃው ያሉ የፀጥታ ሠራተኞች፤ ሀሉም እንዲሳተፉ ጥሪ አቀርባለሁ። እሑድ በጽዳት እንገናኝ። መልካም ጊዜ።

**አመሰግናለሁ!**

**ድሉ ይደገም!**

# የግብርናግብአትማሻሻል ስብሰባ ንግግር

ግንቦት 18/2011 ዓ.ም.

አሁን በቀጥታ ወደ ችግኝ ተከላ እንሄዳለን። ችግኝ ተከላ በዚያች ጉድጓድ ምክንያት እና በራሱ በችግኙ የተነሣ የአፈር መከላትንና ውሃ የማቆየትን ሚና ይጫወታል። ችግኝ ሲተከል የሙብቀል ያለሙብቀሉ ብቻ አይደለም ጉዳዩ፤ እኛ አካላዊ እንቅስቃሴ እናደርጋለን። ከጤና አንፃር ጥቅም አለው። ስንቆፍር ትንሽም ቢሆን ውሃ ያቁራል። አራት ቢሊዮን ጉድጓድ አስቡት፤ ትናንሽም ቢሆን ያው ስሌቱን በሞያ እናንተ እዩት። የሚያስቀረው ነገር አለ። ከዚያ ውስጥ አብዛኛውን እንዲበቅል ማድረግ ከቻልን ደግሞ በዘላቂነት ለትውልድ ጥቅም አለው። ያ እንዲሆን በከተማ አካባቢ ከተሜዎች፣ የከተማ አስተዳደሮች ችግኞቹ እንዳይጠወልጉ፣ እንዳይደርቁ፣ እንዳይጠፉ እንክብካቤ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። አርሶ አደር በዚህ አይታማም። ችግር ያለው ከተከልን በኋላ በምንሸሸው ሰዎች አካባቢ ነው።





እኛ ደግሞ ግቢያችን ውስጥ፣ በሥራ ቦታችን እና በአቅራቢያችን ከሆነ ለማየት ዕድል እናገኛለን። ሕዝቡ ተጠቃሚ መሆኑን በሚያረጋግጥ መንገድ ከሠራን አራት ቢሊዮን ችግኝ በመትከል ብዙ እንገናኛለን፤ ብዙ እንወያያለን፤ አካባቢያችንን እናያለን፤ በዚያ ውስጥ እንማማራለን። የኢትዮጵያን ቀጣይ ገፅታም እንቀይራለን። ይህ እንዲሆን የኦርቶዶክስ እምነት በቅርቡ ባላቸው የሲኖዶስ ስብሰባ ላይ አንዱ ጥያቄ ያ የእምነት ተቋም ከዚህ ቀደም ደን የማቆየት ባህሉን በማገዝ አሁንም ከጎናችን ሆኖ አራት ቢሊዮን ችግኝ በመትከል ላይ እንዲረባረብ ጥሪ ቀርቧል። በደስታ ተቀብለው እንሠራበታለን ብለዋል። ከሙስሊም ዑለማዎች ጋር በነበረን ውይይት አንሥተነዋል። በቅርቡ በጋራም በተደረገው አፍጣር አንዱ አጀንዳ የአራት ቢሊዮን ችግኝ ተከላ ነው። በሰሞኑ ከዩኒቨርሲቲ ቦርዶች ፕሬዝዳንቶች ጋር ውይይት እናደርጋለን። ከእናንተ የሚጠበቀው ይሄንን መልእክት በየአላችሁበት ሰፈር በማድረግ እና በማሳየት በማስተማር እና አርአያ በመሆን ማኅበረሰቡን መቀስቀስ ነው። ይህንን ህልም ማሳካት ብንችል ለእኛም ለትውልድም የሚጠቅም ሥራ ይሆናል። ይሄ ነገር እንዲሳካ ተስፋ ከሰጡን ነገሮች ጥቂቶቹን አንሥቼ አበቃለሁ።

አንደኛ፤ ባለፈው ዓመት ከፖለቲካ አንጻር ያሳካናቸው ስኬቶች ከዓመት በፊት ስናያቸው የሚታሰቡ አልነበሩም። የታጠቁ ኃይሎች አገር ውስጥ ገብተው ውጭ የነበረው ፖለቲካ ኢትዮጵያ ገብቶ፤ ምንም እንኳን የሚጎረብጥ ነገር ቢመስልም፤ አሁን ባለው ሁኔታ መነጋገር ይቻላል የሚል ሐሳብ በየትኛውም ደረጃ ያለ ሞያተኛ እና ፖለቲከኛ የማያስበው ቢሆንም ተከናውኗል። ከኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ከውጪ ከተለያየ አገር ከዓሥር ሺሕ በላይ እስረኞች አስፈትተን አምጥተናል። በአንድ ዓመት ውስጥ በእጃችን ያለውን መፍታት ይቻል ይሆናል። ከግብፅ፣ ከሳዑዲ፣ ከታንዛኒያ፣ ከተለያዩ ሀገራት መቶ ሳይሆን ዓሥር ሺሕ ሰው ማምጣት ግን ቀላል ነገር አይደለም። ስለዚህ እንደሚቻል የሚያሳይ ጉልበት ይሆናል።

“እያየን ያለነው ፈተናስ ምንድነው?” ያላችሁ እንደሆነ አዲስ ልምምድ ነው። በበጋ ቆይተን ክረምት ሲጀምር በጣም ብዙ ችግር ነው ያለው፤ አንዳንድ ቀን ጥላ እንረሳለን። በደንብ ለብሰን ስንወጣ ዝናብ ይመታናል። መሐል ክረምት ስንገባ ግን ጥንቃቄ እናደርጋለን። ልክ ሲጀመር ከበጋ ወደ ክረምት ስንሸጋገር የሚያጋጥመን ፈተና በክረምት መሐል ላይ አያጋጥመንም። ጉንፋን የሚበዛው ልክ ክረምት ሲጀምር ነው። ዝናቡ ዘንቦ አዲስ ጠረን አዲስ ነገር ስለሚያሳይ ክረምት መሐል ሲመጣ ይቀየራል። እኛም አዲስ ልምምድ ነው የተለማመድነው። እስከ አሁን የነበረው ጃንሆይ ወደቁ መንግሥቱ መጣ፤ መንግሥቱ ወደቀ ኢሕአዴግ መጣ ነው። እንጂ፤ አንዱም ሳይወድቅ ሌላ የመጣበት ልምምድ አልነበረንም። ጠርገን ማሸነፍ እና ጠርገን መሸነፍ ነበር። ያ በመቀየሩ አዳዲስ ነገር አይታችሁ ይሆናል። አዳዲስ ነገር መማር፣ በዚያ ውስጥ ማለፍ ከኛ ቢጠበቅም፣ በፖለቲካው ዘርፍ የተገኙ ድሎችን ማዝለቅ ከቻልን ተስፋ ይሰጣል።

ከኢኮኖሚው አንጻር፤ ኢትዮጵያ በአደገኛ አዘቅት ውስጥ ልትወድቅ የነበረች አገር ናት። አምና የጀመርናቸውን ፕሮጀክቶች መጨረስ ሳንችል፤ የተበደርናቸውን ብድሮች መክፈል አቅቶን፤ ለሠራተኞቻችን ደሞዝ መክፈል የማንችልበት ደረጃ ላይ ነበርን። ዘንድሮ ከውስጥም ከውጭም ከፍተኛ ብድር ቀንሰን አራት በመቶ የበጀት ዴፊሲት ቀንሰናል። የነበረውን የበጀት ጉድለት አራት በመቶ ቀንሰናል። ጉድለቱ ብዙ ቢሊዮን ስለነበረ በውጭ ምንዛሪም ዝርዝር ሪፖርቱን ብሔራዊ ባንክ ያቀርበዋል።

ዘንድሮ ያገኘነውን የውጭ ምንዛሪ መጠን ያህል በየትኛውም ዓመት ኢትዮጵያ ውስጥ መጥቶ አያውቅም። ቱሪዝም ብቻ 28 በመቶ ነው ያደገው። ስለኢኮኖሚ ደጋግመን የማንናገርበት ምክንያት ኢኮኖሚውን የምንገነዘብበት መንገድ አደገ ከተባለ መታየት ያለበት በደሞዝ ጭማሪ ብቻ ተደርጎ ስለሚታሰብ ነው። አሁን በየሴክተሩ የደሞዝ ጭማሪ የሚያነሡት ሞያተኞች አንዳንዴ “ኢትዮጵያዊ ናቸው? ወይስ ኢትዮጵያዊ አይደሉም?” ብዬ አስባለሁ። ምክንያቱም ልጅ እናቱን ሄዶ ምሳ ካላመጣሽ የሚለው በመሶብ ውስጥ የተዘጋጀ ነገር ያለ እንደ ሆነ፤ ወይም በቆሎ ምናምን አይቶ ቆላ አድርገሽ አምጪ የሚል ከሆነ እንጂ፤ ህፃን ልጅ እንኳን እናቱ ምንም እንደሌላት ካወቀ ተለጥፎባት ያለቅሳል እንጂ ምግብ አምጪ አይልም። በባዶ ቋት ያለች አገር እንደሆነች እያወቀ የሚጠይቀው ማነው የሚለው ጉዳይ ግራ ይገባኛል። ምክንያቱም ማክሮ ኢኮኖሚክ ኢምባላንሱ አስጊ ነበረ። ያንን ለመፍታት ሰዎች “አምጪ እማማ” ሳይሆን “እንኪ እማማ” የሚሉበት ጊዜ ነው። እንዳያችሁት ከውስጥም ከውጭም ባደረግነው ሙከራ ኢትዮጵያውያን “አምጪ” እንጂ “እንኪ” ማለት ያልለመዱ መሆኑን በንግግር ሳይሆን በተግባር አረጋገጥን።

ለምሳሌ፤ ከአንድ ሚሊዮን በላይ ዳያስፖራ ስላለ “እባካችሁ ችግር ላይ ነው ያለነው ከአንድ ቡና አንድ ብር” ብለን እስከ አሁን ከአንድ ሚሊዮን ዳያስፖራ፤ በቀን ብዙ ጥያቄ ማቅረብ የሚችል ዳያስፖራ ቢኖርም አራት ሚሊየን ዶላር ብቻ ነው የተዋጣው። ጥያቄው እና መዋጮው እንደማይመጣጠን በንግግር ሳይሆን በተግባር አረጋገጥን። አዲስ አበባን ለማስዋብ “በአምስት ሚሊዮን ብር ራት ብሉ” ብለን ለኢትዮጵያውያን ጥያቄ አቀረብን። ኢንቨስትመንት ነው። እዚያ ቦታ ቻይናዎች እና አንዳንድ አገረ መንግሥታት የነበሩበትን ቁጥር እና የኢትዮጵያውያን ቁጥር ሲታይ አሁንም ኢትዮጵያውያን ለ“አምጪ” እንጂ ለ“እንኪ” ያልተዘጋጁ መሆናቸውን ያሳያል። በተግባር አየን። እዚህም አሁን የቀረን አርሶ አደር ነው። ታማኙ አርሶ አደር በገንዘብ ሳይሆን ችግኝ በመትከል፣ የመኸር ምርት እና ምርታማነትን በማሳደግ፣ ጉልበቱን በመስጠት ያለውን ችግር ለመሻገር አስተዋጽዖ ያበረክታል። ሰው ጓደኛውን ብድር ቢጠይቀው ጓደኛው ዕቁብ የበላ እንደሆነ፣ ደሞዝ የወሰደ እንደ ሆነ ነው። ያው ታውቁታላችሁ ዝም ብሎ በወር መካከል ተሄዶ ብር አበድሩኝ አይባልም። እስከ ደሞዝ ጠብቀኝ ይባላል። አሁን እኛም ውስጥ ያለው ነገር እንደሱ ነው። እንደ ምንም ብለን ያለውን ችግር ተጋግዘን ብንሻገር ተስፋ፣ ዕድል

ከፊታችን ይኖራል። ያንን ማድረግ ካልቻልን ግን ያው ሁላችንም ስንጠያየቅ ጊዜ እንዳያልፍ ያሰጋል። ይሄ የኢኮኖሚ ጉዳይ አንገብጋቢ ነው። በጣም ብዙ ዝርዝር ማንሣት ይቻላል።

ማኅበራዊ ዕድገትን በምንመለከትበት ሰዓት የዛሬ ዓመት ‹የአሜሪካው ሲኖዶስ እና የኢትዮጵያው ሲኖዶስ ታርቀው በጋራ አንድ ስብሰባ ያደርጋሉ› የሚል እንኳን ፖለቲከኛ የሀይማኖት አባት አልነበረም። አይታሰብም! እንደ ጠላት የሚፈራረጅ ኃይል ስለ ነበረ አንድ ላይ በጋራ አጀንዳ ይነጋገራል ተብሎ አይጠበቅም። ሙስሊሙንም ብንወስድ፤ ሁለቱ የተጋጩ ኃይሎች በጋራ የጋራ ኮሚቴ መርጠው በአንድ ላይ የሚሠሩበት ሁኔታ ይፈጠራል ተብሎ አይታሰብም። ስደተኛው እና አገር ውስጥ ያለው ሲኖዶስ በጋራ፤ እስረኛው እና መጅሊስ ውስጥ ያለው አባት በጋራ ሆኑ ማለት ነው። በጣም ጽንፍ የያዘ ነገር ነው የምነግራችሁ፤ ግን ሆኗል። እነዚህ መሆን ከቻሉ፤ እናም የማይሞከሩ የሚመስሉትን የኢኮኖሚ ተግዳሮቶች፣ የፖለቲካ ተግዳሮቶች፣ የማኅበራዊ ተግዳሮቶች መሞከር እና መሻገር ከቻልን፣ በግብርናው ዘርፍ አርሶ አደሩን አስተባብረን፤ ከላይ እስከ ታች ተሳስረን መምራት ከቻልን ውጤታማ መሆን ይቻላል።

የአራት ቢሊዮን ችግኝ ተከላ ዛሬ በይፋ ይጀመራል። እኔና እናንተ በጋራ አዳማ ላይ እንተክላለን። ይህም ለአዳማ ከተማ ከንቲባ የምንሰጠው አደራ ነው። የአዳማ ሰዎች "ጉዲፈቻ ባህላችን ነው" ስለሚሉ፤ እኛ ልጆቻችንን ተክለን ሄደናል። ሌላ ጊዜ ስንመጣ ቼክ እናደርጋለን ማለት ነው። በሚቀጥለው ባሕር ዳር፣ መቀሌ፣ ጅግጂጋ፣ ጋምቤላ ላይ ስብሰባ ስናደርግ በተመሳሳይ ሁኔታ፤ በየትኛውም ስብሰባ መክፈቻ እና መዝጊያ፤ የተማሪዎች መመረቂያ ቀን ችግኝ እየተከሉ መመረቅ ተግባራችን ይሆናል። የተተከለበት ቦታ ሕዝብ ደግሞ ተንከባክቦ አደራውን ጠብቆ ማሸጋገር ይጠበቅበታል። ይሄንን እያደረግን ስንሄድ የኢትዮጵያን መጻኢ ሁኔታ መቀየር ይቻላል። ኢትዮጵያ እያደጉ ያሉ





በጣም በርካታ ወጣቶች ያላት አገር ናት። ሊለማ የሚችል ምድር ያላት አገር ናት። የተማረ የሰው ኃይል የበረከተባት አገር ናት።

ነገር ግን የፖለቲካ ውጥረቱን ስንመለከት ወንድሞቻችን ጥቂትም ቢሆኑ በምዕራብ፣ በምሥራቅ፣ በሰሜን፣ በደቡብ የማይመቻቸው አሉ። እነሱን በመታገስ፣ በማቀፍ፣ ብዙዎቹም እያረጁ ስለሆነ ትንሽ በመጠበቅ፣ አዲሱ ትውልድም በምክንያት ላይ የተመሠረተ ንግግር፣ በትዕግሥት ላይ የተመሠረተ ውይይት፣ በዕውቀት ላይ የተመሠረተ መግባባት እያደረገ አገሩን ካለማ የተሰደዱ ይመለሳሉ። የታሰሩ ይፈታሉ። መስጠት ያልለመዱም ቀስ እያሉ መስጠት ይለምዳሉ። ይሄ እንዲሆን መጻኢ ኢትዮጵያን መገንባት፣ የመጻኢ ኢትዮጵያን ህልውና ማስጠበቅ እና ማሳመር የሁላችንም ድርሻ ነው። በሁሉም ሞያ ላይ ያለ ሰው የሚጠበቅበት ግዴታ ነው። እዚህ ውስጥ "እኔ ብቻኛው ኢትዮጵያዊ ነኝ" የሚል እሳቤ አያስፈልግም። ሁሉም ኢትዮጵያዊ እኩል ኢትዮጵያዊ ነው። በኢትዮጵያ ውስጥ ሁሉም ሀይማኖቶች እኩል ናቸው። ሁሉም ብሔረሰብ እንደ ብሔረሰብ የተከበረ ነው። ሰው ሰው በመሆኑ ክቡር ነው። በመበላለጥ፣ በመነታረክና በመገፋፋት የምናጠፋው ጊዜ ልማታችንን የሚያዘገይ፣ ሰላማችንንም የሚያደፈርስ እና ልመናን የሚያስቀጥል ስለ ሆነ ከልመና ወጥተን ረጂ መሆን እንድንችል የትብብር መንፈሱ እና የትብብር አካሄዱ አስፈላጊ ነው።

ቀደም ሲል ያነሣሁላችሁ የውጭ ዳያስፖራዎች እና በኢትዮጵያ ያሉ ባለሀብቶች በበቀደሙ ራት 2.2 ቢሊየን ብር አዋጥተዋል። በአንድ ቀን ራት የተዋጣው ብር እስከ አሁን ስናወጣ ከነበረው አንፃር ሲታይ ከፍ ያለ ነው። ነገር ግን፤ በቤተ መንግሥት ለምንሠራው፤ ለቢሮ እና ለሙዚየም ሁለት ሰዎች ስድስት ቢሊየን ብር ነው ያገዙን። ሁለት የውጪ ሰዎች። ስለዚህ ዳያስፖራው እና የኢትዮጵያ ሀብታም ተደምሮ አንድ ሦስተኛውንም አላዋጣም ማለት ነው። ሁለት ሰው ያዋጣውን በኅብረት ማውጣት ያልቻልነው የገንዘብ

ብቻ ሳይሆን የልምምድም በሽታ ስለአለብን ነው። ሲዘረጋ ለመቀበል እንጂ ሲዘረጋ ለመስጠት አልተለማመድንም። ያልሰጠ ደግሞ ወይ አይቀበልም፤ ወይም አይበላውም። ማረስ ብቻውን በቂ አይደለም። መሰብሰብ ብቻውን በቂ አይደለም። መብላት ለራሱ ጊዜ ይፈልጋል። እናም እኛ በጣም ብር አፍቃሪ የሆንን ሰዎች መስጠት ብንለማመድ፤ ብር የምንመኝ ግን ደግሞ የሚጠይቀውን ጥረት እና ድካም ያልተገነዘብን ደግሞ መጣር እና መሮጥ እንዳለብን መምከር  እፈልጋለሁ።

በመጨረሻ አሁን ያለውን ሁኔታ በአጠቃላይ በአንድ እሳቤ መጠቅለል እፈልጋለሁ።

> በአንድ ሰፈር ውስጥ የሚኖሩ የሆኑ ትላልቅ ሰዎች፤ የሀይማኖት አባቶች ነበሩ። በየጊዜው እየተሰባሰቡ በጋራ ፈጣሪን ይለምናሉ። ፈጣሪን ከለመኑና ከጸሎት በኋላ አንዱ ትንሽ ሽምገል ያሉ አባት ልክ ከሰው ጋር እንደሚያወራ ሰው ብቻቸውን ይንሾካሾካሉ። ሌሎቹ 'ከማን ጋር ነው የምታወራው?' ሲሏቸው 'ከፈጣሪ ጋር ነው የማወራው' ይላሉ። ሰዎቹም 'ፈጣሪን አብረን ለምነነው የለም እንዴ? ለአንተ ብቻ ነው የሚታየው? ለምን ለእኛ አይታየንም? ለምን ከእኛ ጋርስ አያወራም?' ብለው ጥያቄ ያነሣሉ፤ እልህም ይጋባሉ። በዚህ ጊዜ ሽማግሌው 'እባክህን እነኚህ ጓደኞቼ እያስቸገሩኝ ስለሆነ ለእነሱም ታያቸው' ብለው ይለምናሉ። ፈጣሪን ታውቃላችሁ፤ ከለመናችሁት መልስ የሚሰጥ ስለ ሆነ 'በቃ ችግር የለውም በሚቀጥለው ቀን እዚያ ተራራ ላይ ጠብቁኝ እንገናኝ' ይላቸዋል። ይህም ለሁሉም የማኅበሩ አባላት ተነገራቸው። 'ፈጣሪ በዚህ ቀን፤ በዚህ ሰዓት እዚያ ተራራ ላይ ጠብቁኝ' ብሏል። ሲሉ ሽማግሌው ተናገሩ። በዚያ ቀን ፈጣሪን ለማየት የቸኮሉት ሰዎች ሰዓቱ ሳይደርስ እየቀደሙ ወደ ተራራው ይሄዳሉ። የማኅበሩ አባላት እየሄዱ ሳለ ተራራው ጫፍ ላይ አንድ በጣም የደከሙ ሽማግሌ ተኝተው ያገኛሉ። እኚህ ሽማግሌ 'ፈጣሪ ሊመጣ ነው አሉ እኔ ግን ተራራውን መውጣት አቃተኝ እባካችሁን ተሸከሙኝ' ይላሉ። ሰዎቹም 'አይ አንተን ስንሸከም ጊዜው ያልፍብናል' እያሉ ትተዋቸው ይሄዳሉ። መጨረሻ ላይ ሰዎቹ እኚያ ቀድመው ሲሄዱ ሲያዩ የነበሩ አዛውንት በከዘራ አንከስ እያሉ ሲደርሱ እኚህ ሽማግሌ 'እባክህን ሰውን ሁሉ ስለ ምን ቸኩለው ጥለውኝ ወጡ አንተ ተሸከመኝ እና ሂድ፤ ከእናንተ ጋር ሆኜ ልየው' ይላሉ። ሽማግሌውም 'አዬዬ ከኔ ቀድመው የወጡት ይበረቱ ነበር፤ እኔ እንኳን አልችልዎትም ግን ልሞክር' ብለው ያንን በጣም የቆሸሸ ልብስ የለበሰ ሰውዬ አንስተው ተሸክመው በከዘራ ደገፍ እያሉ መንገድ ይጀምራሉ። አንድ ሁለቴ ሲራመዱ ሰውዬው የበለጠ እየከበደ፣ እየከበደ፣  እግራቸውን ማንሣት እስኪያቅታቸው ድረስ እየከበደ ሄደ። ይኼኔ እኚህ ሽማግሌም 'አይ ፈጣሪዬ አውቄሀለው እባክህ ውረድልኝ'፣ አንተን የምሸከምበት ጉልበት የለኝም ውረድልኝ' አሉ ይባላል። ፈጣሪም ድሮም ያየኸኝ አንተ፤ አሁንም ያየኸኝ አንተ፤ እነዚያ የሚመኙኝ የኔን ነገር ስለማያውቁ እንደ ተመኙኝ እንደባከኑ ቀሩ፤' አላቸው ይባላል።

እኛም እንደ ባከንን እንዳንቀር የመጣውን ዕድል እንጠቀምበት ለማለት ነው።

**አመሰግናለሁ!**

# የሃምሊን ሆስፒታል 60ኛ ዓመት የምሥረታ በዓል ንግግር

ግንቦት 22/2011 ዓ.ም.

ዶክተር ካትሪን ሃምሊን የብዙ ድሆች እናት፣ የብዙ ሴቶች እናት፣ ብዙ አስተዋይ ያጡ፣ ተመልካች ያጡ ሴቶችን እና ህፃናትን ሕይወት መቀጠል የቻሉ እናት ናቸው። እርሳቸውን በዚህ መልክ ለማሰብና ለማስታወስ፣ ወደፊት ለምንሠራው ነገርም ትምህርት ለመቅሰም እዚህ ቦታ በመገኘታችን ጥልቅ ደስታና ክብር የተሰማን መሆኑን ልገልጽላችሁ እፈልጋለሁ። እኛ ኢትዮጵያውያን ኢትዮጵያዊ ያልሆኑ ሰዎች በተለያየ መስክ ወደአገራችን መጥተው ጀግንነት ሲሠሩ፣ ታሪክ ሲሠሩ፣ የማይረሳ ነገር ሲሠሩ እናውቃለን። የሲልቪያ ፓንክረስት ቤተሰቦች ከጀግና የበለጠ ጀግና ሆነው ለኢትዮጵያ ነፃነት ከነቤተሰቦቻቸው ሲታገሉ እናውቃለን። ከእነሱም ውጭ ካርል የሚባል በአገሩ ታዋቂ ዝነኛ ሰው ዝናውንና ክብሩን ጥሎ በተለያየ የኢትዮጵያ ገጠር ክፍል ተዘዋውሮ በትምህርት፣ በጤና ልማት ለማሰብ የሚከብዱ ብዙ ታላላቅ ሥራዎች ሲሠራ አይተናል። እንዲሁም ሶኮሎፍ የሚባሉ ከዚህ ቀደም በሕክምናው





ዘርፍ ኢትዮጵያ ውስጥ ብዙ አገልግሎት የሰጡ እና ለብዙ ሐኪሞች አርአያ የሚሆኑ ሰውም እናስታውሳለን። በጃንሆይ ጊዜ መጥተው በኋላ በችግር ጊዜ የሀገራቸው መንግሥት "ብትወጣ ይሻልሃል" ሲሏቸው፤ "በችግሬ ጊዜ መጥቼ በችግሯ ጊዜ ኢትዮጵያን ጥዬ አልሄድም" ብለው እዚሁ አርጅተው እዚሁ የሞቱ ሰው ናቸው። እንዲሁም ቢልጌት ባለፉት ዓመታት ከስድስት መቶ ሚሊዮን ዶላር በላይ ርዳታ ሰጥቶ በብዙ መልክ የኢትዮጵያን ልማት የደገፈ ሰው ነው።

ኢትዮጵያውያን በቀለማቸው ነጭ የሆኑ፤ ከእኛ ጋር በምንም መልኩ የማይዛመዱ ሰዎች መጥተው ከኛ የተሻለ ሥራ ሲሠሩ ለማየትና ለመማር የቻልን ቢሆንም፤ ዶ/ር ካትሪን ሃምሊንን ግን አንድ ጥያቄ ልጠይቃቸው እፈልጋለሁ። ዶ/ር ሃምሊን እርስዎ ጉራጌ ነዎ? ወላይታ ነዎ? አማራ ነዎት? ኦሮሞ ነዎ? ዛሬ እኮ ኢትዮጵያ ውስጥ ‹ከእኔ ዘር ውጪ ሌላ የሚሠራ ሰው የለም› በሚባልበት አገር ከየትኛው ዘር ቢወጡ ነው እነዚህን ምስኪን የሚመለከታቸው ያጡ ሴቶች ሰብስበውና አድነው ሰው ያደረጉት? እንዲያው ከየትኛው ብሔር ተፈጥረው እንደሆነ ባውቅ ደስ ይለኛል?!

እኚህ እናት እውነተኛ እናት ናቸው። ለምን እንደ ተፈጠሩ የሚያውቁ፤ ሰው ሆነው ሰውን ያዳኑ፤ ሰው ሆነውም ማለፍ የሚችሉ ናቸው። ከዘር በላይ፤ ከቀለም በላይ፤ ከፆታ በላይ ሰውነት ሰው ለማዳን መዋል እንደሚችል ያስተማሩም ጀግና ሴት ናቸው። በኢትዮጵያ ውስጥ 60 ሺሕ ገድሎ የሚዘፈንበት እና ጀግና የሚባልበት አገር፤ እርሳቸው ሰው የማያስባቸውን 60 ሺሕ ሴቶች፤ 60 ሺሕ ወጣቶች፤ 60 ሺሕ ጭቁኖች አድነው በምን ስያሜ ልናጀግናቸው እንደምንችል እኔ አላውቅም። ጀግንነት ሰው መሆን፤ ጀግንነት ሰው ማዳን፤ ጀግንነት ለተረሱት መቆም መሆኑን እኚህ ሴት፣ ባልተቤታቸውና ቤተሰቦቻቸው በተግባር አስተምረውናል።

ዶ/ር ሃምሊን በተግባር ከአስተማሩት ትምህርት ውጪ እኛ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችንን ዝቅ ብለን ማገልገል ተስኖን፥ በብሔር፣ በእምነት፣ በጾታ ተከፋፍለን፤ አንዳችን ለሌላችን አለኝታ ሳይሆን እንደ ጠላት በምንተያይበት በዚህ ጊዜ፤ እርሳቸውን ፈጣሪ አስነሥቶ ሰውን ማገልገል፣ ሰውን ማክበር፣ ለሰው መቆም ክብር ነው ብሎ የእኛን እብሪትና ጉራ ያስተነፈሰበት ተግባራዊ ማስተማሪያ መድረክ አድርጌ ነው የምወስደው።

ዶ/ር ሃምሊን፤ ኢትዮጵያውያን ውለታ አይረሱም። በዘመን መካከል ስለአደረጉልን ውለታ ልጆቻችን እያሰቡ እያመሰገኑ እየጻፉ እያስተማሩ ይኖሩበታል። ዶ/ር ሃምሊን ከእኛ የተሻለ አገር፤ ከእኛ የተሻለ የበለፀገ ምቹ ሁኔታ ቢኖሯቸውም፤ በእኛ መካከል ሳይሆን እኛ እንኳን በማናስባቸው መካከል ሆነው ብዙዎችን ስለታደጉ፤ እኛ ልንከፍልዎ የምንችለው ነገር ባይኖርም ፈጣሪ በመጨረሻው ጊዜ ለጥሩዎች፣ ለደጎች በሚከፈለው ክፍያ እንዲያስብዎ እንጸልያለን። ኢትዮጵያዉያን እኚህን የደሃ እናት ስናስብ የደሃ እናት መሆን እንደሚቻል ትምህርት መውሰድ ነው። ብዙ የገደለ፣ ብዙ ያባረረ፣ ብዙ ያፈናቀለ፣ ማምሻውን ኩራት ሳይሆን ሃፍረት ይሰማዋል። ብዙ ያዳነ የሚከበረው እንደርሳቸው ሲሆን ነውና በዘር፣ በሃይማኖት፣ በቀለም ሳንከፋፈል እንደ ሰው ሰውን አድነን፤ እንደ ሰው ሰውን አገልግለን፤ በመጨረሻው ዘመን እንደእርሳቸው ተከብረን ለማለፍ ይህንን አጋጣሚ ለመማር እንድንጠቀምበት አደራ እላለሁ።

የኢፌዲሪ መንግሥት እና እዚህ የተገኙ የሥራ ሐላፊዎች እዚህ ቦታ ተገኝተን 60ኛ ዓመት ስናከብር አቧራ ማስነሣት ሳይሆን አሻራ ማተም በትውልድ መካከል የሚያስገኘውን ታላቅ ውጤት ተገንዝበን መሆኑን እየገለጽን፤ እርሳቸውን በዚህ መልኩ ማመስገን በቂ ባይሆንም ባለፉት 60 ዓመታት ኢትዮጵያ ውስጥ ለሠሩት ተአምር፣ ለማይጠበቅ፣ ለማይታሰብ፣ ድንቅ ሥራ የኢፌዲሪ መንግሥት የሚያቀርብላቸውን የዕውቅና ሽልማት ሳቀርብ ልዩ





ክብር እየተሰማኝ መሆኑን እገልጻለሁ።

እናታችን የኢትዮጵያ መንግሥትና ሕዝብ እናቶችን ይወዳል፣ እናቶችን ያከብራል፤ እርስዎ ከእናቶች ግን ሁሉ ድንቅ እናት እንደሆኑ እየገለጽኩ ስለአደረጉልን ሁሉ አመሰግናለሁ!

# የሕዝበ ሙስሊሙ አንድነት የተበሠረበት ሥነ ሥርዓት ንግግር

ግንቦት 27/2011 ዓ.ም.

## እጅግ የተከበሩ ሙፍቲ ሐጂ ዑመር ኢድሪስ፣

እስተናጋጁ እንደገለጸው ቀድመው እሳቸው እንዲጋብዙኝ ያልፈለኩት ከፈጥር በኋላ ረመዳን ትንሽ አድካሚ እንደሆነ ስለማውቅ ነው። እናም፤ እሳቸው ከሚነሡ ብዬ ፕሮቶኮል ስላበላሸሁ ይቅርታ እጠይቃለሁ!

ዑለማዎች፤ ታዋቂ የእስልምና ሊቆች፤ ብዙ ሰው እዚህ አዳራሽ ውስጥ እንዳለ እያየሁ ቢሆንም፤ በእንደዚህ ዓይነት አንድነት ውስጥ በመገኘት አብሮነትን በመመኘት የሚታወቁት መጋቤ ሐዲስ እሸቱ በመካከላችን ስለአሉ እሳቸውን እና ስማቸውን ያልጠራሁ በርካታ ታዋቂ ሰዎች እንዲህ ባለ ሁኔታ የሙስሊሙን ማኅበረሰብ በጋራ፣ በደስታ፣ በአንድነት፣ በአብሮነት፣ ሲያፈጥርና ሲደሰት በማየታችን የተሰማን ስሜት ጥልቅ መሆኑን ልገልጽላችሁ እፈልጋለሁ። ሙስሊሞች በጣም ደስ የሚል ነገር ሲያዩ "ማሻ አላህ!" ይላሉ። እጅግ የሚያምር ምሽት እንደሆነ እና ያንን ስሜት በሁላችንም ላይ እንዳጋባችሁ መላው የኢትዮጵያ ሙስሊም ይህችን ዕለት በተለየ ሁኔታ እንደሚመለከትና እኔም በግሌ ልዩ ደስታ የተሰማኝ መሆኑን ልገልጽላችሁ እፈልጋለሁ።

አሁን የአለንበት የረመዳን ወቅት ሁለተኛው የይቅርታ እና የንሰሐ አሻራ ምዕራፍ መሆኑን ሁላችሁም ታውቃላችሁ። ይህን ወቅት ለለቱልቀድር የምንጠብቅበት፤ ሰዎች በይቅርታ እና በንስሐ ረመዳንን የሚጾሙበት ወቅት ስለሆነ ያቺ ምሽት አንዷ ዕለት በሚገባው ልክ ዱአ ያደረገ ሰው ከ83 ዓመት በላይ ዱአ እንዳደረገ ጀዛ የሚያገኝበት ስለሆነ፤ በዚህ አስደናቂ የአሹራ ምዕራፍ ውስጥ በመገናኘታችን ድርብ ደስታ የተሰማኝ መሆኑን ልገልጽላችሁ እፈልጋለሁ።

ሰዎች እንደ አንድ የተዋቀረ ግንብ ሊመሰሉ ይችላሉ። ከዚያ ግምብ ውስጥ አንዱ አካል የጎደለ እንደሆነ ሙሉ ሕንጻ እንደማይባል ሁሉ፤ ሰዎችም አንዳችን ለሌላችን መድኃኒት እና አስፈላጊ ነን። በተለይ ሙስሊም በጀምአ ያምናል። ጀምአ ኅብረት ነው። በጀምአ ሆኖ የሚሰገድ ሰላት በግል ከሚሰገድ ሰላት ጀዛው የጨመረበት ዋናው ምክንያት አላሁሱባላህ በኅብረት ስለሚያምን ነው። ይህንን እምነት በተለይ በረመዳን ወቅት ቀዳ የማይወጣለት የተራዊ ሰላት በጀምአ የሚሰገድ መሆኑ ሕዝበ ሙስሊም በዓመት አንዴ በሚከበረው የረመዳን ወር ወሩን በሙሉ በጋራ በመሆን ተራዊ እየሰገደ የጀማን ክብር የሚገልጽበት ጊዜ መሆኑን ለእናንተ መግለጽ አያስፈልግም።

የአገራችን ዕውቁ ገጣሚ ከበደ ሚካኤል ለልጆች በገጠሙት ግጥም ውስጥ "ፋኖስ እና ብርጭቆ" የሚል ግጥም አላቸው። በድሮ ዘመን መብራት ከፋኖስ ይገኛል። የፋኖስ ታችኛው አካል ጋዝ የሚይዝ ታንከር ያለው ሲሆን፤ በውስጡም ክር ይሸከማል። እናም በአንድ ወቅት ፋኖስ ብርጭቆ አያስፈልገኝም

ብሎ በእብሪት ብቻዬን ማብራት እችላለሁ የሚል ሐሳብ ያነሣል። ምክንያቱም ጋዝ የሚይዘው ታንከር ክሩ በውስጡ ስለአለ የብርጭቆ ዋጋ አልገባውም። ነገር ግን ፋኖስ ከተለኮሰ ከጥቂት ደቂቃ በኋላ ንፋስ የሚከላከለው ብርጭቆ ባለመኖሩ ፋኖሱ ተግባሩን መፈፀም አልቻለም። ከእኛ መካከል የሚጎድል ካለ ልክ እንደዚያ ማለት ነው። ስንሰባሰብ፣ በጀምአ ስንሆን፣ አንድ ላይ ስንሆን፣ የሚኖረን ውበት እና ኃይል ስንነጣጠል አይኖርም።

ነብዩ መሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ከተከታዮቻቸው ጋር በአንድ ወቅት ሲጓዙ፤ አንደኛው ተከታይ "በግ ማረድ እችላለሁ" አላቸው ይባላል። ሁለተኛው ተከታይም "መግፈፍ እችላለሁ" አላቸው። ሦስተኛው ተከታይ ደግሞ "መጥበስ እችላለሁ" አላቸው። እንዲያማ ከሆነ "እኔም እንጨት ለቅሜ ማምጣት እችላለሁ" ብለው ሲነሡ ተከታዮቻቸው ‹እኛ እያለን እርስዎ ሊያመጡ አይገባም የሚል የተቃርኖ ሐሳብ አነሡባቸው። እርሳቸው ግን፤ "ማንም ከማንም አይበልጥም፤ ማንም ከወዳጆቹ ተለይቶ ከፍ ብሎ ሊታይ አይገባም" በሚል ሐሳብ እንጨት ለቅመው እንደአመጡ ዐዋቂዎች ያስተምራሉ። ይህ የሚያመለክተው ምንም የላቀ ጉልበትና ኃይል ቢኖራችሁም ከጀማው ጋር ዝቅ ብላችሁ አንድ መሆን እንደሚገባ በሙስሊም አስተምህሮ ያለና የሚያስፈልግ እውነታ መሆኑን ነው።

በዚሁ አግባብ ረመዳን ሲፆም ለአንዳንዶች ቆሎ ለሌሎች ደግሞ አሻሮ ሊሆን ይችላል። ልክ ብረት ምጣድ ላይ የተጣደ ገብስ ግማሹ ቆሎ ግማሹ ደግሞ አሻሮ ሆኖ እንደሚወጣው ሁሉ፤ ረመዳንም በፍቅር፣ በለጋስነት፣ በደግነት የሚጾሙ እንደቆሎው ምግብና ስንቅ ይሆናሉ። ነገር ግን፤ አዳብ ተብሎ በሚታወቀው በግዴታም በውዴታም በተቀመጠው ነገር በረመዳን ወቅት የሚያደርጉ ሰዎች ካሉ ፆሙ እንደ አሻሮ ይቆጠራል። ይህም ውሸትን፣ ሀሜትን፣ ነሚማን ወይም ማሳበቅን ያካተተ ነው። ሕዝበ ሙስሊም ከውሸት፣ ከሀሜት እና ከማሳበቅ የራቀ እንደሆነ አንድነቱን ሊገዳደር ሊያቆም የሚችል ኃይል የለም። ሙስሊምን ከሙስሊም የሚለይ ውሸት፤ ሙስሊምን ከሙስሊም





የሚለይ ሀሜት፤ ሙስሊምን ከሙስሊም የሚለይ ነሚማ ወይም ማሳበቅ ስለሆነ ሕዝበ ሙስሊም ከእነዚህ ጉዳዮች ተጠብቆ ረመዳንን እንደቆሎ ፍሬያማ ማድረግ ይጠበቅበታል። በእስልምና አስተምህሮ ከቅናት መጠበቅ በተደጋጋሚ የተገለጸ ሲሆን፤ እሳት ደረቅ እንጨት እና ሳር እንደሚያቃጥል ቅናትም እንዲሁ መልካም ነገርን የመብላት ኃይል አለው። የሙስሊም በዚህ መልኩ አንድ መሆን፤ በጀምአ ማፍጠር እንኳን ለሙስሊም ለክርስቲያን ውበት እና መከታ መሆናችሁ ሲታይ፤ ይህንን ለሚጠላ ማንኛውም ኃይል የሚያስቀና ስለሚሆን፤ ቅናት ደግሞ በእምነቱ የተከለከለ ስለሆነ፤ ሰው በንስሐ ከዚህ እሳቤ እንዲላቀቅ እና የጀምአውን አንድነት በፍቅር እንዲቀበል አደራ ማለት እፈልጋለሁ።

የሙስሊም አንድነት፣ የሙስሊም ሰላም፣ የሙስሊም አብሮነት ለሙስሊም ብቻ ሳይሆን ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚጠቅም በመሆኑ፤ በዘንድሮው ረመዳን አንድ ቀን ለኢድ ሲቀር የክርስቲያን ወንድሞቻችሁ የኢድ በዓል ያማረ እንዲሆን በየከተማው ከተሞቹን በማጽዳት ለእናንተ ምቹ ለማድረግ በዝግጅት ላይ ይገኛሉ። የእናንተን የመስገጃ ቦታዎች እና ኢድን ውብ እና ጽዱ ለማድረግ ክርስቲያን ወንድሞቻችሁ በማጽዳት ሲያግዙ፤ እናንተም በኢድ ዕለት ዱአ በማድረግ፣ ያላችሁን ለሁሉም በማካፈል የዘንድሮው ኢድ ከሁሉም በተለየ መንገድ ለሁላችን ያሸበረቀ እንደሚሆን ያለኝን እምነት ልገልጽላችሁ እፈልጋለሁ።

ይህ የምናየው ውበት ከአዲስ አበባ እስከ ታች ቀበሌ ድረስ እንዲደርስ በይቅርታ እና በአቃፊነት መንፈስ እንዲሆን፤ ይህ ጉዳይ ያልገባችሁ፣ ምናልባትም ያልተመቻችሁ፣ ያልተቀበላችሁ ሙስሊሞች ከአላችሁ በቅንነትና በውይይት የሙስሊም አንድነት ከሁሉ በላይ እንደሚልቅ አስባችሁ በመላው ኢትዮጵያ አንድ ጠንካራ የሙስሊም አንድነት እንዲፈጠር ሚናችሁን በቅንነት

እንድትወጡ ከአደራ ጭምር እጠይቃለሁ። በእኛ በኩል ሙፍቲ "በፍጥነት ወደ አላህ መሄድ እፈልጋለሁ፤ ያንን ከማድረጌ በፊት ግን እንድታደርግልን የምፈልገው ነገር አለ" ብለው አጥብቀው ጠይቀውኛል። አንደኛው፤ ኢስላማዊ ባንክ በኢትዮጵያ እንዲፈጠር ነው። ሙፍቲ ሙስሊሙን አንድ በማድረግ ከነበራቸው ሚና በተጨማሪ ወደማይቀረው ከመሄዳቸው በፊት የሙስሊም ባንክ በኢትዮጵያ እንዲያዩ በሚቻለው ሁሉ አድርገን በፍጥነት የምናሳካ መሆኑን ቃል ልገባላችሁ እፈልጋለሁ።

ሁለተኛው፤ ሕዝበ ሙስሊም በኢድ ወቅት፤ እንዲሁም በረመዳን ወቅት ሰብሰብ ብሎ ልዩ መለያ የሆነውን የጀምአ ሰላት በጋራ እንዲሰግድ ሰፋ ያለ ቦታ በመጠየቅ "ለኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች ብቻ ሳይሆን ከሌላ ዓለም ለሚመጡ ሙስሊሞች የሚጎበኙትና የሚያዩት ተለቅ ያለ የኢስላም ምልክት የሆነ መስጊድ እና የጀምአ ሰላት ቦታ መሥራት እንፈልጋለን" ስለአሉ ይህንንም ለማሳካት በጽኑ የምንሠራ መሆኑን በዚሁ አጋጣሚ ላረጋግጥላችሁ እፈልጋለሁ። ነገር ግን፤ ይህ ቦታ ሲሠራ የኔ ፕሮፖዛል፤ የኔ መሻት ሕዝበ ሙስሊሙ ብቻ ሳይሆን ሕዝበ ክርስቲያኑም እንደ ከዚህ ቀደሙ አዋጥቶ ለሁላችን ኩራት የሆነ ነኛሽን የምናስታውስበት ተለቅ ያለ፤ ሌላ ቦታ የማያስመኝ ነገር እንደ ሀገር እንድንገነባ በዚሁ አጋጣሚ ጥሪዬን አቀርባለሁ።

እንደ ሀገር አንድነት፣ ኅብረት አስፈላጊ መሆኑ እሙን ነው። ኢትዮጵያ ተቋማዊ የሆነ እና በሕግ የተደገፈ ጠንካራ የክርስትና እምነት እና ጠንካራ የሙስሊም እምነት ያላት እንደመሆኗ ሁሉም ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሁሉም እምነቶች ካለ ምንም ችግር ይህንን ዘመን መሻገር የሚያስችል ጉልበት ስለሚሆናቸው መንግሥት በጠየቃችሁት እንዲሁም ዐቅም በፈቀደ ሁሉ ከጎናችሁ ሆኖ ለአንድነታችሁ የሚሠራ መሆኑን በድጋሚ ላረጋግጥላችሁ እፈልጋለሁ፤ አረጋግጥላችኋለሁ። በመጨረሻም ሕዝበ ሙስሊም ተፈጥሮን የሚወድ፣ ተፈጥሮን የሚያደንቅ መሆኑ ይታወቃል። ኢትዮጵያ አገራችን ከጥቂት





ዓመታት በፊት 30 በመቶ ገደማ የደን ሽፋን ነበራት። አሁን ግን በአገር ደረጃ 4 በመቶ የደን ሽፋን ደርሶ፤ በረሐማ አካባቢዎች እየበዙ በዝናብ እጥረት ከፍተኛ ችግር እያጋጠመን ስለሆነ ለትውልድ የሚተርፍ የችግኝ ተከላ ዘመቻ ከአንድ ወር በኋላ በክረምቱ ወቅት እንጀምራለን። በዚህም በኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ 4 ቢሊዮን ችግኝ ለመትከል መንግሥት ሙሉ ዝግጅት አድርጓል። ይህ ፕሮጀክት ይቺን ሀገር ከበረሓነት ወደ ለምነት፤ ከችግር ወደ ልማት፤ ከመበታተን ወደ አንድነት የሚያመጣ፤ ለሁላችን የሚጠቅም፤ ለልጆቻችን የሚተርፍ በመሆኑ ከተለያየ የሰላት ወቅት በኋላ ቢያንስ አንድ ሰው ከአርባ ችግኝ በላይ በመትከል መላው የሙስሊም ኅብረተሰብ ከመንግሥት ጎን በመሆን የችግኝ ተከላውን እንዲያግዝ በታላቅ ትሕትና በዚህ በረመዳን ወቅት እጠይቃለሁ!

**መልካም ረመዳን! መልካም አንድነት!**
**በሁሉ ነገር አላህ ይርዳችሁ!**
**አመሰግናለሁ!**

# የኢኖቬሽን ሳምንት መዝጊያ ንግግር

ሰኔ 5/2011 ዓ.ም.

**የተከበራችሁ የዚህ ድንቅ ፕሮግራም ተጋባዥ እንግዶች፣**
**ተሸላሚዎች፣**
**የተሸላሚዎች ቤተሰቦች፣**

ብዙ የሚሸለሙ ሰዎች እንደሚሸለሙ እንኳን ሳያውቁ፣ ሳይወዳደሩ በቀሩበት አገር ውስጥ ጥቂት ተሸላሚዎች ሆናችሁ በመገኘታችሁ እንኳን ደስ ያላችሁ! ማለት እፈልጋለሁ። መፍጠር ከመገልገል የሚለይ በመሆኑ የሚፈጥሩ ሰዎች እየሰጡ መሆናቸውን እንጂ የሚያሸልም መሆኑን የማያውቁ ብዙ አርሶ አደሮች፣ አርብቶ አደሮች፣ በስም የማናውቃቸው ሰዎች፣ ድንቅ ድንቅ ነገር በየሰፈራቸውና በየመንደራቸው እየፈጠሩ እንዳሉ መገመት ይቻላል። ይህ ፕሮግራም እነዚያ ሰዎች ሥራቸው የሚያሸልም፤ ሥራቸው ለማኅበረሰብ የሚተርፍ መሆኑን አውቀው እንዲበረታቱ የሚያደርግ ስለ ሆነ ያዘጋጀውን የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴርን እንዲሁ ማመስገን እፈልጋለሁ።





መፍጠር በአእምሮ የሣሉትን፤ በአእምሮ ያሰቡትን አውጥቶ ለሰው ማሳየት ነው። ፈጣሪዎች ወይም የሚፈጥሩ ሰዎች ወይም ኢኖቬተርስ ያሰቡትን ሕንጻ፣ ያሰቡትን መኪና፣ ያሰቡትን ማሽን በአእምሮአቸው ከሣሉና ከሠሩ በኋላ ትግሉ በአእምሮአቸው የሣሉትን ለሰው በመግለጥ ሂደት ላይ ነው። በአእምሮ ሲሣል ግብዓት አያስቸግርም። ብዙ ገንዘብ አይጠይቅም። በቀላሉ ተገጣጥሞ ማየት ይቻላል። ወደ ውጭ ወጥቶ ሲገለጥ ግን በገንዘብም፣ በአቅርቦትም፣ በሁኔታዎች አለመመቻቸትም ብዙ ስለሚያዳግት መፍጠር የሚችሉ ሰዎች ያዩትን ማሳየት ይቸገራሉ። እንዲህ ዓይነቱ አጋጣሚ ባላደጉ አገራት፤ ብዙ ሀብት በሌላቸው አገራት የሚበራከት ቢሆንም፤ በብዙ የዓለማችን ክፍሎች ሰዎች በአሰቡትና ባለሙት ልክ ገልጠው ለማሳየት ብዙ ድግግሞሽና ጊዜ ያስፈልጋቸዋል።

ለመፍጠር በዓለም ላይ ሁለት የእሳቤ ምሰሶዎች አሉ። የመጀመሪያው የእሳቤ ምሰሶ ክሪቲካል ቲንኪንግ ወይም ሂሳዊ ሐሳብ ይባላል። ሂሳዊ ሐሳብ ብዙ ዳታ፣ ብዙ መረጃ፣ ብዙ ዕውቀት ከውጭ የምንሰበስብበት እና “እንትና ያለው ትክክል ነው፤ እንትና ያለው ግን ይቀረዋል” እያልን የምንተችበት በአካዳሚክሱ የሚገኝ ውጫዊ ዕውቀት ክሪቲካል ቲንኪንግ ላይ ያተኮረ ሲሆን፤ ሁለተኛው ክሬቲቭ ቲንኪንግ የሚባለው፤ ክሪቲካል ቲንኪንግን እንደመሠረት የሚጠቀም ግን ሙሉ በሙሉ በዚያ ብቻ የማይወሰን፣ ከውስጥ ወደ ውጭ የሚወጣ ነው።

በውጫዊ መረጃዎች ላይ የተንተራሰ ሳይሆን በውስጥ ባለው ዕውቀት እሱን ወደ ውጭ ለማውጣት የሚሠራ ሥራ ክሬቲቭ ቲንኪንግ ይባላል። ኢትዮጵያ ውስጥ እንደ እናንተ ያሉ ክሬቲቭ ቲንኪንጋቸውን ተጠቅመው የፈጠሩ ሰዎች ያሉ ቢሆንም፤ መስኩ ከፍተኛ ውስንነት ያለበት ነው። ሰዎች ተመርቀው ሥራ ከያዙ በኋላ ወደ ክሬቲቭ ቲንኪንግ ማደግ ሲገባቸው በክሪቲካል ቲንኪንግ ውስጥ ይቆያሉ። የብዙ ሰው ሐሳብ በማንበብ፣ በመተቸት፣ በመቀነስ ጊዜ ያጠፋሉ። እንደዚያ ዓይነት ዕውቀት አስፈላጊ ቢሆንም፤ ሰዎች ከክሪቲካል

ቲንኪንግ ወደ ክሬቲቭ ቲንኪንግ ማደግ ካልቻሉ ዕውቀት አይወጣም። ለዚህ ነው የኢማጅነሪ ዐቅማችን በጣም ውስን ሆኖ በአገር ደረጃ በብዙ መስክ የምንቸገረው። ለዚህም ነው የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የሚባለውን የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር በማድረግ የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር ለብቻ የሆነበት ዋናው ምክንያት። ክሪቲካል ቲንኪንጉን በከፍተኛ ትምህርትና በሳይንስ ከሠራን በኋላ በኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር አብዛኛው ክሬቲቭ ቲንኪንግ  እንዲሆን ታሳቢ ተደርጐ የተፈጠረ ተቋም ነው። ይህንንም የክሬቲቭ ቲንኪንግ ሐሳብ ለማስፋትና ብዙ ፈጠራ ለማብዛት ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ሀገር ብዙ የምትጠብቅበት መሆኑን መገንዘብ ይኖርበታል።

በክሬቲቭ ቲንኪንግ በአእምሮ የመጀመር፣ የጀመርነውን ለማሳየት ለመጨረስ ዳዴ የምንልበት ሥራ ቀደም ሲል እንዳያችሁት ዓይነት ጅምር ፕሮቶ-ታይፖች ሰው በጭንቅላቱ የሣለውን፣ በአፉም የተናገረውን ለሰው ለመግለጥ የሚያደርገው ጥረት ሲሆን፤ እነዚህ ሥራዎች ከሰው በሚገኝ ትችት በክሪቲካል ቲኒኪንግ እየበለጸጉ እያማሩ እየተዋቡ ወደ መጨረሻው ውጤት ይሄዳሉ። መጀመር ብቃት ነው። መጨረስ ግን ጀግንነት ነው። ዛሬ የተሸለማችሁ ተሸላሚዎች ጀማሪዎች እንጂ ጨራሾች አይደላችሁም። የሸለምናችሁ ስለጀመራችሁ ነው። ጨርሳችሁ ጀግና ስትሆኑ ግን አንድ ሚኒስቴር ሳይሆን ሀገር፣ ምናልባትም አህጉር፣ ከዚያም አልፎ ዓለም ይሸልማችኋል። ዓለም እንዲሸልማችሁ የጀመራችሁት ነገር በጅምር እንዳይቀር ለመጨረስ ለመጀገን እንድትተጉ አደራ ልላችሁ እፈልጋለሁ።

በመጀመር መዘናጋት፣ በመጨረስም መኩራራት አያስፈልግም። ብዙዎች ይጀምሩና ይዘናጋሉ። አንዳንዶች ደግሞ የጨረሱ ይመስላቸውና ይኩራራሉ። መጨረስ ከእኛ አልፎ ብዙዎችን ሲነካና ሲቀይር ስለሆነ በመጀመር እንዳትዘናጉ፣ በመጨረስም እንዳትኩራሩ የስኬት የመጨረሻው የደስታ





መለኪያ መስጠት መሆኑን አውቃችሁ ከጭንቅላታችሁ አውጥታችሁ በማሳየት እንደሰጣችሁ ያ የሰጣችሁን የመጀመሪያው ውጥን አርሶ አደሩን በማዘመን፣ አርብቶ አደር በማዘመን፣ ሀገረ መንግሥቱን በማዘመን የሰዎች ሕይወት እንዲቀይር በቀጣይነት መስጠት ያስፈልጋል።

ኢኖቬተርስ በክፍያ ሳይሆን በነፃ ስጦታ ያምናሉ። ከዚህ ቀደም ያነሣሁት ፍሪሊዮን ወይም የነፃ ስጦታ ሐሳብ ፍሪ ሚል የሚሠራው ለሚፈጥሩ ሰዎች ነው። የሚፈጥሩ ሰዎች በዘመናቸው እንኳን ሊመሰገኑ፤ እንኳን ሊሸለሙ ይቅርና ብዙ ሰው አይገነዘባቸውም። ቤተሰብ አይገነዘባቸውም። መምህር አይገነዘባቸውም። ካሉበት ዐውድ ወጣ ያለ ሐሳብ ስለሚያራምዱ ብዙ ሰዎች ንክ እንጂ ፈጣሪ አድርገው አይወስዷቸውም። ያን እልህ አስጨራሽና አድካሚ ሁኔታ አልፎ ውጤት ለማምጣት በነፃ መስጠትና ክፍያ ፈጽሞ አለማሰብ ይፈልጋል። ምክንያቱም ሰዎች ላልተገነዘቡን ሐሳብ ሊከፍሉን ይቅርና ሊያበረታቱንም አይችሉም። ክፍያ ሳናስብ በነፃ ከሠራን ጨርሰን ጀግኖች እንሆናለን። ክፍያ እያሰብን መሐል ላይ ከቆምን ግን ያሰብነውን ሳንሰጥ እንድንቀር ያደርጋልና ከዚያ ለመውጣት እውነተኛውን የመስጠት ደስታ ለመጎናጸፍ በርትታችሁ ሥራችሁን እንድትቀጥሉ አደራ ማለት እፈልጋለሁ።

በሀገራችን ብዙ ጊዜ ላለመፍጠር እንደ ምክንያት የሚነሣው ኢትዮጵያ የሰጠችን ውስን ስለሆነ በዚያ ውስን ስጦታ አዲስ ነገር ፈጥረን አበልጽገን መስጠት እንቸገራለን የሚለው ሐሳብ ነው። ነገር ግን የስጦታ ማነስ ስኬታችንን አንቆ ሊያስቀር አይችልም። በዓለም ላይ አዳዲስ ነገር የፈጠሩ ሰዎች መሠረታዊ ስጦታ በመጠቀም እንጂ የተለየ ድጋፍ ታሳቢ በማድረግ አይደለም። መፍጠር ባልተመቸ ሁኔታ የሚመች ነገር መሥራት እንጂ፤ በሚመች ሁኔታ ነገር ማሻሻል ስላልሆነ ባይመችም መፍጠር እንደሚቻል በዓለም ላይ ያሉ የፈጠሩ ሰዎች ብቻ ሳይሆኑ ኢትዮጵያውያንም በተደጋጋሚ

በተለያየ መስክ አስመስክረዋል። ለምሳሌ፡- መሠረታዊ ቀለማት የሚባሉት ሰባት ናቸው። ከእነዚህ ሰባት ቀለማት ውስጥ በማቀላቀል አዳዲስ ቀለማትንና ውብ ሥዕሎችን በማሳየት ከዓለምም ከአገር ውስጥም መጥቀስ የምንችላቸው ሰዎች አሉ።

ሊዮናርዶ ዳቬንቺን ብንወስድ፤ ይህ ሰው ከብዙ መቶ ዓመታት በፊት አውሮፕላንን ጨምሮ፣ መኪናና የተለያዩ ፈጠራዎችን ሲፈጥር፣ በሥዕል ሲያሳይ በወቅቱ አውሮፕላን የሚባል ነገር አልነበረም። በዚያ ጊዜ እብድ ተብሎ የተወሰደው ሊዮናርዶ ዳቬንቺ ከዓመታት በኋላ ከ70 ገጽ ያላለፈው ጹሑፉ ግን በብዙ ሚሊዮን ዶላር ተሽጧል። በዘመኑ ባይገነዘቡትም ትውልድ ሲደርስና ሲነቃ ፈጠራውን ማየት ችሏል። በዚህ ቀለማትን ተጠቅሞ ፈጠራ በመፍጠር እንደ ዓለም ሁሉ በእኛም ዘንድ አፈወርቅ ተክሌን፣ ገብረ ክርስቶስ ደስታን መጥቀስ ይቻላል።

ሌላ ቦታ ያየነውን የፈጠራ ብቃት ኢትዮጵያውያን ውስን ቢሆኑም ድንቅ በሆነ ሥራቸው ከእኛ አልፈው ዓለም እንዲያወድሳቸው መሆን የቻሉት የተለየ ስጦታ፤ የተለየ ትምህርት ቤት ስለነበረ ሳይሆን መፍጠር ከችግር ውስጥ የሚያምር ፍሬ ማውጣት መሆኑን በመገንዘባቸው ነው።

እንደዚሁም የሙዚቃን ኖታ ብንወስድ ስምንት መሠረታዊ ኖታዎች አሉ። ከነዚህ ድምፀት ውስጥ አዋሕዶ ጣዕመ ዜማ በማፍለቅ ሞዛርት እንደሚጠቀሰው፣ ቬትሆቨን እንደሚጠቀሰው ሁሉ፤ እኛም ቅዱስ ያሬድን እንጠቅሳለን። ዶ/ር አሸናፊን እንጠቅሳለን። ሙላቱ አስታጥቄን እንጠቅሳለን። ይህም መሠረታዊ ኖታዎች ለቬትሆቨንም ለሙላቱ አስታጥቄም እኩል መሆናቸውን የሚያሳይ ሲሆን፤ እዚያ ያለው ሥልጣኔና የግብዓት መገኘት ግን እዚህ እንደዚያ ቀላል ላይሆን ይችላል። ለመፍጠር መሠረታዊ ስጦታን ብቻ መጠቀም ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ እነዚህ ሰዎች ህያው ማስረጃ መሆን ይችላሉ።





የሒሳብ መሠረትን ብንወስድ ከዜሮ እስከ 10 ያሉ ቁጥሮች ናቸው። ቢሊዮን፣ ትሪሊዮን እያልን የምንቆጥረው ከዜሮ እስከ 10 በተሰጡን መሠረታዊ ስጦታዎች ነው። እነዚህን በመጠቀም በሳይንሳዊ ስሌት በርካታ የፈጠራ ግኝቶች ያስገኙ ዓለም አቀፍ ሰዎች አሉ። ዛሬ ተሸላሚ ከሆኑ ሰዎች መካከልም አንዱ የሒሳብ ቀመር ሠርቷል። ይህ የሒሳብ ቀመር የሠራው ወጣት ኢትዮጵያዊ፤ በአዲስ አበባ አካባቢ የማይገኝ ራቅ ካለ ቦታ ብዙ ግብዓት፣ ብዙ ቴክኖሎጂ ከሌለበት የሚኖር፤ ግን ምጡቅ አእምሮውን በመጠቀም እና መሠረታዊ ስጦታውን በማድነቅና ዕውቅና በመስጠት ወደላቀ ነገር ለመሄድ የወሰነ በመሆኑ ጅምሩ ከፍሬ እንዲበቃ የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ከጐኑ በመሆን ሐሳቡን በሶፍትዌር በመደገፍ ለዓለም የሚበረከት አዲስ ስጦታ ከእኛ መካከል ሊወጣ እንደሚችል አመላካች ሆኖ አግኝቼዋለሁ።

የዲጂታሉን ዓለም ብንወስድ ዜሮን እና አንድን እንደ መነሻ አድርጐ በጣም በርካታ ነገሮች መፍጠር ተችሏል። እነዚህን መሠረታዊ ስጦታዎች ለእኛም የተሰጡን መሆኑን አምነን ከተቀበልን፤ እኛም እንደሌሎቹ መፍጠር የማንችል፤ ያልተሰጠንና ድሃዎች መሆናችንን እያሰብን የምንሄድ ከሆነ ግን ያላቸው አዳዲስ ነገር እየፈጠሩ፤ እኛም የእነሱን እያየን እንድንቀር ይሆናል። ከነዚህ ውጭ ባሉ መስኮች በፍልስፍናው መስክ እንደ አንድ ምሳሌ ብንወስድ ፍልስፍና በራስ ብርሃን እውነትን መፈለግ ነው። በውስጥ ብርሃን እውነትን መፈለግ ነው። በውጫዊ ብርሃን የሚፈለግ እውነት ሳይሆን በውስጣዊ ብርሃን የሚፈለግ እውነት በዓለም ላይ ስመጥር ከሆኑ ሰዎች በፊት የእኛው ዐዬ ዘርዓ ያዕቆብ ድንቅ ፈላስፋ መሆኑን በብዙ ማስረጃ ማረጋገጥ ይቻላል። ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ከሚያስደቁ ፍልስፍናዎቹ አንዱ ለፍርድ ወይም ለብያኔ ያለዉ እሳቤ ነው። ከግራም ሲሰማ የሚበይን፣ ከቀኝም ሲሰማ የሚበይን፤ ሳይሆን ከግራና ከቀኝ የሰማውን አድምጦ አክብሮ የራሱን እሳቤ ለማፍለቅ የሚደፍር ጀግና ነበር።

እንደዚህ ዓይነት ዕውቀት ራሳችንን የምናውቅበት፣ አካባቢያችንን የምናውቅበት፣ ማኅበረሰብ የምንጠቅምበት መሣሪያ መሆኑን ለማየት ይቻላል። ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ወይም ደቀ እስጢፋኖስ አንዳንዶች ወርቅ ብለው የሚጠሩት ፈላስፋ ኢትዮጵያ ነበራት። በውጭ ከምናውቃቸው ፈላስፋዎች ባልተናነሰ ደቀ እስጢፋኖስ ብቻ ሳይሆን እጓለ ገብረዮሐንስንም ብንወስድ ልክ አሪስቶትል እንደምንለው፤ ሶቅራጥስ እንደምንለው የእኛዎቹም ፈላስፋዎች የውስጥ ብርሃናቸውን ተጠቅመው ለእኛም ለዓለምም ድንቅ እሳቤ እንዳበረከቱ ማየት ይቻላል። ከዘርዐ ያዕቆብ ፍልስፍና ውስጥ አንዱን ብንወስድ፤ እሳቤው ራስህ ጥሩ ሳትሆን፣ ራስህ መልካም ሳትሆን መልካም ነገር ማየት የምትችግር መሆኑን የሚያሳይ ነው። በውስጥህ የሌለን ደስታ፣ በውስጥህ የሌለን ብርሃን፣ በውስጥህ የሌለን መልካምነት ለሌላው መስጠት አይቻልም።

ክሪቲካል ቲንከርስ ሁል ጊዜ ጨለማ ጐልቶ የሚታያቸው ናቸው። ከውስጥ ፍንጣቂ ብርሃን ማየት የሚችሉት በመጀመሪያ ደረጃ የነሱን ማንነት ነው። በእያንዳንዱ ሥራ ጨለማን አጐልተው የሚገልጡ ሰዎች በውስጣቸው የብርሃን ማነስ እንዳለ ያሳያል። ራስህ መልካም ሆነህ መልካምነትን መግለጽ" የሚል ትልቅ ትምህርት የገለጠው ፈላስፋ ኢትዮጵያዊ ነው። ሶቅራጥስ በተወለደበት ሀገር ብቻ ሳይሆን በእኛም አገር ድንቅ እሳቤ ማፍለቅ የሚችሉ ፈላስፋዎች መፍጠር ተችሏል። ይህ ጉዳይ እንዲያድግ እንዲበለጽግ ማድረግ ከሚገባን አንዱ ነገር በየጊዜው ተማሪ መሆን ነው። ትምህርት አያልቅም። መፍጠር አያልቅም። ማይክሮሶፍት የተባለለትን ዕድሜ እና ገንዘብ ያፈለቀው በየዓመቱ አዳዲስ ነገር በመፍጠር ነው። በሳምሰንግና አፕል እድገት የምታዩት በየጊዜው አዳዲስ መተግበሪያዎችን እየጨመሩ በቀጣይነት እየፈጠሩ የሕዝብን ፍላጐት ለማርካትና ቀድመው ለመገኘት በመትጋታቸው ነው።

የዛሬ ተሸላሚዎች እንድትገነዘቡ የሚያስፈልገው ብረት የድንጋይ ዘመንን ተከቶ ሲመጣ ብረትም ድንጋይም የተፈጠሩት ከአፈር ነው። የብረት ዘመን ሲፈጠር ድንጋይ ስላልነበረ አይደለም። የብረት ዘመን ሲፈጠር ድንጋይ ከሥራ ውጭ ሆኖም አይደለም። ድንጋይ እያለ ብረት ልቆ መጣ። ብረትን ብረት የሚያደርገው በየጊዜው መሳሉ፣ መወልወሉ፣ መጠበቁ ነው። ብረት ለአንድ አፍታ እንክብካቤ አጥቶ ከአፈር ጋር እንዲኖር ካደረግነው ፈጥኖ አፈር ከሚሆኑ ቁሶች አንዱ ነው። ብረት ብረት ሆኖ እንዲቀጥል በየጊዜው መሞረድ አለበት፣ መወልወል አለበት። ፈጠራም ፈጠራ እንዲሆን በየጊዜው መሻሻል አለበት። መተቸት አለበት። በአንድ ጊዜ የሚያበቃ አይደለም። በብረት ዘመን ድንጋይን ጠቅልለን እንዳልጣልነው ሁሉ በፈጠራ ዘመንም አዲስ ነገር ስንፈጥር የቀደመውን ጠቅለን እንጥላለን ማለት አይደለም። መሠረት እየሆነ እየተሰናሰለ አብሮ እንዲሄድ ማድረግ ያስፈልጋል። የቀደመውን ሳትጥሉ አዳዲስ ለመፍጠር ከተጋችሁ ኢትዮጵያ የምትኮራባችሁ፣ አህጉራችንም የምትመካባችሁ ፈጣሪዎች ከዚህ መካከል ልትኖሩ እንደምትችሉ ከሥራችሁ ተነሥተን መገመት አንቸገርም።

ከዕውቀታቸው ለኢትዮጵያ ከፍለው የሰጡ፤ ከዕውቀታቸው ኢትዮጵያን ከፍ የሚያደርግ ነገር የሠሩ የፈጠራ ሰዎች እንዳሉ ሁሉ፤ ዕውቀት አለን ብለው ጭለማን የሚዘሩ፣ መለያየትን የሚዘሩ፣ መጠፋፋትን የሚዘሩ ሰዎች አሉ። የዕውቀት የመጨረሻ መለኪያ ለማኅበረሰብ መጥቀም እንጂ ማኅበረሰብን ማባላት አይደለም። ዕውቀት በመተባበር፣ በመደጋገፍ፤ እንዲሁም በውድድርና በፉክክር እነዚህን በማዋሐድ የሚሠራ እንጂ ሁል ጊዜ በእሽቅድድም እና ጥሎ በማለፍ መርሕ የሚሠራ ባለመሆኑ እናውቃለን ብለው ሕዝብን የሚያጋጩ፣ እናውቃለን ብለው ጦርነት የሚያውጁ ሰዎች ዕውቀት ማኅበረሰብን ማስታረቅ፣ ማኅበረሰብን ማዋሐድ እና ማሻገር እንደሆነ ከእነዚህ ወጣት አዳጊዎች ትምህርት እንዲወስዱ አደራ ማለት እፈልጋለሁ።

ፈጣሪዎች የብቸኝነትን ጉድለት መሙላት ይኖርባችኋል። የሒሳብ ቀመር ከአእምሮ አፍልቆ የሠራው ወጣት የሶፍትዌር ሙያተኛ ያስፈልገዋል። ያን

እሳቤውን በዘመናዊ መንገድ በአፕልኬሽን ለመሥራት ሌላ ሙያ ሌላ ዲሲፕሊን ያስፈልገዋል። ቅድም ከደቡብ ያያችሁት ሕፃን ልጅ የግንባታ መሣሪያ የሠራው በብረት እነዚያን ፕሮቶታይፕ የሚሠሩ ስሪንጁንም ሳይታይ በተች በተን የሚቀይሩ ሌሎች ሙያተኞች ያስፈልጉታል። ከእነዚህ ጋር በመደመር አዳዲስ ዕውቀት መፍጠርና ዕውቀትን ለጥቅም ማዋል ስለሚያስፈልግ የፈጠራችሁ ሰዎች ዓለም ሁሉ በእጃችሁ እንዳለ ሳይሆን በሌላ መስክ ከእናንተ የሚሻሉ ሰዎች እንዳሉ በመረዳት፤ የእናንተን በመስጠት የእነሱን በመቀበል የተሻለና የላቀ ነገር መፍጠር አለባችሁ። ቦይንግ የብዙ ሰዎች የፈጠራ ውጤት ነው። ኮምፒውተር የብዙ ሰዎች የፈጠራ ውጤት ነው። ስልክም እንደዚሁ የብዙ ጭንቅላት ውጤት ነው። አንድ ሰው ጀምሮ የሚጨርሰው ሳይሆን በትብብርና በመደመር እንዲጐለብት ማድረግ ይኖርብናል።

አሁን ባለው ዘመን 4.0 ወይም አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ የሚባለው አራተኛ ኢንዱስትሪያል አብዮት እየበለፀገና እያደገ የሰዎችን ሥራ እየተካ እንደመጣ ይታወቃል። ከጥቂት ዓመታት በኋላ በአሜሪካ ብቻ 15% የሚጠጉ ሠራተኞች በአርቴፊሻል ኢንተለጀንስ እንደሚተኩ ተገምቷል። እየታየም ይገኛል። መኪናም አውሮፕላንም ሰው አልባ እየሆኑ ስለ ሆነ ኢትዮጵያ ውስጥ ሰው አልባ ነገር መፍጠርና የሰው ሥራ መተካት ሳይሆን ሰው አልባ ነገር ከፈጠሩት ጋር ለመወዳደር፤ ሰውን ይበልጥ ለመጠቀም እያንዳንዱ ሰው ያለውን ህልቆ መሳፍርት የሌለውን አቅም ማውጣትና ለውድድር የሚያበቃ ዐውድ መፍጠር ያስፈልጋል። ከዚህ አንፃር የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የተጣለበት ሐላፊነት ኢትዮጵያውያን በየዓመቱ አዳዲስ ነገር እየፈጠሩ እንዲሸለሙ እና በሚቀጥለው ዓመት እንዲረሱ ሳይሆን፤ የፈጠሩ ሳይዘነጉ ወደ ውጤት እንዲቀየር ሥራቸውን ከሌሎች ዲሲፕሊኖች ጋር ማዋሐድ፣ በፋይናንስ ማገዝ፣ ከኢንደስትሪዎች ጋር ማስተሳሰርን ጨምሮ ውጤታማ እንዲሆኑ ለማድረግ በከፍተኛ ሐላፊነት መሥራት ይኖርባችኋል።





በአጠቃላይ ወጣት ተመራማሪ መምህራን ኢትዮጵያውያን አእምሮአችሁ መልካም አዝመራ የሚመረትበት ለም መሬት እንጂ የሞት ነጋሪት የሚጐሰምበት የመቃብር ሥፍራ እንዳይሆን፤ አእምሮአችንን መልካም መልካም ነገር በማፍለቅና ለፈጠራም በማዋል እንድንገለገልበት ከእኛ አልፈን ሰዎችን ማገልገልና ማገዝ እንድንችል፤ ይህ ደግሞ ከቅንነትና ከውስጠ ብርሃንነት ውጭ የሚታሰብ ስለአልሆነ ለአሉታዊ ጉልበት የምናጠፋውን ጊዜ በመቀነስ፣ በመደመርና በጋራ እድገት ውስጥ በመመሥረት አዲስ አድማስ መመልከት፣ ውቅያኖስን ተሻግሮ ማየትና የላቀች ኢትዮጵያን ለመፍጠር መተባበር ከሁላችን የሚጠበቅ መሆኑን በዚሁ አጋጣሚ ልገልጽላችሁ እፈልጋለሁ።

አብሮነት እንጂ የአፓርታይድ አስተሳሰቦች፣ ዘረኝነት፣ ጥላቻ ለእኛ ለኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆን ለመላው ዓለም ጥፋት መሆናቸው በዘመናት መካከል ትምህርት ተወስዶበታል። ጥላቻ የሚያኮስሰን አዳፋ ጨርቅ እንጂ የሚያለመልመን ነገር አይደለም። አዳፋውን ጨርቅ ወይም አጥበን ወይም ቀይረን በማስወገድ ኢትዮጵያ አዲሲቷ የተስፋ አድማስ እንድትሆን በትብብር መንፈስ ከትናንሽ ነገር እስከትላልቁ የተደመረ፤ የተሰናሰለና የተቀናጀ ሥራ በመሥራት ለትውልድ መልካም ሀገር መተው እንድንችል በታላቅ ትሕትና ሁላችሁንም አደራ እላለሁ። በመጪው ሰኔ 16 ያለፈውን ዓመት ሰኔ በማስታወስ፣ በመቆዘም፣ በመራገም ከምናጠፋው ሁላችንም በአለንበት አካባቢ የአካባቢ ጽዳት እና ችግኝ በመትከል፣ ክፉውን ነገር በመልካም በመተካት፤ ንጹሕ ንጹሑን በሠፈራችን፣ ንጹሕ ንጹሑን በጭቅላታችን፣ ለትውልድም አረንጓዴ ኢትዮጵያን ለመተው በጋራ እንድንሠራ አደራ ልላችሁ እፈልጋለሁ።

በድጋሚ እንኳን ደስ አላችሁ! ጅምራችሁ ፍሬ እንዲያፈራ መንግሥት በሚችለው ሁሉ ከጐናችሁ እንደሚሆን አረጋግጣለሁ።

**አመሰግናለሁ!**

# የደሴ ነዋሪዎች ውይይት ንግግር

ሰኔ 8/2011 ዓ.ም.

ወሎ ከመጣህ ሰው መሆን ያስፈልጋል። ይህም ማለት ወሎዎች እንደ ሰው የመጣባቸውን በዘር በሀይማኖት ሳይለዩ የሚቀበሉ፣ ወደሰው ሲሄዱም እንደ ሰው የሚቀርቡ ናቸው። እንደ ሰው መጥተንባችኋልና እናንተም እንደ ሰው ተቀበሉን። የባህል ማእከሉን በጣም ነው የማመሰግነው! ድንቅ በሆነ መንገድ ኢትዮጵያዊነትን እና የወሎ ነገሥታት ወሎን ባስቀመጡት ልክ ወሎን ስለገለጣችሁት እጅግ አድርጌ ላመሰግናችሁ እፈልጋለሁ! ስለወሎና ስለነገሥታቶቿ ብዙ መናገር አያስፈልግም። እዚህ አዳራሽ ውስጥ ያለ ሰው ወሎን በዚህ ልክ ነበር የሚያስበው። የዛሬን አያድርገውና የቀደሙቱ ልካችንን አሻራ አስቀምጠው ስለአሳዩን የወሎ ልክ እንደዚህ ነው። ከፍ ያለ ግርማ ሞገስ ያለው፤ ብዙ የሚያቅፍ፤ ብዙ የሚይዝ፤ ለብዙ የሚበቃ መሆኑን የዚህ አዳራሽ ሥራ ብቻውን ምስክር መሆን ይችላል። ከፍልስፍናው አንፃር ብዙዎቻችሁ የምታውቁት የሼህ ሁሴን ጅብሪል ለብዙዎች ዕውቀት የሆነ ሐሳብ፤ ከዚያ ትንሽ ለመጨመር በፍልስፍናው ዓለም ጎበዝ ፈላስፋዎች ተብለው የሚወደሱ ሰዎች፣ የሚነገርላቸው ሰዎች፤ በመጠየቅ ብርታት ጠይቀው ጠይቀው ‘ፈጣሪ አለ ወይ?’ ብለው ሲጠይቁ ተፈላሰፉ ይባላል። ብዙዎቹ ፈላስፋዎች ይጠይቁና መልስ የላቸውም። የወሎ ፈላስፎች ግን መልስ አላቸው።





ሰይድ እና ሙሄ የሚባሉ የወሎ ሰዎች ጓደኛሞች እየተጨዋወቱ እያወቁ ሰኢድ ሙሄን “እንደው አላህ እንዳለ በምን ታውቃለህ?” ብሎ ጠየቀው ይባላል። ሙሄም ጥያቄው የፍልስፍና ጥያቄ መሆኑን ስለሚያውቅ በፍልስፍና መንገድ ሲመልስለት “ካላሰብኩት ሲያውለኝ” አለው ይባላል። ፈጣሪ አለ ወይ የለም ብሎ መጠየቅ ፍልስፍና ከሆነ፤ ሙሄ እንዳለው ከአሰብኩበት ውጪ ሆኜ መገኘት ደግሞ በእኔ ሥልጣን የተወሰነ ስላልሆነ ከእኔ ባሻገር ኃይል አለ የሚለውን ወለዬዎች በክርስትናና በእስልምና እምነት ብቻ ሳይሆን በፍልስፍናም ያረጋገጣችሁት ስለሆነ እንዲሁ እምነት የሌለው ሰው አይኑር። እምነት አስፈላጊ ነው። ሰው ፈጣሪውን ሲያምን፤ ሰው ወንድም እኅቱን ሲያምን፤ ሰው ጎረቤቱን ሲያምን፤ ሰው አገሩን ሲያምን ብዙ መልካም ነገሮች አሉ። እዚህ አዳራሽ ይኼን የሚያክል ሰው የተሰበሰበው እምነት ስለአለ ነው። እምነት ባይኖር ኖሮ ከፊት ለፊት የተቀመጡት ሰዎች ከኋላቸው ጀርባቸውን ለማያውቁት ሰው ሰጥተው አንድ ሰአት መቀመጥ አይችሉም። ያምናሉ። ከኋላ ያለው ወንድሜ ነው፤ ክፉ አይደርስብኝም ብለው ስለሚያምኑ ነው። እምነት ከሌለ ወጥቶ መግባት አይቻልም። ለወሎ ባህል ማእከል ስለ መደመር በጣም ጥልቅ ሐሳብ አንሥተዋል። ሐሳቡ ጥልቀት ኖሮት እንዲሰፋ የመደመር ሐሳብ ልክ እንደ ሙሔና ሰይድ ፍልስፋና መነሻው አንድ ሰው ነው። ከሰው የተነሣ ነው አንድ ሰው ራሱን በመስታወት ሲያይ ያየሁት እኔን ነው ብሎ ያስባል። ግን ሞኝ ነው። ያየው ራሱን አይደለም።

አንድ ሰው በቢሊዮን በትሪሊየን የሚቆጠሩ ራሳቸውን ችለው የሚንቀሳቀሱ ሴሎች አሉት። ሰው ሴል ነው። እነዚያ ትሪሊየን ሴሎች ባይደመሩ ኖሮ ያ ሰው እኔ ብሎ የገለጸው ነገር አይፈጠርም። ያ ሰው ጆሮ አይደለም። ያ ሰው ዐይን አይደለም። ያ ሰው እጅ አይደለም። ጥርስ አይደለም። ያ ሰው አንድ ሰው ነው። እኔ ያለው ግን ጆሮውንም፣ ጥርሱንም፣ ዐይኑንም፣ በቢሊዮን የሚወከል ሴሉንም ጨምሮ ወክሎ ነው። እኔ ያለው እነሱን አታስፈልጉም፤ ዐይን አያስፈልግም፣ ጆሮ አያስፈልግም ቢል አምባቸው አምባቸው መሆን አይችልም። ዐይኑ ስም አለው። ዐይኑ ቦታ አለው። ዐይን አድራሻ አለው፤ ልክ

እንደ ኦሮሞ እንደ አማራ ዐይን አድራሻ አለው። ነገር ግን፤ አምባቸው እጅ አለው፤ ጆሮ፣ አድራሻ አለው። ሲሰበሰብ አምባቸው ነው።

ይኼም የማይገለጥና የማይገባ ከሆነ ብዙ ሰዎች ሲናገሩ በአማርኛ "እኔ ራሴ" ይላሉ። እኔ ማነው? ራሴ ማነው? "ከራሴ ጋር ተጣላሁ"ም ይላሉ። እንዴት ሰው ከራሱ ጋር ይጣላል? ሁለት ካልሆነ በስተቀር እኔ እና ራሴ ማን እና ማን ናቸው? በውስጣችን የሚደመር ማንነት እንዳለ ስንገነዘብ ከጎረቤት፣ ከሌላ ሰው፣ ከሌላ ጉርብትና እና መደመር አስፈላጊ መሆኑ ይገባናል። በዚህ ዘመን ብዙ ሰው የመደመርን አስፈላጊነት ካለመገንዘብ ስለ ራሱ፣ ስለ ሰፈሩ፣ ስለ መንደሩ የሚናገር ብዙ ሰው ነው ያለው። እኔ የወሎ ሕዝብ የፍቅር ሕዝብ ስለሆነ፣ ስለሚገነዘብ እዚህ ደሴ ላይ መናገር የምፈልገው በጋራ ከሆንን ምንም ይሁን ምን ማሸነፍ እንችላለን። በተናጠል ምንም ያህል ገንዘብ ይኑረን፣ ምንም ያህል መሣሪያ ይኑረን፣ ምንም ያህል የተደራጀን እንሁን፣ ለተወሰነ ጊዜ አቧራ እናስነሣለን እንጂ በዘላቂነት አሸናፊ መሆን አንችልም። ዘላቂ ድል የሚገኘው ከትብብር፣ ከፍቅር፣ ከአብሮነት እና ከመስጠት ነው። ይኼን ለወሎ ሕዝብ መናገር አያስፈልግም። ሕይወታችሁ ስለ ሆነ።

ኢትዮጵያን የሚያክል ድንቅ አገር ብዙ ገራገር ማንነት የተላበሱ ሰዎች ያሉበት አገር፣ ብዙ ፈላስፎች፣ ብዙ ምሁራን፣ ብዙ የተጉ ሰዎች ባሉበት አገር፤ ከፊታችን ያለውን ተግዳሮት በጋራ እንዴት እንደምንወጣ እያሰብን፤ ሁሉም ያለውን እያዋጣ፣ በዕውቀትም በገንዘብም በሐሳብም ካልሄድን በስተቀር፤ አሁን ዓለም ላይ ያለው ሁኔታ አንዱ ዘንድ ግጭት ሲፈጠር ሌላ ማስታረቅ የሚችልበት ሁኔታ አይደለም። ሁሉም በራሱ ሰፈር ጉዳይ ተጠምዷል። የእኛ አካባቢ ጉዳይ ድንበር ተሻግሮ መፍትሔ መሆን እንዲችል የወሎ ሕዝብ ወሎ ሆኖ ከተገኘ በቂ ነው። ራሱ ወሎ ማለት መደመር ማለት ስለሆነ፤ ወሎዬዎች አማራንና ትግራይን ማስተሳሰር የሚችል የሚጨበጥ ታሪክ አላቸው። እኛ እኮ በዚህ ጊዜ እንዲህ አድርገን፤ እንዲህ አድርገን ብላችሁ፤ ከፈለጋችሁ አማራንና ትግራይን ድልድይ ሆናችሁ አንድ ማድረግ ትችላላችሁ። የሚጨበጥ ታሪክ ስለአላችሁ፤





ወሎዬዎች ኦሮሞን እና አማራን አንድ ማድረግ ትችላላችሁ። በተጨባጭ ታሪክ ስለአላችሁ፤ ወሎዬዎች እስላምና ክርስቲያንን በአንድ መብላት፤ በአንድ መኖር እንደሚቻል ታሪክ ሠርታችሁ አንድ ማድረግ ትችላላችሁ። ሁሉም እናንተ ዘንድ ስለአለ እንደ ትልቅነታችሁ፣ ልክ እንደ አዳራሻችሁ ከፍ ብላችሁ ይሄንን ከራሱ ጋር የተጣላውን ማንነት እንዲሰባሰብና ትልቋን ኢትዮጵያ ከፍ ማድረግ የሚችል ትውልድ እንዲነሣ የበኩላችሁን አስተዋጽዖ እንደምታደርጉ ሙሉ እምነት አለኝ።

ዛሬ ወደዚህ የመጣነው መደመርን ጀምረነው በደንብ እንዲገባን፤ ፍቅርን ጀምረነው በደንብ እንዲገባን፤ ይቅርታን ጀምረነው በደንብ እንዲገባን ለምን ከዋናው ከምንጩ ጋር አንገናኝም? ወደ ምንጩ ብንሄድ እኮ ይገለጽልናል! ወሎዬዎች ጠላት ሲመጣ ሰይፍ መዝዘው አድዋ ላይ ተዋግተዋል። ያኔ የነበረው ሰይፍ የጠላት አንገት የሚቀላ ነው። የአሁኑ ሰይፍ ደግሞ የመጀመሪያው "ሰ" ሰላም፤ ሁለተኛ "ይ" ይቅርታ፤ "ፍ" ፍቅር ከሆነ ኢትዮጵያን አንድ ማድረግ ይችላሉ ብለን ተማምነን፣ የምናውቀውን ተናግረን፣ የማናውቀውን ተምረን፣ ከእናንተ ጋርም ያለውን አብሮነትና ፍቅር ገልጠን፣ ልማት ሰላም ከአለ፤ ፍቅር ከአለ፤ አንድነት ከአለ ሊመጣ እንደሚችል የጋራ ዓላማ ሰንቀን በጋራ እንድንሠራ ጥሪ ለማቅረብ እፈልጋለሁ። እስከ አሁንም ቢያንስ ደሴ ላይ ወሎ አላልኩም። ላሊበላ ቢያንስ ሁለቴ ስለ ሄድኩኝና ደሴ እስከአሁን ስለአልመጣሁ በአካል መጥቼ ሰላምታ ለማቅረብ ነው። ስለ መጣንም በጣም ደስታ ይሰማናል! እንኳን አየናችሁ! ከሩቅ እንደሚባለው ደሴ የፍቅር ሕዝብ ነው። እናንተ መሐል በመገኘታችን ትልቅ ክብር ይሰማናል። ምናልባት ምክር፣ ተግሣጽ፣ ጥያቄ፣ አስተያየት ከአላችሁ መድረኩን ለእናንተ ሰጥተን የእናንተን ብንሰማ የበለጠ ውይይታችን የተሻለ ስለሚሆን እንድታቀርቡ መድረኩን ለእናንተ ክፍት አደርጋለሁ።

**አመሰግናለሁ!**

# የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የምረቃ በዓል ንግግር

ሐምሌ 6/2011 ዓ.ም.

**ክብርት ወ/ሮ መዐዛ አሸናፊ፣ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት፣
ክቡር ፕሮፌሰር ጣሰው ወልደሃና፣ የአዲስ አበባ ዩኒቪርሲቲ ፕሬዚዳንት፣
እጅግ የተወደዱ የተከበሩ የዘመናችን ድንቅ አባት ሙፍቲ ሀጂ ዑመር እድሪስ፤
የተከበራችሁ የአዲስ አበባ ዩኒቪርሲቲ የቦርድ አባላት፣ የሴኔት አባላት፣ መምህራን፣ እንዲሁም የአስተዳደር ሠራተኞች፤**

*ሁሉም የኢትዮጵያ ዜጐች እንደ እናንተ ፈንድቀው ተደስተው የምናይበት ዘመን ይመጣል!*

**ከሁሉ በላይ ለዚህ ድንቅ ቀን ዋነኛ ባለቤት የሆናችሁ ወላጆች፤ እንዲሁም በጥረታችሁ ጣፋጭ ህልምና ታላቅ ግብ ዛሬ እውን ያደረጋችሁ ውድ ተመራቂዎች**





**እንኳን ደስ አላችሁ!**

በኑሮ ቀንበር ሳትጐብጡ፣ በውጣ ውረድ ሳትደናቀፉ፣ የመጨረስን ጣፋጭ ጣዕም ቀምሳችሁና አጣጥማችሁ ለትውልድ መጨረስ እንደሚቻል በተግባር ያስተማራችሁ የዕለቱ ሙሽሮች በድጋሚ እንኳን ደስ አላችሁ!

ደስታችሁ እንዲውል፣ ደስታችሁ እንዲያድር፣ ደስታችሁ እንዲከርም፣ ደስታችሁ ለዜጐቻችን ሁሉ እንዲጋባ ያለኝን ታላቅ ምኞት ልገልጽላችሁ እፈልጋለሁ። ትልቁ የዕውቀት መሸመቻ ምኩራብ ዩኒቨርሲቲ ቢሆንም፤ የሰው ልጅ ሁሌም እንደ አዲስ በየዕለቱ ከበላይና ከበታቹ፤ ከተፈጥሮ እንደ ተማረ የትምህርትን መጨረሻ ሳያይ ይዘልቃል። ነገር ግን፤ በዩኒቨርሲቲ ያውም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ መመረቅ ያለውን ክብር ከጥቂት ዓመታት በፊት ቀምሼ ስለማውቀው ከእናንተ ፊት ሆኜ በዚህ የምርቃት ሥነ ሥርዓት ንግግር ላደርግ በመቻሌ እና የደስታችሁ ተጋሪ በመሆኔ የተሰማኝን ልዩ ክብር ልገልጽላችሁ እፈልጋለሁ።

እጩ ተመራቂዎች፤ በተለይም ወጣቶች ከፊታችሁ አዳዲስ ዩኒቨርሲቲዎች ይጠብቋችኋል። የትዳር ዩኒቨርሲቲ ይጠብቃችኋል። ይህ የትዳር ዩኒቨርሲቲ ከዋን ኦ ዋን የሚጀምር አይደለም። የፈተና ሥርዓቱም እዚህ እንደ ለመዳችሁት አይደለም። ነገር ግን እሱም መውደቅም መመረቅም አለው። ከትዳር ዩኒቨርሲቲ በተጨማሪ የሥራ ዩኒቨርሲቲ በሥራ ዓለም ውስጥ ከታላላቆች፣ ከሴቶች፣ ከወንዶች፣ ልምድ ከአላቸውና ከሌላቸው ሰዎች ጋር ሠርቶ ውሎ ለመግባት አዲስ ልምምድ የሚጠይቅ፤ እሱም እንዲሁ ሌላ መመረቅና መውደቅ በውስጡ ያለ ዩኒቨርሲቲ ከፊታችሁ አለ።

እንዲሁም የሕይወትን ፈተና ተጋፍጣችሁ በጥሞና በማስተዋል ከአካባቢያችሁ የምትማሩበት፤ የፈተና ሂደቱ በውጤት የሚለካበት ሌላ ዩኒቨርሲቲ ከፊታችሁ አለ። እስከ ዛሬ በሚሰጣችሁ ኮርስ የላቀ ውጤት ለማምጣት የማንበብ ልማዳችሁ ተቀይሮ ከምትማሩት ትምህርት ውጪ አዳዲስ ጽሑፎች፣ አዳዲስ ሐሳቦች ለማንበብ ለማወቅ የምትለማመዱበት ሌላ ዩኒቨርሲቲ ከፊታችሁ አለ። ሌሎች ያልጠቀስኳቸው በርካታ የሕይወት ልምድና ትምህርት የሚወሰዱባቸው ዩኒቨርሲቲዎች ከፊታችን ያሉ ቢሆንም፣ የመመረቂያ ሥነ ሥርዓቱ ግን ዛሬ ከምናየው የተለየ ነው። የምትለብሱት ጋዎን፣ አቀማመጣችሁ፣ የዲፓርትመንቶች ፉክክር እንዲሁም የላቀ ጥረትና ውጤት ያመጡ ሰዎች የመጨረሻውን የደስታ ፅዋ የሚቀምሱበት ይህ የምርቃት ሥነ ሥርዓት ከሁሉም የተለየ የሚያደርገው በዩኒቨርሲቲ በመሆኑና በአንድ ጊዜ ዘጠኝ ሺሕ ሰዎች የሚመረቁበት መሆኑም ጭምር ነው።

ይህን ምርቃት የተለየ የሚያደርገው በዩኒቨርሲቲ መማራችሁ ሲሆን፤ 'ዩኒቨርሲቲ ማለት ምን ማለት ነው?' የሚለውን ማንሣት ጠቃሚ ይሆናል። ዩኒቨርሲቲ ማለት በላቲን ቋንቋ የተሟላ ማለት ነው። አንድ ሰው ወደ ሙላት የሚያድግበት ተቋም ማለት ነው። ወደ ሙላት ለማደግ ማወዳደር የግድ ነው። ወደ ሙላት ለማደግ ማነፃፀር ይጠይቃል። ወደ ሙላት ለማደግ ማስተያየት፣ ማገናዘብ አመዛዝኖም የጐደለ ለይቶ አክሎ መሙላት ይጠይቃል። በዩኒቨርሲቲ ውስጥ የአንድ የምትወዱትን ሰው ትምህርት ብቻ ተምሮ መመረቅ አይቻልም። የአንድ ሰው መጽሐፍ አንብቦ ፕሮጀክት መጻፍ አይቻልም። ከተለያየ አቅጣጫ የተለያየ እይታ ማየትና ማገላበጥ፣ መሞገት፣ ማመዛዘንና የላቀውንና የተሻለውን አስበልጦ መውሰድ ይጠይቃል። ለዚህ ነው ወደ ሙላት የሚታደግበት የተሟላ ተቋም ያሉት፤ የያኔው ዐዋቂ የላቲን ምሁራን።





እንዲሁም ግራጁዌሽን ማለት በመካከለኛው የአውሮፓ ዘመን ቋንቋ የተለመደ መሆኑና ስርወ ቃሉ ከላቲን እንደ መጣ እየተዘነጋ ያለ ቢሆንም፤ ግራጅዌት ማድረግ ወይም ግራጅዌሽን ማለት 'እላይ መውጣት' ማለት ነው። መላቅ ማለት ነው። መሻል ማሻሻል ማለት ነው። ከነበረው ከእናንተ ጋር ዩኒቨርሲቲ ከገባው ሰው ሁሉ ልቃችሁ፣ ተሽላችሁ መመረቃችሁን በኩራት ልመሰክርላችሁ እፈልጋለሁ። ነገር ግን ግራጅዌሽን (የአማርኛው ትርጉም) ከላቲኑ ወይም በመካከለኛው ዘመን አውሮፓውያን ከሚጠቀሙበት ግራጅዌሽን በእጅጉ የላቀ ነው። ለጭንቅላት ብቻ ሳይሆን ለመንፈስም፣ ለውስጥ ማንነትም ትምህርት አለው። መመረቅ ማለት መባረክ ማለት ነው። መመረቅ ማለት ባዩህ፣ ባዩሽ፣ በቀመሱህ፣ በለኩህ ሰዎች ታምኖብህ፤ ይበል ይሁን ተሽለሃልና ይጽደቅልህ ማለት ነው።

ይህንን ምርቃት ለማዝለቅ ገፊ ኃይል ሆኖ እንድንማር ያደረገንን ነገር በተወሰነ ደረጃ ማንሣት እፈልጋለሁ። አንድ ሰው ለማወቅ፣ ለመላቅ ወደ ሙላት ተቋም ገብቶ አዳዲስ ዕውቀት ሲገበይ፤ ቀዳማይ መግፍኤ ምክንያቱ ምንድን ነው? ዋናው ለመማር ገፊ የሆነው ኃይል ምንድን ነው? የሚለውን ማወቅ በእጅጉ ያስፈልጋል። ሰዎች ለመማር፣ ለማወቅ፣ ለመላቅ የሚያደርጉትን ጥረት የተለያየ ምሁራን በተለያየ መንገድ ገልጠውታል። ሁሉም ምሁራን ለመማር የሚደረገውን ገፊ ኃይል ተመሳሳይ የሆነ ትርጓሜና ብያኔ አልሰጡትም። ለምሳሌ፤ ፍሬድሪክ ኒቼን ብንወስድ፤ ሰው ለመማር፣ ለመጣር፣ ለመላቅ የሚያደርገው ገፊ ኃይል ዊል ቱ ፓወር (will to power) ነው ይለዋል። ለመግዛት መሻት ነው ይለዋል። ሌላውን ለመግዛት፤ ሌላውን ለማሸነፍ፤ ከሌላው ለመላቅ ነው ሰው አልትሜትሊ መማር የሚፈልገው ብሎ ያስባል።

ፍራንሲስ ፉኪያማ ይህንን ከግለሰብ ወደ ቡድን ሲወስደው ሜጋ ኦቶሚያ ይለዋል። 'ሜጋ ኦቶሚያ' የሚለውን ሐረግ ሲያብራራው፤ በበላይነት፣ በገዢነት የመኖር መሻት ነው ለመማር ገፊ ኃይል የሆነው ይላል። ነገር

ግን፤ የሰው ልጅ ዘለዓለማዊ አይደለም። ለዘለዓለም አይኖርም። ለዘለዓለም መግዛትም አይችልም። በመሆኑም የሁሉም ሰው ፍላጐት መግዛት ነው የሚል ትርጓሜ ትክክል አይደለም ብለው የሚሞግቱ ሌሎች ምሁራን አሉ። ከእነዚህ መካከል የሚጠቀሰው ምሁር ጀርሚ ቤንተሃም ነው።

ጀርሚ ሰው ለመማር ገፊው ኃይል (push factor) የሐሴት ጥማት ነው ይላል። የመግዛት ፍላጐት ሳይሆን ዊል ቱ ፕሌዠር ነው (will to pleasure) ነው ይላል። የራስን ደስታ ለመሸመት ሰው መማር እንደሚፈልግ የሚገልጸው ጀርሚ፤ የሰው ልጅ ደስታውን ለማግኘት የማይከፍለው ዋጋ የለም ይላል። ለመደሰት ይሰርቃል። ለመደሰት ይገድላል። ለመደሰት ይቀማል። ደስታውን ለማግኘት ማንኛውንም ዋጋ ይከፍላል። ምሁራን ይህንን የወንጀል ሕግ መሠረቱ ምን እንደ ሆነ ጐን ለጐን ለማሳየት ሲሞክሩ ወንጀለኛው ወንጀል በመሥራት ከሚያገኘው ደስታ ይልቅ ቅጣቱን በማከበድ፤ የቅጣቱን ህመም፣ የቅጣቱን ስቃይ በማግዘፍ ወንጀሉን ለመቀነስ ፋይዳ እንዳለው ይገልጻሉ። ወንጀልን የምንቀንስበት የቅጣት ሕመሙ ጠንከር ያለ ካልሆነ ሰው ደስታውን ለመሸመት ሲል የማያደርገው ነገር እንደ ሌለ የጀርሚ ቤንታሚንን እሳቤ በመደገፍ ሐሳብ ይሰነዝራሉ። ሌሎች የሚቃወሙ ምሁራን ደግሞ አሉ፤ ወይም የተለየ ሐሳብ ያራምዳሉ። ከእነዚህ መካከል አንዱ ቻርልስ ዳርዊን ነው።

ዳርዊን ዊል ቱ ሰርቫይቭ (will to survive) ወይም ለመኖር መሻት ነው ይላል። ሰው ለመኖር ሲሻው እያባላ፤ አልያም እየበላ የራሱን ኗሪነት ብቻ ለማረጋገጥ ጥረት ያደርጋል ይላል። ለህልውና ሲባል መብላት፤ ለህልውና ሲባል ማባላት ግን እስከ መቼ? ሰው ዘላቂ ህላዌ እንደ ሌለው እያወቀ ለመብላት የሚያባላ፤ ለመብላት የሚበላ ከሆነ፤ ህልውናን በዘላቂነት እውን ማድረግ ስለማይቻል፤ ይህም ትክክል አይደለም ብሎ የሞገተው ቪክቶር የሚባለው ምሁር፤ ሰውን ለመማር የሚገፋው ዋናው ኃይል ዘ ዊል ቱ ሚኒንግ ነው ይለዋል። ትርጉም ላለው ነገር ለመኖር ባለ ፍላጎት ነው ሰው የሚማረው ብሎ ይተረጉመዋል። ይህ ትርጉም ያለው የመኖር ዘዬ ማለት መስጠት ነው። ማፍቀር ነው። መውደድ ነው። ማገልገል ነው።

ሰዎች በመስጠት የሚያገኙትን ደስታ በመግዛት ሊያገኙት አይችሉም። የመጨረሻው የደስታ ምንጭ ከራስ አልፎ ለወገን ማድረግ መቻል በመሆኑ የቪክቶር እሳቤ ለእኛ ጠቃሚ ይሆናል። መልካምነትን፣ ደግነትን፣ ፍቅርን በምን መለካት ይቻላል? አንድ ሰው አንድ ኪሎ ስኳር መግዛት ቢፈልግ ሌላ አንድ ኪሎ ክብደት ያለው መዳብ፣ ብረት፣ ነሐስ ወይም ድንጋይ በአንድ ጐን አስቀምጦ በሌላ ወገን ስኳሩን እያስቀመጠ አንድ ኪሎ መሆኑን መለካት ይችላል። አንድ ኪሎ ስኳር ለመለካት አንድ ኪሎ የሚመዝን ክብደት ያለው ሌላ ነገር ከሌላው አቅጣጫ ያስፈልጋል። ወይም አንድ ሊትር ውሃ ወይም ዘይት ለመለካት የፈለገ ሰው ያን መለካት የሚያስችል እቃ መያዝ ይኖርበታል። መልካምነትን፣ ፍቅርን፣ ደግነትን፣ መስጠትን በምን መለኪያ ልንለካው እንችላለን? መልካምነትንና ደግነትን የምትሰጡ ሰዎች በዚያኛው ወገን የሰጣችሁት ካልተለካ ችግሩ እናንተ ዘንድ አይደለም። በሰውዬው ዘንድ መለኪያው የለም ማለት ነው። መሰላቸት፣ ተስፋ መቁረጥ፣ ማኩረፍ ሳይሆን የመልካምነት ሚዛን፤ የመልካምነትን መመዘኛ መጐናጸፍ እንዲችል አበክራችሁ መሥራት ይኖርባችኋል። መልካምነት ያላችሁ ሰዎች መልካምነት በሚዛን የማይለካ ስለሆነ ሁሌ በመስጠት፤ ሁሌ በማፍቀር፤ ሁሌ በመተግበር ብቻ እውን እንዲሆን ብዙ ጊዜ መልፋት ይኖርባችኋል። ካልለፋችሁ በኋላ የሚነገር መሆኑን አውቃችሁ ዛሬም ነገም በተለይ ለዚህች ድንቅ አገር መልካም መሆንን እንደ ክብር መውሰድ ይኖርባችኋል።

ውድ ተመራቂዎች ትላልቅ ዛፍ መቁረጥ የሚችል መጥረቢያ ምንም ያህል የተሞረደ የተሳለ ቢሆን፣ ምንም ያህል ባማረ መንገድ የተሠራ ቢሆን ከተናቀ አንድ ዱላ ከዛቢያው ጋር መዋደድ ካልቻለ መጥረቢያውን ብቻ ይዞ ግንድ

መቁረጥ አይቻልም። መጥረቢያው ብቻውን ዛፍ እንዲሰብር ቁመቱ አጭር ውፍረቱም መካከለኛ የሆነ ዛቢያ ያስፈልገዋል። ዛቢያን ሳይንቅ ከዛቢያ የተዋደደ መጥረቢያ ትላልቅ ዛፍ መቁረጥ ይችላል። እናንተ የተማራችሁ፣ ያወቃችሁ ራሳችሁን አሸንፋችሁ የተሰጣችሁን ፈተና አልፋችሁ የተመረቃችሁ ድንቅ ምሩቃን፤ ካልተማረው ሕዝብ ጋር ካልተዋደዳችሁ በስተቀር ፍላጐታችሁን ማሳካት አትችሉም። የእናንተ መጠረብ፣ የእናንተ መዘጋጀት ብቻውን ምንም የሚመስለውን ዛቢያ መርጦ መዋደድ ይሻልና በየሄዳችሁበት ባይማርም ከአስተማራችሁ፤ ባይኖረውም ቆርሶ ከሰጣችሁ ማኅበረሰብ ጋር ተዋድዳችሁ ኢትዮጵያን ማላቅ፤ ማስቀጠል የሁላችሁ የነገ ተልእኮ እንደሆነ በዚሁ አጋጣሚ ላሳስባችሁ እፈልጋለሁ።

በቅርቡ በዚህ ክረምት በኢትዮጵያ አራት ቢሊዮን ችግኝ ለመትከል ሥራ ጀምረን ነበር። አራት ቢሊዮን ዛፍ ለመትከል ስንወስን የተሳለው መጥረቢያ ዛቢያው ከሌለ ብቻውን እንደማያሳካው ስለሚያውቅ ይህንን ቅዱስ ሐሳብ ለመላው ሕዝብ በቀረበው ጥያቄ መሠረት እስከ ዛሬ ድረስ ከሁለት ነጥብ አምስት ቢሊዮን በላይ ዛፍ ተክለናል። ኃያል ከሚባሉ የአውሮፓ አገራት መካከል አንዱ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ደውሎልኝ፤ “በእኔ አገር በሙሉ አራት ቢሊዮን ዛፍ የለም። አንተ በአንድ ክረምት አራት ቢሊዮን ዛፍ እተክላለሁ ብለህ ማሰብህ ትልቅ ነገር እንደምታስብ ያሳያልና ምን ላግዝ?” ሲለኝ ‘ፕሮግራሙን ለማስፈፀም አንዳንድ ነገር ያስፈልጋል’ ብዬው መቶ ሠላሳ ሚሊዮን ዩሮ ርዳታ ሰጠን። ትልቅ ሐሳብ ትልቅ ሆኖ ትልልቆቹን የሚያሳምነው ሲተገበር ነው። አራት ቢሊዮን ብለናል፤ አራት ቢሊዮን የምናደርግ ሕዝቦች መሆናችንን፣ ትላልቅ ማሰብ፣ ትላልቅ መከወን የምንችል መሆናችንን ለዓለም ስናሳይ፤ ድህነትንም እንደዚሁ አሸንፈን፤ ስንኖር ኢትዮጵያዊ ስንሞት ኢትዮጵያ መሆናችንን ዳግም እናረጋግጣለን።





ውድ ተመራቂዎች ስንኖር ኢትዮጵያዊ ከሆንን ኢትዮጵያችን አረንጓዴ መሆን አለባት። ስንሞት ኢትዮጵያ ከሆንን ቢያንስ መቃብራችን በጥላ ስር፣ በዛፍ ስር መሆን አለበት። ስንኖር ኢትዮጵያዊ ስንሞት ኢትዮጵያ ከሆንን ቢያንስ ልጆቻችን ድህነትን ዳግም የማያስተናግዱ፤ የዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ወጥቶ “በጀት አንሶኛል” የሚልበት ዘመን ማብቃት ይኖርበታል። ይህ እንዲሆን የተሳላችሁ፣ የተጠረባችሁ፣ የተዘጋጃችሁ ምሁራን ዛቢያውን ሳትዘነጉ ከዛቢያው ጋር ተዋድዳችሁ፤ ካልተማረው፣ ካልተዘጋጀው፣ ብዙዎች ከሚንቁት ግን ታሪክ ከሚሠራው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር እጅና እጅ ሆነን ኢትዮጵያን ማስቀጠል ከማንም በላይ ከእናንተ የሚጠበቅ ይሆናል።

አዲስ አበባ ላይ በዚህ ክረምት አራት መቶ አርባ ስምንት ትምህርት ቤቶች ለማደስ ሥራ ተጀምሯል። ይህንን ሥራ በመንግሥት በጀት ቢሆን ኖሮ አምስት ዓመት፣ ዓሥር ዓመት ይፈጅብን ነበር። ምክንያቱም የጨረታ ሕግ ስለአለ፤ ምክንያቱም የበጀት ሥርዓቱ ውስንነት ስለአለበት። ነገር ግን ብዙ ባለሀብቶች እና የበጐ ፈቃድ አገልጋይ ወጣቶች ተባብረው አራት መቶ አርባ ስምንት ትምህርት ቤት በክረምቱ አድሰን፤ ብላክ ቦርድ ቀይረን፤ ወንበር ጠግነን፤ አጥር ጠግነን፤ ዛፍ ተክለን በንፅፅር ሻል ያለ ትምህርት ቤት ለልጆቻችን ለማዘጋጀት የምናደርገው ጥረት ከተባበርን ሌሎች ትላልቅ ጉዳዮችን ማሳካት እንደምንችል ምስክር መሆን ይችላል።

በዚሁ መንገድ በዚህ ክረምት በመንግሥት ትምህርት ቤቶች ለሚማሩ ስድስት መቶ ሺሕ አዳጊዎች ሰባት ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ደብተር እያዘጋጀንላቸው ሲሆን፤ ተማሪዎች መስከረም ላይ ወደ ትምህርት ቤት ሲሄዱ ለእያንዳንዳቸው ደብተር ሰጥተን፤ ለስድስት መቶ ሺሕ ተማሪ ዩኒፎርም አሰፍተን፤ ትምህርት ቤት አድሰን፤ አምና ጥለው የሄዱትን አስውብን ብናስገባቸው ከስድስት መቶ ሺው ስልሣ ሺው ቢሳካልን፤ ከስልሳ ሺው ስድስት ሺሕ ቢሳካልን፤ ከስድስት

ሺው ስድስት መቶ ቢሳካልን፤ ከዚያም ስልሣ ቢሳካልን ቢያንስ ቢያንስ ስድስት ቢሳካልን፤ ስድስቱ ለኢትዮጵያ ብርሃን ሊሆኑ ይችላሉ።

የዛሬው እያንዳንዱ ኢንቨስትመንት የጊዜ ጉዳይ እንጂ፣ ራሱን አባዝቶ ሃብት እና ጉልበት ላፈሰሱ ሰዎች መልስ መሆኑ ስለማይቀር የምንሠራው እያንዳንዱ ሥራ ሲሰናሰል ኢትዮጵያን ውብ፤ ኢትዮጵያን ከለማኝነት የሚያወጣ መሆኑን መገንዘብና መትጋት ከሁላችን ይጠበቃል። ከዚህ በተጨማሪ ቀደም ሲል ፕሮፌሰር ጣሰው የገለጹትን ሆስፒታል ጨምሮ በከተማ ውስጥ የሚገኙ ከዓሥር በላይ የመንግሥት ሆስፒታሎች በእድሳት ላይ ይገኛሉ። ብዙ ማኅበረሰብ ለሕክምና ሄዶ የሚቸገርባቸውን የሕክምና ጣቢያዎች በማደስ ለአገልግሎት ዝግጁ ማድረግ በመንግሥት ቢሆን አሁንም አድካሚና በአጭር ጊዜ የማይከወን ነው። በሌላ በኩል ከአንድ ሺሕ በላይ ዐቅመ ደካማ እናቶችና አባቶች የሚኖሩበትን ቤት አድሰን ክረምቱን “ዝናብ ይዘንብብኛል” ብለው ሳይሳቀቁ፤ ዝናብ ሳይሆን የልጆቻቸው ጉልበትና ሀብት ደስታ የሚሰጥ መሆኑን አምነው ለእናንተም ተጨማሪ ምርቃት የሚመርቁ እናቶችን ለማስደሰት በተጀመረው ሥራ ከአራት መቶ ሀምሳ ቤት በላይ እድሳት ተጀምሯል። አንድ ሺው በክረምት ይጠናቀቃል።

ውድ ተመራቂዎች፤ አሁን ኢትዮጵያ ውስጥ ብዙ ችግር ይነገራል። ነጋ ጠባ መርዶ አለ። የሚያስፈራ ነገር አለ። ዛሬ ስትመረቁ ዘጠኝ ሺሕ ስድስት መቶ ሰባ ሰባት ተማሪዎች ከኔ ጋር ከወሰናችሁ እና በልባችሁ አምናችሁ ከአረጋገጣችሁ፣ በእርግጠኝነት የምገልጽላችሁ ኢትዮጵያ አንድ ሆና ወደ ብርሃን የምትሻገርበት እንጂ ነገርዋ ወደኋላ የሚመለስበት ሁኔታ አይኖርም። ይህ ውሳኔ ከእያንዳንዳችን የሚጠበቅ ይሆናል። ኢትዮጵያን ማፍረስ፣ ኢትዮጵያን ማሳዘን፣ ኢትዮጵያን መዝረፍ ለኢትዮጵያውያን አዲስ አይደለም። ኢትዮጵያንም ቆፍራችሁ ብትጠይቋት ትነግራችኋለች። በዘመናት መካከል ብዙዎች ሞክረዋል። ሰዎችን ገድለዋል። ኢትዮጵያን ማፍረስ ግን አይቻልም።





ኢትዮጵያውያን ለኢትዮጵያውያን ውድና መከታ እንድንሆን ዛሬ በዚህ ታላቅ ዩኒቨርሲቲ የተመረቃችሁ ተማሪዎች ቀላሉን ሳይሆን ትክክለኛውን መንገድ መምረጥ ስትችሉ፣ ትርጉም ለሚሰጡ ነገሮች መኖር ስትችሉ፣ ስትመራመሩ፣ ስትጠይቁ፣ የመኖር ትርጉም ሲገባችሁ የምላችሁን ኢትዮጵያ መፍጠር እንችላለን።

በዚህ ዓመት የኢትዮጵያ ጂ.ዲ.ፒ ከኬንያ ይበልጣል። የኢትዮጵያ ጂ.ዲ.ፒ በዓሥር ቢሊዮን ገደማ ከኬንያ ጂ.ዲ.ፒ ይበልጣል። ነገር ግን የኬንያ የዓመት በጀት ከኢትዮጵያ መንግሥት በጀት በእጥፍ ይበልጣል። እኛ ዓሥራ ሦስት ቢሊዮን ዶላር ገደማ በጀት ስንይዝ ኬንያውያን ሃያ ሰባት ቢሊዮን ገደማ በጀት ይዘዋል። ከጂዲፒያቸው አንድ ሦስተኛውን ወይም የሚበልጠውን የመንግሥት ወጪ አድርገው ይዘውታል። ሁላችሁም እንደምትገነዘቡት ኢትዮጵያውያን በዓለም ላይ በሚሊዮን የሚቆጠር ዲያስፖራ ጉልበቱን ጊዜውን፣ አልፎ አልፎ ምላሱን የሚጠቀም ዲያስፖራ በብዛት አላት። በተንደላቀቀ ሁኔታ የሚኖሩ ዲያስፖራዎች ብዙ ላይሆኑ ይችላሉ። ብዙዎቹ ለፍተው፣ ጥረው ግረው ራሳቸውንና ቤተሰቦቻቸውን የሚያግዙ መሆናቸው ይታወቃል። ይሁን እንጂ በዓመት እያንዳንዱ ዲያስፖራ አምስት ሺሕ፣ በስድስት ወር ሁለት ሺ አምስት መቶ፣ በሦስት ወር ሰባት መቶ ብር ሂሳቡን ለእናንተ ትቼ ማዋጣትና የጋራ ኩባንያ መፍጠር ቢችል፤ አንድ ሰው አምስት ሺሕ ዶላር ከአወጣ አንድ ሚሊዮኑ አምስት ቢሊዮን፤ ሁለት ሚሊዮኑ ዓሥር ቢሊዮን ዶላር በዓመት ማውጣት ይችላሉ ማለት ነው። ስጦታ አይደለም ኢንቨስትመንት ነው። ዲያስፖራው በየዓመቱ ዓሥር ቢልዮን ዶላር ወደ እኛ ጂ.ዲ.ፒ ቢያዋጣ በየዓመቱ ምን ያህል ዕድገት እንደምናመጣና ባጠረ ጊዜ በአፍሪካ ትላልቅ ኢኮኖሚ ካላቸው አገራት ተርታ እንደምንመደብ ሒሳቡን ኢኮኖሚስቶች ከእኛ የተሻለ ማስላት ይችላሉ።

ለኢትዮጵያ ሳንሰጥ፤ ዕውቀታችንን፣ ጉልበታችንን፣ ጊዜአችንን ሳንሰጥ የምንመኛትን ኢትዮጵያ መፍጠር አንችልም። የምንፈልጋትን ኢትዮጵያ ለመፍጠር የወሰነ በየትኛውም ሥፍራ ያለ ዜጋ ካለ ገንዘቡን ዱባይ ከሚያስቀምጥ፤ ገንዘቡን ለንደን ከሚያስቀምጥ፤ ገንዘቡን ቻይና ከሚያስቀምጥ፤ እነርሱ የእኛን ተቀማጭ ገንዘብ ኢንቨስት ከሚያደርጉ ኢትዮጵያውያን በተባበረ መንገድ በሕጋዊና ሥርዓት ባለው መንገድ ኢንቨስት ብናደርግ ባጠረ ጊዜ ኢኮኖሚያችንን ማሻሻልና ተመርቀው ሥራ የሚያጡ ልጆቻችንን ሥራ ለማስያዝ ሰፊ ዕድል ይሰጠናል።

ነገር ግን፣ የዛሬ ሰባ አምስት ዓመት ገደማ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በንጉሠ ነገሥቱ ቤት ሥራ ሲጀምር የኢትዮጵያ አርሶ አደሮች በሁለት በሬና በሞፈር ያርሱ ነበር። ዛሬ ከሰባ አምስት ዓመት በኋላ አባትና እናቱን ከሞፈርና ቀንበር መገላገል ያልቻለ ትውልድ ቢማር ባይማር ምን ትርጉም አለው? ሌላ ሰባ አምስት ዓመት እንዳንቆይ ንስር ሆኖ የተፈጠረ አሞራ ጅግራ ሆኖ መሞት ስለሌለበት፤ የተማረ ኢትዮጵያዊ እንዲሁ በከንቱ መጥቶ በከንቱ ዲግሪ ቆጥሮ መመለስ ስለሌለበት፤ በተባበረ ክንድ አርሶ አደሩ ከመድከም፣ ከቀምበር፣ ከበሬ ተላቅቆ በዘመነ መንገድ አርሶ በልቶ የሚያበላን እንዲሆንና ለማኝነት ከኢትዮጵያ እንዲወገድ በተባበረ ክንድና በዩኒቨርሳል ቫልዩ በጋራ እንድንሠራ በታላቅ ትሕትና ጥሪዬን ላቀርብላችሁ እፈልጋለሁ።

ከእናንተ የሚፈለገው ነገር ወጥቶ ሠርቶ ገቢ ማግኘት ብቻ ሳይሆን በዩኒቨርሲቲ ቆይታችሁ የተማራችሁትን ዩኒቨርሳል ቫልዩስ የማኅበረሰቡ ቫልዩ ማድረግ ነው። ዩኒቨርሳል እሴት በዩኒቨርሲቲ ውስጥ በስፋት መኖር ያለበት እንደ ሆነ ይታመናል። ስምንት ሜይን ዩኒቨርሳል ቫልዩ እሴቶች አሉ፣ አንደኛው ክብር ነው። የሁሉንም አበርክቶ፣ የሁሉንም ዕውቀት፣ የሁሉንም ችሎታ ማክበርና በፀጋ መቀበል አንድ ዩኒቨርሳል ቫልዩ ተብሎ በዩኒቨርሲቲ የሚታወቅ ነገር ነው። ሁሉንም ማክበር ማለት ከመሳደብ መቆጠብ ማለት ነው። ሁሉንም ማክበር





ማለት ሌላው ወገን ዘንድ ቫሊዩ እንዳለ ማመን ማለት ነው። ይሄን ማስተማር ከእናንተ ይጠበቃል። ሁለተኛው ልህቀት ነው። በምንሠራው ሥራ በጥናትና በምርምር በመድከም የተሻለ ነገር ማምጣት መቻል ነው። ይህንን ከእናንተ አሳልፋችሁ ማኅበረሰቡን ማስተማር ይጠበቅባችኋል። ሦስተኛው እሴት ትሕትና ነው። ትሑት ሰብዕናን መላበስ ነው። ሰው ትሑት ሆኖ ደካሞችን ማክበርና ማገልገል ቢችል፣ ማዘንና ማፍቀር ቢችል ትርፍ እንጂ ኪሳራ የለውም። ሚዛኑ ተመልሶ ራሱ በጐነት ስለ ሆነ በጐነትን በኪሎ፣ በጐነትን በሜትር፣ በጎነትን በሊትር ሳንለካ ሁሌም በመስጠትና ትሑት በመሆን ማኅበረሰባችንን መቅረጽና ማስተማር ከእናንተ ይጠበቃል። አራተኛው ዩኒቨርሳል ቫልዩ አገልግሎት ነው። ዛሬ ከዘጠኝ ሺሕ ምሩቃን ተማሪዎችና ቤተሰቦቻቸው ቢያንስ መቶ ሺሕ ችግኝ እንጠብቃለን። ቤት ስትገቡ በእናንተ ግቢ ውስጥ፣ በእናንተ ሰፈር ወይም በእናንተ ትምህርት ቤት ውስጥ አምስት አምስት፤ ዓሥር ዓሥር ችግኝ ብትተክሉ ትልቅ የማገልገል ልምምድ ስለ ሆነ ዛሬ መጀመራችሁ ለነገ ፈር ቀዳጅ ስለሚሆን እንደ አንድ ማስተማሪያ መንገድ አገርና ሕዝብ ለማገልገል፤ ራሳችሁን ለትውልድ ለመስጠት እንደ ማሳያ ተጠቀሙበት። አምስተኛው እንግዳ መቀበል ነው። በርካታ ቱሪስቶች፣ ኢንቨስተሮች እየጋበዝን ነው። ኢንቨስተርና ቱሪስት መቀበሉ ቆይቶ ኦሮሞዎች ሳይቸገሩ በባሕር ዳር፤ አማራዎች ሳይቸገሩ በመቀሌ፤ ትግራዮች ሳይቸገሩ በቦረና በጉጂ፤ ሲዳማዎች ሳይቸገሩ በሶዶ፤ ጉራጌዎች ሳይቸገሩ በወራቤ የሚንቀሳቀሱባትን ኢትዮጵያ እንፍጠር። ኢትዮጵያ ለመቶ ሚሊዮን ኢትዮጵያውያን በቂ ናት። ኢትዮጵያ መቶ ሚሊዮን ኢትዮጵያዊ ከተባበረና ከተደመረ አንቀባራ ማኖር ትችላለች። ስግብግብነትና ንፉግነት ኖሮ “አንተ የኔ አይደለህም” የሚል ሐሳብ ግን ኢትዮጵያን ትንሽ ስለሚያደርግና ኢትዮጵያ ካነሰች የዛሬ ኢትዮጵያውያንና የነገ ኢትዮጵያ ስለምታንስ፣ ለራሳችሁ ክብር ብላችሁ የኢትዮጵያን ክብር ለመጠበቅ ሁላችሁም መትጋት ይኖርባችኃል። ስድስተኛው ጽናት ነው። በዚህ መከራ፣ በዚህ ችግር፣ በዚህ ክፉ ጊዜ ጽናት ያስፈልጋል። እናንተ ምሩቃን ተማሪዎች ዕድለኞች ናችሁ። ከብዙ ሚሊዮን

መመረቅ ችላችኋል። ሳይማሩ፣ ሳይመረቁ ያለፉ ብዙ አሉ። ለኢትዮጵያ በጽናት መታገልና የነገን ኢትዮጵያ ብርሃን ለማምጣት መሥዋዕት መሆንም ቢሆን ክብር መሆኑን አውቃችሁ በጽናት ለኢትዮጵያ ልማትና ለኢትዮጵያ ብልፅግና እንድትሠሩ በከፍተኛ ትሕትና እጠይቃችኋለሁ። ሰባተኛው ጎብር ነው። በዚህ ዩኒቨርሲቲ ዛሬ ሁለት ሺሕ ሴቶች ባይመረቁ፤ አካል ጉዳተኞች ባይመረቁ፤ ወንዶች ዕድሜአቸው ከሃያ አምስት እስከ ሠላሳ ብቻ ቢሆን ምን ያክል ጐዶሎ እንደሚሆን አስቡት። የሴቶች፣ የአካል ጉዳተኞች፣ የሰማንያውም ብሔር ብሔረሰቦች ተቀላቅሎ መመረቅ ከዚያም አልፎ ከጐረቤት አገራት አገራችንንና እናንተን አምነውና ወድደው ከእናንተ ጋር ተምረው የተመረቁት ሰዎች መኖራቸውን ማየት እጅግ በጣም የሚያኮራና አስደሳች መሆኑን አውቃችሁ፣ ለኀብረትና ለመሰባሰብ ልባችሁን ክፍት አድርጉ።

ዶ/ር ኃይሌ ፊዳ በፈረንሳይ በነበረው ቆይታ ከፕሬዚዳንት አልፋ ኮንዴ ጋር የአንድ ክፍል ተማሪዎች ነበሩ። በጋራ ይማሩ ነበር። ፕሬዚደንት አልፋ ኮንዴ ኢትዮጵያ ሲመጣ የመጀመሪያ ጥያቄው ዶክተሩን፣ እነ ንግሥትንና የባሏን ቤተሰቦች የት እንዳሉ ለማወቅ ጠየቀ፤ እነዚያን ዕንቁ ሰዎች አፍሪካ አጣች ብሎ አሰበ። ዛሬ ከእናንተ ጋር የተማሩ ነገ ቻይና፣ አሜሪካ፣ አውሮፓ ስትሄዱ የሚማሩ ሰዎች መድረሻቸው አይታወቅም። የእናንተም እንዲሁ። ከእናንተ ውስጥ ሳይንቲስቶች አሉ። ከእናንተ ውስጥ የሀገር መሪዎች አሉ። ከእናንተ ውስጥ ችግር የሚፈቱ ትላልቅ ጭንቅላቶች አሉ። ሌላውን ሰው ስታገኙት እናንተ ሳይንቲስት ከሆናችሁ እሱ የሀገር መሪ መሆኑን አስባችሁ አክብራችሁ ተቀበሉት። የመጨረሻውና ስምንተኛው ትምህርት ለሕይወት ነው። ትምህትር መነሻ እንጂ መድረሻ የለውም። ትምህርት አያበቃም ሁሌ ተማሪ መሆን፤ ሁሌ ለመማር መዘጋጀት ከተፈጥሮ መማር እንዳለንብን ማሰብ ከሁላችን ይጠበቃል። ዛሬ ከየቤታችሁ ስትመጡ ያሸከረከራችሁበት መንገድ የሆነ አርሶ አደር መሬቱን ለቅቆ፤ የሆነ አርክቴክት ዲዛይን አድርጎት፤ የሆነ ሲቪል ኢንጅነር አስፋልቱን ገንብቶት፤ የሆነ ኢኖቬተር መኪናውን ሠርቶ፤





መካኒካል አላልኩም ዲስቻርጅ እየሆነ ስለመጣ በብዙ ሰዎች መሠረትና ጥረት ላይ እየነዳችሁ እንደመጣችሁ አስባችሁ፤ እናንተም ለትውልድ አዲስ መሠረት ለመጣል መነሣትና መዘጋጀት ይኖርባችኋል። ብቻውን ያለቀ ነገር የለም። በአንደኛው መሠረት ላይ ሌላ መሠረት እየጣልን ትውልድ በቅብብሎሽ የሚቀጥልባት ሀገር እንድትሆን አዲስ መሠረት፤ አዲስ ማንነት ለመገንባት ከልብ እንድትነሡ፤ ያንን ማድረግ እንድትችሉ ምኞቴን ልገልጽላችሁ እፈልጋለሁ።

ውድ ተመራቂዎች፤ በአንድ መርከብ የተሳፈሩ ሰዎች በተለያየ ክፍል ቢቀመጡም ያች መርከብ በአንድ አቅጣጫ መቅዘፏንና መጓዟን ማረጋገጥ አለባቸው። ግማሹ ከላይ፣ ግማሹ ከታች፤ ግማሹ ከፊት፣ ግማሹ ከኋላ፤ ከተቀመጠ በተለያየ አቅጣጫ ቢቀዝፉ መርከቧ መድረስ የሚገባት ቦታ አትደርስም። እያንዳንዳችን የጋራ ታሪክ መፍጠር ካልቻልን ምሁራን ተመካክራችሁ ተወያይታችሁ የማያስፈልገንን ትታችሁ የሚጠቅመንን የጋራ ታሪክ መጻፍ ትችላላችሁ። ምሁራን ተመካክራችሁ የሚጠቅመንን የጋራ ራእይ ማስቀመጥ ትችላላችሁ። ኢትዮጵያውያን የኢትዮጵያ ዕጣ ፈንታ ብልፅግና መሆኑን አምነን በአንድ አቅጣጫ መቅዘፍ ካልቻልን፣ ያኮረፈ ሁሉ ወደ ቀበሌዬ ካለ ኢትዮጵያ ትንሽ ትሆናለች። ይህ እንዳይሆን መብራቱ ጨለማውን ገፍፎ መንገድ ማሳየት ሲገባው፣ ራሱ ብርሃኑ በጨለማ ተውጦ ብርሃን ማሳየት ከተሳነው ጉዞው ይደናቀፋል። የተማረው፣ ያወቀው፣ ለኢትዮጵያ መንገድ ማሳየት የሚገባው ተምሬአለሁ፤ አውቄአለሁ ብሎ መንገድ የሚያጠፋና የሚያደናብር እንዳይሆን ማስተዋል፣ መመካከር፣ መወያየት፣ መደማመጥ እና ለሁሉ ሕዝቦቻችን የሚበጀውን መንገድ መፍጠር ከእናንተ የሚጠበቅ ይሆናል።

በመጨረሻም፣ የዛሬ ምሩቃን ውለታ አለባችሁ። የመጀመሪያው ውለታ፤ ሳይማሩ፣ ጠግበው ሳይበሉ፣ መቀነታቸውን ፈትተው ያስተማሩ ወላጅ

ቤተሰቦች ናቸው። ወላጆቻችሁ ከእናንተ የሚፈልጉት የመጀመሪያው ነገር የእናንተን ስኬት ማየት ነው። ከስኬታችሁ በኋላ እንደ ኢትዮጵያ ባህል እነሱን መጦር፤ እንዳስተማሯችሁ የመጨረሻ ጊዜያቸውን በደስታ እንዲያሳልፉ ማድረግ ከእናንተ ይጠበቃል። ወላጆቹን የዘነጋ አገሩን ማስታወስ አይችልም።

ሁለተኛው ውለታችሁ የመምህራኖቻችሁ ነው። መምህራኖቻችሁ በትውልድ ስፍራችሁ በመጀመሪያ ደረጃ፣ በሁለተኛ ደረጃ ያስተማሯችሁ ሰዎች፣ እናንተ ዛሬ ያላችሁን ወይም የምታገኙትን ዲግሪ ከዚያ በላይ ያላገኙ ብዙ አሉ። እነሱ ቀልጠው እናንተን አሻግረዋችኋል። ዛሬ በዩኒቨርሲቲ የተማሩ ሰዎችም እናንተ ከምትደርሱበት ለመድረስ ብዙ ይቸገራሉ። የእነርሱ እያለቀ፣ የእናንተ እየጀመረ ስለ ሆነ፣ ባለፋችሁበት መንገድ ሁሉ ወደ ኋላ መለስ ብላችሁ ረግጣችሁ ያለፋችሁበትን ድልድይ ማስታወስና ማመስገን ያስፈልጋል። ለምሳሌ፤ ከረምት የገጠር ልጆች በእናንተ ትውልድ ስፍራ ያሉትን የመጀመሪያ ትምህርት ቤት ተማሪዎች አስተባብራችሁ ብታስተምሩ፣ ችግኝ ብትተክሉ፣ የጥገና ጉድለት ለመሙላት ብትሳተፉ ለመምህራኖቻችሁ ውለታ እንደ ዋላችሁ ይቆጠራል።

ሦስተኛው የቀደምቶቻችሁ ውለታ ነው። ቀደም ሲል እንዳነሣሁት፣ የእኛ ቀደምት አባቶች መሠረት እየጣሉ ያቆዩትን ሀገር ማስቀጠልና ለትውልድ ማስረከብ ከእናንተ ይጠበቃል። በማንኛውም ጉዳይ ተከራከሩ፤ በማንኛውም ጉዳይ ተወያዩ፤ በማንኛውም ጉዳይ ተመካከሩ፤ ነገር ግን ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያውያንን የሚመለከት ጉዳይ ላፍታም ቢሆን ለድርድር አታቅርቡ።

በመጨረሻም የሀገር ውለታ አለባችሁ። እናንተን ለማስተማር ኢትዮጵያ ከአስቀመጠችው በጀት ትልቁን ድርሻ ያኖረችው ለትምህርት ነው። ይሄን ሁሉ ሀብት የምታፈስሰው ተምረው ድህነትን፣ ችግርን፣ ረኃብን፣ እርዛትን





አለመደማመጥን፣ አለመሠልጠንን አስቀርተው ሥልጡን ኢትዮጵያን ይፈጥሩልኛል የሚል እምነት ስለ አላት ስለ ሆነ፤ እስከ አሁን ለአስተማረች፤ ኢንቨስት ላደረገች ሀገር በመሥራት ብድራቷን እንድትከፍሉ በዚሁ አጋጣሚ በትሕትና ልጠይቃችሁ እፈልጋለሁ። አገር በፈተና ወቅት፣ በመከራ ጊዜ፣ በችግር ጊዜ፣ ስቃይዋን የሚያበዛው ችግሯን የሚያገዝፈው የማያውቁ ሰዎች ጩኸት ሳይሆን፣ የሚያውቁ ሰዎች ዝምታ ነው። የምናውቅ ሰዎች ዝም ካልን፤ የምናውቅ ሰዎች አይተን እንዳላየን ከሆንን ዮፍታሔ ንጉሤ እንዳሉት፤

**“አገሬ ተባብራ ካልረገጠች እርካብ፤
ነገራችን ሁሉ የእንቧይ ካብ የእንቧይ ካብ”።**

## አመሰግናለሁ!

# የአዲስ አበባ የወንዝ ዳርቻ ልማት ፕሮጀክት ማስጀመሪያ ንግግር

መስከረም 20/2012 ዓ.ም.

እንዴት አደራችሁ!
ኒህው!

**የተከበሩ አምባሳደር ተሬዢ፤**
**የተከበሩ ሚኒስትር፤ እንዲሁም የተከበራችሁ እንግዶች፤**

ዛሬ በዚህ ፕሮግራም ሥራው በሚጀምረው ፕሮጀክት "አዲስ አበባን እንደ ስሟ አበባ እናደርጋታለን" ብለን ለሕዝባችን ሀዋሳ ላይ በገባነው ቃል መሠረት፣ ባለፈው አንድ ዓመት ቃል የገባነውን ለመተግበር የሚያስችል ሰፋፊ ሥራ ስንሠራ የቆየን ሲሆን፤ አዲስ አበባችንን አበባ ለማስመሰል፤ እንደ ስሟ ትልቅ መሆን እንድትችል እየሠራን ነው። በመጀመሪያ የጀመርነው ቤተ መንግሥቱን አድሶ ለሕዝብ ክፍት ማድረግ የሚለው ፕሮጀክት ባለፉት ስድስት ወራት ቀን እና ማታ በመሥራት፣ ማሰብ፣ ሀብት ማሰባሰብ እና በተጨባጭ የተማርንበት እጅግ ድንቅ የሆነ ፕሮጀክት፣ በሚቀጥለው ሁለት ሳምንት መስከረም ላይ በይፋ ይመረቃል። ይህ ፕሮጀክት ማሰብ ብቻ ሳይሆን መሰብሰብ፣ መሰብሰብ ብቻ ሳይሆን ማድረግ እንደምንችል የአረጋገጥንበት ፕሮጀክት ሲሆን፤ ሐሙስ መስከረም 29 ቀን በግልፅ ከተከፈተ በኋላ ዓርብ መስከረም 30 ጠዋት የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር እስከ መቶ አለቃ የሚደርስ ማዕረግ ያላቸው የሰራዊት አባላት እንዲጎበኙት ይደረጋል። ከሰዓት በኋላ፣ ከመቶ አለቃ በታች የሆኑት የፌደራል እና የአዲስ አበባ ፖሊስ አባላት እንዲጎበኙት ይደረጋል። ይህ የሚሆንበት ዋናው ዓላማ፣ ሰላም ማስጠበቅ ከቻልን አገራችን በአጭር ጊዜ ወደ ብልፅግና የምትሸጋገር መሆኑን አምነው ተቀብለው ሥራቸውን በትጋት እንዲሠሩ ለማድረግ ስለሚያስችል ነው። በማግስቱ ቅዳሜ ጠዋት፣ ታላላቆችን ማክበር ኢትዮጵያዊ ባህል በመሆኑ ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጋር በመተባበር ዕድሜያቸው ከ60 ዓመት በላይ የሆኑ አዛውንቶች የቤተ መንግሥቱን ፕሮጀክት እንዲጎበኙ ይደረጋል። ቅዳሜ ከሰዓት በኋላ፣ ከአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር ጋር በመተባበር የጎዳና ተዳዳሪዎች ይጎበኛሉ። አዛውንቶችን እና ከፍለው ማየት የማይችሉትን አስቀድሞ ማስጎብኘት፣ ኢትዮጵያ ለደሃውም፣ ለሃብታሙም፣ ለትልቁም፣ ለትንሹም፣ ለሁሉም ብሔር እኩል ማድረግ የምትችል የሁላችን እናት መሆኗን፣ ከምንናገረው በላይ የምናሳይበት ምልክት ይሆናል። ከአዲስ አበባ መስተዳደር ጋር በመተባበር በአዲስ አበባ የሚገኙ ዕድሜያቸው ከ15 ዓመት በታች የሆኑትም እንዲጎበኙ ይደረጋል።

ከሰኞ ጥቅምት 2 ቀን ጀምሮ፣ በይፋ እያንዳንዱ ዜጋ ሁለት መቶ ብር እየከፈለ የሚጎበኝበት በቪ.አይ.ፒ ወይም ባለመሰለፍ ቅድሚያ ማግኘት የሚፈልጉ ሰዎች ደግሞ አንድ አንድ ሺሕ ብር እየከፈሉ የሚጎበኙት ቦታ ይሆናል። ይህ ኢትዮጵያውያን ታሪካችንን፣ የማድረግ ባህላችንን እና ተስፋችንን የሚያሳይ ድንቅ ፕሮጀክት ሲሆን፤ ብዙዎች በቀን ከ16 ሰዓት በላይ ሠርተው ያከናወኑት ነው። ሥራውም ማሰብ እና መጨረስ እንድናውቅ እና እንድናምን ያደረገን

ስለ ሆነ፣ ከዚያ ቀጥለን የቻይና መንግሥት አጠቃላይ አዲስ አበባን የማስዋብ ዕቅዳችንን ተቀብሎ በማከናወንና በግንቦት ወር 2012 ዓመተ ምሕረት ወይም በፈረንጆች ግንቦት 2020 የመጀመሪያውን ምዕራፍ አጠናቅቆ ያስረክበናል።

## የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች፣

ከቦሌ ኤርፖርት ጀምሮ እስከ አራት ኪሎ ያለው ዕድሳት በሚቀጥሉት ሁለት ሦስት ወራት የሚጠናቀቅ ይሆናል። ይህ የምታዩት አበባ ተፈጥሯዊ አበባ ከቦሌ ጀምሮ መርካቶን ጨምሮ እስከ አራት ኪሎ ይነጠፋል። ከዚያም ቤጂንግ ወይም ዱባይ ስንሄድ የምንጓጓውን ነገር እዚሁ አዲስ አበባ ማየት እንጀምራለን። በቦሌ መንገድ ላይ ከምናደርገው ሥራ በተጨማሪ የቤተ መንግሥቱን እና ይሄኛውን እናገናኛለን። ከዚህ በተጨማሪ፤ ቦሌ አካባቢ ወደ ፒኮክ እና ወደ ወደ የዱሮው አውሮፕላን ማረፊያ፤ አቦ አካባቢ ያለውን ዞማ የግለሰብ ፓርክ በማስፋት እና በማዘመን ቀጥታ ወደ እንጦጦ እንሄዳለን። እንጦጦ በዕረፍት ቀን ከመቶ ሺሕ በላይ ሰው የሚሮጥበት፣ የሚጓዝበት፣ የሚዝናናበት ስፍራ እንዲሆን የዲዛይን እና ሀብት የማፈላለግ ሥራ እየተጠናቀቀ ሲሆን፤ እነዚህን ደምረን ለሕዝብ ክፍት ስናደርግ አዲስ አበባ እንደ ስሟ አበባ ብቻ ሳይሆን ቱሪስቶች በስፋት የሚመጡባት የኮንፍረንስ ከተማ መሆኗን ያሰፋዋል። ቱሪስት በስፋት መጣ ማለት፣ ዶላር በስፋት መጣ ማለት ነው። ቱሪስት በስፋት መጣ ማለት የሻይ ቡና አገልግሎት የሚሰጡ፤ የትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ፤ የሆቴል አገልግሎት የሚሰጡ የግሉ ሴክተር ባለ ሀብቶች አስተማማኝ የሆነ ገበያ አገኙ ማለት ነው። በዚህ የሚገኘውን ሃብት ከሌሎች ሀብቶች እና ዕውቀቶች ጋር በማሰናሰል በግብርና፤ በኢንዱስትሪ የምንሠራቸው ሥራዎችን የምናዘምንበት እና ብልፅግናችንን የምናረጋግጥበት ይሆናል።

በዚህ ሁሉ ሥራ ውስጥ የአይ.ሲ.ቲ ሚና ከፍተኛ ነው። በቀላሉ መገብየት፤ ሸርቹዋሊ ቡክ ማድረግ እንዲቻል አይ.ሲ.ቲአችን ማደግ ኮሙኒኬሽናችን ማደግ አለበት። እነዚህ ጉዳዮች ተደምረው በዚህ ዓመት ማድረግ የምንችል መሆናችንን ከአሳየን በኋላ፣ በሚቀጥሉት 10 ዓመታት ኢትዮጵያ ኢትዮጵያውያንን ብቻ ሳይሆን ሌሎች የሚመኟት ሊሄዱባት፣ ሊያዩዋት፣ ሊኖሩባት የሚፈልጓት እንድትሆን ኢትዮጵያውያን ተረዳድተው እንዳይሰደዱ እና የሥራ ዕድል በመፍጠር ማስቀረት የምንችልበትን ዕድል ያሰፋል። ብዙዎች አዲስ አበባን እንደ ስሟ አበባ እናደርጋታለን ሲባል አላመኑም ነበር። በሚቀጥለው ዓመት በስድስት ወር ቤተ መንግሥቱ ውስጥ ምን እንዳደረግን ሲያዩ፤ በሚቀጥለው ስድስት ወር ይህንን ስፍራ እንዴት እንደምንቀይረው ሲያስቡ፤ አዲስ አበባ የሚገባት እንደ ስሟ አበባ መሆኑን ያምናሉ። ይህ ሐሳብ ሙሉ በሙሉ ይሳካል። እዚህ አካባቢ እየተገነቡ ያሉ ፎቆች፣ ሆቴሎች፣ መዝናኛ ቦታዎች እንዲሆኑ፤ በዚህ አካባቢ የሚገነቡ ግንባታዎች በሙሉ ይህንን ስፍራ የሚመጥኑ እና ለቱሪስት ምቹ እንዲሆኑ፤ በእሽቅድድም እና በአቋራጭ ቦታውን የመያዝ ነገር እንዳይፈጠር በከፍተኛ ጥንቃቄ ማረጋገጥ ከአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድር የሚጠበቅ ተግባር ይሆናል። መላው የከተማችን ኅብረተሰብ ባለፈው ዓመት ከተማዋን አጽድቷል፤ ዛፍም ተክሏል። አሁንም አበባ እየተከልን ነው። ከጠበቃችሁት ከአጸደቃችሁት አዲስ አበባችን እንደ ስሟ ትሆናለች። ኢትዮጵያችንም እንደ ስሟ ለሁላችንም እናት እና የምትበቃ ትሆናለች።

ዘመኑ የብልፅግና ዘመን ነው። አቧራ ከግራ እና ከቀኝ ከፍ ብሎ ሊታይ ይችላል። አሻራችንን ማስቀመጥ እስከቻልን ድረስ ግን የኢትዮጵያን ህልውና እና ብልፅግና ሊያስቆም የሚችል አንዳች ነገር የለም። ከኢትዮጵያ ብልፅግና ተቃርነው የሚቆሙ ኃይሎች ለምን ቆሙ ከሚለው ሐሳብ

በፊት ኢትዮጵያውያን እንዲገነዘቡት የምፈልገው፤ እኔና እናንተ ዕንቁላል ፍርፍር ጠብሰን ለመብላት የግድ ዕንቁላሉ መሰበር አለበት። ዕንቁላሉን ሳንሰብር ዕንቁላል ፍርፍር ማዘጋጀት አንችልም። እንቁላሉን መጥበስ እኛ ብንስማማበትም ዶሮዋ በቀላሉ የምትስማማበት ጉዳይ አይሆንም። ዶሮዋ ዕንቁላሏ ከሚሰበር አቅፋው ጫጩት መፈልፈል ትፈልጋለች። እኛ ደግሞ ሰብረን ጠብሰን መብላት እንፈልጋለን። ይህንን የለውጥ ተቃርኖ መገንዘብ ያስፈልጋል። ዶሮዋ ዕንቁላሉን ከመሰበር አታድነውም፤ እኛም ፈርተን ዕንቁላላችንን ከመብላት አንመለስም። ኢትዮጵያ ትበለፅጋለች። አቧራዎች ይነሣሉ።

አሻራዎች እንደተባለው ቦታቸውን እየያዙ አዲሲቷን ኢትዮጵያን እንፈጥራለን።

**አመሰግናለሁ!**





# የአንድነት ፓርክ ምረቃ ሥነ ሥርዓት ንግግር

መስከረም 30/2012 ዓ.ም.

**የተከበሩ አምባሳደር ሣህለወርቅ ዘውዴ፤ የኢፌዴሪ ፕሬዝዳንት፣**
**የተከበሩ ዩዎሪ ሙሴቬኒ፤ የኡጋንዳ ፕሬዝዳንት፣**
**የተከበሩ ሳልቫኪር ማየርዴት፤ የደቡብ ሱዳን ፕሬዝዳንት፣**
**የተከበሩ ኡሁሩ ኬኒያታ፤ የኬኒያ ፕሬዝዳንት፣**
**የተከበሩ መሐመድ አብደላ ፎርማጆ፤ የሱማሊያ ፕሬዝዳንት፣**
**እንዲሁም፤ ፕሬዝዳንት እስማኤልን ወክለው የተገኙት ሚኒስትር፤**

ፕሬዝዳንት ኢሳይያስ አፈወርቂ፤ እኔ እንድወክላቸው ስለጋበዙኝ የእርሳቸውንና የኔን ጠቅልዬ እኔ አጠር ያለ ንግግር አደርጋለሁ። የኤርትራ እና የኢትዮጵያ ዝምድና ውክልና እስከ ማሰጠት የደረሰ ስለሆነ እንኳን ደስ አላችሁ!

የተከበራችሁ የኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን ልጆች፤ ይህንን ነገር በዚህ አጭር ጊዜ ተከናውኖ እንደምታዩ ሐሳብ ብቻ ተቀብላችሁ ለአንድ ራት አምስት ሚሊዮን ብር ያዋጣችሁ፣ የሰጣችሁ፣ ያገዛችሁ ወድ ኢትዮጵያውያን፤ ኢትዮጵያ በሚኖራት ክብረ በዓል ሁሉ እናንተ ሁሌም የክብር እንግዳችን ስለ ሆናችሁ፣ እንኳን በሰላም መጣችሁ!

ይህን ግቢ በዚህ መልክ ለመቀየር ለኢትዮጵያውያን ጥሪ ስናቀርብ ጥቂት የወሰኑ ቃል ተቀብለው፤ ቃል አምነው የተሳተፉ ሲሆን፤ የእነርሱን መሳተፍና እየተገኘ ያለውን ውጤት ከአዩ በኋላ በርካታ ኢትዮጵያውያን መሰል ራት ድጋሚ እንዲዘጋጅ እና ለማዋጣት ዝግጁ መሆናቸውን ቢገልጹም፣ ያ ራት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ስታንዳርድ ሆኖ የሚቀር ስለ ሆነ ድጋሚ ላለማድረግ የወሰንን መሆናችንን በዚሁ አጋጣሚ ልገልጽላችሁ እፈልጋለሁ።

ተጨማሪ ዕድሎች ወደፊት እንዳያመልጡን ቃል በማመን በመተባበር፣ ይህችን ታላቅ አገር እንደ ስሟ ታላቅ እንድናደርጋት መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ እነዚህን ቆራጥ ባለ ሃብቶች ተከትሎ እንዲሳተፍ ከወዲሁ ጥሪዬን ማቅረብ እፈልጋለሁ። ይህ ግቢ ብዙ ይናገራል። ቀደም ሲል እንዳያችሁት የሚያኮራ ታሪክ እንዳለን በደንብ ያሳያል። የሚያሳፍርም ታሪክ እንዳለን እንዲሁ ያሳያል። የተሟላ ታሪክ እንዳለን ይህ ግቢ ያሳያል። ያልተሟላም ታሪክ እንዳለን ይህ ግቢ በደንብ ያሳያል። ታሪካችንን በየልኩ አጥንተን ከተጠቀምንበት እንኳን የሚያኮራው የማያኮራውም ቢሆን ለነገ የሚሆን ወረት ለማቆየት የሚያግዝ መሆኑን ከአባቶች ከድሎቻቸው ብቻ ሳይሆን ከውድቀታቸው እና ከሽንፈታቸውም መማር አስፈላጊ እንደ ሆነ ይህ ፕሮጀክት ለሁላችንም ያስተማረ ነበር።

በዚህ ፕሮጀክት እያፈረሱ ከመሥራት እያሟሉ መሥራት አዋጭ እንደ ሆነ እኛ ተምረንበታል። ቆርጠን ከጀመርን መፈፀም እንደምንችል አስመስክረናል።





በዚህ ፕሮጀክት ኢትዮጵያ በክረምትም ቢሆን እስከ ምሽቱ ስድስት ሰዓት ቆመው ማከናወን የቻሉ ቆራጥ ሞያተኞች እንዳሉአትም ለማረጋገጥ ችለናል። የተከበራችሁ ባለሃብቶች የዛሬ ሦስት ወር ገደማ ለራት ስትመጡ የዚህ ሙዚየም ግማሹ ክፍል በተለይ ዋሻው አልተሠራም። በሰማንያ ቀን ውስጥ በዲዛይን እና ግንባታ ማጠናቀቅ የቻሉ ቀደም ሲል የሸለምናቸው ጠንካራ ኢትዮጵያውያን፤ በተለይ የራማ ኮንስትራክሽን ባለቤት አቶ ፍሬው እንዲሁም ከእርሱ ጋር በትብብር ይሠሩ የነበረው በመንግሥት ሲ.ኢ...ዎች አቶ አብረሃም፣ አቶ ሃብታሙ፣ አቶ ዮናስ ለአደረጉት አስተዋጽዖ፤ እኛ አምበሲት ብለን ለምንጠራት ክብርት ወ/ሮ ደሚቱ ላቅ ያለ ክብር እንድታቀርቡልኝ እጠይቃለሁ። ሁሉም ሚኒስትሮች እንደ ደሚቱ እስከ ስድስት ሰዓት ማምሸት ከወሰኑ፤ ሁሉም ሲ.ኢ.ኦዎች እንደነ ሃብታሙ ስድስት ሰዓት መንገድ ላይ ቆመው አበባ ማስተከልን ከመረጡ፣ የኢትዮጵያ ብልጽግና ቅርብ መሆኑን በገሐድ የሚያሳይ ክንውን ስለ ሆነ፣ የኢፌዴሪ መንግሥት ለእነዚህ ጀግኖች ከሸለመው በላይ ሁልጊዜም የከበረ ምስጋና ያለው መሆኑን ልገልጽ እፈልጋለሁ።

በመደመር እሳቤያችን እንደምናየው ሀገር ወረትም ውዝፍ ዕዳም አላት። ከእኛ የሚጠበቀው ወረቷን ማከማቸት እና ማቆየት፤ ውዝፍ ዕዳዋንም እየከፈሉ ማስተካከል እንጂ በውዝፍ ዕዳዋ እያላዘኑ ወረቷን ማሳነስ ከትውልድ የሚጠበቅ አይደለም። እኛ ኢዮጵያውያን ታሪክ አለን። እኛ ኢትዮጵያውያን እንደ ንስር አሞራ በሰማይ ስንቀዝፍ ከታየን በኋላ ዱካ የሌለን ሕዝቦች አይደለንም። እኛ ኢትዮጵያውያን እንደ መርከብ በባሕር ከቀዘፍን በኋላ በዚያ ቅጽበት ያልታየን እንደ ሆነ ዱካችን ከዋለ ከአደረ በኋላ የማንታይ ሕዝቦች አይደለንም። ታሪክ አለን። ነገር ግን እኛ በታሪክ አንኖርም። ታሪክ ግን በእኛ ውስጥ ይኖራል። እኛ በትናንት መኖር አንችልም። ትናንት ግን በእኛ ውስጥ አለ። አእምሮአችን ትናንትን በስሜታችንና በኅሊናችን ውስጥ ያኖራል። የሰው ሥልጣኔ መሠረቱ ትናንትን በመዘከር፤ ዛሬን በመኖር፤ ነገን በሥዕለ ኅሊና

በማየት ነው። ምክንያቱም ሥልጣኔ የተከማቸ የዕውቀት ጥበብ ነውና፤ የሰው ልጅ ሥልጣኔ ሁሉን ጠራርጎ እንደሚወስድ ጎርፍ ሳይሆን ሳያቋርጥ እንደሚፈስ ጅረት ነው። ፍሰቱ ከትናንት ወደ ዛሬ፣ ከዛሬ ወደ ነገ አቅጣጫ ይፈስሳል። በመሆኑም አባቶቻችን በሠሩት ጀግንነት እንደምንኮራ ሁሉ በጥፋቶቻቸው የምናፍር ሳይሆን፣ ከዚያ ተምረን ዳግም ጥፋት የማንሠራ ትውልድ ለመሆን መወሰን ይጠበቅብናል። የዚህ ፓርክ ዋነኛ ዓላማዎች አንደኛ፤ የአገራችንን ታሪክ በአንድ ቦታ የምናየበትና ብዙ ሆነን አንድ መሆናችን የምናሳይበት፤ አባቶቻችን በሁሉም መንገድ አንድ አድርገው ያቆዩአትን አገር አንድ አድርገን ለትውልድ ማሻገር ግዴታ እንዳለብን ብቁ ማሳያ ሆኖ የተገነባ ነው። ሁለተኛው፤ አገራችን ከየትኛውም የሞተ ከሚመስል ነገር ውስጥ ሕይወት እንዳላት ሕይወት ማውጣት እንደምትችልም የተማርንበት ነው።

እዚህ ስፍራ ከስምንት ወይም ከዘጠኝ ወር በፊት ያየ ሰው ዛሬ ያየውን በፍፁም ሊያስብ አይችልም። እንደዚህ ዐይነት በጣም ብዙ ቦታ ስላለ እነዚያን ቦታዎች አቧራቸውን በማራገፍ መልካም ነገር ሊወጣቸው እንደሚችል በቂ ማሳያ ነው። እንዲሁም ልጆቻችን ቤተ መንግሥት መኪና የማይቆምበት፤ ፎቶ የማይነሡበት፤ የሚፈራ ወደ ውስጥ ለመግባት የግድ መገዳደል የሚጠይቅ ሳይሆን በማንኛውም ሰዓት የሚጎበኝ፤ እንደየትኛውም ቢሮ ለአገልግሎት ብቻ የተሠራ መሆኑን እንዲገነዘቡም ጭምር ነው። ቤተ መንግሥቱን መክፈት የፈለግነው አሁን በምንገኝበት ዘመን ሀብት የደረጀ ዕውቀት ነው። ማይክሮ ሶፍት፣ ጎግል፣ ፌስ ቡክ የመሳሰሉት በዓለም ላይ ታላላቅ ሀብታም ኩባንያዎች ያደረጉት ዕውቀት እና ዳታ ማከማቸት ብቻ ነው። እኛ ኢትዮጵያውያን ያሉን ዕውቀቶች፣ ያሉን ዳታዎች ከተከማቹ ብዙ ሀብት ሊያመጡ እንደሚችሉ በእውን ያረጋገጥን ስለ ሆነ፤ ከነገ ጀምሮ ይሄ ቡድን ከቦሌ አውሮፕላን ማረፊያ እስከዚህ ቤተመንግሥት የተጀመረውን የመንገድ ማስዋብ ሥራ በከፍተኛ የሐላፊነት ስሜት በመሥራት በሚቀጥሉት ሦስት ወራት ይጠናቀቃል። እንዲሁም፤ የእንጦጦ ፓርክ ምንአልባት ከዓለም አንደኛው ፓርክ ሊሆን ይችላል። በአሜሪካን በርካታ ቦታ ፓርኮች እንዳሉ አውቃለሁ። ነገር ግን በጣም መጠናቸው ያነሰ ሲሆን ከየካ መገናኛ አካባቢ ጀምሮ እስከ መድኃኒዓለም ወደ አስኮ መሄጃ በብዙ ኪ.ሜ. የሚገመት ጫካችንን የወጣቶቻችን የሳይክል፣ የሩጫ፣ የወክ የመዝናኛ ቦታ በማድረግ በአዲስ አበባችን ፓርክ የለም ሳይሆን ከአፍሪካ ትልቁን ፓርክ እንገነባለን። ይህን ከማድረግ ሊያቆመን የሚችል አንዳች ኃይል የለም። የቻሉ ያግዙናል፤ ያልቻሉ ይተውናል። ያልገባቸው ይተቹናል፤ ያልፈለጉ ይቃወሙናል። ነገር ግን ወገባችንን አስረን ነገን እያየን ከሠራን ያለጥርጥር ማሸነፋችን አይቀርም።

ማሸነፍ የምንፈልገው ሰዎችን አይደለም። እኛ ማሸነፍ የምንፈልገው ነጋችንን ነው። ለልጆቻችን የምንተወውን ነገ ማሸነፍ እና አገራችንን ማስዋብ እንፈልጋለን። በዚህ ቤተ መንግሥት፣ በተለይም በዚህ ግብር አዳራሽ በርካታ አስደናቂ ግብዣዎች ተደርገዋል። በወቅቱ የመጡ ሰዎች ግብዣውን አድንቀው ሔደዋል። በወቅቱ የነበሩ ሰዎች ግብዣውንና ሥራውን አጣጥለዋል። ነገር ግን እኛ ከብዙ ትውልድ በኋላ ግብዣዎቹን ሳይሆን ሥራዎቹን እያወሳንና እያስታወሰን ለትውልድ ለማሸጋገር እንደ ወሰንነው ሁሉ ዛሬ ግብዣዎቻችንን፣ የፕሮቶኮል ሥራዎቻችንን፣ የምግብ አቀራረባችንን የሚተቹ ቢኖሩም የሠራነውን ሥራ ግን ለዘመናት ማስታወስ ለትውልድ ግድ ይሆናል።

ዛሬ ለመላ ኢትዮጵያውያን እርግጠኛ ሆኜ መናገር የምፈልገው እኛ እንቀጥላለን፤ በምንሠራው ሁሉ የአገራችንን ብልጽግና እናረጋግጣለን። የኢትዮጵያን ብልጽግና በሚቀጥሉት ዓሥር ዓመታት መሠረት የመጣሉ ጉዳይ የሚጀምረው ዛሬ መሆኑን አምነን የዚችን አገር ታላቅነት በሚመጥን መልኩ፤ ታሪክን ከዛሬ ጋር ለነገ በሚበጅ መልኩ በማስተሳሰር በብርታት የጀመርነውን ሥራ አጠናክረን እንቀጥላለን። የሚያግዘን ከአገኘን የወሩን በሳምንት እንጨርሳለን፤ የሳምንቱን በዕለት እንጨርሳለን። የሚያግዘን ከጠፋም የሳምንቱን በወር፤

የወሩንም በዓመት እየሠራንም ቢሆን እንቀጥላለን። ፈጽሞ ግን አናቆምም። የጀመርነውን ጨርሰን ሪቫን እንቆርጣለን እንጂ ተስፋ አንቆርጥም። ተስፋ የሚያስቆርጡ ነገሮች በየሰከንዱ በሚታዩበት፤ በየዕለቱ በሚያስደምም ሁኔታ የተሰፋው በሚተረተርበት አገር ውስጥ ብንሆንም ተስፋ አንቆርጥም። ሥራዎቻችንን ለማየት በመንገድ ላይ እንቆማለን እንጂ የጀመርነውን ሳንጨርስ ከመንገድ አንቆምም። ካለፈው እንማራለን። ዛሬ ላይ እንሠራለን። ለነገ እናቅዳለን። በዚህ ሂደት ውስጥ ዛሬ ከእኛ ጋር ሆናችሁ ኢትዮጵያን ለማበልጸግ በገንዘብ፣ በዕውቀት፣ በጸሎት በሁሉም መስክ የምታግዙ ኢትዮጵያውያን፣ በሥራ የማናሳፍራችሁ መሆኑን እና ከምትሰጡን ገንዘብ አንዱን ብር እንኳን የማንሰርቅባችሁ መሆኑን፣ ላረጋግጥላችሁ እወዳለሁ። የኢትዮጵያ እናቶችና አባቶች ባለፈው አንድ ዓመት በየጓዳችሁ ስታለቅሱ፣ ስትጸልዩ የነበራችሁ፤ ነገር ግን በምትሰሙት አዳዲስ ዜና ጸሎታችሁ ያልተሰማ የሚመስላችሁ ወላጆች ከአላችሁ ተሳስታችኋል። ጸሎታችሁ ተሰምቷል። በሚያስደንቅ ሁኔታ የጀመርነውን የጨረስነው በእኛ ብርታት ብቻ ሳይሆን በእናንተም ጸሎት ነውና እንዳታቋርጡት አደራ ልላችሁ እፈልጋለሁ። በአለፈው ዓመት አራት ቢሊዮን ችግኝ ተክለናል። በሚቀጥለው ዓመት አምስት ቢሊዮን ችግኝ እንተክላለን። አበበ ቢቂላ የጀመረውን ኃይሌ አሻሻለው እንጂ እንዲሁ አላስቀጠለውም። በየዓመቱ አዳዲስ ሪከርድ በማስመዝገብ ወደኛ መቅረብ የሚፈልጉትን አገራት ወደ ኢትዮጵያ መቅረብ ቀላል አለመሆኑን እናሳያቸዋለን። በብዙ አሳዛኝ ዜና ልባችሁ የሚሰበር ኢትዮጵያውያን ዛሬ ብቻ ሳይሆን ጥንትም፤ ሁልጊዜም ኢትዮጵያ የሚያሳዝን ታሪክ ሳይገጥማት ቀርቶ ሳይሆን ቆራጥ ልጆቿ ከሐዘን በላይ ሆነው አሻግረዋት ስለ ሆነ፤ ዛሬም የእነዚያ ጀግኖች አባቶች ልጆች ስለአሉ ኢትዮጵያ በፌስቡክ ከምናውቃት በላይ መሆኗን አስባችሁ ለብልጽግናዋ በጋራ እንድንረባረብ፤ መጪው ዘመን ብሩህ እንዲሆን፤ ምርጫችን ዲሞክራሲዊ እንዲሆን፤ አገራችን ሰላም እንዲሆን፤ ፍቅር ጥላቻን እንዲያሸንፍ ሁላችሁም በአንድ ልብ በኢትዮጵያዊነት መንፈስ በጋራ እንድትቆሙ በታላቅ ትሕትና ልጠይቃችሁ እፈልጋለሁ።

ፍቅርም ጥላቻም እኩል ጉልበት አላቸው። የጥላቻ ጉልበት እዚህ ቤት ውስጥ አዛውንቶች፣ ሴቶች፣ ሕፃናት እንዳሉ ቢያውቅም ጋዝ አርከፍክፎ ለማቃጠል ጉልበት ያለው ነው። የፍቅር ጉልበት ማለት እነዚያ ሕፃናት እነዚያ ሴቶችና ወላጆች ዘመዱ ባይሆኑም በመስኮት ዘልሎ ገብቶ የሚቃጠሉ ሰዎችን ለማትረፍ ለራስ መቃጠል ነው። ኢትዮጵያውያን መምረጥ ያለብን ሕፃናትና ሴቶችን በሚያቃጥል የጥላቻ ጀግንነት ከማጀገን፣ ሕፃናትና ሴቶችን በሚያተርፍ የፍቅር ጀግንነት ኢትዮጵያን አትርፈን እንድናሻግር በታላቅ ትሕትና እለምናችኋለሁ። በመጨረሻም ሁሌም የማያሳፍረንን ያስጀመረንን፣ ያስፈጸመንን ፈጣሪያችንን እጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ!

**ኢትዮጵያን ትናንትናም፣ ዛሬም፣ ወደፊትም የሚባርካትና የሚጠብቃት አምላክ የተመሰገነ ይሁን!**

## አመሰግናለሁ!

# የ“መደመር” መጽሐፍ ምረቃ ንግግር

ጥቅምት 8/2012 ዓ.ም.

ከዚህ ቀደም አራት የታተሙ፣ በብዙ ሺሕ ኮፒ የተሸጡ መጽሐፎች ነበሩኝ። ሁለት የገጻቸው ብዛት ዳጎስ ያለ፣ ሙሉ በሙሉ ያለቁና በአሳታሚ ምክንያት ያልታተሙ መጽሐፎችም ነበሩኝ። ነገር ግን ሁሉም መጽሐፎቼ “ዲራአዝ” በሚል ስም ይታተሙ ነበር። ዲራአዝ ማለት የመጀመሪያዋ ልጄ ዲቦራ፣ ሁለተኛዋ ልጄ ራኬብ፣ ሦስተኛዋ ልጄ አሜን እና ሦስቱን ልጆቼን እናት እና አባት ሆና ላሳደገችው ዝናሽ የተሰጠ ስጦታ ነበር። እነዚህ መጽሐፎች በስሜ ያልታተሙበት ምክንያት ለልጆቼ ያቆየሁት ወረት ስለአልነበረ ከመጽሐፍ በኋላ የሚገጥመኝ ችግር እንኳን ለልጆቼ ለቤተሰቦቼ ስጦታ እንዲሆን ታስቦ ነበር። በተለይ ሁለቱ የመጨረሻዎቹ መጽሐፎች “ሰተቴ” እና “እርካብና መንበር” በአደጋ የተሞሉ ነበሩ። “ሰተቴ” በታሪክ ውስጥ የሚታወቅ ሰው ቢሆንም፣ በዚያ መጽሐፍ ውስጥ 90% ሐሳቡ ያንን ገፀ ባሕሪ በመጠቀም፣ በውስጤ የነበረውን ጩኸት የጮኩበት መጽሐፍ ነው። ሁለተኛው “እርካብና መንበር”ም እንዲሁ አሁን ያለውን ሁኔታ፣ መደመርን በከፊል የሚያሳይ መጽሐፍ ነው። ለመደመር ለራሱ ክብር ምስጋና ይግባውና፣ አምስተኛው መጽሐፌ ግን ሳይሸሽግ በዚሁ ሁኔታ ተመረቀ።

ይሄንን ጉዳይ እንዳነሣ ያስገደደኝ የማር ውሃ ልጅ ፈለቀ “እንኳን ማሪያም ማረችህ!” ስለአለኝ ነው። መደመር ያለፈውን መልካም ወረት አጥብቆ መያዝን ያምናል። “ምን ወረት አለና?” ትሉኝ እንደሆን ቢያንስ ቢያንስ እስላምና ክርስቲያን ተከባብረው ተዋድደው ለሺሕ ዓመት የኖሩባት ድንቅ ሀገር ስለ ሆነች ይህ ወረት ነው ብዬ ስለማምን ነው። የትናትናውን ስሕተት ማረም ነው። “የትኛውን ስሕተት?” ትሉኝ እንደ ሆነ፣ ቢያንስ በኢትዮጵያ ውስጥ ከአራት ሰዎች አንዱን የድሃ ድሃ ያደረገው፤ በሚሊዮን የሚቆጠር ሕዝብ መጠለያና የዕለት ጉርስ እንዳይኖረው ያደረገው፤ በኤርትራ ስሕተት፣ በጅቡቲ ስሕተት፣ በኬንያ ስሕተት ሊሆን አይችልም። በእኛው ስንፍናና ድካም እንጂ፤ እሱን ነው ማረም የሚያስፈልገው።

መደመር ትንቢታዊ ነው። መደመር ነገን ያያል፤ ነገን ማሸነፍ ያልማል። ወደ ብልጽግና የምንጓዘውን ጉዞ ያመላክታል ስንል ደግሞ ሰው ሆኖ ዘር የማይተካ፤ ተክቶም ለልጆቹ የተሻለ ዓለም መፍጠር የማይፈልግ የለምና እኛ ኢትዮጵያውያንም ቢያንስ ድህነትን፣ ችግርን የምናሸጋግር የምናወርስ ሳንሆን፤ ብልጽግናን ለልጆቻችን የምናወርስ እንድንሆን መልካም ምኞትና የተግባር ንድፍ ጠቅልሎ የያዘ መጽሐፍ ነው። መደመር ልዩነት የለንም ብሎ አይነሣም። ነገር ግን፣ የእኛ ልዩነቶች ተከብረው እና ጌጥ ሆነው ለአንድነታችን ምሰሶ መሆን ይችላሉ ብሎ ያምናል። በቋንቋ፣ በባህል፣ በሀይማኖት፣ በፆታ ያሉን ልዩነቶች አንድ እንዳንሆን የሚከለክሉን ሳይሆን ፀጋ ሆነው ለአንድነታችን ግርማ፣ ለአንድነታችን ፍካት፣ ለአንድነታችን ውበት ሊሆኑ ይችላሉ ብሎ በጽኑ ያምናል።

ይሄንን በብዙ ምሳሌዎች ማስረዳት እችላለሁ። መደመር ከእኛው ባህል፣ ከእኛው እሴት፣ ከእኛው ልማድ፣ ከእኛው ማንነት የተነሣ ነው። የእኛ መጽሐፍ ነው የተባለው፣ ፕሮፌሰር ነብዩ ከተለያዩ ክልሎች ሲያነብ እና ሲያካፍል

የነበረው ሐሳብ ኢትዮጵያውያን ውስጥ መደመር የቆየ ያደረ ሐሳብ መሆኑን በደንብ ያመላክታል። ብዙዎች በመጽሐፉ ውስጥ ያሉትን ሐሳቦች በማየት "መደመር እንዴት ሀገርኛ ነው ይባላል?" የሚል ሐሳብ ሊያነሱ ይችላሉ። መደመር ቀይ ቀበሮ አይደለም። በኢትዮጵያ ብቻ ያለ አይደለም ግን እንደ ዝርያ ነው። እንደ ዝርያ ነው የሚያሰኘው፣ መደመር በሚል የፖለቲካና የኢኮኖሚ ንድፍ በየትኛውም ሀገር፣ የየትኛውም ግለሰብ ለአንድ ሀገር ካለችበት ውጣ ውረድ መሸጋገሪያ ይሆናል የሚል እስካሁን የቀረበ ሙሉ የሆነ ሐሳብ የለምና ነው። ነገር ግን በመደመር ውስጥ ስለፍቅር ስናወራ፤ ስለ ወረት ስናወራ፤ ስለ ዲሞክራሲ ስናወራ፤ ስለ እኩልነት ስናወራ፤ እነዚህ ሁሉ እሳቤዎችና ዓረፍተ ነገሮች ዛሬ እዚህ የተፈጠሩ ናቸው ማለት ግን አይደለም። ከተለያየ ዓለም በተለይም ከተፈጥሮ በእጅጉ ተምሮ ለእኛ እንዲመችና እንዲሆን አድርጐ በሀገርኛ ቋንቋና በሀገርኛ መንገድ የተጻፈ የእኔና የእናንተ፤ የሁላችን መጽሐፍ ነው።

ከዚህ ቀደም የነበሩ ርእዮተ ዓለሞችን በጥራዝ በጥራዝ በማንበብ፤ በመተርጎም፤ በመተንተን፤ በማስተማር የደከሙ ትውልዶች በሀገራችን ብዙ አሉ። ከእናንተ የሚጠበቀው የሰው በመተርጐምና በመተንተን ከመድከም ይህንን ዶ/ር ምሕረት እንደገለፀው መደመርን መነሻ መሠረት አድርገን ማሳደግ፣ ማስዋብ፣ ማተለቅና ከእኛ አልፎ ለሌላው ዓለም እንዲሆን ማድረግ ነው። ይህንን ለማድረግ አብዝቶ መተቸት ብቻ ሳይሆን ከተቸን በኋላ አማራጭ ሐሳብ ማምጣት ያስፈልጋል። መደመርን ስንተች የተሻለ ማባዛትን መፍጠር አለብን። በመተቸት ውስጥ ተጽናንተን እንዳንቀር እየተቸን ግን የተሻለ አማራጭ የምናመጣ ከሆነ ራሱን መደመርን የሚያሳድገው፤ እንዲያብብ የሚያደርገው፤ የሚያተልቀው ስለ ሆነ፣ ይህንን አተላቂ ሐሳብ ለማምጣት መተቸት ብቻ ሳይሆን፣ አማራጭ ሐሳብ ማምጣትንም መለማመድ ይኖርብናል። መደመር ሰው የመሆን እሴት ነው። መነሻውም መድረሻውም ተፈጥሮና ሰው ነው። የሰው ልጅ የሚገነባበት የመጀመሪያ የግንባታ ጡብ የሚጀምረው ከሴል ነው።





ሴል የሚባለው ጡብ በዝቶ ተሰናስሎ፤ አንዱ በአንዱ ተደራርቦ ሥራውን ለይቶ በተደመረ መንገድ የአንድን ሰው ግንባታና ክንውን ከፍፃሜ ያደርሳል። ይህ ሴል ምንም እንኳን የሰው ልጅ መሠረት ጡብ ቢሆንም አንድ ጡብ ሲሠራ አፈር፣ ውሃ እሱን በማዋሐድና በማቃጠል ምሉዕ እንደሚሆን ሁሉ በሴል ውስጥም ክፍልፋይ ማንነቶች አሉ። በሴል ውስጥ ካሉ ክፍልፋይ ማንነቶች ውስጥ አንዱ ክሮሞዞም ይባላል። ክሮሞዞም በሴል ዉስጥ ያለ ያነሰ ነገር ቢሆንም፤ ይህ ክሮሞዞም ሲሰናሰልና ሲደመር ዲ.ኤን.ኤ.ን ወይም ዘረ መልን ይፈጥራል። አንድ ዘረ መል የመደመር መነሻ እና መሠረት ነው። በአንድ ዘረ መል ውስጥ ከአባትና ከእናት የተውጣጣውን ማንነት የምናይበት ከሴል ያነሰ እጅግ ከማነሱ የተነሣ በዐይን ሊታይ የማይችል ግን የሰው ልጅ የመደመር መጀመሪያ ጡብ ሆኖ የሚያገለግለው ዲ.ኤን.ኤ. ይገኛል። ይህ ዲ.ኤን.ኤ. ከእናትና ከአባት የሚወረስ ማንነት ብቻ ሳይሆን፣ ዲ.ኤን.ኤ. ሲበላሽ ራሱን አያበላሽም ፍጡር ያበላሻል። አንድ  ጡብ ሲበላሽ ሕንፃ እንደሚያበላሸው ሁሉ፣ አንድ ዲ.ኤን.ኤ. ሲበላሽ ፍጡር ነው የሚያበላሸው፤ ትንሽ በመበላሸቱ፣ ትንሽ በመጥፋቱ ትልቁ ምንም አይሆንም የሚባል እሳቤ ትክክል አለመሆኑን ተፈጥሮ ያስተምረናል።

መደመር ትልቁ በደቂቁ፣ ሊቁ በረቂቁ ይሠራል ብሎ በጽኑ ያምናል። የረቂቁ ውሕደት የትላልቁን ደኅንነት እና ሕይወት ያረጋግጣል ብሎም ያምናል። ደቂቁ ከሌለ ትልቁ አይኖርም፣ ዲ.ኤን.ኤ. ከሌለ፣ ሴል ከሌለ፣ የሰው ሙሉ ማንነት አይፈጠርም። እናም መደመር ከሰው ነው የሚነሣው ስንል የሰውን ተፈጥሮ በዝርዝር ያጠና ሰው የመደመርን አስፈላጊነት በእጅጉ ሊገነዘብ ይችላል።

ሀገርኛ ያሰኘንና ከቀደሙት በተለየ መንገድ እንድናይ ያደረገን ኢትዮጵያ ውስጥ ላለፉት 40 እና 50 ዓመታት ሲቀነቀኑ የነበሩ እሳቤዎች ከሁሉም ሐሳቦች፣ ከሁሉም የእሳቤው አባቶች ተቀነጫጭቦ እኛ ሀገር ሲሠራበት የነበረው

እሳቤ ወይም አይዲዮሎጂ ምን ጉዳት እንዳመጣ ሁላችሁም ታውቃላችሁ። የሶሻሊዝም አባት ተብሎ የሚታወቀው ማርክስ ወይም ማርክሲዝም ከአስተማራቸው እሳቤዎች ውስጥ አንዱ የመደብ መከፋፈል ነው። ማርክስ ከመቶ ዓመት በፊት የሚያውቀው የባሪያ ሥርዓትን ነበር። ባሪያ አሳዳሪና ራሱ ባሪያ በሚል በሁለት የተከፈለ መሆኑን፤ ከዚያም የከበርቴውና የፊውዳል ጠብ፤ የከበርቴው አሸናፊነት የከበርቴ እና የሠራተኛ መደብን እንደ ፈጠረ ያውቅ ነበር። በእርሱ ዘመን የተከፋፈሉ መደቦች ስለአሉ ሁል ጊዜ ትንታኔ የሚጀምረው ከመደብ ነው። ላይ እና ታች፣ ሀብታም እና ደሃ፣ አሠሪ እና ሠራተኛ፣ ባሪያ እና የባሪያ አሳዳሪ በሚል እሳቤ ያየዋል። አንዳንዶች ማርክስን የተምታታበት ሰው ይሉታል። ምንም እንኳን ማርክ የኅብረተሰብ ክፍልን እና መደብን በለየ መንገድ ሐሳቡን ለዚያ ዘመን በሚበጅ መልኩ ያስቀመጠ ቢሆንም፤ ዛሬም እኛ ከመቶ ዓመት በኋላ መደብ የሌለው ፖለቲካ የለም እንላለን።

ከ30 ዓመት በፊት እንኳን መደብ በቁመት እንዳንለያይ ሀብታም መሆን የማይቻልበት ሀገር፤ ፈጣሪ መሆን የማይቻልበት ሀገር፤ ሰፋፊ እርሻ ማረስ የማይቻልበት ሀገር አድርገን ፈጥረን ስናበቃ፤ ሀብታም በሌለበት ምንም ኢንዱስትሪ በሌለበትና ሠራተኛ በሌለበት በግድ የማርክሲስት ሐሳብ ተከታይ ለመሆን በመደብ ካልተከፋፈልን ብለን እንቸገራለን። ማንን ከማን ነው የምንከፋፍለው? በኢትዮጵያ ውስጥ ሀብታም እንደ ሆነ የለም። በኢትዮጵያ ውስጥ የባሪያ አሳዳሪ የለም። በኢትዮጵያ ውስጥ ባሪያ የለም። በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ጥሮ ግሮ፣ ሠርቶ ለመብላት የሚቸገር ሰው ነው። ይህ ሰው በሰሜንም አለ። በምዕራብም አለ። በደቡብም አለ። በምሥራቅም አለ። ይሄንን የእኛን ነባራዊ ሁኔታ ያላገናዘበ እሳቤ ከማርክስ በኋላ ያመጣው ሌኒን በማርክስ ሐሳብ ላይ የተንተራሰ ቢሆንም የቸገረው ነገር አለ። "የሠራተኛው መደብ አሸንፎ አምባገነናዊ መንግሥት መፍጠር እንዴት ይችላል?" የሚለውን ሐሳብ ማርክስ በትክክል ስላልመለሰ ሌኒን ያን ለመመለስ የፓርቲ ግንባር ቀደም የሆነ





ፓርቲ ያስፈልጋል አለ። የሠራተኛውን መደብ ጥቅም የሚያስከብር ግንባር ቀደም ፓርቲ ያስፈልጋል አለ። ከማርክስ የመደብ ክፍፍሉን ወሰድን፤ ከሌኒን ግንባር ቀደም ፓርቲ ያስፈልጋል ብለን አውራ ፓርቲ አልን። ቀጠልንና፣ እነዚህ እሳቤዎች በሩሲያ አካባቢ የነበሩ ስለ ሆነ፣ ማኦ ደግሞ የሩሲያን እሳቤ እንዳለ ስላልወሰደ ማኦ "አዲሱ ዴሞክራሲ" በሚለው መጽሐፉ፤ ሠራተኛ በሌለበት ቻይና ውስጥ አርሶ አደር ነው ታሳቢ መሆን ያለበት አለ። ዛሬም ኮሚኒዝም ኢን-ቻይኒስ ካራክተርስቲክስ ብለው የሚያስቡት ያኔ ሲጀምሩ በሀገራቸው የሠራተኛው መደብ ስለ ሌለ፣ የአርሶ አደሩን መደብ ታሳቢ ያደረገ የማኦን እሳቤ፣ እኛ ውግንናችን ለአርሶ አደር ነው ብለን ደግሞ ቀንጨብ አደረግን። ነገር ግን፣ ለአርሶ አደር መወገን በጣም አስፈላጊ ነበር። ኢትዮጵያ ውስጥ የሚያሳዝነው ለከተማው ነዋሪ ዘይት ስንደጉም፤ ስንዴ ስንደጉም፤ መብራት ስንደጉም፤ ነዳጅ ስንደጉም ለአርሶ አደሩ ማዳበሪያ እንኳን ማቅረብ ያልቻልን፤ በዚች ለም ምድር ውስጥ አርሶ ኢትዮጵያውያንን እንዲመግብ እንኳን ያላስቻልን፤ በስሙ የነገድን የስም ነጋዴዎች ነበርን እኛ።

ይህ የስም ነጋዴነት ከመነሻው ከመርሑ የተነሣ ነው። ከመነሻው ማኦ ሲጀምር "አርሶ አደር ቅን የዋህ ነው። አንዴ ካመነ ለረጅም ጊዜ ይከተልሃል።" ይልና "የራሱን ሐሳብ ማፍለቅ የማይችል፤ ራሱን መምራት የማይችል፤ የተውሶ አመራር የሚሻ ነው" በሚል "ተራማጅ ምሁር" ይልና "ተራማጁ ምሁር አርሶ አደሩን ይምራው" ይላል። "የማያውቅ ለራሱ ሐሳብ ማፍለቅ የማይችል" ያለውን አርሶ አደር በንጹሕ አእምሮ ይከተለኛል ከሚል እሳቤ እንጂ፣ ከጅምሩም ውግንና ቢሆን ኖሮ አርሶ አደሩ በራሱ ጉዳይ፣ በራሱ ልክ፣ በራሱ ዐቅም እንዲወስን የሚያስችል እሳቤ በሆነ ነበር። ነገር ግን ተራማጅ የሚባለው ምሁር ልክ ካፒታሊስቶች "የሠራተኛው መደብ ፈጣሪ አይደለም፤ ተግቶ አይሠራም፤ እኛ እንፈጥራለን፤ ቀጥረን እናሠራዋለን" እንደሚሉት፤ ለአርሶ አደር የሚወግን ነው የሚባለው ኃይል ደግሞ "አርሶ አደር ለራሱ አያውቅም እኔ አውቅለታለሁ" ብሎ የሞግዚት አስተዳደር ይፈጥራል።

አራተኛው፣ ስታሊን የሚባለው ሰውዬ “ይህ ሐሳብ ተግባራዊ እንዲሆን ዓለም አቀፍ ሶሻሊዝምን መገንባት አስፈላጊ አይደለም፤ በሀገር ደረጃ ብቻ መሆን አለበት” ካለ በኋላ “ይህ እንዲሳካ ጠንካራ ሠራዊት መገንባት ያስፈልጋል። ሠራዊቱም የሚጠብቀው ፓርቲውንና መሪውን መሆን አለበት። ቁጥጥር የበዛበት፤ ኃይል የበዛበት ነገር ሁሉ ልማት ልማት የሚል መሆን አለበት” ይላል። እንግዲህ ከእነዚህ አራቱ ምን ያህል ቀንጨብ ቀንጨብ አድርገን እንደኖርን ባለፉት ዓመታት በደንብ የምትገነዘቡ ይመስለኛል።

አሁን የምንጨቃጨቅበት አብዮታዊ ዴሞክራሲ በ1917 ከአንድ መቶ አንድ ዓመት በፊት ሌኒን የፈጠረው ነው። የዛሬ አንድ መቶ አንድ ዓመት ሌኒን አብዮታዊ ዴሞክራሲን ሲፈጥር ማርክስ ያለው “ሶሻሊዝም ሊፈጠር የሚችለው ካፒታሊዝም አድጎ፤ አብቦ ከተንኮታኮተ በኋላ ነዉ።” የሚል እሳቤ ስለነበረው፤ በሩሲያ ያኔ ካፒታሊስት ሥርዓት ስላልነበረ “ካፒታሊስት ሥርዓትን ሳናይ ሶሻሊዝምን መገንቢያው አቋራጭ መንገድ አብዮታዊ ዴሞክራሲ ነው” አለ። እኛ ደግሞ “የካፒታሊስት ሥርዓት መገንቢያው መንገድ አብዮታዊ ዴሞክራሲ ነው” አልን። ሁለቱ ሐሳቦች እርስ በእርስ የሚቃረኑ መሆናቸው ብቻ ሳይሆን፤ ሌኒን በዚያ ዘመን ቢያንስ ኮምፒውተር አያውቅም። ሌኒን በዚያ ዘመን ቢያንስ ፕሮጀክተር እንዳለ አያዉቅም። ብዙ የምናውቀው አሁን ዓለም የፈጠረው ነባራዊ ሁኔታ ነው። ይሄንን ነባራዊ ሁኔታ ታሳቢ ያደረገ አዳዲስ እሳቤ መፍጠር፣ ለሁሉም ትውልድ የሚሰጥ እንጂ አንዴ የተፈጠረ ሐሳብ ለዘላለም መከተል ተገቢ አይደለም ብሎ መደመር በጽኑ ያምናል።

ወደ ሰው ልመልሳችሁና በሰው ውስጥ የደም ዝውውር እንዲከናወን “ልብ” የሚባለው አካል ደም ይረጫል። ነገር ግን፣ የደም ስሮች ባይኖሩ የተረጨው ደም ከአንድ ስፍራ ወደ ሌላ ስፍራ እንዴት መድረስ ይሆንለት ነበር? ልብ ደም መርጨቱ ብቻውን በቂ አይደለም። የደም ስሮችም ያስፈልጋሉ። በሰው ውስጥ





ሳንባ የሚባል የመተንፈሻ አካል አለ። ሳንባ ቢተነፍስም ቀይ የደም ሴል ያንን አየር ማጓጓዝ ባይችሉ ሌሎች ሕዋሳት ምን ይሆኑ ነበር? አንደኛው መሥራቱ ብቻውን በቂ አይደለም። ከዚያም በላይ በአናት ቅል ውስጥ ተደብቆ ያለው የራሱን ደጅ እንኳን አይቶ የማያውቀው አንጎል ዓሥር ኢንች ፈቀቅ ብሎ እሱ ደጅ ያለውን እንኳን ማየት አይችልም። ነገር ግን እጅን ያዝዛል፤ እግርን ያዝዛል። እግርና እጅ በአንጎል ታዝዘው ሥራ መከወን የሚችሉት ስፓይናል ኮርድ የሚባል ነገር ባይኖር ኖሮ ትዕዛዝ ተቀብሎ ወደሚታዘዘው ሊያደርስ የሚችል አካል ባልኖረ ነበር። አንጎልን ስለአላየሁት መጥቶ በማርክሲስት ሌኒኒሊስት ቲዮሪ ካልተነተነልኝ በስተቀር እግር አልንቀሳቀስም ቢል ኖሮ ምን ሊፈጠር እንደሚችል አስቡት።

እነዚህን ሳይተያዩ የሚተጋገዙ፤ ሳይተያዩ የተደመሩ አካላት ያየ ሰው እንዴት ኢትዮጵያን ደምሮ መሄድ እንዳለበት ብዙ አይቸገርም። ሕይወት የሚፈጠረውም ሆነ የሚኖረው ተደምረው በሚፈጠሩ ራስን በሚያውቅና በሚሆን ሌላውንም በሚያከብርና በሚወድድ ጥምር ማንነት ነው። ለብቻዬ የሚባል ነገር የለም። ለብቻዬ የሚባል ነገር አያዛልቅም። ይህን ከሰው አልፈን በሌላም ነገር ማየት እንችላለን። ነገር ግን ሰውን ሰው የሚያደርገው ጆሮ የአንበሳ ድምፅ ሰምቶ እግር መሮጥ ከቻለ ብቻ ነው። ጆሮ ለሰማው ምን አገባኝ ካለ መበላት አይቀርም። እግርን እንቅፋት ሲመታው ዐይን ምን አግብቶት ነው የሚያለቅሰው? አልተመታ፤ የእግር ሕመም ሕመሜ ነው ስለሚል ነው። መደመርን ሰው ለማወቅ ብዙ መቸገር የለበትም። ራሱን ወደ ውስጥ በጥልቀት መመርመርና ማየት ከቻለ፣ መደመር ቁልጭ ብሎ በሰው ውስጥ ይታያል። ነገር ግን፣ በሰው ብቻ ምን ያደርጋል ያላችሁኝ እንደሆነ ዕፅዋት ውስጥም አለ።

ባለፈው ጊዜ የኢሬቻ በዓል ተከብሯል። የኢሬቻ በዓል ቢሾፍቱ ሲከበር ሰዎች የኦዳ ዛፍ እንዳለና በዚያ ስፍራ የምስጋና ሥነ ሥርዓት እንደሚከወን እንጂ

ራሱ ኦዳውን በጥልቀት አይመለከቱትም። ኦዳው ግን ስድስት ወር ሴቴ ነው። ስድስት ወር ወንዴ ነው። አንዱ ኦዳ ሁለት ፆታ አለው። ሁለት ፆታ ያለው ኦዳ መሆኑ ብቻ ሳይሆን ሴቴዋ ተረኛ ሆና በምታብበት ጊዜ ወንዴው ይጠፋል ማለት አይደለም። በሴቴዋ ውስጥ ተደብቆ ይኖራል ማለት ነው። መደመር ማለት እሱ ነው።

አሁን አዳዲስ ምርምሮች ደግሞ እየወጡ ነው። የተፈጥሮ ሳይንስ ተመራማሪዎች በዚህ ጉዳይ ዘርዘር ያለ ነገር አንብባችሁ ብታስተምሩ ደስ ይለኛል። በዚህ ሐሳብ ድረገጽም በስፋት ይገኛል። አሁን ደግሞ የሚገርመው እኛ እዚህ በዘር ተከፋፍለን መተጋገዝ ነውር በሆነብን ዘመን ውስጥ ዛፎች ይተጋገዛሉ የሚል ሳይንስ ወጣ። ዛፎች ጐን ለጐን ሲኖሩ ሥራቸው ልክ እንደ ኔትዎርክ፤ እንደ ስልክ ኔትዎርክ የተሳሰረ ነው። አንደኛው ዛፍ ሲቆረጥ ለጐረቤቱ አደጋ እየመጣብህ ነውና ተጠንቀቅ የሚል ምልክት ይልካል አሉ። ዛፍ እራሱ አደጋ እየመጣ መሆኑን እሱ አደጋ እየተጋፈጠ ለጐኑ ላለው ዛፍ ጥንቃቄ እንዲያደርግና እራሱን እንዲያባዛ የሚመክር ከሆነ፤ አማራ ሲጠቃ የማይደነግጥ ኦሮሞ፤ ኦሮሞ ሲጠቃ የማይደነግጥ ትግሬ፤ ትግሬ ሲጠቃ የማይደናገጥ አፋር እንዴት ሊኖር ይችላል?

ዛፍና ሰው ብቻ ሳይሆን ጽንፈ ዓለምን ብንመለከት ወሰን በሌለው ከረጢት ውስጥ ይህን ሁለንተናችንን አቅፎ የያዘው ጽንፈ ዓለም የሚባለው ከረጢት ግዙፉን፣ ሩቁን፣ ከዋክብቶቹን፣ ረቂቅ አተሞችን በሚደንቅ ሁኔታ አስተሳሳሮ፣ አስተፃምሮ አዋድዶ የያዘ ነው። አንዳንድ ቦታ እየተገፋፉ፤ አንዳንድ ቦታ ደግሞ እየተሳሳቡ፤ እኛ ኒውተን ያወጣውን ቲዮሪ የመሬት ስበትን ብቻ ማየት ስለምናዘወትር እንጂ ሁሉም በዚህ በጽንፍ ዓለም ውስጥ ያሉ ተፈጥሮዎች አንዱ አንዱን በመግፋትና አንዱ አንዱን በመጐተት ሚዛናቸውን ጠብቀው መኖር ባይችሉ ኖሮ ዛሬ ፀሐይ ብትወድቅ ምን ልንሆን እንደምንችል አስቡት። ተፈጥሮም ተከባብሮ፣ ተገፋፍቶና ተሳስቦ የሚኖርበት ሁኔታ ተራርቆ፣ ተቀራርቦና ተሰናስሎ አንድ ላይ መኖር፤ መደመር በአስተፃምሮ ምን መምሰል እንዳለበት የሚያመላክት ነው። በሰው፣ በዕፅዋት በጽንፍ ዓለም ብቻ የሚወሰን አይደለም።

ከዚያም አልፎ በሙዚቃም ያየን እንደ ሆነ፣ እያንዳንዱ የሙዚቃ መሣሪያ የራሱ ድምፅ፣ የራሱ ማንነት፣ የራሱ ስም፣ የራሱ ባለሙያ አለው። ነገር ግን፣ አንዱ ድምፅ ብቻ አንድ ሰዓት ቢደመጥ ምን ያክል ሰው ሊይዝ እንደሚችል አላውቅም። በሕብረት በሚሆኑበት ሰዓት ግን አፍ አውጥተው ይናገራሉ። ቅድም ስናደምጥ የነበረው ክላሲካል ነው። እናንተ ግን ሠላም እያላችሁ ትዘፍኑ ነበር። ማን ነገራችሁ? እነዚህ ግኡዛን አፍ አውጥተው መናገር ብቻ ሳይሆን ሰው መቀስቀስ ይችላሉ። ሙዚቃ እየሰማ የሚያጨበጭብ፣ እግሩን የሚያንቀሳቅስ፣ ሰውነቱን የሚያንቀሳቅስ፣ ከዚያም ሻገር ሲል ራሱን መቆጣጠር አቅቶት ከወንበሩ ዘሎ የሚነሣው ማን ቀስቅሶት ነው? ግኡዛን ተደምረው ሰው ከቀሰቀሱ፤ ሰው ተደምሮ ምን ማድረግ እንደሚችል እስኪ አስቡት። ሕያዋንና ግኡዛን ተናብበው እና ተግባብተው፤ ተከባብረው መኖር ሲችሉ ዓለም ትበለጽጋለች። አፈር፣ ውሃ፣ አየር፣ ብርሃን ተደባልቀው በረቂቅ የዕፅዋት እና ሕዋሳት ውስጥ ተሰናስለው ሕይወት ይሰጣሉ። ከእነዚህ መካከል አንዱ ባይኖር የዕፅዋት ሕይወት አይኖርም። ብርሃን ባይኖር፣ ውሃ ባይኖር፣ አፈር ባይኖር አይታሰብም። ዕፅዋት ባይኖሩስ? እንስሳት እርስ በእርስ ተበላልተው ያልቁ ነበር። እንስሳትና ዕፅዋት ባይኖሩስ? እኛ መኖር አንችልም ነበር ማለት ነው። የእኛ ምግብ ዕፅዋትና እንስሳት ስለሆኑ፤ ግኡዛንና ነፍስ ያላቸው ነገሮች እንዲህ ተስማምተው በሚኖሩበት ዓለም ውስጥ እኔ አልደመርም የሚል በብቸኝነት ጉድለት ውስጥ ከመዳከር ውጭ ወደ ሙላት የሚደረገውን ጉዞ አያረጋግጥም።

ፕላቶ የተሰኘው ፈላስፋ ሰውን በሦስት መንገድ ከፍሎ ይገልጸዋል። አንደኛው አመክንዮ ነው። ሰው የማወቅ፣ በንድፈ ሐሳብ፣ ፅንሰ ሐሳብ እንዲሁም በምናብ ዓለም የማለምና የመጓዝ ፍላጐትና ጥማት አለው። ሰው ለማወቅ የሚያደርገውን ጥማትና ፍላጐት በሆነ መንገድ ልንመልሰው አንችልም። እራሱን አስችለን ማወቅ፣ መሻቱ መገብየት የሚችልበትን ግልጥ ያለ የገበያ ዓውድ መፍጠር ይፈልጋል።

ሁለተኛው ቁሳዊ ፍላጐት ነው። ሰው በቁሳዊ ፍላጐት የማደግ፣ የመበልፀግ፣ ጤነኛ የመሆን ፍላጐት አለው። ቀደም ሲል በነበረን እሳቤ ሰው ጤነኛ መሆን አለበት ስንል ጤነኛ ከሆነ ያመርታል ይላል። ሰውን እንደ የግብ መድረሻ እንጂ እንደ ግብ አይወስደውም። መደመር ግን ሰው በራሱ ግብ ስለሆነ የሰውን ጤነኝነት እንደ መሣሪያ ከሥራ ጋር አያያይዘውም። እያንዳንዱን ጽሑፋችንን ስትመለከቱ ሰውን እንደ ማሽን ጤነኛ አርገን የማምረቻ መሣሪያ እናድርገው ከሚል እሳቤ እንጂ፣ ሰው በራሱ ጤነኝቱና ደስተኝነቱ ተፈጥሮአዊ ፍላጐቱ ሊሟላለት የሚገባ እንደሆነ አያምንም። ሦስተኛው የፕላቶ እሳቤ ቀነኢነት ወይም ቁጭት ነው። እያንዳንዱ ሰው በውስጡ እምቅ ዐቅም አለው። የተደበቀ ፍላጐት አለው። ይህንን ፍላጐት፤ ይህንን ቁጭት ማውጣት የሚችልበት ዐቅም መፍጠር ይላል። መደመር ከእስከ አሁኑ እሳቤዎች ለየት የሚያደርገው እነዚህን ሐሳቦች በሙሉ አሰናስሎ፣ አዋድዶ ኢትዮጵያን ወደ ላቀ ደረጃ ለማሸጋገር በሚችል መንገድ የተቀረጸ ሰነድ በመሆኑና የእኔ ብቻ ሳይሆን የእናንተም ሰነድ መሆኑ ነው። በመሆኑም ይህንን ሀገርኛ ሐሳብ አሳድጉት፣ አስፋፉት፣ ተንትኑት። እናንተ በዕውቀት ከተነተናችሁት ራሱ መደመር ባሕሪው የሚያውቀው ጉድለቱን ከወገኑ መሙላት ስለ ሆነ እያደገ እያበበ ይሄዳል። ሳታነቡት ብትተቹት እሱን አትጥሉትም፣ እናንተ ግን አታድጉም።





በዚሁ፣ የሰሞኑን የኖቤል ሽልማት አስመልክቶ ለመላ የኢትዮጵያ ሕዝቦች መናገር የምፈልገው እኔ ከበሻሻ የወጣሁ፤ የኖቤል ሽልማት ቀርቶ ጥሩ ጥሩ ሰርተፊኬት እንኳን ያላየሁ የድሃ ልጅ ነኝ። ይህ የእናንተ ውጤት ነው። የኖቤል ሽልማቱ የኢትዮጵያውያን ነው። ነገር ግን ሰሞኑን አንድ ወዳጄ አንድ ታላቅ ቁም ነገር ነገረኝ። “ይህ የኖቤል ሽልማት ተሰጥቶሀል። ድጋሚም አታገኘውም፤ ደግሞም ከአንተ አይወሰድብህም” አለኝ። ኢትዮጵያውያን ይህ ሽልማት ተሰጥቷቸዋል፤ አውቀው ካልጠበቁት ግን ሊወሰድባቸው ይችላል። በዓለም ላይ ኢትዮጵያ ከፍ ብላ በሚያስደንቅ ሁኔታ ስሟ ገንኖ ተነሥቷል። ዐቢይና ኢትዮጵያ፤ ኢትዮጵያ እና ዐቢይ የማይነጣጠሉ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታ ስለ ሆኑ፤ አሁን የኖቤል የሠላም ሽልማቱ “ለምን? እንዴት? መቼ? ከማን?” የሚለውን ፍልስፍና እንተውና “እንዴት ብለን ነው በፊዚክስ፣ በኬሚስትሪ፣ በሥነ ጽሑፍ አዳዲስ ኖቤል ሽልማት የምናመጣው?” ብለን ብናስብ ጥሩ ነው።

በዚሁ አንድ ወዳጄ የነገረኝን አንድ ሐሳብ ላካፍላችሁ፤ በዐረብ ሀገር የሚገኙ እኅቶቻችን ብዙ ጊዜ ከፎቅ ተወረወሩ፤ ሀብታቸው ተቀማ፤ እጅ እግር ተሰበረ ሲባል እንሰማለን ታወቃላችሁ። በዐረብ ሀገር የምትገኝ አንድ ሠራተኛ ለአንድ ወዳጄ መልእክት ላከችለት። “ይኼ ኖቤል የምትሉት ምን እንደ ሆነ አላውቅም። ዐቢይ ምን እንደ ተሸለመ አላውቅም። እኔ ግን ይገርምሃል ማዳሜ ቤት መጥታ ‘ነይ ከጐኔ ቁጭ በይ’ ብላ ‘የእናንተ መንግሥት...’ እያለች የሚያስደንቅ ነገር አወራችኝ። ይሄ ሽልማት ለእርሱ ይሁን ለእኛ፣ በዐረብ ሀገር ላለነው ሠራተኞች ይሁን ባይገባኝም እኔ ግን ተከበርኩበት” ብላ ነገረችው። አሁን እኛ ያለን ሐሳብ የኖቤል ሽልማት ለመጀመሪያ ጊዜ ኢትዮጵያ አግኝታለች፤ በቅርቡ ደግሞ ኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ በሕዋ ውስጥ የራሷ ሳተላይት እንዲኖራት እየሠራን ነው። ያለፈውን የኖቤል ሽልማት እየዘከርንና እየዘፈንን ወይም እየረገምንና እየተሳደብን ጊዜ አናባክን። አዳዲስ ኖቤል ለማግኘትና አዳዲስ ሳተላይት ለማምጠቅ ወደ ፊት ብናስብ መልካም ነው።

በዚሁ ሰሞኑን ከፓርቲ ውሕደት ጋር ተያይዞ ብዙ ሐሳቦች ሲነሡ ስለምሰማ፤ ይሄ የመጀመሪያ ያገኘሁት ዕድል ስለሆነ፣ እዚህም ያለው ስብስብ ቀላል ባለመሆኑና ለመላው ኢትዮጵያውያን ይህንን ጉዳይ በአጭሩ መግለጽ እፈልጋለሁ። የፓርቲ ውሕደት ጉዳይ አላለቀም። እኛ የመደመር ፍልስፍናን የምናምን ሰዎች በዲሞክራሲያዊ ፍልስፍና ስለምናምን አንድ ዓመት ከስድስት ወር ሙሉ ተጠንቶ ያለቀ ሰነድ ቢሆንም ሳለመበተን ስንለማመንና ስንወያይ ከርመናል። አሁንም ውይይቱ አልተቋጨም። ውይይቱ ሳይቋጭ አንዳንዶች "ይህ የፓርቲ ውሕደት መጨፍለቅ ነውና ኢትዮጵያን ከፌዴራላዊ ሥርዓት ወደ አሐዳዊ ሥርዓት መመለስ ነው" የሚል በእኛ ውስጥ ታስቦ ታልሞ የማያውቀውን መርዶ አረዱን። የፓርቲው አንድ መሆን ኢትዮጵያን የሚጨፈለቅ ከሆነ ኢትዮጵያ አልነበረችም ተጨፍልቃለች ማለት ነው። ምክንያቱም ትግራይ ውስጥ ቲ.ፒ.ኤል.ኤፍ. የሚባል ድርጅት እንጂ ኩናማ የራሱ ድርጅት የለውም። ኢሮብ የራሱ ድርጅት የለውም። ኢሮብ የራሱ ልዩ ወረዳ አለው። ኩናማ የራሱ ልዩ ወረዳ አለው። በቲ.ፒ.ኤል.ኤፍ. ይተዳደራል። ነገር ግን የፌዴራል ሥርዓት አልተጨፈለቀም።

በአማራ ክልል ኦሮሞ፣ ቅማንት፣ አገው፣ አርጐባ የሚባሉ ሕዝቦች በብአዴን መንግሥት ሥር ይተዳደራሉ። በብአዴን መንግሥት ውስጥ እና ፓርቲ ውስጥ ማዕከላዊ ኮሚቴ፣ ከፍተኛ አመራር ሆነው በፌዴራል ሥርዓት ውስጥ ለአለፉት 27 ዓመታት ኖረዋል። በአማራ ክልል የአገው የሚባል ፓርቲ፣ የቅማንት የሚባል ፓርቲ፣ የወሎ ኦሮሞ የሚባል ፓርቲ በሌለበት እስከአሁን ተጨፍልቀን ነበር ማለት ነው። በደቡብ ደኢሕዴን የሚባለው ፓርቲ 56 ገደማ ብሔር ብሔረሰቦችን ደምሮ እንደ አንድ ፓርቲ ሆኖ ሲሠራ፣ በወላይታ ዞን ወላይትኛ አይነገርም፤ በሲዳማ ዞን አፉ ሲዳማ አይነገርም፤ በሀዲያ ዞን ሀዲይሳ አይነገርም ብሎ አያውቅም። አንድ ፓርቲ 50 ብሔር ብሔረሰቦች ማስተዳደር ከቻለ እንዴት ነው አንድ ፓርቲ ኢትዮጵያን ሲያስተደድር መጨፍለቅ የሚሆነው? እንዴትስ ነው እኛ ኢሕአዴጐች ራሳችን ለ30 ዓመታት አንድ መሆን ተስኖን ኢትዮጵያን አንድ ማድረግ የምንችለው? የትናንትናውን ስሕተት እናርማለን ስንል ኢሕአዴግ በአለፉት ዓመታት ሕገ መንግሥቱን በብዙ መንገድ ሲጥሰው ቆይቷል። ከዚያ ውስጥ አንዱ ሕገ መንግሥቱ አንድ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ማኅበረሰብ መፍጠር ቢልም እንኳን ኢትዮጵያን አንድ ማድረግ ራሱም አንድ መሆን ተስኖት ቆይቷል።

ሌላ የሚያሳዝነው ነገር ግን፣ መደመር ፍልስፍና ከሆነና ፓርቲው ከተዋሐደ ወደ እልቂት እንገባለን የሚለው ጉዳይ "እልቂትን ምን አመጣው?" ነው። አንድ ፓርቲ መሆንና መደመር የማያዋጣ ከሆነ ጀግና ሰው ውስኪውን አስቀምጦ "መባዛት" የሚል አማራጭ ሐሳብ ይዞ ይመጣል። ያኔ የኢትዮጵያ ሕዝብ መደመር እና መባዛትን ጐን ለጐን ያይና "መደመር አያስፈልገኝም" ይላል። በ21ኛው ክፍለ ዘመን ሐሳብ እያለ ምን ያገዳድለናል? "እኔ ያልኩት ካልሆነ የሚቀጥለው አማራጭ መገዳደል ነው" የሚለው የ19ኛው ክፍለ ዘመን የማርክስ የሌኒን እሳቤ ነው። መደመር እንደዚህ አያምንም። መደመር "ውስኪ ጠጪ ኢሕአዴጐች እባካችሁን ውሃ የናፈቀው ሕዝብ እንዳለ አትርሱ" ይላል።

መደመር ሌብነትን "ቀይ መስመር" ያለበት ምክንያት፤ በስም፣ በአጐት፣ በአክስት በምናምን አዲስ አበባ ላይ ፎቅ መደርደር ብቻ ሳይሆን ዱባይ፣ አውሮፓ፣ አሜሪካ ደርድረህ፤ አንተ ሀገር ውስጥ በ10 ሰው ስም ፎቅ ደርድረህ ቤት አልባውን 50 ሚሊዮን ሕዝብ "አስብልሃለሁ" ብትለው ስላቅ ነው። ሆቴል ተቀምጠህ ከዓመት ዓመት የሆቴል ምግብ እየተመገብክ በአምስት ሺሕ ብር ደመወዝ (ምንጩን እግዚአብሔር ይወቀው) ዳቦ የራበውን ሕዝብ "ለአንተ ቆሜልሀለሁ" ማለት ተረት ተረት ነው። በሰሜን፣ በምዕራብ፣ በምሥራቅ፣ በደቡብ ያላችሁ የተማራችሁ የተሻለ ማገናዘብ የምትችሉ ወጣቶች የምንቀልድባችሁን ቀላጅ ፖለቲከኞች ወደ ጐን አራግፋችሁ አገራችሁን ጠብቁ። በተሰጠው ዕድል መጠቀም ሳይችል ዕድል ሲነጠቅ በትውልድ ዕድል መቀለድ አይቻልም።

“የኢሕአዴግ ፓርቲ እንዴት ይዋሐዳል? ምን ስምና ምን ግብር ይኖረዋል?” የሚለውን እኔ አልወስንም። እኔ ዲሞክራት መሪ ስለሆንኩ ለውይይት ሐሳቤን አቀርባለሁ። የተሻለ ሐሳብ እና የኢሕአዴግ አባል ድርጅቶች ብዙኃን ሐሳብ የሆነውን ግን በቅርቡ ለሕዝባችን እንገልጻለን። መደመር “እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ተስፋ የሚያደርግባት ሀገር ትኑረን” ይላል። ጠቅላይ ሚኒስትር መሆን የማይችል ሶማሌ፤ ጠቅላይ ሚኒስትር መሆን የማይችል አፋር፤ ጠቅላይ ሚኒስትር መሆን የማይችል ቤንሻንጉል እና ጋምቤላ ሳይሆን፣ እያንዳንዱ ዜጋ ሀገሬን ልመራ እችላለሁ ብሎ አስቦ የሚዘጋጅባት፤ ለሁሉም እኩል የሆነች ኢትዮጵያን መፍጠር ያስባል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ለመሆን የታደላችሁ ክልሎች፤ እናንተ በመደብ ክፍፍል ስለምታምኑ አርብቶ አደሩን “አልደረሰም፤ እሱ በጕሳ ይተዳደራል” ስትሉ ኖራችኋል።  ነገር ግን በኦሮሚያና በደቡብ ያለው አርሶ አደር፤ በሶማሌና በአፋር ካለው አርሶ አደር ይበልጣል። መነሻው አርሶ አደር ቢሆን ኖሮ የኦሮሚያና የደቡብ ፓርቲዎችም አብዮታዊ ባልተባሉ ነበር። አግላይነት ከቤት ይጀምራል። እያንዳንዱ በሕዝብ ስም ተወዳድሮ በወረዳው ፓርላማ የተቀመጠ የኢሕአዴግ ሹም ለዚያች ወረዳ አንድ ጉዳጓድ ውሃ ቆፍሮ እንደሆን ያ ወረዳ ይጠይቀዋል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ። የሚቀጥለው ምርጫ የምናላግጥበት ሳይሆን ሐሳብ ይዘን ቀርበን በሐሳብ ተወይይተን የነቃውን 70% የሆነውን ኢትዮጵያዊ ወጣት እንደ አርሶ አደሩ ያልገባውና አንዴ ከአመነ የማይነቃነቅ የሚል ሞኛ ሞኝ ሐሳብ ሳይሆን፤ ተጽፎ፣ ተሰንዶ ይሄ ነው አማራጩ በሚል ዴሞክራሲያዊ መንገድ ብቻ ይሆናል። ኢትዮጵያውያን በፍፁም መገዳደል የለብንም። ሐሳብ ብቻ ነው ማፍለቅ ያለብን፤ በሐሳብ ብቻ ነው መሞገት ያለብን፤ መደመር የተሻለ ሐሳብ ያለውን ለመምረጥና ለመቀበል የኢትዮጵያውያን ጭንቅላት ያንሳል ብሎ በፍፁም  አያምንም። በልዩነት፣ በትብብር፣ በስምምነት ይህቺን ታላቅ ሀገር መልሰን ታላቅ ብቻ ሳትሆን፣ ብልጽግናዋ የሚታይባት ሀገር እናድርጋት ብሎ ያምናል። ደግሞም ያደርጋል።

ብዙዎች የብልጽግና ጉዞ የሚደናቀፍና የሚቆም ይመስላቸዋል። ዛሬም በድጋሜ ላረጋግጥላችሁ የምፈልገው ኢትዮጵያ ትበለጽጋለች። ኢትዮጵያ ካለችበት ሁኔታ ከፍ ትላለች። ኢትዮጵያ እንዳትበለጽግ የሚፈልጉ ይጠፋሉ እንጂ የኢትዮጵያ ብልጽግና አይጠፋም። ባለፉት ዓመታት ድህነትን አብዝተን ስንረግም፣ ስንወቅስ፣ ጠላታችን ስንል ቆይተናል። መደመር ድህነትን አይጠላም። ነገር ግን ብልጽግናን አብዝቶ ይወድዳል። አብዝተን ለምንወደው ብልጽግና ተግተን እንሠራለን። ያ ሥራችን ድህነትን ያጠፋዋል እንጂ ነጋ ጠባ “ድህነት ጠላት ነው” እያልን ከድህነት ጋር ወዳጅ ጓደኞሞች ሆነን 20 ሚሊዮን ሕዝብ ከዚያ በላይ በቀን አንድ ጉርስ እንኳን መጉረስ የማይችል ሕዝብ እንዲኖረን አናደርግም። ብልጽግናን እንናገራለን፤ ብልጽግናን እናውጃለን፤ ብልጽግናን እንሠራለን፤ ብልጽግናን እናረጋግጣለን። ሠላም ሠላም የምንለው ጦርነትን ስለምንፈራ ሳይሆን ሠላምን አብዝተን ስለምንወድድ ነው። ጦርነት ጥፋት ነው። በኢትዮጵያ ውስጥ “ተነሡ እንዋጋ” ካልን በኋላ የሞተውን የመቁጠርና የመናገር ልምድ ስለሌለን ነው እንጂ፣ ከወንድም የኤርትራ ሕዝብ ጋር ተጣልተን ያጠፋነው ሕይወት ራሱ በታሪክ ውስጥ ከፍተኛ ቁስል ነው። ተጨማሪ ግድያ፣ ተጨማሪ ቁስል አያስፈልግም። ተጨማሪ ሐሳብ ብቻ ነው የሚያስፈልገው።

የኤርትራ መንግሥትና የኤርትራ ሕዝብ ለኢትዮጵያ ስጋት አይደሉም። ተስፋ ናቸው። የኤርትራ መንግሥትና የኤርትራ ሕዝብ ወንድም ሕዝብ ነው። በእምነቱ፣ በቋንቋው፣ በአሳቤው፣ በብዙ ነገሩ ከእኛ ጋር የሚመሳሰል ወንድም ሕዝብ እንጂ ጠላት ሕዝብ አይደለም። ወንድም ወንድሙን ያኮርፋል እንጂ እስከ ወዲያኛው ጠላቴ ስለማይለው ከወንድሞቻችን ጋር የጀመርነውን ዕርቅ ወደ ብልጽግና እናሸጋግራለን እንጂ ወደ ኋላ አንመልስም።

በመጨረሻም ዛሬ ይህ ፕሮግራም ሲዘጋጅ ቀደም ሲል የተያዘ ፕሮግራም የነበራችሁ፤ ኤግዚቢሽን ተይዞ ያበላሸንባችሁን ወንድም እኅቶቻችንን በታላቅ ትሕትና ይቅርታ ልጠይቃችሁ እፈልጋለሁ። የእኛ መደመር የእናንተን ጉዳይ እንዲያበላሽ ሳይሆን፣ ለእናንተ ዐውድ ለመፍጠር ነውና ስለተፈጠረው የፕሮግራም ስሕተት ከፍ ያለ ይቅርታ እጠይቃለሁ?

በመጨረሻም ዛሬ ይህንን ፕሮግራም ያዘጋጃችሁ፤ መደመር መደመር ሆኖ እንዲወጣ ብዙ ያገዛችሁ፤ በጣም ታላላቅ ጸሐፊዎችና ደራሲዎች፤ እዚህ መጥታችሁ መደመርን በሚያስደንቅ መንገድ የተረካችሁ፤ የጻፈው እስኪመስል ድረስ አራቱን የመደመር አንጓዎች በዝርዝር የተነተነውን ሌንጮ ባቲን፣ እንዲሁም ሥርጸንና የብሔራዊ ቴአትር ወንድምና እኅቶቻችንን እጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ!

ይሄን ሁሉ ከአልኩ በኋላ ማምዬ ስለአደረግሽው ሁሉ እግዚአብሔር ብድራቱን ይክፈልሽ! ዛሬ የሆነው መደመርም ቦታውን የሚይዘው፣ ብልጽግናም የሚመጣው የኢትዮጵያ አምላክ ኢትዮጵያን ስለማይጥል ነውና ስላደረገው ሁሉ ምስጋና ይገባዋል! በተደጋጋሚ “ፈጣሪ” ስንል ሰዎች ይገረማሉ። እኛ በማርክስና በሌኒን የእውር አስተሳሰብ የታጠብን ስለአልሆንን የፈጣሪን ልዕልና የምናምን መሆናችንን፤ በዚያም የማናፍር መሆናችንን፤ 99% አማኝ ያለበት ሀገር መሪ ሆኖ እምነትን ማራከስ ሕዝብን አለማወቅ ስለ ሆነ፤

**ፈጣሪ ዛሬም ኢትዮጵያንና ሕዝቦቿን አብዝቶ ይባርክ!**

**አመሰግናለሁ!**





# የ“ሰላም መቶ በመቶ ያሸልማል” መርሐ ግብር ንግግር

ጥቅምት 9/2012 ዓ.ም.

**ክብርት ፕሬዝዳንት፤**
**ኤክሰለንሲ ሙሳ ፋኪ ማህማት፤ የአፍሪካ ሕብረት ሊቀመንበር፤**
**እጅግ የተከበራችሁ የዚህ ሥነ ሥርዓት ታዳሚዎች፤**

የተባለውን በሙሉ ሰምቻለሁ። እንደዚህ ዓይነት ስምና ክብር የሚገባው ለእኔ ነው ብዬ በፍፁም አላምንም። ክብሩን ሁሉ እግዚአብሔር ይውሰድ!

በመቀጠልም እጅግ የተወደዱ ወንድሜ የኤርትራዉ ፕሬዝዳንት ኢሳይያስ አፈወርቂ በሐሳብ ከእኛ ጋር እንዳሉ በማሰብ፣ ይህ ክብርና ምስጋና ለእርሳቸውም ይድረሳቸው። ምናልባት የሰላም ሚኒስቴር እና እዚህ ያላችሁ

ሰዎች እንደምትፈቅዱልኝ በማመን በብዙ መከራ፣ በብዙ ችግር፣ በብዙ ድህነት አብረውኝ ለነበሩ ወንድሞቼ፣ ጓደኞቼ እና የእነርሱ ሁሉ አስተባባሪ እና መሪ ለነበረው የድህነት ጓደኛዬ እና ወንድሜ ለማ መገርሳ የዚህ ክብር ባለቤት እና መሪ ስለ ሆነ የዛሬውን ሽልማቴን ኢትዮጵያን እንድሸልመው ፍቀዱልኝ።

ብዙ ለመናገር ዐቅም ስለ ሌለኝ፣ ዛሬ ግን ሕፃናት አዳጊዎች እንዳይሳሳቱ፤ በሰሙት ባዩት ነገር እንዳይሳሳቱ፤ ለእነርሱ መልእክት አለኝ። እዚህ ከፊታችሁ ቆሞ ዕጣ የወደቀበት ሰውዬ እስከ ሰባተኛ ክፍል ድረስ አንድም ቀን አልጋ ላይ ተኝቶ የማያውቅ በመደብ ላይ ያደገ የድሃ ልጅ ነው። እኔ ሰባተኛ ክፍል እስከደረስኩበት ጊዜ ድረስ ሁልጊዜም የምተኛው መደብ ላይ ነበር። ከሰኞ እስከ ዓርብ ከተማርን በኋላ ዓርብ ዓርብ ከዕረፍት በኋላ እስከ ስድስት ሰዓት የእኛን ትምህርት ቤት ጭቃ ለቅልቀን ነበር የምንሄደው። ቅዳሜና እሑድ ደርቆ ሰኞ ስንመጣ እንድንማርበት፤ ቁንጫ ስለሚያስቸግር ማለት ነው። ከዚያ በኋላ ያሳለፍኩት ሕይወት የሚታወቅ ሲሆን በልጅነት አእምሮዬ መደብ ላይ ከመተኛቴ በፊት ተንበርክካ የምትጸልይልኝ፣ የምታበረታኝ፣ ሁሉም የሆነው እንደሚሆን በየቀኑ እየነገረች ያሳደገችኝን እናቴን ማመስገን እፈልጋለሁ።

በውትድርና ዓለም ውስጥ እኔና ባለቤቴ ስንገናኝ እኔ መቶ አለቃ እሷ ዓሥር አለቃ ነበረች። እርሷም እዚህ ስላለች በርግጠኝነት እነግራችኋለሁ። እኔና ባለቤቴ ስንጋባ ፍራሽ አልነበረንም። ሣር ጐዝጉዘን አንሶላ በመሸፈን ነበር የምንተኛው። ውዷ ባለቤቴ ጀግና የእናቴ ምትክ ስለ ሆነች፣ እርሷንም ማመስገን እፈልጋለሁ! መላው የኢትዮጵያ አዳጊዎች እጅግ ድሃ ብዙ የማያውቅ፤ ይህ ሁሉ ክብር የማይገባው ሰው እንዲህ ሆኖ መከበር የሚችል ከሆነ፤ እናንተ ከእርሱ የተሻለ ዕድል ያላችሁ ሰዎች፣ ከእርሱ የተሻለ ጊዜ ላይ ያላችሁ ሰዎች፣ ብዙ ኑሮ ስለምትችሉ ለመከበር መጀመሪያ ሁሉ ነገር ይሟላ ሳትሉ፣ በችግር ውስጥ ብትሆኑም ትልቅ እያለማችሁ በፊዚክስ፣ በኬሚስትሪ፣ እነ ሎሬት ፀጋዬን የመሳሰሉ ድንቅ ድንቅ ጸሐፊያን ተፈጥረው ኢትዮጵያ ስሟ





እንደ ተጠራ ሁሉ፤ በዚያ መስክም ስሟ እንዲጠራ ተግታችሁ እንድትሠሩ በታላቅ ትሕትና ላሳስባችሁ እፈልጋለሁ።

የሀይማኖት አባቶች ሆይ፤ ፕሬዝዳንት ኢሳይያስ በምንገናኝበት ጊዜ ሁሉ አንድ ነገር ሲናገሩ እሰማቸዋለሁ። በመቀሌ ጐዳና ላይ በእግራቸው መጓዝ ይፈልጋሉ። የትግራይ እናቶችና አባቶች ማንም እንግዳ ሲመጣ ነጭ ለብሰው፣ ዘንባባ ይዘው፣ ፈንዲሻ እየረጩ በፍቅር ሰው መቀበል ያውቁበታል። የፕሬዝዳንት ኢሳይያስ በመቀሌ ከተማ በእኛ ሁሉ አጃቢነት በእግራቸው እየተራመዱ ከሚወዱት ሕዝባቸው ጋር የመገናኘት ጥማቸው እንዲሳካ፣ በጸሎታችሁ እንድታግዙን አደራ ልላችሁ እፈልጋለሁ።

ለኢትዮጵያ ሰላም! ለአፍሪካ ሰላም! ይህ ግን እውን እንዲሆን እያንዳንዳችን በውስጣችን ሰላም ይኑረን። በውስጥ ሰላም ከሌለ ወደ ውጭ የሚወጣ ሰላም የለም። የውስጥ ሰላም በጣም አስፈላጊ ነው። ውስጡ ሰላም የሆነ ሰው ከመሬት ተነሥቶ የሚደባደብ፤ ከመሬት ተነሥቶ የሚሳደብ፤ ከመሬት ተነሥቶ የሚጣላ አይሆንም። በመጣላት መግደል ይቻል ይሆናል እንጂ ማሸነፍ አይቻልም። ለማሸነፍ ዝቅ ማለት፤ ለማሸነፍ መውደድ፤ ለማሸነፍ ይቅር ማለት፤ ለማሸነፍ እግዚአብሔርን መፍራትና ማመን ያስፈልጋል።

## አመሰግናለሁ!

# የብልጽግና ፓርቲን አቋምና ምኞት የሚገልጥ ንግግር

ኅዳር 18/2012 ዓ.ም.

**ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብና ለብልጽግና ፓርቲ አባላት በሙሉ፤**

የብልጽግና ፓርቲን የመመሥረት ሂደት በምሁራን ሲጠና ቆይቶ በየደረጃው ሁሉም አመራሮች እንደተወያዩበት ይታወሳል። በትናንትናው ዕለት የኦዲፒ እና የአዴፓ አስቸኳይ ጉባኤዎች በሙሉ ድምፅ ያጸደቁት ሲሆን፤ በዛሬው ዕለት የደኢሕዴን አስቸኳይ ጉባኤ እንደሚያጸድቀው ይጠበቃል። ይህ የፓርቲው ምሥረታ ሁሉንም ሕጋዊ መሠረት የያዘና ሕግን ተከትሎ የተፈፀመ መሆኑን ስገልጽላችሁ በታላቅ ደስታ ነው።





ሁለተኛው፤ የብልጽግና ፓርቲ ፕሮግራሙን ያሻሻለ፤ ለሚቀጥሉት ዓሥር ዓመታት ኢትዮጵያን ወደ ብልጽግና ጎዳና የሚወስደውን ዕቅድ የነደፈ፤ ይህንንም ከመላው ሕዝብና አባላት ጋር የሚወያይበትና የሚያዳብረው፤ ኢትዮጵያን ወደ ብልጽግና የመውሰድ ሕልማችንን እውን የምናደርግበት ትክክለኛው መንገድ የተጀመረ መሆኑን ሳበስር በታላቅ ደስታ ነው።

ከዚህ ጋር ተያይዞ አንዳንድ ኃይሎች "ይህ አዲሱ የብልጽግና ፓርቲ አሐዳዊ ሥርዓትን የሚያመጣ፤ የፌዴራል ሥርዓትን የሚያጠፋ ነው" የሚል አሉባልታ ሲነገሩ ይደመጣል። ይሁንና በፕሮግራማችን ላይ በግልጽ እንደአስቀመጥነው የብልጽግና ፓርቲ ኅብረ ብሔራዊት፣ ፌዴራላዊት፣ ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን የሚያጠናክር፤ የሚገነባ እንጂ የማያፈርስ መሆኑን በንግግር ብቻ ሳይሆን በፕሮግራማችንም ጭምር ያካተትነው መሆኑን እየገለጽኩ፤ ሌሎች ፓርቲዎች ብልጽግናን በመክሰስ ሳይሆን አማራጭ ሐሳብ በማምጣት እንዲሞግቱንና ለኢትዮጵያ ሕዝብ አማራጭ ሐሳብ ይዘው እንዲቀርቡ በዚሁ አጋጣሚ ጥሪዬን ላቀርብላቸው እፈልጋለሁ። የብልጽግና ፓርቲ መሠረቱ በኦሮሚያ ክልል የቄሮ ትግል፤ በአማራ ክልል የፋኖ ትግል፤ በደቡብ ዘርማና ሌሎች ወጣት አደረጃጀቶች በጋራ ያደረጉት ትግል፤ ከተረት ተረት ወደ እውነታኛ ብልጽግናና ሰላም፤ ዴሞክራሲያዊና አንድነት ለማሸጋገር የተደረገ ሂደት መሆኑ ታምኖ ቄሮዎች፣ ፋኖዎች እንኳን ደስ አላችሁ! የታገላችሁለት ፓርቲያችሁ ተመሥርቷል። ከፓርቲያችሁ ጋር ሆናችሁ ስታነሡት የነበረውን ጥያቄ ተግባራዊ እንዲሆን አስፈላጊውን ጥረት እንድታደርጉ ጥሪዬን ላቀርብላችሁ እፈልጋለሁ። ከዚሁ ጋር ተያይዞ ድርጅታችን የፋኖንና የቄሮን ትግል የሚዘክር የተግባር ማስታወሻ እንደሚያስቀምጥ ሳበሥርላችሁ በታላቅ ደስታ ነው።

እንዲሁም የብልጽግና ፓርቲ ሥራ አስፈፃሚ አባላት በሰሞኑ በአደረጉት ውይይት ኢትዮጵያ ውስጥ የሕግ ልዕልናን የማረጋገጥና ሕግ የማስከበር ጉዳይ ዋነኛ አጀንዳ ሆኖ ተነሥቷል። ከእንግዲህ በኋላ በኢትዮጵያ ውስጥ ማንኛውም ሰው ሐሳብ ካለው በሐሳብ ገበያ ውስጥ አሳምኖ ሥልጣን ከመያዝ ውጭ በኃይል እና ትክክል በአልሆነ መንገድ የሕዝብን ሰላም የሚያውክ ከሆነ መንግሥት ሕጋዊ እርምጃ በመውሰድ የሕግ ልዕልናን እንደሚያረጋግጥ ፓርቲያችን ለሕግ ልዕልና አበክሮ እንደሚሠራ የተግባባን መሆናችንን ልገልጽላችሁ እወዳለሁ።

መላ የኢትዮጵያ ሕዝቦች የብልጽግና ፓርቲ ያለብንን ድህነት፣ ያለብንን የዲሞክራሲያው እጥረት፣ ያለብንን የሰላም ችግር በመፍታት፤ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ሥራ እንዲያገኝ፣ በልቶ እንዲያድር፣ በሰላም ወጥቶ እንዲገባ የሚተጋ ፓርቲ ነው። ይህንንም በፕሮግራማችን ላይ በግልጽ ያሰፈርን መሆኑን አውቃችሁ ሌሎች ከእኛ የሚቃረኑ ኃይሎች ከአሉ፤ አማራጭ ሐሳብ እያቀረቡ በሐሳብ ልዕልና ብቻ ማሸነፍ የሚችሉበት እና ሰላማዊ መንገድ የሚከተሉበትን መንገድ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከብልጽግና ፓርቲ ጋር በመሆን እንዲያረጋግጥ ጥሪዬን አቀርባለሁ። የብልጽግና ፓርቲ ለሰላም፤ የብልጽግና ፓርቲ ለእኩልነት፤ የብልጽግና ፓርቲ ለነፃነት፤ የብልጽግና ፓርቲ ለእውነተኛ የፌዴራል ሥርዓት፤ የብልጽግና ፓርቲ ለእያንዳንዱ ዜጋ በልቶ የማደርና ወጥቶ የመግባት ሰላምን የማረጋገጥ ተግባር ለመፈፀም ታጥቆ የተነሣ፤ ሙሉ ዝግጅት ያደረገ፤ ግልጽ ፕሮግራም ያለው መፃኢውን የኢትዮጵያ አቅጣጫ የነደፈ መሆኑን አውቃችሁ ከጐናችን በመሆን የኢትዮጵያን ብልጽግና እውን እንድታደርጉ በታላቅ ትሕትና እጠይቃለሁ!

**አመሰግናለሁ!**



# የብልጽግና ፓርቲ ውሕደት ሥነ ሥርዓት ንግግር

ኅዳር 21/2012 ዓ.ም.

በመጀመሪያ ለዚህ ታሪካዊ ቀን ስለ በቃችሁ፤ ስለ በቃን እንኳን ደስ አላችሁ! ማለት እፈልጋለሁ። ብልጽግና በእውነት እና በዕውቀት ላይ ተንተርሶ ኢትዮጵያን ካለችበት ሁኔታ የሚያሸጋግራት ጠንካራ፣ አስተማማኝ፣ በፍቅር የደረጀ ድልድይ ነው። የብልጽግና መለያ እውነት፤ የብልጽግና መለያ ዕውቀት ነው። በጭንቅላታችን እናስባለን። በልባችን እንገናኛለን። ባለን ዐቅም ሁሉ እንሠራለን። ኢትዮጵያን ታሪኳንና ደኅንነቷን ለመቀየር ለሕዝቦቿ ተስፋ የምትሆን፤ ለመኖር የምታጓጓ፤ ሁሉም ዜጋ ደስተኛ የሚሆንባት አገር አድርጎ ለመፍጠር በእውነት እና በዕውቀት ላይ እንሠራለን። በስሜት እና በምኞት የሚዋልሉ ኃይሎች በእውነት እና በዕውቀት ካለን ፍላጎት ጋር የተለያየ ሐሳብ ሊያቀርቡ ይችላሉ። ብልጽግናዎች እውነትን እና ዕውቀትን መያዝ፤ ምኞትን እና ስሜትን መቀነስ ይጠበቅብናል። ስሜት ካልተገራ፣ ምኞት በጥረት፣ በስኬት የሚከወን ከአልሆነ ባዶ ተስፋ ይሆናል። ብልጽግናዎች በኢትዮጵያ ፖለቲካ

ውስጥ ከፍተኛ ችግር እየፈጠረ ያለውን ባዶ ምኞት እና ያልተገራ ስሜት እንጠየፈዋለን። በዕውቀት እና በእውነት ላይ ብቻ ተንተርሰን ሀገራችንን ለማሸጋገር ድልድይ የሆነ ፓርቲ እንደምንሆን ዛሬ በድጋሚ እዚህ ለአላችሁ የብልጽግና አመራሮች እና ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ በከፍተኛ ደስታ ልገልጽ እፈልጋለሁ።

የታገልንበት ድርጅት በርካታ ደካማና ጠንካራ ጎኖች አሉት። በአለፉት ጥቂት ዓመታት ሁላችሁም እንደምትታዘቡት ኢሕአዴግ መታመም ብቻ ሳይሆን በኮማ ያለ ድርጅት ነው። ይህ የታመመው ድርጅት በዕንቁላል ሲመሰል በውስጡ ጠንካራ ራእይ ያላቸው ሰዎች ዕንቁላሉን በወጉ ከሰበሩ ሕይወት ሊያወጡ እንደሚችሉ፤ ዕንቁላሉ መሰበር ከአልቻለ ግን ሊከረፋ፣ ሊገማ እና ሕይወት ሊያጣ ስለሚችል፤ ብልጽግና ኢሕአዴግ ውስጥ ዕንቁላሉን ሰብሮ ሕይወት እንዲወጣ ስለአደረገ ከፍተኛ ኩራት እና ደስታ ሊሰማችሁ ይገባል። ዕንቁላሉን በጊዜው ባንሰብረው ኖሮ አንዳንዶች እንደሚሉት ብንዘገይ ኖሮ ኢሕአዴግ ሕይወት ሊወጣው በፍፁም አይቻለውም። ሕይወት ኖሮት ይህችን አገር ተሸክሞ ማሻገር እንዲችል ዘመኑን የሚመጥን ብቃት፣ ዘመኑን የሚመጥን ራእይ እና አደረጃጀት ያስፈልገው ነበር።

ዛሬ ይህ ያልገባቸው ግለሰቦች እና ቡድኖች ቢኖሩም ነገ በኢትዮጵያ ብልጽግና ላይ ቆመን ወደ ኋላ ስንመለከት ይህ ውሳኔ በዕውቀት እና በእውነት ላይ የተመሠረተ፤ ይችን ታሪካዊ ድንቅ አገር ወደሚገባት ቦታ የሚያደርስ መሆኑን ሁሉም የሚያምነው እና ብዙው ደግሞ የሚያየው ይሆናል። ብልጽግና ዲሞክራሲን እና ልማትን ደምሮ የያዘ ፓርቲ ነው። ብልጽግና ስንል ሆድ መሙላትን ብቻ ሳይሆን የአእምሮ ነፃነትን እኩል ቦታ እንሰጠዋለን። በብልጽግና በልቶ ማደር፤ በብልጽግና በነፃነት ማሰብ እና መናገር፤ በብልጽግና ያሻን ቦታ መሄድ፤ ያልታሰረ እግር፤ ያልታሰረ ማንነት፤ ያልተቆለፈ አንደበት፤ እንዲሁም ተግቶ ለፍቶ በጥረት የሚያገኝ፤ በአገኘውም የሚኖር ዜጋ





የመፍጠር ዓላማ የያዘ ነው። ብልጥግና "መንገድ ሠርተንልሀልና ይበቃሀል። ጤና ጣቢያ ተሠርቶልሀልና ይበቃሀል" ብሎ አያምንም። መንገድ ያስፈልጋል። ውሃ ያስፈልጋል። ትምህርት ቤት ያስፈልጋል። ደግሞም የአእምሮ ነፃነት እና ሰው በአገሩ የሚኮራ፤ በአገሩ ደስተኛ ሆኖ ያሻውን የሚሰማውን የሚገልጽበት ነፃነት ያስፈልገዋል፤ ብሎ በጽኑ ያምናል።

ይህ ብቻ ሳይሆን፤ በሕዝቦች መካከል እኩልነት ያስፈልጋል ብሎ በጽኑ ያምናል። 'ብልጽግና በዕውቀት እና በእውነት ላይ የተመሠረተ ነው' ሲባል እንዲሁ የሚነገር ሳይሆን ሁላችሁም እንደምትመለከቱት ግልፕ ያለ፤ ሁሉም የኢትዮጵያ ሕዝቦች በእኩልነት የሚጠቀሙበት፤ በብዙ ጭንቀት፤ በብዙ ምክክር፤ በብዙ ውይይት የተሠራ ግልፅ ፕሮግራም አለው። ይህ ፕሮግራም የሚደበቅና የሚሸፈን ሳይሆን፤ ለመላው አባላችን፤ ለሕዝባችን በግልፅ የሚሰራጭ እና ሕዝብ እና አባሎቻችን ተወያይተውበት የሚያዳብሩት፤ የሚያበለጽጉት፤ የሚታገሉለት፤ የሚጠብቁት ይሆናል።

ብልጽግና ፕሮግራም ብቻ ሳይሆን የሚመራበት ሕገ ደንብም አለው። በሕግ እና በዕውቀት የሚመራ፤ በእውነት ላይ የቆመ ድርጅት እንጂ እንዲሁ ግለሰቦች ስለ ፈለጉ ተሰባስበው የፈጠሩት ድርጅት አይደለም። ግልፅ ፕሮግራም እና ሕገ ደንብ ብቻ ሳይሆን ለሚቀጥሉት 10 ዓመታት ኢትዮጵያን ከአለችበት ሁኔታ ወደ ብልጽግና ጎዳና የሚያሸጋግር የ10 ዓመት ዕቅድ በግልጽ ቋንቋ በርካቶችን አወያይቶ ያዘጋጀ ድርጅት ነው።

በኢትዮጵያ ውስጥ የሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ኃይሎች ይህንን ለኢትዮጵያ ድልድይ ሆኖ የሚያሻግር ፓርቲ ሲገመግሙ፣ ሲተቹ፣ ሲደግፉ አንድ እንዲገነዘቡት የምፈልገው ነገር ብልጽግና አንዱ የመታገያ መርሑ ተግባራዊ እውነታ መሆኑ ነው። በእውነተኛ ተግባር የሚያምን ነው። በማንኛውም ሰዓት ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ትችት ቢቀርብብን ለመማር ዝግጁዎች ነን።

በማንኛውም ሰዓት ጠቃሚ ሐሳብ፤ ለሕዝቦቻችን የሚበጅ ሐሳብ ከመጣ በፕሮግራማችን ውስጥ ለማካተት፤ ለመማር ዝግጁዎች ነን። እኛን መተቸት ብቻውን በቂ አይደለም። ይኽችን አገር ከአለችበት ጭንቀት የሚያሻግር አማራጭ ሐሳብ ማቅረብ የግድ ይጠይቃል። እኛ የነበርንበት ፕሮግራም፤ የነበርንበት አደረጃጀት ኢትዮጵያን ከአለችበት ሁኔታ እንደማያሻግር በማመን ግልፅ ፍልስፍና፣ ፕሮግራም፣ ሕገ ደንብ፤ እንዲሁም ለሚቀጥሉት 10 ዓመታት ሀገራችን እና ሕዝቦቿ የሚመሩበት እና ወደ ብልጽግና ጎዳና የሚሸጋገሩበት ዝርዝር ዕቅድ አዘጋጅተናል። አማራጭ ሐሳብ አለኝ ብሎ፣ ራሱን ከምኞት እና ከስሜት አርቆ፣ ሐሳብ ይዞ የሚመጣ ኃይል ከአለ ለመማር ለማሻሻል ዝግጁ መሆናችንን በዚሁ አጋጣሚ ለመግለጽ እፈልጋለሁ።

ብልጽግና ከአብዮታዊ ዲሞክራሲ ዓላማ የሚለየው አንዱ፤ አብዮታዊ ዲሞክራሲ በግልፅ በፕሮግራሞቹ እንደአስቀመጠው "የኔ ዓላማ አይተኬ ነው" ይላል። የብልጽግና ፕሮግራም አይተኬ ነው ብሎ አያስብም። ከአሉት የተሻለ፤ ከዚህ የሚሻል ሐሳብ ከመጣ ለመማር ዝግጁ የሆነ፤ ለሕዝባችን ብናቀርብ የሚሻለው አማራጭ ሐሳብ እንጂ አማራጭ ስሜት እና አማራጭ ምኞት እንዳይሆን አበክሮ የሚያምን ድርጅት ነው።

መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ እና የብልጽግና ፓርቲ አባላት ነገን ማመን ይኖርብናል። ከሁለት ምዕተ ዓመት በፊት የዩናይትድ ኪንግደም ወይም የብሪታኒያ ሕዝብ እና መንግሥት በነገ ላይ በነበረው እምነት ለኢንዱስትሪ ጉልበቱን፣ ሀብቱን፣ ዕውቀቱን በመጠቀም በዘመኑ የማይታወቀውን የኢንዱስትሪያል አብዮት በማካሄድ ለሀገሩ፣ ለአውሮፓ፣ እንዲሁም ለዓለም ፈር ቀዳጅ የሆነ ዕድገት ማረጋገጥ ችሏል። አሜሪካኖች ዕድገቱን ከእንግሊዝ ሲቀበሉ የእንግሊዝን ኢንዱስትሪያል አብዮት አልደገሙም። ነገር ግን በወቅቱ እምብዛም የማይታወቀውን ኤሌክትሪሲቲ እና በዚህ ደሞ ዘመን አይ.ቲ ማንም ሳያምን፤ ማንም ሳይቀበል ሀብታቸውን፣ ዕውቀታቸውን ነገን በማመን ስላፈሰሱ አሜሪካውያን የበለጸጉ እና የዐደጉ ከራሳቸው አልፈው ሌሎችን የሚያግዙ መሆን ችለዋል። እኛ ኢትዮጵያውያን ነገን በማመን ተስፋ በመሰነቅ ለመበልጸግ የማንተጋ ከሆነ፤ ነገን የምንጠራጠር ከሆነ ሌሊቱ አይነጋም። ብልጽግና ነገን በማመን፤ ጭለማው እንደሚነጋ በማመን የሚተጋ ድርጅት ነው። ነገር ግን ብልጽግና እጃችን ሳይቆሽሽ፤ እንቅልፍ ሳናጣ፤ አእምሮአችን ሳይደክም እንዲሁ በምኞት የሚተገበር ባለመሆኑ ከሁላችን ተግቶ መሥራት፤ ሌብነትን መጠየፍ፤ ለራስ ማካበት ሳይሆን በጋራ አገርን ማሸጋገርን እንደ ትልቅ ዓላማ መያዝ ይኖርብናል።

ብዙዎች ብልጽግናን የሚቃወሙት እና የሚጠሉት በግልፅ ቋንቋ "ሌብነት ጥዩፍ ነው፤ የማይሠራ የማይተጋ ሰነፍ ከእኛ ጋር መቀጠል አይችልም" የሚል በጽሑፍ የተቀመጠ፣ ሐሳባችን ሰነፎችን የሚያስፈራ እና የሚያስጠነቅቅ ስለሆነ ነው። በመትጋት በመሥራት መለወጥ ለሚያስቡ ግን ተስፋ የሚሆን ድርጅት ነው። መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ቢያንስ ከውሻ የተሻለ እምነት እና ማንነት መያዝ ይኖርበታል። ውሾች ለመብላት አጥንት ላይ ይራኮታሉ፤ ይጣላሉ፤ ይጯጯሀሉ። ነገር ግን ጅብ ከመጣ፤ የጋራ ጠላት ከመጣ አጥንቱን ጥለው ሁሉም በጋራ በመሆን ወደ ጅቡ ያተኩራሉ። አሁን እርስ በርስ የሚያባላን፤ እርስ በርስ የሚያጨቃጭቀን ነገር ከውጭ ሊበላን ከሚሻው ጠላት አንፃር ሲታይ ምንም አይደለም። እናም በተባበረ ክንድ፤ በተስማማ ማንነት አንድ ሆነን፤ ይቺን አገር ከታሪኳና ከስሟ በላይ ሆና ለልጆቻችን ማስረከብ እንድንችል፤ በጋራ ብንተጋ ሌሎች ከእኛ የሚማሩ፤ እኛም በታሪክ ውስጥ ደማቅ ማንነት እና ስም ይዘን የምናልፍ እንሆናለን።

መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ እንደሚገነዘበው ፖለቲካ ይመጣል፤ ፖለቲካ ይሄዳል። ድርጅት ይመጣል፤ ድርጅት ይሄዳል። መንግሥት ይመጣል፤ መንግሥት ይሄዳል። ነገር ግን እውነት ሁሌም አይዛነፍም። በታሪክ ውስጥ የማይናወጥ ሆኖ ይቆማል። ብልጽግና ፌደራሊዝምን የሚያጠናክር፤ የሁሉንም

ሕዝቦች እኩልነት የሚያጠናክር እንጂ ፕሮግራማችንን ሳያዩ እንደሚሉት ፌደራሊዝምን የሚያጠፋ አይደለም። በሴቶች እኩልነት እና ወደ ሥልጣን መምጣት የሚያምን፤ በሁሉም ሕዝቦች እኩልነት እና ተሳትፎ የሚያምን፤ ለሁሉም ሕዝቦች ክብር የሚሰጥ፤ ለሁሉም ቋንቋዎች ክብር የሚሰጥ፤ ከአባባል እና ከንግግር የዘለለ እውነተኛ ኢትዮጵያን እና ኢትዮጵያውያንን ተሸክሞ የሚያሻግር ድልድይ መሆኑን ተገንዝበን፤ በመትጋት፣ በመሥራት ይህቺን ታላቅ አገር እንደስሟ ማድረግ እንድንችል መላው የብልጽግና ፓርቲ አባላት ከዚህ ቀደም ከነበረው በላይ በተባበረ ክንድ፣ በተስማማ ማንነት፣ ፕሮግራማችንን በማንበብ፤ ሕገ ደንባችንን በማንበብ፤ አጠቃላይ ፍልስፍናችንን በማወቅ በወንድማማችነት እና በተከባበረ ስሜት፤ በዕውቀት እና በጥበብ ይህቺን አገር እንድናሽጋግር ጥሪ አቀርባለሁ። በዚህም ኢትዮጵያን ከመበልጸግ፤ ብልጽግናንም ድልድይ ሆኖ ከማሻገር የሚያቆም አንዳች ኃይል እንደ ሌለ በድጋሚ ላረጋግጥላችሁ እፈልጋለሁ።

የያዝነው በእውነት እና በዕውቀት መትጋት በምድርም በሰማይም የተደገፈ በመሆኑ ሁሉንም ሕዝቦች ይዘን ኢትዮጵያን እናሻግራለን። ሌሎች የፖለቲካ ድርጅቶች የእኛን ፕሮግራም እና ሕገ ደንብ በማንበብ ግብአት እንድትሰጡ፤ ምናልባት የእኛ ፕሮግራም ኢትዮጵያን የሚያሻግር መሆኑን ከአመናችሁ እና ጥያቄ ከአቀረባችሁ አሁን አገር መምራት ላይ ከአለን ድርጅቶች በተጨማሪ ሌሎች ድርጅቶች ከእኛ ጋር በመሆን ለመታገል ፍላጎቱ ካላቸው እንደከዚህ ቀደሙ በራችን ዝግ ያልሆነ መሆኑን እና በመደራደር ማንም ድርጅት ከእኛ ጋር ሆኖ ኢትዮጵያን እንዲያሻግር ፍላጎት ያለን መሆኑን በዚህ አጋጣሚ አረጋግጣለሁ። ሌሎች የፖለቲካ ድርጅቶች ከእኛ በመማር ሰብሰብ፣ ጠንከር ማለት እና የሐሳብ እና የድርጅት ቁመናችሁን በማጠናከርና ግልፅ አቋም በመያዝ ለኢትዮጵያ ዲሞክራሲ እና ብልጽግና የበኩላችሁን እንድትወጡ አደራ እያልኩ፤ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ እስከ አሁን ከነበርንበት ሁኔታ ቢቆይ ከሚበሰብሰው ዕንቁላል ተሰብሮ የወጣው ብልጽግና በትክክለኛ መንገድ፤ በትክክለኛ ማንነት ኢትዮጵያ እና ሕዝቦቿን የሚያሻግር መሆኑን በታላቅ አክብሮት እገልጻለሁ።

በጋራ ዲሞክራሲን እንገንባ፤ ሰላምን እናምጣ፤ ፍትሕን እናረጋግጥ፤ እኩልነት እና ነፃነት በኢትዮጵያ የሚታዩ አርማዎች ይሁኑ፤ ብልጽግና በተሟላ መንገድ በእያንዳንዱ ግለሰብ እና ሕዝብ የሚታይ ኢትዮጵያ ስሟ ከፍ ብሎ የሚነገር እንዲሆን በጋራ እንትጋ ማለት እፈልጋለሁ።

## አመሰግናለሁ!

# ከኖቤል ሽልማት መልስ የተደረገው አቀባበል ንግግር

ታኅሣሥ 2/2012 ዓ.ም.

**ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ፣**
**እንዲሁም ለኤርትራ ሕዝብ፤**
**ለክቡር ፕሬዚዳንት ኢሳይያስ አፈወርቂ**
**እና ለኢትዮጵያ ወዳጆች፤**

እንኳን ደስ አላችሁ! እንኳን ደስ አለን! ማለት እፈልጋለሁ። ዛሬ ለኢትዮጵያና ለኤርትራ እንዲሁም ለምሥራቅ አፍሪካ በዓለም ደረጃ ከፍተኛ ዕውቅና ያገኘንበት ዕለት ሲሆን፤ እናንተን ሁላችሁንም በመወከል በዚያ ስፍራ ተገኝቼ ለኢትዮጵያ፤ ለኤርትራ እና ለምሥራቅ አፍሪካ ያለው እሳቤ ከዚህ ቀደም ከነበረው በተለየ መንገድ ትኩረት እንዲያገኝና ሀገራት በዚህም አካባቢ ታሪክ ሊሠራ እንደሚችል ማሰብ እንዲችሉ የማስታወስ ሥራ ለመሥራት ዕድል አግኝቻለሁ። ሁላችሁም እንደምትገነዘቡት የኖቬል ኮሚቴው የሚያውቀውን የሚያየውን ጠርቶ የሸለመ ቢሆንም፣ ይህ ሽልማት እውን እንዲሆን ብዙ እናቶች በዱዳ ያለቀሱ የጸለዩ የተጨነቁ ያማጡ እንዳሉ በውል ይታወቃል።

በመሆኑም ሁላችሁን ወክዬ ሽልማቱን የተቀበልኩት እኔ ብሆንም ሽልማቱ ለኢትዮጵያና ለኤርትራ፤ ለፕሬዝዳንት ኢሳያስና ለእኔ፤ እንዲሁም ለተቀሩት ለኢትዮጵያና ለኤርትራ ወዳጆች ሁሉ የተሰጠ በመሆኑ፣ እንደ መልካም ዕድል በመጠቀም ሌሎች ችግሮቻችንን ለመፍታት እንደ መነሻ አድርገን የምንገለገልበት ቢሆን መልካም ነው። መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዲገነዘብ የምፈልገው ድህ ብንሆንም ታሪክ ያለን ሕዝቦች መሆናችንን፤ ባህል ያለን ሕዝቦች መሆናችንን፤ ለሥራም የምንተጋ ሕዝቦች መሆናችንን ከዚህ ቀደም ያልታወሱ ታሪኮቻችንን ሁሉ እንዲታወሱ ዕድል አግኝተናል። ከአንድ ሺሕ አምስት መቶ ዓመት በፊት በክርስትና፤ እንዲሁም ከአንድ ሺሕ አራት መቶ ዓመት በፊት በእስልምና በርካታ ሰዎች የሰላምና ችግረኞችን የምታቅፍ ሃገር መሆኗን አምነው የተጠለሉባት ሀገር ኢትዮጵያ፤ ከአንድ ሺሕ ዓመት በኋላ ታሪኳ እየቀጨጨና እየተረሳ የመጣ ቢሆንም፤ አሁን መልሶ የሚታደስበት ዕድል በመገኘቱ በተባበረ ክንድ፤ በተስማማ ማንነት ሀገራችን ከአለችበት ሁኔታ ወደ ብልጽግና እንድትሸጋገር በጋራ ጠዋት ማታ እንድንተጋ ይህ አጋጣሚ ለመማር፣ ለመቀየር፣ አንድ ለመሆን፣ ለመሻሻልና በዓለም መድረክ በአዳዲስ ማንነቶች ከፍ ብለን ለመታየት እንድንጠቀምበት አደራ ማለት እፈልጋለሁ።

በኢትዮጵያ ውስጥ ትውልድ የሚበላ ሾተላይ አለ። ይህንን ሾተላይ ማከም ያስፈልጋል። ወደ መሰላል የሚወጡ ልጆቻችን ከአሉ ጐትቶ ማውረድ ሳይሆን ገፍተን ጫፍ እንዲደርሱ ማድረግ ከሁላችን ይጠበቃል። ኢትዮጵያ ብዙ ጀግኖች ያላት ሀገር መሆኗ ይታወቃል። ነገር ግን፣ ማንኛውም ጀግና

የሚወጣበት መሰላል ከሌለው ከጫፉ ለመድረስ አይችልምና አንዱ አንዱን ደግፎ ከጫፉ ቢደርስ ትሩፋቱ ለሁሉም መሆኑ በዚህ በሰሞኑ ሽልማት የተረጋገጠ ነው። ሁላችሁም እንደ ሰማችሁት፣ ፕሮግራሙን በቀጥታ ስርጭት በዓለም ከአንድ ነጥብ አምስት ቢሊዮን ሕዝብ በላይ መከታተሉን ሙያተኞች ገልፀውልናል። ይህንን ፕሮግራም ስለ ሀገራችን፣ ስለ አካባቢያችን፣ ስለ ሕዝባችን የነበረውን ፕሮግራም ለአንድ ቢሊዮን ሕዝብ በቀጥታ ለማስተላለፍ ሁሉን የዓለም ሚዲያ በመጠቀም ሳይሆን አንድ ታዋቂ ሚዲያ በመጠቀም እንኳን በብዙ ሚሊዮን ብር ክፍያ የሚሳካ አልነበረም። ይህ መልካም ዕድል በርካታ ቱሪስት ለመሳብ፣ ኢንቨስትመንት ለማምጣት፣ ሥራ አጥነትን ለመቀነስ፣ ወደ ብልጽግና ለመሸጋገር የምንጠቀምበት እንዲሆን በታላቅ ትሕትና መላውን የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ የኤርትራን ህዝብ እንዲሁም የምሥራቅ አፍሪካን አገራት መጠየቅ እፈልጋለሁ። የድህነት፣ የጦርነት፣ የጉስቁልና፣ የግጭት ታሪኮቻችን እንዲያበቁ እና የመተባበር፣ የመስማማት፣ የመደማመጥ በጋራ ሆኖ ሀገርን፣ አካባቢን የመቀየርና እኛም እንደ ሌሎቹ መርዳት የምንችል ሀገር እንድንሆን ይህንን አጋጣሚ እንድንጠቀምበት በታላቅ ትሕትና እጠይቃለሁ።

ለኢትዮጵያ፣ ለኤርትራ፣ እንዲሁም ለአካባቢ አገራት አሁን የሆነው ነገር በአዳዲስ ነገር እንዲደገም፣ ልጆቻችን ተስፋ እንዲኖራቸው፣ በዚህ መድረክ በተለያየ ስም መሸለም እንዲችሉ አበክረን ተባብረን እንሥራ፤ ሰላም ለኢትዮጵያ በእጅጉ ያስፈልጋል። ፍቅር፣ ወንድማማችነት ያስፈልጋል። ጦርነትና ግጭት፤ ምቀኝነትና ስድብ እንደምታውቁት ወደ ኋላ ያስቀረን በመሆኑ ከዚህ ወጥተን በተባበረ መንፈስና በፍቅር ስሜት ሀገራችንንና አካባቢያችንን እንድናበለጽግ አደራ እላለሁ።

በመጨረሻም፣ ይህ አንድ ከበሻሻ ተወልዶ የመጣ ሰው የኢትዮጵያን ሕዝብ፣ የኤርትራን ሕዝብ ወክሎ በዚህ ታላቅ ሥፍራ ለመቆም የሚያበቃ ማንነት እንደ





ሌለው በግልጽ ሁላችሁም ትገነዘባላችሁ። ይህንን ያሳካውን፣ ያደረገውን እና በአዲስ መልክ ኢትዮጵያን የገለጠውን እግዚአብሔርን አብዝቼ ማመስገን እፈልጋለሁ። የኢትዮጵያን ሕዝብ፣ የኤርትራን ሕዝብ ማመስገን እፈልጋለሁ። ፕሬዝዳንት ኢሳይያስ አፈወርቂን በተለየ መንገድ ማመስገን እፈልጋለሁ፡ በቅርቡ እንደምንገናኝና በጋራም እንደምናከብር ተስፋ አደርጋለሁ።

**እንኳን ደስ አላችሁ! እንኳን ደስ አለን!**
**አመሰግናለሁ!**

# ከኖቤል ሽልማት መልስ የኢዮቤልዩ ቤተ መንግሥት ንግግር

ታኅሣሥ 2/2012 ዓ.ም.

**የሁለቱ ምክር ቤት አፈ ጉባኤዎች፣**
**እንዲሁም የፓርላማና የፌዴሬሽን ምክር ቤት አባላት፣**

ስለዚህ ፕሮግራምና ስለመገኘታችሁ እጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ!

**የተከበራችሁ የካቢኔ አባላት፣**
**የተከበራችሁ የሀይማኖት አባቶች፣**
**ታላላቅና ታዋቂ ሰዎች፣**

በመገኘታችሁና የደስታችን ተካፋይ ስለሆናችሁ እጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ!

ስለዚህ ምሽት እጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ!





ለኢትዮጵያ ሕዝብ፣ በተለይም ዛሬ በዚያ ፀሐይ አቀባበል ለአደረጉልን ኢትዮጵያውያን በሙሉ ከፍ ያለ ክብርና ምስጋና ማቅረብ እፈልጋለሁ። እንግዲህ ጀምረነዋል። እንዲቀጥል እጅ ለእጅ መያያዝ ያስፈልጋል። ሰው ፍቅር ሰጥቶ ከስሮ አያውቅም። ለሀገር ተግቶ ከስሮ አያውቅም። ይቅር ብሎ ከስሮ አያውቅም። ያለውን አካፍሎ ከስሮ አያውቅም። ከፍቅር፣ ከመስጠት፣ ከይቅርታ የሚጐድል ስለማይኖር ኢትዮጵያውያን የከፋን እንኳ ብንኖር ይቅር ተባብለን፤ እጅ ለእጅ ተያይዘን ወደፊት መገስገስ እንድንችል በዚሁ አጋጣሚ አደራ ማለት እፈልጋለሁ።

የኤርትራው ፕሬዚዳንት ክቡር ኢሳይያስ አፈወርቂ እና ሕዝባቸውን የኤርትራን ሕዝብ እንዲሁ በእናንተ ፊት ማመስገን እፈልጋለሁ።

ትናንትና፣ ከትናንት ወዲያ በኦስሎና ስቶክሆልም በነበረን ቆይታ የማናውቃትን ኢትዮጵያን ልኳን ለማወቅ ዕድል አግኝተናል። ለካ እኛ ኢትዮጵያውያን አላወቅነውም እንጂ፤ ትልቅ ታሪክ ያላት የተከበረች ሀገር ናት። አጋጣሚውን ተጠቅመው ነገሥታቱ፣ መሪዎቹ፣ የፓርላማ አባላት፣ ምሁራን ስለ እኛ ሀገር ታሪክና ትልቅነት ሲናገሩ፤ ሀገራችን ስለአልገባችን በሚገባት ልክ እያገለገልናት እንዳልሆነ ተሰምቶን ነው የተመለስነው፤ የወከላችሁን ሽልማቱን እንድናመጣ ብቻ አይመስለኝም። ይህንንም መልእክት እንድናመጣ ጭምር ነው።

በኦስሎ ጠዋት ሦስት ሰዓት ተኩል አይነጋም፤ ጨለማ ነው። ከሰዓት በኋላ ዘጠኝ ሰዓት ተኩል ላይ መሽቷል። ስድስትና ሰባት ሰዓት ብርሃን ሳያገኙ ሀገራቸውን ውብ አድርገው ሠሩ። ኢትዮጵያ ብርቅ አገር መሆንዋ የሚገባን ከኦስሎ ቀጥታ በርረን አዲስ አበባ ስንመጣ ብቻ ነው። እግዚአብሔር የሚሰጠውን ሁሉ ሰጠን። ማመስገንና መሥራት ስለማናውቅ ነው ለማኝ የሆንነው፤ የጐደለብን ነገር የለም። እጅግ የሚያስደንቅ ሀገርና የሚያስደንቅ መልክአ ምድር የተሰጠን ሕዝቦች ነን። በረዶው ብቻ ሳይሆን ጭለማው ምን ያክል እንደሚያሠቃይ

በሁለት ቀን ቆይታ ማየት ችያለሁ። ይህንን ታላቅ ሀገር፣ ይህንን ድንቅ ሀገር እና ትልቅ ጉልበት ያለው ወጣት የሞላባት ሀገር ለክፋት፣ ለስድድብ፣ ለመጥፎ ነገር የምናጠፋውን ጊዜ ቆጥበን እጅ ለእጅ ተያይዘን ብንሠራበት ለሌሎች የምንተርፍ መሆናችንን ማሰብ ጠቃሚ ነው።

ኖርዌይ አምስት ሚሊዮን ሕዝብ ያላት ሀገር ነች። ይህ የጨለማ ጊዜ እንደኛ ክረምት ሁለት ወር፣ ሦስት ወር የሚቆይ አይደለም። ስምንትና ዘጠኝ ወር ጨለማ ነው። ፀሐይ የሚያገኙት በጣም ጥቂት ወር ነው። ግን በጣም የሚያሳፍረው ከኖቤል ሽልማቱ በኋላ ከመሪዎች ጋር በነበረኝ ቆይታ የመቶ ዓሥር ሚሊዮን ሕዝብና የዚች ለምለም አገር መሪ የሆንሁ እኔ፤ የአምስት ሚሊዮን ሕዝብና የዚያ አስቸጋሪ መልከአ ምድር ሀገር መሪዎችን ለመንኳቸው። መሸለሜን ብቻ ሳይሆን በእናንተ ስም ለምኜ ለማኝ መሆናችሁን መናገሬን ላስታውሳችሁ እፈልጋለሁ። ለማኞች መሆናችን ካልገባን እብሪት፣ ትዕቢት እና ፉከራ ብቻውን ከአምስት ሚሊዮንና ከትናንሽ አገራት የሚያስለምን ስለ ሆነ፤ ከልመና ወጥተን ወደ ብልጽግና እንድንሄድ እጠይቃለሁ። ከኤርትራ ወንድሞቻችን፣ ከጅቡቲ ወንድሞቻችን፣ ከሶማሊያ ወንድሞቻችን፣ ከደቡብ ሱዳን፣ ከሱዳን ወንድሞቻችን፣ ከግብፅ፣ ከሌሎችም ወንድሞቻችን፤ በመካከለኛው ምሥራቅ ካሉት ሀገራት፤ ከመላው የአፍሪካ አገራት ጋር በሰላም፣ በፍቅር፣ በትብብር መንፈስ ወደ ብልጽግና እንሂድ። ቢያንስ ልጆቻችን እኛ ዛሬ ሄደን የለመንናቸው አገራት ዓሥርና ሃያ ሚሊዮን፤ መቶ ሚሊዮን መርዳት የሚጀምሩበት ጊዜ መፈጠር ይኖርበታል። ኢትዮጵያውያን ከለማኝነት ወደ ረጂነት ለመሸጋገር ከወሰንን እንችላለን። ይሄ ውሳኔ የሚጸናው ግን ከዛሬ ጀምሮ ወደ ሥራ ከአተኮርን ብቻ ነው።

ድግስ ቀንሰን በፈጠነ እና በተባበረ መንገድ ወደ ሥራ መግባት ይኖርብናል። እኔ ዛሬ ከራት በኋላ ቢያንስ እስከ እኩለ ለሊት ድረስ ሥራዬን ለመሥራትና የሰሞኑን ሥራ ለማካካስ ዝግጅት አለኝ። እዚህ ያላችሁ ሰዎች ብዙ ተቋም





የምትመሩ ባለሀብቶች ታላላቅ ሰዎች ናችሁ። አትተኙ! የደሀ አገር ዜጋ፤ የለማኝ አገር ዜጋ ሲተኛ አያምርበትም። ተግተን በመሥራት ጊዜያችንን፣ ጉልበታችንን ይህችን አገር ለማበልጸግ ከተጠቀምንበት ኢትዮጵያ ኖርዌይን የምትረዳበት ጊዜ ሩቅ ነው ብዬ አላስብም።

በዚህ ቆይታዬ አንድ የተማርኩት ነገር የኖቤል ሽልማት ሐሳብ አመንጪና ገንዘቡን የመደበው አልፍሬድ ኖቤል የኖርዌይ ዜጋ አለመሆኑን ነው። የስዊዲን ዜጋ ነው። ነገር ግን ኖርዌይና ስዊዲን ልክ እንደ እኛ እና ኤርትራ ባለ ሁኔታቸው ተመካክረው፤ ኦስሎ ላይ እንዲሆን ስዊዲኖች ፈቀዱ። ሰላም ከመፍቀድ፤ ሰላም ከመስጠት የሚመጣ መሆኑን አንዱ የተማርኩት ጉዳይ ነው። ዛሬ በዓለም ላይ እንደ ኖርዌይና እንደ ስዊዲን ጠንካራ ዲፕሎማሲ እና የኢኮኖሚ ትስስር ያለው አገር የለም። እንደ አንድ አገር ተቀራርበዋል። ምክንያቱም ስዊዲኖች የራሳቸው የሆነን ነገርም ጭምር ለመስጠት ዝግጁ ስለሆኑ ነው። ለኤርትራ መስጠት፤ ለጅቡቲ መስጠት፤ ለደቡብ ሱዳን መስጠት ማነስ አይደለም፤ ማቀፍ ነው። ከብዙ ዓለም ለምነን የምንወስድ ሰዎች በመስጠት መቀራረብ ብንጀምር መልካም ስለሚሆን፣ ኢትዮጵያውያን ልባችን የሰፋ፤ ትከሻችንም ብዙ መሸከም የሚችል፤ የምንቻቻልና ወደ ላቀው የዕድገት ጐዳና በጋራ የምንጓዝ እንድንሆን በዚህ አጋጣሚ በታላቅ ትሕትና ጥሪዬን አቀርባለሁ።

የኢትዮጵያ ሕፃናት፤ አዳጊዎች እና ወጣቶች ትናንት የሰማችሁት ዜና ከእናንተ አንፃር እጅግ ደካማ በሆነ ሰው ላይ ያረፈ ዕድል ነው። ሰው እንዴት ከበሻሻ ወጥቶ ኦስሎ ድረስ ሄዶ ይህንን ክብር ይወስዳል? የአዲስ አበባ ሰዎች ባያላግጡ ኖሮ፤ የአምቦ ሰዎች ባያላግጡ ኖሮ፤ የጐንደር የጥንታዊ ከተማ ሰዎች ባያላግጡ ኖሮ፤ የመቀሌ ሰዎች ባያላግጡ ኖሮ፤ የባሕር ዳር ሰዎች ባያላግጡ ኖሮ፤ እንዲያውም የጅማ ሰዎች ባያላግጡ ኖሮ ሰው እንዴት ከበሻሻ ሊወጣ ይችላል። በሻሻ ማለት እኮ ጫማ አድርጋችሁ መጓዝ የማይቻልበት

ጭቃ እስከጉልበት የሚውጥበት፤ መብራት ማየት ብርቅ የሆነበት አገር ነው። እና እናንተ የታደላችሁ፤ ትምህርት የምታገኙ፤ መብራት ቴሌቪዥን ያላችሁ የከተማ ልጆች ጊዜአችሁን ፌስቡክ ላይ አታባክኑ። ተግታችሁ ሠርታችሁ አዳዲስ ከፍታ፤ አዳዲስ ክብር ለሀገራችሁ ለማምጣት ጊዜያችሁ አሁን ነው።

**አልፎ እንዳይቆጫችሁ አሁን ሥሩበት!**
**አመሰግናለሁ!**





# ኢትዮጵያ የመጀመሪያዋን ሳተላይት ያመጠቀችበት ዕለት ንግግር

ታኅሣሥ 10/2012 ዓ.ም.

**ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ፣**
**እንኳን ደስ አላችሁ! እንኳን ደስ አለን! ማለት እፈልጋለሁ።**

ዛሬ ለመጀመሪያ ጊዜ ኢ.ቲ.አር.ኤስ.ኤስ-1 የተሰኘች ሳተላይት ወደ ምህዋር ማምጠቅ ችለናል። ይህ በታሪካችን የመጀመሪያ የሆነው ሳተላይት ብዙዎቹን ከኋላ የሚያስከትል፤ የመጨረሻ ያልሆነም እንደሚሆን ሙሉ ተስፋ አለኝ። ይህች ሳተላይት በወሳኝነት ግብርናችንን ለማዘመን፤ በዕውቀትና በመረጃ ተንተርሰን ሥራችንን እንድንሠራ የምታደርገን፤ በአፍሪካና በዓለም ገበያ በዕውቀት ላይ ተመሥርተን እንድንወዳደርና ውጤታማ እንድንሆን የምታግዘን ሳተላይት ስትሆን፤ እስከ አሁን የእኛ የሆነ ሳተላይት ስላልነበረን ምስሎችን ከተለያየ ሀገር በግዢ

እናገኝ ነበር። አሁን ግን በድንበር አካባቢ ያለውን እንቅስቃሴ ትላልቅ ፕሮጀክቶችን የምንከታተልበት፣ የአየር ጠባይ የምናይበት፣ የግብርናችንን ሁኔታ የምናዘምንበት፣ በቂ መረጃ የምንሰበስብበትና በመረጃ ላይ ተንተርሰን ሥራችንን እንድንሠራ ለውድድር የሚያበቃ መሠረት ሆና የምታገለግል ይሆናል፡፡ የዚህች ሳተላይት አብዛኛው ወጪ በቻይና መንግሥት የተሸፈነ ሲሆን፤ ወደፊት ከተለያዩ ሀገራት ጋር በጋራ በመሆን አዳዲስ ሳተላይቶች እናመርታለን። በዚህችኛዋም ላይ ኢትዮጵያውያን ምሁራን ከዲዛይን ጀምሮ እስከምርት የተሳተፉ ሲሆን፣ የቁጥጥር ማዕከሉ ሙሉ ለሙሉ እዚሁ አዲስ አበባ ላይ የተሠራ መሆኑን ሳረጋግጥላችሁ ኢትዮጵያ ወደ ምህዋር የሚደረገውን እንቅስቃሴና የመረጃና የዕውቀት ፍለጋ ጅማሬዋን ዛሬ "ሀ" ብላ የጀመረችና በፍጥነት የምታስቀጥል መሆንዋን፤ ወደ ብልጽግና የምናደርገው ጉዞ መጀመሩንና ሳያቋርጥ ለልጆቻችን፤ ለትውልድ በሚተርፍ መንገድ የሚረጋገጥ መሆኑን በድጋሚ ልገልፅላችሁ እፈልጋለሁ::

**እንኳን ደስ አላችሁ!::**
**እንኳን ደስ አለን!**



# "ለሁላችንም የምትመች ኢትዮጵያን በጋራ እንገንባ" ዝግጅት ንግግር

ታኅሣሥ 10/2012 ዓ.ም.

**እንዴት ዋላችሁ**
**አካም ቡልተኒ! ነጌኙ በዳዳ!**

በመጀመሪያ ሀብታም መሆን ብቻ በቂ አይደለም ብላችሁ የአመራርነት ሚናችሁን ለመወጣት ጊዜአችሁን፣ ገንዘባችሁን በማባከን ሳይሆን በማበልጸግ ለሀገር ሰላም የሠራችሁ የኢትዮጵያ ባለሀብቶች እንኳንም ባለሀብት ሆናችሁ! ባለሀብቶቻችንን በተለየ መንገድ መመልከት እንድናቆምና እንድናከብራቸው የሰላም አምባሳደር መሆን፣ ማስተባበር፣ ማቅናት፣ ማልማት፣ መምራት እንደምትችሉ ያሳያችሁበት አጋጣሚ ስለሆነ ከብልጽግና ፓርቲ ጋር ጠንካራ አመራር በመስጠት ኢትዮጵያን እንደምታሸጋግሯት ያለኝን ተስፋ ላረጋግጥላችሁ እፈልጋለሁ፡፡

እንዲሁም አባገዳዎች፣ የሀገር ሽማግሌዎች፣ የመንግሥትም የሕዝብም አባት የሆናችሁና ማኅበረሰቡ ወድዶና ፈቅዶ አባገዳ፤ ሽማግሌ ብሎ የሰየማችሁ የከበዳችሁ የዕድሜ ባለፀጐች፤ እናንተ የሁለት ሕዝቦችን ሳይሆን የዚህችን ዓለም ሰላም ለማምጣት የምትጸልዩ፣ የምትመክሩ፣ የምትገሥጹ ስለሆናችሁ ኢትዮጵያ እንኳንም አባገዳዎች፤ እንኳንም ሽማግሌዎች ያሏት ሀገር ሆነች! ምሁራን በተለየ መንገድ እዚህ ሥራ ላይ የአደረጋችሁት አስተዋጽዖ ከምሁር የሚጠበቅ ነውና፣ ወደፊትም በሐላፊነት ስሜት እንደዚህ ያለ መልካም ሥራ በመሥራት የማሰብም ብቃት ማሳየት እንድትችሉ፤ በዚህ የሰላም ጉዞ የጀመራችሁትን ሥራ በብልጽግና ጉዞአችንም እንድትደግሙት ላደረጋችሁት እያመሰገንኩ ወደፊትም  ከእናንተ ብዙ እንደምንጠብቅ በዚሁ አጋጣሚ ልገልፅላችሁ እፈልጋለሁ፡፡

ቄሮዎች፣ ፋኖዎች የሰላም አየር እንዲመጣ፤ ጠቅላይ ሚንስትርን ለማማት የምንፈራበት ሀገር ጠቅላይ ሚኒስትርን በሚዲያ ወጥተን መሳደብ እንድንችል ነፃነት እንዲመጣ የታገላችሁ፤ መሥዋትዕነት የከፈላችሁ፤ በቅርቡ እናንተን ለማሰብ በአዲስ አበባ ምልክት እንደምናስቀምጥ ቃል የገባንላችሁ ወጣቶች የታገላችሁት፣ የደማችሁት፣ የደከማችሁት ተጨማሪ ወጣት እንዳይሞት እንጂ ሊማር የሄደ በዚያው እንዲቀር አይደለምና የሁለቱ ክልሎች ወጣቶች ተቀራርባችሁ በመነጋገር በሐሳብ ልዕልና ለሁለቱ ክልሎች ብቻ ሳይሆን ለመላው ኢትዮጵያ ሰላም እንዲመጣ ለአደረጋችሁት ጥረት በዚሁ አጋጣሚ ላመሰግናችሁ እፈልጋለሁ፡፡

እንዲሁም ዛሬ የደስታ ቀን ስለሆነ በውስጤ የሚፈሰውን የደስታ ስሜት ሳላጋራችሁ ማለፍ ስለማልፈልግ እንኳን ኢትዮጵያ በድጋሚ በዓለም መድረክ የሳተላይት ባለቤት ሆነች! እንኳን ደስ አላችሁ! ይህንን ጉዳይ በሚመለከት እራሱን አስችዬ ሌላ ጊዜ በዝርዝር የማወራችሁ ቢሆንም፣ የዛሬ ዓሥራ ሁለት





ዓመት ለመንግሥት  ሳተላይት እንዲኖረን በሰነድ ፕሮፖዛል አቅርቤ ነበር። ኮፒው አሁንም  በእጄ አለ። በወቅቱ የተሰጠው ምላሽ በጣም አሳዛኝ ነበር። የዛሬ አራት ዓመት ደግሞ የስፔስ ኤጀንሲ እንዲቋቋም ለመንግሥት ፕሮፖዛል አቅርቤ የመጀመሪያው የካቢኔ ስብሰባ ይህንን ፕሮፖዛል “ደፋሮች” ብሎ ውድቅ አደረገው። የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስትር እያለሁ  ዛሬ ከሰማችሁት የቻይና ኩባንያ ጋር ስፔስን በሚመለከት እንዲተባበሩን ለመፈራረም ዕድሉን አግኝቼ ዛሬ ሳተላይቷ ወደ ምህዋር ስትላክ በወቅቱ የሶሻል ክላስተርና አስተባባሪና አለቃዬ ለነበረው አቶ ደመቀ ዛሬ ቅድሚያውን አንተ ውሰድ ብዬ ወደ እንጦጦ ላኩት። በዚሁ አጋጣሚ ሦስት ሰዎችን ማመስገን እፈልጋለሁ። አቶ ተፈራ ዋልዋ የዐቅም ግንባታ ሚኒስትር የነበሩ፤ ሐሳብ የማይፈሩ፣ ሀሳብ የሚያደፋፍሩ፤ አቶ አባዱላ ገመዳ ብዙ ነገር የነበሩ፣ አሁንም ያኔም አባዱላ የነበሩ፤ ያኔ ያበረታቱ በዚሁ አጋጣሚ ላመሰግናቸው እፈልጋለሁ፡፡

ከአንድ አመት ተኩል በፊት ለረጂም ጊዜ አለቃዬ የነበረው እና ይህን ሐሳብ በማካፍለው ሰዓትም በሚገርም ሁኔታ ከጐኔ የነበረው በኋላም ይህ ጉዳይ በካቢኔ ጸድቆ እውን እንዲሆን የረዳኝን የዛሬውን ምክትል ጠቅላይ ሚኒስቴር እጅግ አድርጌ ማመስገን እፈልጋለሁ፡፡ ብዙዎች “ሳተላይት ማምጠቅ ያን ያህል ያስፈነድቃል ወይ?” ይላሉ። የሚያስፈነድቀው ምን እንደሆነ በኋላ እነግራችኋለሁ። ሁለተኛው፤ “ሳተላይቱ ከቻይና ነው የተወነጨፈው” የሚሉ ሰዎችም አሉ። ስለ ሳተላይት ብዙ እንደማያውቁ ከንግግራቸው ይገባኛል። ሳተላይት በአፍሪካ ውስጥ ዓሥር አገራት በዓለም ላይ ሰባ አገራት ያላቸው ሲሆን ብዙዎቹ በሦስትና በአራት አገራት ብቻ ነው የሚወነጨፉት፡፡ የሳተላይት ባለቤት መሆንና የማስወንጨፊያ ዐቅም ለየቅል ስለሆኑ፣ ወደፊትም ብናመርት ወይ ወደ ቻይና ወይ ወደ አሜሪካ እየላክን ማስወንጨፍ ወይ ወደ ራሽያ እየላክን ማስወንጨፍ እንጂ ማስወንጨፊያውና የሳተላይት ባለቤት መሆኛዋ ጊዜ አንድና ያው አለመሆኑን በዚሁ አጋጣሚ ማሳወቅ እፈልጋለሁ፡፡

የኦሮሞና የአማራ ጉዳይ ብዙ የተባለለት ነው። ኦሮሞዎችና አማራዎች በኢትዮጵያ ውስጥ በርካታ ቁጥር ያላቸው ታላላቅ ሕዝቦች አድርጐ የፈጠራቸው ፈጣሪ በጋራ እንድትበለጽጉ፤ ብትለያዩ ግን የምትደኸዩ መሆናችሁን ዛሬ በድጋሚ ልነግራችሁ እፈልጋለሁ፡፡ እናንተ ታምናችሁ አገር እንድትጠብቁ፣ አገር እንድታቀኑ፤ ኦሮሞ በአፍሪካ በቁጥር አንደኛው ብሔር ነው። በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በአፍሪካ የኦሮሞን ያክል ቁጥር ያለው ብሔር የለም። ለአፍሪካ በዚያ ልክ ሐላፊነት መውሰድ አለበት ማለት ነው። አማራ ከኦሮሞ ቀጥሎ በጣም ትልቁ ሕዝብ ነው። እነዚህ ሁለት ሕዝቦች በተናጥል በቁጥራቸው ከፍ ያሉ ቢሆንም በቁጥር ከፍ ማለት በቁጥር ያነሱትን ማቀጨጭ ወይም ማሳነስ ማለት አይደለም። ማክበር፣ መውደድ፣ ማቀፍ ማለት እንጂ፤ እነዚህ ሁለት ሕዝቦች አርአያ ሆነው በቅርቡ በደቡብ የሚገኙ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በምሥራቅ የሚገኙ፤ በሰሜን የሚገኙ ሌሎች ወንድሞቻችንና እኅቶቻችን ጋር በመደመር አዳዲስ የውይይት ጉባኤ፣ የምክክር ጉባኤ፣ የሐሳብ እና የነፃነት ጉባኤ እንደምትፈጥሩ ይህ የዛሬው መድረክ ለሌሎች እርሾና መሠረት የሚሆን እንጂ የመጨረሻው እንዳልሆነም ተረድታችሁ ዋናው ሥራ ከዚህ በኋላ ያለው መሆኑን እንድትገነዘቡ አደራ ማለት እፈልጋለሁ፡፡

በኦሮሞና በአማራ ብቻ ሳይሆን በኢትዮጵያ ውስጥ በቋንቋ፣ በፆታ፣ በዕድሜ፣ በዕውቀት፣ በተለያየ መንገድ ልዩነቶች አሉ። እነዚህ ልዩነቶች ፀጋዎች ናቸው። ወጥ ነገር አያምርም። ጨለማ ባይኖር ጠዋትም፤ ከሰዓትም፤ ማምሻውም፤ እኩለ ሌሊትም ፀሐይ ቢሆን አይመችም። ጨለማ የሚያስፈራ እንኳ ቢሆን ያስፈልጋል። የሚያስፈልገው ወጥ የሆነ ነገር ሳይሆን ልዩ ልዩ የሆነ ነገር ነው። በኢኮኖሚ እንኳን በነዳጅ ላይ ብቻ የተመሠረተ ሃብት፤ በቱሪዝም ላይ ብቻ የተመሠረተ ሀብት፤ ወይም በወደብ ላይ ብቻ የተመሠረተ ሀብት አያዋጣም።





የኢኮኖሚ አዋቂዎች “ሀብታችሁን፤ የሀብታችሁን ምንጭ የተለያየና በርከት ያለ አድርጉት” ይላሉ። ሕዝቦች በተለያየ ቋንቋና ባህል፤ ትውፊትና ማንነት እሴቶች ላይ ሲመሠረቱ አንዱ ከሌላው ለመማር ዕድል ያገኛል። እኛ በሄድንበት “ኒሀው” በምንልበት ዓለም ውስጥ አማሮች ደፈር ብላችሁ “አካምቡልቴ” ማለት መጀመር አለባችሁ። የሚያቀራርበው መተዋወቅ ነው። የሚያቀራርበው አብሮ መብላት ነው። የሚያቀራርበው ሆድ ለሆድ፤ ልብ ለልብ መተዋወቅ ነው። ሳንተዋወቅ እንጠላላለን። ስንቀራረብ ሁሌ እንደምታዩት እናላቅሳለን። ስንገናኝ የሚያጋጩን ነገር እምብዛም ስለአልሆነ አብሮ ለመኖር አራት መሠረታዊ ነገሮች ያስፈልጉናል።

አንደኛው፤ በርካታ ሰዎች የአብሮ መኖርን ጥቅም መገንዘብ ሰላምን በሚመለከት ተናግረዋል። ለዚያ ጊዜ አላባክንም። አብሮ መኖር የአንደኛውን ስሜት፣ የአንደኛውን ቁስል፣ የአንደኛውን ፍላጐት መገንዘብ ይፈልጋል። በቤታችን ውስጥ እንኳን ትዳር መሥርተን ስንኖር ባል የሚስቱን፤ ሚስት የባሏን ስሜት ማዳመጥ ከአልቻለች አንድ ሳምንት ወጥ በሆነ መንገድ ሰላም ማረጋገጥ አይቻልም። ሰላም መቻቻል ይፈልጋል። መቻቻልና ሰላም ደግሞ ለአብሮነት መሠረት ናቸው። አብሮ ለመኖር ሰላም ወሳኝ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

ሁለተኛው፤ የሌላውን እሴት ማወቅ ነው። የሌላውን ባህል፤ የሌላውን ቋንቋ ማወቅ ነው። ከቅርብ ግዜ ወዲህ በኢትዮጵያ ውስጥ “የሌላውን ማወቅ አስፈላጊ አይደለም” ብለው የሚያስቡ ብዙ ሰዎች ይደመጣሉ። እነዚህ ሰዎች ግን ልብሳቸውን አውልቀው ራቁታቸውን ሲሄዱ አይታይም። ከእናንተ መካከል፤ እዚህ ከአላችሁ በሺሕ የምትቆጠሩ ሰዎች ወይ ጫማው፤ ወይ ካልሲው፤ ወይ ሸሚዙ፤ ወይ ከረባቱ ከቻይና ያልመጣ የለም። ለምን የሰው ትለብሳላችሁ? ከእናንተ መካከል የያዛችሁት ስልክ ምናልባት ዘጠና አምስት በመቶው ከተለያየ ሀገር የመጣ ነው። የሰው የማያስፈልግ ከሆነ

ለምን ትጠቀማላችሁ? ኢትዮጵያ አምፖል አልሠራች፤ ስፒከር አልሠራች እዚህ አዳራሽ ውስጥ የምታዩት አብዛኛው ነገር የእኛ አይደለም። ግን እንጠቀምበታለን። አብሮ መኖር የሚያስፈልገው አንዱ ዘንድ ያለውን ጠቃሚ ነገር ሌላ ጋ ካለው አዋድዶ እና ደምሮ ኑሮን፤ የኑሮን ዘዬ ማዘመንና ማሻሻል ስለሚቻል "አያስፈልገኝም" የሚባል ነገር እምብዛም ጠቃሚ አይደለም። በሀያ አንደኛው ክፍለ ዘመን በሠለጠነ ዓለም ይህንን ሐሳብ የሚያራምዱ ሰዎች ደጋግመው ማሰብ ይኖርባቸዋል።

ሦስተኛው፤ አብረው መኖር፤ ሳይጠፋፉ መኖር ይቻላል? ወይስ አይቻልም? የሚለውን ማሰብ ነው። በቅርቡ በአንድነት ፓርክ ስንሠራ አንድ አዲስ ትምህርት ተማርን ። እንደምታውቁት ባሕር ዛፍ ውሃ ይጠጣል። በአካባቢው ያለውን ተክል ይጐዳል ሲባል ነበር የማውቀው፤ የምሰማው፡፡ እና አንድ ሁለት ባሕር ዛፍ ቆርጠን ሌሎችን ዛፎች አልነካናቸውም ነበር። ባሕር ዛፉ ከተቆረጠ በኋላ በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ሌሎቹ ዛፎች ደረቁ። እውነተኛ ታሪክ ነው የምነግራችሁ፡፡ እና በዘርፉ ያሉ ምሁራን ስናነጋግር ዛፎች ተደጋግፈው ይኖራሉ። አንዱ ከአጠገባቸው ሲጠፋ አንዱ ተቋቁሞ ለመኖር ይቸገራል። እንኳንስ ሰው፤ እንኳን አማራ እና ኦሮሞ ዛፎች በትብብር የሚኖሩበት ዓለም ስለሆነ በትብብርና በፍቅር አብሮ መኖርን መውደድና መለማመድ ያስፈልጋል።

ኦሮሞና አማራ በባህላቸው ችግር አይፈጠርም ብለው የሚያምኑ ሕዝቦች አይደሉም። ሰላም ለማምጣት የሰላም መፍቻ ቁልፍ አዘጋጁ እንጂ፤ በፍፁም ችግር የሚባል አጋጥሞን አያውቅም፤ ወደፊትም አያጋጥመንም አይሉም። በመጀመሪያው ሀሳብ ላይ አንድ የዘነጋሁት ነገር፤ እነዚህ ሕዝቦች ለዚህ ሁሉ ሺሕ ዓመታት እንዴት አብረው መኖር ብቻ ሳይሆን መባዛት፤ መብዛት ቻሉ? አብሮ መኖር ያበዛቸውና ያባዛቸው ከሆነ ወደፊት በተሻለ መንገድ መኖር





የሚያስችል ልምምድና ቅሬት አላቸው ማለት ነው፡፡ እስከአሁን ከኖሩ ወደፊት የማያኖር አይደለም።

ችግርን በሚመለከት ግን በኦሮምኛም በአማርኛም ብዙ ገላጭ አባባሎች አሉ። "ጉልቻና ጉልቻም ይጋጫል" ይላሉ እናቶች፤ ጉልቻና ጉልቻ ስለሚጋጭ ሦስት ጉልቻ አስቀምጠው መጋገር ግን አይተውም። እንዳይጋጩ ቦታ ቦታቸውን ያስይዛሉ እንጂ፤ እግር ከእግር ስለሚጋጭ "ይሄ ቀኝ እግሬ ግራዬን እየገጨ አስቸግሮኛል" ብሎ ግራ እግሩን ቆርጦ ጥሎ በአንድ እግሩ የሚሄድ ሰው የለም። ግን በአባባል "ግራ እግርና ቀኝ እግር" ይጋጫል ይባላል። አብረን ስንኖር የሚያጋጭ፣ የሚያጣላ፣ የሚያቃቅር ነገር ይኖራል። እንኳን ሕዝብና ሕዝብ ብቻችሁን አንድ ሳምንት ከጎሊናችሁ፣ ከሐሳባችሁ ሳትጋጩ አትኖሩም። በስፋት ስታስቡ ከራሳችሁ ሐሳብ ጋር የምትቃረኑባቸው በርካታ ጊዜያት ይኖራሉ። በቅራኔ ውስጥ ግን መገዳደል ተገቢ አይደለም። በቅራኔ ውስጥ ደም መፋሰስ ተገቢ አይደለም። በተለይ ዩኒቨርሲቲ ከሄድን በኋላ ጩቤ እምንማዘዝ ሰዎች፣ ጩቤ ለመማዘዝ ሀገር ማቋረጥ የአውቶቡስ መክፈል አስፈላጊ አይመስለኝም። እዚያው ሰፈር ውስጥ መዋጋት ስለሚቻል ሰው ዩኒቨርሲቲ የሚሄደው በጩቤ መዋጋት ጐጂ መሆኑን ለማስተማር፣ ለማሰብ፣ ለመጻፍ እንጂ እዚያ ከሄደ በኋላ ዓሥራ ሁለት ዓመት የለፋበትን፤ ቤተሰቡ የደከመበትን ነገር ከንቱ ለማድረግ አይደለም። ነገር ግን ሁላችሁም እንደምትገነዘቡት በዩኒቨርሲቲ አካባቢ የሚያስፈልገው ተማሪዎች ብቻ ሳይሆኑ ከተማሪዎች ውጪ ያንን ወጣት ያንን ስብስብ ባልተገባ መንገድ ኢጋጭቶ ከግጭት ማትረፍ የሚፈልጉ በርካታ ኃይሎች አሉ። ለእነርሱ የወጣት ወቀሳው "እምቢ" ማለት አለመቻሉ እንጂ ቀስቃሽ ኃይል የለም ማለት አይደለም።

ከእንግዲህ በኋላ የኢፌዲሪ መንግሥት በሁሉም ዩኒቨርሲቲዎች ጠንካራ ጥበቃ ማድረግ የጀመረ ሲሆን መረጃ ባገኙ ቁጥር ሕጋዊ የሆኑ ማስተካከያዎችን ይወስዳል። መንግሥት በትዕግሥት የቆየባቸውን ጊዜዎች ደካማ እንደሆነ

ያሰብን ካለን በጣም ቀላሉ ነገር ደካማ ሆኖ ዲሞክራሲን መገንባት እንጂ አምባገነን ሆኖ ብዙዎችን መጨረስ ቢያንስ ለእኛ ለኢትዮጵያውያን ብዙ ልምምድ አያስፈልገውም። ታሪክ ሰምተናል። ስናድግ ሕፃን ሆነን አይተነዋል። ሥራ ከያዝን በኋላ አይተነዋል። ሲገረፍ፣ ሲገደል እያየን፣ እየሰማን ያደግን ሰዎች ስለሆንን እሱ ቀላሉ የሌላ አገር ልምምድ፤ የሌላ አገር ብድር የማይፈልግ ጉዳይ ነው። ግን የሚሻለን ጨክነንም ቢሆን ወደ ዲሞክራሲ የምናደርገውን ጉዞ ማሳካት ነው። ያን ካላደረግንና የከፋ እርምጃ ከወሰድን ደም ከተቃባን መመለሻ የለውም። የቦረና የአገር ሽማግሌዎች ከዚህ ቀደም ሳነጋግራቸው ከነገሩኝ ውስጥ በጣም ብዙ የሚጠቅሙ ነገሮች አሉ።

የአማራ ምሁራን እዚያ ሄዳችሁ እንድትመራመሩ እኔ አበረታታችኋለሁ። አንደኛው፤ ቦረና እንደሌላው አካባቢ "ደኅና አደርክ" አይልም። "ነጌኝ በዳዳ" ይላል። በዳዲና ማለት ብልጽግና ማለት ነው፤ የፓርቲያችን ስም የወጣው ከቦረና ነው ማለት ነው፡፡ እራሱ ሰላም የሚበለጽግ ነገር እንደ ሆነ በኦሮሚያ አምናለሁ። "ሰላም ነህ? ሰላም አይደለህም?" ብቻ ሳይሆን "ሰላም በዝቶልሃል ወይ በልጽጐብሃል ወይ?" እንደማለት ነው። ይህ እሳቤ በጣም ጥልቅ መልእክት በውስጡ አለው።

ይሄን ጉዳይ በቀደመው ንግግሬ ውስጥ ያመጣሁበት ምክንያት በኢትዮጵያ ውስጥ በሰላማዊ መንገድ አንድ ተርም ሁለት ተርም እያገለገልን "አመሰግናለሁ!" ብለን መለያየት መጀመር አለብን። ያ እንዲሆን ከፈለጋችሁ ደም መቃባት የለብንም። ብዙ የአፍሪካ መሪዎች በሰላማዊ መንገድ ለወጣት አመራሮች መልቀቅ ይፈልጋሉ። ግን ችግራቸው ደም ተቃብተዋል። ኬንያ ድረስ ተከትለው ገድለዋል። ጅቡቲ ድረስ ተከትለው ገድለዋል። ብዙ አገር ሄደው አጥፍተዋል። "ከወረድኩ ምን ይደርስብኛል?" ስለሚሉ አንዴ ደም ከነካኩ በኋላ እዚያው እንደተጠበቁ መኖር ይፈልጋሉ። እኔ ደግሞ በሰላም በተርም ማስረከብን ኢትዮጵያ ውስጥ መጀመር እፈልጋለሁ። በሰላም ማለት እንደባለፈው በቄሮና በፋኖ ግፊት ማለት አይደለም። በምርጫ ያ እንዲሆን ከአስፈለገ ደም መቃባት የለብንም። ደም ካለማመዳችሁኝ እንደከዚህ ቀደሙ እኔም እዚያው ነው የሚሆነውና ለራሳችሁ ስትሉ ደም ከመቃባት ይልቅ ተባባሪ ሁኑ። ልክ እንደ ሀብታሞቹ፣ እንደ ምሁራን፣ እዚህ እንዳላችሁ ወጣቶች እንደዚሁም የአማራና የኦሮሚያ ተፎካካሪ ፓርቲዎች በዚህ ጉዳይ ከፍተኛ ተሳትፎ አድርገዋል። እነሱንም ማመስገን እፈልጋለሁ። ደም ሳንቃባ ዲሞክራሲ የምንገነባባት ኢትዮጵያ እንድትሆን ልባችን የሰፋ፣ ትከሻችን የሰፋ፣ አርቀን የምናስብና የምናስተውል ብንሆን መልካም ነው።

በመጨረሻ እስከዛሬ ያላካፈልኳችሁ አንድ የሕይወት ልምድና ዛሬ ላጋራችሁ የምፈልገው ሐሳብ አለ። የሳተላይቱም ጉዳይ እዚህ ዘንድ ተመልሶ ይመጣል። ይሄን ጉዳይ የማነሣው በርካታ ወጣቶች እዚህ ስለአላችሁ ነው። በመደበኛ ንግግር የማይመች ቢሆንም ግን ልምዱን ባካፍላችሁ ስለሚጠቅማችሁ ነው። ብዙ ጊዜ ከበሻሻ መምጣቴንና እኛ አካባቢ ብዙ ሰዎች ደሃ መሆናቸውን ነግሬአችሁ ነበር። እኛ አካባቢ ነው ያልኩት፤ አንዳንድ ሰዎች ሲጠይቁኝ እናትና አባቴ ደሃ መሆናቸውን ተናግሬአለሁ። ነገር ግን አንድም ቀን በድህነት ኖሬ አላውቅም። እናቴ መኪና የላትም፤ እኔ አንድም ቀን በእግሬ ሄጄ አላውቅም። አልሰማችሁኝም፣ እኛ ቤት የደብረ ብርሃን ብርድ ልብስ ብቻ ነው በሰሌን ላይ የሚለበሰው። እኔ ግን አንድም ቀን ከታች አንሶላ ከላይ አንሶላ እና የአልጋ ልብስ ሳላደርግ ተኝቼ አላውቅም።

ስለዚህ እንዳትሸወዱ ከበሻሻ የመጣው የደሃ ቤተሰብ ልጅ እያላችሁ፤ ነገር ግን ይህ እንዴት ነው ያላችሁ እንደሆነ ጠዋት ጠዋት እናቴ ሂድና ስኳር ገዝተህ ና ትለኛለች። እኔ ከሱቅ ስኳር ለመግዛት ከቤታችን ስወጣ ቀጥ ብዬ ወደ ሱቅ አልሄድም። ከቤታችን ልክ ከደረጃ ወርጄ በጐን ላይ ጐራ እልና በር እከፍታለሁ በምናብ ማለት ነው። በር እከፍትና ራሴ ከከከ አድርጌ መኪናዬን አስነሣለሁ። ቁልፉን እስከ ሱቅ ድረስ ድምፅ እያወጣሁ "ቩቩ" እያልኩ እሄዳለሁ። ወደ

ሱቅም ዘው ብዬ አልገባም። መኪናዬን አቁሜ፤ ሱካሬን ገዝቼ ስመለስ መኪና አስነሥቼ እና እየነዳሁ፤ ድምፄን እያሰማሁ፤ እየሮጥኩ ነው የምሄደው፡፡ መሃል ላይ ደግሞ ማርሽ እየቀየርኩ “ሃን” እያልኩ ደግሞ ማለት ነው። እና እናቴ ቤት ስደርስ ፈጥኜ ስለመጣሁ ትመርቀኛለች። ሮጬ ሄጃለሁ። ከአካል ጥንካሬም አንፃር፣ ከምናብም፣ ከኃይልም አንፃር አሁን አሁን የገባኝ ማለት ነው። ማታ ማታ ደግሞ ስንተኛ መጀመሪያ ሰሌን አለ። ቀጥሎ የደብረ ብርሃን ብርድ ልብስ አለ። እኔ ብርድ ልብሱን መጀመሪያ የመጀመሪያ አንሶላ ብዬ አነጥፈዋለሁ። ቀጥዬ እሱኑ አነሳና ሁለተኛ አንሶላ ብዬ አነጥፈዋለሁ። እሱኑ አነሳና ብርድ ልብስ አደርገዋለሁ። መልሼ አልጋ ልብስ አደርግና በደንብ እጥፍ አድርጌ እከፍተዋለሁ። ሰዎች ሰሌን ላይ የተኛሁ ይመስላቸዋል። እኔ ግን ምን የመሰለ አልጋ ላይ ከታች አንሶላ ከላይ አንሶላ፤ ወጣቶች አሁን ባላችሁበት ሁኔታ አትያዙ፤ የማሰቢያ ዐቅማችሁን ከአላችሁበት ሁኔታ አሻግራችሁ አስቡ። ሰው ከበሻሻ (በሻሻ ሲባል ሄዳችሁ ካላያችሁ አይገባችሁም፤ እንዲሁ ስታይዋት ድህነትዋ ያስታውቃል እንኳን ኖራችሁባት) ሰው ከእሷ ወጥቶ ያለመውን፣ ያሰበውን ማሳካት ከቻለ፤ ከተያዛችሁበት ጉዳይ ወጣ ብላችሁ ማሰብ ከቻላችሁ መሆን ይችላል።

የሳተላይቱ ጉዳይም እንደዚሁ ነው። መሪዎች በተቀያየሩ ቁጥር በቀላሉ ለመቀበል ቢቸገሩም እኔ ተስፋ አልቆረጥኩም፤ እገፋ ነበር። ለእናንተ ሳተላይት ነው የመጠቀላችሁ፤ ለእኔ ግን እንደ ብርድ ልብሷ፣ ልክ እንደ ድሮ መኪና በማይታሰብ ጊዜ የታሰበ ነገር ተሳክቶ ማየት ስለሆነ ደስታዬ ድርብ ነው፡፡ እና ኢትዮጵያ ትበለጽጋለች፤ እንዳትጠራጠሩ ይሄ የኢትዮጵያ ወቅት ነው። የኢትዮጵያ ጊዜ ነው።

የኢትዮጵያ ወቅት ለመሆኑ ጠዋት ዐቢይ ይሸለማል ከሰዓት ፕሬዚዳንትዋ ይሸለማሉ። ዛሬ ደግሞ የዓለም ምርጥ ፋይናንስ ሚንስትር ተብሎ አሕመድ ሺዴ ተሸልሟል። እና በቃ ነገር ሲዞር እንደዚህ ነው። ወቅቱ ሲመጣ የተረሳ





ሁሉም ይታወሳል። እናንተ በጋ ላይ ሆናችሁ ዝናብ እንደሚለምን ሰው አይደላችሁም። ነሐሴ አጋማሽ ላይ ዝናብ እንደሚጠብቅ ሰው ናችሁ። አሁን ጊዜው የኢትዮጵያና የኢትዮጵያውያን ነው። ይህ ስለሆነ ዐቢይ ቢኖርም ባይኖርም ኢትዮጵያ ትበለጽጋለች፤ የተጀመረው ነገር ይቀጥላል። ይህ ማለት ግን የሚያላዝኑ ውሾች አይኖሩም ማለት አይደለም። ብልጽግናዋን ማቆም ግን አይችሉም። ለምሳሌ፤ በሰሞኑ በአገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ አጀንዳችን ዓሥር ቢሊዮን ዶላር ተጨማሪ ሀብት ወደ ኢትዮጵያ እናመጣለን ብለን ነበር። ይሄ ማለት ኢትዮጵያ አሁን አጠቃላይ ሰማንያ ስድስት ቢሊዮን ጂ.ዲ.ፒ አላት። ዓሥር ከውጪ ከመጣ አንድ አምስቱን ከውስጥ ከአመነጨን በሁለት ሦስት ዓመት ውስጥ መቶ ቢሊዮን ገባን ማለት ነው። መቶ ቢሊዮን ገባን ማለት ከአፍሪካ ከአንድ እስከ አምስት ያለው ብልጽግና፤ ከአፍሪካ ከአንድ እስከ አምስት የተሻለ ጠንካራ ኢኮኖሚ ካላቸው አገራት አንዱ ያልነው ተሳካ ማለት ነው።

አይ.ኤም.ኤፍ ለእኛ እየወሰነ ያለው ሀብት ሰባት መቶ ፐርሰንት ዕድገት አለው። እስከ አሁን ከነበረው ሰባት መቶ ፐርሰንት አንዳንዶች አሁንም ድሮም ብድር ነበረብን፤ አሁንም ብድር እየጨመራችሁብን ነው የሚሉ ሰዎች አሉ። ከአይ.ኤም.ኤፍና ከወርልድ ባንክ መበደር ከእናት እንደ መበደር ነው። እሱ ብድር አይደለም። ምክንያቱም አንድ ቢልዮን ብር ከሰጡን በኋላ በሃያ ዓመት፤ በሠላሳ ዓመት ወለዱም ሁለት ሦስት አራት ፐርሰንት እያረጋችሁ ክፈሉት ማለት ነው። ኢትዮጵያን የጐዳት ከእነዚህ ተቋማት ሳትበደር ከኩባንያዎች ከአንዳንድ አገራት ትበደርና፤ ለምሳሌ፤ ለባቡር ትበደርና ባቡር ተሠርቶ ሳያልቅ ክፍያ አምጪ ትባላለች። አንድ ሃብታም ከባንክ ተበድሮ ሥራውን ሠርቶ ለማትረፍ የሚያበቃ ጊዜ ከአገኘ እና የመሥራት ፍላጐት ከአለው ትርፋማ መሆኑ አያጠራጥርም። ችግሩ ዛሬ መቶ ብር አበድሮ ነገ መቶ ሃምሳ ብር አምጣ ካለ እሱ ብድር ሳይሆን አራጣ ይባላል።

በአማርኛ እና እስከአሁን በነበረው ሁኔታ ወርልድ ባንክ እኛን የሚከሰው ከእኛ ትበደራላችሁ፣ ገንዘቡን ለአራጣ አበዳሪዎች ትከፍሉታላችሁ የእኛን ብድር ልማት ላይ አታውሉትም የሚል ክስ ነበር። አሁን በጀመርነው የኢኮኖሚ ማሻሻያ ፕሮግራም የምናገኘውን ሃብት ልክ እንደ ሰላሙ ተባብረን፣ ጥረን ግረን ከሠራን የኢትዮጵያ ብልጽግና በማያወላዳ መንገድ እውን ይሆናል። በቅርቡ ከበርካታ የኅብረተሰብ ክፍሎች ጋር በተለያየ መድረክ ውይይት ይኖረኛል። በዚያ መድረክ ውስጥ የኢትዮጵያ ብልጽግና የሚፈነጥቅበትን የመጀመሪያውን ብርሃን አሳያችኋለሁ። ዛሬ ብጀምረው ስለማልጨርሰው ድህነትን፣ ረብሻን፣ ብጥብጥን የሚናገሩ ሰዎች አሉ። በዚህ በኩል ደግሞ ተቃራኒዎች አሉ። ሁለታችሁንም አልሰማም።

**ኢትዮጵያ ትበለጽጋለች!**
**አመሰግናለሁ!**



# “የገራ የድል ምዕራፍ ማክበር” የምስጋና መርሐ ግብር ንግግር

ታኅሣሥ 17/2012 ዓ.ም.

እስከዚህ ምሽት ድረስ ስናወራ፣ ስንመለከት የነበረው ስለብልጽግና ብቻ ነበር። ኢትዮጵያ ተስፋ ያላት ሀገር፤ ወደ ብልጽግና የምትጓዝ ሀገር መሆኗን፤ ጊዜ የደረሰላት ሀገር መሆኗን ብዙ ማስረጃ በመጥቀስ ቢያንስ ፕሬዚዳንት ኢሳይያስ አፈወርቂን ማሳመን ችያለሁ። ፕሬዚዳንቱም ሁለት ከባድ ጥያቄ ጠይቀውኛል። ለጊዜው መልስ ሳገኝለት አልቻልኩም። አንደኛው ለምሳሌ፤ ይህ አዳራሽ ባለፉት 30 ዓመታት እዚህ ቦታ ነበረ። ሳናውቀው ሳያውቀን፤ ሳንጠቀምበት ሳይጠቀምብን፤ እንደዚሁ በከንቱ፤ እኛ አንዴ ስካይላት ለስካይላይት ሌላውን አልጠራም ብዬ ነው፤ ስንሽከረከር ቆይተን በመጨረሻ  ሆነን የተሻለ ቦታ ስንፈልግ ይሄንን ድንቅ አዳራሽ በጥቂት ወራት ውስጥ ማዘጋጀት ቻልን። አሁን ሁላችሁም እንደምትገነዘቡት ሽራተን ላሊበላም ሄድን፣ ስካይላይትም ብትሄዱ እንደዚህ ዓይነት የሚያምር ድንቅ አዳራሽ እንደ ሌለ ልባችሁ ስለሚያውቀው፤ እና ፕሬዚዳንት ኢሳይያስ “ይህንን አዳራሽ ሠርታችሁት ነው ወይ?” ሲሉን “አልሠራነውም እዚሁ ነበረ ግን ወደዚህ መልክ ቀይረነው ነው” አልናቸው። “እንዴት እስከአሁን የነበሩ

ሰዎች ይህንን ነገር ማየት ተሳናቸው?” አሉን። ይህን ብቻ አይደለም ብዙ ነገር አይተናል፤ ያየነው ነገር በሙሉ የነበረ ነው አዲስ የፈጠርነው ነገር የለም። ግን በአዲስ መልክ ስለአየነው ሁሉም ውብ ድንቅ ሆኖ አንዳንዶች አጠገባቸው ምንጭ እንዳለ ማየት ተስኗቸው፤ ምንጭ እንዳየችው አጋር ማለት ነው ለሚገባችሁ፤ በዚያ መልክ እንዴት ማየት ተሳናቸው የሚለውን ጥያቄ መመለስ አልቻልኩም በጋራ እንመልስላቸዋለን።

ሁለተኛው ከባድ ጥያቄ፤ “ራእይህ ገብቶኛል፣ ወደ ብልጽግናም እንደምትሄዱ አምኛለሁ። ግን እንዴት አድርገህ ነው ኢትዮጵያውያንን ማሳመን የምትችለው?” አሉኝ። ይሄም በጣም ከባድ ጥያቄ ነው። ኢትዮጵያውያን ሰምተው ብቻ ሳይሆን አይተውም ለማመን ስለሚቸገሩ ማለት ነው። ከእዚህ አቧራ በእንደዚህ ዓይነት መንገድ መጠቀም ከሚያስቸግር ቦታ ድንቅ አዳራሽ መሥራት ከቻልን፣ አዲስ አበባን በሚቀጥሉት ሦስት ዓመታት ምን እንደምናደርጋት አብረን እናያለን። በሚቀጥሉት ሦስት ዓመታት አዲስ አበባን ቢያንስ በአፍሪካ በምንም መመዘኛ ትልቁ የቱሪስት መስህብ ከተማ ማድረግ የምንችልበትን ሁኔታ ከታችኛው ቤተ መንግሥት ጀምሮ፤ ይሄኛውን ቤተ መንግሥት፣ ፓርላማውን፣ ከፍ ብለን የኢሕአዴግን ቢሮ ለሕዝብ ክፍት ብናደርግ እና ይሄ የስብሰባ ማዕከል ቢሆን፤ እኔ የምኖርበት ቤት የጣልያን ሬስቶራንት ቢሆን፤ ሌላው ቪላ የፈረንሳይ ሬስቶራንት ቢሆን፤ ከአራት ኪሎ እስከ አሜሪካን ኤምባሲ የገንዘብ ሚኒስቴር፣ የባህል ማዕከል፣ የፕላን ኮሚሽን፣ ክብርት ወ/ሮ መዐዛን - ፈራሁ - የሳቸውን ጨምሮ መንግሥት ካለአግባብ አስፋፍቶ የያዛቸውን ቦታዎች የዩኒቨርሲቲ ሲቲ ብለን ሙሉ በሙሉ የዩኒቨርሲቲ ከተማ ብንፈጥር፤ ከአሜሪካን ኤምባሲ እስከ እንጦጦ ድረስ ድንቅ ቦታ ብንፈጥር፤ እስከሚቀጥሉት ሦስት ዓመታት ቢያንስ ድንቋን የቱሪስት መስህብ ኢትዮጵያን መፍጠር እንደምንችል ፕሬዚዳንት ኢሳይያስ አምነዋል። እሳቸው እናንተን ያሳምኗችሁ።



ባለፈው ስንገናኝ ብዙ ጊዜ የምናወራው ስለ ጦርነት እና ስለ ሰላም ነበር። ጦርነት እና ሰላም ብዙ ሰዎች ሲደግሱ፣ ሲያቅዱ፣ ሲዘጋጁ የሚገድሉ፣ የሚቀጡ እንጂ የሚቀጡ አይመስላቸውም። ነገር ግን በኢትዮጵያ እና በኤርትራ መካከል በነበረው ጦርነት በብዙ የተቀጣን መሆናችንን ሁላችንም በውል እንገነዘባለን። ኢኮኖሚያችን ደቅቋል። ወጣቶች፣ አዛውንቶች ተጎድተዋል። ጎረቤት ሕዝቦች ተጎድተዋል። አንዳች ጥቅም አልተገኘበትም። ከዚህ ጉዳት መማር ያልቻሉት ሰዎች በአለፉት ጥቂት ወራት በኢትዮጵያ ውስጥ መጀመሪያ የብሔር ግጭት ጀመሩ። አልተሳካም፤ ከሸፈ። ቀጥለው በየዩኒቨርሲቲው ግጭት ጀመሩ። አልተሳካም፤ ከሸፈ። አሁን በየሀይማኖት ተቋማት ግጭት ጀምረዋል። ዛሬ በድጋሚ አረጋግጥላችኋለሁ ይከሽፋል። ይሄ የኢትዮጵያ የብልጽግና ወቅት ስለሆነ በጣም ብዙ ሊያደናቅፉ የሚችሉ ኃይሎች ቢኖሩም ዕይታችንን ከብልጽግና እስከአላነሣን ድረስ ማጥፋት የሚፈልጉ ኃይሎች አይሳካላቸውም። እኛ ወደ ብልጽግና እንጓዛለን። ግን አደራ የምላችሁ ነገር እነዚህ የሚያበላሹ ሰዎች ሲሠራ ደግሞ ሐሳብ መስረቅ ይችላሉ። ትንሽ ቆይተው የዚህ አዳራሽ እድሳት ሐሳብ የእኛ ነው እንዳይሉ፤ ከወዲሁ ፍራቻዬን እየገለፅኩ ብልጽግናችን ይቀጥላል። ሰላማችን ይቀጥላል። እንፈተናለን፤ መሥዋዕትነት እንከፍላለን፤ እንደክማለን፤ የኢትዮጵያን የወደፊት ዕጣ ፈንታ ብሩህ እናደርጋለን። ከዚህ ሊያቆመን የሚችል አንዳች ኃይል እንደ ሌለ ብዙ ጊዜ ብያለሁ፤ አሁንም እደግምላችኋለሁ ከንቱ ሙከራ ነው የብልጽግና ጉዞ አይደናቀፍም ።

ፕሬዚዳንት ኢሳይያስ እንኳን ወደ ሁለተኛ ቤትዎ በሰላም መጡ። የኢትዮጵያ የሀይማኖት አባቶች፣ ባለሀብቶች፣ ታዋቂ ሰዎች ከሁሉም ጫፍ እዚህ አዳራሽ ይገኛሉ። ለእርስዎ ስለአላቸው ፍቅር ፊታቸው ስለሚናገር ብዙ ማለት አይጠበቅብኝም። በኢትዮጵያ እና በኤርትራ መካከል ሰላም ከጀመርን ወዲህ በብዙ መልክ የኢኮኖሚ ትስስር ጀምረናል። ቢያንስ ቴሌኮምን እንደምሳሌ ብንወስድ፤ ባለፈው ዓመት ከ 4.5 ሚሊዮን ዶላር በላይ በቴሌኮም ሴክተር

ብቻ በሁለቱ አገራት መካከል የንግድ ልውውጥ ተካሂዷል። በአየር መንገድ ትንሽ ከፍ ያለ ነው። እኔ ከተናገርኩ ባለቤቱ ስለአሉ ስለሚቆጡ፣ በብዙ መልክ የጀመርነውን የሀብት ልውውጥ እያሰፋን በጋራ ለማደግ፤ በጋራ ለመበልጸግ እንደ ሁለት ነገር ግን፤ እንደ አንድ ሕዝቦች አብረን የምንተጋ እንሆናለን። ስለመጣችሁ እናመሰግናለን! ስለ አዳራሽ ምርቃት እናመሰግናለን! ወደፊት ጳዳ ያለ ግብዣ ያለው ሰው ካለ፤ ወደድ ያለ ገንዘብ እየከፈለ እዚህ ግብዣ ማከናወን ይችላል። ያው እንደምታውቁት የብልጽግና መሪ ጥሩ ነጋዴ ማለት ነው። ገንዘብ ነው የምናነፈንፈው ከውስጥም ከውጭም፤ በቅርቡ በሀገር በቀል ማሻሻያ አጀንዳችን 10 ቢሊዮን ዶላር ያህል ማሰባሰብ ችለናል። ገንዘብ ያለው ወደ እኛ መምጣት ይችላል። እኛ ደግሞ ወደ ብልፅግና እንጓዛለን።

## አመሰግናለሁ!



# “የወዳጅነት አደባባይ” የሥራ ክንውን ጉብኝት ንግግር

ታኅሣሥ 22/2012 ዓ.ም.

ይህ የፍሬንድሺፕ ስኲዌር ወይም የወዳጅነት አደባባይ ያልነው ቦታ እንደምታስታውሱት የዛሬ ሦስት ወር ነው የተጀመረው፤ በሦስት ወር ውስጥ ይህንን የሚያክል ሥራ አይጠበቅም። አንደኛው፤ በመንግሥት የማስፈፀም ሥራዎች ውስጥ ያየነውን ችግር የቀረፈ ሥራ ነው የተሠራው። ይህ ፕሮጀክት እንጦጦ ላይ የምንሠራውን ሥራ፤ አንድነት ፓርክ ላይ የምንሠራውን ሥራ፤ እንዲሁም ከእንጦጦ እስከ ፒኮክ ያለውን የወንዞች ፕሮጀክት የሚያገናኝ እና የአዲስ አበባን ገፅ በየዕለቱ የሚቀይር ፕሮጀክት ነው።

እንግዲህ በብልጽግና ጉዞ ዘመናችን አንዱ ማረም የምንፈልገው ነገር የምናስበውን መጻፍ፤ የምንጽፈውን ኮሙኒኬት በማድረግ ለሕዝብ እና ሀገር የተናገርነውን ፈፅመን መገኘት ነው። ከዚህ አንፃር ይህ ፕሮጀክት ለብዙ ሥራዎቻችን አርአያ ተደርጎ የሚወሰድ ነው። በኢትዮጵያ ውስጥ በዚህ ፍጥነት ሥራ ተጀምሮ ሲጠናቀቅ እምብዛም አናይም። ነገር ግን ይሄ በጣም ሰፊ ሥራ ነው። 47 ሄክታር ገደማ ነው። ብዙ ሬስቶራንቶች የቡና መጠጫ

ቤቶች፤ የሚያምሩ ቦታዎች አሉት። ግን ሥራው በሦስት ወር ውስጥ 45 በመቶ ደርሷል። በሚቀጥለው ግንቦት ሙሉ በሙሉ ክፍት ይሆናል። ጥብቅ ክትትል ይደረግበታል።

እንዲሁም፤ የእንጦጦውን በዚህ ጊዜ ጨርሰን መሀል ላይ የሚቀረን ከእንጦጦ እስከ ፒኮክ ያለው 12 ኪ.ሜ የወንዝ ዳር ፕሮጀክት ይሆናል። በሚቀጥለው ዓመት የምንሠራው ማለት ነው። ከዚህ አንፃር በጣም ጉልበት የሚሰጥ የሚያስደስት ነገር ነው። ሁላችሁም እንደምትገነዘቡት “አዲስ አበባን እውነተኛ አዲስ አበባ እናደርጋታለን፤ እንደ ስሟ አዲስ አበባ ትሆናለች” ካልን በኋላ የአፍሪካ ካፒታል መሆኗን ለማረጋገጥ ሰፊ ሥራዎች እየተሠሩ ነው። ዛፍ መትከል፣ ማጽዳት፣ ፓርኮች ማስፋት፣ ይህንን ሥራ በሚቀጥሉት ሦስት ዓመታት ወደሚቀጥለው ደረጃ ከአሳደግነው ሙሉ በሙሉ የአንድነት ፓርክ ግቢውን ከያዘ፤ ይሄ ሥራውን ጨርሶ ለሕዝብ ክፍት ከሆነ፤ በቦሌ መንገድ ላይ የጀመርነውን ሥራ ከአሣለጥን እና እስከ እንጦጦ ከወጣን፣ ያለ ምንም ጥርጥር በየትኛውም የአፍሪካ አገር በዚህ ደረጃ የቱሪስት መስብ መሆን የሚችል ታሪክ ያለው፤ ዛፍ ያለው፣ እጅግ የሚያምር የአየር ጠባይ ያለው እና መልከአ ምድሩ የተለየ ውበት ያለው ቦታ ያለ አይመስለኝም። ካለም ለእኔ አንደኛው ቦታ ይሄ ነው።

አዲስ አበባን ድንቅ ከተማ ማድረግ ይቻላል። ይህ እንዲሆን ግን “አዲስ አበባ የእኛ” የሚሉ ኃይሎች ሁሉ ዛፍ በመትከል፣ በማጽዳት፣ ይህንን ቦታ በመጠበቅ አርአያ መሆን አለባቸው። እኛ አዲስ አበባ የእኛ መሆኗን የምናረጋግጠው በሥራ ብቻ ነው። ሌላ ማረጋገጫ መንገድ የለም። በመሥራት፣ በማጽዳት፣ በማልማት፣ በመቀየር፣ የሰዎችን ኑሮ በማሻሻል፣ ሥራ አጥነትን በማሻሻል ብቻ ነው ለአዲስ አበባ ተቆርቋሪ መሆን የሚቻለው። እና እዚህ ቦታ እንደምታዩት ዛሬ አንድ ሺሕ 300 የሚሆኑ የኢትዮጵያ ወጣቶች እየሠሩ ነው። ከሁለት ወራት በኋላ አራት ሺሕ ሰው ይቀጠራል። ይህንን ነው እኛ የምንፈልገው።





ሥራ መፍጠር፤ ሥራ ከፈጠርን በኋላ ከተማው የቱሪስት መስህብ እንዲሆን ለሥራ አጦች አዳዲስ ሥራ ለመፍጠር የሚያመች እንዲሆን ነው።

እዚህ ዘንድ የሚሠሩት ሕንጻዎች ሲሠሩ ይሄ ነገር አልነበረም። አሁን ይሄ በመሠራቱ ብቻ እያንዳንዱ ሕንጻ ሸራተንን ጨምሮ በከፍተኛ ደረጃ ዋጋው ከፍ ይላል። ሸራተን የሚመጡ እንግዶች ያለምንም ችግር የሚዝናኑበት ቦታ አላቸው ማለት ነው። ይህ ሥራ እንዲከናወን የቻይና መንግሥት ሙሉ ወጪውን ያገዘ ሲሆን፤ በተለይ በኢትዮጵያ የቻይና አምባሳደር እና የቻይና ካውንስለር ሚስስ ዲው ሁለቱ ሰዎች በተለየ ሁኔታ በየሳምንቱ ክትትል እያደረጉ፣ ሲ.ሲ.ሲ የተሰኘው የቻይና ኩባንያ ፕሮጀክቱን ሙሉ በሙሉ እያከናወነ ይገኛል። ለዚህም የቻይናን ኤምባሲ፣ ኩባንያውን እና የቻይናን መንግሥት ላመሰግን እወዳለሁ። ከሦስት ወር ወይም ከአራት ወር በኋላ ተመልሰን እንገናኛለን። ለአዲስ አበባ የብልጽግና ዘመን ፀሐይ እየወጣላት ነው። ይህንን ፀሐይ ወደ ሌሎች ከተሞች ማስፋት ይጠበቅብናል። ወደ መቀሌ፣ ወደ ባሕር ዳር፣ ወደ ጅማ፣ ወደ ነቀምት፣ ወደ አምቦ፣ ወደ አርባ ምንጭ፣ ወደ ሐዋሳ እያሰፋን ከሄድን እና ዓሥር እና ዓሥራ አምስት ከተሞች ካሉን በቀላሉ ከቦታ ቦታ ተንቀሳቅስን ለመዝናናት እና ቱሪስት ለመሳብ እንዲሁም ገቢያችንን ለማሳደግ፤ በኢትዮጵያ ውስጥ እውነተኛውን ብልጽግና ለማየት ዕድል የሚሰጥ ስለሆነ ለሁላችንም እንኳን ደስ አለን! በጣም የሚያበረታታ ሥራ ነው። እናንተም በየወሩ እየመጣችሁ ያለውን ዕድገት ሪፖርት ብታደርጉ ከሞያ አንፃር ተገቢ ይመስለኛል።

**በጣም አመሰግናለሁ!**

# የኮንስትራክሽን ዘርፍ የንቅናቄ መድረክ ንግግር

ታኅሣሥ 23/2012 ዓ.ም.

ቅዝቃዜያችሁ እኔንም ቀዝቀዝ አድርጎኛል። ዛሬ እንደተገናኘን አይቆጠርም። ወደ ሚሊኒየም አዳራሽ እየሄድኩ ነው ጎራ ያልኩት፤ የቀብድ ጥያቄ ስለአላችሁ ለእኔም እንደቀብድ ይያዝልኝና ግማሽ ቀን ጊዜ ወስደን እንወያያለን። ከዘርፉ ጋር የምንወያየው ነገር አለ። አልሞላላችሁም። በእናንተ ምክንያት አልተገናኘንም። ሚሊኒየም አዳራሽ እየሄድኩ ያለሁት ወጣቶች ዘንድ ነው። 10 ሺሕ ገደማ ወጣቶች ይጠብቁኛል። መድረኩ የተዘጋጀበት ምክንያት ብልጽግና ማለት የዕውቀት፣ የማድረግ ዐቅም እና የንዋይ ጋብቻ ነው። ንዋዩ ዕውቀት ከሌለ፤ ዕውቀት ኖሮም የማድረግ ዐቅም ጉልበት ከሌለ ብልጽግናን ማረጋገጥ አይቻልም። ስለዚህ ንዋይ ከፋም ለማም ያለው እዚህ ነው። ጉልበት ወዳለው ሲሄድ ምናልባት የሚገናኝበት ዕውቀት መሀል ላይ ከተሸመተ፣ ከማልፍ ጎራ ብዬ ልሸምት ብዬ ነው የመጣሁት። በብልጽግና ዘመን ውስጥ የእናንተ ሚና ከፍተኛ ነው። ብዙ ጥያቄ እንዳላችሁ አውቃለሁ። ብዙ ተግዳሮትም እንዳለባችሁ አውቃለሁ። የውጭ ምንዛሬ ጥያቄ እንዳላችሁ አውቃለሁ። የገንዘብ ግሽበት ጥያቄ እንዳላችሁ አውቃለሁ ። በኮንትራት ላይ የሚገጥሟችሁን ችግሮች እንደምታነሡ አውቃለሁ። ያ ችግር ባይኖር ኖሮ ብልጽግና ምን ያደርጋል ነው መልሱ፤ ብልጽግና የተወለደው ችግር ስለአለ ነው። በእያንዳንዱ የሥራ መስክ አብሮ በመኖር ሂደታችን አብሮ መሥራት ላይ፣ ኮንትራት ላይ፣ ስምምነት ላይ በርካታ ችግሮች ስለአሉብን ነው በብልጽግና አስተሳሰብ "እንዴት እንፍታው?" የሚለው የሚወለደው። እና ችግር እንዳለባችሁ የማይታወቅ አድርጋችሁ አትውሰዱት።

ችግሮቻችሁን አውቃለሁ። ኢንዱስትሪውን እንደምታውቁም አውቃለሁ። የዓለም መንግሥታት ስለ ዕድገት ስለ ብልጽግና የሚያወሩት 70 እና 80 ፐርሰንት እናንተን ተማምነው ነው። አንዱ የብልጽግና እና የዕድገት ምልክት ከተሜነት ነው። ሰው ዱባይን የሚያደንቀው የተፈጥሮ ሀብት፣ ተራራ ስለአለ አይደለም። ታውቃላችሁ አረንጓዴ ቦታም ስለአለ አይደለም። ከተሜነት እየተባለ የዓለም መንግሥታት የሚያውጁት የእናንተ የእጅ ሥራ ነው። ሁለተኛ፤ እርሻም ቢሆን ጎተራ ያስፈልገዋል። እርሻም ቢሆን ወጥቶ ለመሸጥ መንገድ ያስፈልገዋል። ግብአት ለማግኘት መንገድ ያስፈልገዋል። ሱቆች ያስፈልጉታል። እነዚያን ሁሉ እናንተ ከአልገነባችሁ እርሻም አይዘምንም፤ አይሣለጥም።

አግሮ ኢኮኖሚ የሚባል፣ ማኑፋክቸሪንግ የሚባል፣ ይሄ ሂውማን ካፒታል ነው ቢባልም ትምህርት ጤና ያለ ግንባታ ሙሉ መሆን አይችልም። ግንባታ ትኩረት አግኝቶ ካልተመራ በስተቀር ብልጽግናን ማረጋገጥ እንደማይቻል በግልፅ ይታወቃል።

ከዚያ በላይ ግን በኢትዮጵያ ትልቁ ችግር በምናብ የማሰብ ኃይል፤ አስቀድሞ አንድን ነገር የማየት ዐቅም ውስንነት ነው። የኢማጅነሪ ፓወር ውስንነት እስከ አሁን ባለው፤ ወደፊትም ሊቀንስ የሚችለው በእናንተ ሴክተር ብቻ ነው። እናንተ ይሄ ሕንጻ ሳይሠራ ሕንጻውን በጭንቅላታችሁ ሠርታችሁ

ሰዎች በአስቀመጣችሁት ምናባዊ ሥዕል መልክ ግንባታ እንዲገነቡ ማድረግ ትችላላችሁ። ልክ ለአንድ ሕንጻ፣ ለአንድ መንገድ ማለም እንደምትችሉት፤ ለአንድ አገርም መተለም፣ ዲዛይን ማድረግ ቢያንስ ለእናንተ ይቀርባል። እኛ አካባቢ ሲሆን ቢያንስ ለዓሥር ዓሥራ አምስት ዓመት ስንል አንደኛ ጥንቅቅ ያለ አይደለም። ሕንጻውን ሠርተን በር የለውም። ሕንጻውን ሠርተን መጸዳጃ የለውም። ምክንያቱም ዲዛይኑን ስንሠራ ልምዱ ስለሌለ ማለት ነው። ጂ.ቲ.ፒ 1፣ 2 እንልና ከላይ በጣም የሚያምር ሕንጻ እናስቀምጣለን። ግን መውጫ መግቢያ በር ስለማንሠራለት ቤቱ ቢገነባም አገልግሎት የሚሰጥ አይሆንም። እናንተ ግን ታያላችሁ። መስኮቱ የት መቀመጥ እንዳለበት፤ ላይኛው ሽንት ቤት እና የታችኛው ሽንት ቤት ቦታቸው ቢለያይ እንዴት ሊገናኙ ይችላሉ በሚል በጥልቀት ስለምታዩ ቢያንስ በአሰባችሁት እና በዲዛይናችሁ መካከል ሰባ ሰማኒያ በመቶ ቅርርብ ይኖራል።

በእርግጥ ዲዛይነር ያሰበውን ያክል ማስቀመጥ ይቸገራል። አልመጣልኝም እያለ ይሠቃያል። ከመጣለት በኋላም አንዳንዴ ገንቢው ፊቱን ወደ ኋላ አዙሮ ይገነባበታል። ይሄ ችግር በኢትዮጵያ ውስጥ የተለመደ ስለሆነ ታውቁታላችሁ ብዬ ነው። ቢሆንም ግን አስቀድሞ የማለም ብቃት ያለው ይብዛም ይነስም እናንተ ጋ ነው። በዓሥር ዓመት የብልጽግና ዕቅዳችን ውስጥ የእናንተ ንቁ ተሳትፎ የሚያስፈልገው ለዚህ ነው። “ሙሉ ነው ወይ? ፍላጎት ራእይ ብቻ ነው የያዘው? ወይስ ራእዩን ከፋፍሎ መተግበር የሚያስችል ዝርዝር ትልም አለ?” የሚለውን ከእኛ የተሻለ ማሰብ ትችላላችሁ። በዚህ ምክንያት ይህንን ሴክተር ሳንይዝ ብልጽግናን ማረጋገጥ እንደማንችል እናውቃለን።

ይሄ ሴክተር አዳጊ ነው። በጀመራችሁት የሚያቆም አይደለም። ለምሳሌ፤ የዩኒቲን ፓርክ እንደምሳሌ ብወስድላችሁ፤ የፕሮጀክት ማናጀር ሆኜ የሠራሁበት አንዱ እሱ ስለሆነ ዩኒቲ ፓርክ ከ18 ሀገር የተውጣጡ ዲዛይነሮች ናቸው ዲዛይን ያደረጉት። የአንድ አገር ዜግነት የሌላቸው የካናዳ፣ የፈረንሳይ፣ የማሌዥያ፣ ኢንዲያ የብዙ አገራት ሞያተኞች መጥተው፤ ናሙና ወስደው፣ ጊዜ ወስደው፣ ዲዛይን አድርገው፤ ኩባንያዎች ሥራውን ሰጥተው ዲዛይን ተነጋግረን ተጨቃጭቀን ሄዱ። እነሱ ከሠሩት በኋላ የመሬቱን አቀማመጥ ሉብቻ ብንወስድ ፍሳሽ ማስወገጃ አልነበረውም። መብራት አልነበረውም። በጣም ብዙ ሞያተኞች ናቸው የሠሩት። እነሱ የሚያውቁት በመካከለኛው ምሥራቅ አካባቢ ያለውን ልምምድ መሰለኝ። እኛ ጋ ያለው የዝናብ ችግር አልገባቸውም። እኛም ስናስመርቅ እንደምታውቁት ግንቦትና ሰኔ ዝናብ ነበር። ዘንድሮ ዝናቡ ሲመጣ ግቢው ጭቃ በጭቃ ሆነ። እነዚያን የሚያክሉ ሞያተኞች ጠንቅቀው ማሰብ ስለአልቻሉ በአካባቢው ሰዎች መሠራት ነበረበት። መብራት መሠራት ነበረበት። የፍሳሽ ማስወገጃው ሲሠራ የበቀለ ሳር እየቆረጥን ቱቦ ስለገጠምን ሳሩ ተበለሻሸብን። ያንን ለመደበቅ ብለን ነጭ አሸዋ፤ የማርብል ስብርባሪ ዳር ዳሩን ስንረጭ ሌላ መልክ ሰጠው። ዲዛይኑን ቀየረው ማለት ነው።

ከአስመረቅን በኋላ ብዙዎቻችሁ ደጋግ ሀብታሞች ነበራችሁ። የአምስት ሚሊዮን ራት ሁላችሁንም አይመለከትም። ንፉግነታችሁን በአገኘነው አጋጣሚ ሁሉ ማስታወስ ስለሚገባን ነው። ያን ዕለት ሲመረቅ ያላየነው ክፍል ደግሞ ነበር። ይሄ ጥቁር አንበሳ ያለበት ዋሻ በመጀመሪያው ዲዛይን አልነበረም። ሲመረቅም አልነበረም። በኋላ አጋጣሚ ፒኮክ ላይ የሚሠራው ሥራ በጣም ጥሩ ስለነበረ “እንይ” ብለው አንድ ቀን እሑድ ወሰዱኝ እና ሳይ በጣም ጥሩ ስለነበረ “የዚያን ሻል አድርገን እኛ ግቢ እንሥራ” ብለን፤ የአካባቢ ሰዎች ናቸው 100 ፐርሰንት ዲዛይን ያደረጉትም፤ የሠሩትም።

እነርሱ ከሠሩ በኋላ ትክክለኛ የዱር እንስሳት ማቆያ ፕላን ነበረው። ግቢው አሁን አልቋል፤ ማየት ትችላላችሁ። የመጨረሻው ምዕራፍ ላይ ስለሆነ ያ የዱር እንስሳት ማቆያ ፕላን ትንሽ የሳፋሪ መልክ እንዲኖረው ብለው ክፍታ ክፍት አድርገውታል ግን ግንባታው እንዳለ ይታያል። የእኛዎቹ ገብተው ያንን ዋሻ

ከሠሩ በኋላ የመጨረሻው የማስዋብ ሥራ የእኛ ስለሚሻል በሙሉ ዋሻውን፤ በሌላኛው ጫፍ ያለውን የዱር እንስሳት ማቆያ በሙሉ የሚታየውን ግንባታ፤ ከእኛዎቹ ልጆች የመጨረሻውን ግንባታ ወስደው ለእነርሱ ሰብ ኮንትራት ሰጥተው በእነርሱ አሠሩት።

በየቀኑ አንዱ ከአንዱ እየተማረ፤ አንዱ ከአንዱ እየገለበጠ ነው አሁን ያለውን መልክ የያዘው። ጨርሶ ማሰብ፤ ጨርሶ ማለም አልተቻለም። ምንም እንኳን የብዙ አገር ሞያተኞች የተሳተፉበት ቢሆንም፤ ብዙ በተግባር ሥራ ውስጥ ልምምድ እና ዕውቀት መሸመት ይጠይቅ ነበር። አሁን በዚያ ውስጥ ያለፉ ሰዎች በዚያ ውስጥ የነበረውን ስሕተት ቀንሰው ሊሠሩ እንደሚችሉ ይጠበቃል።

የእናንተን ዘርፍ በሚመለከት ዝርዝር ውይይት ማድረግ እንደሚጠበቅ ሆኖ ከውጭ ምንዛሪ ጋር ያለባችሁ ችግር በተደጋጋሚ የሚነሣው እኔ ብዙ ችግር አድርጌ አልወሰደውም። ምክንያቱም የውጭ ምንዛሪን እንደችግር የማያነሣ ዘርፍ እና መንግሥት ስለሌለ። በእኛ በየቀን ሥራችን ውስጥ፤ በየዕለት ሥራችን ውስጥ የውጭ ምንዛሬ ችግር ይነሣል። ለምንድነው? ኤክስፖርት አናደርግም።

ኤክስፖርታችን ውስን ስለሆነ ብዙ የውጭ ምንዛሪ ገንዘብ አናገኝም። እናንተ ቢቸግራችሁ የሚገርም አይደለም። ከእናንተ የሚጠበቀው ኢማጅነሪ ፓወር ተጠቅማችሁ "እንዴት ነው እርሻው ዘምኖ፤ ኤክስፖርት አድርገን፤ የውጭ ምንዛሪ አድጎ፤ የእኛም ሴክተር የሌላውም ሴክተር ችግር የሚፈታው?" የሚለውን እንድትነግሩን እንጂ የምናውቀውን ችግር እንድትነግሩን አንፈልግም። ሁለት እና ሦስት ቢሊዮን ወደ ውጭ ሸጠን 15 እና 20 ቢሊዮን ፍላጎቶች ስለአሉ ማለት ነው። እንዴት እንፍታው? ላይ ነው ማተኮር የሚጠበቅባችሁ።





ሁለተኛው፤ አነሣሣችሁን አትርሱ፤ ግን ደግሞ እዚያው አትኑሩ! እዚያው የምትኖሩ ሰዎች ችግር እያጋጠመ ነው። ለምሳሌ፤ ፒክአፕ አትቁጠሩ፤ እኔ ሰባ ፒክአፕ አለኝ፤ ሰማኒያ ፒክአፕ አለኝ አትበሉ። ከዚያ ወጥታችኋል። እናንተ በርግጥ ስትጀምሩ አንድም ፒክአፕ አልነበራችሁም። ሰባ መድረሱ ደስ ይላል። ግን አሁን ሰባ ፒክአፕ አለኝ፤ ሰማኒያ ፒክአፕ አለኝ እያለ የሚቆጥር ኮንትራክተር የኢትዮጵያን ብልጽግና ሊያረጋግጥ አይችልም። አንተ ከፒክአፕ ቆጠራ ወጥተሀል። የቤት ችግር የለብህ፤ የከረባት ችግር የለብህ፤ የመኪና ችግር የለብህ፤ የአንተ ሚና በጋራ አስበህ ከድህነት ወለል በታች ያለን 25 ሚሊዮን የኢትዮጵያን ሕዝብ ማውጣት ነው። ፒክአፕ ከቆጠርክ አታደርገውም። ሰባውን ሰማኒያ፤ ሰማኒያውን ዘጠና ስለምትል፤ አብዛኛው ኮንትራክተር የነበረበትን አለመርሳቱ ጥሩ ሆኖ ከዚያ እያወዳደረ ሀብቱን ስለሚለካ ብዙ ርቀት አልሄደም። አልገባችሁም። ቢገባችሁ ኖሮ በጣም ትስቁ ነበር።

ሁለተኛው ሐሳብ ከዚህ ጋር የሚያያዝ ነው። ለምሳሌ፤ ኤክስ የሚባል ኩባንያ ራሱ ጀምሮ፣ ለፍቶ፣ ጥሮ ዛሬ በጣም ብዙ ሥራ የሚሠራ አንድ ቢሊዮን ብር ያለው ኩባንያ ከአለ፤ ሌላ ዋይ የሚባል ኩባንያ ከአለ፤ እሱም እንዲሁ ያደገ ከሆነ እነዚህ ሁለት ኩባንያዎች ሽርክና መሥርተው፤ ከቻይና ጋር ብቻ ሳይሆን እርስ በእርስ ተጣብቀው ሥራቸውን ሞያዊ ማድረግ አለባቸው።

ለምሳሌ፤ በገምሹ በየነ እና በሲሳይ አፍሮ ጽዮን መካከል ያሉ ኩባንያዎች ሁለቱ አንድ ሆነው፤ ፕሮፌሽናል ማናጀር ተቀጥሮ በአግባቡ ቢሠራ ሦስት፣ አራት፣ አምስት ብትጨምሩ አንደኛ መደመር ማለት እሱ ነው። ያልተደመረ ስለማያድግ፤ ሁለተኛ፤ ከፒክአፕ ቆጠራ የምትወጡት እንደዚያ ከሆነ ብቻ ነው። "የእኔ" የሚል እሳቤ ካለ አታድጉም። ወደዚያ የምትሄዱ ከሆነ፤ ሦስት አራት ኩባንያ አብሮ ሆኖ ተለቅ ያለ ኩባንያ የሚፈጥር ከሆነ፤ እኛም በተለየ ትኩረት እነዚህን ኩባንያዎች እናግዛለን። ለምን? እንደዚያ ዓይነት

ጠንካራ ዐቅም ያላቸውን ኩባንያዎች ስለምንፈልግ፤ የግለሰብ ኩባንያ ሲሆን የሚቀጥረው ከሰፈሩ ነው። የሚገዛው ከሰፈሩ ነው። ሲቃጠልም እንደዚያ ነው የሚሆነው። ኩባንያ ሲሆን ዘለዓለማዊ ይሆናል። ኢትዮጵያዊ በሚሆንበት ሰዓት የትም ቦታ ቢንቀሳቀስ እና ቢሠራ የሚጠቀመው ሐሳብ ያለው፤ የሥራ ሰው ቢሆንም የእንትና ኩባንያ የሚል ስም ይቀንሳል። ይሄን ማሰብ ይኖርባችኋል። ይሄንን አድርጋችሁ እንውጣ፤ ወደ ጅቡቲ እንሂድ፤ ወደ ኬንያ እንሂድ፤ ወደ ሱዳን እንሂድ።

እንደምታውቁት እዚህ ሴክተር ላይ ብቻ የሚመደበው በጣም ብዙ ሀብት ነው። መንገድ ላይ ብቻ የመደብነው 47 እና 48 ቢሊዮን ብር ነው። ይሄ ሁሉ ሀብት እናንተን አሳድጎ፤ አጠናክሮ ከኢትዮጵያ ወደ ሌሎች አገራት የማይወስደን ከሆነ የእናንተ ዕድገት በመጨረሻ ችግር ይፈጥርብናል። ዕድገታችሁ የማይቋረጥ እንዲሆን ሰብሰብ ያለ ዐቅም መፍጠር ይኖርባችኋል። ያንን ስታደርጉ መንግሥትም እናንተን ለመደገፍ በተለየ መንገድ ይሠራል።

ከውጭዎቹ ጋር በምክክር ደረጃ የጀመርነው ነገር አለ። መቶ ፐርሰንት በኢትዮጵያ በጀት የሚሠሩ በግልጽ ጨረታ የሚሠራ ነገር ሲኖር ጉዳቱን እያጠናን ነው። ከአሁን በኋላ የምናደርገው ነገር ቢኖር ሙሉ በሙሉ በጀቱ በእኛ በሚሆንበት ሰዓት ቢያንስ ከኢትዮጵያ ኩባንያ ጋር ሽርክና መሆን እንደቅድመ ሁኔታ እንወስዳለን። ምክንያቱም የእኛ ሀብት እዚሁ ዐቅም እየፈጠረ የሚሄድበት መንገድ ፍላጎት አለን።

በሌላ መንገድ በአገር አጠቃላይ ዕድገት እና ኢኮኖሚያዊ ጉዞ ውስጥ የእናንተ ዘርፍ ከፍተኛ ጫና እያመጣ መሆኑን ብታስቡ ጥሩ ነው። ለምሳሌ፤ የዓለም ባንክ ከሚያበድረን 100 ብር ሰባት ብር ብቻ ነው ለልማት የምትጠቀሙት፤ ዲስፐርስመንት ሬሾ 7 በመቶ ነው የሚል ክስ አለ። እናንተ መንገድ ትይዛላችሁ። ለሦስት ዓመት ይባላል። ስድስት ዓመት ሲዘገይ ገንዘቡ አይለቀቅም፤ ወይም





ሥራ ላይ አይውልም። ያንን ባለማድረጋችን ተጨማሪ ሀብት ማግኘት ሲገባን እናጣለን። አሁን ዲስፐርስመንት ሬሾአችሁ 30 እና 40 በመቶ ቢሆን እስከ ግማሽ ሚሊዮን ዶላር በጀት እንለቅላችሁ ነበር። ግን በጣም ዝቅተኛ ነው የሚል ክስ አላቸው። ይህ አብዛኛው መንገድ ላይ፤ የኢንደስትሪ ፓርክ ላይ፤ ከኮንስትራክሽን ጋር የሚያያዝ አካባቢ ላይ ያተኩራል። በእርግጥ ግንባታ ላይ ያላችሁ ሰዎች የዋጋ ግሽበት እንደሚያስቸግራችሁ እናውቃለን። በተለየ ሁኔታ በሕንጻ ግንባታ ላይ ያለው የዋጋ ግሽበት ችግር ወደ አገር ውስጥ የሚገባውን ዕቃ በመተካት ላይ አስባችሁ ከሠራችሁ እናንተም የተለየ ድጋፍ ይደረግላችኋል። "ከውጭ የምናመጣው ምንድነው?" የሚለውን ለይቶ፤ ሰብሰብ ብሎ የሚሠራ ኩባንያ ካለ መንግሥት ድጋፍ ያደርጋል።

በዛሬው ውይይታችሁ ብዙ ጉዳይ እንደሚነሣ ተስፋ አደርጋለሁ። አብዛኛውን ጥራት ላይ፤ ዓለም አቀፍ ደረጃ ላይ፤ እውነተኛ ኩባንያ መፍጠር ላይ፤ ከዚህ ወጥቶ ደቡብ ሱዳን፤ ኬንያ ላይ ሲወዳደር መንግሥት ተጨማሪ የፋይናንስ ድጋፍ ስለሚደርግለት ኩባንያ ስለመፍጠር እንድታወሩ ነው አደራ የምላችሁ! ዑጋንዳ እየሄድኩ ነው። "ኩባንያዬ አምስት ስድስት ሰው ሆነን ትልቅ ኩባንያ 10 ሺሕ ሰው አለን። እና 1 ቢሊዮን ዶላር ያስፈልገኛል። መንግሥት ሦስት መቶ አራት መቶ ዶላር ጋራንቲ ይስጠኝ" የሚል ኩባንያ ነው የምንፈልገው እንጂ፤ "ዕቃ ላመጣ፤ ፒካፕ ላመጣ ብዬ የውጭ ምንዛሬ አነሰኝ" የሚል ጥያቄ አይደለም ዛሬ የሚፈለገው። ወደ ብልጽግና እየሄድን ስለሆነ ትንሽ ከአለንበት ነገር ወጣ ያሉ ሐሳቦች አንሥታችሁ ተመካከሩ። ጠቃሚ ግብአቶች ከአሉ ሙሉ በሙሉ የ10 ዓመት ዕቅዳችን ወስጥ አስገብተን እንጠቀምበታለን። ሌላ ቀን በጎ ፍቃዳችሁ ከሆነ ግማሽ ቀን ወስደን ብንወያይ እና ብንነጋገር እኔም ፍላጎት አለኝ። የዛሬው ውይይታችሁ የተሳካ እንዲሆን፤ ከእናንተ በላይ ደግሞ ወጣቶቹ ስለሚሻሉ ወደ እነሱ ብሄድ ይሻላል።

የመጨረሻው መልእክቴ ሌብነት እያስቸገረን ነው። ባለሥልጣናትን ሌባ፤ ሀብታም እያደረጋቸሁ በተለያየ ደረጃ የማይታዘዙ ሹማምንቶች በዝተዋል። “ባንክ ላይ ብድር የለም” ትላላችሁ። ዕድሜ ለእናንተ አባለጋችሁ፤ ሰዎቹም ብር ለመዱ። ማጭበርበር ለመዱ። የውሸት ሪፖርት ለመዱ። ለመንግሥት ዕዳ ሆኑ። ሰዎች ሥራ አይወዱም። ባለሥልጣናት 8 ሰዓት መሥራት አይችሉም። በረባ ባልረባው ባንኮክ ይሄዳሉ። ዕድሜ ለእናንተ የውጭ ምንዛሪ ችግር የለባቸውም። ዕድሜ ለእናንተ፤ እና እባካችሁን ሌብነት እንዲቆም ወስናችሁ ሥሩ።

ሌብነት ካልቆመ ለጊዜው ያቀለለ ይመስላችኋል እንጂ ዞሮ ዞሮ የእናንተን ሥራ ይበላዋል። ምክንያቱም አንዴ መቅመስ የለመደ ሰው በሰጠኸው ልክ አይቆምም። ከሚሠራው በላይ የሚሰርቀው በበዛበት ሀገር ወደ ብልጽግና መሄድ አይቻልም። እናንተን ዋሽቶ የሰረቀ፤ መንግሥትን ዋሽቶ የሰረቀ፤ አገሩን ዋሽቶ የሰረቀ፤ ለእናንተ ዕድገት ሊሠራ አይችልም። አይችልም። የሌብነት ዋናው መገኛ ኣካባቢ ኮንስትራክሽን ነው። ሌላ ቦታ የለም ማለቴ ሳይሆን ዋናው፤ በተቻለ መጠን ግምገማ አታድርጉ፤ ምርመራ አታድርጉ ግን ወስኑ። ሌቦች እያለማመድኩ አገሬን አልጎዳም ብላችሁ ወስኑ። ሌብነት ከተዋችሁ እኛም መምራት እንችላለን። በጋራ እናቅዳለን። የምናቅደው ሀብታሞች ላይ ነው። እኛን ከመስማት እናንተን መስማት ይሻላል። እኛ አምስት ዓሥር ሺሕ ነው የምንከፍለው ታውቃላችሁ፤ እናንተ በመቶ ሺሕ ትከፍላላችሁ። የእናንተ መሆን ይበልጣል። ለእናንተ እንዳይሠሩ በዚህ ተይዘዋል፤ ለእኛ እንዳይሠሩ በእናንተ ተይዘዋል። መሀል ላይ ያለውን ደላላ እና ሌባ አጥፍቶ መንግሥት ለሕዝብ ብቻ አገልጋይ እንዲሆን እባካችሁን አግዙን! ይሄንን ማድረግ ከቻላችሁ ብልጽግናችን ይረጋገጣል። ሌቦች እስከአሉ ድረስ ግን ምንም ብንሠራም ገንዘብ ልናመጣ እንችላለን። የሌባ ስብስብ ያለበት አገር በለጸገ ማለት አይቻልም። ብልጽግና የአእምሮም ስለ ሆነ፤ የቁስ ብቻ አይደለም። ስለዚህ ሌብነት እንዲቀንስ ለመተባበር ዛሬ በውይይታችሁ ውስጥ አንዱ ቁልፍ ጉዳይ





ጥራት፤ ሰብሰብ ብሎ እውነተኛ ኩባንያ መሆን እና መንግሥትን በአዳዲስ ጉዳይ መገዳደር፤ ሌብነት እንዲቆም የበኩላችሁን መጫወትን ከወሰናችሁ በሚቀጥለው ውይይታችን በርካታ የድጋፍ ሐሳቦች ይዘን እንመጣለን። እንድናምናችሁ ሆናችሁ ካልመጣችሁ ለመተጋገዝ ስለሚያስቸግር ማለት ነው። ቢገባችሁም ባይገባችሁም በጣም ነው የማመሰግነው!

**መልካም ውይይት!**

# የ“በኅብር ወደ ብልጽግና” መድረክ ንግግር

ታኅሣሥ 23/2012 ዓ.ም.

## በጣም ነው የማመሰግነው!

በመጀመሪያ ወጣቱ ብልጽግና ከወጣቶች ጋር በሚገናኝበት በዚህ መድረክ ላይ ተገኝቼ በጥቂት ደቂቃዎች ብልጽግናን ለእናንተ ማስተዋወቅ እንድችል ዕድል ስለሰጣችሁኝ የአዲስ አበባን ወጣቶች እጅግ አድርጌ ማመስገን እፈልጋለሁ።

ብልጽግናን በሚመለከት ብዙ ጥያቄዎች እንዳላችሁ እገምታለሁ ቢኖራችሁም ተገቢ እንደሆነ ይሰማኛል። ነገር ግን ዛሬ የመጣሁት ወጣቶችን በአንዳንድ ምሳሌ እና ልምድ ለማስተማር ስለሆነ በመጀመሪያ የቻይናውን ፕሬዚዳንት ሺን የሚመለከት ጉዳይ ባካፍላችሁ ምናልባት ለሕይወታችሁ ይጠቅማችኋል ብዬ፤ ብልጽግናን ለመረዳት ያመቻችኋል ብዬ ስለማስብ ከሱ እጀምራለሁ።

ፕሬዚዳንት ሺ እንዳሉት፤ በልጅነት ጊዜያቸው ስግብግብ ነበሩ። ስግብግብ ከመሆናቸው የተነሣ ጓደኛ አይወጣላቸውም ነበር። ጓደኛ ይይዛሉ ይቀራረባሉ። በጣም ገብጋባ ስለነበሩ ሰዎች እየሸሹ አስቸገሯቸው። ጓደኛ አልባ ሆነው ግን ለምን ጓደኛ እንዳጡ ደግሞ አያውቁም ነበር። ሁሌ ይወቅሳሉ። “የእኔ ጓደኞች አይረቡም፤ ከዱኝ፤ ተውኝ” ይላሉ እንጂ “ምን ባጠፋ ነው?” ብለው ራሳቸውን አይጠይቁም። በዚህ ጊዜ የፕሬዚዳንት ሺ አባት የልጃቸው የወደፊት ዕጣ ፈንታ ስለአሳሰባቸው አንድ ከመጽሐፍ የማይገኝ የተግባር ትምህርት ሊያስተምሯቸው ወሰኑ። በዚያ ጊዜ በእሳቸው ዕድሜ የዛሬ 50 እና 60 ዓመት ቻይና ውስጥ ሥጋ፣ ዕንቁላል እና ወተት እያንዳንዱ ቤተሰብ የሚያገኘው ምግብ አልነበረም። ልክ እንደ አሁኑ እንደኛ ማለት ነው። አልፎ አልፎ የሚገኝ ነበር።

የፕሬዚዳንት ሺ አባት አንድ ቀን ሁለት ፓስታ ይቀቅሉና በአንደኛው ፓስታ አናት ላይ አንድ ዕንቁላል አስቀምጠው በአንደኛው ፓስታ አናት ላይ ምንም የሚታይ ነገር የለም። ገበታ ላይ ከአቀረቡ በኋላ ልጃቸውን ሺን “እጄን እስክታጠብ ድረስ ያገኘኸውን ያሻህን እየበላህ ቆየኝ” ይሉትና እጃቸውን ሊታጠቡ ይሄዳሉ። ፕሬዚዳንት ሺ አላቅማማም፤ ዕንቁላል አልፎ አልፎ በገና፣ በመውሊድ፣ በጥምቀት የሚገኝ ውድ ነገር ነው፤ በዚያን ጊዜ። እና ዕንቁላሉን ሲያይ ምንም ሳያንገራግር ዕንቁላል ያለበትን ወስዶ መብላት ጀመረ። አባት መጥተው ሁለተኛውን ፓስታ መብላት ሲጀምሩ ከውስጡ ሁለት ዕንቁላል ወጥቶ ያያል፤ ፕሬዚዳንት ሺ በጣም ይበሳጫል። አልፎ አልፎ የሚገኝ ዕንቁላልን የሚያህል ነገር አንድ ከላይ አይቶ ዘሎ ቢመርጥ እና ቢወስድ ከውስጥ ሁለት ዕንቁላል ያለውን አባትየው መብላት ሲጀምሩ “አምጣ” እንዳይል አባት ነው።

በጣም በከፍተኛ ብስጭት ፊቱ ሲቀላ አባትየው “ዐይኖችህ የሚያዩትን ሁሉ እውነት ነው ብለህ አትቀበል። ሁለተኛ የበዛ ስግብግብነት አንተን መልሶ ሊጎዳህ ስለሚችል ብልጣብልጥ እና ስግብግብ አትሁን” ብለው መከሩት። “የአየኸውን ሁሉ እውነት ነው ብለህ አትውሰድ ምክንያቱም ዐይን እና አእምሮ

በጣም ብዙ ነገር ያሳስታሉ እና ሁለተኛ ሲበዛ ብልጣብልጥ እና ስግብግብ አትሁን" አሉት።

ይሄ ትምህርት በቂ አይደለም። ከተወሰነ ቀን በኋላ መልሰው ለሁለተኛ ጊዜ ፓስታ ቀቀሉ። ፕሬዚዳንት ሺ የዚያን ዕለት ዕንቁላል ያጣበት ዕለት የራስ ምታት ሆኖበት ነው የቆየው፤ እና ለሁለተኛ ጊዜ ከቀቀሉ በኋላ ልክ እንደዚያን ጊዜው በአንደኛው ላይ አንድ አስቀምጠው በሚታይ ሁለቱንም ማዕድ ላይ አስቀመጡና "ልጄ ሆይ ታጥቤ እስከምመጣ ያሻህን መርጠህ ብላ" አሉት። ልጁ ከባለፈው ትምህርት ስለወሰደ "ሞኝህን ፈልግ" ይልና ከላይ ያለውን ዕንቁላል ትቶ የሌለውን ዕንቁላል ወስዶ መብላት ይጀምራል። መብላት ሲጀምር ቢጎረጉር ቢጎረጉር ከውስጥ ምንም ያጣል። አባት አንድ ዕንቁላል የአለውን ይበላሉ። አሁንም ፕሬዚዳንት ሺ በጣም ይበሳጫል። "ባለፈው ሁለት ዕንቁላል ቀብሯል ብዬ የተቀበረውን ላወጣ ብሄድ አንዱንም አጣኋት" ይላል። የበዛ ስግብግብነት እና ብልጣ ብልጥነት የተባለውን ቢያስታውስ ኖሮ ቢያንስ አንዱን ያገኝ ነበር። አባትየው ዳግም ሲበሳጭ አዩትና "ልጄ ሆይ" አሉት፤ "በልምድህ ብቻ አትታመን፤ አዳዲስ ዕውቀት፤ አዳዲስ ልምምድ፤ አዳዲስ ሐሳብ ሊመጣ እንደሚችል አስብ እንጂ፤ በታሪክ እና በትናንትና ዕውቀት ብቻ ከአሰብክ ነገን ታጣታለህ" አሉት።

ሦስተኛ ቀን አሁንም ፓስታ ቀቀሉ። ምክንያቱም ልጃቸው ጓደኛ አጥቷል፤ ካልሠሩበት በስተቀር ዛሬ የታላቋ ቻይና ፕሬዚዳንት መሆን አይቻለውም ነበር። ሦስተኛ ቀን ቀቀሉና አሁንም ከላይ አንድ ዕንቁላል አድርገው አስቀመጡ። "ልጄ ሆይ መርጠህ ብላ" አሉት። ልጁም "አባባ ይህማ ስሕተት ነው። ከውጭ ደክመህ ሠርተህ ሸምተህ አምጥተህ እንደገና ደግሞ አብስለህ እኔ መራጭ መሆኔ ትክክል አይደለም። አንተ መርጠህ ከወሰድክ በኋላ ሁለተኛውን አማራጭ እኔ እመገባለሁ" ይላቸዋል። አባትም ሳያቅማሙ ከላይ አንድ ዕንቁላል ያለውን ብድግ አድርገው መብላት ይጀምራሉ። ልጁ ውስጥ





ገብቶ መብላት ሲጀምር ሁለት ዕንቁላል ከውስጥ ያገኛል። እና አባት "ከብልጣ ብልጥነት እና ከአየኸው እውነት ርቀህ ለሰዎች መልካም ስታደርግ ተፈጥሮ ራሷ ነች የምትሰጥህ አሉት። እኔ ደግሞ ፈጣሪ ራሱ ብድራትን ይከፍላል፤ እላለሁ።" እና ሲበዛ ብልጣ ብልጥ ለመሆን ማሰብ ሳይሆን ያለንን ለመስጠት ማሰብ ይከፍላል የሚል ወጣት እንድትሆኑ አደራ እላችኋለሁ።

"ይሄ ምን ማለት ነው?" ያላችሁ እንደሆነ የአዲስ አበባ አመራሮች፤ የአዲስ አበባ ወጣቶች ለአዲስ አበባ መትጋት ተገቢ ነው። ከአዲስ አበባ መስረቅ ግን አሳፋሪ ነው። የምትሰርቁ ከሆነ ከዚህ ቆሻሻ አበባ ማየት ብርቅ ከሆነበት፤ በደሳሳ ጎጆ ሰዎች የሚሠቃዩበት፤ በሺዎች የሚቆጠሩ ሕፃናት እና ሴቶች በረንዳ ከሚያድሩበት ከተማ ከምትሰርቁ አዲስ አበቤ ባትባሉ ይሻላችኋል። ስለዚህ በዚያ ብልጣ ብልጥ መሆን እና የአያችሁትን ላፍ ላፍ ማድረግ በኋላ ዕዳ ስለሚሆን በማገልገል ላይ ብቻ አተኩሩ ለማለት ነው።

ከጥያቄዎቻችሁ ሁሉ በጣም የደነቀኝ ጥያቄ "ለምን ብልጽግና ተባለ?" የሚለው ነው። ብልጽግና የአስተሳሰብ ግልጽነት እና የልብ ንጽሕና ያለው እሳቤ ነው። በጣም ግልጽነት ያለው። ለእኛ ሰፈር ልጆች "አጭበርብሬ ሥልጣን ላይ መቆየት መስረቅ ምናምን" የሚል ሳይሆን "ይህቺ ሀገር እንዴት ተደምራ ትበለጽጋለች" የሚል ግልፅ ያለ ሐሳብ አለው። ደግሞም ደፋር ነው። ሳይመሠረት መጽሐፉን እንካችሁ እንዳሻችሁ ተቹ ያለ የመጀመሪያው ፓርቲ ነው። የአስተሳሰብ ግልጽነት ስለአለው ብልጽግና ለትውልድ እንጂ ለምርጫ አይሠራም። የምንሠራው ለትውልድ እንጂ ለምርጫ አይደለም።

ምናልባት የብልጽግና አባላት "ምን እያልክ ነው?" ያላችሁ እንደሆነ፤ ብልጽግናን። የብልጽግናን ሐሳብ፤ የብልጽግናን የአሠራር ሥርዓት በፍፁም በሚቀጥሉት 50 እና 60 ዓመታት ማሸነፍ አይቻልም። እንዳትሳሳቱ ዐቢይን ማሸነፍ ይቻላል። ማንም ዐቢይን ቢያሸንፍ ግን ከእንግዲህ ወዲያ ከብልጽግና

ሐሳብ እና ቀን ከሌት ከመሥራት ውጪ ኢትዮጵያን ለስድስት ወር ማስተዳደር አይቻልም።

ስለዚህ የእኛ ሐሳብ የአስተሳሰብ ግልጽነት እና ንጽሕና ስለአለው ኢትዮጵያ ውስጥ ማንም ቢመጣ ከዚያ ውጭ እንቀሳቀሳለሁ ቢል ራሱን እንደመግደል ስለሚታሰብ፤ ውጭ ሆነንም በሐሳብ እንደምንመራ፤ ውስጥ ብንሆንም ተጨማሪ ዕዳ እንደሆነ ስለምናውቅ ሁሌም አሸናፊዎች ነን ብለን እናስባለን። ብልጽግናን በመክሰስ ሳይሆን ከብልጽግና በመማር እና የብልጽግናን እሳቤዎች በማሻሻል የሚመጣ ብቻ ነው ከእንግዲህ በኋላ በኢትዮጵያ ቦታ ያለው። የበዛ ብልጣ ብልጥነት እንደ ፕሬዚዳንት ሺ አያዋጣም። በቅንነት፣ በታማኝነት፣ ከመስረቅ ራስን ነፃ በማውጣት የሚሠራ ብቻ ነው መቆየት የሚችለው።

መልሼ ወደቻይና እወስዳችኋለሁ። ቻይና ውስጥ በ1907 አካባቢ አንድ መሪ ነበሩ። በጣም የተወደዱ፤ የታወቁ መሪ ነበሩ። እኚህ መሪ ብዙዎች የቻይናን መንግሥት ወደ ንግሥና እንዲቀይሩ፣ የግዛት መንግሥት የሆነውን ወደ ንግሥና ግዛት እንዲቀይሩ ይመክሯቸዋል። ሰውየው ሲመከሩ ሊሰሙ አልቻሉም። ልጃቸው እሳቸው ንጉሡ ከሆኑ በቀጥታ ወራሽ የመሆን ዕድል እንዳለው ስለሚያውቅ ይህንን ሐሳብ በጣም ስለወደደው አባቱን ጠዋት ማታ ቢጎተጉት እምቢ አሉት። ከዚያ አንድ ጋዜጣ ማሳተም ጀመረ። ይሄ ጋዜጣ አንድ ኮፒ ብቻ ነው የሚታተመው፤ ለአባቱ ብቻ። አባቴ አይልም የፕሬዚዳንቱን ስም እየጠራ "ሕዝብ ሁሉ ይወድሀል፤ መንገሥ አለብህ፤ ቻይናን የሚያክል ታላቅ ሀገር እንደ መንግሥት ሳይሆን እንደ ኪንግደም ነው መሆን ያለበት" የሚሉ ጽሑፎች ያለበት ጋዜጣ አንድ ኮፒ ይታተማል። የአባቱ ጠረጴዛ ላይ ጠዋት ይቀመጣል። እናም አባት ያነብባሉ። "ይህ ጋዜጣ የት የት ይሰራጫል?" ሲሉት፤ "በመላው ቻይና አሁን ያለው ወሬ ይኼ ብቻ ነው። ሕዝብ ሁሉ "ንገሥ" እያለ ነው ለምን አንተ እንደማትሰማ አናውቅም? የትም ሻይ ቤት ብትገባ የምትሰማው ይሄን ብቻ ነው። ለምን አንተ እንደማትሰማ አናውቅም?" ይሉታል። ይሄ ጋዜጣ እየመጣ ሲሄድ አባት ጓጓ፤ እንደዚህ ሕዝብ ከወደደኝ እና ሁሉም ሕዝብ የሚያነብበው ጋዜጣ ይኼ ከሆነማ፤ ብሎ የቻይናን መንግሥት ወደ የንጉሥ ግዛት ቀየረው። ከቀየረ በኋላ በንግሥና የቆየው 87 ቀን ብቻ ነበር። እውነተኛ ታሪክ ነው። ይሄ ራሳቸው በሚቀልቧቸው የፌስቡክ ቅልበኞች የሚደሰቱ ፖለቲከኞች ከአሉ ዕድሜያቸው 87 ቀን ነው የሚሆነው። መሥራት፣ ከሌብነት መጠበቅ፣ በቅንነት ሁሉን ማገልገል ብቻ ነው፤ ከእንግዲህ ኢትዮጵያ ውስጥ የሚሠራው። የሄድንበት ዘመን ዳግም ሊመጣ አይችልም። ማንም ኢትዮጵያዊ በምርጫ የኢትዮጵያ መሪ መሆን ይችላል። ስለዚህ ሁላችንም ልባችንም አእምሯችንም ክፍት መሆን አለበት።

በቅርቡ እስራኤልን ለአለፉት አራት ዙር ሲመሩ የቆዩትን የዚያን አገር ጠቅላይ ሚኒስትር ለመቀየር ምርጫ አካሂዳ ነበር። በመጀመሪያው ምርጫ አሁን ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር እና አዲስ የሚወዳደሩት ሁለቱም መንግሥት ለመፍጠር የሚያስችል ድምፅ ሊያገኙ አልቻሉም። ቢደራደሩ ቢደራደሩ ሁለቱም መንግሥት አብላጫ ድምፅ መሆን ስለአልቻሉ የእስራኤል ሕግ ግልፅ ነው ሁለተኛ ምርጫ አዘዘ። ሁለተኛ ምርጫ ተካሄደ። አሁንም ከሁለት አንዳቸውም መንግሥት ለመፍጠር የሚያስችል ድምፅ አላገኙም። ቢደራደሩ ቢደራደሩ አልቻሉም። በዚያ አገር ሥልጣን መሠረት ፕሬዚዳንቱ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ "መንግሥት መሥርት" አሉ። አልቻሉም። "አልቻልኩም" ብለው ሪፖርት አደረጉ። ለተቃዋሚውም "ማሻሻያ አድርግ" አሉት። አብላጫ ድምፅ ሊያገኝ አልቻለም። "አልቻልኩም" አለ። ሦስተኛ ምርጫ አዘዙ። ሦስት ምርጫ ሊያደርጉ ቢዘጋጁም አንድም ሰው በምርጫ ምክንያት በቅድመ ምርጫም፤ በምርጫም፤ በድኅረ ምርጫም አልሞተም።

የአዲስ አበባ ወጣቶች ብልጽግናን ከወደዳችሁ ድምፃችሁን ስጡት! ብልጽግናን ከጠላችሁ በድምፃችሁ ቅጡት! ሕይወታችሁን ለእኛ አትስጡ! ሕይወታችሁን ለየትኛውም ፓርቲ አትስጡ! እሱ ትክክል አይደለም። በድምፅ የምትፈልጉትን

መምረጥ የማትፈልጉትን መተው እንጂ፤ እስከ ዛሬ ኢትዮጵያ ውስጥ ባለን ልምድ በእናንተ ዕድሜ እንኳን በምታውቁት ከምርጫ ጋር ተያይዞ የሚመጣ ጦስ ብታዩ ፖለቲከኞች ወንድሞቻቸው፣ ልጆቻቸው፣ ቤተሰቦቻቸው ምንም አልሆኑም። አዲስ አበባ ውስጥ የድሀ ልጅ ተቀጠፈ። ያንን የድሀ ልጅ ማንም አያስታውሰውም። እናት ናት ያለጧሪ የቀረችው። በቅርቡም የምታዩት ወጣቱን ገፋፍቶ ወደ መገዳደል የሚወስዱ ኃይሎች ሲሞቱ አይታዩም። ሲያስገድሉ፣ ሲያጋድሉ እንጂ። የእናንተም ሕይወት የእነርሱም ሕይወት አንድ መሆን ብቻ ሳይሆን ወጣት ስለሆናችሁ ከእነርሱ የመሻል ተስፋ ስላላችሁ ለማናችንም ቢሆን ካርዳችሁን እንጂ ሕይወታችሁን መስጠት የለባችሁም። በምርጫው እናሸንፋለን! ከተሸነፍን ግን እናበጣብጣለን የሚሉ ኃይሎች ወጣቶች "ተሳስታችኋል ድምፅ እንሰጣችኋለን ከአሸነፋችሁ እና ሰውየው አይሆንም ካለ በገባው ቃል መሠረት ጎትተን እናወርደዋለን። አሊያ ግን ከተሸነፋችሁ እንደሠለጠነው ዓለም ሞክረናል። የተሳካልን ይሄንን ያክል ነው ብላችሁ ሂዱ እንጂ ከእንግዲህ በኋላ ለእናንተ መሞት አቁመናል" የሚል መልስ ከእናንተ ይጠበቃል።

ወጣት ለውጥ ናፋቂ ነው። የማይቀረው የጉዞ ሂደት ለውጥ ነው። ወጣት በየቀኑ ለውጥ ይፈልጋል። ፂሙ እንዲያድግ ይፈልጋል። ፀጉሩ እንዲያድግ ይፈልጋል። ፂም የሌላቸው ወንዶች እንዲያድግላቸው ምን ያህል እንደሚፈገፍጉ ስታዩ ወጣት ለለውጥ ያለው ጥማት ይገባችኋል። ይህ ለውጥ ግን አዳጊ እና አሳዳጊ እንጂ አንዱን ገድሎ አንዱን የሚያበለጽግ መሆን የለበትም። የእናንተ የለውጥ ፍላጎት ድምር መሆን አለበት።

ወጣትነት ድልድይ ነው። ሕፃን ሳለን አድጌ፤ ሃይስኩል ጨርሼ፤ ዲግሪ ይዤ እያልን ወደፊት ብቻ ነው የምናስበው፤ ነገራችን ሁሉ ነገ ነው። ስናረጅ ነገራችን ሁሉ ትናንት ነው። አሁን እንደሚያጋጥመው የኢትዮጵያ ፖለቲካ ማለት ነው፤ ትናንትና የበዛበት ነገር። አዲስ ነገር መፍጠር ካልቻልክ ወደ ትናንትናው መግባት ግድ ነው። ወጣትነት ግን ድልድይ ነው። ወደኋላም "ሃይስኩል ሳለሁ፤ ኮሌጅ ሳለሁ" ብሎ የሚናገረው ቢያንስ ታሪክ አለው። ወደፊትም "ነገ እንደዚህ እና እንደዚያ እሆናለሁ" እያለ የሚናገረው ተስፋ የሚያደርገው መሻት ህልም አለው። ሁለቱ ቦታ ላይ የቆመው ወጣት በትዝታ ለሚኖሩት ሕይወቱን ከሰጠ ዓለም የትዝታ መድረክ ትሆንና ተስፋ ይጠፋል። ሲሆን ሲሆን በትዝታ የሚኖሩት ጠፍተው ለተስፈኞቹ ቦታ መስጠት እንጂ፤ ተስፈኞቹን ገድሎ በትዝታ የሚኖሩት መቆየት የዓለምን የጉዞ ዑደት ያስቀራል። ስለዚህ ወጣቶች በተስፋ እና በትዝታ ለሚኖሩ ሰዎች እንዲሁ በለውጥ ፍላጎት ስሜት ጊዜያችሁን፣ ዕድሜያችሁን ማባከን የለባችሁም። ወጣትነት ኃይል ነው። ከተማ መጥረግ ይችላል። መትከል ይችላል። ማጽዳት ይችላል። መፍጠር ይችላል። ይህንን ኃይል አሁን ካላችሁበት ዕድሜ ብዙ ቀድማችሁ ማየት ከቻላችሁ ከተወሰነ ዓመት በኋላ አይቻልም። ሰው እየደከመ ይሄዳል። አሁን ጉልበት ባለበት፤ ኃይል ባለበት ጊዜ ጉልበታችሁን ለቀና ነገር ማዋል ይኖርባችኋል።

ዛሬ ኦሮሞን እና አማራን አጋድሎ ሥልጣን መያዝ የሚፈልግ ኃይል ካለ፤ ዛሬ እስላምና ክርስቲያንን አጋድሎ፤ ቤተክርስቲያን እና መስጊድ አቃጥሎ ሥልጣን ለመያዝ የሚሻ የትኛውም ቡድን ከአለ፤ አመጣጡ ራሱ የቆሸሸ ነውና ለኢትዮጵያ አይበጃትም። አጋድሎ፤ አቃጥሎ የመጣ ያቃጥልሀል እንጂ ወደ ብልጽግና አይወስድህም። ለመምጣት መመኘት ተፈጥሮአዊ እና ተገቢ ነው። ለመምጣት ማጋደል ግን ነውርም ወንጀልም ነው። ማጋደልና ማቃጠል አያስፈልግም። ወጣቶች ወጣትነት ሐላፊነትም ጭምር ስለሆነ መንቃት ይገባችኋል። ሐላፊነት ወስደን ጊዜያችንን በሐላፊነት መወጣት እና እንደዚያ ዓይነት ሐሳብ ያላቸውን ሰዎች መሞገት ይጠበቅብናል።

ወጣትነት ተስፋ ነው። ዛሬ ላይ ሆኖ ነገን ማየት ነው። ዛሬ ላይ ሆኖ ነገን ማለም ነው። የነገ ህልምህን የሚያቀጭጭ ኃይል ሲመጣ መቀበል የለብህም። ህልም የሚያቀጭጭ ህልሙ ያለቀበት ብቻ ስለሆነ፤ ህልም ያለቀባቸው ህልማችሁን እንዳይወስዱባችሁ፤ ወይም ማታ ማታ እንደ እናንተ ጦሽ ብለው መተኛት የማይችሉ፤ እናንተ ስትተኙ ህልማችሁን እንዳይሰርቁባችሁ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርባችኋል። ወጣት ምሳሌ መሆን አለበት።

ይሄንን ሁሉ ከአልኩ በኋላ፤ አረጋውያንን የሚያከብር፣ የሚፈራ፣ ትሕትና ያለው፣ ሕፃናትን የሚንከባከብ ደግሞ መሆን አለበት። ትውልድ የሚሠራው እናንተ ጋ ነው። ጉልበት ብቻ ሳይሆን ማስተዋልም ስለሚያስፈልግ፤ ይሄ እንዳለ ሆኖ፤ “እችላለሁ!” የሚል መንፈስ በእጅጉ እናንተ ውስጥ መተከል፣ መብቀል፣ ፍሬ ማፍራት ይኖርበታል። ትችላላችሁ! ሁልጊዜ እንደምናገረው ከፊት ለፊታችሁ ያለው ሰው እዚህ መቆም ከቻለ ከእናንተ መካከል መቆም የማይችል አንድ ሰው አይኖርም። ስለዚህ ያላችሁበት ነገር እንዳይዛችሁ እና እንዳያስቀራችሁ መኪና ባይኖርም ችግር የለውም። እየነዳችሁ መሄድ፤ ወደ ቤታችሁ ስትሄዱ በድምፅ እና በእግር መንዳት ስለሚቻል፤ ስናገር ሰምታችኋል ብዬ ነው። ስልክ የሌላችሁም ችግር የለውም። እጃችሁን ጆሮአችሁ ላይ አድርጋችሁ መሄድ ነው፤ ይመጣል። ግዴላችሁም ይመጣል። ድሃ ሆኖ በድህነት ለመኖር መፍቀድ ነው ስሕተት። ድሃ ሆኖ ወደ ብልፅግና ተስፋ ማድረግ እና ለዚያ መትጋት ነውር አይደለም። “ለምን ብልጽግና ተባለ?” ወደዚያ ልመለስ፤ ብልጽግና ለሚወደው የሚተጋ እንጂ የሚጠላውን በተደጋጋሚ በመናገር የሚኖር ፓርቲ አይደለም።

ድህነትን አጥብቀን እንጠላለን። የምናወራው ግን ስለ ብልጽግና፤ የምንሠራው ስለ ብልጽግና፤ የምናልመው ስለብልጽግና፤ በዚያ ህልም ውስጥ ድህነት ተፈጥሯዊ በሆነ መንገድ ይሞታል። በተቃራኒው የምንጠላውን ድህነት አሁንም አሁንም ድህነት ድህነት ብንል እንወዳጀዋለን፤ እንለማመዳለን፤





ጓደኛሞች እንሆናለን። ብዙ ጊዜ ብዬዋለሁ፤ ሰዎች ጥሩ ለብሰው አቧራ ውስጥ ጭቃ ውስጥ ሲራመዱ መጀመሪያ ይጠነቀቃሉ ቦታ ይመርጣሉ። ቀስ እያሉ ጫማው ሲቆሸሽ ሱሪው ሲቆሸሽ ግን ምርጫ ይቀራል ጭቃ እያንቦጫረቁ ይሄዳሉ። ድህነት እንደሱ ነው። ስንለማመደው እንጠየፈዋለን። ግን ንግግራችን፤ ሥራችን፤ ጽሑፋችን ድህነት ሳይሆን ብልፅግና ነው። ድህነትን የሚያጠፋው ስለእሱ አብዝቶ መናገር ሳይሆን ስለ ብልጽግና አብዝቶ ማለም ስለሆነ ብልጽግና ያልነው ለሱ ነው።

ቻይናዎች አንድ አባባል አላቸው። “ድመቲቱ ጥቁር ወይም ነጭ መሆኗ ሳይሆን አይጥ መያዟ ነው ዋናው ነገር፤” ኢትዮጵያ ውስጥ የድመቷ እግር ስንት ጥፍር አለው በሚል ክርክር ሁለት አብዮቶች አልፈዋል። ድመቷ ዘንድ ስንደርስ የድመቷን ጥፍር በተመለከተ ስንከራከር ማለት ነው። አሁን ቶሎ ብለን ድመቷን በመፍጠር ድህነትን ማስወገድ ያስፈልጋል። ከዚያ ውጭ ያለው እሳቤ ውጤት እስከ አላመጣ ድረስ፤ ወደ እውነት እስከአላስጠጋን ድረስ ፋይዳ የለውም። እውነት ደግሞ የሚለካው በሚሰጠው ጥቅም ነው። ረቂቀ እውነት የለም። እውነት ራሱ ሰጪ ነው። እውነት ራሱ ንጹሕ ነው። እውነት ራሱ የበለጠ ነው። የሚለካውም በሚያስገኘው ጥቅም ነው። ወደ እውነት ተጠግቶ የከሰረ ወይም የሚከስር ስለሌለ፤ እውነት የሚለካበትን መነፅር ለማምጣት የሚለካበት ከለር እና ጥፍር ላይ የምናጠፋውን ጊዜ ትተን በመደመር እሳቤ ብልጽግናን እውን ማድረግ ይኖርብናል። ይህንን ማድረግ ደግሞ እንችለለን።

“ብልፅግና አሁን ባለው ሁኔታ ምን ሊያደርግ ይችላል? የብሔር ፅንፈኝነት በዝቶ፣ የሀይማኖት አክራሪነት በዝቶ፣ ድህነት፣ የኑሮ ውድነት፣ የዋጋ ግሽበት በሰፋበት ቦታ ብልፅግና ምን ያደርጋል?” የሚል ጥያቄም ጠይቃችኋል። ይሄ ሁሉ ችግር ባይኖርማ ብልጽግናን ምን አመጣው? ብልጽግና ሀገር ውስጥ ባሉ ችግሮች ትንታኔ ላይ ተንተርሶ የተፈጠረ ፓርቲ ነው። “አሁን ያለብን ችግር

የሚፈታው በምንድነው?” ተብሎ በችግር ትንታኔ ላይ የተፈጠረ ፓርቲ ነው። ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ችግር ድህነት ብቻ አይደለም ሐሳብም ነው።

ብልጽግና የሦስት ነገሮች ጋብቻ ውጤት ነው። አንደኛው ነዋይ፤ ነዋይ ብቻውን ብልጽግና መሆን አይችልም። ሁለተኛው፤ ዕውቀት ያንን ንዋይ የምናባዛበት እና የበለጠ ነዋይ የምንፈጥርበት መሠረት ስለሆነ። ሦስተኛው፤ የማድረግ ዐቅም ነው። ሦስቱ ሲጋቡ ነው ብልጽግና እውን የሚሆነው። የማድረግ ዐቅም ያለው ወጣቶች ዘንድ ነው። ብልጽግና ከሁሉም እንደ ዐቅሚቲ ይሰበሰባል። ዕውቀት፣ ጥበብ ከውስጥም ከውጭም ይገበያል። ሦስቱ ሲጋቡ ብልጽግና እውን ይሆናል። ይህንን ታሳቢ ያደረገ ዕውቀት አልባ፣ ንዋይ አልባ፣ የማድረግ ዐቅም ያለውን ወጣት የዘነጋ ከሆነ ብልጽግና እውን አይሆንም፤ የሚል ከነባራዊው ሁኔታ እና ከተጨባጭ ችግር ትንታኔ የተወለደ ፓርቲ ነው። ይህንን ማድረግ እንደሚችል በተፈጠረ በሁለት ወር ጊዜ ውስጥ ወይም በመፈጠር ሂደት ላይ እያለ የአገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ አጀንዳ፤ የብልጽግና ሐሳብ ያለው አጀንዳ በሀገር ውስጥ ምሁራንን፤ በተቃዋሚ ፓርቲዎች፤ አጋዥ ድርጅቶችን ከአወያየን በኋላ በዓለም ላይ ለማስተዋወቅ ባደረግነው ሙከራ እስከአሁን ባለው እውነት ኢትዮጵያ ውስጥ አይተን የማናውቀውን ርዳታ አግኝተናል። እስከአሁን 10 ቢሊየን ዶላር ማግኘት ተችሏል። ይሄ ማለት አይ.ኤም.ኤፍን ብቻ ስንወስድ እስከአሁን ከሚሰጠን ኮታ 700 በመቶ የበለጠ በጀት ሰጥቶናል።

የብልጽግና እሳቤ እና ጎዳናው ኢትዮጵያን መለወጥ ይችላል የሚል እምነት በውስጥ ብቻ ሳይሆን በውጭም መፈጠር ስለጀመረ ነው። ነገር ግን ይህ ያመጣነው ገንዘብ ንዋይ የሚባለው ነው። የማድረግ ዐቅም ያለው እናንተ ዘንድ ነው። ካልተጋቡ ብልጽግና የለም። ሌቦች የሥራ ሐላፊዎች፣ ሌቦች ሹማምንቶች ካሉ ግን ብልጽግና የለም። ሌቦችን ማጥፋት ከቻልን፤ ቀን ከሌት መሥራት ከቻልን፤ ያ የምናመጣው ሀብት ብዙ ሀብት መፍጠር ይችላል። ያ





እንዲሆን ጋብቻው እንዳይበላሽ ከእናንተ የሚጠበቀው በእያንዳንዱ የልማት ጥግ በፍፁም ፈቃደኝነት መሳተፍ ነው።

በሐዋሳው ጉባኤ “አዲስ አበባን እንደስሟ አበባ እናደርጋታለን” ብለን ቃል ከገባን በኋላ የተጀመሩ ሥራዎች ለእኛ ከአሰብነው በላይ እርካታ እየሰጡን ያሉ ናቸው። እስከሚቀጥለው ሰኔ ድረስ ቢያንስ እንጦጦን፣ የወንዝ ዳር ፕሮጀክቱን፣ ማዕከለዊውን ፓርክ ወይም የወዳጅነት የሚባለውን እና የአንድነትን ፓርክ እና የአዲስ አበባን መንገድ እናገናኛለን። ይሄ በከተማችን ገፅታ ላይ ከፍተኛ እና ትልቅ ለውጥ ያመጣል። በተደጋጋሚ እንዳልኩት የታችኛው ቤተ መንግሥት 30 ሄክታር ገደማ መሬት ይዟል። ከጎኑ ግዮን የሚባል ሆቴል አለ። 20 እና 30 ሄክታር ያለው። ከጎኑ ፊንፊኔ እና ፍል ውሃ የሚባሉ ሬስቶራንቶች አሉ። ከዚያ አለፍ ብሎ የመንግሥት ቢሮዎች አሉ። በዚያ በኩል ሂልተን ነው። እዚህ የውጭ ጉዳይ እያለ መሀል ላይ ሸራተን ሆቴል አለ። ከሸራተን በኋላ የወዳጅነት ፓርክ የሚሠራበት 47 ሄክታር አለ። ራሱ ቤተ መንግሥቱ 40 ሄክታር ነው። ከቤተ መንግሥቱ በኋላ የፓርላማ እና የኢሕአዴግ ቢሮን ስትጨምሩ አራት ኪሎ አደባባይ እንደርሳለን። ከአራት ኪሎ አደባባይ ከፍ ስትሉ 4፣ 5፣ 6 እየተባሉ ዩኒቨርሲቲዎች፣ የገንዘብ ሚኒስቴር፣ የስብሰባ አዳራሽ፣ የፕላን ኮሚሽን እስከ አሜሪካን ኤምባሲ ድረስ 90 ፐርሰንቱ የመንግሥት ነው። ይሄንን ሁሉ ሀብት፤ ይሄንን ሁሉ የያዘ መንግሥት በየግቢው አንድ አንድ ሰው እያስቀመጠ ለምን ከተማዋን ያደኸያል? በ30 ሄክታር አንድ ፕሬዝዳንት፤ በ40 ሄክታር አንድ ጠቅላይ ሚኒስትር፤ በምናምን ሄክታር እያስቀመጠ በከተማዋ እምብርት ላይ ይሄንን የሚያክል ሀብት ይዞ ከተማ የሚያደኸይ መንግሥት የብልጽግና እሳቤ የለውም። ስለድህነት ስለሚያወራ ተለማምዶታል። በሚቀጥሉት ሦስት ዓመታት ከቦሌ እስከ እንጦጦ ለማገናኘት ትልቅ ህልም ሰንቀን እየሠራን ነው። ይሄ አዲስ አበባን በከፍተኛ ደረጃ ይቀይራል።

በዓለም ላይ በቤተ መንግሥት ውስጥ የዱር እንስሳት መጠበቂያ ወይም የዱር እንስሳት የሚገኙበት ቦታ አዲስ አበባ ብቻ ነው። ኮራ ብላችሁ መናገር ትችላላችሁ። በታችኛው ቤተ መንግሥት ያሉን መኪናዎች መኪና ብቻ አይደሉም። ለንጉሥ የተሠሩ፤ ከገበያ ያልተገዙ፤ በትዕዛዝ የመጡ፤ አንዷን መኪና ብቻ በጨረታ በሚሊዮን ዶላር መሸጥ የሚቻል ሀብት አቧራ ለብሶ፤ እኛም ስለድህነት እያወራን፤ እርሱም የደሃ ዕቃ ሆኖ ቀርቷል። እሱን ማውጣት ያስፈልጋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሮች፣ ፕሬዝዳንቶች፣ ገንዘብ ሚኒስትሮች አነስ ባለ ቢሮ በፎቅ ላይ እየሠሩ ከተማዋን ማበልጸግ እንጂ ማቆርቆዝ የለባቸውም። ግማሹን ከፍተነዋል፤ የቀረውም ቢሮ የምትሆን ነገር ስናገኝ ሙሉ በሙሉ ይከፈታል። ለምሳሌ፤ እኔ ባለሁበት ቪላ ውስጥ በጣም ብዙ ክፍት ቦታዎች፣ ትልቅ የስብሰባ አዳራሽ አለው። አስቡት አሁን እኔ ያለሁበት ቤት የጣልያን ሬስቶራንት ቢሆን፤ አንደኛው ቪላ የፈረንሳይ ሬስቶራንት ቢሆን፤ አንደኛው የዐረቢያን ሬስቶራንት ቢሆን፤ ከስብሰባ ማዕከሉ ጎን የልጆች መጫወቻ ቢኖር እሱን እንኳን አከራይቼ ምን ያህል ሀብት ላመጣ እንደምችል አስቡት። ሳልሸጠው እኔና ግቢው እየተያየን፤ እናንተም ፎቶ ማንሣት አትችሉም እየተባላችሁ ከምትዘልቁ፤ በብልጽግና መንገድ እያንዳንዷን ታሪክ፤ እያንዳንዷን ቁስ፤ እያንዳንዷን ጊዜ ወደ ገንዘብ እና የድህነት ቅነሳ መንገድ አድርገን ከሠራንባት፤ በተለይ በተለይ ካልሰረቅን ብልጽግናን እውን ማድረግ እንችላለን። ሌቦች ገንዘብ መስረቃቸው ብቻ አይደለም ለማዘዝ አስቸጋሪ ስለሆኑ ነው። ሌቦችን እንደማዘዝ አስቸጋሪ ነገር የለም። ደሃ ጠቅላይ ሚኒስትር ሀብታም ሚኒስትር እንደማዘዝ የሚከብደው ነገር የለም። ስለዚህ ሌቦች እንዳይበራከቱ በከፍተኛ ደረጃ እጃቸውን እንዲሰበስቡ ተባብረን ካልሄድን፤ የእነርሱ ጉልበት እየበረታ የእኛ እየደከመ ከሄደ፤ ድህነትን አጥፍቶ ወደ ብልጽግና መሄድ ያስቸግራል። እሱን ማድረግ ከቻልን ቅድም እንዳነሣሁላችሁ በቤተ መንግሥት ውስጥ በጣም ብዙ ቅርሶች አሉ። መኪና ብቻ ሳይሆን ወርቅ አለ። የዝኖን ጥርሶች አሉ። የከበሩ ዕቃዎች አሉ። እነርሱን ጨምሮ የእንስሳት መቆያውን ጨምሮ፣





ታሪኩን ጨምሮ፣ ፓርላማን ጨምሮ እስከ እንጦጦ ድረስ ከሄዳችሁ እኔ እስከአሁን ባለኝ ልምድ ዓለም ላይ ይሄንን የሚያክል ታሪክ፤ ይሄንን የሚያክል መልክአ ምድር ያለው፤ ስፋት ቦታ የያዘ ዋና ከተማ የለም። ላታምኑ ትችላላችሁ! የለም።

እንጦጦ አሁን ከያዝነው ፕሮጀክት ስትሻገሩ ለሁለት ተቋማት የታጠረው ቦታ አንድ ሺሕ ሄክታር ነው። እናንተም አታውቁትም፤ እሱም አያውቃችሁ። ምክንያቱም ያ የተረሳ ዕቃ ስለሆነ። ነገር ግን እንጦጦ 10 ቢሊዮን ዶላር ብንጨምርበት በልቶ አላየሁም የሚል ከፍተኛ ብቃት ያለው ቦታ ነው። አሁን ወጣ ብላችሁ እንጦጦን ብታዩ ፕሮጀክት ስለተጀመረ በጣም የሚገርም ነገር ነው ያለው፤ በካቦ ላይ የሚሄድ መጓጓዣ ማድረግ እንችላለን። የውሃ ፏፏቴ ማድረግ እንችላለን። የፈረስ መጋለቢያ ማድረግ እንችላለን። የሳይክል መጫወቻ ማድረግ እንችላለን። የእግር ኳስ መጫወቻ ማድረግ እንችላለን። እዚያ ሆኖ አዲስ አበባን በደንብ፣ በጥራት ማየት የሚያስችሉ ቦታዎች ለይተን መሥራት እንችላለን። ይሄ እያለ ፓርክ የለም፤ መሄጃ የለም የምትሉ ወጣቶች በእግራችሁ እሑድ እሑድ እንጦጦን ማየት ይኖርባችኋል። በ1966፤ በ1983 ዓ.ም. ኢትዮጵያ ውስጥ ሁለት አብዮቶች ተካሂደዋል። አሁን 2010 ዓ.ም. በሌላ መልክ ራሱን ይዞ መጥቷል። ከእንግዲህ ወጣቶች መወሰን ያለብን የአንድም ሰው ሕይወት ሳይጠፋ፣ አብዮት ሳይኖር፤ ስለ ድመቷ ጥፍር ሳንከራከር፤ ወደ ብልጽግና በሐሳብ እና በዕውቀት የምንሄድበት፤ ሰው የሚመርጥባትን እንጂ የማይሞትባትን ኢትዮጵያ ለመፍጠር የሁላችሁ ትብብር በጣም በእጅጉ የሚያስፈልግ መሆኑን በዚህ አጋጣሚ ከአደራ ጭምር ለአሳስባችሁ እፈልጋለሁ።

በመጨረሻም በሁላችሁም ውስጥ፤ በእኔም ውስጥ ሁለት ተኩላዎች አሉ። ሁለት የሚያስፈሩ ተኩላዎች በእያንዳንዱ ሰው ውስጥ አሉ። አንደኛው ተኩላ ዘረኛ፣ ጥላቻ የሞላበት፣ ተሳዳቢ፣ የማይሠራ፤ ግን ሥራ የሚነቅፍ፤ የሚሳደብ፣ የሚነቅፍ፣ የሚዋሽ፣ የሚሰርቅ፣ ለራሱ የሚያግበሰብስ ተኩላ ነው። አንደኛው

ተኩላ እውነት የሚወድ፣ የሚሠራ፣ የታሪክን ልክ የሚገነዘብ፣ በይቅርታና በፍቅር የሚያምን፣ በመደመር ወደፊት መሄድ ይቻላል የሚል እሳቤ ያለው ነው። “ከእነዚህ ሁለት ተኩላዎች ማን ያሸንፋል?” የሚል ጥያቄ የሚያነሣ ሰው ካለ በእያንዳንዳችሁ ውስጥ ያለው ሁለት ተኩላ አሸናፊ የሚሆነው ይበልጥ የመገባችሁት ነው። ይበልጥ የመገባችሁት እና ያፋፋችሁት ምቀኝነትን፣ ሌብነትን፣ ተንኮልን ከሆነ በበላው ልክ ስለሚፋፋ ደግነትን ይውጠዋል። በየቀኑ የምትመግቡት ደግነትን፣ መልካምነትን፣ እውነተኝነትን ከሆነ ይፋፋና ክፋትን ይውጠዋል።

ምርጫው የእናንተ ነው። በውስጣችሁ የሚፋፋው ተኩላ የእውነትም ይሁን የውሸት ያንን ተኩላ ብቻ በልቶ አያበቃም። እናንተንም አካባቢያችሁንም ያጠፋል። በውስጣችሁ ያለው ተኩላ መልካምነት የተሞላ፣ ፍቅር የተሞላ፣ ሥርቶ ማለፍን የሚያስብ እንዲሆን ወጣቶች ጊዜያችሁን፣ ጉልበታችሁን፣ ዕውቀታችሁን ለመልካም ነገር እንድታውሉ አደራ እያልኩ፤ የሚወደን የረዳን በኢትዮጵያ የማይጨክነው ፈጣሪ ልቦናችሁን ያብራላችሁ! ማለት እፈልጋለሁ።

ልብ ካልበራ በስተቀር በ40 ሄክታር ተቀምጠህ ሰው በኮንዶሚኒየም እንደሚሰቃይ አይገባህም። እና የልብ አብርሆት በጭንቅላት ብቻ ሳይሆን ከልብም ስለሆነ እግዚአብሔር ልባችሁን ያብራላችሁ! ሰላማችንን ያብዛልን! ይጠብቅልን! የብልጽግና ጎዳና የተረጋገጠ ይሁን! በመገናኘታችን በጣም ደስ ብሎኛል።

**መልካም የውይይት ጊዜ ይሁንላችሁ!**
**አመሰግናለሁ!**





# የኤሌክትሮኒክስ የአንድ መስኮት አገልግሎት ፕሮጀክት መጀመር ማብሠሪያ ንግግር

ታህሳስ 25/ 2012 ዓ.ም.

ዩኼ የተሰበሰብንበት አዳራሽ ከተመረቀ ሳምንት ገደማ ይሆነዋል። እንደ ዛሬ ግን ግርማ ሞገስ አግኝቶ አምሮ አላየሁትም። ቁጭ ብዬ እያሰብኩ ነበር። በኢትዮጵያ ውስጥ የሚያማምሩ መንገዶች ብንሠራ፤ የባቡር መንገድ ብንሠራ፤ የሚያማምሩ ፎቆች ብንሠራ፤ ደስተኛ ዜጎች መፍጠር እስከአልቻልን ብልጽግና፤ ብልጽግና አይሆንም። የሚያምር አዳራሽ ሠርተን ለአለፈው አንድ ሳምንት ስናይ ነበር። ዛሬ ያየነውን ውበት ያጣዉ እንደ እናንተ የሚያማምሩ ሰዎች ደስተኛ ሆነው ውስጡ ስለአልተቀመጡ ነው። ስለዚህ ብልጽግና ማለት መሠረተ ልማቱ ብቻ ሳይሆን የሚስቡ ደስተኛ ዜጎችን ማየትም ጭምር መሆኑን እግረ መንገድ ለማስታወስ ነው።

የአንድ መስኮትን ጠቀሜታ ሮቤል ጥሩ አድርጎ ገልፆታል። እሱ በሙያ ስለገለጸው ደግሞ ድሮ የአንድ መሥሪያ ቤት ሠራተኞች ስለነበርን ማርኬቲንግ ላይ ትንሽ ስለሚቀረው እኔ ላግዘው ብዬ ነው። የአንድ መስኮት አገልግሎት ማለት፤ አንድ ሰው ምግብ ማዘጋጀት ቢፈልግ አትክልት ተራ ሄዶ አትክልት መግዛት፤ በርበሬ ተራ ሄዶ በርበሬ መግዛት፤ ቄራ ሄዶ ሥጋ መግዛት፤ መርካቶ ሄዶ የቀሩትን ነገሮች መግዛት ሳይጠበቅበት፤ አንድ ሱፐር ማርኬት ሄዶ አትክልቱንም፤ ቅቤውንም፤ በርበሬውንም ገዝቶ ባጠረ ጊዜ ምግቡን ማዘጋጀት የሚያስችል ቴክኖሎጂ ማለት ነው።

ይሄ ቴክኖሎጂ በኢትዮጵያ ውስጥ የኢኮኖሚ ማሻሻያው አንዱ አጀንዳ “ኢዝ ኦፍ ድሪም ቢዝነስ” ነው። የሚነግዱ ሰዎች ሐሳብ እያላቸው፣ ገንዘብ እያላቸው፤ በመንግሥት አገልግሎት አሰጣጥ ችግር የተነሣ ለረዘመ ጊዜ ስለሚንገላቱ ትርፋማ አይሆኑም። ይሰላቻሉ። ይበልጥ እንዳይሠሩም ያደርጋቸዋል። መንግሥት ሰርቪሱን አሣልጦ ነጋዴዎች በሚያስገቡትም በሚያስወጡትም የንግድ ዕቃ ላይ ሳይቸገሩ ማጓጓዝ እንዲችሉ፤ ከዚያ ጋር ተያይዞ ደግሞ የሎጀስቲክስ ሥርዓት ማዘመን፤ የሚል በመንግሥት ስብራት ውስጥ ያየነው ጉዳይ ነው። አንድ ሱፐር ማርኬት ብቻ ሄዶ መግዛቱ ዘመናዊ አያሰኘውም። ያ ሱፐር ማርኬት በሰፈራችን ከሌለና አምስት ዓሥር ኪሎ ሜትር መጓዝ ካለብን ዞሮ ዞሮ መርካቶና አትክልት ተራ ከመሄድ አላዳነውም። አንድ ቦታ ማድረግና ማፍጠን ስለሚፈልግ የአንድ መስኮት አቅርቦት ጋር ሲቀናጅ እጅግ በጣም ዘመናዊ የሆነ የንግድ ሥርዓት መፍጠር ያስችላል።

ይህም ሆኖ ዛሬ የተሸላለሙ ሚኒስትሮች እኔ የመሰለኝ ቀብድ እንደወሰዱ ነው። ገና ዛሬ የጀመርን ስለሆነ እንዳትዘናጉ ለማለት ይመስለኛል። እስከአሁን ለተሠራው ሥራ ሳይሆን ከዚህ በኋላ ለሚሠራው ሥራ የተሰጠ ሽልማት ይመስለኛል። በተለይ ሙያተኞች አዳዲስ መተግበሪያ ሲጀመር በባሕሪው እስኪለመድ ድረስ የማሰልቸት እና አልፎ አልፎም የመቋረጥ ባሕሪ ስለአለው ዛሬ እንዳስመረቃችሁ ሳታስቡ ተግታችሁ በዚህ መተግበሪያ የሚጠቀሙ ተዋንያን በሙሉ ሳይቸገሩ መገልገል እስከሚችሉ ድረስ የተሻለ እና የተለየ ጥረት ማድረግ እንዳለባችሁ እንዳትዘነጉ አደራ ማለት እፈልጋለሁ።

እንግዲህ ይሄም ሆኖ እኛ በጣም ኋላ ቀር ነን። አሁን ዓለም እየተነጋገረ ያለው በአንድ መስኮት አገልግሎት ሳይሆን ሰው ቤቱ ተቀምጦ፤ ግማሽ ኪሎ ሥጋ እና ግማሽ ኪሎ በርበሬ ኦንላይን አዝዞ፤ ድሮን ወይም ሰው አልባ አውሮፕላን በቤቱ ቁጥር ልክ እንደ ፖስታ አምጥታ በር ላይ እስከምትጥልለት ነው። ቴክኖሎጂ በዓለም ላይ እያደገ ያለው። አሁንም በጣም ሩቅ መሆናችንን አውቀን ከጀመርን አልቀረ በፍጥነት የቀሩትን ዘርፎች ማስተሳሰር፤ ብዙ ነጋዴዎች ወደእዚህ እንዲገቡ ማድረግ የኢዝ ኦፍ ድሪም ቢዝነሳችንን አሁን ካለበት በጣም ወደኋላ ከቀረው ትንሽ ወደፊት ማምጣት ይኖርብናል። ጠቀሜታው ብዙ ስለሆነ፤ ኢንቨስተሮች የወርልድ ባንክን የኢዝ ኦፍ ድሪም ቢዝነስ ኢንዴክስ ያያሉ፤ ኢትዮጵያ በጣም ወደኋላ የቀረች ሀገር ናት። ያ ማለት ገንዘብ ይዤ ብሄድ በቀለለ መንገድ ቢሮክራሲው ሰርቪስ ሰጥቶኝ ሠርቼ ማትረፍ አልችልም የሚል መልእክት ስለአለው፤ የመንግሥት ተቋማት ብዙ ሃብት እንዲመጣ፤ ንግድ እንዲሣለጥና ብልጽግና እውን እንዲሆን ከፈለጋችሁ ይህንን መረጃ ጠቋሚ /ኢንዴክስ ማዘመን ማሻሻል የግድ ይሆናል።

የግሉ ሴክተር ደስተኛ ሆኖ በየዕለቱ አዳዲስ ነገር እየፈጠረ የማይሠራ ከሆነ ወደ ብልጽግና መሄድ አይቻልም። መንግሥት ለብልጽግና ድልድይ መሆን ይችላል እንጂ ብልጽግናን ማረጋገጥ አይችልም። ብልጽግና የሚረጋገጠው ፈጣሪ በሆኑ ባለሀብቶች ነው። ይሄንን የባለሀብቶች ሚና ሳይሻማ ደጋፊ ሚናዉን የሚጫወት ከሆነ በአቀድነው ጊዜ የኢትዮጵያን ብልጽግና እውን ማድረግ ስለሚቻል ከእኛ የሚጠበቀው የተቀላጠፈ አገልግሎት መስጠት፤ ከናንተ የሚጠበቀው ሲጐድል ማፈግፈግ ሳይሆን ሲጐድል የጐደለውን እየሞላችሁ እንዲሻሻል እና ይበልጥ እንዲስተካከል ማድረግ ይሆናል።

ተባብረን ከሠራን ብልጽግናን እውን ማድረግ ይቻላል። ብልጽግና አማራጭ አይደለም። ግዴታ ያስፈልገናል። ለዚህ ለሚያስፈልገን ነገር ደግሞ በትብብር በቅንነት ማገልገል ያስፈልጋል። የአንድ መስኮት አንዱ ጠቀሜታው ሌብነትን ለመቀነስ ነው። ኢትዮጵያ ውስጥ አንዱ ካንሰር ሌብነት ነው። ሌብነት ገንዘብ መውሰድ ብቻ ሳይሆን ሰው ገንዘብ ከወሰደ በኋላ ሥራን ማደናቀፍ እንደ ባህል እያደገ ስለመጣ፤ ሌብነት እንዳይስፋፋ በቴክኖሎጂ ቨርቹዋል ሰርቪስ መስጠት መጀመር በእጅጉ ጠቃሚ ስለሆነ ለዚህ ነው። በዚህ መንገድ እንዲመረቅና ሁላችንም ግምት የምንሰጠው ሥራ መሆኑን ለማሳየት የተፈለገው ዋናው ውጤት የሚለካው ግን ነጋዴዎች በሚቀጥለው ሁለት ሦስት ወር ይህ ሲስተም ትናንት ከነበረው ኋላ ቀር አገልግሎት የተሻለ መሆኑን እነርሱ ሲያረጋግጡ ነው። እነሱ ማረጋገጥ እንዲችሉ ዛሬ ያስመረቃቸው ሙያተኞችና እና የተሸለማችሁ የመንግሥት ተቋማት ይህ ደስተኝነት እስኪረጋገጥ ድረስ በትብብር መሥራት እና ማረጋገጥ ከእናንተ የሚጠበቅ መሆኑን ላሳስባችሁ እፈልጋለሁ።

የመጨረሻው መልእክቴ ሰሞኑን "ኤክሳይስ ታክስ ተጨምሯል" በሚል ከፍተኛ ሽብር በከተማ ውስጥ እንዳለ ሰምቻለሁ። ይህ ኤክሳይስ ታክስ የተፈለገበት ዋናው ምክንያት በአሮጌ መኪና እና በመጠጥ፣ በሲጋራ አካባቢ ላይ ተጨማሪ ታክስ በመጨመር የመንግሥት ገቢ ማሻሻል ብቻ ሳይሆን፤ ከሲጋራና መጠጥ የሚገኘው በቀጥታ ለጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ፈሰስ የሚደረግና እዚያ ያለውን ጉዳት ለመቀነስ ነው።

በኢትዮጵያ በቀን ምን ያህል ሰው በካንሰር፤ ምን ያህል ሰው በወባ እንደሚሞት ስለማይታወቅ፤ ፌስቡክም ስለማይናገር፤ ተጠያቂ የጠፋበት አንዱ ችግር የማይተላለፉ በሽታዎች በጣም ብዙ ሰው እየቀጨ ነው። ስትሮክና ካንሰር በጣም ብዙ ሰው እየቀጨ ነው ያለው፤ ግን ባለቤት የለውም። በበሽታ ሞቱ ስለሚባል ያንን ነገር የማዘመንና የማስተካከል ሥራ ባለቤት እንደሌለው እየተወሰደ ስለሆነ፤ በአንድ በኩል መጠጥና ሲጋራን እንዲቀንስ ለማድረግ፤ በሌላ መንገድ ከዚያ የሚገኘውን ገቢ ለጤና ጥበቃ ፈሰስ ለማድረግ፤ በዚህ ረገድ ያለውን አደጋ ለመቀነስ፤ የእናቶችን፣ የሴቶችን፣ የሕፃናትን ሞት ለመቀነስ መሆኑን ከግምት ማስገባት ያስፈልጋል።

መኪናን በሚመለከት፤ ሁላችሁም እንደምታውቁት ኢትዮጵያ ውስጥ ከፍተኛ የመኪና አደጋ አለ። ከፍተኛ የመኪያ አደጋ ያለው በብዙ ምክንያት ቢሆንም አንደኛው መሠረተ ልማት ነው። ሁለተኛው የምናመጣቸው መኪናዎች ናቸው። ከዱባይ ወደ ኢትዮጵያ የሚመጡ የሚሰፉ መኪናዎች አሉ። ከተለያየ ቦታ አካላቸው ተወስዶ ልክ እንደጨርቅ ተሰፍተው፤ መሪያቸው ዞሮ ወደዚህ ይመጣሉ። ለጊዜው በረከሰ ገንዘብ የገቡ ቢሆንም ብዙ ሰው እየቀጩ ነው ያሉት። ከሕይወት ቅጥፈት በተጨማሪ ነዳጅ የሚባል ችግር አለ። ከሱ ጋር ተያይዞ የውጭ ምንዛሬ የሚባል ነገር አለ። የመንገድ ጥበት አለ። የትራፊክ መጨናነቅ የሚባል ነገር አለ። ሲሰናሰል የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ በእጅጉ እየጐዳ ስለሆነ አሮጌ መኪና በረከሰ ብር ለጊዜው አምጥተን ውሎ ሲያድር የገዛውን ሰው ወይም ወንድሙን ከሚገድል፤ እኛንም በመለዋወጫና በነዳጅ ከሚያስቸግረን ትኩረታችን አዲስ መኪና ይሁን ነው። አዲስ መኪና ሲሆን መካከለኛ ገቢ ያላችሁ ሰዎች እንደምትቸገሩ ስለሚገባን በአዲስ መኪና ላይ ያለውን ታክስ መቀነስ ይሻላል። አዲስ መኪና ውድ አድርጐ አሮጌ መኪና በአነሰ ታክስ እያስገቡ ሕይወት የሚቀጠፍበት ምክንያት ከሚሆን፤ በመለዋወጫ ችግር ከምንቸገር አገልግሎቱም ያጠረ ጊዜ ከሚሆን፤ አዳዲስ መኪና ላይ የጫነውን ታክስ በመቀነስ በተቻለ መጠን ሻል ያሉ መኪናዎች ማስገባት ይሻላል። ለጊዜው የተጎዳችሁ የሚመስላችሁ ሰዎች ከአላችሁ ከጥቂት ዓመታት በኋላ ብልጽግና እውን ሲሆን እና መኪና ማምረት ስንጀምር አሁን እየተሰፉ የሚገቡ መኪኖች "የት እንጣላቸው?" የምንልበት ጊዜ ሊመጣ ስለሚችል፤ ከወዲሁ ነገን እያሰብን አዳዲስ መኪናዎች ለማምጣት፤ እነሱን ለማምጣት የነበረባችሁን የአገልግሎት እና የታክስ ጫና ግን መንግሥት

ቢቀነስ፤ የሰውን ሕይወት ብንታደግ፤ በመለዋወጫ ያለውን ችግር ብንቀንስ፤ አንድ አዲስ መኪና በኪሎ ሜትር የሚጠይቀው ነዳጅና አሮጌ መኪናም እኩል ባለመሆኑ በብዙ መንገድ አገርንና ሕዝብን የሚጎዳ መሆኑን ተገንዝባችሁ እና የማይቀየር ሐሳብ መሆኑን አውቃችሁ ወደ አዲሱ መንገድ ለመሄድ መሞከር ይኖርብናል። የማይቀየር ያልኩበት ምክንያት ኢትዮጵያ ውስጥ እስከአሁን አንድ ሚሊዮን የማይበልጥ መኪና ነው ያለው። 110 ሚሊዮን ሕዝብ ነው ያለው። አንድ ሚሊዮን የመኪና ባለቤቶች እንዳታኮርፉ ተብሎ ሕግ አይቀየርም። 109 ሚሊዮን መኪና የሌለው ሰው ስለአለ። በደንብ በመደመጥ ሳይሆን ለሁላችን በሚጠቅም ነገር መሆን ስለአለበት፤ ለታክሲ ሹፌሮች፣ ለፐብሊክ ትራንስፖርት ለሚሰጡ ሰዎች የተለየ ድጋፍ ተደርጎ አዳዲስ መኪኖች እንዲገቡ ይደረጋል። መካከለኛ ገቢ ያላቸው ሰዎችም አዲስ መኪና ለመግዛት ሲፈልጉ የሚጠቀሙበት፤ አልፎ አልፎም ራይድ በሚባለው አገልግሎት አማካኝነት ወጪያቸውን የሚመልሱበት መንገድ ማምጣት ከረጅም ጊዜ አንፃር አዋጭ ስለሆነ፤ ምናልባት በደንብ ሳትገነዘቡ ለመንግሥት ብዙ ገቢ ለማስገባት ብሎ የወጣ ሕግ አድርጋችሁ የምትወስዱ ሰዎች ካላችሁ፤ ብዙ ገቢ ለማስገባት ሳይሆን ገቢያችንን ቀንሰን ብዙ ሕይወት ለማዳን መሆኑን እንድትገነዘቡ አደራ ለማለት ነው። መልካም ምሽት!

**ስለመጣችሁ እጅግ አድርገን እናመሰግናለን!**





# የገና በዓል ዕለት ለአረጋውያን፣ ለአካል ጉዳተኞች እና ለአዳጊዎች ያደረጉት የምሳ ግብዛ ንግግር

ታኅሣሥ 28/2012 ዓ.ም.

ይህን ዕለት ስናስብ ከእምነት ባሻገር አረጋውያን እናም አዳጊ ኽፃናት በጋራ ሆነው ምሳ እየበላን ብናከብረው፤ ይህም ልምምድ በመላ አገራችን በሁሉም ቦታ ቢዳረስ፤ ቢያንስ ሁላችንም ደስ እያለን የምናሳልፍበት ቀን ይሆናል ማለት ነው።

በኢትዮጵያ ውስጥ ላሉ ሀብታሞች፣ ባለሥልጣናት ወይም ማድረግ ለሚችሉ ሰዎች ልነግራቸው የምፈልገው ነገር ዛሬ ከአረጋውያን እና ከአዳጊ ሕፃናት ጋር የማሳልፈው ጊዜ የሚሰጠኝን ደስታ ከየትም ሽምቼ ላገኘው አልችልም። ሁሉም ቦታ ይህንን ብናደርግ ለአንዳንዶቻችን ተርፎ የሚደፋ፤ ለሌሎቻችን

ደግሞ በጣም አስፈላጊ የሆነ ነገር የምናገናኝበት ቀን ቢሆን፤ ያላችሁ ሰዎች ከሌላቸው ጋር፤ ጉልበት ያላችሁ ጉልበት ከሌላቸው ጋር፤ የምታዩ ማየት ካልቻሉት ጋር በጋራ በመሆን የሚታወስ ቀን ቢሆን ይጠቅማል፤ ይበጃል። ጥሩ ልምምድም ይሆናል።

እዚህ ያላችሁ አዳጊዎች የጊዜ ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር እናንተም አረጋዊ መሆናችሁ አይቀርም። ዛሬ አረጋውያንን ካላከበራችሁ፤ ዛሬ መንገድ ካልለቀቃችሁ፤ ዛሬ ወንበር ካልለቀቃችሁ ነገ አረጋዊ ስትሆኑ ማንም አያከብራችሁም። ሁሉም የሚያጭደው የዘራውን ነው ። ታላቅን ማክበር፣ አረጋውያንን መርዳት፣ ልብሳቸውን ማጠብ፣ መንከባከብ ነገ ለሁላችንም የሚሆን ነገር ነው፤ ይከፈላል። አድርጎ የማይከፈለው ሰው የለም። በራሱ ባያገኘው በልጆቹ ያገኘዋል፡፡ በመልካምነት ታላላቆችን የማክበር፤ የእነሱን ምርቃት፤ የእነሱን ጸሎት መቀበል ጠቃሚ እንደሆነ እያሰባችሁ እንድታድጉ ያስፈልጋል፡፡

አረጋውያንም ብትሆኑ ኢትዮጵያ መልካም አገር ናት። ብዙ ደጋጎች ያሉበት አገር ነው። ምንም እንኳን ክፉዎችም እየበቀሉ ያሉ ቢሆንም መስጠት፣ መርዳት፣ ማገዝ የሚፈልጉ ሰዎች ያሉበት አገር ነው። መስረቅ፣ መቀማት የሚፈልጉ ሰዎች ያሉበት አገር ቢሆንም፤ የሚሰርቁትን ብቻ ሳይሆን የሚለግሱትንም ማየት ጠቃሚ ነው። የሚያጠፉትን ብቻ ሳይሆን የሚያለሙትን ማየት ጥሩ ነው። ትውልድ ይቀጥላል። አገር ይቀጥላል። በምድር ስንኖር ማናችንም ብንሆን እናልፋለን። እስክናልፍ መልካም ነገር ሠርተን ለማለፍ እንድንችል፤ የሚያሳዝን ጉዳይ ቢኖርም እንኳን ሐዘናችሁን ቀንሳችሁ በልጆች፤ በአዳጊዎች ላይ መልካም ቃል እንድትዘሩ፣ እንድትመርቁ፣ እንድትጸልዩላቸው እናንተንም አደራ ማለት እፈልጋለሁ።

**አመሰግናለሁ!**

# በደቡብ አፍሪካ ለሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ያደረጉት ንግግር

ጥር 4/2012 ዓ.ም.

**የተከበራችሁ የሀገሬ ልጆች፤**
**ክቡራት እና ክቡራን በደቡብ አፍሪካ እና በአካባቢዋ የምትገኙ ወዳጆቼ፤**

ከምትወዱት እና ከምትናፍቁት ሀገር እና ሕዝብ የከበረ ሰላምታ ይዤላችሁ መጥቻለሁ። እንደ ምን ከረማችሁ? ወቅቱ የአዲስ ዓመት እና የገና በዓላት የሚከበሩበት እንደመሆኑ መጠን እንኳን አደረሳችሁ! እያልኩ፤ አዲሱ ዓመት የብልጽግና ዘመን እንዲሆንላችሁ ያለኝን ምኞት ልገልፅላችሁ እፈልጋለሁ።

በኢትዮጵያ ወቅቱ የእኛ ነው፤ ጊዜው የኢትዮጵያ ነው። ጉዞውም ወደ ብልጽግና ነው ብለን ነበር። ይህ ዛሬ በደቡብ አፍሪካ በመደገሙ እንኳን ደስ

አላችሁ! ልላችሁ እፈልጋለሁ። በእናንተ ታሪክ እንደምታውቁት የአገራችሁ መሪ የእናንተ ጉዳይ ግድ ብሎት ከዚህ አገር መንግሥት ጋር ተነጋግሮ ፍሬያማ፤ ተስፋ ሰጪ ድርድር ያደረገበት የመጀመሪያው ቀን ከመሆኑም ባሻገር፤ ኢትዮጵያ ለማዲባ በጭንቁ ዘመን ፓስፖርት ሰጥታ የትግል አጋር እንደሆነችው ሁሉ፤ ዛሬ ደቡብ አፍሪካን ቤታችን ብለው የሚሠሩ የሚተጉ ኢትዮጵያውያን ተከብረው እንዲኖሩ፤ ሕጋዊ ፍቃድ እንዲሰጣቸው ለደቡብ አፍሪካ ፕሬዚዳንት ሲሪል ራማፉዛ “ያለን ጥያቄ አንድ ብቻ ነው። እሱም የዜጎቻችን ጉዳይ ነው” ብለን አበክረን ስለአነሣን እሳቸው በውጭ ጉዳይ ኮሚቴያቸው የሚመራ ኮሚቴ አቋቁመው የኢትዮጵያን ዳያስፖራ ጉዳይ በተለየ መንገድ በማየት ሕጋዊ ርምጃ እንደሚወስዱ ቃል ገብተውልናል።

ኢትዮጵያውያን ደቡብ አፍሪካን እንደምትወዱ ስነግራቸው፤ እሳቸውም ሁለት መልእክት ነግረውኛል። “ኢትዮጵያውያን ለፍቶ አደር፣ ሠርቶ አደር፣ ላብአደር መሆናቸውን እናውቃለን” ብለውኛል። ከዚህ በተጨማሪ በእኛ አምባሳደር በኩል በቅርቡ የማኅበረሰቡ ተወካዮች ከፕሬዚዳንቱ ጋር በዝርዝር እንድትወያዩ ቀጠሮ ተይዞላችኋል። 2020 በኢትዮጵያ በደቡብ አፍሪካም አዳዲስ ዜና የምንሰማበት የብልጽግና እና የተስፋ ዘመን ስለሆነ እንኳን ደስ አላችሁ!

ውድ የአገሬ ልጆች፤ ራስን አሸንፎ ለወገን ለመትረፍ መታተር የኢትዮጵያዊ ማንነት ሆኖባችሁ በየብስ እና በባሕር፤ በእግር እና በአየር አገራትን አቋርጣችሁ ከኢትዮጵያ እስከ ደቡብ አፍሪካ በተዘረጋው ጉዞ ውስጥ ያለፋችሁት ውጣ ውረድ እጅግ ከባድ እንደሆነ ምንም ጥርጥር የለውም። እዚህ ከደረሳችሁ በኋላ በሰው አገር የምትመሩት ኑሮ ምን ያህል አስቸጋሪ እንደሚሆንባችሁ አስረጅ አያሻውም። እነዚህን ሁሉ ችግሮች ተቋቁማችሁ ለወገናችሁ ሕይወት መለወጥ የምትከፍሉት ዋጋ የሚደነቅ ብቻ ሳይሆን ታላቅ ክብር የሚሰጠው ሆኖ ስለአገኘሁት፤ የእናንተን ጉዳይ ዋነኛ አጀንዳ አድርጌ ከደቡብ አፍሪካ





መንግሥት ጋር በመነጋገሬ እና ተስፋ ሰጪ ምላሽ በማግኘቴ የተሰማኝን ልባዊ ደስታ ልገልፅላችሁ እፈልጋለሁ።

ለእኛ ለኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆን ለደቡብ አፍሪካ መንግሥትም ኩሩ ሠርቶ አደር መሆናችሁ በመረጋገጡ ሀገራችሁ ኢትዮጵያ እና እኔም እጅግ የኮራሁባችሁ መሆኑን ልገልፅላችሁ እፈልጋለሁ። በባዕድ ምድር ተግታችሁ ራሳችሁን ከችግር አረንቋ ልታወጡ ታግላችኋል። ያገኛችሁትን ዕድል በመጠቀም ከራሳችሁ አልፋችሁ ለሌሎች መትረፍን በተግባር አሳይታችኋል። ለሕዝባችሁ እና ለአገራችሁ የምታደርጉትን ሁሉ ከፍተኛ ዋጋ የምንሰጠው መሆኑን ስገልፅላችሁ በታላቅ ደስታ እና አክብሮት ነው። ከሩብ ክፍለ ዘመን ባነሰ ጊዜ በደቡብ አፍሪካ የፈጠራችሁት ጠንካራ የዳያስፖራ ማኅበር እጅግ በጣም የሚደነቅ ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያዊነትን ያሳያችሁበት የአንድነታችሁ ቀመር ነውና እንኳን ደስ አላችሁ! ይህንን ያደረጋችሁት ለአገራችሁ እና ለወገናችሁ ባላችሁ ፍቅር እና ተቆርቋሪነት የመነጨ በመሆኑ ኢትዮጵያውያን ሁሉ በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በመላው ዓለም የሚገኙ ዳያስፖራዎች ከእናንተ የሚማሩ እና የሚኮሩባችሁ መሆኑን አረጋግጥላችኋለሁ።

የተከበራችሁ ወገኖቼ፤ በዚህ ልዩ ቦታ ላይ ቆሞ ታላቁን የነፃነት እና የሰላም አባት፤ የይቅርታ እና የምሕረት ሰው፤ የአፍሪካ ኩራት እና የኢትዮጵያችን ወዳጅ የነበሩትን ኔልሰን ማንዴላን ሳያነሱ መቅረት በፍፁም አይታሰብም። ዘረኝነትን በመቃወም ለወገኖቻቸው ነፃነት እና እኩልነት ባደረጉት መራራ ትግል ሳቢያ በብዙ ተንገላተዋል። ለ27 ዓመታት በሮቢን ደሴት የወህኒ ሕይወታቸው ብዙ ሥቃይ እና ግፍ ተቀብለዋል። ቢሆንም ግን ስቃያቸው እኩልነትን፤ እንግልታቸው ሰላምን፤ መታሰራቸው ነፃነትን፤ መገፋታቸው ዕርቅን አስገኝቷል። በእንቅፋት ከተሞላው መንገድ ባሻገር ያለውን ደልዳላ ሜዳ ማየት በመቻላቸው ለአገራቸው እና ለወገናቸው አንጻራዊ ለውጥ አስገኝተዋል። ብዙዎች “የእኚህ ሰው ጥንካሬ ከየት መነጨ?” ሲሉ ይጠይቃሉ።

“እንዴት የሰላም፣ የይቅርታና የፍቅር ሰው ለመሆን ቻሉ?” ብለውም አክለው ይጠይቃሉ። ለአገር እና ለወገን እየተሰቃዩ ዓመታትን መቆየት ቢከብድም ብዙዎች ዋጋ ለመክፈል ሲዘጋጁ ብናይ ያን ያህል አይገርመን ይሆናል። ነገር ግን የረገሙትን የመረቀ፤ ያቆሰሉትን ያከመ፤ በአጠቃላይ የበደሉትን ይቅር የሚል እና በፍቅር የሚያቅፍ ሲገኝ ግን በእጅጉ ይደንቃል። “ምን ዓይነት ጥንካሬ ነው?” ብለን እንድንጠይቅም ያስገድደናል።

በተለይ ዛሬ አገራችን በብዙ ፈተና ውስጥ በምታልፍበት በዚህ ጊዜ የምትኖሩ ኢትዮጵያውያን ይህንን ጥያቄ መጠየቅ ብቻ ሳይሆን ትክክለኛውን መልስ ለማግኘት የመፍትሔው አካል ለመሆን አሁን ከምትኖሩባት ደቡብ አፍሪካ ብዙ እንደተማራችሁ እና እንደምትጠቀሙበትም ጽኑ እምነት እንዳለኝ ልገልፅላችሁ እፈልጋለሁ። ማዲባ በአንድ ወቅት እንዲህ ብለው ነበር። “ከእስር ቤት ወጥቼ ወደ ነፃነት በሚወስደኝ በር ላይ ስደርስ ምሬቴን እና ጥላቻዬን ጥዬው ካልወጣሁ በቀር እስር ቤቱ እንደማይለቀኝ አስቤ በመወሰን እናም በማድረግ ነፃነቴን እዚያው ሮቢን ደሴት ላይ ዐውጄ በመውጣቴ የመጨረሻው ዘመን ሥራዎቼ የተሳኩ እንዲሆኑ ረድተውኛል” ብለው ነበር። ምንም እንኳን አፍላ ዕድሜያቸውን እስር ቤት ቢበላባቸውም የ72 ዓመቱ ማዲባ ጥላቻ እና ምሬትን እዚያው ሮቢን ደሴት ጥለው ለመውጣት አላቅማሙም። አፓርታይድ ከቆለፈባቸው እስር ቤት ብቻ ሳይሆን በኅሊናቸው ውስጥ ከተገነባው እስር ቤትም ነፃ ወጥተዋል። በዚህም ቂም እና በቀል ሊመዝዘው ይችል የነበረውን ሀገር አጥፊ የሞት ሰይፍ ዳግም ላይወጣ ከሰገባው መክተት ችለዋል። በምትኩም ሀገር ማዳን የሚችለውን አዲስ ያልተለመደ ሰይፍ መዘዙ። እሱም “ሰ” ሰላም “ይ” ይቅርታ እና “ፍ” ፍቅርን ያነገሡበት፤ እንዲሁም ጦርነት፣ በቀልና ጥላቻን ያሸነፉበት የዕርቅ ሰይፍ ነው።

እኛም ሁላችን የምናስታውሳቸው በደሎች፤ የተሠቃየንባቸው ቁስሎች፤ ያመረርንባቸው መከራዎች ይኖራሉ። ቂም እንድናበቅል፤ ቁርሾ ውስጥ





እንድንገባ፤ የጥላቻ መርዝ በአእምሮአችን እንዲዘራ የተደረገባቸው ታሪካዊ አጋጣሚዎች ቀላል አይደሉም። አሁን ግን ሁለት አማራጮች በእጃችን ላይ ወድቀዋል። አንደኛው፤ እንደማዲባ የሰላም፣ የይቅርታና የፍቅር ሰዎች በመሆን ሀገራዊ ዕርቅ እና ፈውስ ማምጣት ሲሆን፤ ሌላኛው በጥፋት አዙሪት ውስጥ ገብተን ወደ መቀመቅ መውረድ ይሆናል።

መቼም ራሳችንን ለማታለል ካልፈለግን በቀር ቂም ይዘን መልካም ዘመን ማምጣት እና ብልጽግናን ማወጅ እንደማይቻል ሁላችንም እንገነዘባለን። ስለዚህም ሁሌም በሕይወታችን ከሚገጥሙን ጭቆናዎች ራሳችንን ነፃ ስናወጣ ከውስጣችን የቸኮላውን ሐሳብ አራግፈን መጣል ይገባናል። ከአስከፊ ሥርዓት ስንላቀቅ አስከፊውን ሥርዓት ከውስጣችን ጠራርገን ማጽዳት አለብን። ጥላቻን ከዙሪያችን ገለል ከማድረግ ባሻገር ከልባችን ፍቀን መጣል ይኖርብናል። ከክፉ ነገር ውስጥ ለመውጣት የምናደርገውን ትግል ክፉውን ነገር ከውስጣችን ለማውጣት ተጨማሪ ጥረት እና ትግል ካላደረግን አሸናፊነታችን ትርጉም አይኖረውም። የማንዴላ የማሸነፍ ሚስጥርም ይህ ነው። ልክ እንደ ማንዴላ ሁሉ በውጭ ያለውን ጠላት ከማሸነፍ በፊት በውስጣችን ያለውን ጥላቻና ቂም ማሸነፍ ከእያንዳንዳችን የሚጠበቅ ተግባር ይሆናል። አለበለዚያ ጠላታችንን ያሸነፍን ቢመስለን እንኳን የጥላቻውን ሐሳብ በውስጣችን እስከተሸከምነው ድረስ ተሸናፊዎች እኛ ነን።

የተከበራችሁ የኢትዮጵያ ልጆች፤ ክቡራት እና ክቡራን፤ ትናንት ትዝታ ነውና በትናንት በሬ ለማረስ አይቻልም። ትናንትን ተረድቶ ከትናንት መማር ግን ይቻላል። ያለፈ ታሪክ ሁሌም ደግነትን እና ክፋትን፤ ጥሩና መጥፎን፤ ወረት እና ዕዳን ይዞ ይመጣል። ትልቁ ቁምነገር ከትናንት የወረስነውን ወረት እንዴት እንጠቀመዋለን? የሚለው ጉዳይ ይሆናል። የትናንት ወረት ለዛሬ መነሻ እንደሚሆን ምንም ጥርጥር የለውም። ሌላው ቀርቶ እዚህ ደቡብ አፍሪካ ከዘመነ አፓርታይድ የወረሱትን መልካም ወረት በትክክሉ ተጠቅመውበታል።

መሠረተ ልማቱ፣ የከተማ ሥሪቱ፣ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴው፣ የፍትሕ እና የፓርላማ ተቋማት፣ የተከማቸው የሀገሪቱ ሀብት ሁሉ ለሀገሪቱ ዕድገት እንደመነሻ እና መስፈንጠሪያ ሆኖ አገልግሏል። የሕዝቦቿን ሁለንተናዊ እኩልነት ለማረጋገጥ ለምትተጋው አገር ደቡብ አፍሪካ ቀድሞ የተከማቸውን ወረት በጥንቃቄ ለይታ ተጠቀመችበት እንጂ ሁሉንም በዜሮ አላባዛችውም።

የአገራችንም ጉዳይ እንዲሁ ነውና ወረታችንን ከዕዳችን መለየት እንጀምር፣ ትናንትናችንን በጥቅሉ ብርሃን ወይም ድቅድቅ ጨለማ፣ ስንዴ ወይም እንክርዳድ፣ ጠቃሚ ወይም ጎጂ፣ አኩሪ ወይም አሳፋሪ አድርጎ መሣል ስሕተት ነው። የዜሮ ድምር አካሄድ ማንንም አይጠቅምም። አልጠቀመም። ስለዚህ መልካሙን ከክፉ ለይተን አብረን እናስወግደው። ሁሌም ጥንቃቄ ማድረግ የሚገባን የሚጠቅመውንም የማይጠቅመውንም ደርበን ያጠፋን እንደሆነ ነው። ምርቱን ከገለባው እንለየው፣ እንክርዳዱን ለቅመን እንጣለው፣ ምርቁን ነጥለን እንድፋው፣ የሚያሳፍረውን ተግባር ደግመን አንፈፅመው። እንዲህ ከአሰብን መነሻ ወረት ይኖረናል። ወረት አልባ መሆን ጉዳት፣ መነሻ ወለል በሌለበት መድረሻ ጣሪያ ሊኖር አይችልም። ሁሉንም የፈጠርነው እኛ ነን ብሎ በመቀበል ወደፊት መጓዝ ይኖርብናል። የሀገራችንን ደስታዋንም ሆነ ሐዘኗን፣ ሳቋንም ሆነ ሕመሟን አብሮ መካፈል እንችላለን። የድል አድራጊውን ድል ብቻ ሳይሆን የተጎጂውንም ጉዳት "የእኔ ነው" ብሎ መቀበል ያስፈልጋል። የደስተኛውን ሳቅ ብቻ ሳይሆን የሐዘንተኛውንም ለቅሶ አብሮ ማልቀስ ያስፈልጋል። ሀገር መውደዳችን፣ ሕዝብ ማፍቀራችን፣ ኢትዮጵያዊ መሆናችን በአፋዊ ቁልምጫ ወይም በፌስቡክ ውርጅብኝ ብቻ ሳይሆን በተግባር ተግቶ በመሥራት ጭምር ሊሆን ይገባል።

በጥንት የኢትዮጵያውያን አዳኞች ባህል ከአንድ መንደር የወጡ አዳኞች ከአንድ ጫካ ገብተው ለወራት ይቆያሉ። አንበሳም፣ ነብርም፣ ዝኆንም አድነው ይመለሳሉ። ወደ መንደራቸው ሲገቡ መንደሩ የደስታ እና የሐዘን ቅልቅል ነው የሚሆነው፣ አድነው እና ግዳይ ይዘው በመጡት ይደሰታሉ። ይጨፍራሉ። በአደን ጊዜ በአውሬ ተበልተው፣ በጫካ ጠፍተው ወይም በበሽታ ተቀስፈው እንደወጡ ለቀሩት ደግሞ ያዝናሉ። የድል ብሥራቱም፣ የሐዘን ለቅሶውም የእነርሱ ነው። ያሸነፉትም የሞቱትም እነርሱ ናቸው። ድሉም ሆነ ሞቱ የእነርሱ ነውና "የእኛ" እና "የእነርሱ" የሚል አስተሳሰብ የላቸውም።

የሀገራችን የትናንት ታሪክ የዛሬ ድላችንን እና የነገ ተስፋችንን አስሮ እና ጠፍሮ እንዲያስቀርብን መፍቀድ የለብንም። ለዛሬ ስንፍናችን ከትናንት ምክንያት መፈለግ ማቆም አለብን። እየታመምን፣ እየተራብን እና እየሞትን ያለነው ዛሬ ነው። ሥራ በማጣት እየተሰደድን እና እየደኸየን ያለነው ዛሬ ነው። ሀገራችን ሁሉ እያላት እንደሌላት፣ ለሌላው መትረፍ ስትችል ለራሳችን መሆን ያቃተን እኛ ነን። ትናንት ሳይሆን ዛሬ፣ ይህንን ሁሉ ማስተካከል የሚቻለውም ትናንት አይደለም፣ ዛሬ ነው። ትናንትን ብንወደውም ብንጠላውም እነዚህን ሁሉ አይሸከምም። ዛሬ ላይ ያልተጠቀምንበት ዕድል እና ያልፈታናቸው ችግሮች ደግሞ ነገ ላይ የተቆለለ ጫና እና ክፉ ዕዳ መሆናቸው አይቀርም። ወደኋላ ስንሄድ የዛሬ ዕድል የነገ ጫና ሆኖ እየተከማቸ ይሄዳል። ለዚህ ያለ የሌለ ጉልበት፣ ገንዘብ እና ጥበብ ማፍሰስ ያለብን እና መገንባት የሚኖርብን ዛሬን ለነገ ነው። መከራከር መሟገት ያለብን ስለትናንት ሳይሆን ስለነገ ነው። ዳያስፖራ በአፓርታይድ ሁኔታ ቢከራከሩ ነገን ለልጆቻቸው መገንባት አይችሉም። አፓርታይድን አግልለው ነገን ደቡብ አፍሪካ ለዜጎቿ ብቻ ሳይሆን ለእኛም የምትመች አድርጎ መሥራት ይጠበቅባቸዋል። በየጊዜው ትናንትን ሲረግሙ ከመኖር ነገን ለማበጀት መሞከር የበለጠ ዋጋ አለው የምንለው ለዚሁ ነው።

ውድ የኢትዮጵያ ልጆች፣ "ዳገት ከፊት እያለ አትረፍ፣ ዕዳህን ሳትከፍል አትኩራ" እንዲሉ፣ ዛሬ የምናፍርበት እና የምንኩራራበት፣ እንዲሁም ለማረፍ የምንወስንበት ጊዜ አይደለም። ድሃ አገር ይዘን የፈለግነውን ያህል ታሪክና ባህል፣ ቋንቋና ቅርስ፣ ነፃነት እና ጀግንነት፣ ምርጥ አየር እና ውብ ምድር

ቢኖረን ከድህነት በላይ ልንሆን አንችልም። ወደር የሌለውን ቅርሳችንን ባዶ ሆዳችን ይሸፍንብናል። አስደናቂው ባህላችንን ልመናችን ይጋርድብናል። ነፃነታችንን ኋላ ቀርነታችን ያኮስስብናል። አኩሪ ታሪካችንን አሳፋሪው ድህነታችን ያሳድፍብናል።

በአክሱም ሀውልት እና በላሊበላ ውቅር አብያተ ክርስቲያናት፤ በጀጎል ግንብ እና በአባጅፋር ቤተ መንግሥት፤ በጎንደር ፋሲለደስ እና በባሌ ተራራ፤ በጢያ ትክል ድንጋዮች፤ በኤርታሌ እሳተ ገሞራ አጠገብ የርዳታ እህል የጫኑ መኪኖች ካለፉ ይህ ሁሉ አስደናቂ ታሪክ ምን ዋጋ አለው። ከዘጠኝ በላይ ታላላቅ ወንዞች፤ ከ12 በላይ ታላላቅ ሐይቆች ያሏት ሀገር ሕዝቦቿ ውሃ በፈረቃ ከጠጡ፤ ግብርናቸው የክረምት ዝናብ ከጠበቀ፤ እናቶች ለሰዓታት ተጉዘው ውሃ ከቀዱ ምን ዋጋ አለው? ለሺሕ ዘመናት የዘለቀ የትምህርት ታሪክ ባላት አገር ኢትዮጵያ ልጆቿ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ ተስማምተው መማር ካቃታቸው ምን ትርጉም አለው? ከብዙ ዘመናት በፊት ስደተኞችን የመቀበል ታሪክ ያላት ሀገር፤ ለፕሬዚዳንት ማንዴላ ሥልጠና እና ፓስፖርት መስጠት የቻለች አገር፤ ዛሬ ልጆቿ ጥለዋት በገፍ ሲሰደዱ ከማየት በላይ ምን የሚያሳዝን ነገር ይኖራል? የውሃ ወፍጮን የዛሬ 500 ዓመት መጠቀም በጀመረች አገር ውስጥ ዛሬም እናቶች እህል ለማስፈጨት ድንጋይ ሲገፉ ማየት፤ ጀንያ ተሸክመው ኪሎ ሜትሮችን ሲጓዙ መመልከት ያስደነግጣል። ከብዙዎች አገሮች ቀድማ ሦስቱን ታላላቅ እምነቶች የተቀበለች አገር ዛሬ በሃይማኖት ምክንያት ግጭት ማስተናገዷ እምነቶቹን በቅንነት ያስተማሩንን አባቶች፤ በተለይ ደግሞ የኢትዮጵያን አምላክ ፈጣሪንም እንደመካድ ይቆጠራል። ከሁሉ ቀድማ እርሻ የጀመረች ምድር ከሌሎች አገራት የምግብ ርዳታ መቀበሏ በእጅጉ ያስቆጫል። በገዳ ሥርዓት ዲሞክራሲያዊ አስተዳደርን ስትለማመድ የኖረች አገር ጊዜው የሚጠይቃቸውን ተቋማት ገንብታ ልምምዷን ለማስፋት እንደምን ተቸገረች? ብለን እንድንጠይቅ ያስገድዳል።

በርግጥ እነዚህ ሁሉ አኩሪ የትናንት ዕሴቶች ካሉን ዛሬ እንድናጎለብታቸው የማያደርገን ምንም ምክንያት የለም። ጠላት ካለንም ዋና ጠላታችን ስንፍናችን ነው። እንቅፋት ከተገኘም ዋነኛው እንቅፋት ሌላ ሳይሆን እኛው ራሳችን ነን። ማሸነፍ ካለብንም ቅድሚያ ማሸነፍ የሚገባን ራሳችንን ነው። መግራት ካለብንም ቅድሚያ ልንገራ የሚገባው መጥፎ ልማዶቻችንን ነው። እነዚህም ሀዲያ፣ ሲዳማ፣ ጉራጌ፣ አማራ፣ ኦሮሞ ብሎ በሰው ሃገር መከፋፈል መጥፎ ልምምድ ስለሆነ በአንድነት ቆማችሁ ክብራችሁን እንድታስጠብቁ እና ኢትዮጵያዊነታችሁን በውጭም እንድታረጋግጡ በዚሁ አጋጣሚ ከአደራ ጭምር ላሳስባችሁ እወዳለሁ።

ውድ የኢትዮጵያ ልጆች፤ አሁን ሀገራችን ታሪካዊ ወቅት ላይ ትገኛለች። የዜጎች የሕይወት ጥራት የሚሻሻልበት ወሳኝ ምዕራፍ ከፊታችን ተዘርግቷል። ሁላችሁም እንደምትገነዘቡት በውጭው ዓለም ኢትዮጵያ እያመጣች ባለችው ለውጥ ከፍተኛ ክብር እና ዝና ከማግኘቷ በላይም የዜጎቿን ጥያቄ ጠይቃ ምላሽ ለማግኘት እና የመደራደር ዐቅም ማግኘቷን በዚሁ አገር በተተደረገው ድርድር እናንተም መገንዘብ ትችላላችሁ። ይሄ ለሀገራችን ተጨማሪ ወረት፣ ተጨማሪ ካፒታል ሲሆን ለዘመናት ሲንከባለሉ የቆዩት የዲሞክራሲ ጥያቄዎች በተግባር የሚታዩበት እና እነሱን ለማሳካት ያለን ቁርጠኝነት የሚፈተሽበት ትክክለኛው ጊዜ መጥቷል።

አሁን ጥያቄው ይህንን ታሪካዊ ድል እንጠቀምበታለን? ወይስ እንደከዚህ ቀደሞቹ ጊዜያት መክኖ ይቀራል? ይህ የሚወሰነው በእኛ በልጆችዋ ይሆናል። የዴሞክራሲ ሥርዓት የሚቆምባቸውን ምሰሶዎች ተግተን ልንጠብቃቸው እና በልምምድ ልናዳብራቸው ይገባል። ዴሞክራሲ በነፃነት ብቻ አይመጣም። ዴሞክራሲ እኩልነት ስለተባለ ብቻ ሊሳካ አይችልም። ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ያለ ሰጥቶ መቀበል መርሕ እውን እንደማይሆን በታሪካችን ደጋግመን አይተናል። በዚህ በምትኖሩበት አገር ኤ.ኤን.ሲ. የሚባለው ድርጅት ከአሸነፈ

በኋላ ኔልሰን ማንዴላ፣ ታቦ ኢምቤኪ፣ ዙማ፣ እንዲሁም ራማፎሳ የሚባሉ ፕሬዚዳንቶች በዴሞክራሲያዊ መንገድ ቀያይሮ ማየት እና አገር ሳትፈርስ አንድነቷን ጠብቀው ማስቀጠል ችለዋል። ይህ ልምምድ በኢትዮጵያ ውስጥ እንዲሰፋ፣ እንዲያድግ እና እንዲያብብ እያንዳንዳችን ተግተን መሥራት ይጠበቅብናል። ይህንን መከወን ያለወንድማማችነት ዕሴት፣ ነፃነት እና እኩልነትን መዋደድን ብቻ ካልፈጠርን እንዲሁ ልንተገብረው የምንችል ጉዳይ አለመሆኑን ልንገነዘብ ይገባል።

ስለሆነም ከፊታችን ለሚመጣው የዴሞክራሲ ችቦ ማስሪያው ገመድ ወንድማማችነት መሆኑን ማናችንም አንዘነጋም ብዬ አስባለሁ። ዛሬ የደቡብ አፍሪካን ፕሬዚዳንት ስለእናንተ ሳናግራቸው "በዚህ አገር በመቶ ሺሕ የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን አሉ። ነገር ግን ከነዚህ ውስጥ 99 በመቶው በብዙ ስፍራ የሚነግድ፣ የሚለፋ፣ ጥሮ ግሮ ሀብት የሚያፈራ እንጂ እንደሌሎች የሚዘርፍ አለመሆኑን ላረጋግጥልዎ እፈልጋለሁ" ስላቸው፤ "ይህንንማ እኛ ደቡብ አፍሪካውያንም ጠንቅቀን እናውቃለን። ኢትዮጵያውያንን ሥራ ፈጣሪ፣ ተግቶ አዳሪ ብለን ነው የምንጠራቸው" ብለው መልሰውልኛል።

ይህ ስማችን በመላው ዓለም እንዲስፋፋ በማይመለሰው ትናንት ላይ ያለንን ጠንከር ያለ ትችት እና ጊዜ ማባከን ከእንግዲህ በማስወገድ ሀገሩን እና ሕዝቡን የሚወድ ሁሉም ከመቆራቆስ እና ከመጠፋፋት የሚያድን ቀና አስተሳሰብ ኖሮን ሀብት ጉልበታችንን ከማባከን ይልቅ፤ ወደሚቀየረው ነገር አተኩረን እንድንሠራ በድጋሚ ከአደራ ጭምር ላሳስባችሁ እፈልጋለሁ። በመደመር ጎዳና የብልጽግናን ፋና እያየ ዛሬ ቀን ሳለ ነገ የሚኮራበትን ሀገሩን ለመገንባት እና ከፍ ለማድረግ መትጋት ከሁላችን ይጠበቃል። አሁን የአገራችን ብልጽግና በይደር የምናቆየው ተግባር ሳይሆን ሰርክ ልንናፍቀው የሚገባና እውን ለማድረግ የምንተጋበት ጊዜ መሆኑን ለሁላችንም ግልፅ ነው። ሁለንተናዊ የሆነ ቁሳዊ እና መንፈሳዊ ብልጽግና በአገራችን እስከናረጋግጥ ለዐይናችን እንቅልፍ ለጎናችን ረፍት ልንሰጥ አንችልም። የሕዝባችንን የኑሮ ደረጃ በማሻሻል እና መሠረታዊ ፍላጎቶቹን በብቃት እና በበቂ ሁኔታ በማሟላት ለኢኮኖሚያዊ ብልጽግና ተግተን ልንሠራ ቃል የምንገባበት እና የምንተጋበት ጊዜው አሁን ነው።

ይህም ብቻውን በቂ አይደለም። እምነቱን እና ምግባሩን፤ ባህሉን እና ቅርሱን፤ ነፃነቱን እና እኩልነቱን፤ ወንድማማችነት እና ማኅበራዊ ወረቱን፤ የመደጋገፍ ዕሴቱን እና ዲሞክራሲያዊው ዓለም ከደረሰበት ደረጃ ኢትዮጵያን ማድረስም የዚህ ትውልድ ሐላፊነት ነው። ለዚህም ጉዞው የብልጽግና ዘመን ነው። ይህም የማኅበራዊ እና ፖለቲካዊ ብልጽግና ሁለንተናዊ በሆነ መንገድ የሚተገበር ሲሆን፤ በሚቀጥሉት ዓሥር ዓመታት በደቡብ አፍሪካ ካሉት ወገኖቻችን ቢያንስ 80 እና 90 በመቶው በአገራችን ተመልሶ ሥራ ፈጣሪ ኢንቨስተር እንደሚሆን እና ኢትዮጵያ ለልጆችዋ ምቹ አገር እንደምትሆን በልበ ሙሉነት ላረጋግጥላችሁ እፈልጋለሁ። ይህ የብልጽግና ጉዞአችን ከግብ እንዲደርስ በምኞት ሳይሆን የጀመርነውን የዕድገት ጉዞ ተባብረን በድል ማጠናቀቅ ስንችል ነው። ከፊታችንም በአንድነት የምንተገብራቸው የድርጊት አቅጣጫዎች ተቀምጠዋል። አገራዊ የኢኮኖሚ ማሻሻያውን ከግብ በማድረስ መሠረታዊ የሆኑ ፍጆታ አቅርቦቶችን በሕዝብ ዐቅም ማቅረብ፤ የድሃውን ኑሮ ማሻሻል እና የሥራ አጥ ቁጥርን መቀነስ፤ አሁን ያለውን 25 በመቶ ገደማ የሚገመተውን ከድህነት በታች የሚኖረውን ኢትዮጵያዊ በሚቀጥሉት ዓሥር ዓመታት ከዓሥር በመቶ በታች እንደምናወርደው በእርግጠኝነት ልገልፅላችሁ እፈልጋለሁ። የሕግ እና የፍትሕ ሥርዓት፤ የደኅንነት እና የጸጥታ፤ እንዲሁም የዴሞክራሲ ተቋማት ማሻሻያዎች በተገቢው ፍጥነት መከናወናቸውን ለማረጋገጥ ቀን ከሌት እንደምንተጋ እንዲሁ ላረጋግጥላችሁ እፈልጋለሁ።

የሐሳብ ነፃነትን እና የሰብአዊ መብትን አያያዝ በሕግ ማሕቀፍ ለማረጋገጥ፤ የአገሪቱን ሉዐላዊነት ለማስከበር በውስጥ በድንበር፣ በባሕር፣ በሳይበር እና በሌሎችም ግንባሮች ለመጠበቅ እና የኢትዮጵያን አንድነት ዛሬም

እንደትናንቱ የምናስቀጥል መሆኑን በእርግጠኝነት አረጋግጥላችኋለሁ። የግጭት መነሻዎችን አስቀድሞ በማጥናት ለመከላከል፤ ሲከሠቱም የከፋ አደጋ ሳያደርሱ ለማምከን፤ እንዲሁም ራስን ከማስተዳደር፣ ከማንነት፣ ከወሰን ጋር የተያያዙ ጥያቄዎችን በሰላማዊ እና በሕጋዊ መንገድ ብቻ ለመፍታት መንግሥት የበኩሉን ሁሉ እንደሚያደርግ ላረጋግጥላችሁ እፈልጋለሁ። ኅብረ ብሔራዊነታችንን የሚያጠናክሩ ሀገራዊ ተግባራትን ለማከናወን ዛሬም ነገም ቁርጠኞች መሆናችንን እንዲሁ ላረጋግጥላችሁ እፈልጋለሁ።

የሕዝቦችን ተጠቃሚነት በአረጋገጠ ኅብረ ብሔራዊ አንድነትን እና እኩልነትን በአስጠበቀ ሉዓላዊነታችንን በአስከበረ መልኩ መልካም ወረቶቻችንን እያስቀጠልን አዳዲስ ዕሴቶችን መፍጠር ከቻልን በእርግጠኝነት ሁላችንም ከኢትዮጵያችን ጋር ወደ ብልጽግና ማማ እንደምንወጣ ቅንጣት አልጠራጠርም። የእኛ ጥረት ብቻውን ግን የትም አያደርስም እና በትብብር ሠርተን አገራችንን እንደምንቀይራት ሁላችንም ከልብ ቃል ልንገባ ያስፈልጋል።

የአገር ግንባታ የአንድ መሪ ወይም የአንድ ፓርቲ አሊያም የአንድ ትውልድ ሐላፊነት ብቻ አይደለም። ኢትዮጵያ የጋራችን ናት። የኢትዮጵያ ስኬት በመሥዋዕትነት እንጂ በምኞት አይመጣም። በሥራ እንጂ በወሬ፤ በፌስቡክም እውን አይሆንም። በንቁ ተሳትፎ እንጂ እጅን አጣጥፎ በመጠበቅ ለውጥ ፈፅሞ ሊመጣ አይችልም። ስለዚህ ሁላችንም በአንድነትና በወንድማማችነት ስሜት ለለውጥ እንድንነሣ ከአደራ ጭምር አሳስባችኋለሁ።

በአንድ ወቅት የሰብአዊ መብት ተሟጋቹ ማርቲን ሉተር ኪንግ ለለውጥ ለመነሣት ሲናገር እንዲህ ብሏል። “ወደ ታላቁ ግብህ ለመድረስ መብረር ካልቻልክ ሩጥ፤ መሮጥ ካልቻልክ ተራመድ፤ መራመድ ካልቻልክ ተንፏቀቅ፤ ምንም አድርግ ምን ብቻ ወደፊት ገስግስ።” ወደ ብልጽግና በምናደርገው ጉዞ ከቻላችሁ አግዙን፤ ካልቻላችሁ ጸልዩልን፤ ነገር ግን አታደናቅፉን፤ ምክንያቱም የኢትዮጵያ ብልጽግና የማይቀር ጉዳይ ስለሆነ። ለውጥ ወደፊት በማየት፤ ወደፊት በመገስገስ የሚመጣ ነው። በተለይ ደግሞ ወደ ብልጽግና የሚደረግ ጉዞ በመቆም ወይም ወደ ኋላ በማየት የሚሳካ አይደለም። በመንቀራፈፍ ወይም ወደ ኋላ በመሮጥ የተሸለመ ሰው የለም። ወደፊትም አይኖርም። የኖቤል ሽልማቱን ጨምሮ ማለት ነው። ሽልማት ሁል ጊዜ ትጋት፣ አብሮነት እና ፍጥነት ይጠይቃል።

ውድ የአገሬ ልጆች በየትኛውም ዓለም የሚኖሩ ወገኖቻችን አብዛኞቹ በስንት ሥቃይ እና እንግልት እዚያ እንደሚደርሱ ለማናችንም መገመት አይከብድም። በጉዞ ቁጥራቸው ጥቂት የማይባሉ ሰዎች ህልማቸውን በአጭር ያስቀረ እና ሕይወታቸውን እስከ መቅጠፍ የሚያደርስ አደጋ ይገጥማቸዋል። ኩላሊት እና ጉበታቸውን የሚዘረፉ፤ የለፉበትን ደሞዝ የማያገኙ፤ በየእስር ቤቱ ተረስተው የሚሞቱ፤ በአሠሪዎቻቸው የሚደፈሩ እና በባሕር ውስጥ ሰምጠው የሚቀሩ ወገኖቻችን ብዙ ናቸው። ድህነትን በመሸሽ ስንቱን መከራ ተቀብለዋል። ድህነት እንዲህ አገርን እና ዜጎችን ያዋርዳል። ድህነት ለስደት እና ማለቂያ የሌለው ሥቃይ ይዳርጋል። ይህ ሊቀጥል አይገባም። “ይህም ያልፋል” እያልን ለችግር ትከሻችንን እያሰፋን፤ ለተጎጂዎች እያዘንን፤ በእንባ ጎርፍ እየታጠብን እስከመቼ? ከዘመናችን ከሐዘናችን ማግስት ሁላችንም ወገባችንን ታጥቀን መነሣት አለብን። ድህነትን ባለማሸነፋችን ምክንያት የምንከፍላቸው ዋጋዎች ከእንግዲህ በቃችሁ ሊባሉ ይገባል። ዋጋ ከከፈልንም አይቀር ለእኛ እና ለልጆቻችን ዘላቂ የሆነ ብልጽግና ለማምጣት እና ኢትዮጵያን ወደሚገባት የዕድገት ማማ ለሚያወጣት ጉዳይ ብቻ መሆን አለበት።

በባሕር ውስጥ ለሻርክ የተጣለውን ባለህልም ወጣት ወይም በጠረፍ ጠባቂዎች ሕይወታቸው የተቀጠፉትን ወገኖቻችንን አስቡ። እያንዳንዳችሁ ያለፋችሁበትን፤ ለማንም ያልነገራችሁትን ታሪካችሁን አስቡ። በሚገባ ካጤንነው ሀገራችንን ለመለወጥ ወደ ብልጽግና ለመውሰድ ከዚህ በላይ

የሚያስከፍለን ዋጋ አይኖርም። ከ25 ዓመት በፊት ይህ አገር እንኳን ከሌላ አገር ለመጡ ስደተኞች ለዜጎቹም የከፋ ነበር። በዚያን ጊዜ ምናልባት ከጥቂት ወገኖቻችን በቀር ብዙ ኢትዮጵያውያን እዚህ አልነበሩም። በእነዚህ ጥቂት ዓመታት ውስጥ ምን ዓይነት ጠንካራ እና በብዙ ሺሕ የሚቆጠር ኢትዮጵያውያን ዳያስፖራ ማኅበረሰብ እንደተፈጠረ ልብ በሉ። እያንዳንዳችሁ የራሳችሁ የኋላ ታሪክ፤ የዛሬ ኑሮ እና የነገ ህልም አላችሁ። ብዙዎቻችሁ ከተወለዳችሁባቸው እንደ ሆሳዕና እና ዱራሜ ያሉ ውብ የአገራችን ከተሞች ውስጥ የሚገኙ የቤተሰቦቻችሁን ሕይወት ቀይራችኋል። አሁን ሌሎች ታናናሽ እኅት እና ወንድሞቻችሁን ለስደት ሕይወት የምትጠሩበት ጊዜ ሳይሆን በአላችሁ ዕውቀት እና ጉልበት በአገኛችሁት ልምድ እና ጥሪት ሀገራችሁን በመለወጥ ሌሎች እንዳይሰደዱ፤ ኢትዮጵያም እንድትበለጽግ የምታደርጉበት ወቅት ነው። አገራችን በውበትም ሆነ በሀብት ከደቡብ አፍሪካ አታንስም። ዛሬ ለሁላችሁም የማቀርበው ጥሪ ስደት እና ኮሽ ባለ ቁጥር በሰው አገር በሰቀቀን መኖር እንዲበቃን ነው። እዚህ ያፈራችሁትን ዕውቀት፣ ልምድ እና ጥሪት አገራችሁ ላይ ተደምራችሁ በማፍሰስ ራሳችሁንም ሀገራችሁንም ለመለወጥ እንድትንቀሳቀሱ በታላቅ ትሕትና እጋብዛችኋለሁ።

መንግሥታችሁ በደቡብ አፍሪካ ያለ ዳያስፖራ ተደራጅቶ ለአገሩ ብልጽግና ለሚያደርገው ጥረት ከምንጊዜውም በተሻለ ከጎናችሁ ሆኖ እንደሚደግፋችሁ ላረጋግጥላችሁ እፈልጋለሁ። አሁን የሩጫ ጊዜ ነው። የመነሻው ጥይት ተተኩሷል። ፉክክርንም ትብብርንም አንድ አድርገን ለመሮጥ እንነሣ! በጋራ ለማሸነፍ እንተባበር! የተሻለ የሥራ እና የበለጠ ውጤት ያመጣ የተሻለ እንዲሸለም ጤናማ ውድድር እናድርግ፤ ስንፍናን እና ዳተኝነትን ሌብነትን እና ያልሠሩበትን ሀብት ማግበስበስን በማስቀረት በችሎታ፣ በትጋት፣ በልምድ፣ በመልካም ሥነምግባር እንወዳደር፤ አሸናፊዎችን እናክብር፤ ብዙ አሸናፊዎችም እንፍጠር። ሁሉም የሚያሸንፈው ትብብር ባለበት ውድድር ውስጥ ስለሆነ ምቀኝነትን እና ክፋትን፤ ቅናትን እና ሸርን ትተን ወደፊት በትብብር አብረን እንገስግስ። ማሸነፍ ሁልጊዜም ቀድሞ መግባት አይደለም። እና ብዙዎችን ይዘን ወደበለጸገች ሰላማዊት ኢትዮጵያ ለመግባት ወደፊት እንገስግስ። ነፋሱን እና ማዕበሉን ተጋፍጠን፤ አቀበት ቁልቁለቱን አቋርጠን፤ አሰናካዮችን በብልሀት እና በብስለት እያለፍን ሳንታክት እንጓዝ። መንገድ ሲዘጉብን አማራጮችን ተጠቅመን፤ “ሆ” ብለው ሲቃወሙንም ሆነ “ሆ” ብለው ሲደግፉን ለሁሉም በልኩ እየመለስን ከፊት ለፊታችን ያለውን የኢትዮጵያን ብልጽግና እያየን ወደፊት በአንድነት ለማሸነፍ እንሩጥ። እንደዚያ ከአደረግን ያለጥርጥር ኢትዮጵያ ትበለጽጋለች። ዜጎቿ በምቾት የሚኖሩባት ሀገር ትሆናለች። አልጠራጠርም! ይህ የሁላችን መሻት እውን ይሆናል! እናንተም እንዳትጠራጠሩ!

**ጊዜው የኢትዮጵያ እና የኢትዮጵያውያን ነው!**
**እጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ! እወዳችኋለሁ!**
**ስለአደረጋችሁት ሁሉ እግዚአብሔር ብድራቱን ይክፈላችሁ!**

**አመሰግናለሁ!**

# የጄነራል መኮንኖች ሹመትና ማዕረግ ማልበስ ንግግር

ጥር 9/2012 ዓ.ም.

**ክብርት ፕሬዚዳንት ሣህለ ወርቅ ዘውዴ፤**
**ክቡር የቀድሞ ፕሬዝዳንት ሙላቱ ተሾመ፤**
**ክቡር የቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስትር ኃይለ ማርያም ደሳለኝ፤**
**የአፍሪካ ኩራት የኢትዮጵያ መከታ የሆነው የመከላከያ ሰራዊት ጦር አዛዦች፤**
**የተከበራችሁ እንግዶች፤ ዛሬ በከፍተኛ መዓርግ የጀነራል መኮንንነት መዓርግ የምናለብሳቸውን ጀነራል መኮንኖች ሥነ ሥርዓት ለማክበር የተገኛችሁ እንግዶች በሙሉ፤**

እንኳን ደኅና መጣችሁ! ለማለት እፈልጋለሁ፡፡

በሀገሩ የሚኮራ፤ ሀገሩንም የሚያኮራ፤ ለዘመናት ጀግንነቱን እየደጋገመ ያስመሰከረ፤ የሀገሩን ሉዓላዊነት ለማስከበር ፈፅሞ ግንባሩን የማያጥፍ፤ ድል ማድረግ ዜማው፤ ማሸነፍ ቋንቋው የሆነ የአፍሪካ ኩራት፤ የኢትዮጵያ መከታ፤ የራሱን የማይሰጥ፤ የሰው የማይነካ፤ ሰላምን ከፍ ለማድረግ ራሱ ዝቅ የሚል፤ ሕዝቡን በነፃነት ለማኖር የደም ዋጋ የሚከፍል ማነው? ተብሎ ቢጠየቅ፤ ዓለም ሁሉ ተስማምቶ “የኢትዮጵያ ወታደር ነው” ማለቱ አይቀርም፡፡ የኢትዮጵያን የዘመናት የነፃነት ታሪክ ስናስብ ይህንን ለመጠበቅ እና ለማስከበር የተሠውትን የኢትዮጵያን ልጆች በጽኑ እናስባቸዋለን፡፡ ኢትዮጵያ ቅኝ ያልተገዛች አገር ናት ስንል፤ የቅኝ ግዛትን ቀንበር የሰበሩትን ኢትዮጵያውያን ማሰብ ይኖርብናል፡፡ እንደ እሳት ወላፈን በሚጋረፉ የኢትዮጵያውያን አጥንቶች የታጠሩትን ድንበሮቿን ስናስብ አጥር ቅጥር ሆነው የወደቁትን ኢትዮጵያውያን ማሰብ አለብን፡፡ ኢትዮጵያውያን ሁሉ በተፈጥሮ ወታደሮች ናቸው፡፡ የኢትዮጵያ ወታደሮች ደግሞ የተፈጥሮ ወታደርነትን ከዘመናዊ ሥልጠና እና ከዲሲፕሊን ጋር ያዋሐዱ ምርጦች ኢትዮጵያውያን ናቸው፡፡ ይህ ነው የዘመናት የመከላከያ ሰራዊት የማሸነፍ ጥበብ፤ ዛሬ የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት በውስጥ የሀገራችንን ሰላም እና ደኅንነት፤ በውጭ የሀገራችንን ድንበር እና ሉዓላዊነት በንቃት እያስጠበቀ ይገኛል፡፡ በጦርነት ጊዜ ጋሻ፤ በሰላም ጊዜ ትከሻ ሆኖ ሀገሩን የሚደግፍ፣ የሚጠብቅ፣ የሚያኮራ የመከላከያ ሰራዊት ስለአለን በእናንተ የምንኮራ መሆኑን ልገልፅላችሁ እፈልጋለሁ፡፡

ከድሆች ጓዳ እስከ ገበሬው አጨዳ ድረስ ተሰማርቶ ሰላም የሚያስከብር ብቻ ሳይሆን ልማት የሚያሣልጥ የመከላከያ ኃይላችን የሀገር ፍቅሩ ረቂቅ፤ ዲሲፕሊኑም ጥብቅ፤ ተልእኮው ትልቅ፤ ራእዩ ሩቅ ነው፡፡ የዚህ ጀግና ሰራዊት አካል ሆነው ሺዎች ግዳጃቸውን በላቀ ክብር ፈፅመው አልፈዋል፡፡ እሳት እሳትን እየተካ፤ ኮከብ ኮከብን እየወለደ የኢትዮጵያ ማኅፀን ጀግና ማፍራቱን ቀጥሏል። ወደፊትም ይቀጥላል። ሰራዊቱ ምትክ ለሌላት ሀገራቸው ግንባር

ቀደሙን ተልእኮ በመውሰድ ከታች እስከላይ የሚሰለፉ መሪዎችን ሲያፈራ ኖሯል። የዛሬም ተሿሚዎች ከእነዚህ መካከል በርካታዎቹ ተደርገው ሊወሰዱ ይችላሉ። ወደፊትም በዚሁ መልክ ጀግና የማፍራት ሥራው በመከላከያ የሚቀጥል የሪፎርም አሠራር ይዘናል። ዛሬ የተሰጠው ከፍተኛ የማዕረግ ሹመትም ቢሆን ትንሽ ከዚህ ቀደሙ በቁጥር ላቅ ያሉ ሴት ጄነራሎችን ጨምሮ ሹመት የተከናወነ ሲሆን፤ ይህም መከላከያን ጨመሮ ለሀገራችን የጾታ እኩልነት የሪፎርም አጀንዳ ማሳያ ምልክት ሆኖ የሚያገለግል ይሆናል።

የመከላከያ ሰራዊታችን በሁሉም መስክ ንቁ፣ ብቁ እና ዝግጁ እንዲሆን የጀመርናቸውን የሪፎርም ሥራዎች ፍሬ ማፍራት ጀምረዋል። ሥልጠናውን እና ትጥቁን ከጊዜው ጋር ለማዘመን፣ አኗኗሩን፣ አደረጃጀቱን እና ተልእኮውን የሚመጥን ለማድረግ፤ የሪፎርም ሥራዎች ሲሠሩ ሰንብተዋል። ሰራዊቱ በአኗኗርም ሆነ በአመራር፤ በመልከአ ምድርም ሆነ በአቀማመጥ፤ በመርሕም ሆነ በሥርዓት አሁን ያለችውን ኅብረ ብሔራዊት ኢትዮጵያ እስኪመስል ድረስ፤ ገና የሪፎርም ሥራችን የሚቀጥል ቢሆንም ዛሬ ሁሉም ኢትዮጵያዊ በእኩል የእኛ ወታደር ለማለት በሚያስችል መልኩ ተዋጽዖውን የጠበቀ ጥረት ተደርጓል። ሠራዊቱ ለብዙ ዓመታት ሲጠይቃቸው የነበሩ በርካታ የሪፎርም ጥያቄዎች፤ ዐዋጅ ማሻሻልን ጨምሮ የመዓርግ፣ የዩኒፎርም፣ የምግብ አበል፣ እንዲሁም ደመወዝ የመሳሰሉ በርካታ ማሻሻያዎች ተደርገዋል። በጥቅሉ የሀገር መከላከያ ሰራዊት ከመንግሥት የሚጠብቃቸው ሁሉም ጥያቄዎች ሙሉ በሙሉ የተመለሱ ሲሆን፤ መንግሥት ከሀገር መከላከያ ሠራዊት የሚጠብቀው ሰላም እና ደኅንነትን የማረጋገጥ ሥራ የእናንተ ቀጣይ ሐላፊነት ይሆናል።

ሠራዊታችን በመልኩ ኅብረ ብሔራዊ፤ በዲሲፕሊኑ ወታደራዊ፤ በወገንተኝነቱ ሕዝባዊ ነው። የፖለቲካ ፓርቲ አባልነትም ሆነ፤ የፖለቲካ ፓርቲ ታዛዥነት የለውም። ዘብ የሚቆመው ለሕገ መንግሥቱ ብቻ ነው። የአንዱን ብሔር ወይም የአንዱን ፓርቲ አሊያም የአንድ እምነት ወይም የአንድን አመለካከት ደግፎ አይቆምም። ሠራዊታችን የሚቆመው ለሕገ መንግሥቱ መርሖዎች መከበር እና ለኢትዮጵያ ሰላም፤ ለነጻነት እና ለሉዓላዊነት ብቻ ነው። ለሕጉ እና ለሥርዓቱ እየታዘዘ፤ ሁሉንም በእኩልነት፤ በገለልተኝነት ነጻ ሆኖ በሙያ ብቃት ያገለግላል። የብሔር ብዝኃነት ብቻ ሳይሆን፤ የሐሳብ ብዝኃነት ባለበት ሀገር የሚኖር መሆኑን የሚያውቅ፣ የሚተገብር፣ ጠንካራ ዲሲፕሊን ያለው የሀገር መከላከያ ሠራዊት በመገንባት ላይ እንገኛለን።

ዛሬ ከፍተኛውን መዓርግ የተቀዳጁ የሠራዊታችን አመራሮችም ሆኑ እስከታች ድረስ የሚገኙ የሠራዊቱ አባላት የኢትዮጵያን ብልጽግና እውን ለማድረግ ሀገራቸው ኢትዮጵያ አንድነቷን ጠብቃ እንድትኖር የማይናወጥ አቋም እንዳላቸው ይታመናል። ማንኛውም ነገር ከሀገር ሕልውና እና ሉዓላዊነት አይበልጥም። ሁሉም የፖለቲካ ኃይሎች ሕግ እና ሥርዓት አክብረው መጫወት ግዴታቸው ብቻ ሳይሆን ሐላፊነታቸውም ጭምር ነው። የመከላከያ ሠራዊታችን ከሁሉም የፖለቲካ ኃይሎች ገለልተኛ፤ ለሕገ መንግሥት ሥርዓቱ ታማኝ፤ የሕዝቡን ሰላም እና ደኅንነት ጠባቂ ሆኖ መቆም ይኖርበታል። ማንኛውም በመርከቧ ውስጥ የሚደረግ እንቅስቃሴ የመርከቧን ሕልውና አደጋ ላይ እንዳይጥለው መጠበቅ ብቻ ሳይሆን የሚጥል አደጋ ሲያጋጥም ዛሬም እንደተለመደው መሥዋዕት ለመሆን ዝግጁ የሆነ የመከላከያ ሠራዊት እንዳለን ይታመናል። ለዚህ ተልእኮውም በሁሉም ዘርፍ ብቁና ዝግጁ ነው ተብሎ የሚታመነው የመከላከያ ሠራዊታችን የኢትዮጵያን ብልጽግና የማረጋገጥ ጉዞው በሰላም እና በደኅንነት እጦት እንዳይደናቀፍ የበኩሉን ሚና እንደሚጫወት መንግሥት ያለውን ሙሉ እምነት በዚሁ አጋጣሚ ልገልጽላችሁ እፈልጋለሁ።

ሀገሩን የሚወድ፤ መለዮውን የሚያከብር፤ የሀገሩን ሕልውና እና ብልጽግና ቀዳሚ ርእይ አድርጎ የሚይዝ ፕሮፌሽናል በሚል የመገንባት ሂደት ውጤታማ እንዲሆን ጄነራል መኮንኖች ሐላፊነታችሁን በታማኝነት እንድትወጡ ብቻ

ሳይሆን፤ ለራሳችሁ፤ ለተቋማችሁ፤ ለሀገራችሁ ያላችሁን ክብር በተግባር እንድታሳዩ በዚሁ አጋጣሚ አሳስባችኋለሁ። አንድ ወጣት አባቱን “የሕይወት ዋጋ የሕይወት ትርጉም ምንድን ነው?” ብሎ ሲጠይቀው፤ አባቱ ለልጁ አንድ የተጠረበ ድንጋይ ወይም የሚያምር ድንጋይ ከሰጠው በኋላ፤ “ይህንን ድንጋይ ወደገበያ ስፍራ በመውሰድ እንደሚሸጥ ሰው ከአሳየሀቸው በኋላ ዋጋውን ከጠየቁህ አትናገራቸው። ሁለት ጣትህን ብቻ ድንጋዩ ላይ በማስቀመጥ አሳያቸው” ብሎ ልጁን ይመከረዋል። ያንን ድንጋይ ይዞ ወደ ሱቅ የሄደው ልጅ ድንጋዩን ከአስቀመጠ በኋላ የሚያምር ጥርብ ድንጋይ ስለሆነ ገዢው ዋጋው ስንት ነው ሲለው ሁለት ጣቱን ሲያስቀምጥበት፤ “አሃ 2 ዶላር ነው?” ልገዛህ ዝግጁ ነኝ” ይለዋል። ልጁ አትናገር በተባለው መሠረት ድንጋዩን ይዞ አባቱ ዘንድ በመሄድ “እጄን ሳሳየው ሁለት ዶላር ከሆነ ልግዛህ ብሎኛል” በማለት ይናገራል። አባቱ መልሶ “ይህንን ድንጋይ ወደሙዚየም ይዘህ ሄደህ ቅድም ያደረግኸውን ደግመህ አድርግ” ይለዋል። ይህም ልጅ ያንን ድንጋይ ወደ ሙዚየም በመውሰድ ሁለት ጣቱን አስቀመጠበት። በጣም የሚያምር ድንጋይ ስለሆነ፣ “ልገዛህ እፈልጋለሁ” ሲባል አሁንም ሁለት ጣቱን ብቻ ያስነካል። ገዢውም፣ “አህ፣ 200 ዶላር ነው? ልገዛህ ዝግጁ ነኝ” ይለዋል። ልጁም በመደሰት ወደ አባቱ ይመለስና፣ “ቅድም 2 ዶላር አሁን ደግሞ 200 ዶላር ተብያለሁ” ይለዋል። “አሁን ደግሞ ይህንን ድንጋይ፣ የድንጋይ ስብስብ ወደሚሸጡ ሱቆች በመሄድ ተመሳሳይ ነገር አድርግ” ብሎ አባቱ ሲያዝዘው፤ ያንን ድንጋይ ወደ መሸጫ ሲወስድ፣ በጣም በመደሰት “ልገዛህ ፍላጎት አለኝ፣ ስንት ነው?” ሲባል አሁንም ሁለት ጣቱን ድንጋዩ ላይ ያስቀምጣል። “አህ! 200 ሺሕ ዶላር ነው? ልገዛህ ዝግጁ ነኝ” ይለዋል ሰውየው፤ ልጁ በመደንገጥ ወደ አባቱ ሮጦ በመመለስ፤ ያየውን የሰማውን ይነግረዋል። አባቱም ለልጁ “ያንተ ዋጋም እንደዚሁ ነው” ይለዋል።

ክቡራን ጄነራሎች፤ ከየትኛውም ብሔር ብትወለዱ፤ ከየትኛውም እምነት ብትገኙ፤ ከየትኛውም የኢትዮጵያ ጫፍ ብትወለዱ፤ በጾታችሁ ወንድ ወይም ሴት ብትሆኑ፤ የእናንተ ዋጋ የሚተመነው በውሏችሁ እና በሥራችሁ ነው። ውሏችሁ እና ሥራችሁ ከፍ እንዲል በምትመርጡት ጓደኛ ፕሮፌሽናችሁን በማክበር፤ መለዮአችሁን በማክበር፤ የዕለት ተዕለት ተግባራችሁን በማክበር ስትገኙ፤ ያያችሁ ሁሉ ሳትናገሩ ዋጋችሁን ከፍ ያደርገዋል። አንድ ጄነራል ጄነራል ለመሆን በወታደር ቤት ከ30 ዓመት በላይ በከፍተኛ ዲሲፕሊን አገልግሎ ጄነራል ከሆነ በኋላ ማንኛውም ፖለቲከኛ ወደቀኝ እና ወደግራ የሚያዞረው ከሆነ ዋጋው በዚያ ልክ ይሆናል። ጸንቶ በመቆም ባንዲራውን፣ መለዮውን፣ ሀገሩን፣ ሕገ መንግሥቱን ሲጠብቅ፣ ክብሩ፣ ሞገሱ እና ማንነቱ ለዘመናት የሚዘልቅ ይሆናል። የአንድ ጄነራል ክብሩ ውሎው ነውና ውሏችሁን በማሳመር ክብራችሁን እንድትጠብቁ አደራ ልላችሁ እፈልጋለሁ።

## አመሰግናለሁ!

# የኢትዮጵያ የሕዳሴ ግድብ ጉብኝት ንግግር

ጥር 23/2012 ዓ.ም.

ዛሬ ለሁለተኛ ጊዜ የሕዳሴ ግድብን ለመጎብኘት ዕድል አግኝተናል። አምና ስንመጣ ብዙ ነገሮች እጅግ በጣም አሳሳቢ ነበሩ። መቼም ይሄ ፕሮጀክት ትልቅ ህልምና ለኢትዮጵያውያን የሚያኮራ ፕሮጀክት ሆኖ ሲያበቃ ከነበረን የአመራር እጥረት እና ቅንጅት የተነሣ በከፍተኛ ደረጃ አክሳሪ እንዲሆን ተደርጎ ነበር የተመራው። ለምሳሌ፤ ከዚህ እስከ ሆለታ የዘረጋነው የኤ.ሲ ማስተላለፊያ ትራንስሚሽን ኬብሎች በኢትዮጵያ ውስጥ ትልቅ የማስተላለፍ ዐቅም ያለው ኬብል ነው። ይህ ኬብል ልክ ትልቅ ሃይ ዌይ መንገድ በብዙ ኪሎ ሜትር ገንብቶ አንድም መኪና እንደማይሄድበት ማለት ነው። ባለፉት ሁለት ዓመታት ፕሮጀክቱ አልቋል። ሙሉ በሙሉ ከዚህ ሆለታ ተገናኝቷል። ግን አንዲት ዋት ኢነርጂ የሚተላለፍበት የለም። ሁለት ዓመት ሙሉ ዝም ብሎ የቆመው ብረት ሌላ ቦታ ከፍተኛ እጥረት ባለበት ኢንቨስት አድርገነው ቢሆን ኖሮ ምን ያህል ገንዘብ ልናገኝ እንደምንችል በቀላሉ ማስላት ይቻላል። እሱ ብቻ አይደለም። ይሄ የተዘረጋው የትራንስሚሽን ኬብል መስመር ስለአልተሞከረ ኢነርጂው ጀነሬት አድርጎ ሲሞከር አዳዲስ ጣጣዎች ሊያመጣብን ይችላል። ልክ ሥራ የሌለው ገንዘብ ባንክ እንደማስቀመጥ፤ ሥራ የሌለው መንገድ ወይም ሃይ ዌይ ገንብቶ እንደማስቀመጥ፤ ይሄንን የሚያክል ረጅም ርቀት መሄድ የሚችል ትራንስሚሽን ኬብል በዚያ ላይ ደግሞ ከፍተኛ ካፓሲቲ ያለው ነው። በአገር ውስጥ ካሉት ካፓሲቲዎች ከፍተኛ ካፓሲቲ ያለው ትራንስሚሽን ላይን ይሄ ነው፤ ግን ሁለት ዓመት ካለቀ ጊዜ ጀምሮ ምንም ሥራ አልሠራም። ይሄንን ብናሰላ ምን ያህል ሀብት እንዳወደምን ማሰብ ይቻላል።

እውን ኢትዮጵያ ደሃ አገር ነች ወይ? ሀብቷን አልባሌ ቦታ ካለአግባብ፤ ከዕውቀት ማነስ እያፈሰሰች፤ ሌላ ቦታ ደግሞ የሚገጥማትን ችግር ለመፍታት በከፍተኛ ደረጃ የሀብት ውስንነት ሲያጋጥማት ይታያል። በዚህ ፕሮጀክት መዘግየት ምክንያት በዓመት አንድ ቢሊዮን ዶላር የሚገመት ሀብት ኢትዮጵያ አጥታለች። የዛሬ ሦስት ዓመት ጨርሰነው ቢሆን ኖሮ ሦስት ቢሊየን ዶላር በየዓመቱ ስለምናገኝ የፕሮጀክቱን ግማሽ መልሰን ነበር ማለት ነው። ፕሮጀክቱ ዘገየ ማለት ብዙ ልናገኝ የነበረውን ሀብት አጣን፤ ተጨማሪ ሀብት እንድናፈስ ያደርገናል።

አሁን ከፍተኛ ውስንነት የነበረው በሜቴክ ተይዞ የነበረው የኤሌክትሮ ሜካኒካል ክፍል ባለመሠራቱ ሳሊኒ ሥራውን ሊሠራ አልቻለም። በዚያም የተፈጠረው መዘግየት በእኛ ምክንያት ስለሆነ ተጨማሪ ገንዘብ ጠይቆናል። የእርሱን ተጨማሪ ገንዘብ መደራደር እና መክፈል ብቻ ሳይሆን ፕሮጀክቱን ሞያ ላላቸው፤ ብቃት ላላቸው ሰዎች ሰጥተን እንደ አዲስ ማሠራት ይጠይቅ ነበር። እንግዲህ አምና መጥቼ በማይበት ሰዓት ያዘንኩበት ሥራ ነው። እና ትንሽ ጠንከር ያለ ርምጃም የወሰድንበት ሥራ ነው። ቦርድ ቀይረናል። የኤልፓን ማኔጅመንት ቀይረናል። በፕሮጀክት ላይም ሰፊ ማኔጅመንት ቀይረናል። ኩባንያዎች ኮንትራታቸውን ቆርጠን አዳዲስ ኩባንያዎች ሰጥተናል። እውነት ለመናገር ከሪፎርም በኋላ እጅግ የሚያኮራ አመራር የተገለጠበት፤ በጀግንነት በመወሰን ፕሮጀክቱን ማዳን የቻልንበት መሆኑ እና ፕሮጀክቱም አሁን ውጤቱ ሲታይ እንኳንም ወሰንን፤ እንኳንም ጨክነን፤ ማስተካከያ ርምጃ አደረግን እንድንል የሚያስደፍር ነው።

እንግዲህ ይሄ ፕሮጀክት ለኢትዮጵያ፣ ለሱዳን፣ ለግብፅ፣ ለመላው በምሥራቅ አፍሪካ ለሚገኙ አገራት ትልቅ ፀጋ ነው። አንደኛ፤ የማድረግ ዐቅማችን የተፈተነበት ነው። ማለም ብቻ ሳይሆን መከወን እንደምንችል ያሳየንበት ነው። ይሄንን ከከወንን ሌሎችን ፕሮጀክቶች መሥራት መከወን እንደምንችል ለእኛም ለወገኖቻችንም ጉልበት ይሆናል። በተጨማሪም ባለፈው በነበረው ጥራት አልቆ ቢሆን እና ግድቡ የቴክኒካል ስሕተት ቢያጋጥም ኖሮ እምነት ያጎድል ነበር። የታችኛው ተፋሰስ አገራት በጥራት አትሠሩም ብለው ይጠረጥሩ ነበር። አሁን በዚህ ጥራት መሠራቱ ምንም አደጋ የማያመጣ ስለሚሆን እነርሱም በቴክኒኩ ረገድ በራስ መተማመን እንዲያዳብሩ ያደርጋል። ለእኛም ደግሞ የሕዝብ ፕሮጀክት ነው። የመላው ኢትዮጵያውያን ዐይን ያለበት ፕሮጀክት ነው። ጨርሰን ለውጤት ማብቃት አገራዊ ኩራት ነው። ይሄንን ማስጨረስ ከትውልድ ሁሉ ይጠበቃል። ይሄንን ህልም ያለሙ፣ ያሰቡ፣ የአስጀመሩ፣ በዚህ ሥራ ውስጥ የተሳተፉ ጀግኖችን በሙሉ እናደንቃለን። እናከብራለን። የጀመሩትን በመጨረስ ደግሞ የኢትዮጵያ የትውልድ ቅብብሎሽ ሀገር ግንባታን እናረጋግጣለን።

በዚህ ፕሮጀክት የምናየው ሀገር እንደ ሀገር የሚቀጥል መሆኑን፤ ትውልድ የተጀመረን የሚጨርስ መሆኑን፤ ነገር ግን ስሕተት ሲያጋጥም ወደኋላ ስሕተት የሚያርም መሆኑን ያየንበት ስለሆነ የመደመር ፍልስፍና የታየበት አንዱ ፕሮጀክት ሕዳሴ ነው። የነበሩትን ክፍተቶች ቀርፈን የነበረውን ጥራት እንዳለ ጠብቀን፤ ለትውልድ ደግሞ ይተርፍ ዘንድ መሠራት ያለበትን ሥራ አከልን፤ ይሄንን በሁሉም ሥራችን ውስጥ ማምጣት ከቻልን በኢትዮጵያ ውስጥ ብልጽግናን የምናረጋግጥበት ጊዜ ቅርብ እንደሆነ ያሳያል። ይህ ፕሮጀክት በኢትዮጵያውያን ላይ በአካባቢው አገራትም ጭምር በጣም ብዙ ወርድና ስፋት ያለው ተጽዕኖ ይፈጥራል። ይሄንን አሳክተን ውጤታማ ከሆንን በርካታ ሥራ ለመሥራት ዕድል አለን። ኢትዮጵያ በሃይድሮ ኢነርጂ የማመንጨት ዐቅም በከፍተኛ ደረጃ ከታደሉ አገራት አንዷ ናት። ውሃም አለን። መልክአ





ምድሩም ይመቻል። ይሄንን አፋጥነን በመሥራት በኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን የኃይል እጥረት መቀነስ ይጠበቅብናል። በአለፉት ዓመታት የኢትዮጵያ መንግሥታት የነበራቸው ትልቁ ባሕርይም ይህንን ሴክተር መድፈር መጀመር ስለሆነ፤ እጥረቱን ቀንሰን፣ ጥራት ጨምረን፣ በርካታ ፕሮጀክቶች መሥራት ከቻልን ኢትዮጵያ ውስጥ ብዙ ችግር ይፈታል። ከሥራ አጥነትም አንፃር፤ ሀብት ከማመንጨትም አንፃር። ከዚያ በተጨማሪ ተመልከቱ። ይህንን መልክአ ምድር ምን ዓይነት ከተማ ሊገነባ እንደሚችል እዚህ አካባቢ ማሰብ ይቻላል። የዚህ ውሃ ግድብ ወደኋላ የሚሄደው ከአዲስ አበባ እስከ ሻሸመኔ የሚያክል ርቀት ነው። የጣናን ሐይቅ ሁለት ተኩል ገደማ የሚሆን ውሃ ይይዛል። ከአዲስ አበባ እስከ ሻሸመኔ የሚደርስ ሐይቅ አለን ማለት ብዙ ሪዞርቶች፣ ብዙ ሆቴሎች፣ ዓሣ ማጥመጃ፣ ምናልባትም የጀልባ ትራንስፖርት፤ በርካታ ጠቀሜታዎች በውስጡ ልናገኝ እንችላለን።

እንግዲህ አሁን ኢትዮጵያውን ሀብታሞች ማሰብ ያለባቸው በሚቀጥለው ዓመት ቢያንስ ሁለቱ ተርባይን ሥራ ይጀምራሉ። ከዚያ በኋላ በ2015 ዓ.ም. ሙሉ በሙሉ ይጠናቀቃል። ከወዲሁ ተራሮቻቸውን ማሰስ ቢጀምሩ፤ ለሪዞርት ዲዛይን ማድረግ ቢጀምሩ፤ እዚህ ያሉት ኮንትራክተሮች ሳይወጡ የሞያ ድጋፍ ወስደው አዳዲስ ሪዞርት ቢሠሩ፤ ዛፎች ስንተክል፣ ውሃው ሲታቀብ፣ በከፍተኛ ደረጃ የሃብት ምንጭ እና የመዝናኛ ቦታ ስለሚሆን ይህንን ውብ መልክአ ምድር እና አፈጣጠር ለሀብት ማመንጫነት እና ለብልጽግናችን ድልድይ አድርገን መጠቀም ይኖርብናል። ይህንን ለማድረግ የሚያስችል ሁለንተናዊ ለውጥ ይታያል። በሪፎርሙ ከታዩ ሥራዎች የሠራነው አንዱ እዚህ ቦታ ላይ ነው። ይሄንን በማሣለጥ የኢትዮጵያን ብልጽግና ማረጋገጥ የሁላችንም ሐላፊነት ይሆናል። ይህም እንደሚሆን ተስፋ እናደርጋለን!

**አመሰግናለሁ!**

# ለፌደራል እና ለትራፊክ ፖሊስ የተደረገ የምስጋና ሥነ ሥርዓት ንግግር

የካቲት 4/2012 ዓ.ም.

**የተከበራችሁ የፌደራል፣ የአዲስ አበባ፣ የትራፊክ ፖሊሶች፤**

መከላከያ ሠራዊታችንን ጨምሮ በሰሞኑ የአፍሪካ ኅብረት የመሪዎች ስብሰባ እኔንም የአፍሪካ መሪዎችንም በሚያስደንቅ ሁኔታ ግዳጃችሁን የተወጣችሁ ሁሉ፤ በአፍሪካ ኅብረት ተወክላችሁ እዚህ ያላችሁ ፖሊሶች፤ እንደ ወታደር እንደ ሀገር መሪ ቀና ብዬ እንድቆም ስለአደረጋችሁኝ የተሰማኝን ታላቅ ኩራት ልገልጽላችሁ እፈልጋለሁ። የፌደራል ፖሊስ የትራፊክ ፖሊስ አባላት እንደዚህ ጀግና፤ አገር ወዳድ መሆናችሁን ሳላውቅ በዝግጅቱ ሳምንት ብዙ ስለማላምናችሁ ማታ ማታ እዞር ነበር። አንድ አራት ቀን አምስት ቀን ሲቀረው እና ትራፊክ ፖሊሶችና ፖሊሶች በየቦታው በዚያ ምሽት ቆመው ሳይ አልፎ አልፎ የምታዩኝ ትኖራላችሁ። ብዙ ሰው እንደምንቀሳቀስ አያውቅም። በዚህ ደረጃ ግን የሚያኮራ ሥራ የፌደራል ፖሊስ ይሠራል ብዬ አላሰብኩም ነበርና ራሴን ታዘብኩት። እውነቴን ነው የምነግራችሁ፤ ከአሁን በኋላ ፊቴን ወደ እናንተ አዞራለሁ። እናንተም በጀመራችሁት መንገድ ቀጥ ብላችሁ ትቆማላችሁ ማለት ነው።

በፌደራል ፖሊስ ላይ መጠነኛ ማሻሻያዎች ስናደርግ ቆይተናል። በብዙ እጥፍ አጠናክረን እንቀጥላለን። የአገኘሁት መሪ ሁሉ የአዲስ አበባን መንገድ አበባ እና የእናንተን ጥበቃ፣ የዩኒቲ ፓርክን ጽዳትና ዝግጅት “ኢትዮጵያ ምን እየሆነች ነው?” የሚል ጥያቄ የማያነሣ መሪ አልነበረም። አንድ ወታደር ድንበር መጠበቅ፤ አገር መጠበቅ ብቻ ሳይሆን ዩኒፎርም አስተካክሎ ለብሶ፣ መለዮውን ሲያከብር በቀጥታ አገር ይከበራል። እናንተ በሰሞኑ ሥራችሁን የሠራችሁ ሊመስላችሁ ይችላል። ግን አይደለም። ኢትዮጵያን በአንድ ዐይናቸው ሸውረር አድርገው ማየት የሚፈልጉ ሁሉ ድጋሚ ማሰብ እንዲችሉ አስገድዳችኋቸዋል። ቅንጅቱ፣ የምታዩበት መንገድ፣ ጥበቃችሁ ደስ ስለአሰኘኝ ክብርት ወ/ሮ ሙፈሪሃትን ሁሉንም ወታደር መጥራት ባይቻል ከተወካዮቻቸው ጋር አንድ ቀን በዩኒቲ ፓርክ ራት ብንበላ ብዬ ጠየኳት። ስለመጣችሁና አብረን ራት መብላት ስለቻልን በጠቅላይ ሚኒስትር ቢሮ ያሉ አመራሮችም ከፍተኛ ደስ የተሰማን መሆኑን እየገለጽኩ፤ ሁለት ሦስት መልክእቶች አሉ።

አንደኛ፤ ፖሊስ ዘር የለውም። ፖሊስ ሰው ነው የሚጠብቀው እንጂ ዘር አይጠብቅም። ሰው እንዳይቆስል፤ ሰው እንዳይሞት፤ ሰው እንዳይቆጣ ይከላከላል። ያ ሰው የሚባለው ሱዳናዊም ሊሆን ይችላል። የመናዊም ሊሆን ይችላል። ኤርትራዊም ሊሆን ይችላል። ማንም ሰው እንዳይጎዳ የሚከላከል፤ ሙያውን የሚያከብር፤ መለዮ የሚያከብር፤ ለኢትዮጵያ ህልውና የሚቆም መሆን አለበት። ዘር ዘር የሚሸት ነገር ፖሊስ ውስጥ እንዳይገባ ጥንቃቄ አድርጉ። ሁለተኛው፤ ከበረታችሁ እና ከጠበቃችሁ ብልጽግና በደጃችን ነው። በርካታ ለውጦች እየመጡ ነው። ኢትዮጵያም የምትለወጥበት ጊዜ ቅርብ ነው። ከተዳከማችሁ እና ከተዘናጋችሁ ግን የመን፣ ሊቢያ ከእኛ የሚያንሱ ስለአልነበሩ አሁን ዜጎቻቸው ያሉበት ችግር እኛንም ሊገጥመን ይችላል።

ሊቢያ በጋዳፊ ዘመን ብዙ የአፍሪካ መሪዎች እጅ የሚነሱት በንጉሥ ደረጃ የሚታይ ሰው አሁን በዋና ከተማው ሆቴሎች ሥራ አይሠሩም። ጦርነት አስቀያሚ ነው። ያለን ነገር ያበላሻል ይሸፍናል። ያ እንዳይሆን አገራችንን ከጥቃት፣ ከመከፋፋል፣ ከመለያየት እንድንጠብቅ ወታደራዊ ሙያችሁን አትዘንጉ።

ሌሎች የፖርቲ ሰዎች በፖለቲካ ወይም በዘር ምክንያት እናንተን ሊያዝዙ ከፈለጉ መለዮዋችሁን ንቀውታል ማለት ነው። ሰው ካልናቀ በስተቀር እናንተን በዚያ ጎራ ወይም በዚህ ጎራ ተሰለፍ አይላችሁም። እናንተ ግልጽ የሙያ ሥነ ምግባር ያላችሁ፣ ምን እንደምትሠሩ የምታውቁ፣ እንዴት እንደምትሠሩ የምታውቁ ሰዎች ናችሁ። ብዙዎቻችሁም ሃያ፣ ዓሥር፣ ዓሥራ አምስት፣ ሠላሳ ዓመት ልምድ ያላችሁ ናችሁ። አማተር ፖለቲከኞች የፖለቲካ ሰው ስለሆኑ ብቻ እናንተን ወደ ግራ ወደ ቀኝ እንዲነዷችሁ መፍቀድ የለባችሁም። ብልጽግና ኖረም አልኖረም፣ የሆነ ፓርቲ ኖረም አልኖረም ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኖራለች። ፌደራል ፖሊስም እየተወራረሰ ለዘለዓለም ይኖራል። ሥራችሁን፣ ባንዲራችሁን፣ መለዮአችሁን የምታከብሩ ከሆነ ማንም ቢመጣ ማንም ቢሄድ በአገር ደረጃ አደጋ አያጋጥምም። ያም እንዳያጋጥም ብዙ ሥራ ይጠቅባችኋል።

ከፊታችን በብዙ መንገድ ብሩህ ተስፋ አለ። በኢኮኖሚም በርካታ ማሻሻያዎች ተሠርተዋል፤ እየተሠሩ ይገኛሉ። በፖለቲካውም እንደዚሁ፤ ያልጠሩ ጉዳዮች እዚህም እዚያም አሉ። ተፈጥሮአዊ ነገሮች፣ ሰው ልጅ ወልዶ ወዲያው በሰዓታት መካከል አይስመውም። እናትም ዐይን ዐይኑን ታያለች እንጂ አትስመውም። ምክንያቱም ገና አልለየለትም። ደምና ሰው ስለሆነ ጠፈፍ ማለት አለበት። ሰው ሆኖ ጉንጬን ለመሳም ጠፈፍ ማለት አለበት። የእኛም ማሻሻያ ጠፈፍ አላለም። ጠፈፍ እስኪል ዐይን ዐይኑን ማየት ይኖርባችኋል። ዘልለን ጉንጬን አልሳምነውምና ማሻሻያው በእግሩ አልቆመም ብትሉ ታሪክ አታውቁም ማለት ነው።





ኃይለ ሥላሴ ከልጅ እያሱ በኋላ ሥልጣን ሲይዙ ባልቻ አባ ነፍሶ ከሲዳሞ /የሲዳሞ ገዥ ነበር/ በሺሕ የሚቆጠር ወታደር አሰልፎ አዲስ አበባ ድረስ መጥቷል። "እንዴት ተፈሪ ይነግሣል!" ብሎ፤ ብዙ ግርግሮች ነበሩ። ዘውዲቱም ከዚህ ግቢ እንጦጦ ተልከው ነበር። ነገር ግን ጠፈፍ የሚልበት ጊዜ ሲመጣ ያው እንደምታውቁት ረዝሞ እስኪሰለች ንጉሡ ቆይተው ነበር። መንግሥቱ ኃይለ ማርያም የንጉሡን ሰዎች እዚህ ቤት ብዙዎቹን ገድሎ፤ አባርሮ መንግሥት ከሆነ በኋላ እስከሰባ ሁለት ሰባሦስት ዓመተ ምሕረት ድረስ ከሰው እጅ ሳይሆን ከቅርብ ኮሚቴዎቹ ውሃ የማይቀበል፣ ከላይ አማን አንዶምን ከታች አጥናፉንም ጭምር የቀጠፈ፤ በብዙ ግርግርና መደናገር ውስጥ የቆየ፤ ምናልባት ሰባ አራት፣ ሰባ አምስት ዓመተ ምሕረት አካባቢ መንግሥት እየሆነ የመጣ ነበር፡፡ ለምን ስቴት ቢውልድ የማድረግ ባህል አልነበረም።

በኢሕአዴግ ዘመን ታጋዮች የነበራችሁ እንደምታውቁት 83፣ 84 ዓ.ም. መርካቶ ላይ አንድ ሌባ ፌስታል ይዞ ሲሮጥ ታጋይ ከአየ ጎምበስ ብሎ አነጣጥሮ ግምባሩን ይመታዋል እንጂ መያዝ፤ ፍርድ ቤት መውሰድ አልነበረም። በየቀበሌው ሌባ እያልን ሰው ይዘን፤ ሰብስብ አድርገን ፈራጅ ዳኛ ሆነን እንሰቅል ነበር። በብዙ ከተማ ሰው ሞቷል። 88፣ 89፣ 90 ዓ.ም. ነገሮች መልክ እየያዙ ሲሄዱ ግን ሌባም ቢሆን ተይዞ ፍርድ ቤት፤ ጥፋተኛም ቢሆን ተይዞ ፍርድ ቤት፤ በዚህ ሁሉ ጊዜ ውስጥ የአብዮት ባሕርይ ስለአለው ቀድሞ የነበረውን አዲስ የመጣው እያጠፋው ስለሚሄድ በቀለለ መንገድ ባጠረ ጊዜ መንግሥት መፍጠር ይቻላል።

የእኛ ግን ማሻሻያ ነው። ማሻሻያ ማለት ከዚህ ቀደም የነበረውን ፌደራል ፖሊስ ጠርገን አጥፍተን አዲስ ፖሊስ አላመጣንም። አዲስ መከላከያ አላመጣንም። አዲስ ደኅንነት አላመጣንም። በዚህ ምክንያት ሰው ይደናገራል። ማሻሻያው ለመላ የኢትዮጵያ ሕዝቦች የመጣ መሆኑን እናንተ ለማመን ጊዜ ያስፈልጋችኋል። የሰው ባሕርይ ነው። ሁለት ጓደኞች አንድ ዓመት፤

አምስት ዓመት፤ ዓሥር ዓመት ሲኖሩ በመጀመሪያው ዓመትና በዓሥረኛው ዓመት ላይ እኩል አይተማመኑም። በብዙ ችግር አብረው ከአለፉ በኋላ እምነት ይጨምራል፤ ያድጋል። ይሄ ማሻሻያ የትግራይን ሕዝብ እንደማይጎዳ፤ የጋምቤላን ሕዝብ እንደማይጎዳ፤ የአማራን፣ የኦሮሞን፣ የደቡብን እንደማይጎዳ፤ የአፋርን፣ የሱማሌን እንደማይጎዳ፤ እርግጠኛ ለመሆን ጊዜ ይፈልጋል።

ሰዎች ሲጠራጠሩ ተፈጥሮአዊ መሆኑን ማወቅ አለባችሁ። ነገር ግን ጠፈፍ ማለቱ አይቀርም። መጠራጠር የሌለባችሁ ነገር ጠፈፍ ማለቱንና የኢትዮጵያን ብልጽግና መረጋገጡ የማይቀር መሆኑን ነው። በዚህ ጊዜ ውስጥ ታሪክ የሚያውቅ አሁን ያለው ውጣ ውረድ የሚታለፍ መሆኑን የሚያምን፤ ጽናት ያለው፤ ለትውልድ ቅብብሎሽ ዝግጁ የሆነ፤ መለዮ የሚያከብር፤ ባንዲራ የሚያከበር፤ ሕግ የሚያከብርና የሚያስከብር ወታደር ከሆናችሁ፤ ኢትዮጵያ የሰላምና የብልጽግና አገር ትሆናለች። ነገሩም እየጠራ፤ ዳመናውም እየጠራ ሲሄድ ሁሉም መልክ መልኩን ይይዛል። ያ እንዲሆን ግን ፌደራል ፖሊስ በነበረበት ጉልላት፤ በነበረበት ዳገት ራሱን ማስቀጥ አለበት።

አንድ ሰው ከፍ ያለ ቦታ ላይ ሲቀመጥ ጠዋት ጉም ይሸፍነዋል። ተራራ በጉም መሸፈን ባሕሪው ነው። ዝናብ ሲመጣ ቀድሞ ጨለም የሚለው የተራራ አካባቢ ነው። አሁን የምታዩት ንፋስ ከዚህ ወጥታችሁ መስቀል አደባባይ ብትሄዱ የለም። ትንሽ ከፍ ስለሚል ይሄ ንፋስም ቀድሞ ያለው እዚህ ነው። ንፋስ መጣ ብለህ ተራራህን አትልቀቅ። ጉም መጣ ብለህ ተራራህን አትልቀቅ። በአለህበት ከጸናህ አንተ በተራራ ላይ ትቀጥላለህ። ጉሙ ግን ያልፋል። ዝናቡ ያልፋል፤ ንፋሱ ያልፋል። ሸሽተህ ዝቅ ካልክ ግን ተራራው በሌሎች ይወረሳል። ባለህበት የመቆም ብቃት ካለህ ኃላፊ አግዳሚው ችግር ይታለፋል። ጽናት ያስፈልጋል።





አዲስ አበባ ላይ እናንተ እያላችሁ ቦሌ መንገድ የተቀመጠው አበባ በትንሹ ሃምሳ ጊዜ ውሃ አጠጥቼዋለሁ። በትንሹ ብዙ ማታ አንዳንዶቻችሁ አይታችሁን ሊሆን ይችላል እኔ ያጠጣሁት እኔን እንድትመስሉ ነው፤ እንድታጠጡ ነው። ጠንከር ብለን አገር የማቆም የማስቀጠል ጉዳይ ሐላፊነት እንዳለባችሁ አምናችሁ በታማኝነት ሥሩ። መንግሥት አለባበሳችሁን፣ ትጥቃችሁን፣ ኑሮአችሁን ለማሻሻል አቅዶ ይሠራል። በአሁኑ የአፍሪካ ኅብረት ስብሰባ ኢትዮጵያ አይደለም አፍሪካ በሙሉ ኮርቶባችኋል። ብዙ መርዶ፤ ብዙ የውሸት ትንቢቶች ነበሩ። ግን ጎማ አልተነፈሰም። ጎማ ያልተነፈሰው አስተማማኝ ፖሊስ ስለአለን ነው። አስተማማኝ ፖሊስ መሆናችሁን መንግሥታችሁንም አስተምራችኋል። ሕዝባችሁንም አስተምራችኋል። እንግዶቹንም አስተምራችኋል። መንግሥታችሁ ራሱ እንደዚህ ጠንካራ መሆናችሁን አያውቅም። ስግቼ ብዙ መከላከያ ይሳተፍ ብዬ ነበር። ኮሚሽነሮቹ እንበቃለን ብለው በብቃት ሠርተዋችኋል። በመቶ የሚቆጠር መከላከያ ነው የተሳተፈው፤ በሺሕ የሚቆጠር ፖሊስ ነው የተሳተፈው፤ የትራፊክ ፖሊሶች በዚያ ንፋስ፤ በዚያ ብርድ፤ በዚያ ማታ፤ በዚያ ፍጥነት ሕይወታችሁን አደጋ ውስጥ እየከተታችሁ ያደረጋችሁትን ሥራ ሁሉ በቅርበት አይቻለሁ።

በብራዚል የትራፊክ ፖሊስ እቀና ነበር። ተሳስቻለሁ። በጣም ታኮራላችሁ። እናንተ ተጨማሪ ሥልጠና ያስፈልጋችሁ ይሆናል። ቆራጥ ወታደር መኖችሁ ግን ተረጋግጦላችኋል። ከተራራችሁ ላይ ቁጭ በሉ። ዝቅ እንዳትሉ። ይሄ ተነግሯል ብላችሁ ነገ ደግሞ ዝቅ ከአላችሁ ደረጃው ዝቅ እንዳይል፤ ከዚህ በኋላ "የወርልድ ቱሪዝም ፎረም፤ የወርልድ ኢኮኖሚክ ፎረም፤" ትንሽ ቆይቶ የአፍሪካ ኤክስፖ አዲስ አበባ ላይ ይካሄዳል። ምርጫ ይካሄዳል። ብዙ አያስጨንቀኝም። ምርጫ ሰላማዊ መሆኑን ስለአየሁት ሰላማዊ ነው አትስጉ። ሰላማዊ አይደለም ብሎ የሚፎክር ሰላም ማደፍረስ አይችልም። የምታደፈርስ ከሆነ አትፎክርም።

ኢትዮጵያ ውስጥ ዲሞክራሲ፤ ኢትዮጵያ ውስጥ ሰላም፤ ኢትዮጵያ ውስጥ ብልጽግና ሕልማችን ነው። በአትዮጵያ ህልውና ከመጣ ግን የተውነውን መለዮ እናነሣለን እንጂ ኢትዮጵያን ለአልባሌ ጭልፊቶች ለአደጋ አናጋልጥም። ይሄ መሠመር አለበት። ውትድርና መጥፎ ነገር አለው። ከውስጥህ አይሞትም። ታውቁታላችሁ። አንተ እያረጀህም፤ እየደከምክም አይሞትም፤ ከእናንተ ውስጥ ማታ ቤት ገብቶ ልብሱን ሲያወልቅ ሳያጣጥፍ የማይተኛ ሰው አለ። ይገርማችኋል! ድሮ ይሁን አሁን ለምዶብኝ ሱፍ ካወለቅሁ በኋላ እጥፍጥፍ አደርጋለሁ። ውትድርና እንደሱ ነው። ኮሚሽነሮቻሁን እዚያ ሊቀበሉኝ ሳገኛቸው አንደኛው ኮሚሽነር ወታደር ነበር። ከመሃል አንዱ ሲጠነቀቅ አይቼው ሄጄ አቀፍኩት፡፡ ወደዚህ ደሞ ስመጣ እዚያ ዘንድ አንድ ወጣት ሰላምታ ሰጠኝ፤ እንደወታደር ማለት ነው። ውትድርና እንደሱ ነው። ሰላምታ ስታይ፤ አቋቋም ስታይ፤ አለባበስ ስታይ፤ ሰልፍ ስታይ ነሸጥ ያደርግሃል። ብታረጅም ባታረጅም ባንዲራ ስታይ፤ የኢትዮጵያን ህልውና ስታይ፤ አባት ጦር ተዋግቷል። አባት ጦር ሆነህም አገርህን መጠበቅህ አይቀርም። የአገርን ህልውና አሳልፎ መስጠት ስለማይቻል፤ አይቻልም። ይሄ ደግሞ በኢትዮጵያውያን ደም ውስጥ ያለ ነው።

የፌደራል ፖሊስ፤ የአዲስ አበበባ ፖሊስ፤ የትራፊክ ፖሊስ በአፍሪካ ኅብረት የመሪዎች ስብሰባ ወቅት ያሳያችሁትን ብቃትና ጀግንነት በቅርቡ ለአዲስ አበባ ሕዝብ ሰፊ ትርኢት በማሳየት እንደምትደግሙት ተስፋ አደርጋለሁ። ወታደር ወታደር መሽተት ጀምራችኋል። ጽና፤ ባለህበት ቀጥል፤ ኢትዮጵያ ትበለጽጋለች! የአሁኑ ጉም ያልፋል። ጸጥ ረጭ ያለ፤ የአፍሪካ ፈርጥ የሆነ መንግሥት ኢትዮጵያ ውስጥ ይፈጠራል።

**አመሰግናለሁ!**



# የሀላባ ዞን ንግግር

የካቲት 18/2012 ዓ.ም.

**“አብሰንቴንታ ሰጀጎጂ ከምባቶም፤**
**አብሰንቴንታ ለመላሞሌ ጠምቦሮታ፤**
**አብሰንታታ ሃኒጋሲ ዶንጎ ጦማ፤**
**ጦምባቲ ጦማ፤**
**ጠምባሮ ጦማ ዶንጊ ምንዳቦ፤”**

እጅግ የተወደዳችሁና የተከበራችሁ የከምባታ ጠምባሮ ሰላም ወዳድ፤ ብልጽግና ወዳድ፤ አገር ወዳድ ዜጎች በሙሉ፤ ይገርላችሁ የመጣሁትን የሰላም፣ የብልጽና፣ የመደመር ዜና በፍጥነቱ የማይደረስበት ከልካይ የሌለው ፈጣሪ ቀድሞኝ በዝናብ ትናንት ነግሯችኋል። ትናንት ምሽት ሊነጋጋ አካባቢ ሲዘንብ የተኛችሁ ወጣቶች አሁን በዚህ ስፍራ በምታዩት ዳመና የተፈቀደ ስብሰባ መሆኑን ከላይ ግልጽ ምልክት ይታያል። ከላይ ሲፈቀድ ከታች መስማማት ጥሩ እንደሆነ የከምባታ ጠምባሮ ሕዝብ ስለሚገነዘብ፤ ይህ ጉባኤ፤ ይህ መሰባሰብ፤ ይህ ውይይት በጸሎት የተጠየቀው መንገድ፤ የተጠየቀው ውሃ ተመላሽ መሆኑን ዳመናው ይናገራል።

ከምባታ ጠምባሮ ተባብሮ የሚኖሩ የዳበረ ባህል፣ ወግ ባለቤት የሆኑ ጠንካራ የሥራ ባህል ያላቸው፤ ብዙ ወንዝ የተሻገሩ ምሁራን ያፈሩ ተምሮ ለከምባታ ብቻ ሳይሆን ተምሮ ለኢትዮጵያ፤ ተምሮ ለዓለም የሚበጁ ድንቃ ድንቅ ጭንቅላቶች የወጡበት አከባቢ ነው። የብልጽግና ጉዞአችን የማይቀለበስና የሚከወን መሆኑን የከምባታ ምሁራን በሚያደርጉት ድጋፍ ምሁሯዊ አስተዋጽዖ እያረጋገጡ ስለሆነ እናንተን ይዘን የማንሻገረው የማናልፈው ችግር የለምና በመደመር ጉዞ ብልጽግናችን እውን ይሆናል።

የከምባታ ሕዝብ ጥንታዊ ሥልጣኔ ያለው መሆኑን በደምብ እንገነዘባለን። ከ14ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ የኢትዮጵያን መዛግብት ያገላበጠው ሁሉ ከምባታን በቀላሉ ይገነዘበዋል። ከምባታ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ መልካም ነገር ከሚነገርላቸው ሕዝቦች፤ በበጎ ከሚነሡ ሕዝቦች፤ ከጠምባሮ፤ ከዶንጊ፤ ከምንዳቦ ጋር ተደምሮ ለምለም አገር መፍጠር የቻለ ድንቅ ሕዝብ ነው። “ሞሱኔ ገንሹአ ያሁኔ ያበዳአ አሳኡኔ አኒታ” ይላል። በተለይ በተለይ “አሳኡኔ አኒታ” “ቃላችን እውነት ነው” የሚል አባባል ለብልጽግና በጣም ወሳኝ ነው። ምክንያቱም ብልጽግና በእውነትና በዕውቀት የሚያምን ስለሆነ፤ ብልጽግናም “አሳኡኔ አኔታ” ይላችኋል።

የከምባታ ሕዝብ የሰባት ጎሳዎች ፌደሬሽን ውጤት ነው። ወያታ፣ ጉል፣ ጊኒራ፣ ታዛ፣ ኢሬኛ፣ ዲቤኛና ፎጋ የተባሉ ጎሳዎች አንድ ላይ ለመኖር ወስነው በመደመር ፍልስፍና የፈጠሩት አንድ ድንቅ ሕዝብ ነው። ጠምባሮም ቢሆን ጠንካራ ብቻ ሳይሆን መሬት የሚያስገብር፤ ሞላን ሲል የማይመለስ ጠንካራ ሕዝብ መሆኑን ሁላችሁም ትገነዘባላችሁ። ይህ ጠምባሮ ሰባቱ የሞላ ልጆች ላምሌ ሞት ብለው በሚናገሩት ልክ ከአንድ ሞላ ቤተሰብ ራሱን በመንገድ ሠውቶ፤ ጥንካሬን አውርሶ፤ ከምባታና ጠምባሮን እንዳይለያዩ አድርጎ፤ አንድ ሕዝብ አንድ ወገን ወንድማማች ያደረገ የሰባት ሞላ፤ የሰባት ጎሳዎች ታሪክ ያለው የተደመረ፤ ለኢትዮጵያም መደመርን ያስተማረ አንድ ጠንካራ ሕዝብ ነው።

እንዲያውም በጥንቱ ዘመን ሰው በአገሩ የማይኖርበት ምክንያት ሲገጥመው “ከምባታ ጠምባሮ ሂድ” ነበር አሉ የሚባለው። ብዙ ሰዎች ከገዥዎቻቸው፤ ከመሬት ባላባቶቻቸው፤ ከአራጣ አበዳሪዎቻቸው ጋር መኖር ሲከብዳቸው መኖሪያቸውን ጥለው ከምባታ ጠምባሮ ነበር የሚመጡት። ከምባታ “ማንነህ? ከየት ነህ? ለምን መጣህ?” ሳይል ልጁን ድሮ፤ ከብቱን ሰጥቶ፤ እህሉን መግቦ ያኖራቸዋል። እነሱም “ከምባታ ጠምባሮ” ሆነው ይኖራሉ። ምክንያቱም ከምባታዎች ጠምባሮዎች “ሰው ሰው የሆነው በሌሎች ሰዎች ምክንያት ነው” የሚል ጽኑ እምነት አላቸው። ይህ እምነታቸው ነው ብዙ ኢትዮጵያውያን ወደ ከምባታ እንዲመጡ ያስገደዳቸው። ከምባታዎችም እንዲሁ በመላው ኢትዮጵያ ተሰማርተው እንዲኖሩ ያደረጋቸው። በሰው ላይ ያላቸው ጽኑ እምነት ነው ማንም ወደ ከምባታ ጠምባሮ መጥቶ ባእድነት አይሰማውም። የሌሎች ሰዎች መኖር ለከምባታ ተጨማሪ ባህል፤ ተጨማሪ ዕሴት፤ ተጨማሪ ዕውቀት፤ ተጨማሪ ሀብት ነው።

ይህንንም ቅድም አጋሮ ናፈቀኝ ሲሉ ሰምታችኋል። ለመሆኑ መደመርን ለከምባታ ማስተማር ምጥን ለእናት ማስተማር አይደለምን? የተለያዩ ማኅበረሰቦች ተደምረው የሚኖራቸውን ኃይልና ታላቅነት ለማወቅ የፈለገ ከምባታ መጥቶ ዱራሜን ይመልከት። አብሮ መኖር፤ ተግባብቶ መኖር እንዴት ያለ ውበት እንዳለው መረዳት የፈለገ እዚህ ከምባታን ቢጎበኝ በቂ ምለሽ ያገኛል። በከምባታ ብዙ ሆኖ አንድ፤ አንድ ሆኖ ብዙ መሆን ይቻላል፤ ብሎ ለሚጠይቅ ሁሉ መልስ የሆነ ሕዝብ ነው።

የዚህን አካባቢ በዝርዝር ያጠኑ የአገር ውስጥም ሆነ የውጭ ሊቃውንት በአንድ ነገር ይስማማሉ። የዚህ አካባቢ ሕዝቦች፤ የሕዝቦች መዋሐጃ ስፍራ አንዱ ምልክት መሆናቸውን በከምባታ በጠምባሮ እና በዚህ አካባቢ ሌሎችም ሕዝቦች የሚባል አንድ ነገር አለ። “አንድ ሰው ነበር አሉ አያቱ ኦንጎታ፤ ሚስቱ ደግሞ ከገባራ፤ ልጁ ዶዳ ኢኒማና አግብቶ አራት ልጆች ወለደ። አራቱ ልጆች ጁማ፤ ወሬዛ፤ ቡልቡላ፤ ቦሮዳማራ አግብተው ከምባታ ማለት ይሄ ነው አሉ።” ከምባታ ማለት ከኦሮሞ የሚጋባ፤ ከአማራ የሚጋባ፤ ከሌሎች ከጋሞ፤ ከወላይታ፤ ከአዘርነት በርበሬ ከአልጠቀስኳቸው ሕዝቦች ጋር በሰላም ተዋሕዶ መኖር የሚችል የመደመር ሁነኛ ምሳሌ ነው። ለዚህም ነው ብዙዎች “ከምባታ ጠምባሮን ትንሿ ኢትዮጵያ” የሚሏት፤ ፍላጎታችን ኢትዮጵያ እንደከምባታ እንድትሆን ነው። በኢትዮጵያ ውስጥ ሁሉም ቤተኛ የሚሆንበት፤ ሁሉም በአንድነት የሚኖርበት ሁሉም የየራሱን ማንነት ይዞ ግን ሌላ ደግሞ የጋራ ማንነት የሚገነባበት፤ ማንም መጥቶ የሚጠጋበት፤ ለሁሉም መብት መከበር ሁሉም ፈቅዶ የሚሠራበት ከአንድነት ትልቅነት እንደሚፈጠር የሚያምን ሕዝብ እንዲሆን ነው። ለዚህ ሕዝብ ማኅበረሰብ ትልቅ ቦታ አለው። “የየራስህ ጠባይ ሊኖርህ ይችላል። የየራስህ እምነት ሊኖርህ ይችላል። የየራስህ ቋንቋ ሊኖርህ ይችላል። የየራስህ ቤትም ሊኖርህ ይችላል። ነገር ግን አንተ የምትኖረው ሕዝቡ ሲኖር ነው” ይላል። ለዚህም “ማኅበረሰብ ሲሞት ግለሰብ ይሞታል” ይላሉ። ከምባታዎች አንተ የምታደርገው እያንዳንዱ እንቅስቃሴ ለሕዝቡ ተጨማሪ ሀብት፤ ተጨማሪ ክብር፤ ተጨማሪ ዕሴት፤ ተጨማሪ ፀጋ የሚያስገኝ እንጂ ሕዝቡን የሚያፈልስ መሆን የለበትም።

“አንተ የምትኖረው ትልቁ ሕዝብ ሲኖር ነው፤ ማኅበረሰቡ ሲጠነክር ነው አንተ የምትጠነክረው፤” ይላሉ። የከምባታ ጠምባሮ ሽማግሌዎች ሲመክሩ “ኢትዮጵያ ከሌለች ከምባታ የለም። ኢትዮጵያ ከሌለች ጠምባሮ የለም። ኢትዮጵያ ከሌለች ደቡብ የለም።” ይላሉ። ኢትዮጵያ ከአለች ሁሉም የሚከበርባት፤ ከፍ ብሎ የሚታይበት፤ ለሁላችን የምትበቃ ድንቅ አገር ያለን ሲሆን፤ ያለን የተሰጠን ካልገባንና ያን መጠበቅ ካልቻልን ግን በተናጥል መኖር አስቸጋሪ ነው።

ከምባታዎች በዚህ መርሕ ጠንካራ ማኅበረሰብ ብቻ ሳይሆን ከ500 ዓመታት በላይ የዘለቀ ጠንካራ መንግሥትም ነበራቸው። የኮያታ ስርዎ መንግሥት ከዓሥራ ሰባት በላይ ነገሥታት ተፈራርቀውበታል። ኢትዮጵያ ጠንካራ አገር

እንድትሆን ተግተው ሠርተዋል።

መመሪያቸውም “መኒጋሪታ ባይሶት” አሁን ጀምሬው የነበረው ሐሳብ፤ መኒጋሪታ ባይሶት ማለት “የአንተ መብት እንዲከበር የሌላውን አክብር፤ እንድትወደድ ውደድ፤ እንድትመሰገን ሥራ፤ እንድትጠየቅ ጠይቅ፤ እንድትመረጥ ምረጥ” ማለት ነው። በዚህ አካባቢ ያሉ ሕዝቦች ሰላም ሳይሆኑ አንተ ብቻህን ሰላም አትሆንም። በአካባቢህ ያሉ ሕዝቦች ተገፊ አንተ ገፊ ሆነህ መኖር አትችልም። በአካባቢህ ያሉ ወገኖች ተሸናፊ አንተ ብቻህን አሸናፊ ሆነህ ልትቀጥል አትችልም። የምናሸንፈው በጋራ፤ የምንገፋው ድህነትን በጋራ፤ የምንነናጸፈውም ብልጽግና በጋራ ብቻ ይሆናል። ዛሬ ያጋጠሙንን ፈተናዎች በዚህ ዕሴት ነው ማየት የሚኖርብን፤ በተለይ በሁለቱ ዕሴቶች “ማኅበረሰብ ሲሞት ግለሰብ ይሞታል።” በሚለውና “የአንተ መብት እንዲከበር የሌላውን አክብር” በሚለው በከምባታ ጠምባሮ የደረጀ እሳቤ ውስጥ ታላቅ አገር መመሥረት ጥቅሙ ለሁላችን እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል። ታላቅ አገር ሳትኖር ታላቅ ሕዝብ አይኖርምና፤ ግለሰብ ማኅበረሰብን አያፍርስ እንደተባለው ሁሉ ማኅበረሰብም አገርን ማፍረስ የለበትም። ለግለሰብ ማኅበረሰብ ለማኅበረሰቦች ደግሞ አገር ታስፈልጋለች። ከምባታዎች “ማኅበረሰብ ሲሞት ግለሰብ ይሞታል” እንዳሉት ብልጽግና ደግሞ “አገር ስትሞት ማኅበረሰቦች ይሞታሉ፤ አገር ስትሞት ብሔሮች ይረሳሉ፤ እንዳንሞትና እንዳንጠፋ ኢትዮጵያን መጠበቅና ማበልጸግ ከሁላችን የሚጠበቅ ቀዳሚ ተግባር ሊሆን ይገባል።

በእርግጥ ኢትዮጵያን ስለመጠበቅ ለከምባታ ጠምባሮ መናገር የማይገባ ቢሆንም ለማስታወስ ያህል የከምባታ የጠምባሮ አርበኞች ጀግኖች አድዋ ድረስ ዘምተዋል። ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ወንድሞቻቸውና እኅቶቻቸው ጋር ለአገራችን ነፃነት መሥዋዕትነት ከፍለዋል። “ጠላት እኛ ድረስ ካልመጣ...” አላሉም። ሰሜኑን የነካ እኛን የነካ፤ ደቡቡን የነካ እኛን የነካ፤ ምሥራቁን የነካ እኛን የነካ፤ ምዕራቡን የነካ እኛን የነካ ብለው ነው የዘመቱት፤ ማይጨው ዘምተዋል። ካራማራ ዘምተዋል። መዝመት ብቻ አይደለም፤ ጣልያን ገፍቶ ሲመጣ ከጊቤ በረሓ የከምባታን ጀግንነት ዛሬ ድረስ ይናገራል።

አባቶቻችሁ ኢትዮጵያን ሰሜን ድረስ፣ ምሥራቅ ድረስ፣ በጊቤ በረሓም ለዓመታት ታግለው በደማቸው ያስከበሯትን ይህችን ድንቅ አገር ማስቀጠልና ወደሚገባት ከፍታ ለማውጣት የእኔና የእናንተ ቀዳሚ ተግባር ይሆናል። ከምባታ የወላጆቹን አደራ የሚበላ ስለአልሆነ የዛሬው ትውልድ ሰሜን መዝመት፤ ጊቤ በረሓ መግባት አይጠበቅበት ይሆናል። ተደምሮ በፍቅር በይቅርታ ወደ ብልጽግና ኢትዮጵያን የማውጣት ተግባር ግን ከሁላችን የሚጠበቅ መሆኑን አበክሬ ላሳስባችሁ እፈልጋለሁ። አንድን ችግር ዛሬ ዝም ብለን ለራሳችን ስንል ብንገፋው ነገ ተመልሶ ችግሩ ራሱ እኛን ይገፋናል። በከምባታ አንድ አባባል አለ። “በቁልቁለት ያባረርከው መልሶ በዳገት ያባርርሃል።” ዛሬ አንተ ዐቅም አግኝተህ፣ ጉልበት አግኝተህ፣ ጊዜ አግኝተህ፣ አንድን ጉዳይ አንድን ሰው ከገፋኸው፤ ጉዳዩ በከፋ መንገድ ይመጣብሀል ማለት ነው። ጉልበተኛ መሆን፤ ባለጊዜ መሆን አያስፈልግም። የሚያስፈልገው ሰው መሆን ነው። ሰው ከሆንክ መስጠትን፣ መሥራትን፣ ማፍቀርን፣ ይቅርታን፣ ፈጣሪን መፍራትን፣ ስለምታውቅ፤ በቂውና አስፈላጊው ሰው መሆን እንጂ ባለጊዜ መሆን አይደለም። ባለጊዜ መሆን አላፊ ጠፊ፤ እንደማታው ዝናብ ታይቶ የሚረሳ ስለሆነ፤ ወጣቶቻችን ለምንድን ነው አገራቸውን ትተው የሚሰደዱት?

በደቡብ አፍሪካ በነበረኝ ቆይታ ከአገኘኋቸው በርካታ ወጣቶች መካከል የከምባታ ጠምባሮ ወጣቶች ይገኙበታል። ከምባታዎች ስኬታማ ሥራ በመሥራት ትላልቅ ሀብት ያፈሩ ልጆችም ስለአሏችሁ እንኳን ደስ አላችሁ! ልላችሁ እፈልጋለሁ። ነገር ግን በደቡብ አፍሪካ ሀብት ያፈሩ የከምባታ ልጆች ጥያቄያቸው የከምባታ ጠምባሮ የትምህርት፣ የጤና፣ የመሠረተ ልማት፣ የሥራ

ዕድል ጥያቄ ነው።

ሰው አካሉ ቢሄድ መንፈሱ እዚሁ ነው። ሃብት ቢያገኝ የወገኑ ችግር ይገደዋል። በአዲስ አበባ በበርካታ ቦታ ትላልቅ ምሁራን ያሉት የዚህ ዞን ሕዝብ እነዚያ ፕሮፌሰሮች፤ የምታውቋቸው ምሁራን ሲያገኙኝ ጥያቄያቸው የግላቸው ጉዳይ ሳይሆን የከምባታ ጠምባሮ የልማት የብልጽግና ጉዳይ ነው። ይህ የሚያሳየው የትም ብንሄድ ተባብረን ሠርተን የሕዝባችንን የኑሮ ደረጃ መለወጥ ካልቻልን፤ በግል በሚገኝ ሃብት. ትምህርት እና የኑሮ ምቹነት የተሟላ እርካታ እንደማይገኝ በደቡብ አፍሪካ፤ አዲስ አበባ ካሉ ምሁራንም ትምህርት መቅሰም ችያለሁ። ልባችሁ የሸፈተ ወጣቶች ካከአችሁ ሃብት ታገኙ ይሆናል። ዕውቀት ታገኙ ይሆናል። ከምባታ ጠምባሮን መቀየር እስከአልቻልን ግን የሰላም እንቅልፍ እንደማይኖራችሁ ከወዲሁ ልገልጽላችሁ እፈልጋለሁ። ለዚህ ነው ተባብረን ለሁላችን የምትሆን ኢትዮጵያን እንፍጠር የምንለው፤ በድሃ አገር ውስጥ የሚኖረው ድሃ ክልል፣ ድሃ ዞን፣ ድሃ ወረዳ ነው። ሃብታም አገር፣ ጠንካራ አገር ካለን ፍላጎታችንንም በዐቅማችን ልክ እናሳካለን።

ወቅቱ የሚፈጥራቸውን ሙቀቶች የከምባታ ሕዝብ አይከተልም አምናለሁ። ከምባታ እኮ ኢትዮጵያ ስትሠራ አምድ ያዋቀረ ሕዝብ ነው! ከምባታ እኮ ኢትዮጵያ ስትገነባ ዋልታውን ያቆመ ሕዝብ ነው! ከምባታ እኮ ምሶሶ ሲተከል “ቆመህ አትመልከት” የሚል ጠንካራ ብሔር ያለው ሕዝብ ነው! አገር እንዴት እንደሚገነባ የራሱን መብት ሲያስከብር የሌሎችን መብት እንዴት መጠበቅ እንደሚቻል የሚያስተምር ሕዝብ እንጂ፤ ከሌሎች ትምህርት የሚሻ ሕዝብ እንዳልሆነ እኔም እናንተም በጽኑ የምናምነው ነው። የከምባታ ጠምባሮ ባህል በመላ ኢትዮጵያ ተስፋፍቶ ስለድምበር፣ ስለቤት አሠራር፣ ስለአቀበት ስለሥራና እውነት ያላችሁን ጥልቅ ብሂል ለመላ ኢትዮጵያ እንድታካፍሉ፤ የዘነጋችሁም ካላችሁ ለማስታወስ “ገበና ዘኒኒ ሚኒ ለሚኒ ቦርቹ ቦሊኒ ጎሮ ኡቼኔ” ይላል ከምባታ፤ “ጎሩ ወቺኒ” ያለው፤ በባለ ጊዜነት ብልጽግና አይመጣም፤ ረሃብ የሚጠፋው፣ ድህነት የሚጠፋው በሥራ ብቻ ነው ብሎ ስለሚያምን ነው።

አሁን መንገዱ ተጀምሯል። መደመር ለኢትዮጵያ ፖለቲካ አዲስ መንገድ ነው። ብልጽግና ደግሞ አዲስ መዳረሻችን፤ የሚያጋጥሙንን ፈተናዎች አዳዲሶች ናቸው። ነገር ግን፤ ቦምቦች ቢወረወሩ፣ መሣሪያዎች ቢተኮሱ፣ የጦርነት ነጋሪዎች በየስታዲየሙና በየፌስቡኩ ቢታወጁ፣ ነጋሪቶች ቢጎሰሙም፣ ከግራ ከቀኝ ጫና ቢመጣ፣ መንገዳችን መደመር ብቻ ነው። ግባችንም ብልጽግና ነው።

እኛኮ የእነ ዶ/ር ቦጋለች ገብሬ ልጆች ነን። እንኳን ፈተና ዓለምን ታግለው ያሸነፉት፤ እኛኮ የተራሮቹ ልጆች ነን። የማይነቃነቁት፤ የጸኑት፤ የማይረሱት፤ የሕይወት ትርጉም ለሌሎች ሲኖር መሆኑን የማያምኑትና የኖሩት አባቶች ልጆች ነን። የማንፈራ፤ የማንታጠፍ፤ የምንወድድ እና ይቅር የምንል። በጉዞአችን ከመደመር ውጪ አንዱ ባለጊዜ፤ ሌላው የበይ ተመልካች የሚሆንበት ዘመን ድጋሚ በኢትዮጵያ እንዳያጋጥም ሁሉም አትዮጵያዊ ተዋድዶ፤ ተከባብሮ፣ ይቅር ተባብሎ፤ ለምድርም ለሰማይም ተመችቶ፤ በብልጽግና ማማ ላይ የምትቆም አገር ብቻ መገንባት የምንሻ የአምበርቾ ከምባቱ፤ የነጌሌ ጠምብሩታ፤ የጦሮቦሪ ዶንጉ የእነዚህ ልጆች ነን። አንታጠፍም! ይህ እንደማይሆን የአምበሪቾን፤ የነገሬን፤ የጦራቦሪን ያየ ሰው፤ እያየም ያደገ ሰው፤ እነዚህ ተራሮች ታሪክ እየመሰከሩ እንድትኖሩ እና ኢትዮጵያን ወደ ብልጽግና ማማ እንድታወጡ ነው።

ከእናንተ የሚጠበቀው ፍቅር፣ ሰላም፣ ይቅርታ፣ ተግቶ መሥራት፣ ሌብነትን መጠየፍ ነው። እኔ ብቻ ጀግና፤ እኔ ብቻ ዐዋቂ፤ እኔ ብቻ ባለጊዜ፤ እኔ ብቻ ሁሉን ማድረግ የምችል፤ ሌላው ሞኝ ያልገባው ፤የሚል አጓጉል እምነት ትተን፤ ተዋድደን ተከባብረን ሰው ሁሉ ዐዋቂ፤ ሰው ሁሉ አስፈላጊ፤ ኢትዮጵያዊ ሁሉ

ዕንቁ መሆኑን አምነን፤ አምበርቾ ደገሌና ቶራባይ ተራሮች ኢትዮጵያውያን ሁሉ እንደምልክት የሚኮሩበት፤ መጥተው የሚጎበኙት፤ ከዚህም ሕዝብ የሚማሩበት እንዲሆን፤ በሄድንበት ሁሉ ለምለም፤ በሄድንበት ሁሉ ፍቅር፤ በሄድንበት ሁሉ ወግ ያስተማረን፤ ኢትዮጵያዉያንን በሙሉ በንጹሕ ልብና በቅንነት ለማገልገል ያለንን ፍላጎትና ዝግጁነት እኛ ባንነግራችሁ፤ ከእኛ ባታምኑ የለሊቱ ዝናብ ይነግራችኋል።

**ፈይመት ግኒየ ጡሞ ጦጴ ይሁን**
**መገን ማሳጉየ ገለታን ኢንኬይ!**

**እጅግ አድርጌ አመሰግናችኋለሁ!**

**ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር!**
**ፈጣሪ ኢትዮጵያንና ሕዝቦቿን አብዝቶ ይባርክ!**
**ዝናብ፤ ሰላም፤ ፍቅር፤ ይቅርታ አይወሰድባችሁ!**
**አመሰግናለሁ!**





# የተባበሩት ዐረብ ኢሚሬትስ ንግግር

የካቲት 20/2012 ዓ.ም.

አመሰግናለሁ! ስትደመሩ የምታስፈሩ፤ በጋራ ድምፃችሁ ሲወጣ የአገር ኩራት የሆናችሁ፤ የኢትዮጵያዊነትን ልክ እና ደርዝ ማሳየት የቻላችሁ፤ ኪሳችሁ ሳይሆን ልባችሁ ጠንካራ የሆነ በመካከለኛው ምሥራቅ የምትገኙ ውድ የአገሬ ልጆች! ለፍታችሁ፣ ጥራችሁ፣ ግራችሁ ሕይወታችሁን፣ ኑሯችሁን ከማሸነፍ በተጨማሪ፤ ለኢትዮጵያ ወገኖቻችሁ አርአያ የሆናችሁ በዚህ ቀጠና የምትገኙ የአገሬ ልጆች ዛሬ በዚህ መልክ የዐረቡ ዓለም ድምፃችሁን፣ አንድነታችሁን፣ ክብራችሁን፤ ማንነታችሁን እንዲያይ ስለአደረጋችሁ ላቅ ያለ ምስጋና ላቀርብላችሁ እፈልጋለሁ።

በብዙ አገራት በርካታ ወዳጆች ቢኖሩንም የተባበሩት ዐረብ ኢመሬት ፕሬዚዳንት እጅግ የተከበሩ ሼክ መሐመድ ቢን ዛይድ ለኢትዮጵያ ለአላቸው ፍቅርና ክብር ላለፉት 15 ዓመታት ስንጠይቅ የነበረውን የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ማስገንቢያ ስፍራ ስለፈቀዱልን፤ በዚህ አገር የሚኖሩ የመኖሪያ ፍቃድ ያላገኙ ኢትዮጵያውያን የሚያገኙበት ሁኔታ እንዲመቻች ስለፈቀዱ፤ እዚህ ያሉ ብቻ ሳይሆን ተጨማሪ በብዙ ሺሕ የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ወደ ሁለተኛ አገራቸው መጥተው መሥራት እንዲችሉ ስለፈቀዱልን በጋራ እንድናመሰግናቸው፤ ለእኚህ ታላቅ ሰው ኢትዮጵያ በጊዜ መካከል ምስጋናዋ

ሳይቋረጥ የምትከፍል መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ እኔም በእናንተ ፊት ጤና፣ ዕድሜ፣ ሰላምና ብልጽግና እመኝላቸዋለሁ!

“ከበጃ ናኬኑፍ በከ ከነቲ አርገሙዳን ጃለለ ኬሰን፤ ቶኩማ ኬሰን፤ አገርሲሱፍ ቢፋአዳን በከ ከነት ነሞት አርገምተን ኡንዳ ጃለላፍ ከበጆሙን ሲኢብሳ በኪ ኩን ነሞን ባዬ ከኒቲ አርገሙን ዋንተኤፍ አፋን ኡንዲኬኛ ደገኡ ደንዴኙን አካ አሳ ጎጎቹ ደደኡፍ ነኦፎ ኮልቻ ኢሲኢን ከበጃ፤ ኢሲኢን ጃለዳ በገ ዱፍተን፤ በገ ወላገሬ ጆቹን በርባዳ!”

ክብራትና ክቡራን! በተለያዩ የመካከለኛ ምሥራቅ አገራት፤ በተለይም የንግድና የድርጅቶች መናኸሪያ በሆነችው በዱባይ ከተማ በዚህ በአማረ ስፍራ ተገናኝተን ኢትዮጵያዊነትን፣ አንድነትን፣ መደመርን፣ ብልጽግናን ከፍ እንድናደርግ ለአደረጋችሁ ወገኖቼ ሁሉ ያለኝን ላቅ ያለ ምስጋና ልገልጽላችሁ እፈልጋለሁ።

ከምትወዷት እና ከምትወዳችሁ አገራችሁ የከበረ ሰላምታ እና ፍቅር ይዤላችሁ የመጣሁ ስለሆነ እንደምን ከረማችሁ ልላችሁ እፈልጋለሁ።

ኢትዮጵያውያን ዛሬ በዚህ ስፍራ በዚህ መልክ ተገናኝተን ደስታችንን ስንካፈል ባለፈው ዓመት በአሜሪካ እና በአውሮፓ ከሚኖሩ አያሌ ኢትዮጵያውያን ጋር የመገናኘትና የመወያየት ዕድሉ ነበረኝ። ከጥቂት ሳምንታት በፊትም በደቡብ አፍሪካ ከሚኖሩ በብዙ ሺሕ ከሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ወንድሞችና እኅቶቻችን ጋር ተገናኝተን ልብ ለልብ ተመካክረን ተጨዋውተን የብልጽግና ጎዳናችንን በጋራ ለመቀየስ ከስምምነት ደርሰናል። ዛሬ ደግሞ ፈጣሪ ፈቅዶ እጅግ ብዙ ኢትዮጵያውያን እኅቶቻችንና ወንድሞቻችን የምትገኙበት መካከለኛው ምሥራቅ ተገኝተን ስለአገራችን፣ ስለእናንተ፣ ስለቀጠናችን፣ ስለሰላም፣ ስለብልጽግና፣ ስለፍቅር፣ ስለአንድነት ስለይቅርታ መነጋገር በመቻላችን ልባዊ

ደስታና ክብር የተሰማኝ መሆኑን ልገልጽላችሁ እፈልጋለሁ። በሌሎች አገራት እንደሚኖሩ ወገኖቻችሁ ሁሉ በዚህ የምትኖሩ ኢትዮጵያውያን እና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ወደእዚህ የመጣችሁት በሥራና ድካም ኑሮአችሁን ለማሸነፍ፣ ቀን ከሌት ታግላችሁ ድህነትን ለማምለጥ እና ፈተናዎችን ወደ ድል ለመቀየር ነው። ብዙዎቻችሁ የተገኘውን ሥራ ሠርታችሁ፤ ከራሳችሁ አልፋችሁ ለሌሎች ለመትረፍና ለማካፈል በማሰብ በዚህ ስፍራ ቀን ከሌት የምትተጉ መሆናችሁን ኢትዮጵያውያን በኩራት ይመለከቱታል። ጆሮ ሰጥቶ የሚያዳምጣችሁ ቢገኝ እያንዳንዳችሁ ከሕይወታችሁ ተጽፎ ያልተነበበ አስገራሚ ልምድና ደርዝ ያለው ፍቅር በመጽሐፍ መልክ ሊወጣ የሚችል ልምድና የሕይወት ጉዞ እንዳላችሁ መገመት ይቻላል። አኗኗራችሁ እና ለአገር የምታበረክቱት አስተዋጽዖ በልዩነት ሊነገር የሚገባው እና ትምህርት ሊቀሰምበት የሚገባው እንደሆነም በጽኑ እናምናለን።

እንደሚባለውም ደግነት ሁሉም ሰው የሚሰማው ቋንቋ የሚናገሩት ግን ጥቂቶች ናቸው። በተለይ ደግሞ እኅቶቻችን በሰው አገር በስደት ለፍታችሁ ያፈራችኋትን ገንዘብ ቤተሰቦቻችሁ እንዳይቸገሩ፣ እንዳይራቡ፣ መማር እንዲችሉ በማድረግ የምትጫወቱት ሚና እጅግ የሚያኮራ በመሆኑ እንኳን ደስ አላች ልላችሁ እወዳለሁ። በእናንተ ጥሪት፣ በእናንተ ርዳታ የሚማሩ እና ለወግ ለቁም ነገር የበቁ ኢትዮጵያውያን ነገ አገራችን ስትበለጽግ በብዙ መምራት ማሻገር የሚችል ሐሳብ በመፍጠር ኢትዮጵያን ከሚገባት ማማ ላይ ሊያውሏት እንደሚችሉ በማመን ጭምር ከወዲሁ የምታደርጉት ኢንቨስትመንት ፍሬያማ መሆኑን እንድታስቡ እና እንድትኮሩ አሳስባችኋለሁ። ይህ የችግር ዘመን አልፎ አገራችን በብልጽግና ማማ ላይ ወጥታ ከልጆችዋ ተርፋ የሌሎች መጠለያ የምትሆንበት ጊዜው ሩቅ አይደለም። ያኔ በዚህ አንፀባራቂ መልካም ሥራችሁ ሁሌም ስናመሰግናችሁና ስናስታውሳችሁ እንኖራለን። እስከዚያው ግን በዚህ በመካከለኛው ምሥራቅ የምትኖሩ ዜጎቻችን ክብራችሁ ተጠብቆ እንድትሠሩ ለማድረግ መንግሥት ከየአገራቱ ጋር የሁለትዮሽ ስምምነቶች

አድርጓል። የሚደርስባችሁ ሥቃይና እንግልታችሁ እንዲቀልል ወደፊትም ተከታታይ ሥራዎችን ማከናወናችንን እንደምንቀጥል በዚህ አጋጣሚ አረጋግጥላችኋለሁ። እናንተ ቤተሰብ ለመርዳት እና አገር ለመለወጥ ስትዋትቱ የሚደርስባችሁ ሕመም እኛንም ያመናል። የውስጥ ቁስላችሁ እኛንም ነጋ ጠባ ይቆጠቁጠናል። ምክንያቱም እያንዳንዳቹ ለእኛ ውድ ዜጎቻችን ከመሆናችሁ በላይ ልጆቻችን፣ እኅትና ወንድሞቻቻን ናችሁና፤ እናንተ ክብር ስታገኙ አገራችን ትከበራለች። እኛም ወገኖቻችሁ ዕረፍትና ኩራት ይሰማናል። በእናንተ ለቅሶ አገር እንደሚያለቅሰው ሁሉ በእናንተ ሳቅና ስኬት ወገን ሁሉ እፎይ ይላል። ይደሰታል።

ውድ ወገኖቼ! ሁላችሁም እንደምትገነዘቡት እኛ ኢትዮጵያውያን ከሌላው የዓለም ክፍል በተለየ ከመካከለኛው ምሥራቅ አገራት ጋር በብዙ የምንተሳሰር፤ ብዙ ሺሕ ዘመናትን ያስቆጠረ ዝምድናና ትስስር ያለን፤ በታሪክ፤ በእምነት፤ በባህል እና በቋንቋ እንዲሁም፤ በንግድ እና በሥጋ ከጥንታውያን ሥልጣኔዎች ጀምሮ የነበረን ትስስር እስከ አሁንም ዘመን ተሻግሮ እንደቀጠለ ነው። ቀደምቶቹ የአገራችን አንጋፋ እምነቶች ክርስትናና እስልምና ምንጫቸው እዚሁ መካከለኛ ምሥራቅ ነው። በእስልምና ታሪክ ውስጥ ጉልህ ድርሻ ከሚሰጣቸው ቦታዎች መካከል አገራችን ኢትዮጵያ በግምባር ቀደምትነት ተጠቃሽ ነች። ለምሳሌ ነብዩ መሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) በፍትሕ ዐዋቂነታቸው፤ በመልካም የመንግሥት አስተዳደር ሥርዓታቸው ምክንያት ኢትዮጵያውያንን አምነው ልጆቻቸውን፣ የቅርብ ዘመዶቻቸውንና ሳቦቻቸውን ጨምረው ወደእኛ ሰድደዋል። ኢትዮጵያውያን በመካከለኛው ምሥራቅ ታሪክ ውሰጥ በእምነት አስተማሪነት፣ በአገር መሪነት፣ በሥነ ጥበብ ዐዋቂነት በንግድ ታላላቅ ቦታዎችን ይዘው መኖራቸው ይታወቃል። የባበል መንደብ ሰርጥ የመገናኛችን ድልድይ ሆኖ ለዘመናት ኖሯል።

መሬቶቻችን ሲቆፈሩ የእኛ ቅርሶች በመካከለኛው ምሥራቅ፤ የመካከለኛው ምሥራቅ ቅርሶች በእኛ ከርሰ ምድር ውስጥ ይገኛሉ። የመካከለኛው ምሥራቅ አገራት እንደዛሬው በሀብት ሳይደረጁ በፊት ሥራ ፍለጋ እና ኑሮን ለማሸነፍ ከሚሰደዱባቸው አገራት አንዷ ኢትዮጵያ ነበረች። ዛሬም ቢሆን በሶሪያ እና በየመን ባለው አሰቃቂ ጦርነት ችግር ምክንያት የእነዚያ አገራት ዜጎች ሲበተኑ አገራችን ኢትዮጵያ እጆቿን ዘርግታ እየተቀበለቻቸው ነው። ከዚህም በተጨማሪ፤ ከሶማሊያ፣ ከደቡብ ሱዳን እና ከሌሎች አገሮች በተለያየ ምክንያት የተፈናቀሉ ጎረቤት ወገኖቻችን አስጠለል እንረዳለን። እናግዛለን። ይህ ሁሉ የሚያሳየን ምንም እንኳን ለጊዜው ሚዛን ደፍቶ ተሰዳጅ እና ችግረኞች እኛ ብንመስል ታሪክም ሆነ መጪው ዘመን የሚያስረዳን አገራችን ተቀባይ ብቻ ሳትሆን ሰጪም፤ ተሰዳጅ ብቻ ሳትሆን ስደተኞች ተቀብላ የምታስተናግድ የደግ ሕዝቦች ምድር መሆኑዋን ነው።

ስለዚህም ይህ ጊዜ አላፊ መሆኑን በመረዳት ከአንገታችሁ ቀና ብላችሁ ሂዱ። ዛሬም በኢትዮጵያዊነታችሁ ኩሩ። እመኑኝ ነገ እናንተም በቤታችሁ እና በቢዝነስ ድርጅቶቻችሁ ሌሎችን ቀጥራችሁ የምታሠሩ ትሆናላችሁ። ይህ እውን እንዲሆን ዛሬ ጠንክራችሁ በመሥራትና ጠቃሚ ዕውቀት በመሰብሰብ ታሪክ ለመቀየር ወገባችሁን ታጥቃችሁ ተነሡ። ውድ የኢትዮጵያ ልጆች አንድ ቁልፍ እውነት ልንገራችሁ፤ በዚህ ዘመን የአገራት ኃያልነት መወዳደሪያው እንደጥንቱ ዘመን በወታደር ብዛትና በጦር መሣሪያ ጋጋታ አይደለም። የመንግሥታት ገናናነት ማሳያ፤ የአገራት ተሰሚነት ማረጋገጫ፤ የዜጎች ኑሮ ምቾትና የሕይወታቸው ጥራት ማሻሻያ፤ ዋነኛው መለኪያ ብልጽግና ነው።

የቁስና የፖለቲካ ብቻ ሳይሆን የሞራል፣ የአስተሳሰብና ማኅበራዊ ብልጽግና፤ ዛሬ ጭንቅላታቸውን ተጠቅመው የሐሳብ የበላይነት የተቆናጠጡ ሕዝቦች የተፈጥሮ ሀብት ባይኖራቸውም ኃያል ከመሆን የሚያግዳቸው ነገር አለመኖሩን

በብዙ የአእምሮ ብልጹግ አገራት ውስጥ ማየትና መማር ችለናል። ዱባይም የዚህ አንዱ ማሳያ መሆን ትችላለች። እነዚህ አገራት በለጸጉ የሚያስብላቸው የመፍትሔ ክምችታቸውን ማሳደግ በመቻላቸው ነው። ይህንን ክምችት ለማብዛት ቁልፉ ነገር ዕውቀትና ተመጣጣኝ የሞራል ልዕልና ነው። ሰዎች የሚፈትኗቸውን ችግሮች በማለፍ በእጃቸው ላይ ያለውንን ዕድል ተጠቅመው የሚፈጥሯቸው መፍትሔዎች ተጠራቅመው ባለጸጋ ያደርጓቸዋል። ለአለፉት ብዙ ዓመታት በዘህ ምድር ስትኖሩ በጋራ፣ በኅብረት በዚህ መልክ ድምፃችሁን ማሰማት ያልቻላችሁ ቢሆንም፤ ዛሬ ባለን ግንኙነት በመላው የዐረብ ዓለም ኢትዮጵያውያን መልካችሁ፣ አንድነታችሁ፣ ድምፃችሁ ሲያስተጋባ ከዛሬ ማታ ጀምሮ የምታዩት እውነት ይሆናል። በመላው ዓለም የሚገኙ ትላልቅ የሚዲያ አውታሮች የእናንተን ኅብረትና አንድነት ለመዘገብ በዚህ ስፍራ ያሉ ሲሆን፤ እንኳን ለእነርሱ ለእኔም የሚያስደምመኝ ውበታችሁ እና መልካችሁ በመላው መካከለኛው ምሥራቅ አገራት ኢትዮጵያውያን ድንቅ፤ ውብ የምንሻገር እና የምናሻግር፤ የምናቅፍና የምናግዝ መሆናችን የማሳያ ምልክት ሆኖ ለዘመናት በታሪክ ውስጥ የሚገለጽ ይሆናል።

አሁን ያለንበትን ለመፍታት የሚያስችሉንን የመፍትሔ ክምችቶች ለመፍጠር ለመተባበር በግለሰቦች ጥረት ብቻ እውን መሆን የሚችሉ ባለመሆኑ መደመር ለእኛ ቁልፍ የመሻገሪያ ምስጢር ነው። አንድ ሰው ብቻውን ምን ቢለፋ አገርን ሊያበለጽግ አይችልም። አገር የምትበለጽገው ሁሉም ዜጎች ተደምረው ከችግር ተንታኝነት ወደ መፍትሔ አመንጪነት በሚያደርጉት ሽግግር ነው። አገር የምትገነባው ሁሉም የየራሱን ጡብ እያስቀመጠ ሲሄድ ነው። እንደ ሕዝብ መበልጸግ የሚቻለው እንደ ሕዝብ አስበን የግላችንን ሐላፊነት መወጣት ስንችል ነው።



ዛሬ ከመቼውም ጊዜ ይልቅ ኢትዮጵያ ዜጎችዋን የምትፈልግበት ወቅት ላይ እንገኛለን። ተጋግዘው እና ጠንክረው የሚሠሩ ልጆችዋ የድህነት ከልዋን ከላይዋ ላይ ገፍፈው የክብር ካባ እንዲያጎናጽፏት ትሻለች። አገርንና ሕዝብን ወደ ብልጽግና ከፍታ ማማ የማውጣት በኢኮኖሚ እና በፖለቲካ ወደ ተሻለ ምዕራፍ በፍጥነት የማሸጋገር ሐላፊነት የሚሆነው የማንም ሳይሆን የዚህ ትውልድ ብቻ ነው። ማንም ጎታች፤ ማንም ተጎታች ሳይሆን ሁሉም የዚህ ዘመን ኢትዮጵያዊ እኩል ሐላፊነት አለበት። ሁሉም አገሬ ብሎ ተነሥቶ ያለውን አንጠፍጥፎ ለአገሩ ከሰጠ፤ ነገ አገራችን ዛሬ ለእኛ ህልም የሆነብንና አሠሪዎቻችሁ ከሚኖሩት ኑሮ በእጥፍ የተሻለ የተትረፈረፈ ኑሮ ለልጆቻችን መስጠት ትችላላችሁ። ይሄ አገር በትጋት፣ በብቃትና በቆራጥነት አመራር መበልጸግ መለወጥ እንደቻለ ሁሉ፤ የእኛም አገር ለውጥ የሚረጋገጠው በተደመረ ክንድና በብልጽግና እሳቤ መሆኑን ለእናንተ መንገር አያሻኝም። ትጋት የተረጋገጠ የስኬት ምንጭ ብቻ ሳይሆን በራሱም የከበረ ሀብት ነው።

የተጉ የለፉ ጥሪት ብቻ ሳይሆን የየዕለት ኩራት እንዳላቸው ከእናንተ ሕይወት መማር ይቻላል። ራእይ እንደንጋት ጮራ ወገግታ የሚፈጥር የተስፋ ብርሃን ምንጭ ነው። ኅብረትና አንድነት በግል ያቃቱንን ፈተናዎች በጋራ የምናልፍበት፤ አንዱ በሌላው ተደግፎ በደረጃ ከፍ ካለው የብልጽግና ማማ ላይ የምንወጣበት ብቸኛ መሰላል ነው። ስለዚህም ስንፍናን አራግፈን በትጋት ሌት ተቀን እንሥራ፤ ተስፋ መቁረጥንና ጨለምተኝነትን አስቀርተን በጋራ፣ በትብብር፣ በፍቅር ለማሸነፍ እና ለመሻገር እንትጋ፤ የዛሬውን ድህነታችንን ሳይሆን መጪውን የአገራችንን ብልጽግና እያየን ለነገይቱ ኢትዮጵያ የአለንን ሳንቆጥብ እንስጥ፤ የወገናችንን ጥቃት የእኛ ጉዳት፤ የእያንዳንዳችንን ድል የሁላችን ስኬት እንደሆነ በማሰብ፣ በመረዳት እና በመተባበር በባእድ ምድር ውስጥ ጠንካራ ሕዝቦች መሆናችንን እናሳይ፤ ጠንክረን ተባብረን በተስፋ ከሠራን መበልጸግም፤ መከበርም እንችላለን። የአገራችን መልኳም፣ ሀብቷም፣ ስኬቷም የሚወሰነው በእኔና በእናንተ የዛሬዎቹ ታታሪ የኢትዮጵያ ልጆች

ተጨባጭ ተግባር ነውና የማይናወጥ የነገን መሠረት አስቀምጠን እንለፍ። በሚያልፍ ዕድሜ የማያልፍ ታሪክ እንሥራበት። ለዚህ ስብሰባ የመረጥነው ቦታ ይህ ባይሆንም የዚህ አገር መንግሥት "ለኢትዮጵያውያን የሚመጥነው ይህ ስፍራ ነው" በማለት በነፃ በዚህ መልክ አሳምሮ የሰጠን የመከበር ጅማሬው "ሀ" ብሎ መጀመሩን ማረጋገጫ ነው።

የተከበራችሁ ወገኖቼ እንደምታውቁት በዚህ በመካከለኛው ምሥራቅ አገራት ያሉ ሕዝቦች ሁለት ዓይነት ጠባይ አላቸው። ለምሳሌ፤ አሁን የምንገኝበትን የተባበሩት ዐረብ ኤመሬትን ብትወስዱ ሰባት አገር መሆን የሚችሉ ግዛቶች በአንድ ላይ ተጣምረው የፈጠሩት ፌደሬሽን ነው። በተጨማሪም በአገሪቱ ከሚኖሩ ወደ ዓሥር ሚሊዮን የሚጠጉ ነዋሪዎች ውስጥ ሰማንያ በመቶ እና ከዚያ በላይ የሚሆነው ከመላው ዓለም የተሰባሰበ ስደተኛ ነው። ከራሳቸው ጎሳዎች በተጨማሪ ከህንድ፣ ከፓኪስታን፣ ከባንግላዲሽ፣ ከፊሊፒንስና ከሰሜን እና ምሥራቅ አፍሪካ አገራት የመጡ ሕዝቦች በአንድ ላይ ይኖሩባታል። ታዲያ እነዚህ ሕዘቦች በአንድነት ለጋራ ብልጽግና እንዲተጉ ብዝኃነታቸው እንቅፋት አልሆነባቸውም። ትልቁ ሀብታቸው የነዳጅ ዘይት ሳይሆን ይህንን ሁሉ ልዩነት አጣጥሞ ሥራን አክብሮ እና ተባብሮ ለመሥራት የፈጠሩት ባህል ነው። በሌላ በኩል፤ እንደ የመንና ሶሪያ ባሉ አገሮች ውሰጥ ሀብት ሳይጠፋ ሰላም ባለመኖሩ እየተፈጠረ ያለውን አሳዛኝ ነገር ትገነዘባላችሁ ብዬ አምናለሁ።

ይሄ ለእኛ ትልቅ ትምህርት ሊሆነን ይገባል። የአንድ አገር ዜጎች አንዳቸው ሌላቸውን ለማሸነፍ በሚያደርጉት ጥረት በቀላሉ ወደ ሀብት ሊቀየር የሚችለው ዕድል መጥፊያቸው ሲሆን አይተናል። ዛሬም በእኛ አገር በብሔርና በሀይማኖት፤ በክልልና በፖለቲካ አመለካከት መለያየታችን ሳይሆን ይህንን ልዩነታችንን የምናይበት አመለካከትና የምንይዝበት የምናስተናግድበት መንገድ ውጤታችንና መጨረሻችንን ይወስናል። በጥላቻ የበለጸገ፣ በፍቅርም የቆረቆዘ ሕዝብ የለም። በመለያየት ያሸነፈ፤ በመተባበርም የከሸፈ አገር በታሪክ ውስጥ ታይቶ አይታወቅም። በስንፈናና በሌብነት የከበረ፤ በትጋትና በደግነት የከሰረ ማኅበረሰብም ታይቶ ተሰምቶ አይታወቅም። በዚህ አገራችን የወደፊት አቅጣጫ በሚወሰንበት ወሳኝ ወቅት መልካም ምሳሌነት ከአላቸው አገሮች ተሞክሮ መማርና አገራችን ወደ ብልጽግና እና ሰላም የሚወስዳትን ጎዳና እንድንመርጥ ጥሪዩን በታላቅ ትሕትና አቀረባለሁ! ዛሬ በብዙ ተስፋ አስቆራጭ ነገሮች ውስጥ እያለፍን ይሆናል። "የማይገድለን የሕይወት ፈተና ያጠነክረናል እንጂ አይጎዳንም።" የሚለውን የጠቢብ ምክር በመስማት እንቅፋቱን ወደ ድልድይ ችግሩን ወደ ዕድል በመቀየር የብልጽግናን መንገድ አሻግረን እያየን ወደ ፊት መጓዛችንን፤ ስሜታችንን ገርተን በፍቅር መተሳሰራችንን ማስቀጠል ይኖርብናል።

አሁን በአገራችን ሊጠፋ የማይችል የለውጥ ችቦ ተለኩሷል። ዳር ቆመን የምንተዛዘብበት፣ የምንነቃቀፍበት፣ የምንቃወምበት ጊዜ ሳይሆን፤ ሁላችንም የየበኩላችንን ድርሻ ለመወጣት ባለን ዐቅም ሁሉ፤ ገንዘብ፣ ዕውቀት፣ ችሎታ፣ በአንድነት ተደምረን አገራችንን ወደ ብልጽገና ግብ ለማድረስ መሮጫው ትክክለኛው ጊዜ አሁን ነው። ይህንን መልካም አጋጣሚ በትክክል በመጠቀም ከግባችን ደርሰን ፈጣሪን ለማመስገንና ድላችንን በአገራችን ውብ ምድር ለማክበር እናንተም በክብር ተመልሳችሁ የምንገናኝበት ጊዜ ሩቅ እንደማይሆን አምናለሁ።

በእርግጥም ለአገራችን የሚታየኝን ዛሬ ልነግራችሁ እፈልጋለሁ። አገራችን ከድህነት ተርታ ወጥታ ከበለጸገው ዓለም ጎራ ተቀላቅላ ይታየኛል። በዚያን ጊዜ እኅቶቻችን ተሰድደው በሰው አገር የሚጎሳቆሉበት፤ ወንድሞቻችን እንጀራ ፍለጋ ወጥተው አንገታቸው የሚቀላበት፤ ጨቅላዎቻችን በበሽታ እና በረኃብ የሚቀጠፉበት ዘመን አክትሞ ኢትዮጵያ ኢትዮጵያ የምትሆንበት ጊዜ ከፊታችን ይመጣል። ለኢትዮጵያውያን በምቾትና በደስታ መኖር የሰርክ ሕይወት እንጂ ብርቅ አይሆንባቸውም። በዚያ ዘመን በነፃነት መንቀሳቀስ፤ ሐሳብን ያለገደብ

መግለጽ፤ በነፃነትና በእኩልነት መኖር እውን የሆነባት፤ ኢትዮጵያውያን ሁሉ ተከባብረው እና ተዋድደው በጋራ የሚኖሩባት ኢትዮጵያ የምትሰኝ ምርጥ አገር በምሥራቅ አፍሪካ አያለሁ። ይህ ኢትዮጵያን በልጽጋ እና አምራ የማየት ምኞቴ እውን እንደሚሆን ለአፍታ ለአንዳች ሰከንድ እንኳን አልጠራጠርም። ይቺ ኢትዮጵያ ፍትሐዊ የሀብት ክፍፍልና ሰው ሁሉ በሰውነቱ ነፃነት ተከብሮ ተስማምቶ የሚኖርባት፤ ሰላም የሰፈነባት ዲሞክራሲያዊት አገርና ሁሉን ሕዝብ በእኩል የምታይ፤ እጇን ለልመና ሳይሆን ለመርዳት የምትዘረጋ አገር እንደሆነች በእውን በግልጽ እመለከታለሁ።

ደግሞም አምናለሁ፤ የሰማነውን እናያለን፤ ያየነውንም እንጨብጠዋለን። የዛሬው የስደት ዘመን አክትሞ አገራችን ወደ ብልጽግና ምዕራፍ ትሻገራለች። ችግርና ችጋርን አልፈን ለደስታ እና ለመዝናናት በሚል ወደ ሌሎች ዓለማት የምንዘዋወርበት ጊዜው ሩቅ አይሆንም። የኢትዮጵያ ሴት ልጆች በከበሩ የዱባይ ሱቆች ለመገብየት እና ከፍተኛ የንግድ ሥራዎች ለመሥራት ሲሉ ይመጣሉ። የቤት ሠራተኛ ለመሆን የሚመጡበት ዘመን ግን ያከትማል። የኢትዮጵያ ሕፃናት ልጆች ለዕረፍት እና ለመዝናናት ሲሉ ወደእዚህ ይመጣሉ። አዛውንትና ምእመናን ለጸሎት እና ከፈጣሪ ጋር ለመገናኘት ሲሉ ወደ መካከለኛው ምሥራቅ ይሻገራሉ። ወጣቶች እና ባለሙያዎች ለከፍተኛ ትምህርትና ለአማካሪነት ሥራ ብቻ ወደ መካከለኛው ምሥራቅ ይሻገራሉ። ይህ ጊዜ ሩቅ እንደማይሆን አምናለሁ። አንድ ሆነን ከሠራን ደግሞ ጊዜውን በጣም ቅርብ ማድረግ እንደሚቻልም እገነዘባለሁ። የዚህ አካባቢ አገራት ዜጎች ወደ አገራችን ተቀጥረው ለመሥራት ወይም የቢዝነስ አጋር ለመሆን፤ አልያም በመልካሙ የአገራችን ተፈጥሮ የአየር ንብኚ እና ታካሚ ሆነው የሚመጡበት ጊዜም እንደሚኖር ምንም ጥርጥር የለኝም።

ውድ የአገሬ ልጆች የዛሬ ሠላሳ እና አርባ ዓመት ሼክ ዛይድ ይሄን ፌደሬሽን ሳይመሠርቱ ኢትዮጵያውያን ሳምንት፤ ሁለት ሳምንት ለመቆየት የሚመኙት





ምድር አልነበረም። ባለፉት ሠላሳ ዓመታት እንደ ሼክ ዛይድ ያለ ብሩህ አእምሮ ያለው ድንቅ መሪ ስለአገኙ ለራሳቸው ብቻ ሳይሆን በሚሊዮን ለሚቆጠር ሕዝብ መጠለያ መሆን ችለዋል።

ይህ ለኢትዮጵያ ያለኝን ራእይ እና እምነት ለመግለጽ ነብይ መሆን አይጠበቅብንም። እናንተ ባላችሁበት አገር ባለፉት ሃያ ሠላሳ ዓመታት ድንቅ ሰዎች በረሓን ገነት ማድረግ ከቻሉ፤ እኛ ኢትዮጵያውያን እንዴት ገነትን ገነት አድረገን ማቆየት ይሳነናል። ውድ የአገሬ ልጆች ኢትዮጵያ ድንቅ አገር ናት። ሕዝቦቿም ውብ ሕዝቦች ናቸው። በምትሠሩበት ስፍራ ሁሉ እንደምታዩት ያልተማርን ድሃ ብንመስልም ውበታችንን፣ መልካምነታችንንና ሥነ ምግባራችንን የማያደንቅ የዓለም ሕዝብ አላያችሁ? መሬት፣ የአየር ንብረት፣ ውብ ሕዝብ፣ ብዙ ቋንቋ ተሰጥቶናል። ይህ ሁሉ ፈርጥና የኩራት ምንጭ ሆኖ ኢትዮጵያን ድንቅ እንድናደርግ የግል ስሜታችሁን፣ ቂም ጥላቻችሁን ትታችሁ፤ በፍቅር በአንድነት መደመር ከቻላችሁ፤ ስሜታችሁን መግዛት ከቻላችሁ፤ እመኑኝ ኢትዮጵያ የአፍሪካ ፈርጥ የዓለም ኩራት ትሆናለች።

የተከበራችሁ ውድ ኢትዮጵያውያን! እናንተ ኪሳችሁ እንጂ ልባችሁ ሃብታም ነው። ኪሳችሁ እንጂ አእምሮአችሁ ሃብታም ነው። ወገኖቼ ፍቅርን፣ መደመርን፣ ትዕግሥትንና ይቅርታን ታጥቀን ኢትዮጵያን ለኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆን ለሌሎች አገራት ምሳሌ እንድናደርጋት፤ የተበደላችሁት ካለ "ይቅር!" ብላችሁ፤ ያኮረፋችሁት ካለ ትታችሁ፤ በፍቅር ስሜት ኦሮሞ፣ አማራ፣ ትግራይ፣ ወላይታ፣ ሲዳማ፣ አፋር፣ ሱማሌ ሳትሉ ብትተባበሩ፤ እኛም ባገኘነው ዕድል ከልብ ሳንሰርቅ በታማኝነት ብናገለግላችሁ፤ ኢትዮጵያ ታላቅ የመሆኗ የማይቀየረው ወቅት አሁን ነው። ስለአከበራችሁኝ፣ በዚህ ስፍራ ስለመጣችሁ፣ ያለኝን ራእይ እንዳጋራችሁ ስለፈቀዳችሁ፤ እያንዳንዳችሁን በአላችሁበት ስፍራ መጥቼ አቅፌ መሳም የማይቻለኝ ቢሆንም፤ እጅግ አብዝቼ የምወዳችሁ፣ የማከብራችሁ፣ እንደ እናት ልጅ የማያችሁ፣ የእናንተን

ለውጥ የምሻ መሆኔን ልገለጽላችሁ እፈልጋለሁ። እዚያ የማያችሁ የትግራይ ተወላጆች፤ እዚያ የማያችሁ የኦሮሞ ተወላጆች፤ እዚያ የማያችሁ የአማራ ተወላጆች፤ ሁሉም ኢትዮጵያውያን በየአላችሁበት ለአንድ ደቂቃ ሁላችሁም ተቃቅፋችሁ በፍቅር ይቅር እንድትባባሉ በታላቅ ትሕትና እለምናችኋለሁ! ለዚያ ምሳሌ እንዲሆን እኔም አምባሳደሬን በማቀፍ አርአያ እሆናችኋላሁ።

**ፈጣሪ ኢትዮጵያን እና ሕዝቦቿን ይባርክ!**
**ፈጣሪ በሰላም ወደ አገራችሁ ይመልሳችሁ!**
**ፈጣሪ አገራችንን ባላት ክብር ልክ**

**የምንገልጽበትን ዘመን ለሁላችን ያሳየን!**
**አመሰግናለሁ! እወዳችኋለሁ!**


የኢኖቬሽን ሳምንት ማጠናቀቂያ

ከመጋቢት እስከ መጋቢት

ንግግሮች

እንግሊዘኛ

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት

የካቲት

ጵያገር



# Belt and Road Forum for International Cooperation

April 26, 2019

**Your Excellency Xi Jinping, President of the People's Republic of China,**
**Your Excellencies Heads of State and Government,**
**Honorable Ministers,**
**Heads of International Organizations,**
**Ladies and Gentlemen,**

I want to express my heartfelt appreciation to President Xi, the Chinese Government and its people, for the warm invitation and welcome. I convey sincerest greetings and well wishes from the people of Ethiopia. On the occasion of the second Belt and Road Forum, I am delighted to be

here in Beijing to share my thoughts with you.

Ethiopia and China have shared strong bilateral relations rooted in progress for almost fifty years. And the role of Chinese investments, particularly in infrastructure development, is one such measure of our continued cooperation. China has stood by Ethiopia's side at all times. Today, our collaboration has reached new heights, and our friendship has blossomed. Ethiopia is therefore a grateful partner and a beneficiary of the Belt and Road Initiative.

The Belt and Road Initiative, in my view, is a grand global initiative. It is China's answer to the challenges of growing unequal development in the world. It is indeed a powerful platform that anchors our close cooperation with China.

With its investment in physical and digital interconnectivity – from roads and bridges to ports, reliable power and fiber optic networks – the Belt and Road Initiative has targeted and addressed our binding constraints to development while respecting our legal framework. China's effort through the Belt and Road Initiative symbolizes a wise and forward leaning effort to build a more fair and equitable international order.





**Excellencies**
**Ladies and Gentlemen,**

Like China, Ethiopia made progress in bringing a significant proportion of our citizens out of poverty. However, unlike China, the foundation of Ethiopia's economic transformation has yet to evolve. We believe China has set a successful model in which sustained investment in infrastructure and manufacturing, coupled with focused and competent leadership have played a transformational role. These are also Ethiopia's priorities today. For our economic transformation project to succeed, we have come to realize that our politics also needs fixing. Hence, this has also been one of my priority areas since I took office just over a year ago.

In efforts to shape a comprehensive political and economic reform program which we launched in April 2018, we introduced our philosophy of MEDEMER - an Amharic word for "synergy". This home-grown philosophy challenges all of us to complement each other and to build on our individual and collective strengths. This for the purpose of securing our future together.

When I say we are inspired by China's leadership and its Belt and Road Initiative, we have good reasons behind it. Projects such as the Addis Ababa - Djibouti Railway, part of Belt and Road Initiative, are essential for the economic progress and prosperity of the two countries. But, for us,

they are more than that. They are investments in closer relations between neighbors; they are investments in peace. By allowing us to trade together, these projects make each one a stakeholder in the peace and prosperity of the other.

Ethiopia is also actively working towards ensuring peace and security in the Horn and similarly pioneering sub-regional integration. The often-volatile Horn of Africa region is looking more stable politically, and more attractive economically than ever before. And Ethiopia, for the first time in its history, has become a founding member of the highly promising African Continental Free Trade Area which is expected to be launched in July 2019.

Finally, Ethiopia is firmly following on the path of investment-led economic policy, ready to invite private capital in public enterprises such as telecommunications, shipping and logistics, transport by road or rail, and power. We invite more Chinese companies to participate in investments within state-owned enterprises operating in these sectors.

**Excellencies**
**Ladies and Gentlemen,**

Ethiopia considers China, a reliable friend in the course of our national development and reform agenda. As my administration works tirelessly to make Ethiopia a beacon





of hope for its citizens, a source of stability and opportunity for its neighbors, light for the continent, and a responsible member of the global community, it is my hope that our partnership will continue to support these endeavors.

I want to register my appreciation once again to the people and government of China and President Xi Jinping for your principled leadership and of course for hosting us at the Belt and Road forum so warmly.

**Xiexie**
**I thank you.**

# Sudanese Agreement for Peace

August 18, 2019

**Your Excellencies,**
**Brothers and Sisters of Sudan,**

It is with great honor that I stand here before you bearing witness to this momentous day, which marks the birth of a new era for this great nation.

We are gathered here in celebration of the people of Sudan who have sacrificed greatly to guarantee their freedoms.

We give special tribute to the fallen who have paid the ultimate price towards realizing their vision for a democratic country. As the world observes the coming into effect of this agreement between the Transitional Military Council and the Forces for Freedom and Change, let it remain a standing testimonial to remember the lives that have passed, though not in vain.

At the outset, I would like to congratulate the parties to the agreement for choosing country over self; for placing the collective wishes of the Sudanese people above individual interests; and most importantly for showing the world that dialogue is the only way to a win-win solution.

In your commitment to dialogue and openness for engagement, you have all demonstrated that our historic African tradition of coming together to problem solve will always be the beacon lighting our way to our greater potential for harmony.

**Dearest Brothers and Sisters of Sudan,**

The people and Government of Ethiopia celebrate with you today. Your victory is our victory in the same way that your pain is our pain. The relationship between Ethiopia and the Sudan, surpassing many years, has been firmly rooted in mutual respect and solidarity. It is premised upon the undeclared understanding that our fates are intertwined and extend beyond mere neighborliness. The historic relations our two countries have enjoyed; our current socio- economic cooperation and diplomatic ties, and our shared future, are the three key pillars upon which a continuously strengthening relationship between

Ethiopia and the Sudan are built.

It is with a genuine vested interest in seeing the good people of Sudan prosper and thrive that my Government committed itself over the past few months to supporting a peaceful transition - true to the peace-loving nature of the Sudanese people.

It is critical to recognize that the journey to this day has not been easy. Reaching consensus is laborious; requires both emotional and technical intelligence; and demands patience. Nevertheless, through many dark tunneled passages we persist, with the firm belief that our collective well-intentioned efforts will pave the way for a common understanding to emerge. A common ground defined by principles of fairness, equality, dignity and foremost love of country and people.

The progression of the various agreements concluded in today’s ceremony is a clear demonstration of how integration of inputs from well-meaning partners can pave the way to peace. Withstanding minor temporary setbacks, which are a part of any negotiation, the Sudanese-led dialogue process that through today’s signing ceremony births a civilian government, will be remembered throughout history as an embodiment of our often stated, but not always practiced, principle of home-grown solutions.





In our resolve to conceptualize and realize home-grown solutions, we demonstrate to ourselves our potential and clear propensity to manifest regional peace. The essence of our people in the Horn region has always been cooperation over competition. And inherent to our collective survival and prosperity in the region is MEDEMER – the synergistic yarn weaving us together to create collectively, what we can only imagine individually. As we work at the national level to bring peace and stability to our countries, by instilling the principles and mechanisms of democracy, we are simultaneously placing a firm foundation for regional economic, social and political integration.

Beyond the artificial boundaries we have drawn on our maps and, in our minds, our survival and that of generations to come is dependent on making a paradigm shift. This paradigm shift entails examining how we view and relate with one another. From competition to our original essence of cooperation; from dichotomous thinking and zero-sum fragmentation to harmony and amalgamation – recognizing that there is strength in unity.

Let me also take this opportunity to convey my greatest admiration and respect to my Special Envoy for Sudan, Ambassador Mahmoud Dirir. A seasoned diplomat with a desire for peace, his impartial commitment to the Sudan talks has borne fruit. I would also like to express my

gratitude to the African Union's Special Envoy Professor Mohammed Hassen Labat for his tireless contribution to facilitating the dialogue between the two parties. I congratulate both of you and also share my appreciation to all who have played a positive role.

**Dearest Sudanese brothers and sisters,**

Your path to democracy has just began. Let not this achievement overshadow the hard work that awaits all of you. Many seek and speak of democracy but seldom grasp the responsibility that comes with it. Building functioning democracies takes more than merely demanding it. It requires a clear and steady commitment to articulating and living democratic principles by which all will be governed. It requires building the necessary institutions. It demands the combined efforts of various stakeholders working in synchronicity. But most importantly, it entails individuals recognizing that each action they take against another, who they believe is not like them, is actually decomposing the very principles they have fought to bring forth.

And so, my parting words to the new civilian Government and people of Sudan is – be the custodians of peace and the guardians of dignity. Protect today's victory and what it took to get here, from the ill-intentioned. And recognize that regardless of which side of the negotiating table you were seated at, you were all negotiating for Sudan.





Let that common purpose be your anchor as you safeguard this great nation and people. I thank you.

**Shukraan.**

# TICAD7 Special Conference on Peace and Stability in the Horn

August 29, 2019

**Excellencies**
**Ladies and Gentlemen,**

It is my great pleasure to be amongst you here today. I would first like to express my appreciation to the Government of Japan for taking the initiative of convening this special conference dedicated to the Horn of Africa. This is a welcome move demonstrating genuine partnership and considerable goodwill.





I am particularly pleased to share that the situation in the Horn of Africa has been shifting over the past year. The region is undergoing positive changes in the direction of enduring peace, stability and collective prosperity. As we shed our old skin, which has often been synonymous with conflict and disparate interests, we are regenerating a new one of opportunity, cooperation and peace.

Ethiopia firmly believes that having stable and prosperous neighbors is key to our own growth. In the new path that we are forging as a country, my government is determined to make mutual progress the new normal by challenging zero-sum thinking. This is the very reason that we have been supporting conflict prevention and peace building efforts in the region. It is also why we are championing the principles of MEDEMER – synergistically working together with our neighbors towards economic, political and social integration.

As we reflect over positive regional milestones in the recent past, the normalisation of relations between Ethiopia and Eritrea has unlocked great possibilities to work together on a common agenda of peace and development. We have embarked on a journey which was unthinkable only years ago. Today, we are working closely together with a sense of urgency to make up for time lost in conflict, with a view to making our people enjoy the dividends of peace.

**Excellencies,**

Last week, we also witnessed the signing of the final transition agreements that have paved the path for the formation of a civilian government in the Sudan. Following a crisis, that if protracted, would have had grave consequences for regional stability, the August 17th deal between the Transitional Military Council and the Forces for Freedom and Change is testament to our changing narrative and aspiration for peace in the region.

This breakthrough was made possible through combined efforts and a willingness of the negotiating parties to anchor their decisions in the well-being and dignity of their people. There are key lessons to be drawn from the Sudan process for consideration in conflicts that still linger in the region.

A commitment to abandoning the old-fashioned deference to arms and replacing it with devotion to dialogue, will generate the shared growth we envision. Similarly, shifting our ego-based interactions to generative engagements will ultimately unlock our potential to materialize inclusive societies in which our people benefit equitably.

With a noticeably young population in the region, we need to create lasting opportunities for our youth so that they may never view violence as a recourse, but rather become the custodians of peace and guardians of their countries.





Nurturing shared economies that provide decent work for our youth and unlocking the productive capacities of our businesses are both key.

When we work towards a shared vision of regional integration, our artificial borders will then not be a source of tension, but rather become corridors of peace, trade and prosperity. And as leaders, we need to model to our citizens what the possibility of working across lines of divides towards a common purpose looks like.

I would like to take this opportunity to call upon fellow Horn region countries to shift our focus towards fully exploiting our assets and our unity for the good of our people. I would also like to invite partners to assist in building on the many successes and milestones our region is marking.

Coming together in the spirit of MEDEMER to create opportunities for the people of our region will ultimately guarantee sustainable peace and prosperity.

**I thank you!**

# Russia-Africa Sochi Summit

October 24, 2019

**Your Excellency, Vladimir Putin**
**Your Excellency Abdel Fattah el-Sisi**
**Excellencies Heads of State and Government**
**Ladies and Gentlemen,**

I would like to begin by commending President Putin for taking the initiative to host the first ever Russia-Africa summit. Historically, the principle of solidarity has been the defining characteristic of Russia-Africa relations.

And our gathering at this Summit will enable us to explore the potential for a mutually beneficial cooperation that stands on an equal footing to address the myriad of challenges we face as a global community.

The old-fashioned zero-sum game approach in dealing with international peace and security has cost us a lot





historically. And in our current globalized and highly interconnected world, the complexities we face require our collective commitment to developing and sustaining cooperative relations.

We have laid out these commitments in the purpose and principles of the United Nations Charter, which are the basic tenets of global prosperity. Let us uphold these principles for the greater well-being of our nations.

**Excellencies,**

In Ethiopia and within the Horn region, my government is championing the philosophy of MEDEMER - an Amharic word loosely translating to "synergy". Through MEDEMER, we are called upon to take stock of our positive assets from the past, build them into our present and pass the accumulated capital to future generations.

Regionally, we are also encouraging MEDEMER, so as to complement each other and to build on our country's individual and collective strengths and historical assets. My government truly believes an integrated Horn of Africa is the pathway to securing our future together.

There is no doubt we share similar views on a range of regional and international issues of common interest at this gathering. The mechanisms for dialogue partnership that we will establish through the adoption of the Summit

Declaration will go a long way in helping us coordinate our positions in international fora.

And it is my hope that we can inculcate the spirit of MEDEMER in the way forward we are forging.

**Excellencies,**

There is tremendous potential for Africa and Russia to enhance trade and economic cooperation. The continent's abundant natural resources and energetic youth coupled with investments in infrastructure development and innovation, are fast changing the face of our countries.

Our narratives are also shifting - from fighting poverty to building prosperity for our citizens. To maximize on our potential for economic growth, we have also been marking milestones in silencing the guns and mobilizing our industrialization machineries.

We have recognized that peace is the foundation for prosperity and we are working hard to sustain it.

Ethiopia is also actively working, together with its neighboring countries, towards ensuring peace and security in the Horn region. The often-volatile Horn of Africa is looking more stable politically, and more attractive economically.





We have no doubt that the positive narratives we are crafting in our region will radiate throughout the continent.

In closing, I would also like to draw your attention to the abundance of opportunities that are flourishing in Ethiopia. Through our economic reforms, we are focused on creating an enabling investment environment. Therefore, our priority areas like agriculture, tourism, mining, ICT and manufacturing have great potential for mutual growth.

I wish all of us fruitful discussions and let's meet in Addis!

**Spasibo**

# Electronic World Trade Platform Launch

October 25, 2019

**Dear Jack Ma,**
**Distinguished Guests,**

A very Good Morning to all of you,

Thank you, Jack, for following through on our discussions at Alibaba HQ in Hangzhou.

I welcome you all to the launching ceremony of the Electronic World Trade Platform, which is an important part of Ethiopia's digital economy development endeavors.

Advances in technology, particularly the increase in cloud storage, cloud computing, machine learning and artificial intelligence have changed the everyday lives of humans.





Digital technology is rapidly developing in diverse fields, including mobile communications, robotics, artificial intelligence, the internet of things, and 3D printing.

With these kinds of enabling technologies, we are already experiencing profound changes that new technologies bring to the way we live, work, interact, and do business.

There are times in history when the world goes through a transformational shift and the new replaces the old.

Throughout history, technology has been a dominant force in driving economic growth and uplifting countries and their people. History also tells us that rapid technological change presents challenges to countries and people, therefore requiring time and capacity for adaptation.

The world is again in a time of immense change which the 4th Industrial Revolution is introducing. With appropriate policies, developing countries stand to benefit tremendously in this new era.

I see great opportunities in Electronic World Trade Platform, as it is a private sector-led initiative to incubate e-commerce for cross border electronic trade development.

Electronic World Trade Platform creates a fair playing ground for small and medium enterprises, enabling them to access information about export opportunities, access

to trade finance and logistics.

It is proving to be a game changer in the world of commerce and will support Ethiopia's plan to be one of the five leading economies in Africa in the coming ten years.

As a trade platform, it creates direct access to international customers and highly efficient digitalized flows of major components of e-commerce such as products, data and money.

Electronic World Trade Platform works towards simplification of regulations and customs processes, consumer protection, lowering of tariffs and harmonization of taxation.

It also works towards development of internet and logistics infrastructure, facilitation of flow of goods, finance and information.

Taking Electronic World Trade Platform as one of the e-commerce platforms, Ethiopia aims to facilitate the development of eTrade and the digital economy through the development of eTrade infrastructure and adoption of best practices to move towards prosperity.

Through such initiatives, Ethiopia's path to prosperity is ensured.

**I thank you!**





# Speech during visit to Israel

September 1, 2019

**Your Excellency Benjamin Netanyahu**
**Distinguished Guests,**
**Ladies and Gentlemen,**

Shalom Lekulam!

Please allow me to express my sincere appreciation and gratitude for the warm and friendly welcome. I convey the heartfelt greetings of Ethiopians to the beloved people of Israel and special greetings to the Bête-Israel community.

**Your Excellency, Ladies and Gentlemen,**

It is very special to be in this blessed land with a long history symbolizing resilience. A home to the three Abrahamic religions of Judaism, Christianity, and Islam, Ethiopia shares common roots of history, language and culture with

Israel. The relations between our two countries go back to ancient times and thus our forefathers and foremothers have always had an interest to build this special relationship.

Ethiopian churches and monasteries in Israel, like the Deir Es-Sultan, are vivid reminders of our ties. Among the glorious stories that have been recounted for centuries, most Ethiopians know by heart the story of the Queen of Sheba and King Solomon. This shared history will continue to serve as the basis for strengthening our mutual bonds. In our modern history, we all remember the profound cooperation between our countries in various fields during the days of Emperor Hailesellasie, Currently, Ethiopian Jews in Israel are serving as a bridge between us.

**ACHIM ANACH-NU (we are brothers)**

**Your Excellency,**

Ethiopians recall the official visit you paid to Ethiopia in 2016 as the first Israeli Prime Minister to have ever visited. We also remember the important message you shared when you addressed our parliament, on deepening ties with Ethiopia. The business delegation you brought along has served to strengthen links.

This year in particular, we have stood with each other during challenging times. My country mourns together with you for the three Israelis that lost their lives due to circumstances beyond our control. We pay great respect to Mr. Avraham Mats-li-ach and Mr. Shimon Reem, who passed in the devastating airplane accident earlier this year.

Moreover, the death of a young volunteer, Aya Na-am-nah, is deeply saddening. My profound condolences to their families as well as to the people and Government of Israel.

I would also like to comfort the family of Mr. Mats-li-ach that we will continue to work together to find and return his remains to Israel. I would also like to take this opportunity to pay respect to the family of Solomon Tekah, an Ethio-Israeli who lost his life in a tragic event here in Israel.

In times of such grave losses and challenges, we mourn together as two families. Yet by standing with each other, our pains will also begin to ease. Let me then take this opportunity to express my gratitude for demonstrating your solidarity with Ethiopia when you sent the best of your team to support us in containing the Semien Mountains forest fire earlier this year.

This act of collaboration and support is shown in many activities and willingness to share learnings and experiences through medical delegations, agriculture training farms and more.

The ancient ties and bonds are always there.

**Your Excellency,**

I am here to express my readiness to reinvigorate our relations. We need to build on the common interests which are steadily growing over time. I strongly believe that the overall relations between Ethiopia and Israel guided by a strategic partnership should focus on key areas such as modern agriculture and irrigation, ICT, health sector, and tourism.

In Ethiopia, we have given due emphasis to widening the business space for the private sector to engage more. In this context, we look forward to Israeli investors participating in key industries mentioned, as well as in the sectors of telecom, aviation, logistics and energy, which we have opened up for partial privatization. We also look forward to the Israeli government to initiate capacity building efforts, in health and ICT sectors as well as to support modernize our agriculture.

On a final note, I would like to share that Ethiopian monasteries that exist in Jerusalem are very special representatives of our longstanding connections. These are symbols to Ethiopians and all African people in Israel and beyond. Hence, we need to create a technical cooperation platform that will lay the foundations to maintain their stature as our shared heritage sites.

In closing, I would like to emphasize that the cooperation between Ethiopia and Israel is not limited to the bilateral





arena. It also extends to regional and internationals issues. In this regard, let me assure you that Ethiopia will always work for a dynamic and effective partnership in promoting regional and global peace and security.

## I Thank You! Toda RABA

# Homegrown Economic Reform Discussion Opening Address

September 9, 2019

**Distinguished members of the diplomatic community,**
**Distinguished development partners,**
**Ladies and Gentlemen,**

Thank you for joining us today. I would like to begin by expressing my gratitude to the United Nations Economic Commission for Africa and its Executive Director, my good friend Vera Songwe, for supporting today's gathering.

I am quite delighted to share with you our vision of the newly launched Homegrown Economic Reform agenda.





Several months in the making and spearheaded by some of Ethiopia's finest minds, our initiative aims to propel Ethiopia into becoming the African icon of prosperity by 2030.

Catapulting into the future requires us to take stock of the recent past. And as we approach the New Ethiopian Year, I would like to briefly reflect on the progress we have made thus far, and how our MEDEMER philosophy is ushering in an irreversible paradigm shift.

**Ladies and Gentlemen,**

In just over one year, we took a series of measures aimed at shifting the economic growth landscape of Ethiopia. We managed to find a short-term remedy to the inherited macroeconomic and fiscal imbalances. This helped to temporarily stabilize our economy, while my administration diligently worked to develop sustainable measures. Acknowledging that the next chapter of Ethiopia's growth and development requires a more active private sector, we opened up key economic activities to private investments.

I have also been personally leading a national high-level committee formed to drive reforms in investment laws and business climate. This high-level national committee has made progress in facilitating a conducive business environment and removing regulatory obstacles that hamper investments. I have no doubt that the measures

we have taken thus far in this regard, will be reflected in Ethiopia's Ease of Doing Business ranking. These are some of the very few organic milestones we have achieved. We moved the needle further than many had anticipated, and we continue to push further with renewed vigor and enthusiasm!

**Ladies and Gentlemen,**

It is when we create new values while maintaining our good traditions in a way that affirms the benefit of our people and promotes the unity and equality of nation and nationalities, and glorifies our sovereignty that we succeed. I sincerely believe that we can work together and change our country, individual efforts alone will not get us anywhere. Building a country is not the sole responsibility of a leader, a party, or a generation. Ethiopia belongs to all of us. Ethiopia's success comes not through mere wishes, but through sacrifice. It does not become reality just by wishes, but by working towards it. Change cannot be achieved by sitting and waiting, but by active involvement. So, let's all stand up for change!

Martin Luther King, the human rights activist, once spoke of the urge for change saying,

"*If you cannot fly to reach your grand goal, run; if you cannot run, then walk, if you cannot walk, then crawl, but whatever you do you have to keep moving forward.*" Change comes

from looking ahead and moving forward. The journey to prosperity, cannot become a reality by quitting the run or looking behind. No one has ever won races and earned a medal by running slowly or running backwards, and never will be able to do so.

**Dear Fellow Ethiopians!**

It is difficult to imagine the devastating situation and challenges many of our people in any part of the world had to bear to get to where they are. During their journey, not a few people have their dreams cut short and face the risk of ending their lives. Many have had their kidneys and livers harvested; receive no or low wages for their work; are forgotten in prisons, raped by their employers and drowned in the seas. They suffered the consequences of fleeing from poverty. Poverty degrades a country and its citizens. Poverty leads to persecution and endless suffering.

This should not go on. How long will we say "this too shall pass" strengthening our shoulders to bear more trouble, grieving for the victims and bathing in tears? After grieving our losses, all of us must strengthen ourselves. The prices we pay because we have not overcome poverty should be halted. Every price paid should only be to bring lasting prosperity for us and for our children. Think of those who have lost their dreams to sharks in the sea and those who lost their lives at the borders. Think of the stories you chose





not to tell to anyone. If we really think about it, changing our own country does not cost as much.

Twenty-five years ago, even this country was not conducive for its own citizens, let alone immigrants. There were probably not many Ethiopians at that time, except for a few. Note how strong, tens of thousands of Ethiopian Diaspora communities have been here in recent years. Each of you has your own past, present life and tomorrow's dream. You have managed to change the lives of many of your families in the beautiful cities of our country, such as Hosanna and Durame, where many of you were born. Now is not the time to invite your younger siblings for migration, but it is the time where you use the knowledge and energy you have to change their environment and your entire country to prevent migration.

Our country is no less beautiful than South Africa. My invitation to all of you today is to halt migration and living in vulnerability in foreign lands. It is now time to work to transform yourself and your country by investing the knowledge, experience and resources you have gained here. We will gladly support you.

It is now time to race. The starting bullet is fired. Let us rise up to run a race in collaboration and competition. Let's work together to win. Let's create healthy competition to award those who have worked better and achieved the best. Let us compete with wisdom, diligence, and good

manners while avoiding laziness, strife, stealing, and the exploitation of what one has not worked for. Let's celebrate winners, and create more winners. All are winners when competitions are hosted in collaboration. Therefore, let us ignore jealousy and evil and march forward. Winning does not always mean coming first, so let's strive to take grand strides into a prosperous and peaceful Ethiopia. Let's face the wind and the waves, cross the mountain, and press forward without being weary of the stumbling blocks. Let us use alternatives when they block roads on us, let us respond appropriately when they resist us in unison or support us in unison. Let us keep running forward together and in persistence looking at the prize in front of us, which is the prosperity of Ethiopia.

As we continue to do so, Ethiopia will surely prosper and become a conducive country for its citizens. No doubt, this dream of ours will surely come true! Do not waver or doubt!

**May Ethiopia be honored and feared through the efforts of her children!**

**May God bless our country and its people!**

**Thank you!**





# 33rd AU Summit Banquet Dinner

February 9, 2020

**Excellencies Heads of State and Government,**
**Excellency Ambassador Sahlework Zewdie, President of the Federal Democratic Republic of Ethiopia,**
**Excellency Chair of the African Union, President Cyril Ramaphosa,**
**Excellency, Moussa Faki Mahamat, Chairperson of the African Union Commission,**
**Members of the Diplomatic community,**
**Ladies and Gentlemen,**

It is indeed a great pleasure to welcome you to this Gala Dinner prepared to honour your presence and the thirty-third Ordinary Session of the Assembly of the African Union.

Allow me to also acknowledge our special guests here with us tonight:

**His Excellency Justin Trudeau, Prime Minister of Canada;**
**Her Excellency Erna Solberg, Prime Minister of Norway;**
**His Excellency António Guterres, Secretary General of the United Nations; and**
**His Excellency Charles Michel, President of the European Council and Former Prime Minister of Belgium.**

Ethiopia welcomes you with the warmth that emanates from the idea of "**MEDEMER for a prosperous Africa**."

And vigour that befits this august gathering.

Addis Ababa also welcomes you with open arms by availing the Grand Palace as the venue for the first time in decades.

The Grand Palace is the very same venue of the inaugural banquet held for the founding fathers of the Organisation for African Unity – the predecessor to the African Union.

Therefore, I hope you all agree with me that this evening will mark a symbolic moment of our re-dedication of





togetherness and our commitment to meet the goals of Agenda 2063 and the Africa we want.

**Excellencies,**
**Ladies and Gentlemen,**

Almost six decades ago, we expressed our determination to address the challenges to peace, democracy, and security that obstructed the development of the continent.

Similarly, during the golden jubilee of our continental organisation, we made a solemn declaration to achieve a conflict-free Africa and pledged to end wars in the continent by 2020.

Though we have marked many milestones in maintaining peace in our respective countries and regions, our people are still facing the plagues of conflict and instability.

Various threats to peace and security including terrorism, human and arms trafficking and external interferences, continue to fuel conflicts in different parts of the continent.

They have been and continue derailing our efforts to build a peaceful, prosperous and integrated Africa.

Therefore, the theme for our assembly this year, "Silencing the Guns: Creating Conducive Conditions for Africa's Development," requires our collective efforts in not only

addressing the root causes of conflict but also in reorienting our development lens.

**Excellencies,**
**Ladies and Gentlemen,**

A peaceful, prosperous, and conflict-free Africa cannot manifest when we continue thinking in silos. Our motto should be cooperation, not rivalry, compromise, not confrontation, partnership, not interference.

That is the thinking behind MEDEMER.

MEDEMER is Ethiopia's homegrown idea that champions an enduring vision to build an egalitarian, democratic, and peaceful society, by effectively utilizing our resources to champion the growth and prosperity of our people.

For instance, the venue for tonight's occasion is a manifestation of MEDEMER. Housing many incredible historical assets, this compound underwent a radical transformation, capitalising on the foundations of what existed and what those before us had introduced.

It now bears generational fingerprints of all those that have contributed to its current glory.

Therefore, MEDEMER aspires for the continent to build on past achievements, to harness our accumulated historical and cultural assets, and to capitalise on our existing resources for nurturing prosperity.

MEDEMER also aims to bring forth the Africa we want - a continent free from conflict, and attaches great importance to the values of love, forgiveness, reconciliation, and inclusion.

It invests in the future and nurtures the culture of peace and tolerance in our children and youth, to silence the guns in Africa.

As we instil these values in the new generation, we should start making space for change as well.

Our youth come up with new ideas, are innovative, and make demands with the changing times.

We must listen to them, support them, and ultimately make space and way for them, after laying the foundations of prosperity and handing them the tools.

**Excellencies,**
**Ladies and Gentlemen,**

Addis Ababa – your capital — has started the journey towards prosperity. As you can see out into the distance from where we are, the city offers a lot.

We are working tirelessly to unearth the potential that has not been sufficiently tapped.

Abundant natural resources, historical and cultural gems, pleasant weather and an energetic and loving people that call this city home, characterize Addis Ababa.

Using this city as a prototype, we are building prosperity inside out.

We are unleashing the urban tourism capacity of the city.

Several projects are underway, aimed at making Addis Ababa a hospitable and liveable space for its residents as well as its visitors.

These projects, like the progress of Unity Park, where we now find ourselves, are creating jobs and stirring the local economy. They are also demonstrating our capacity to start and finish in a short time frame when we work with laser focus.

By reorienting ourselves away from a disposition and narrative of poverty towards crafting a shared vision for prosperity, we will be able to mobilise our young and able youth to achieve what has always been possible and within reach.





Rest assured that the conducive environment created at the epicentre of Ethiopia will extend to other parts of the country.

This approach is our recipe for prosperity through Medemer.

By recognising that as Ethiopians, and as Africans, we are worthy of prosperity, building the country and continent that we want is conceivable and within reach.

If we want to silence the guns as a continent, embracing change and a new way of doing things needs to be our new norm.

That is what MEDEMER for a prosperous Africa aspires for the continent and its colourful people.

**Excellencies,**
**Ladies and Gentlemen,**

I conclude my welcome remarks by wishing you a truly pleasant and memorable stay in Addis Ababa – your capital!

**Enjoy your evening and I thank you!**
**አመሰግናለሁ**
**Shukraan, Merci, Obrigado, Asante Sana**


ቤልት ኤንድ ሮድ ፎረም

# ከመጋቢት እስከ መጋቢት

መግለጫዎች እና መልእክቶች

አማርኛ

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት

የካቲት ፳፻፲፫



# የጨምበላላ በዓል መልእክት

ግንቦት 22/2011 ዓ.ም.

እንኳን የሲዳማ ሕዝብ የዘመን መለወጫ በዓል ለሆነው ለታላቁ የጨምበላላ በዓል በሰላም አደረሳችሁ፤ አደረሰን!

**አይዴ ጨምበላላ!**

ዘመን የሰው ልጆች የታሪክ፣ የማንነት፣ የባህል፣ የሥነ ልቡና እና የህልውና መከተቢያ፣ ማሳያ፣ መበየኛ፣ መንደፊያ እና ማቆያ ትንግርታዊ ሰሌዳ ነው። ይህንን ድንቅ ሸራ በመቁጠር፣ በመቀመር፣ በማስላት እና በተፈጥሮ ዑደት ውስጥ የሚዘወርበትን ሥርዓት በመዘርጋት የሚጠቀምበት ማኅበረሰብ ደግሞ እርሱ ከዘመን ጋር የማይሄድ፣ ከዘመንም ጋር የማይመጣ፣ በዘመን ገላ ላይ ትናንት በአባቶቹ፤ ዛሬ በራሱ እና ነገም በልጆቹ ህያው የሚሆን ታላቅ ሕዝብ ነው። የሲዳማ ሕዝብ ይህን ታላቅ የሥልጣኔ አበርክቶ አጥሮ፣ ጠብቆ አቆይቶልናል።

የሰው ልጅን የለውጥ፣ የጥበብ፣ የአዝማናት፣ የሥልጣኔ ጫፍ እና ያለፉበትን የታላቅነት የዘመን መልክ የሚያጠኑ ጠበብት በአንድ ቃል እንደሚስማሙት እነዚህ ዘመንን ከዘመን የሚያሰናስሉ አፅማድ የሚለኩባቸው እና

የሚመዘኑባቸው ዐበይት መሥፈሪያዎች አሉ። ከእነዚህ ዐበይት የሥልጣኔ እና የታላቅነት ማሳያ አብነቶች ውስጥ አንዱ፤ ምናልባትም ዋነኛው የማኅበረሰቡ የዘመን ቀመር ዕውቀት ቀዳሚ እንደሆነ አብዛኛዎቹ ልሂቃን ይስማማሉ። በዚህ ዋና ባልነው መለኪያ ስንመዝነው ደግሞ የሲዳማ ሕዝብ በፀሐይ፣ በጨረቃ እና በከዋክብት ድንቅ የተፈጥሮ ዑደት ውስጥ ያለውን ጥልቅ የምልዐተ ዓለም (Universe) ምስጢር በመመርመር ጊዜን እያሰላ ዘመንን የሚቆጥርበት ጥበብ እጅጉን የሚደንቅ እና የሁላችንም የኩራት ምንጭ ነው።

የሰው ልጅ ከጊዜ (Time) እና ከቦታ (Space) ውጪ ለማሰብ፣ ለማሰላሰል፣ ለመፍጠር፣ እና ተፈጥሮን ለመመርመርም ሆነ ራሱን ለማረቅ እጅጉን ይቸገራል። ጊዜን የምናሰላበት መንገድ እና ዘመንን የምንቀምርበት ጥበብም እንደ ሰውም ሆነ እንደ ማኅበረሰብ ለሁለንተናዊ ሥልጣኔያችን እና ራሳችንንም ሆነ ዙሪያችንን ለምንቀርጽበት ሰብእናችን ብዙ ዐቅም ይቸረናል። ተጠቃሚዎችም ያደርገናል።

በሲዳማ የዘመን አቆጣጠር ጥበብ ውስጥ እስከ ማይክሮ ሰከንድ ሽርፍራፊ የጊዜ ቅንጣት ድረስ የሚወርድ ጊዜን የመለኪያ ጥበብ አለ። ይህ ደግሞ ለሲዳማ አባቶቻችን ያለንን ክብር እና ፍቅር እጅጉን ከፍ ያደርገዋል። በመሆኑም፤ ይሄንን የሲዳማን ሕዝብ የአዲስ ዓመት በዓል እና የዘመኑን አዲስነት ለማወጅ ጊዜ የሚቆጥርበትን ግሩም ዕሴት መላው ኢትዮጵያዊ ወገናችን ክብሩንም ሆነ በዓሉን ከልብ ይወድደዋል። ወድዶም እንደ ሁልጊዜው በጋራ ያከብረዋል። ከራስ የሚነሣ የዘመን ቀመር ባለቤት ለመሆን መቻል ያለጥርጥር ታላቅነት ቢሆንም፤ ባሰሉት ዘመን፣ በቀመሩት ቀመር፣ ባሠመሩት የዘመን መሥመር ላይ ዘመን የሚሻገር እና የእኛን እና የልጆቻችንን የዘመን ካብ የሚያተያይ ደማቅ አሻራ ለማኖር መቻል ደግሞ ከታላቅነትም የሚልቅ ዕጹብ ታላቅነት ነው።





ከዋዜማው የፍቼ ትእይንት እስከ ዋናው የጨምበላላ በዓል ድረስ አስደማሚ የዘመን መለወጫ የአከባበር ሂደት እና ሁሌም እንደ አዲስ የሚያስደምም ግሩም ሥርዓት አለው። የሲዳማ ሕዝብ በዘመናት ቅብብሎሽ በሚደንቅ ጥበብ ጠብቆ ያቆየው በመሆኑ ለዚህ ዘመን አይሽሬ የሀገር እና የዓለም ህያው አእምሯዊ ሀብት ያለኝን ከፍ ያለ ክብር እና አድናቆት በዚህ አጋጣሚ ለመግለጽ እወዳለሁ።

በመጨረሻም ዘመኑ የሰላም፣ የይቅርታ፣ የፍቅር እና የአንድነት እንዲሆንልን መልካም ምኞቴን እገልጻለሁ!

**አይዴ ጨምበላላ!**

**መልካም በዓል!**

**ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራ፤**
**ተከብራና በልጽጋ ለዘላለም ትኑር!**
**ፈጣሪ ኢትዮጵያንና ሕዝቦቿን ይባርክ!**

# የ1440ኛው ዓመተ ሒጅራ ዒድ አል ፈጥር በዓል መልእክት

ግንቦት 26/2011 ዓ.ም.

ዒድ አል ፈጥር የጾም ወር ማጠናቀቂያና መሸኛ በዓል ነው። በረመዳን ወር መጨረሻ እና በሸዋል ወር የመጀመሪያ ቀን ላይ የሚውል በዓል ነው ዒድ-አልፈጥር፡፡ በቅዱሱ የረመዳን ወር ከፀሐይ መውጫ እስከ ፀሐይ መግቢያ ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ ሕዝበ ሙስሊሙ ራሱን ከመብልና ከመጠጥ ከማቀብ ባለፈ በመልካም እና በበጎ ተግባርም መትጋት ይጠበቅበታል። በዚህ ረገድ፤ ነቢዩ መሐመድ (ሠለላ አለይህ ወሠለም) “አስከፊ ንግግር እና ተግባራትን ያልተወ ሰው ከምግብና ከመጠጥ መታቀቡ ብቻ በአላህ ዘንድ ከቁምነገር የሚገባ አይደለም” በማለት ትክክለኛውን መንገድ ማመላከታቸው በሐዲስ ሰፍሮ ይገኛል። በመሆኑም በጾምና ሰላቱ፤ በምስጋናና በልግስና ታጅቦ ለሠላሳ ቀናት የሚዘልቀው የረመዳን ወር ነፍስን አለምላሚ፣ ሥጋን ግን ጎሳሚ፤ ከዚያም በተጨማሪ ፈታኞቹ ቀናት ከአለፉ በኋላ የሚመጣው አዲስ ቀን የኢድን በረከት የታደለና ድካምንም የሚያስረሳ ተደርጎ ይወሰዳል።

በእምነታችን የተነሣ ትዕዛዛቱን ለመፈፀም በጽናት የምንቀበለው መከራ ሁሉ ከባድ ቢሆንም ማለፉ ግን አይቀሬ ነው። ያልፋል። አስተላለፉ ግን ‘ሲምር ያስተምር’ እንደሚባለው ምሕረትም ትምህርትም አግኝተንበት ነው። የረመዳን ወርና መሸኛው ኢድ አል ፈጥር በዓል ከመነሻ እስከ መድረሻ ያለው ሥርዓት በእንዲህ ዓይነቱ በረከት የታደለ ነው።

የረመዳን ወር የጾምና የመታዘዝ፤ የድካምና የመፈተንም ወቅት ነው። ነገር ግን ከሚበላባቸውና ከሚጠጣባቸው ወሮች ይልቅ ቅዱሱ ወር ደግሞ እርሱ ነው። ይህ ወር በሥጋዊ እይታ ሲቃኝ እርስ በርሳቸው የሚቃረኑ ሁለት ጉዳዮችን በውስጡ አቅፎ የያዘ ይመስላል። ፈተናና በረከት፤ ከጠዋት እስከ ማታ በጾም፣ በጸሎት እና በመልካም ምግባር ማሳለፍ ከባድ ፈተና ነው። በጾሙ ወቅት የሚገኘው ስጦታ ደግሞ በረከት ነው። አንድን ወቅት ጥሩ ጊዜና ጥሩ ወቅት ነው የምንለው እየተፈተን የምናልፍበት፣ አልፈንም የምንሸለምበት ጊዜ ሲሆን ነው። ከእጭና ኩብኩባ ተሸጋግሮ ወደ ቢራቢሮነት ለመለወጥ እንደሚታገል ተንፏቃቂ ነፍስ፣ ክንፍ አብቅሎ የሚበር ነፍስ እስከ መሆን ባለው ጉዞ በትግልና በፈተና ማለፍ ግድ ነው።  ትግሉ ግን በረከት ያለበት ፈተና ነው።

ሀገራችን አሁን ያለችበት ወቅት የፈተናና የበረከት ወቅት ነው። ከነባርና ከወቅት አመጣሽ ፈተናዎቻችን ተላቅቀን ለማለፍ የምናደርገው ትግል በፈተና የተሞላ ነው። ከባድና የማይቻል ቢመስልም ማለፉ ግን አይቀርም። ይህ ተጋድሏችን ብዙ ነገሮችን ተምረን፣ በብዙ ጠባዮቻችንም የተነሣ እስከ ተስፋ መቁረጥ አስመርረውን የምናልፍበት ጉዞ ነው። ክፉ የተባሉትን ነገሮች ሁሉ ፈጽመናቸው ክፉ ከዚህ በኋላ አያሳየን የምንልበት የፈተና ወቅት ነው። ወቅቱ ግን የፈተና ብቻ አይደለም። የትናንቱን እንደ ወንፊት የምናጠራበት ለነገውም ኃይል የምንሰንቅበት እንጂ፤ የተጠራቀመውን ችግር ሁሉ ጠርገን የምንጨርስበት የጽዳት ወቅት ነው። ለዚህም ነው ይህን የታሪክ ወቅት ፈታኙ ቅዱስ ጊዜ የምንለው፤ ቀዶ ጥገና ለሚያደርግ ሰው ያ ጊዜ ፈታኙ ጊዜ ነው። ሰመመኑም የሞት ታናሽ ወንድም ነው። በሌላ በኩል፤ ለሕመምተኛው በሽታውን ነቅሎ የሚገላገልበት የበረከቱ ጊዜም ነው። ለሀገራችንም

እንዲሁ ነው። ይህ ወቅት ውዲቱ ሀገራችን በሁሉም መስክ ከባድ ሕክምና የምታደርግበት ፈታኙ ጊዜዋ ነው። ግን የተሻለ መድኃኒትና ጤና የምታገኝበት ቅዱሱ ጊዜዋም በዚህ ውስጥ ተፀንሶ ይወለዳል።

የዒድ በዓል ከመከበሩ በፊት ባሉት የመጨረሻ ቀናት ሙስሊሞች "ዘካት አል ፈጥር"ን ማውጣት አለባቸው። "ዘካት" ለድሆች የሚሰጥ ርዳታ ነው። ይህ ዘካት ከራስ በፊት ለሌላው ማሰብን የሚያስተምረን ሥርዓት ነው። ያውም በሁለንተናዊ ዐቅሙ ከእኛ የሚያንሰውን ሰው በማሰብ፤ በሀብት፣ በዕውቀት ወይም በአካላዊ ዐቅም ሊሆን ይችላል። ይህንን ወገን ለማስቀደም ነው የፈጥር ዘካ ከዒድ በፊት መከናወን ያለበት፡፡ የአንድ ማኅበረሰብ የሥልጣኔ መገለጫዎች ከሆኑት ነገሮች አንዱ በሁለንተናዊ መልኩ የተጎዱ የማኅበረሰቡን ክፍሎች ለመደገፍ የሚያስችል ሥርዓት ለመዘርጋት እና ተግባራዊ ለማድረግ መቻሉ ነው። አካል ጉዳተኞችን፣ ድሆችን፣ ዐቅመ ደካሞችን፣ አረጋውያንን፣ ሕፃናትን፣ የተገለሉ ማኅበረሰቦችን ለመደገፍና ማኅበረሰባዊ ተሳትፏቸውን ከፍ ለማድረግ ምን እየሠራን ነው? ብለን መጠየቅ አለብን። እንደ ዒድ ያለውን የደስታ ወቅት በሚገባ ለማጣጣም ከእኛ በፊት መቅደም ያለባቸውን የማኅበረሰብ ክፍሎች ማየት፣ መንከባከብና መደገፍ አለብን። የእኛ አውራ ዶሮ ሌቱ ወደ ንጋት የመሸጋገሩን ብሥራት ከእኛ በተጨማሪ ለሌሎች መንደርተኞችም በ"አኩኩሉ"ው ማገልገል እንደሚችል ሁሉ፤ እኛም በእምነት አስተምህሮቱ መሠረት "ዘካት አል ፈጥር" በማውጣትና የተቸገሩ ወገኖቻችንን በመርዳት ድርብ ድርብርብ ተጠቃሚ እንሁን።

የዒድ በዓል በሚያስገርምና በሚያስደንቅ መልኩ የአዲሶች ኅብረትና አንድነት ግጥምጥሞሽ ነው። ከአዲስ ጨረቃ መወለድ፤ ከአዲስ የንጋት ጀንበር መፈጠር፤ ከወርቃማ ጮራዎች መፈንጠቅ ጋር በመደመር አዲስ ቀንና አዲስ ወር በአድማሱ ላይ በበዓል ድባብ ይዘረጋል።





የረመዳን ወር የጾም ፍቺ እና  የዒድ አል ፈጥር በዓል ሠላት በአብሮነት እና በአንድነት በጀመአ የሚሰገድበት ወቅትም ነው። በዓለም ዙሪያ ከቢሊዮን በላይ በሚሆኑ ሙስሊሞች በተመሳሳይ ቀን በሚከበረው የዒድ በዓል ጀመአና አብሮነት ከምንም ጊዜ በላይ ይፈለጋል፤ ይፈቀዳል፤ ይወደዳል። በዓሉ ለብቻ አይከበርም። በየአካባቢው ያለውን ሕዝብ ሁሉ ሊሰበስብ በሚችል ቦታ ላይ በጀምአ በመስገድ እና ተክቢራ በማሰማት ይከበራል። በመንደር፣ በሰፈርና በቤት ውስጥም ከቤተሰብ፣ ከጎረቤት ከወዳጅ ዘመድ በተጨማሪ ከሌሎች የእምነት ተከታዮች ጋር በመሆን በሃላል ምግብና መጠጥ በዓሉን በአንድነትና በጋራ በደስታ ያከብሩታል፤ ያሳልፉታል። ኢትዮጵያውያን በሚከተሉት ሃይማኖት ሳቢያ በመካከላቸው የሚለያይና የሚያራርቅ ግንብ ከመገንባት ይልቅ እምነታቸውን በየግላቸው በመያዝ በአንድነትና አብሮነት ዘመናት የተሻገሩ ታላቅ ሕዝቦች ናቸው። የኢትዮጵያን ችግሮች ለማለፍና ከደስታው ወቅት ለመድረስ ጀምአ፤ ኅብረትና አንድነት ወሳኝ ነገር ነው። ኢትዮጵያ ከማንኛውም ጊዜ በላይ ዛሬ እንደ ዒድ ጀምአ ያለ አንድነት ትፈልጋለች። ከባድ አቀበት በመውጣት ላይ በመሆኗ ጉልበት እንድታመጣ በአንድ ብቻ ሳይሆን በሁለቱም ሳንባዎቿ መተንፈስ ይኖርባታል። ለዒድ ሰላት ሕዝበ ሙስሊሙ አንድ ሆኖ "ማነህ? ማነሽ? ከየት ነህ? ከየት ነሽ?" ሳይል ለአንድ ዓላማ በጀምአ እንደሚወጣው ሁሉ ኢትዮጵያውያንም "ማነህ? ማነሽ? ከየት ነህ? ከየት ነሽ?" ሳንል ለአንድ ሀገራዊ ዓላማ አንድ ሆነን ከምንሰለፍበት ወቅት ላይ እንገኛለን። ለሀገራዊ ጥሪ ሀገራዊ ምላሽ መስጠት ይጠበቅብናል።

በሀገራችን የሚከሠቱ ግጭቶች፣ መፈናቀሎች፣ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ችግሮች ሁሉ እንደረመዳን ጾም ቀናቸውን ቆጥረው ይጠናቀቃሉ። ያልፋሉ። ኢትዮጵያም እንደ ዒድ የደስታ ዘመን ይጠብቃታል። ረመዳን ምንም እንኳን ፈታኝና ከባድ ወቅት ቢሆንም፤ ብዙ አረጋውያን ሙስሊሞች ግን ሲያልቅ ትዝታው በአእምሯቸው ተሥሎ ይቀራል። ጽናትና ቆራጥነታቸውን ያስታውሱበታልና። ይህ ሀገራችን እያለፈችበት ያለችው ወቅትም ያልቃል።

ይሸኛል። በጽናትና በሀገራዊ ስሜት የጸኑ ዜጎቿ ሁሉ ወቅቱን በተጋድሎ ታሪክ ትናንት በማለት የሚያስታውሱት ትዝታ ይሆናል።

በመጨረሻም፤ ለኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች በሙሉ ለ1440ኛው የዒድ አል ፈጥር በዓል እንኳን አደረሳችሁ! በማለት በዓሉ የደስታ፣ የሰላም፣ የይቅርታ፣ የፍቅር እና የአንድነት እንዲሆንላችሁ መልካም ምኞቴን እገልጻለሁ!

**ኢድ ሙባረክ!**
**ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራ፤**
**ተከብራና በልጽጋ ለዘላለም ትኑር!**
**ፈጣሪ ኢትዮጵያንና ሕዝቦቿን ይባርክ!**





# የብሔራዊ የችግኝ ተከላ ቀን መልእክት

ሐምሌ 19/2011 ዓ.ም.

ለብዙ ዘመናት ከኢትዮጵያ ሰማይ ስር ሲስተጋባ የኖረውና ‘ለምለሚ ሀገሬ’ የሚለው ዕድሜ ጠገብ ዜማ የልጆቻቸን የዛሬ እውነታ፤ የእኛ ደግሞ ከጆሯችን ሁሌም ያለ ቅርብ ትዝታ ነው። ትላንት እውነት እና ሐሴት የነበረው፤ ዛሬ ግን ምኩን እና ቁጭት ሆኖ የቀረው ዝማሬ በሁሉም ኢትዮጵያዊ ኅሊና ውስጥ አብዝቶ ይመላለሳል። እውነት ነው! ሀገራችን ለምለም ነበረች። ዛሬ ግን አይደለችም። ምክንያቱም አባቶቻችን ያቆዩልንን እኛም በተራችን ለልጆቻችን አላቆየንም። እናም ልምላሜዋን እና አረንጓዴ ውበቷን ከትዝታ ብቻ አወዳጅተን አደራችንን በልተናል። ዜማዎቻችን ብቻ ሳይሆኑ ተረቶቻችንም ሀገራችን በደን የተሞላች እንደነበረች ይነግሩናል። በተረቶቻችን ውስጥ የምናገኛቸውን ብዙዎቹን እንስሳት ዛሬ በአካባቢያችን አናገኛቸውም። በየቋንቋችን ስማቸው ብቻ የቀረው የዛፍ ዓይነቶች ሀገራችን ዓይነተ ብዙ ደን እንደነበራት ቋሚ ምስክሮች ናቸው።

የዛፎች ጉዳይ ለእኛ የውበት ጉዳይ ብቻ አይደለም። የህልውናም ጉዳይ ነው። የእምነት ጉዳይ ነው። የባህል ጉዳይ ነው። የኢኮኖሚ ጉዳይ ነው። ዛፍ ማለት እኛ ነን። እኛ ማለት ያለዛፍ ምንም ነን። የበረሓማነት መስፋፋትና የአየር ንብረት መዛባት ያስከተለው ቀውስ ሀገራችንን አደጋ ላይ ከመጣል አልፎ የስሟ መገለጫ እስከመሆን ደርሷል። ባለፉት ዐርባ ዓመታት ብቻ እያሠለሰ

የሚመታን ድርቅ በምግብ እህል ራሳችንን ለመቻል የምናደርገውን ትግል ተፈታትኖታል። ወገኖቻችንንም ከክብር ማማ አውርዶ የተረጂነት ወለል ላይ አስቀምጦብናል። የዝናብ ወቅቶቻችን እየተዛቡ፤ ለጎረቤት ይተርፉ የነበሩት ወንዞቻችን እየጎደሉ፤ ምንጮቻችን እየነጠፉ፤ ወይና ደጋው በረሐ፤ ደጋው ቆላ እየሆነ የህልውና አደጋ ጋርጦብናል። የራሳችንን ህልውና በራሳችን ጥርስ ግጠነው የነበረውን አፍርሰን እንዲያ ያልነበርን መስለናል። ከተሞቻችን በአንድ በኩል በኢንዱስትሪዎችና በተሽከርካሪዎች ጢስ ይበከላሉ። በሌላ በኩል፤ ዛፎቻቸውን ጨርሰው ከአንድ ፀሐይ ቢሆኑም የሦስት ፀሐይ ያህል በገረረ ንዳድ ተንቀልቅለው ህያው በድኑን ያቃጥላሉ። ከተሞቻችን የከተማ መቃጠያ መሆናቸው ቀርቶ የከተማ መኖሪያ እንዲሆኑ ደናማ ከተሞች መሆን አለባቸው።

ወገባችንን አስረን የምንሠራቸው ግድቦች በደለል እየተሞሉና በውኃ እጥረት እየተመቱ ልፋታችንን መና እያስቀረነው ነው። እጃችንን በእጃችን እየበላን ጸጸት ቁጭታችን ብዙ ነው። ይህ ቁጭት እና መብሰክሰካችን የ"ይቻላል" ስሜታችንን አቀጣጥሎ ወደ አረንጓዴ ሰገነታችን በኃይል ከአንደረደረን እሰየው፤ ቁጭት ብቻ ከሆነ ግን ዋይታችንን የማይቋጭ ያው ከንቱ ቁጭት ብቻ ነው። ሐይቆቻችን የነበራቸውን ቦታ እየለቀቁ፤ አንዳንዶቹ ከነባር ይዞታቸው ሲሸሹ ሌሎቹ ጨርሰው እየደረቁ ነው። ሐዘናችን መሪር ሆኗል። ለእነ ሀረማያ ያፈሰስነው እንባ ገና ከጉንጫችን ሳይደርቅ የሌሎች ሐይቅ ጅረቶቻችን ህልውና ጉዳይም ለሌላ ሐዘን እያጨን ነጋችንን ጽልም አርጎታል። በዚህም የተነሣ በዓሣ ሀብታችን ላይ ፈተና እየተደቀነ ነው። በሐይቆቻችን ላይ ሠፍረው ይኖሩ የነበሩት አዕዋፍ ሀገር ጥለው እየኮበለሉ፤ በሐይቆች ውስጥ የሚኖሩ እንስሳትም ዘራቸው እየተመናመነ ነው። እንባችንን ከዐይናችን ለመክላት እና ዋይታችንን ወደ ዝማሬ ለመቀየር ማን ይምጣ? ለእኛ ሕመም እና ሥቃይ መሻርያው እና ፈውሱም ያለው በእኛው እጅ ነው።





ዓለም ያደነቃቸው ታላላቅ ቤተ እምነቶቻችን የተሠሩት ከሀገር በቀል ዛፎች በተገኙ እንጨቶች ነበር። በውስጣቸው የምናገኛቸው ቅርሶችና ንዋያተ ቅዱሳት የተዘጋጁት ከኢትዮጵያውያን እንጨቶች ነበር። ሥዕሎቻችን፣ ቅርጾቻችንና የወግ ዕቃዎቻችን በሙሉ የደኖቻችን ውጤቶች ነበሩ። ቀደምቶቻችን የተጠበቡባቸው ዓምዶችና ወጋግራዎች፣ በሮችና መስኮቶች፣ ጣራዎችና አቴናዎች የደኖቻችን ትሩፋቶች ነበሩ። ትውፊታዊ ክዋኔዎቻችን ደኖቻችንን አበክረው ይፈልጓቸዋል። አረንጓዴው ዓለማችን የሁለነገራችን አልፋ እና ኦሜጋ ነው። ሰርግ ሐዘናችን፤ ስግደት ሶላታችን፤ ልደት ሞታችን፤ አምልኮ ከበራችን ወግ እና ጫወታችን እንኳን ከዛፍ ደኖቻችን ጋር እጅጉን ተሰናስሏል። ሕይወታችን ከደኖቻችን ጋር የተያያዘ ነው። የደኖቻችን መመናመን በጎ ዕሴቶቻችን እንዲመናመኑ አድርጎብናል። ዕርቅ፣ ሽንጎ፣ ውይይት፣ ታሪክ ነገራ፣ በባህላችን ውስጥ የሚከወኑት በዋርካዎቻችን ሥር ነው።

በሁሉም ኢትዮጵያዊ ልብ እና ትውስታ ውስጥ አረንጓዴ ደኖቻችን የደግነት፣ የፍቅር፣ የሰላም፣ የሕይወት እና የተስፋ ውካዮች ናቸው። በገጠሬው ሕይወትና በከተሜው ትዝታ ውስጥ የሚገኙት የዱር ፍሬዎች የባህላችን አካላት ነበሩ። ሌላው ቀርቶ ባህላዊ የሙዚቃ መሣሪያዎቻችን እንኳን የሚዘጋጁት ከደን ውጤቶቻችን ነው። በባህላችን የአንድ ዋርካ መውደቅ፤ የአንድ እንጨት መውደቅ ሳይሆን የአንድ ትልቅ ሰው፤ የአንድ ትልቅ ሽማግሌ መውደቅ ምልክት ነው።

በሀገራችን ብዙ ወገኖቻችን ኑሯቸው በደኖችና በደን ውጤቶች ላይ የተመሠረተ ነው። የደን ፍሬዎችን ለቅመው፤ የደን ቅጠሎችን ሰብስበው፤ የደን ውጤቶችን ቆርጠው፤ የደን ውጤቶችን ወደ ልዩ ልዩ ዕቃዎች ቀይረው፤ በመሸጥ ኑሯቸውን የመሠረቱ ናቸው። የሀገሪቱ ዋነኛ የውጭ ምንዛሪ ምንጮች በአንድም በሌላም መንገድ ከደን ውጤቶቻችን ጋር የተያያዙ ናቸው።

ደኖቻችንና የዱር እንስሶቻችን የቱሪዝም ገቢያችን መሠረቶች፤ የዐይናችን ማረፊያ ጌጦች፤ የባህል ወግ እና እምነታችንም መከሠቻ ናቸው።

እነዚህን ሁሉ ስንመለከት ነው የዛፍ ጉዳይ ለእኛ የቅንጦት ጉዳይ የማይሆነው፤ ከዚህ በፊትም እንደምለው ይህች ሀገር ከአባቶቻችን የወረስናት ብቻ ሳትሆን ከልጆቻችንም የተዋስናት መሆኗንም ማሰብ ተገቢ ነው። እኛም በተራችን ለልጆቻችን ስናስረከባት ከነበረሓዋ፣ ከነንዳዷ፣ ከነድርቋ እና ከነደለሏ እንዳይሆን የቤት ሥራችንን እንሠራ ዘንድ ይገባናል። ከልጆቻችን ነፍስ ላይ የነጠቅነውን በምቹ ሀገር የመኖር የህልውና መሠረት ሳንውል ሳናድር ከመመለስ እና ከመተካት የሞራል፣ የእምነት እና የሰብአዊነት ጽኑ ጥያቄ ጋር የተፋጠጥንበት ወቅት ላይ ደርሰናል። የሀገራችንን የደን ሽፋን እንዲያገግም ማድረግ ህልውናችንን ማጽናት፤ እምነታችንን መጠበቅ፤ ባህላችንን ማበልጸግ፤ ኢኮኖሚያችንን ማዳበር ነው።

አራት ቢሊዮን ችግኝ ለመትከል ስንነሣ ለህልውናችን፣ ለእምነታችን፣ ለባህላችንና ለኢኮኖሚያችን ስንል ታጥቀን መነሣታችንም ጭምር ነው። ሕዝቡ ከሰሜን እስከ ደቡብ፣ ከምዕራብ እስከ ምዕራብ ያሳየው ተነሣሽነት ይህን ዓላማ እንደተረዳው የሚያሳይ ነው። ይህንን ሀገራዊ ዓላማ ለማሳካት እስከአሁን በአደረግነው አረንጓዴ አሻራን የማሳረፍ ርብርብ ቢልዮኖች ችግኞችን ተክለናል። ሰኞ ሐምሌ 22 ቀን በምናደርገው ብሔራዊ የችግኝ ተከላ ቀን 200 ሚሊዮን ችግኞችን በአንድ ቀን በመትከል የዓለምን ክብረ ወሰን እንሰብረዋለን። የያዝነው ክረምት ከማለፉ በፊትም አራት ቢሊዮን ችግኞችን ተክለን ግባችንን እንመታለን።

ይህን ስኬት ለማምጣት የሚኒስቴር መ/ቤቶችና የክልል አመራሮች፣ የሃይማኖት አባቶች፣ በችግኝ ማፍያ ጣቢያዎች የሚገኙ ሠራተኞች፣ የግብርና ባለሞያዎችና ምሁራን፣ የኪነ ጥበብ ባለሞያዎች፣ ኮሜዲያን፣ የሚዲያ





ሐላፊዎችና ጋዜጠኞች፣ ነጋዴዎችና ታላላቅ ኮርፖሬሽኖች፣ ወጣቶችና ሕፃናት፣ አዳጓዦችና የጉልበት ሠራተኞች ለአደረጉት ምትክ የማይገኝለት አስተዋጽዖ በራሴና በኢፌዲሪ መንግሥት ስም ላመሰግን እወዳለሁ! ለአንድ አገር ጉዳይ፣ አንድ ሆነን በዓላማ ከተነሣን የሚሳነን ነገር እንደማይኖር የአረንጓዴ አሻራ ስኬታችን ምስክር ነው። ከደን የተራቆተችውን ሀገራችንን ለማልበስ እንደተነሣነው ሁሉ ከሰላም ከፍቅርና ከይቅርታ እየተራቆተች የመጣችውን ሀገራችንንም አንድ ሆነን ማልበስ አለብን። አራት ቢሊዮን ዛፍ በአንድ ክረምት መትከል ከቻልን አራቱን አስፈላጊ ሀገራዊ ዕሴቶች ሰላምን፣ ይቅርታን፣ ፍቅርንና አንድነትን መትከልና ማሳደግ አያቅተንም። በፍጹም!

በቀሪው ጊዜ የተከልናቸውን ችግኞች በመጠበቅ፤ በመንከባከብና ለፍሬ በማብቃት መትከል ብቻ ሳይሆን ማሳደግም እንደምንችል እናሳይ፤ ዛፍ ብሔር፣ ቋንቋ፣ እምነትና ርእዮተ ዓለም የለውም። ሁሉም ዛፍ የሁላችንም ነው። የሠራነው ሥራም ከእነዚህ ሁሉ በላይ ነው። ክብካቤና ጥበቃውም እነዚህን ልዩነቶች ሁሉ አልፎ ሊደረግ የሚገባው ነው። ሐምሌ 22 ቀን ሁላችንም ማልደን በመውጣት፤ ችግኞችንም በተገቢ መንገድ በመትከል፤ አረንጓዴ አሻራችንን እናሳርፍ! ነገንም ዛሬ እንትከል!

**ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራ፤**
**ተከብራና በልጽጋ ለዘለዓለም ትኑር!**

**ፈጣሪ ኢትዮጵያንና ሕዝቦቿን ይባርክ!**

# ለአረንጓዴ አሻራ ተሳታፊዎች ያስተላለፉት መልእክት

ሐምሌ 23/2011 ዓ.ም.

**ኢትዮጵያውያን አንድ ሆነው ከተነሡ፤ ከአሰቡት ሳይደርሱ አይመለሱ፤**

**ውድ ኢትዮጵያውያን ወገኖቼ ፡-**

- ስለማይበገረው ጽናታችሁ እና ሁሉን ማድረግ ስለሚችለው አስደናቂ ዐቅማችን በተለየ አክብሮት እና ፍቅር እጅ እነሣለሁ!
- በየትኛውም አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ሆነን እንኳን ሀገራችንን የሚመለከቱ ዐበይት ጉዳዮች ሲገጥሙን ከመቅጽበት ዐይን ለሚያጋምደን፣ ያለምንም ልዩነት እንደ አንድ እናትና ልጅ ለሚያዛምደን እና ያለመለያየት ለሚያዋሕደን ዘመን አይሽሬ ኢትዮጵያዊ መንፈሳችን ያለኝን የማይናወጥ ፍቅር በክብራችሁ ጥላ ሥር ሆኜ በክብር እገልጻለሁ።
- መቼም ማንም የትኛውንም የከፋት ሴራ የሚሥራ የጥፋት አበጋዝ አብሮነታችንን ሊያጠለሽ ቢጥር እንኳን አብሮነታችን ከነፍሳችን ውስጥ የተሸመነ እንጂ ከሥጋችን ላይ የተጎነጎነ አይደለምና አብሮነታችንን ላጸደለው የአረንጓዴ አሻራ ድላችሁ የተለየ ምስጋናዬን በፍቅሬ ሙዳይ ሞሽሬ እነሆ ልኬያለሁ።





## ሀገር ታመሰግናለች! እኔም አመሰግናለሁ!

የኢትዮጵያን አረንጓዴ ጸጋ በመመለስ አረንጓዴ አሻራ እንድናሳርፍ ያቀረብኩትን ጥሪ በመቀበል ሐምሌ 22 ቀን 2011 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ሕዝብ በነቂስ ለችግኝ ተከላ ወጥቷል። ከጨቅላ ሕፃናት እስከ ዘጠና ዓመት አዛውንት፤ ከጎዳና ተዳዳሪዎች እስከ ዲፕሎማቲክ ማኅበረሰብ፤ ከታክሲ ተራ አስከባሪዎች እስከ ጳጥታ አስከባሪዎች፤ ከገበሬዎች እስከ ግብርና ባለሞያዎች፤ ከልማት ጣቢያ ሠራተኞች እስከ ከፍተኛ ኤክስፐርቶች፤ ከተማሪዎች እስከ መንግሥት ባለሥልጣናት፤ ከገጠር እስከ ከተማ፤ ከሀገር ቤት እስከ ዳያስፖራ፤ ከድምፃውያን አስከ ተዋንያን፤ ከአትሌቶች እስከ ብሔራዊ ቡድን ተጨዋቾች፤ ከጋዜጠኞች እስከ ፊልም ባለሞያዎች፤ ከሰሜን እስከ ደቡብ፤ ከምዕራብ እስከ ምሥራቅ ያልተሳተፈ የኅብረተሰብ ክፍል አልነበረም። ይህ የተሳትፎ ማእበል እና የ"እምቢ ለሀገሬ" ሆታም በታሪክ ማኅደር ላይ መቼም አይረሳም።

ሕዝቡ አረንጓዴ አሻራውን ለማኖር የነበረውን ትጋትና ቆራጥነት የሚያሳዩ አስደናቂ ክንዋኔዎችን አይተናል። የአረንጓዴው አሻራ አርበኛ ከማለዳው 12 ሰዓት አስቀድሞ ወጥቷል። አያሌ ባለሀብቶች መኪኖቻቸውን በራስ ተነሣሽነት አንቀሳቅሰዋል። ዳያስፖራዎች በገንዘባቸው አግዘዋል። ኮርፖሬሽኖች ሐላፊዎቻቸውንና ሠራተኞቻቸውን አሠማርተዋል። በኢትዮጵያ የሚገኙ ዲፕሎማቶችና የዓለም አቀፍ ድርጅቶች ሠራተኞች ራሳቸውን አደራጅተው አሻራቸውን ለማኖር ወጥተዋል። ሙሽሮች በሰርጋቸው ዕለት ሱፍ፤ ቬሏቸውን ለብሰው ተገኝተዋል። ችግኝ ተካዮችን ለማበረታታት ቀረርቶ፤ ሽለላ፣ ፉከራ፣ ባህላዊ ዘፈን እና እልፍ አእላፍ የኅብር ሆታ በመላ ኢትዮጵያ፣ በመላ ኢትዮጵያውያን ቋንቋ እና ባህል ከጫፍ እስከ ጫፍ ተስተጋብቷል። በአንዳንድ አካባቢዎች የሃይማኖት አባቶች ተከላውን በጸሎት አስጀምረዋል።

እናቶች ምግብና መጠጥ አዘጋጅተው ለዛፍ ተካዮች አቅርበዋል። ወደ ውጭ የሚጓዙ ሰዎች የዜግነት ግዴታቸውን ለመወጣት በዋዜማው ተክለዋል። ሚዲያዎች በሀገር አቀፍ ደረጃ ዜናውን ለመሸፈን ተቀናጅተው ሠርተዋል። ዓይነ ሥውራን በኬን፣ አካል ጉዳተኞች በዊልቸር፣ ወላጆች አራስ ልጆቻቸውን አዝለው ለተከላው ተሠማርተዋል። ልጆች በእናታቸው እቅፍ፣ አረጋውያን በከዘራ ወደ ተራሮች ተምመዋል። ችግኝ በአጠረባቸው ቦታዎች ዜጎች በገዛ ገንዘባቸው እየገዙ ሀገራዊ ተልእኳቸውን ተወጥተዋል። ሐምሌ 22 ማለዳ ከኢትዮጵያ ሰማይ ሥር የነገሠው ትጋት፣ አብሮነት፣ ፍቅር፣ ተነሣሥኦት፣ ጽናት እና የእናሳካዋለን ስሜት ችግኝ ከመትከልም በላይ የሚገለጽ ድንቅ ድል አጎናጽፎን በድል ተጠናቅቋል።

የሐምሌ 22ቱ ሀገር አቀፍ የችግኝ ተከላ ሕዝቡ በአንድነት ወጥቶ ችግኝ የተከለበት ብቻ ሳይሆን ሐሳቡን የገለጠበትም አጋጣሚም ነበር። ሀገሩን የሚወድ፤ ለሀገሩ የሚጠበቅትን ሁሉ ለማድረግ ዝግጁ የሆነ፤ ለትክክለኛ ዓላማ የሚያሠማራው ሲያገኝም አንድ ሆኖ የሚነሣ ሕዝብ እንዳለን አይተናል። ከመከፋፈል ይልቅ አንድነት፤ ከግላዊነት ይልቅ ሕዝባዊነት፤ ከራሱ ይልቅ ለሀገሩ፤ ከሆዱ ይልቅ ለክብሩ የሚሞት ሕዝብ እንዳለንም ነግሮናል። ከትናንሽ አጀንዳዎች ይልቅ ታላላቅ ሀገራዊ ግዳጆች የሚማርኩት ሕዝብ መሆኑን ገልጦልናል። ከአቧራ ይልቅ ለአሻራ ቦታ የሚሰጥ ሕዝብ መሆኑን በማያወላዳ መልኩ አስረግጦ አስረድቶናል። ታላቅ ሐሳብ የሚማርከው ታላቅ ሕዝብ መኖሩን አመላክቶናል። ችግር ነቅሎ ችግኝ የሚተክል ሕዝብ እንዳለንም በውል ተረድተናል።

ይህ ታላቅ ሀገራዊ ተልእኮ እንዲሳካ የበኩሉን ያልተወጣ የኅብረተሰብ ክፍል የለም። ነገር ግን ከጣት ጣት ይበልጣል እንደሚባለው የአንበሳውን ድርሻ የሚወስዱ ወገኖች አሉ። ሂደቱን የመራው ብሔራዊ ኮሚቴ አባላት፤ ሂደቱን ያስፈጸሙት የቴክኒክ ኮሚቴ አባላት፤ መረጃው የተሰባሰበበትን መንገድና ሶፍት ዌር ያዘጋጁ ባለሞያዎች፤ ከክልል እስከ ወረዳ ያሉ አመራሮች እስከ ችግኝ መትከያ ጣቢያ ድረስ በተዘረጋው መረብ ተሠማርተው መረጃውን እያጣሩ ሲያሰባስቡ የነበሩ የመረጃ ወኪሎች፤ የተስተካከለ መረጃ ብቻ እንዲመዘገብ ሲከታተሉ የነበሩ የመረጃ አጣሪዎች፤ በሀገር አቀፍ ደረጃ ተቀናጅተው ሲሠሩ የነበሩ መላው የሀገራችን ሚዲያዎች፤ ለኅብረተሰቡ ትምህርት ሲሰጡና ሲያቀናጁ የነበሩ የልማት ጣቢያ ሠራተኞች፤ የሃይማኖት አባቶች፣ የኪነ ጥበብ ባለሞያዎች፣ የየመሥሪያ ቤቱ የሥራ ሐላፊዎች፤ ለአከናወናችሁት የላቀ የመሪነት ተግባር በራሴና በኢፌዲሪ መንግሥት ስም የላቀ ምስጋናዬን አቀርባለሁ!

ይህ ሀገራዊ የአረንጓዴ አሻራ ቀን ኢትዮጵያውያን አንድ ሆነው ከተነሡ፤ ያሰቡትን ሳያሳኩ እንደማይመለሱ ለሺኛ ጊዜ መልሰው ያረጋገጡበት ነው። 200 ሚሊዮን ችግኝ ለመትከል ዕቅደን ከ353 ሚሊዮን በላይ ችግኞች ተክለናል። የችግኝ እጥረት ባይገጥመንና ቀኑ ባይመሽ ኖሮ እንደ ሕዝቡ አወጣጥ ከዚህም በላይ የመሥራት ዐቅም ነበረን። ከዚህ ሥራችን በበጎው እንደተደሰትን ሁሉ ከስሕተቶቻችንም እንማራለን። ይህ ተግባር የአንድ ቀን ዘመቻ ብቻ አይደለም። ክረምቱን በሙሉ የምንሠራው ነው። ሀገራችን እንደ ስሟ ለምለም እስክትሆን ድረስ በየዓመቱ እንቀጥልበታለን። ያገኘናቸውን በጎ ነገሮች አጠንክረን፤ ድክመቶቻችንን አርመን ቀጣዩን የተሻለ እናደርገዋለን። ከሀገራችን ጥቁር ሰማይ ሥር በጥቁር መዳፍ የተሸመነ አረንጓዴ ሸማ በጥቁር አፈራችን ላይ እንዘረጋለን። የታላቅነታችን ምስጢር የተሰቀለችበትን ክር ጠንቅቀን የምናውቅ ሕዝቦች ነንና ከአዝማናት ታላቅነታችን ጋር እንደገና እንገናኛለን።

መውለድ ብቻ ልጅን እንደማያሳድገው ሁሉ፤ መትከል ብቻ ዛፍን አያጸድቀውም። የወለድናቸውን ማሳደግ፤ የተከልናቸውንም መንከባከብ አለብን። ሕዝቡ በተከላው ቀን ቃል በገባው መሠረት የእገሌ ሥራ ነው

ሳይል የተከላቸውን ዞሮ ማየት፤ መንከባከብና ከጥቃት መከላከል አለበት። ባለሀብቶች ባለሞያ መድበው የተከሏቸውን ችግኞች እንደሚያሳድጉ አምናለሁ። ወጣቶች የተከሏቸውን ችግኞች ለማየት ወደ ተራሮች ስፖርት እየሠሩ እንደሚወጡ ተስፋ አደርጋለሁ። የመንግሥት ተቋማት ሠራተኞችም ተራ ገብተው ችግኞቻቸው የት እንደደረሱ እንደሚጠይቁ እርግጠኛ ነኝ። የተከልናቸውን ችግኞች የማሳደግ ሀገራዊ ዐቅማችን ከ50 በመቶ በታች ነው። ይህን ውሱንነት በመቅረፍ ቢያንስ በቀጣዮቹ ዓመታት ወደ 70 በመቶ ማሳደግ አለብን። ለዚህ ደግሞ ወልዶ ማሳደግ የሚያውቅበት የሀገሬ ሕዝብ ተክሎ በመንከባከብ ታሪክ እንደሚሠራ ምንም ጥርጥር የለኝም።

ለአረንጓዴ አሻራ ቀን ስኬት የሚጠበቅባችሁን ያደረጋችሁ ሁሉ  በደማቅ ቀለም ታሪክ ጽፋችኋልና በድጋሚ አመሰግናችኋለሁ!

**ኢትዮጵያ በታሪክ ሠሪ ልጆቿ ታፍራና ተከብራ ለዘለዓለም ትኑር!**

**ፈጣሪ ኢትዮጵያንና ሕዝቦቿን ይባርክ!**





# የ1440ኛው ዓመተ ሒጅራ የኢድ አል አድሐ በዓል መልእክት

ነሐሴ 4/2011 ዓ.ም.

በመላው ዓለም በሚገኙ ሙስሊሞች በታላቅ ድምቀት በየዓመቱ ከሚከበሩ ሀይማኖታዊ በዓሎች መካከል ኢድ - አል አድሃ አንዱና ዋነኛው ነው። ኢድ አል አድሃ የመሥዕዋት (የእርድ) በዓልም በመባል ይታወቃል። በእስልምና የዘመን አቆጣጠር መሠረት የኢድ አል ፈጥርን በዓል ተከትሎ ከዓሥር ሳምንታት በኋላ ወይም በዓሥራ ሁለተኛው የዙል ሂድራ ወር ውስጥ የሚከበረው የዒድ አል አድሃ በዓል የሐጅ ሥርዓት በሚከናወንባቸው አምስት ተከታታይ ቀናት ውስጥ የሚካተት ታላቅ ሃይማኖታዊ ሥርዓት ነው።  የኢድ አል አድሃ በዓል የተካተተበት የሐጅ ሥርዓት ታላላቅ ተምሳሌታዊ ዕሴቶችን ያቀፉ በርካታ ኩነቶችን አጣምሮ ከመያዙም ባሻገር፤ ከአምስቱ የእስልምና መሠረቶች መካከል አንዱ የሆነውና ማንኛውም ሙስሊም የገንዘብና የጉልበት ዐቅሙ እስከ ፈቀደ ድረስ በሕይወት ዘመኑ ቢያንስ አንድ ጊዜ ሊያከናውነው የሚገባውን የሐጅ ሥርዓትም ይፈፀምበታል። የኢድ አል አድሐ በዓል የተካተተበት የሐጅ ሥርዓት ዘርና ቀለም፣ ሃብታምና ደሀ፣ ሴትና ወንድ ተብሎ መለያየት ሳይኖር ከተለያዩ የዓለም ክፍሎች የተሰባሰቡ ሙስሊሞች በአንድ ሥፍራ በአንድነት በፈጣሪያቸው ፊት በመቆም መራራቅን ሳይሆን መቻቻልን፣ ጠላትነትን

ሳይሆን ዓለም አቀፍ ወንድማማችነትን፣ ጠብና ሁከትን ሳይሆን ሰላምና ፍቅርን ከፍ በማድረግ መታዘዝንና መሥዋዕትን በእምነትና በተግባር፤ በስሜትና በምግባር ከራሳችን ጋር የምናቆራኝበት ታላቅ የመታሰቢያ በዓል ተደርጎም ይወሰዳል።

## ኢድ ሙባረክ!

በእስልምና የዘመናት ታሪክ ውስጥ ከነቢዩ ላህ ኢብራሂም እስከ ነቢዩ መሐመድ (ሠ.ዓ.ወ)፣ ከአደም እና ሐዋ እስከ ጀርና እስማኤል፣ በሕይወት እና ሞት፣ በሥጋዊ እና በመንፈሳዊ ተምሳሌቶች እምነት እና ተስፋ፣ ፈተና እና ደስታ ጎልቶ የተገለፀበት ሀይማኖታዊ ሥርዓት ነው። ሐጅ፤ ይህንን እውነታ የነቢያት ሁሉ ቀደምት አባት የሆኑት ነቢዩ ላህ ኢብራሂም (አላሂሰ ሠላም) በእርጅና ዕድሜ የታደሉትን ልጃቸውን እስማኤልን መሥዋዕት አድርገው እንዲያቀርቡ በፈጣሪ መታዘዛቸው፤ በፈጣሪ ትዕዛዝ ቅስማቸው ቢሰበርም በእምነታቸው ጸንተው ትዕዛዙን ለመፈፀም መፍቀዳቸው፤ በዚህም የተነሣ ፈጣሪ በልጃቸው ምትክ የሚታረድ በግ ያቀረበላቸው መሆኑ፤ በዚህም ከሐዘን ወደ ደስታ መሻገራቸውን አሳይቶናል። በመካ ዙሪያ ቀበሌዎች በሚገኙት በሳፋና በማርዋህ አነስተኛ ኮረብታዎች ሰባት ጊዜ በመመላለስ በጸሎት እና በዝክር የሚከናወነው የነቢዩላህ ኢብራሂም (አላሂሰ ሠላም ) ሚስት ግብፃዊቷ አጃር ወይም አጋር ጡት ከሚጠባ ልጇ እስማኤል ጋር በብቸኝነት መሸኟ፤ በዚያ ምድረ በዳ የሚላስ እህል የሚቀመስ ጠል አጥታ በሠፊያና በመርዋ ኮረብቶች መካከል መባዘኗ በምድረ በዳ የዘምዘም ውኋ ምንጭ የፈለቀላት መሆኑ፤ ሌላም ሳይሆን ያንኑ እምነት እና ተስፋ፣ ፈተና እና ደስታ ማሳያ ተምሳሌት ነው።

ዛሬም በሀገራዊው የለውጥ ጉዞና እርምጃ ተስፋ ማድረግን ሀብትና እምነቱ ያደረገ ሕዝብ በዚያው መጠን በሚያጋጥሙ ፈተናዎች ተስፋ መቁረጥ ቢጫነው አይገርምም። ተስፋ መቁረጥ ግን ከፈተና አያድንም። ወገንንም ወደ ድል አያሻግርም። በእምነታቸው በጸኑ ዜጎች እንጂ በተስፋ ቆራጮች ሀገርና ሕዝብ ፈተናቸውን አልፈው መሰናክሉን ተሻግረው ለድልና ለደስታ አይበቁም። በእንዲህ ዓይነቱ ወቅት ሀገርና ሕዝብ አሻጋሪና ሩቅ ተመልካች ባለራእይ መሪ ያስፈልጋቸዋል። ለሰላም እና ለፍትሕ መሥዋዕትነትን ለመክፈል ዝግጁ የሆነ መሪ፤ ይህ ሲሆን በድካም ተሸንፈው በጉዞ መሐል የወደቁት እና በስብሰው አፈር ወደመሆን ሊሸጋገሩ የተቃረቡት አፈራቸውን ከላያቸው በማራገፍ ቀጥ ብለው ዳግም አብረውን መጓዝ ይጀምራሉ። ሰላም ረዥሙ የታሪክ ጊዜ ነው። ችግሮቻችን ሁሉ በአንድ ጀንበር ሊፈቱ እንደማይችሉ ተገንዝበን፤ የጋራ ችግራችንን በጋራ ለመፍታት ቆርጠን ከተነሣን እንደ ነቢዩ ላህ ኢብራሂም እንደ አጋርና ኢስማኤል ዘመን ተሻጋሪ ሰላምና ብልጽግናን ማረጋገጥ ለእኛ ለኢትዮጵያውያን እጅግም ከባድ አይሆንብንም።

## ውድ ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች!

በላቀ ደረጃ ኅብረት፣ በልዩነት ምትክ አንድነት ከመነሻው አንስቶ እስከ የሚዘልቀው የኢድ አል አድሃ በዓል እና የሐጅ ሥርዓት ለእኛ ለዚህ ዘመን ኢትዮጵያውያን የመልካም ዕሴት መማሪያ ሊሆን ይችላል። በርግጥም ግለኝነትና ስግብግብነት፣ ጽንፈኝነትና ግትርነት ሰፍቶ በተንሰራፋበት ወቅትና ዘመን መራራቅን ሳይሆን መቻቻልን፣ ጠላትነትን ሳይሆን ዓለም አቀፍ ወንድማማችነትን፣ ፀብና ሁከትን ሳይሆን ሰላምና ፍቅርን ከፍ በማድረግ በእምነትና በተግባር፣ በስሜትና በምግባር ከእኛነታችን ጋር የሚያቆራኝ ሥርዓት እጅግ ሲበዛ አስፈላጊ ነው።

በዚህ ረገድ፤ በሐጅ ሥርዓት ሦስተኛ ምዕራፍ የተካተተው የአረፋ ሥርዓት በአንድ በኩል ነቢዩ መሐመድ (ሠለላህ አላይህ ወሰላም) ምድርን ተሰናብተው ወደ ዘለዓለማዊ መኖሪያቸው ከማምራታቸው በፊት የመጨረሻውን የቁርዓን

አንቀፅ በአረፋ ኮረብታ ማውረዳቸው ሲዘከርበት፤ በሌላ በኩል ደግሞ የፍርድ ቀን መኖሩን እና በዚያም ወቅት ገላችንን ከምንሸፍንበት ጨርቅ ባሻገር አንድም ሀብት ንብረት እንደማይከተለን ማስታወሻ ነው። የአረፋ ሥርዓት ከዚህም በተጨማሪ አባታችን አደም እና እናታችን ሀዋ የፈጣሪያቸውን ትዕዛዝ በማጉደላቸው የተነሣ ከገነት ቤታቸው ወደ ምድራዊ ዓለም ተባርረው ተለያይተው ሲኖሩ ከቆዩ በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ አርዱል አረፋ ተብሎ በሚጠራው የአረፋ ኮረብታ ላይ መገናኘታቸው 'አረፍኪኒ አረፍቲኒ' መባባላቸው ይዘከርበታል። በትናትና ጥፋት እና ስሕተት ሳቢያ የሰው ልጅ በሕይወት ከተሳሰረው አካሉ ጋር ለዘለዓለሙ ተለያይቶና ተራርቆ መኖር እንደሌለበት ይልቁንም በንስሐ፣ በይቅርታ፣ በምሕረትና በዕርቅ አብሮነትንና አንድነትን ማስቀጠል መልካም መሆኑን የሰው ልጅ መማር እንዲችል በአባታችን አደም እና በእናታችን ሀዋ (የየአርዱል አረፋ) በአረፋ ተራራ መገናኘት የተገለፀ ታላቅ ተምሳሌታዊ አስተምሮት ተደርጎም ይቆጠራል።

እኛ ኢትዮጵያውያን በትናንት አብሮነታችን ያስመዘገብናቸው በርካታ አኩሪ የጋራ ገድሎች እንዳሉን ሁሉ በትናንት ግንኙነታችን ውስጥ ፍቅርን፣ ፍትሕና ርትዕን አጉድለንና ጎድሎብንም ሊሆን ይችላል። ግን ደግሞ በትናንት ታሪክ ውስጥ ዕድሜ ዘለዓለማችንን ተኝተን በማማረር ማሳለፍ መፍትሔ አይሆንም። በዛሬ ሕይወቱ ዳገት መውጣትን የሚፈራ ትውልድ በነገ ሕይወቱ ቁልቁለት መውረድ ሊጠብቀው አለመቻሉ ግልፅ ነው። ነገን በዛሬ ቀና ራእይና መልካም ተግባር እንጂ በምንም መልኩ ብርሃን ማላበስ አይቻልም። ችግራችን ውስብስብ ቢሆንም መፍትሔም ያለው እዚሁ የአብሮነት ባህላችን ውስጥ ነው። አብረን ከሆንን አንሰበርም። አብረን ከሆንን የማንፈታው ችግር አይኖርም። የዕድገትና የብልጽግናችን ዋስትና ደግሞ እየተቋሰልንም ቢሆን አብረን ተዋደን እና ተከባብረን መኖራችን ነው።





ለዓመታት ተከፋፍሎ የቆየው የሙስሊም ማኅበረሰብ ለውጡ የፈጠረለትን መልካም አጋጣሚ ተጠቅሞ አንድነቱን ለማጠናከር በጋራ መንቀሳቀስ በጀመረበት ማግስት የምናከብረው ይህ በዓል ደስታችንን እጥፍ ድርብ የሚያደርግልን ብቻ ሳይሆን፤ ተስፋችንንም የሚያለመልም ነው። የእስልምና እምነት ተከታይ በሆነው ኅብረተሰባችን መካከል የሚፈጠር አንድነት ለሙስሊሙ ወገናችን ብቻ ሳይሆን ለሀገራችንም አንድነትና ጥንካሬ ምንጭ መሆኑን መንግሥት እንደ ትናንት ሁሉ ዛሬም አበክሮ ይገነዘባል። ይህም ሆኖ ግን ዛሬም ድረስ ውስብብስብ እና ፋታ የማይሰጡ ችግሮች ባለቤቶች መሆናችን ከቶውንም ሊዘነጋን አይገባም። እነዚህ ችግሮቻችን እንኳንስ ተለያይትንና ተከፋፍለን ቀርቶ ተባብረን እና ተዋድደንም ቢሆን ለመፍታት ዘመናት ያስፈልጉናል።  ያን የመፍትሔ ዘመን በአዲሱ የለውጥ መንገድ ከዓመት በፊት አንድ ብለን እንደ ጀመርነው ሁሉ ከዚህ በኋላም የአብሮነትንና የአንድነትን ዋጋ በልኩ በመረዳትና በመገንዘብ ከቀድሞው በላይ የሚያራርቁንና የሚያቃቅሩንን፣ የሚያጠፋፉንን፣ የሚያለያዩንን ተግባራት ሳይሆን በፍቅር፣ በይቅር ባይነት ወደ አብሮነትና ሰላም፣ ወደ አንድነትና ብልጽግና የሚመሩንን የመደመር እሳቤና ተግባራት ተግተን መፈፀም ይኖርብናል።

የአሁኑ ትውልድ ከትናንት ታሪኩ ትምህርት ወስዶ ከሚገኝበት ሀገራዊ የማንነት የቀውስ አዙሪት የሚወጣበትና ወደ ዕድገትና ወደ ብልጽግና ጎዳና መግባት የሚያስችለውን የቁጭት ስንቅ መሰነቂያ ማድረግ ይኖርበታል። ዛሬ በእጃችን  ባለው ተጠቅመን በመለያየት ሳይሆን በአርዱል አረፋ እንደተቀጠለው የአዳምና ሄዋን መገናኘት በአብሮነትና በአንድነት ዘለዓለማዊ የድል ታሪክ የምንሠራ ትውልዶች ለመሆን እንድንተጋ ጥሪዬን አቀርባለሁ።

## ክቡራትና ክቡራን ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች!

በላቀ መደጋገፍ ታጅቦ ከጅማሬ እስከ ማክተሚያ የሚጓዘው በዓል ጠንካሮች ደካሞችን፣ ባለፀጎች ምስኪኖችን፣ ወጣቶች አዛውንቶችንና ሕፃናትን በበዓሉ ላይ በሕብረት በመቆም፣ ከበዓሉ በኋላም መጠያየቅ፣ አብሮ ማሳለፍ ትልቅ ቦታ ይሰጠዋል። በዐቅም ከእኛ ያነሱ ወገኖቻችን በዓሉ ለእኛም ሆነ ለእነርሱ እኩል ቢመጣም በማጣታቸው፤ ጠያቂ በማጣታቸው የተነፃ በዓሉን በባዶ ሆድ እንዳያሳልፉ ከሱም በላይ ሳቅና ወግ ርቋቸው መተከዛቸውና ማዘናቸው ሊሰማንና ሊያሳዝነን ይገባል። ከዚሁ በተጓዳኝ ነቢዩ መሐመድ (ሠለላህ አለይህ ወሠለም) በተለያዩ ሐዲሶቻቸው አረንጓዴ አሻራ አትሞ ማለፍ ያለው ምንዳ ከሰደቃ ሊስተካከል እንደሚችል ከመግለፃቸው ባሻገር፤ "የመጨረሻው የፍርድ ቀን ሊዘረጋ ሰዓቱ የተቃረበ ቢሆን እንኳ እርሱ በእጁ የዛፍ ችግኝ የጨበጠ ሰው ቀሪዋ አንድ ሰከንድ እንኳ ብትሆን እርሷን ተጠቅሞ ችግኙን ይትከል" በማለት አስተምረዋል።

እኛ ኢትዮጵያውያን እንደ ሀገርና ሕዝብ በውዲቷ የሀገራችን ምድርና አፈር የአረንጓዴ አሻራችንን አሳርፈን ለማለፍ ቃል ተገባብተን በችግኝ መትከል እና መንከባከብ ጉዞ ማድረጋችን ብዙም ያልደበዘዘ የቅርብ ጊዜ ትውስታችን ነው። ሐምሌ 22 ቀን በሀገር አቀፍ ደረጃ የተከልነው የችግኝ ብዛት በራሳችን ብቻ ሳይሆን በዓለም ደረጃ ሀገራዊ ስማችንን ከፍ ያደረገና በዓለም የላቀ ክንውን ሪከርድ መዝገብ መስፈርም ያስቻለን ታላቅ ታሪካዊ ዕለት ሆኖ አልፏል። ኢትዮጵያውያን ዛሬም እንደ ትናንቱ ከወሰንንና ከቆረጥን በአንድ ጀንበር በሚሊዮኖች በመትመም ያስቀመጥነውን ዓላማና ግብ ከዳር ለማድረስ የማንሰንፍ ሕዝቦች መሆናችንን ዳግም ለዓለም ሕዝብ ያረጋገጥንበት እና ያስመሰከርንበት ትዕይንት መሆኑ ባይካድም፤ በሀገር ደረጃ ካለብን የተከማቸ እና የዞረ ዕዳ አንፃር የአረንጓዴ አሻራ የማኖር ሥራችንን





መጀመርን እንጂ መጨረስን የሚያሳይ አይደለም። በመሆኑም፤ መልካም ጅምራችንን አጠናክረን በመቀጠል የችግኝ ተከላ እንቅስቃሴያችንን በውሃ ማጠጣት፣ መንከባከብና አረምን በማስወገድ አጠናክረን እንቀጥል። ለዚህም ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች በታሪካዊው ሐምሌ 22 ቀን ከተቀረው የሀገራችን የሌሎች እምነት ተከታዮችና ቤተሰቦች ጋር ጎን ለጎን በመቆም እና እጅ ለእጅ በመያያዝ እንደፈፀማችሁት የላቀ ገድል ሁሉ በቀጣዮቹ ጊዜያትም የጀመርነውን ሀገርን የማስዋብ ሥራ አጠናክሮ በመቀጠል ሀገራችሁን ከምድረ በዳነት እና ከዙሪያ መለስ ብክለት ለመታደግ አረንጓዴ አሻራችሁን ደጋግማችሁ በማኖር የዜግነት ሐላፊነታችሁን እንድትወጡ ዳግም ጥሪዬን አቀርባለሁ።ተፈፃሚ እንደምታደርጉትም እተማመናለሁ!

በመጨረሻም እንኳን ለኢድ አል - አድሃ በዓል በሰላም አደረሳችሁ! በማለት በዓሉ ለመላው ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች የደስታ፣ የሰላም፣ የይቅርታ፣ የፍቅር እና የአንድነት እንዲሆንላችሁ መልካም ምኞቴን እገልጻለሁ!

**ኢድ ሙባረክ!**
**ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራ፤**
**ተከብራና በልጽጋ ለዘላለም ትኑር!**

**ፈጣሪ ኢትዮጵያንና ሕዝቦቿን ይባርክ!**

# የአሸንዳ /ሻደይ/ አሸንድዬ/ ሶለል መልእክት

ነሐሴ 15/2011 ዓ.ም.

**እንኳን ለአሸንዳ /ሻደይ/ አሸንድዬ/ ሶለል በዓል በሰላም አደረሳችሁ!**

በሀገራችን ሴቶችን ወደ አደባባይ እንዲወጡ አስተዋጽዖ ሲያደርጉ ከኖሩት በዓሎቻችን መካከል አንዱ የአሸንዳ /ሻደይ/ አሸንድዬ/ ሶለል በዓል ነው። በዚህ ምድር አረንጓዴ በለበሰችበት በክረምቱ ወቅት በነሐሴ ወር አጋማሽ በትግራይና በአማራ ክልሎች በሚከበረው በዚህ በዓል ወጣት ሴቶች ልዩ የሆነ የሀገር ልብሳቸውን ለብሰውና ከወገባቸው ላይ እርጥብ ሰሌን በአንቀልባ መልክ አሥረው እያዜሙ ይወጣሉ።

አደባባዮቻችን በአብዛኛው በወንዶች ብቻ ተይዘው በነበረበት በዚያ ዘመን እንደአሸንዳ /ሻደይ/ አሸንድዬ/ ሶለል ያሉ በዓላት መኖራቸው በበረሐ እንደተገኙ ቀዝቃዛ ምንጮች የሚቆጠሩ ናቸው። ሴቶች በግጥሞቻቸው፣ በዜማዎቻቸውና በጭፈራዎቻቸው ሐሳባቸውን፣ ባህላቸውንና ምኞታቸውን እንዲገልጡ በማድረግም የማይተካ ሚና ነበራቸው። ለዚህም ነው እስከዛሬም





ድረስ ወጣት ሴቶች ዓመቱን በሙሉ በጉጉት የሚጠብቁት በዓል የሆነው፡፡

የነሐሴ ወር አንድ በዓል ለወንዶች፣ አንድ በዓል ለሴቶች በመስጠት ፍትሐዊነቱን ያሳየ ወር ነው። ወጣት ወንዶች ችቦ ለኩሰው፣ ዳስ ሠርተው፣ ጅራፍ እያስጮኹ የቡሄን በዓል ያከብሩታል። ጭፈራው፣ ሆታው የወጣት ወንዶችን ሐሳብ የምንሰማበት፤ የደረሱበትን ደረጃ የምንለካበት፤ የነገውንም ምኞታቸውን የምናውቅበት ነው። እንዲሁም አሸንዳ/ ሻደይ/ አሸንድዬ/ ሶለል ደግሞ የወጣት ሴቶችን ድምፅና ሐሳቦቻቸዉን የምንሰማበት ወቅት ነው።

የአሸንዳ /ሻደይ /አሸንድዬ /ሶለል በዓል እንደ ሕዝብ የነበረንን አብሮነትና የባህል ውርርስ የሚያሳይ ክዋኔ ነው። በዓሉ በተለያየ ስያሜ በተለያዩ የሀገራችን ክፍሎች ቢከበርም መሠረታዊ የሆነው መገለጫው ማኅበራዊና ባህላዊ ትስስርን የሚያሳይ ነው።

የአሸንዳ/ ሻደይ/ አሸንድዬ/ ሶለል በዓል ሃይማኖታዊ መነሻ የዕርገት በዓል በመሆኑ የሰዎችን ሥነ ልቡና ከፍ በማድረግ ታላቅ ዋጋ አለው። ከቀደመው ዘመን በላይ በዓሉ ዛሬ እንዲያስፈልገን የሚያደርገውም ይህ የወጣት ሴቶች ሐሳብ ነው። የማረግ ሐሳብ፤ ከመውረድ፤ ከመዝቀጥና ተቸክሎ ከመኖር ይልቅ ወደ ላይ ተነጥቆ ማረግ፤

ታዋቂው የሀገራችን ደራሲ ሰሎሞን ዴሬሳ
**“ዳገት፣ ሽቅብ የታየ ቁልቁለት
ቁልቁለት፣ ቁልቁል የታየ ዳገት”**

በማለት እንደገለጠው ዳገትና ቁልቁለት የአተያይ ጉዳዮች ናቸው። “የት ጋ ነው የቆምነው?” የሚለው ነው ወሳኙ፤ ችግርን ከሥሩ ሆነን ከተመለከትነው ያስፈራናል። ሊጫነንም ይደርሳል። ያንን የችግር ቁልል መናድ የማይሞከር

መስሎ ይሰማናል። ችግርን እንደ ንሥር ከላዩ ሆነን ስናየው ግን ቀልሎና ኢምንት ሆኖ ይታየናል። ልንንደው፤ ልናስወግደው እንደምንችል እናምናለን። ከከፍታ ወርደን ታች ለመድረስ ቁልቁለቱ ይቀልለናል። ያንን የወረድነውን መልሰን መውጣት ግን ዳገት ይሆንብናል። ሆኖም የት እንደነበርን ማስታወስ ከዳገቱ የበለጠ ዐቅም እንዳለን እንድንረዳ ያደርጋል። የወረድነውን ዳገት መልሰን መውጣት ብቻም ሳይሆን ከዚያም በላይ ከፍ ማለት እንደምንችል እንድንረዳ ያደርገናል።

ለዚህ ነው ችግርን ለማስተካከል ከመነሣታችን በፊት አስቀድመን ችግሩን የምናይበትን ቦታ ማስተካከል የሚያስፈልገን፤ ማረግ የሚያስፈልገንም ለዚህ ነው። ችግሮቻችንን ከበላያቸው ሆነን ለማየት እንድንችል፤ ኢትዮጵያን ተብትበው የያዟት አያሌ ችግሮች ሊፈቱና እስከ መጨረሻው ሊወገዱ እንደሚችሉ የሚያምኑም የማያምኑም አሉ። የሁለቱ ልዩነት ከአገኙት መረጃና ከአካበቱት ዕውቀት የሚመጣ አይደለም። ከቆሙበት ቦታ የሚመነጭ ነው። እንደ አሸንዳ/ ሻደይ/ አሸንድዬ/ ሶለል ወጣት ሴቶች ለማረግ የወሰኑ፤ ችግሮቹን ከላያቸው ሆነው ያዩዋቸዋል። ራሳቸውንም ከችግሮቹ በላይ ያገኙታል። እንደ እነዚህ ወጣት ሴቶች ለዕርገት ያልተዘጋጁት ግን ራሳቸውን ከችግሮቹ ሥር ወድቆ ያገኙታል። ያኔ ተስፋ ይቆርጣሉ።

ኑ፤ እንደ አሸንዳ/ ሻደይ/ አሸንድዬ/ ሶለል ወጣት ሴቶች እናርግ! ይህ በዓል ሺሕ ዘመናትን ያስቆጠረ በዓል ነው። በደስታ ዘመናት ብቻ ሳይሆን በአስቸጋሪዎቹ ዘመናትም ሲከበር ኖሯል። ለእኅቶቻችን ጉዳዮች ትኩረት ባልሰጠንበትና ሴቶች ከማጀት እንዳይወጡ አስሮ በሚይዘው ዘመን ይህ በዓል ይከበር ነበር። እኅቶቻችን ዙሪያቸውን በአያሌ የሙብት ጥሰቶች ተከብበው፤  በእንቅፋትና በጫና ተይዘው እንኳን ተስፋ መቁረጥ የሚባል አልነካቸውም። ተስፋ ቢቆርጡ ኖሮ ወደ ታች እንዲወርዱ በሚያደርገው ዘመን ወደ ላይ የማረግን በዓል ባላከበሩት ነበር።





ለችግሮቻቸው ከመንበርከክ ይልቅ ችግሮቻቸውን መናቅ ፈለጉ። ለዚህም ነው ከላይ ሆነው ማየትን የመረጡት፡፡ ሕዝባችን አስቸጋሪ ፈተናዎችን ተጋፍጦ እንዲያልፍ የሞራል ስንቅ ከሆኑት ነገሮች መካከል እንዲህ ያሉት የልዕልና አስተሳሰቦች ዋጋቸው የማይተመን ነው። ከእነዚህ ወጣት ሴቶች የማረግን ሐሳብ፤ የከፍታንም ምኞት እንቅሰም፤ ችግሮቻችንንም ከበላያቸው ሆነን እንናዳቸው፤ ያን ጊዜ በቀላሉ እንፈረካክሳቸዋለን። ኑ፣ አብረን ከአሸንዳ/ ሻደይ/ አሸንድዬ /ሶለል ወጣት ሴቶች ጋር እናርግ!

**መልካም የአሸንዳ/ ሻደይ/ አሸንድዬ/ ሶለል በዓል!**

**ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራ፤**
**ተከብራና በልጽጋ ለዘላለም ትኑር!**

**ፈጣሪ ኢትዮጵያንና ሕዝቦቿን ይባርክ!**

# ለከፍተኛ ትምህርት ተማሪዎች ያስተላለፉት መልእክት

መስከረም 12/2012 ዓ.ም.

የ2011 ዓ.ም. የዕረፍት ወራት ከክረምቱ ተሰናብቶ ሄዷል። አሁን ደግሞ 2012 ዓ.ም. ከሙሉ ዕድልና ደስታ ጋር በአደይ አባባ ፍካትና በምድር ገጽታው አረንጓዴ ልምላሜ አስደናቂ ውበት ተላብሶ ወደ አዲሱ የትምህርት ዘመን ይጋብዛችኋል። እንኳን ለዚህ አዲስ ዘመን አደረሳችሁ!

ነባርና አዳዲስ የከፍተኛ ትምህርት ተማሪዎች ተስፋና አዲስ ኃይል ሰንቀው ወደ ዩኒቨርሲቲዎቻችን ሲያቀኑ ከማየት የሚበልጥ ደስታ ወልደው ላሳደጉ ወላጆችም ሆነ ለእኛ ለሁላችን ሊኖር አይችልም። ለምንወዳት ሀገራችንም ቢሆን ልጆቿ ሲማሩና ሲመራመሩ ከማየት በላይ ተስፋ የሚያሰጣትና ደስታ የሚያጭርባት ነገር አይኖርም። ትምህርትን ፍለጋ ከሀገር ወደ ሀገር የመንከራተት ዘመን ታልፎ ትምህርት ራሱ ወደአለንበት ቀዬና ከተማ ድረስ ከሚመጣበት ዘመን ላይ ለመድረስ ውድ ሀገራችሁና ሕዝቦቿ ብዙ ዋጋ ከፍለዋል።





በሁሉም የሀገራችን ቋንቋዎችና ባህሎች የትምህርትንና የዕውቀትን ጥቅም የሚገልጡ አባባሎች መኖራቸው ሕዝባችን ምን ያህል ለዕውቀት ዋጋ እንደሚሰጥና ሊቅን እንደሚወድና እንደሚያከብር ምስክር ነው።

የከፍተኛ ትምህርት ተማሪ አስተሳሰቡ ዓለም አቀፋዊ፣ ተልእኮው ሀገራዊ ነው። ውድድሩም በዋናነት ከራሱና ከጊዜው ጋር ነው። ራሱንና ጊዜውን ያሸነፈ ወጣት ሀገሩን ዓለም ከደረሰበት ማዕረግ ከማብቃት ተሻግሮ ሀገሩን የዕውቀትና የቴክኖሎጂ ፈር ቀዳጅ መሪ ለማድረግ የሚተጋ ምሁር ነው። ውድድሩ ዓለም አቀፋዊ ፉክክሩም የማያቋርጥ ነው። ተሸናፊው ጠላት ሰው ሳይሆን ድህነትንና ኋላ ቀርነት ነው። የሚሮጠው ዛሬን ሳይጠቀምበት እንዳያልፈው፤ ነገም ሳይዘጋጅ ደርሶበት እንዳያመልጠው ነው። ክፉውን በመልካም ለማሸነፍ እንጂ በጎውን በማጥፋት የተሻለ መስሎ ለመታየት ዕውቀትና ጊዜውን አያባክንም። የዕውቀትና የጥበብ ተገዢ እንጂ ለማንኛውም የአካልና የአእምሮ ሱስ ምርኮኛ አይሆንም።

የከፍተኛ ትምህርት ተማሪ በሁሉ የሚማር፤ ከልዩ ልዩ ዕውቀት ምንጮች መቅዳት የሚችል የጥበብ ረኃብተኛ ነው። ከተለያዩ ባህሎች የተለያዩ መላዎችን ለመካን ይተጋል። በየቋንቋዎቻችን የተሰወሩ ልዩ ልዩ ምስጢሮችን ይመረምራል። ከብዙ ማኅበረሰቦች ዘርፈ ብዙ ታሪኮችና ትውፊቶች ተሰናስሎ የሚሸመነውን ታላቅ ሀገራዊ ትርክት ለመረዳት ይማስናል። ልዩነትን ያደንቃል። አንድነትን ያደምቃል። ፍቅርን ያጋምዳል። ከእርሱ የተለየ ወገን ሲያገኝ በፍርሃት ሳይሆን በጉጉት አዲስ የዕውቀት በር ስለተከፈተለት በወዳጅነት በር ዘው ብሎ ይገባል።

የከፍተኛ ትምህርት ተማሪ የሀገር አማካይ የትውልዶች ድልድይ መሆኑን ይረዳል። ከኋላ ለሚከተሉት ሕፃናት አርአያ፤ ቀድመውት ለተራመዱ ጎልማሶችና አረጋውያን ደግሞ መከታ መሆኑን ይገነዘባል። ትናንትናንና ነገን

በጠንካራ የሥራ ሞራል ዐለት የማገናኘትና በማይበጠስ የፍቅር ሰንሰለት የማስተሳሰር ሐላፊነት እንደወደቀበት ከልብ ያምናል። የሚመኛትን ሀገር ለመገንባት፤ የሚፈልገውን ሥርዓት ለመዘርጋት፤ የሚያስበውን ማኅበረሰብ ለመመሥረት የሚያስችሉት ዕድሎች ሁሉ በእጆቹ ውስጥ እንዳሉና የመድረሻ መንገዶቹም ከትምህርት ቤትና ከሕይወት የሸመታቸው ዕውቀቶች እንደሆኑ በትክክል ይገባዋል። ጊዜና ዕድል ከእጁ የጨመረለትን መልካም አጋጣሚ፤ በግዴለሽነትና በሞኝነት እንዳያጣው እንደ ዕንቁ ተጠንቅቆ ይጠብቃል።

በየከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የምትገኙ ወጣት የሀገራችን ተስፋዎችና ተማሪዎች፤

ኢትዮጵያ በብዝኃነቷም በአንድነቷም ምን እንደምትመስል ለማወቅ ግቢዎቻችሁን ማየት ይበቃል። ደግሞም ትናንት እንዴት እንዳለፍን ትምህርቶቻችሁ በታሪክ ይገልጡላችኋል። ነገ ምን መሆን እንዳለብን በውስጣችሁ በተጠነሰሱ ራእዮቻችሁ ልቡናችሁ ያመላክታችኋል። የሀገራችንን ልዩ ልዩ ጸጋዎች እንያዝ፤ ከትናንቱ በጎ በጎውን ወስደን፤ ክፉውን አርመን፤ የሁላችንንም ጥንካሬ በአንድ አዋሕደን ለመጓዝ ካልቻልን እንዴት መቀጠል ይቻለናል? በኢትዮጵያ ውስጥ እንኳን ሰው ይቅርና ለብቻው ደምቆና ገዝፎ መፍሰስ የሚችል አንድም ወንዝ የለም። የወንዞቻችን ታላቅነት በአንድነት ተደምረውና ተደማመረው በሚፈሱት ዝናብና ምንጭ፣ ኩሬና ጅረት በሚገኘው ውሃ ነው። ዓባይ ከሀገር ሀገር ግንድ ቢያንከባልል፤ ግብጽንና ሱዳንን ቀጥ አድርጎ ቢመግብ ምስጢሩ ያለው ባሮና ተከዜ፤ ጣናና ሌሎች ስማቸውን የማናውቃቸው ብዙ ጅረቶች ተደምረውበት ብርቱ በመሆኑ ነው። ብቻውን ታላቅ የሚሆን የለም። የከፍተኛ ትምህርት ተቋሞቻችንም የመደመር ተምሳሌቶችና የአንድነትን ኃይልና የብዝኃነትን ውበት ማንጸባረቂያ ናቸው። ዩኒቨርሲቲ ማለትም ዩኒ - አንድ እና ቨርሲቲ - ብዙ ከሚል ቃል የተሠራ ነው። አንድንና ብዙን የሚያያይዘው ምስጢር ደግሞ የመደመር ኃይል ነው።





ከአላፊው ትውልድ ይልቅ መጪው የእናንተ ትውልድ ጠንካራና የበለጸገች ኢትዮጵያ ያስፈልገዋል። ዛሬ እንደትናንት አይደለም። በአለንበት የ21ኛው ክፍለ ዘመን በራችን ዘግተን፤ ከዓለም ርቀንና ተነጥለን መኖር አንችልም። እኛ ባንሄድም ዓለም ራሱ ደጃችን ድረስ ይመጣል። የያዛችሁት ስልክና ከቤታችሁ ያሉ ቴሌቪዥኖች ይሄንን አስረግጠው ይነግሯችኋል። ብቸኛው አማራጭ ከዓለም ጋር ተወዳድረንና ተባብረን የተሻለን ሆነን አሸንፈን መገኘት ብቻ ነው። ደካማ ሀገር ይዘን ጠንካራ ሕዝብ፣ ድሃ ሀገር ይዘን አሸናፊ ትውልድ ሊኖረን አይችልም።

በገጠር የበጎች ዋና ጠላት ቀበሮ ነው። ቀበሮ ወደ በጎች በረት ራሱ መግባት ካቃተው መጥፎ ጠረኑን በነፋስ ትከሻ ይልከዋል። እርሱ ራሱ ከፍ ያለ ቦታ ይሆንና የነፋሱን አቅጣጫ ተከትሎ እግሩን በማንሣት መጥፎ ጠረኑን ወደ በጎቹ ይልካል። በጎቹ በቀበሮው መጥፎ ጠረን ተደናግጠው መጀመሪያ በረታቸውን ያምሱታል። ቀበሮው ያለበትን አቅጣጫና ቦታ ከማወቅ ይልቅ ሲተራመሱ እርስ በርሳቸው መተማመናቸው ይጠፋል። በመጨረሻም፤ እርስ በርሳቸው በቀንዳቸው ይዋጋሉ። ከዚያም በረታቸውን ሰብረው በገዛ እጃቸው ለቀበሮው ተንኮል ሲሳይ ይሆናሉ።

እናንተም በአንድ ላይ በዩኒቨርሲቲ ውስጥ በማኅበር የምትኖሩ የዕውቀት ባልንጀሮች እንደ በጎቹ የዋሕ መሆን የለባችሁም። ሰላማችንንና ዕድገታችንን የማይፈልጉ በቀበሮ አስተሳሰብ የሚተዳደሩ ብዙዎች አሉ። እነርሱ በሰላማዊ ቦታ፣ በድሎት ሥፍራ ተቀምጠው ባለ መጥፎ ጠረን የቃላት ዘመቻቸውን ወደ መማሪያ ግቢዎቻችሁ ይልካሉ። የሐሰት ወሬ፣ የግጭት ቅስቀሳ፣ የብሔር ጥላቻ፣ በየኮሌጆቹ በየማኅበራዊ ሚዲያዎቹ ይልካሉ። እርስ በርሳችሁ እንድትጠራጠሩ፣ እንድትከፋፈሉና እንድትበጣበጡ ያደርጋሉ። በመጨረሻም በገዛ እጃችን ወደ ቆፈሩልን ጉድጓድ ሰተት ብለን እንገባለን። እነርሱ ምንም አይሆኑም። በድሃው ልጅ ሕይወትና ሕልም ግን ይጫወታሉ። ተዋጉ ብለው

ከቢጤዎቻቸው ጋር በግፍ በሰበሰቡት ገንዘብ ራት ይገባበዛሉ። ተነሡ ብለው ወደምቹ አልጋዎቻቸው ሄደው ይተኛሉ። እናንተን ተሠዉ፣ ሙቱ ብለው ሰብከው ሲጨርሱ እነርሱ ግን ዕድሜያቸውን ለመቀጠል ልጆቻቸውን ይዘው ወደ ዕረፍት ለሽርሽር ይሄዳሉ።

## ወጣቶች በፍጹም አትሞኙ!

ማንኛውንም ነገር ከማድረጋችሁ በፊት ወላጆቻችሁን፣ ሀገራችሁንና የነገ ተስፋችሁን አስቡ። እናንተ ግብ ያላቸሁ ወደ አቀዳችሁት ዒላማ የምትገሠግሡ ባለሕልሞች ናችሁ። በተቆፈረለት መንገድ ሁሉ የምትፈሱ የትውልድ ኩሬና የመስኖ ውሃ አይደላችሁም።

ይህ የትምህርት ዘመን ሰላማዊ እንዲሆንላችሁ እመኛለሁ! ዕውቀት እንጂ ስሜት፣ መተባበር እንጂ መገፋታተር፣ መደናነቅ እንጂ መናናቅ አይሁንላችሁ። በነገዋ ኢትዮጵያ ብሩህ ተስፋ የምታዩበት ዘመን እንዲሆን እንደ መንግሥት አበክረን እንሠራለን። የሀገራችን ዐቅም በፈቀደው መጠን ፍላጎቶቻችሁን ለማሟላት እንተጋለን። ከዚህ አልፎ ከመሥመር የሚወጣውን በጥባጭ በተገቢ መንገድ ወደ ትክክለኛው መሥመር እንዲመለስ ሕግን የማስከበር ሐላፊነታችንን እንወጣለን። እያንዳንዳችሁ ሕልማችሁ እንዲሞላና በሰላም ወጥታችሁ በሰላም ወደ ቤተሰቦቻችሁ እንድትመልሱ እንደመሪያችሁ የሚቻለኝን ሁሉ አደርጋለሁ።

የእናንተንም፣ የሀገራችሁንም፣ የወገናችሁንም የነገ ሕይወት ለማቃናት ዕድላችሁ በእጃችሁ፣ መንገዳችሁ በዕውቀታችሁ ላይ ነው። የአገኛችሁትን ዕድል ለአሰናካዮች፣ የቀሰማችሁትንም ዕውቀት ለጨለማ አበጋዞች አሳልፋችሁ አትስጡ! ነገ የምታከሙን፣ የምትመሩን፣ ደህንነታችንን የምታስከብሩልን፣





ልጆቻችንን የምታስተምሩልንና ሀገራችንን ወደ ላቀ ደረጃ የምታሻግሩልን እናንተ ናችሁ። እናንተን ማገልገልና ማስተማር ከሁሉ የላቀና የከበረ ሥራ ስለሆነ ይህንን የምናደርገው በደስታ ነው።

**አዲሱ የትምህርት ዘመን የዕውቀት ብልጽግና የምትጎናጸፉበት ይሁን!**

**ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራ፤ ተከብራና በልጽጋ ለዘላለም ትኑር!**

**ፈጣሪ ኢትዮጵያንና ሕዝቦቿን ይባርክ!**

# የመስቀል በዓል መልእክት

መስከረም 16/2012 ዓ.ም.

**“ማን ያውቃል?**
**የመስቀል ወፍ እና የአደይ አበባ**
**ቀጠሮ እንዳላቸው መስከረም ሲጠባ።**
**ማን ያውቃል?”**

እንዲል ኢትዮጵያዊው ባለቅኔ፤ እኛ እና መስከረም፤ እኛ እና መስቀልም ዓመት ጠብቀን የምንገናኝ ተነፋፋቂ ባለቀጠሮ ነን። እናም ናፍቆታችንን እንወጣጣ፤ ፍቅራችንንም እንቀባበል ዘንድ ዓመት ጠብቀን አደባባይ እንወጣለን። ያኔ ደመራ ነው። የመስቀል በዓል በዐደባባይ ከሚከበሩ የኢትዮጵያውያን በዓላት መካከል አንዱ ነው። ቀደምት አባቶቻችንና እናቶቻችን ይህንን ታላቅ በዓል በዐደባባይ እንድናከብረው ሥርዓት ሲሠሩ ያለምክንያት አልነበረም። ከበዓሉ ጋር የተያያዙትን ሦስት ታላላቅ ሐሳቦች ሁላችንም እንድንመራባቸው ፈልገው ሳይሆን አይቀርም።

እውነትን ቀብሮ መኖር እንደማይቻል፤ ታሪክ የሚለወጠው በቆራጥነትና በአንድነት መሆኑን፤ አንድ ታላቅ ሐሳብ ኢትዮጵያውያንን እንዲጠቅም ከፈለግን ሐሳቡን ኢትዮጵያዊ ማድረግ እንዳለብን በዓሉ በደመራው ብርሃን ወገግ አድርጎ ያሳየናል።

የክርስቶስን መስቀል የቀበሩት ሰዎች እውነትን ለዘለዓለም ቀብረው ማስቀረት የሚችሉ መስሏቸው ነበር። ለጊዜው መስቀሉ ከአፈር ሥር ሲቀበር ዓላማቸው የተሳካላቸው መስሏቸው ነበር። በመስቀሉ ላይ የቆሻሻ ክምር እንዲከመር ሲያደርጉ መስቀሉን ከታሪክ ገጽ ያጠፉት መስሏቸው ነበር። ይህ ግን የመሰላቸውን መስሎ መቆየት የቻለው እና የዋሆችም መስቀሉ ተቀብሮ፣ ተረስቶ፣ ትቢያ ሆኖ ጠፍቷል ብለው እንዲረሱት ያስቻላቸው ዕሌኒ የምትባል ብርቱ እንስት ከተለየ ብርታት፣ ጽናት እና የ”ይቻላል” መንፈስ ጋር እስክትከሠት ድረስ ብቻ ነበር።

በየዘመናቱ እውነትን ለመቅበር የሞከሩ ነበሩ። በተንኮል፣ በሤራ፣ በግጭት፣ በክፍፍል፣ በጦርነት፣ በጉልበትና በኃይል እውነትን ለመቅበር ብዙዎች ሞክረዋል። እውነተኞችን በማጥፋትና በመግደል፤ በማሰርና በማስፈራራት እውነት የምትጠፋ መስሏቸው ብዙ ደክመዋል። መጻሕፍትን አቃጥለዋል። የዕውቀት ቦታዎችን አውድመዋል። እውነት ግን ብትቀጥንም አትበጠስም። እውነተኞችን በመግደል እና በመቅበር በፍጹም እውነትን ማጥፋት አይቻልም። እውነትና ተስፋ አብረው የሚሄዱ ናቸው። እውነተኞች ተስፈኞች ናቸው። ውሸተኞች ጨለምተኞች ናቸው። ከእውነት ጋር ያልቆመ ሰው ተስፋ ሊኖረው አይችልም። ተስፋ እውነተኛ ሰው ብቻ የሚያደርገው መነጽር ነውና! ተስፋ ባለበት ሁሉ እውነት ትኖራለች። እውነት ባለችበትም እንዲሁ ተስፋ አለ።

መስቀሉን የቀበሩት ሰዎች ሐሰተኞች ስለነበሩ ወደፊት የሚወጣ አልመሰላቸውም። የመስቀሉ ወዳጆች ግን እውነተኞች ስለነበሩ አንድ ቀን እንደሚገለጥ ያምኑ ነበር። ለዚህ ነው መስቀሉ የት እንደተቀበረ ከልጅ ልጅ በሚተላለፍ የቃል ትውፊት መረጃውን ለዘመናት አቆይተው ለመስቀሉ አስተርእዮት ዘላለማዊ ገድል የፈጸሙት።

ኢትዮጵያን ታላቅ፣ የበለጸገችና ለሁላችንም እንድትሆን ለማስቻል የያዝነው ዓላማ መሳካቱ የማይቀር እውነት ነው። ይህን እውነት የሚገዳደሩ ኃያላን ይኖራሉ። ለጊዜው ዝናራቸውን እስኪጨርሱ፤ ጉልበታቸውንም እስኪያፈሱ ድረስ ያሸነፉ ይመስላሉ። ድምፃቸው እንደ ነጎድጓድ፣ ጬኸታቸውም እንደ ብዙ ፏፏቴዎች የወል ጬኸት ጎልቶ ይሰማ ይሆናል። እውነታችንን የቀበሩት መስሏቸው ለጊዜው ይደሰታሉ። በዙሪያችን ያሉትም እውነታችን የተቀበረ መስሏቸው ተስፋ ይቆርጣሉ። ይህ ግን የእውነትን ባሕርይ ካለመረዳት የሚመጣ ነው። እውነትን መገዳደር እንጂ ማሸነፍ፣ መቃወም እንጂ ማጥፋት ፈጽሞ አይቻልም። የብዙዎች ጬኸት፣ የሰነፎች ተረት እና የአላዋቂዎች ትምክህት እውነትን ሊያጠፉት እንደማይችል በጽኑ እናምናለን። እውነት የተቀበረችበትን ዐመድ እንደ ፍግ እሳት አሙቃ እንደ ገሞራ ትፈነዳለች። የተሸፈነችበትን አቧራ እና የከፋት ቁልል ቅርፊቱን እንደሚሰብር ጫጩት ፈንቅላ ትነሣለች። ነገ ከእውነተኞች ጋር ናት። እውነተኞች ዛሬ ጥቂቶች ቢመስሉም ነገ እየበዙ ይሄዳሉ፤ ሐሳውያን ዛሬ ብዙዎች ቢመስሉም ነገ እንደስንቅ እያነሡ ይሄዳሉ። ለዚህ ነው ከኢትዮጵያ እውነት ጋር እንቆም ዘንድ እስከ የትኛውም ጥግ ተጉዘን፤ የትኛውንም እንቅፋት በጀግንነት እንሻገር ዘንድ የምንታገሰው።

ማንም በማያስብበት፤ ነገሩ ሁሉ የተረሳ በሚመስልበት፤ ኃያላን ሁሉ ዝም ባሉበት በዚያ ጊዜ ዕሌኒ የምትባል ቆራጥ እናት ተነሣች። ማንም የማይደፍረውን ደፈረች። ከእውነት ጋር ለመቆምም ቆረጠች። ያልተሞከረውን ለመሞከር፤ የማይታሰበውን ለማሰብ ወሰነች። ታሪክ በሥራ እንጂ በወሬ አይለወጥም። የሚያወሩ ሰዎች በታሪክ ውስጥ ያልፋሉ። ታሪክ ግን አይሠሩም። ማኅበረሰቡ የሚያውቀውን፣ የለመደውን፣ ደጋግሞ የሞከረውን ነገር በማድረግ ታሪክ አይለወጥም። ሌሎች ባዘገሙበት መንገድ ብቻ ደጋግሞ በመጓዝ ከአሰቡት ለመድረስ አይቻልም። አዲስ ታሪክ ለመጻፍ አዲስ መንገድ መከተል፤ አዲስ ልማድም መትከል፤ አዲስ ሥራም መሥራት ይጠይቃል። ጫካ የሚያቃጥል እሳት ከአንዲት ክብሪት ይነሣል። ሀገር የምትለውጥ ውብ ሐሳብም ከአንዲት ቦታ ትመነጫለች። ተገዳድለን፤ ተጨፋጭፈን፤ ተናቁረን ሞክረነዋል። ማሳደድና ማሰር የታሪካችን አካላት ሆነዋል። ሤራና ሸር፣ ይውደምና ይመታ መዛግብተ ቃላትን ሞልተውታል። ለዚህ ነው በአዲስ መንገድ እንሂድ ብለን የተነሣነው።

ዕሌኒ እንደብዙዎቹ የዓለማችን ባለቅን ልብ ቅን ሰዎች ዓይነተኛ የመደመር ተምሳሌት ናት። የእርሷ ቆራጥነት፤ የሕዝቡ ጸሎት፤ የወታደሮቹ ብርታት፤ በኢየሩሳሌም የነበሩት ሰዎች ትጋት፤ መረጃውን የሰጧት ሰዎች ቀናነት፤ እነዚህን ሁሉ አስተባብራ ሐሳቧን ተግባር፤ ተግባሯን ታሪክ ለማድረግ ቻለች። “ተቀበረ” የሚለውን ታሪክ “ወጣ” በሚለው ቀየረችው። “ጠፋ”ን በ”ተገኘ”፤ “ተሰወረ”ን በ”ተገለጠ” አጸደለችው። እውነት እና ተስፋ ነበሯትና የሚቻል የማይመስለውን ቻለች። ተራራውን ናደች። የውሸትን ክምር አፍርሳ የእውነትን ሐውልት አቆመች። አይሆንም የተባለው ሆነ። አይቻልም የተባለው ተቻለ። ቀባሪዎቹ አልፈው የተቀበረው ህያው ሆነ። የቀባሪዎቹ ታሪክ ተዘግቶ የተቀበረው ታሪክ ተከፈተ። ለዚህ ነው ቀደምት አባቶቻችንና እናቶቻችን የመስቀልን በዓል ከየቦታው በሚሰበሰብ እንጨት፣ ከእንጨቶችም በሚሠራ ደመራ እንድናከብረው ያደረጉን፤ እውነትን ለማጽናት ከመደመር የተሻለ ነገር የለም ሲሉን ነው።

መሟላት እንጂ መባላት እንደማይበጀን፤ ትግግዝ እንጂ ውግግዝ እንደማይረባን፤ ትቅቅፍ እንጂ ንቅቅፍ ዋጋ እንደሌለው ዕሌኒ አሳይታናለች። በዚያ የመስቀል ፍለጋ ጉዞዋ ክርስቲያኖችንም፣ አይሁድንም፣ ሌላ እምነት ያምኑ የነበሩትንም አስተባብራለች። መንገዷ የጥበብ እንጂ የመጥበብ አልነበረም። ጉዞዋ ሁሉንም ለእውነት ለማንበርከክ እንጂ አንዱን ለሌላው ለማንበርከክ አልነበረም። ዛሬ ሁሉም የታሪኩ ባለቤት ሆነዋል። ከዕሌኒ የምንማረው መንገዳችን ጠላት የመቀነስ፤ ወዳጅ የማብዛት መሆን እንዳለበት ነው።

መስቀሉ የለም፤ ተቀብሮ ጠፍቷል፤ ከእንግዲህ አይገኝም፤ አለቀለት፤ አበቃለት፤ ሲሉ ለነበሩ ሰዎች ከልኬቷ ወርዳ በመነታረክ፤ ሥራ ፈትታ በመወራወር ዕሌኒ ጊዜ አላጠፋችም። ታሪክ ልኬት ከወረዱ ጋር በመውረድ፤ ከአነሱ ጋር በማነስ ታሪክ እንደማይቀየር ዐውቃለች። በጮኹት ውሾች ላይ መልሳ በመጮህ ጉልበት አላባከነችም። እነርሱ ወደ ዝቅታ ሲሄዱ እርሷ ወደ ከፍታ በማምራት ላይ ነበረች። በየመንገዱ የነበሩ ተስፋ አስቆራጭ ጩኸቶችንና ልብ አፍሳሽ እንቅፋቶችን አልፋ፤ የማይሞከረውን ሞክራ፤ አይቻልም የተባለውን ችላ፤ ታሪክን በሡገነት ላይ አስቀመጠችው። አፈኞች ከማያወርዱበት፤ ወሬኞች ከማይደርሱበት፤ ተንኮለኞች ከማያገኙት ከፍታ ላይ ሰቀለችው።

የእኛም ጉዞ እንደዚያ ይሁን። ለሥራ ካልደረሱ፤ ለሙብል ካላነሱ ሰዎች ጋር ጊዜያችንን አናጥፋው። ጉልበታችንን አናባክነው። ጠላቶቻችን በዘረጉልን የአሽከላ መንገድ ሳይሆን ወደ ልዕልና በሚያደርሰን በራሳችን ጎዳና እንጓዝ፤ ወገባችን አስረን፤ ዐቅማችንን ቋጥረን፤ ድምፃችንን አጥፍተን ታሪክ የቀየርን ለታ የውሸት ክምር ይናዳል፤ የወሬ ኩይሳ ይፈርሳል።

መስቀሉ የተገኘው፤ የመጀመሪያው ደመራም የተደመረው፤ የመጀመሪያው በዓልም የተከበረው ኢትዮጵያ ውስጥ አይደለም። አባቶቻችንና እናቶቻችን ግን ይህን ታላቅ ነገር ወደ ሀገራችን አምጥተው ኢትዮጵያዊ አድርገውታል። ከእኛው መልክአ ምድር፤ ከእኛው የዘመን አቆጣጠር፤ ከእኛው ባህል ጋር አስማምተው ኢትዮጵያዊ መልክ ሰጥተውታል። በብዙ ማኅበረሰቦች ዘንድ፤ በየአንዳንዱ ገጠር ዘመናትን እየተሻገረ እንዲሄድ አስችለውታል። የእኛው የመስቀል አከባበር ዓይነተኛ ቅርሳችን ሆኖ በዩኔስኮ የተመዘገበውም ለዚህ ነው። ኢትዮጵያዊ ስለሆነ፤



ሁሉን ነገር መቅዳት፤ ቀድተን እንዳለ በሀገራችን ምድር ላይ መድፋት ውጤት አላመጣም። ሐሳቦችን፣ ልምዶችን፣ መርሖችን፣ ዕውቀቶችን ከሚገኙበት ወስደን ኢትዮጵያዊ መልክ ልንሰጣቸው ይገባል። ከኛው ባህል፣ እምነት፣ ልማድ፣ አስተሳሰብ፣ አኗኗርና ፍላጎት ጋር ማጣጣም አለብን። መደመር እንዲህ ነው። ከምዕራብም፣ ከምሥራቅም አየን፤ በጎ በጎው ወሰድን፤ የራሳችንን ሐሳብ አዋለድን፤ ከኢትዮጵያ ባህልና ታሪክ፤ ፍላጎትና ዐቅም ጋር አዋሐድን፤ ኢትዮጵያዊ የሆነ የመደመር መንገድንም ጀመርን። ቀደምቶቻችን የመስቀል በዓል በየመንደሩ እስኪደርስ ድረስ እንደ ደከሙት ሁሉ መደመርም በየኪሳችን እስኪገባ ድረስ መድከም አለብን። አንዴ ከምዕራብ፣ ሌላ ጊዜ ከምሥራቅ አምጥተን፤ ምሥራቁንና ምዕራቡን ለመሆን ጥረን ነበር። እየቀዳን የምናመጣው ዘር ግን በኢትዮጵያ ምድር ሊያፈራ አልቻለም። ለዚህ ነው ግራ ቀኙን አይተን የእኛኑ ችግር በእኛው መፍትሔ ለመሞከር የተነሣነው። በመደመር!

መደመር እንደ ደመራው ሁሉ በየመንደሩ፤ በየጥጋቱ ሁሉ ማብራት አለበት። ዛሬ የደመራ በዓላችንን ለማየት ዓለም ሁሉ ወደ እኛ እንደሚመጣው ሁሉ፤ ነገ መደመር ያስገኘልንን ለውጥና ብልጽግና፤ የተለምነውንም የፍቅር ጎዳና ለማየት፤ አይተውም ለመደመር ብዙዎች ይመጣሉ። እውነተኞች ተስፋ አላቸው። ደመራን በየዓመቱ የሚያይ ሕዝብ መደመር የሚኖረውን ኃይል ይገነዘባል። መደመርም እንደደመራው ሁሉ ኢትዮጵያዊ ነው። ለኢትዮጵያ የሚበጅ ኢትዮጵያዊ፤ የኢትዮጵያ መንገድ፤

እንደ ዕሌኒ ታሪክ ለመለወጥ ቆርጠን፤ በዙሪያችን ያሉትን ሁሉ በእውነትና በፍቅር አስተባብረን፤ እንደ ደመራው ተደምረን ኢትዮጵያን ማንም ከማያወርድበት ሡገነት ላይ ለማውጣት እንነሣ!

**መልካም የመስቀል በዓል ይሁን!**

**ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራ፤
ተከብራና በልጽጋ ለዘላለም ትኑር!**

**ፈጣሪ ኢትዮጵያንና ሕዝቦቿን ይባርክ!**





# የእሬቻ በዓል መልእክት

መስከረም 22/2012 ዓ.ም.

ኢሬቻ በገዳ ሥርዓታችን ዕሴቶች የሰላምና የአንድነት ተምሳሌት ነው።

**የተከበራችሁ የኦሮሞ ሕዝቦች፤**

ከሁሉ አስቀድሜ እንኳን ለዚህ የተከበረ የምስጋና፣ የፍቅር፣ የሰላም፣ የዕርቅና የይቅርታ በዓል በሰላም አደረሳችሁ!

**ኢሬቻ የምስጋናና የምልጃ በዓል ነው**

የኦሮሞ ሕዝብ ሁሉን ነገር ለፈጠረው፤ ምድርንና ሰማይን፣ ወንዝንና ባሕርን፣ ቀንንና ሌሊትን፣ ብርሀንና ጨለማን፣ ሕይወትንና ሞትን፣ ክረምትንና በጋን፣ ዝናብንና ሐሩርን፣ ዕፅዋትን፣ እንስሳትንና ሰውን ለፈጠረ፤ ሁሉን ነገር ማድረግ ለሚችል ዋቃ (አምላክ) ምስጋናና ክብር የሚያቀርብበት ሥርዓተ በዓል ነው። የኦሮሞ ሕዝብ በኢሬቻ በዓል ላገኘው ፀጋና በረከት፣ ሰላምና ደስታ፣ ጤናና ዕድሜ፣ ፍቅርና ክብር፣ ብርሃንና ተስፋ፣ ከአንድ ወቅት ወደሌላ ወቅት በአጠቃላይ ከዘመን ወደ ዘመን በሰላም ለአሸጋገረው አንድ አምላኩ (ለዋቃ) ምስጋና የሚያቀርብበት በዓል ነው።

## ኢሬቻ የሰላም በዓል ነው

በዚህ በዓል ለሰላም፣ በሰው ልጅና በተፈጥሮ መካከል ላለው በጸጋና በይቅርታ ለተመላው ግንኙነት፣ ለወላድነትና ለልምላሜ፣ ለእንስሳት፣ ለዕፅዋት፣ ለሕፃናት፣ ለቤተሰብ፣ ለጎሳ፣ ለአገር፣ ለመላው ዓለምና ለመላው የሰው ልጅ ሰላምና ደኅንነት የኦሮሞ ሕዝብ ፈጣሪውን ዋቃን ያመሰግናል። ይማጸናል። ይመርቃል። በመሆኑም ኢሬቻ የምርቃት፣ የተማጽኖ፣ የዕርቅ፣ የይቅርታ፣ የሰላም፣ የፍቅር፣ የአንድነት፣ የወንድማማችነት የእኅትማማችነት፣ የምስጋና እና የበረከት በዓል በመሆኑ የሰላም በዓል ነው። እሬቻ መነሻው እና መድረሻው፤ የመከበሩም አልፋ እና ኦሜጋ ሰላም ነው። ይህንን ይዘን እሬቻን ስንበይነው እሬቻ ማለት ሰላም ማለት ነው።

## ኢሬቻ የቃልኪዳን በዓል ነው

የኦሮሞ ሕዝብ የጾታ፣ የዕድሜ፣ የፖለተካ አመለካከትና የሃይማኖት ልዩነት ሳይገድበው የጋራ ባህሉንና ታሪኩን፣ አንድነቱን፣ ወንድማማችነቱንና እኅትማማችነቱን የሚገልጽበት ከመሆኑም ባሻገር ባህሉን ለማደስ፣ ለማጠናከር፣ ከትውልድ ወደ ትውልድ ለማስተላለፍ ቃል የሚገባበት፤ ለፈጣሪ እና ለተፈጥሮ ምስጋናውን አቅርቦ ለቀጣይ ዘመኑም ለደግ ደጉ ብቻ ቃል ኪዳኑን የሚያጸናበት ሰላም ማጠንከሪያ እና ቃልኪዳን ማሰሪያ ሥርዓተ በዓል ነው።

## በኢሬቻ ባህልና ወጋችንን እናሳድግበት

ከብዝኃ ባህላችን ውስጥ የምንጋራቸውን እርስ በርስ ትስስርና ወንድማማችነት የሚገነቡትን ዕሴቶች አጉልቶ በጋራ ማወደስ ለአገራዊ አንድነት ግንባታ ትልቅ





ፋይዳ አለውና ታላቁን ክብረ በዓል ለዚህ ታላቅ ዓላማ እንጠቀምበት። በዚህም መሠረት ሁሉም የኢትዮጵያ ሕዝቦች ኢሬቻን በጋራ እንዲያከብሩ ጥሪዬን አቀርባለሁ። የክረምቱን ዶፍና ጨለማ ያሻገረን ዋቃ አምላክ ይመስገን! ኢሬቻ የፀደይ በረከት የምንቋደስበት፤ ወደ አዲስ የድል ምዕራፍ ለመሸጋገር ቃላችንን የምናድስበት እና በፍቅር በማቀፍ ጥላቻን የምናሸንፍበት በዓል ይሁንልን!

**ኢትዮጵያ በልጆቿ ታፍራ፤**
**ተከብራና በልጽጋ ለዘላለም ትኑር!**

**ፈጣሪ ኢትዮጵያንና ሕዝቦቿን ይባርክ!**

# በዜጎች ሕይወት ማለፍ እና በንብረታቸው መውደም በተሰማቸው ሐዘን ያስተላለፉት መልእክት

ጥቅምት 15/2012 ዓ.ም.

**የተከበራችሁ የሀገሬ ሕዝቦች!**

ሰሞኑን በተከሠተው እጅግ አሳዛኝ ግጭት በዜጎቻችንና በንብረታቸው ላይ በደረሰው ሁሉ ማዘኔን አስቀድሜ ለመግለጥ እወዳለሁ።

ያጋጠመን ፈተና ኢትዮጵያውያን ካልተባበርንና አንድ ሆነን ካልቆምን መንገዳችን ምን ያህል አስቸጋሪና አስፈሪ ሊሆን እንደሚችል ማሳያ ነው። ችግሩ የብሔርና የሃይማኖት መልክ እንዲኖረው ለማድረግ ተሞክሯል። በዚህም የተነሣ ወገኖቻችን በአሰቃቂ ሁኔታ መሥዋዕት ሆነዋል።

የጸሎት ቤቶች ተቃጥለዋል። የንግድ ድርጅቶችና የመኖሪያ ቤቶች ወድመዋል። የተፈናቀሉ ወገኖች በተለያዩ ቦታዎች ተጠልለዋል። መተላለፊያ ያጡ ዜጎችም በየከተሞቹ ከርመዋል። እንኳንስ ለማየት ለመስማት የሚዘገንን እኩይ ተግባር በወገናችን ላይ ተፈጽሟል።

በልብ ሰባሪው ክሥተት ብናዝንም ኢትዮጵያውያን ዛሬም ታላቅ ሕዝቦች፣ አስተዋዮችና አመዛዛኞች መሆናቸውንም አይተናል። ቤተ ክርስቲያን እንዳይቃጠል የሚከላከሉ ሙስሊሞች፤ መስጊድ እንዳይቃጠል ዘብ የሚቆሙ ክርስቲያኖች አሉን። ከእነርሱ ብሔር ውጭ ለሆነው ወገናቸው ሲሉ መሥዋዕትነት የከፈሉ ኢትዮጵያውያንም አሉን። ሰላምና ደኅንነት ለማውረድ ሌት ተቀን የሚደክሙ ሽማግሌዎች አሉን። ቤት ንብረታቸውን ላጡ መጠለያ የሚሆኑ፤ መንገድ ለተዘጋባቸው ማደሪያ የሚያዘጋጁ ብዙ ወገኖች አሉን። የፈተናው ዓላማ ተስፋ እንድንቆርጥና መንገዳችንን እንድንቀይር መሆኑን ተረድተው፤ ዛሬ በሆነው ነገር ሳይደናገጡ፤ ነገን አሻግረው የሚመለከቱ ዜጎች አሉን። ለሕግና ለኅሊና የሚቆሙ የመከላከያና የፖሊስ አባላት አሉን።

ይህ ሁሉ ለምን እንደመጣብን እናውቃለን። ከዚህ የበለጠ ፈተና ቢያጋጥመንም እንኳን የጀመርነውን ጉዞ አናቋርጥም። አረሙን እየነቀልን፤ ስንዴውን እየተከባከብን እንሄዳለን እንጂ፤ ለአረሙ ስንል ስንዴውን አንተወውም። በመንገዳችን የሚያጋጥመንን እንቅፋት እያነሣን መንገዳችንን እንቀጥላለን እንጂ፤ ወደ ቀኝም ወደ ግራም ወለም ዘለም አንልም። ፈታኞቻችን ያልተገነዘቡት ነገር ቢኖር የተከፈለውን መሥዋዕትነት ሁሉ ከፍለን የኢትዮጵያና የሕዝቦቿን ብልጽግና የምናረጋግጥ መሆናችንን ነው።

የሕግ የበላይነትን ለማረጋገጥና አጥፊዎች በሕግ ፊት ቀርበው ተገቢውን ሁሉ እንዲያገኙ ያለማወላወል እንሠራለን። በተፈጠረው አሳዛኝ ክሥተት የተጎዱት

እንዲያገግሙ፤ ከቤት ንብረታቸው የተፈናቀሉት እንዲመለሱ፤ ንብረታቸው የጠፋባቸው እንደገና እንዲቋቋሙ ከሕዝባችን ጋር ሆነን በጽናት እንሠራለን። ይህንን ለማሳካትም የሃይማኖት ተቋማት፣ የሲቪክ ማኅበራትና መላው ሕዝብ ከጎናችን እንዲቆም ጥሪ እናቀርባለን።

እርስ በርሳችን ከተከፋፈልንና ከተጋጨን አሸናፊዎቹ ሌሎች ናቸው። ማናችንም አናሸንፍም። ጠላቶቻችን ምን እንድንሆን እንደሚፈልጉ በጥቂቱ አይተነዋል።

ከዚህ የከፋ እንዳይገጥመን መንግሥትና ሕዝብ የሚጠበቅባቸውን ማድረግ አለባቸው። መንግሥት ከመንግሥት የሚጠበቀውን ሁሉ ያደርጋል። ሕዝቡም ባለመለያየት፤ ለአጥፊዎች አጀንዳ ባለመመቻቸት፤ አንዱ ለሌላው ጋሻና መከታ በመሆን፤ ወንጀለኞችን አሳልፎ ለሕግ በመስጠት፤ የተጎዱ ወገኖቹን በመርዳት ታላቅነቱን ሊያስመሰክር ይገባል።

**ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራ፤**
**ተከብራና በልጽጋ ለዘላለም ትኑር!**

**ፈጣሪ ኢትዮጵያንና ሕዝቦቿን ይባርክ!**





# የመውሊድ በዓል መልእክት

ጥቅምት 28/2012 ዓ.ም

**እንኳን ለ1494ኛው የነቢዩ መሐመድ (ሰዐወ) የመውሊድ በዓል “መውሊድ አን’ነቢ” አደረሳችሁ!**

በእስልምና የዘመን አቆጣጠር ራቢ አል አወል የተሰኘው ሦስተኛው ወር በገባ በ12ኛው ቀን በየዓመቱ የሚከበረው “መውሊድ” የቃል ምንጩ ዐረብኛ ሲሆን፤ ትርጉሙም “የመወለጃ ቦታ ወይም የመወለጃ ዕለት” ማለት ነው። መውሊድ በመንፈሳዊ ትርጉሙ ደግሞ ነቢዩ መሐመድ (ሰለላ አለይህ ወሰላም) እና የሱፊ ሸኾች የተወለዱበትን ወይም የሞቱበትን ዕለት ለማሰብ የተሰጠ ስያሜ ነው። የነቢዩ መሐመድ የልደት ቀንም “መውሊድ አን’ነቢ” ተብሎ በመጠራት በየዓመቱ በዓለም ዙሪያ የእስልምና እምነት ተከታዮች ዘንድ በተለያየ የእምነቱ ሥርዓት በድምቀት ተከብሮ ይውላል።

**የተከበራችሁ ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች!**

መውሊድ አን’ነቢ በዋናነት የሰደቃን ወይም የምጽዋትን፣ የዱአና የጀባታን፣ የተመረጡ የቁርዐን ክፍሎችንና የመውሊድ ምንባብን፣ የመንዙማ

ፕሮግራሞችን አካትቶ የሚይዝ ነው። በሰደቃው ወይም በምጽዋቱ ሀብታሞች ለድሆች ያበላሉ። ያጠጣሉ። ያለብሳሉ። ዱአና ጀባታ ወይም ስጦታ እየተሰጠ የታመመው እንዲድን፤ የደኸየው እንዲከብር፤ መካኑ ልጅ እንዲያገኝ፤ የተራራቀው እንዲቀራረብ፤ የተበደለው እንዲካስ፤ አገር ሰላም እንዲሆን፤ መንግሥት እንዲረጋጋና ለሕዝብ የሚጠቅም ሥራ እንዲሠራ፤ በምረቃና በርግማን ዘለግ ያለ ዱአ ይከናወናል።

በቁርዐንና በመውሊድ ንባብ ክፍለ ጊዜ ከነቢዩ መሐመድ ጋር የተያያዙ ነቢዩ የዓለሙ እዝነትና መሪ፣ ለሠናዮች መልካሙን አብሣሪ፣ ለእኩይ ሠሪዎች አስፈራሪ፣ ለሕዝባቸው ሀላልና ሀራሙን አስተማሪወዘተ... ሆነው የተላኩ መሆናቸውን በተለይ የሚመሰከሩ የቅዱስ ቁርዐን ክፍሎች ይቀራሉ። ስለነቢዩ መሐመድ ውልደት፣ በሕይወት በነበሩ ጊዜ ስለፈጸሟቸው ገድሎችና ተአምራቶች፣ ስለ ባሕሪያቸው፣ በቀደምት ዓሊሞች የተዘጋጁ “በርዘንጅ”ን የመሳሰሉ የመውሊድ ኪታቦች መሳጭ በሆነ ስልት ይነበባሉ።

ይህንን ታላቅ በዓል የምናስታውሰው የነቢዩን ትምህርቶች በማሰብ ብቻ ሳይሆን ተግባራዊ በማድረግ ጭምር ነው። ነቢዩ መሐመድ (ሰዐወ) ካስተማሯቸው ትምህርቶች መካከል በተለይም በዚህ ወቅት የሚያስፈልጉንን ጥበቦች ልናነሣቸው ይገባል። የሀገራችን ማኅበረሰብ በዋናነት የተገነባው በሃይማኖታዊ ዕሴቶች ነው። የተገነባንባቸውን እነዚህን ዕሴቶች ደጋግመን ባስታወስናቸውና ተግባራዊ ባደረግናቸው ቁጥር ችግሮቻችን እየቀነሱ፤ ሰላምና አንድነታችንም እየተጠናከረ ይሄዳል።

ነቢዩ መሐመድ ዓለም በአራት ነገሮች ተደግፋ እንደምትኖር ተናግረው ነበር። እነዚህም፡- “የጠቢብ ትምህርት፣ የታላቅ ሰው ፍትሕ፣ የመልካም ሰው ጸሎት እና የጀግና ሰው ተጋፋጭነት” ናቸው። እነዚህ አራት ነገሮች የሀገራችንን ሰላምና ብልጽግና፣ የሕዝባችንን ፍቅርና አንድነት ለመደገፍ በዚህ ሰዓት እጅግ





አስፈላጊዎቻችን ናቸው።

የጠቢብ ትምህርት ማኅበረሰብን በዕውቀትና በእውነት ላይ እንዲመሠረት ያደርገዋል። ከስሜታዊነትና ከጭፍንነት ወጥቶ በአመክንዮና በሚዛናዊነት መርሕ ላይ ያቆመዋል። ትናንትን ከዛሬ፣ ዛሬን ከነገ ጋር አያይዞ እንዲመዝን ያስችለዋል። ችግርን ተጋፍጦና አሸንፎ በጥበብ እንዲሻገር ያበቃዋል። ከሰውነት ተራ ወደ አውሬነት እንዳይወርድ፣ ከአእምሮ ሚዛን ወደ ደመ ነፍሳዊነት እንዳይወርድ ያስችለዋል።

ፍትሕ ከጥቅምና ከወገንተኝነት፣ ከሥልጣንና ከክብር ሳይሆን ከሕግና ከኅሊና እንዲመነጭ ታላቅ ሰው ያስፈልገዋል። ለዚህ ነው ነቢዩ “የታላቅ ሰው ፍትሕ” ያሉት፤ ታላቅ ሰው ማለት ለሕግና ለኅሊናው ብቻ የሚታዘዝ ሰው ነው። “ታላቅ ሰው” የሥጋውን ጥቅም ያሸነፈ፤ ለሕጉ ብቻ የወገነ፤ ለእውነት ብቻ የቆመ፤ ለንጽሕና ብቻ የታመነ ሰው ነው። ፍትሕን ለሕዝባችን ለማረጋገጥ እንዲህ ያለው ሰው ዛሬ ያስፈልገናል። ፍትሕ በፍትሕ ተቋማትና በተቋማቱ ውስጥ ባሉት ሰዎች ብቻ አይረጋገጥም፤ ተቋማቱን ታላቅ የሚያደርጉ ታላላቅ የፍትሕ ሰዎች ሲኖሩን እንጂ።

ከሕዝባችን መንፈሳዊ ዕሴቶች አንዱ ጸሎት ነው። ስለ ጸሎት ለኢትዮጵያ ሕዝብ መንገር ለቀባሪ ማርዳት ይሆናል። ለዚህች ሀገር ግን ጸሎት ብቻ ሳይሆን የመልካም ሰው ጸሎት ያስፈልጋታል። በቅንነትና በንጽሕና የሚቀርብ ጸሎት። ከዘረኝነት፣ ከክፋትና ከግፍ የጸዳ የመልካም ሰው ጸሎት። ሰላም፣ ይቅርታና ፍቅርን ገንዘቡ ያደረገ የመልካም ሰው ጸሎት ዛሬ ያስፈልገናል።

ይህ ወቅት ለእውነት ብቻ የምንቆምበት ጊዜ ነው። እውነት የሚያመጣውን መሥዋዕትነት ተቀብለን ለእውነት፣ በእውነት የምንቆምበት ወቅት ነው። ዘመን የወደደውን፤ ጊዜ የወለደውን ሳይሆን እውነት የሆነውን ብቻ

የምንናገርበትና የምንሠራበት ወቅት ነው። ሰዎች ቢቀበሉትም ባይቀበሉትም፤ ወገናችንን ቢያስደስተውም ቢያስከፋውም፤ እውነቱን ተናግረን ከመሸበት ማደር የሚያስፈልገን ወቅት አሁን ነው። ይህን ለማድረግ ደግሞ የጀግና ሰው ተጋፋጭነት ያስፈልገናል። ጀግና ሰው ማለት እውነትን ይዞ ውሸትን፣ ሐቅን ይዞ ሐሰትን የሚጋፈጥ ነው።

እነዚህ አራት ነገሮች አሉን ወይ? ከአራቱስ የቱ ይጎድላል? ለምን? እያልን ነው ይህንን ታላቅ በዓል ልናከብረው የሚገባን፤ በዓሉ የመሰባሰቢያና የፍቅር በዓል ነው። ታላቁን ከታናሹ፤ ሀብታሙን ከድሃው የሚያገናኝ የፍቅር በዓል ነው። እንዲህ ባለው በዓል ጊዜ አራቱ ነገሮች ለሀገራችን ያላቸውን አስፈላጊነት ማየት አለብን። ለበዓሉ በተሰባሰብንባቸው ቦታዎች ሁሉ ስለአራቱ ነገሮች መነጋገር አለብን። የጠቢብ ትምህርት፣ የታላቅ ሰው ፍትሕ፣ የመልካም ሰው ጸሎትና የጀግና ሰው ተጋፋጭነት በእኛ ዘንድ አሉ ወይ?

**መልካም የመውሊድ በዓል!**

**ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራ፤**
**ተከብራና በልጽጋ ለዘላለም ትኑር!**

**ፈጣሪ ኢትዮጵያንና ሕዝቦቿን ይባርክ!**





# የብልጽግና ፓርቲ ውሕደት መልእክት

ኅዳር 9/2012 ዓ.ም.

**ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብና ለብልጽግና ፓርቲ አባላት በሙሉ፤**

የብልጽግና ፓርቲን የመመሥረት ሂደት በምሁራን ሲጠና ቆይቶ በየደረጃው ሁሉም አመራሮች ውይይት እንዳደረጉበት ይታወሳል። በትናንትናው ዕለት የኦዲፒ አስቸኳይ ጉባኤና የአዴፓ አስቸኳይ ጉባኤ በሙሉ ድምፅ ያጸደቀው ሲሆን፣ በዛሬው ዕለት የደኢሕዴን አስቸኳይ ጉባኤ እንደሚያጸድቀው ይጠበቃል። የፓርቲው ምሥረታ ሁሉንም ሕጋዊ መሠረት የያዘና ሕግን ተከትሎ የተፈፀመ መሆኑን ስገልፅላችሁ በታላቅ ደስታ ነው።

የብልጽግና ፓርቲ ፕሮግራሙን ያሻሻለ፤ ለሚቀጥሉት ዓሥር ዓመታት ኢትዮጵያን ወደ ብልጽግና ጐዳና የሚወስደውን ዕቅድ የነደፈ ሲሆን፤ ይህንንም ከመላው ሕዝብና አባላት ጋር የሚወያይበትና የሚያዳብረው ይሆናል። ኢትዮጵያን ወደ ብልጽግና የመውሰድ ህልማችንን እውን የምናደርግበት ትክክለኛው መንገድ የተጀመረ መሆኑን ሳበሥር በታላቅ ደስታ ነው! ከዚህ ጋር ተያይዞ፣ አንዳንድ ኃይሎች ይህ አዲሱ የብልጽግና ፓርቲ አሐዳዊ ሥርዓት የሚያመጣ የፌዴራልን ሥርዓት የሚያጠፋ የሚል አሉባልታ

ሲናገሩ ይደመጣል። ይሁንና በፕሮግራማችን ላይ በግልፅ እንዳስቀመጥነው የብልፅግና ፓርቲ ኅብረ ብሔራዊት ፌዴራላዊት ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን የሚያጠናክር፤ የሚገነባ እንጂ የማያፈርስ መሆኑን በንግግር ብቻ ሳይሆን በፕሮግራማችንም ጭምር ያካተትን መሆኑን እየገለጽኩ፤ ሌሎች ፓርቲዎች ብልጽግና ፓርቲን በመክሰስ ሳይሆን አማራጭ ሐሳብ በማምጣት እንዲሞግቱንና ለኢትዮጵያ ሕዝብ አማራጭ ሐሳብ ይዘው እንዲቀርቡ በዚሁ አጋጣሚ ጥሪዬን ላቀርብላቸው እፈልጋለሁ፡፡

የብልጽግና ፓርቲ መሠረቱ በኦሮሚያ ክልል የቄሮን ትግል፣ በአማራ ክልል የፋኖን ትግል፣ በደቡብ ዘርማና ሌሎች ወጣት አደረጃጀቶች በጋራ ያደረጉትን ትግል፣ ከተረት ተረት ወደ እውነተኛ ብልጽግናና ሰላም ዲሞክራሲያዊና አንድነት ለማሸጋገር የተደረገ ሂደት መሆኑን ያምናል። ቄሮዎች፣ ፋኖዎች እንኳን ደስ አላችሁ! የታገላችሁለት ፓርቲያችሁ ተመሥርቷል። ከፓርቲያችሁ ጋር ሆናችሁ ስታነሡ የነበረውን ጥያቄ ወደ ተግባር እንዲመለስ አስፈላጊውን ጥረት እንድታደርጉ ጥሪዬን ላቀርብላችሁ እፈልጋለሁ፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ ድርጅታችን የፋኖንና የቄሮን ትግል የሚያስታውስ የተግባር ማስታወሻ እንደሚያስቀምጥ ሳበሥርላችሁ በታላቅ ደስታ ነው።

እንዲሁም የብልጽግና ፓርቲ ሥራ አስፈፃሚ አባላት በሰሞኑ ባደረጉት ውይይት በኢትዮጵያ ውስጥ የሕግ ልዕልናን የማረጋገጥና ሕግ የማስከበር ጉዳይ ዋነኛ አጀንዳ ሆኖ ተነሥቷል። ከዚህ በኋላ ኢትዮጵያ ውስጥ ማንኛውም ሰው ሐሳብ ካለው በሐሳብ ገበያ ውስጥ አሳምኖ ሥልጣን ከመያዝ ውጪ፣ በኃይል እና ትክክል በአልሆነ መንገድ የሕዝብን ሰላም የሚያውክ ከሆነ መንግሥት ሕጋዊ እርምጃ በመውሰድ የሕግ ልዕልና እንደሚያረጋግጥ፤ ፓርቲያችንም ለሕግ ልዕልና አበክሮ እንደሚሠራ የተግባባን መሆናችን ልገልጽላችሁ እወዳለሁ።





መላው የኢትዮጵያ ሕዝቦች፤ የብልጽግና ፓርቲ ያለብንን ድህነት፣ ያለብንን የዲሞክራሲ እጥረት፣ ያለብንን የሰላም ችግር በመፍታት እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ሥራ እንዲያገኝ፤ በልቶ እንዲያድር፤ በሰላም ወጥቶ እንዲገባ የሚተጋ ፓርቲ ሲሆን፤ ይህንንም በፕሮግራማችን ላይ በግልጽ ያሰፈርን መሆኑን አውቃችሁ፤ ሌሎች ከእኛ የሚቃረኑ ኃይሎች ካሉ አማራጭ ሐሳብ እያቀረቡ በሐሳብ ልዕልና ብቻ ማሸነፍ የሚችሉበትንና ሰላማዊ መንገድ የሚከተሉበትን መንገድ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ከብልፅግና ፓርቲ ጋር በመሆን እንዲያረጋግጥ ጥሪዬን ማቅረብ እፈልጋለሁ።

የብልጽግና ፓርቲ ለሰላም፣ የብልጽግና ፓርቲ ለእኩልነት፣ የብልጽግና ፓርቲ ለነፃነት፣ የብልጽግና ፓርቲ ለእውነተኛ የፌዴራል ሥርዓት፣ የብልጽግና ፓርቲ ለእያንዳንዱ ዜጋ በልቶ የማደርና ወጥቶ የመግባት ሰላምን የማረጋገጥ ተግባር ለመፈፀም ታጥቆ የተነሣ ሙሉ ዝግጅት ያደረገ ግልጽ ፕሮግራም ያለው፤ መፃኢውን የኢትዮጵያ አቅጣጫ የነደፈ መሆኑን አውቃችሁ ከጐናችን በመሆን የኢትዮጵያን ብልጽግና እውን እንድታደርጉ በታላቅ ትሕትና እጠይቃለሁ።

**አመሰግናለሁ!**

# የብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በዓል መልእክት

ኅዳር 28/2012 ዓ.ም.

**እንኳን የኢትዮጵያዊነት ቀን ለሆነው የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በዓል አደረሳችሁ!**

ይህ በዓል የአብሮነታችን በዓል ነው። ምን ያህል ልዩ፣ ክቡር፣ ውድ፣ አስደናቂ፣ ኅብረ ብሔራዊ ባህሎችና ማንነቶች እንዳሉን የምናሳይበት በዓል ነው። ይህ ብቻ ግን አይደለም። የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የተዛመዱ፤ የተጋመዱ፤ የተወራረሱ፤ የተሰናሰሉ መሆናቸውንም የምናይበት በዓል ነው። እንዲሁ ተሰባስበን አንድ ቦታ ላይ የተከማቸን አይደለንም። አብረን ኖረናል። አብረን በኖርንባቸው ዘመናት ብዙ ነገሮችን ተወራርሰናል። ስኬቶቻችንንና ድሎቻችንን ብቻ ሳይሆን መከራዎቻችንንና ግፎቻችንን ተካፍለናል። ባህሎችንና ዕሴቶችን አንዳችን ከሌላችን ወርሰናል። ተጋብተን ተዋልደን በደም ተሳስረናል። አንድ ቦታ መኖር ብቻ ሳይሆን ለአንድ ዓላማ በአንድ ግንባር ተሠውተናል። በአንድ መቃብር ተቀብረናል።

የኢትዮጵያ ብሔረሰቦች ለእኩልነት፣ ለነጻነትና ለፍትሐዊነት ታግለዋል። ራስን በራስ የማስተዳደር፣ ባህልንና ቋንቋን የማበልጸግ መብት ለማግኘት መሥዋዕትነት ከፍለዋል። ኢትዮጵያ ሁሉም እኩል መሥዋዕትነት ሲከፍሉባት የኖረች ሀገራቸው በመሆኗ ሁሉም እኩል የሚጠቀሙባት ሀገር እንድትሆን ከገዥዎች ጋር ተናንቀዋል።

ይህ የዘመናት ትግላቸው በሕገ መንግሥቱ ዕውቅና አግኝቶ ራስን የማስተዳደር መብታቸው ተረጋግጧል። በተግባር ሲፈተሽ ግን የዘረጋነው ሥርዓት ትግላቸውን በተሟላ ሁኔታ የሚመልስ፤ መብታቸውንም በእኩልነት የሚያስከብር አልነበረም። አሐዳዊነት በፌዴራላዊነት ሳይሆን በእጅ አዙር አሐዳዊነት ተተካ። ብሔረሰቦችን ራሳቸውን በራሳቸው ለማስተዳደር እንዲችሉ የተመሠረቱት አብዛኞቹ ክልሎች በጡት አባቶች እንዲተዳደሩ ተደረጉ። ክልሎች በተፈጥሮና በሰው በሠራሽ ሀብቶቻቸው የበይ ተመልካቾች ሆኑ። ሀገር ለመምራት የሚፈቀድላቸውና የማይፈቀድላቸው ብሔረሰቦች ተፈጠሩ። የተወሰኑት ከበሮውን ሲመቱ ሌሎች አጋሮች ሆነው እንዲያጨበጭቡ ብቻ ተፈቀደላቸው።

በሕዝብ መራራ ትግል የሕዝቡን ሉዓላዊነትና መብት ለማስከበር የወጣው ሕገ መንግሥት እየተሻረ የጥቂቶች አገዛዝ መስፈን ጀመረ። ሰብአዊ መብቶች ተጣሱ፤ የዜጎች ክብር ጠፍቶ ኢትዮጵያ የጨለማ እስር ቤቶችና የማሰቃያ ሥፍራዎች መናኸሪያ ሆነች። የክልሎች መሬት ያለእነርሱ ፈቃድ ለእጅ አዙር አሐዳውያን ተሸነሸነ። ሀብታቸውና ንብረታቸው ተመዘበረ፤ በየክልሉ የተዘረጉት ታላላቅ ፕሮጀክቶች የእጅ አዙር አሐዳውያን የምዝበራ ማዕከላት ሆኑ። “ለምን?” ብለው የጠየቁ ሁሉ ከአራዊት ጋር ታሰሩ። ተኮላሹ፤ እግርና እጃቸው ተቆረጠ፤ ከሀገር ተሰደዱ።

ይህ ነው እንግዲህ የኢትዮጵያን ብሔረሰቦች ወደ ዳግም ትግል የከተታቸው። ከለውጡ በፊት ወደ ነበረው ማዕበል የወሰዳቸው፤ የእጅ አዙሩን አሐዳዊነት "አንፈልግም" ብለው ለመብቶቻቸውና ለነጻነታቸው እንዲዋደቁ ያደረጋቸው። ትክክለኛውን ፌዴራላዊ ሥርዓት ለማምጣት ሲሉ አንድ ሆነው የእጅ አዙር አሐዳውያንን ለመጣል የተነሡት። ሕገ መንግሥቱ በልኩና በመጠኑ ያህል እንዲተገበር ሲሉ የሕይወት መሥዋዕትነት የከፈሉት፤

ዛሬ ያለንበት ጊዜ ለብሔረሰቦች ትግል መልስ በመስጠት ላይ ያለንበት ጊዜ ነው። የእጅ አዙር አሐዳዊነት ቀርቷል። አንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ክልል የሚባለው አሠራር ጠፍቷል። የበዬና የተመልካች አሠራር ተወግዷል። ዋናና ተባባሪ የሚባለው ክፍፍል ላይመለስ አክትሟል። አንድ ከየትኛውም የኢትዮጵያ ክልል የሚመጣ ኢትዮጵያዊ የመጨረሻውን የኢትዮጵያ ሥልጣን ሊይዝበት የሚችለው ሥርዓት ተዘርግቷል። ክልሎች በሞግዚቶች ሳይሆን በራሳቸው የሚተዳደሩበት እውነተኛው ፌዴራሊዝም መሬት ላይ ወርዷል።

የታላቋን ሀገራቸውን የኢትዮጵያን ሀብት፣ ሥልጣን፣ ክብርና ታላቅነት እንዳያልሙ ሲባል ብሔረሰቦች ስለ ልዩነታቸው እንጂ ስለ ኢትዮጵያዊ አንድነታቸው እንዳያስቡ ተደርጓል። ሀገራዊ አንድነት ከብሔር ማንነት ጋር ሆን ተብሎ እንዲጣላ ተሠርቷል። አንዳንዶች ከጠቅላላዋ ኢትዮጵያ እንዲጠቀሙ፤ ብዙዎች ግን ከአካባቢያቸው ብቻ እንዲጠቀሙ ሲሠራ ኖሯል። ያ ጊዜ አሁን አብቅቷል። እኛ ኅብራውያን ነን። ኅብር ስንል በአንድ በኩል እንደኅብረ ቀለማት የየራሳችን ማንነት፣ ታሪክ፣ ባህል፣ ቋንቋ፣ ያለን ነን። በሌላ በኩል ደግሞ "ኅብር" ስንል አብረን፣ ተባብረን የኖርን፣ ኢትዮጵያ የምትባለውን ቤት በጋራ የገነባን፤ አብረን ድል ያደረግን፤ አብረን የተጨቆንን፤ አብረን ብሔራዊ ገዥዎችን የታገልን፤ አብረን ቅኝ ገዥዎችን ያንበረከክን ነን።

ይህን በዓል ስናከብር ወደ ቀደመው አሐዳዊነትም ሆነ ወደ እጅ አዙር አሐዳዊነት ዳግም እንደማንመለስ እያረጋገጥን ነው።





ፌዴራላዊ ሥርዓታችን ስሙን ብቻ ሳይሆን ትክክለኛ አተገባበሩን በትግላችን እንደጨበጥነው እያረጋገጥን ነው። ተጨዋቾችና ተመልካች ክልሎች ከዚህ በኋላ እንደማይኖሩ እያረጋገጥን ነው። ኅብረ ሀገራዊ አንድነታችንን መቼም ቢሆን ለድርድር እንደማናቀርበው እያረጋገጥን ነው። አንድነታችን ልዩነታችንን ሳይጠቀልለው፤ ልዩነታችንም አንድነታችንን ሳይሸረሽረው አብርን ልንኖር ዳግም ቃል የምንገባበት በዓላችን ነው። ስለድህነት መቆዘማችንን አቁመን ስለ ብልጽግና ለመዘመር፤ ስለ መነጣጠል መስማታችንን ትተን ስለ መደመር አብረን ለመቆም መወሰናችንን የምናረጋግጥበት በዓላችን ነው።

ከፊታችን ያለው ዘመን መንፈሳዊ፣ አእምሯዊና ቁሳዊ ብልጽግናችን የሚረጋገጥበት ዘመን ይሆናል። ባህሎቻችን፣ ቋንቋዎቻችን፣ ዕሴቶቻችን፣ የሚበለጽጉበት ዘመን ይሆናል። አንድነታችን፣ አብሮነታችን፣ ወንድማማችነታችን የሚበለጽግበት ዘመን ይሆናል፤ በዕውቀትና በሀብት የምንበለጽግበት ዘመን ይሆናል። በፍትሕ፣ በሰላም፣ በጋራ ደኅንነት፣ የምንበለጽግበት ዘመን ይሆናል። ከአሳለፍናቸው ዘመናት ይልቅ ወደፊት የምናሳልፋቸው ዘመናት ብዙ ናቸው። ስለዚህም በቀደመው ዘመንና አስተሳሰብ ላይ ተቸክለን አንቀርም። በወደፊቱ ጉዟችን ላይ አተኩረን የብልጽግናን ጎዳና አጽንተን እንይዛለን።

በድጋሚ የኢትዮጵያዊነት ቀን ለሆነው የብሔር ብሔረሰቦች በዓል እንኳን አደረሳችሁ!

**ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራ፤**
**ተከብራና በልጽጋ ለዘላለም ትኑር!**

**ፈጣሪ ኢትዮጵያንና ሕዝቦቿን ይባርክ!**

# የገና በዓል መልእክት

ታኅሣሥ 27/2012 ዓ.ም.

**እንኳን ለጌታችን፣ ለመድኃኒታችን፣ ለኢየሱስ ክርስቶስ የልደት በዓል (ገና) በሰላም አደረሳችሁ!**

የኢየሱስ ክርስቶስ የልደት በዓል መለያየት የጠፋበት፤ መከፋፈል የተወገደበት፤ የአንድነት በዓል ነው። ሰውና እግዚአብሔር፣ ምድርና ሰማይ፣ ነፍስና ሥጋ፣ ሰውና መላእክት አንድ የሆኑበት በዓል ነው። ይህንን በዓል የምናከብረውም መከፋፈልንና መለያየትን በማጥፋት መሆን አለበት። ተፈጥሯዊ ልዩነቶች ሰውን አይለያዩትም። ተፈጥሯዊ ልዩነቶች ለሰው ልጆች ከፈጣሪ የተሰጡት ጌጦች ናቸውና። የጾታ፣ የቀለም፣ የብሔር፣ የቋንቋ፣ የአስተሳሰብ፣ የአመለካከት፣ ልዩነቶች የፈጣሪን ድንቅ ጥበብ የሚመሰክሩ ጸጋዎቻችን ናቸው።

ፈጣሪ ተፈጥሮን ያጸናት በልዩነቶች ውስጥ በሚኖር መስተጋብር ነው። ተፈጥሮ ኅብራዊ ሆና በቢሊዮኖች በሚቆጠሩ ልዩነቶች ውስጥ የምትኖር ናት። እነዚህ ልዩነቶች ግን በየራሳቸው ለብቻቸው ለመቆም አይችሉም። ከሌላው ጋር መስተጋብር መሥርተው ይኖራሉ። ብቸኝነትና አንድ ዓይነትነት የተፈጥሮ ጸጋዎቻችንን ያጠፏቸዋል። ኅብራዊ መስተጋብር ደግሞ የተፈጥሮን ህልውና ያስቀጥላል። ተፈጥሮ በልዩነትና በአንድነት መካከል የሚኖረውን ወርቃማ አማካይ ታውቀዋለች። የህልውናዋ መሠረትም እርሱ ነው።





ተፈጥሮ ፈጽማ ተነጣጥላ መነጣጠል በሚያመጣው መገፋፋት እርስ በርሷ እንዳትጠፋፋ መስተጋብራዊ አንድነቷ ይጠብቃታል። ተፈጥሮ በመሳሳብና በመዋዋጥ በሚመጣ አንድ ዓይነትነት እንዳትጠፋ ተፈጥሯዊ ልዩ ልዩነቷ ይታደጋታል። ልዩ ልዩነቷ አንድነቷን እንዳይበታትነው፤ አንድነቷም ልዩ ልዩነቷን እንዳይጠቀልለው ተፈጥሮ ወርቃማውን አማካይ ጠብቃ ትኖራለች። የልደት በዓል ይሄንን ወርቃማ አማካይ የምናስታውስበት በዓል ነው።

በልደት በዓል ሰውና አምላክ፣ እንስሳትና ሰው፣ እረኛና ንጉሥ፣ ሴቶችና ወንዶች፣ ሕፃንና አረጋዊ፣ አንበሳና ጥጃ፣ በአንድ በረት ተገናኝተዋል። እነዚህ ሁሉ በበረቷ ውስጥ ሲገናኙ ሰላምን፣ ይቅርታንና ፍቅርን መሠረት አድርገው ነው። ጠላትነት ጠፍቶ፤ መለያየት ተወግዶ፤ መወቃቀስ ተደምስሶ፤ ቅያሜ ተሠርዞ ነው። ሁሉም በበረቷ አንድ ሆነው በመገናኘታቸው ታሪክ ሠሩ። ከበሩ። የዘለዓለማዊ ክብር ተካፋዮችም ሆኑ።

ኢትዮጵያ የክብር በረታችን ናት። የተለያዩ ማኅረሰቦች፣ አስተሳሰቦች፣ እምነቶች፣ ባህሎች፣ ታሪኮች፣ ቋንቋዎች፣ ዕውቀቶች፣ ለሚበልጥ ክብር ሲሉ የተሰባሰቡባት በረታቸው ናት። እረኞች፣ ነገሥታት፣ አረጋውያን፣ ሴቶች፣ ወደ በረቷ ከመጡ በኋላ ከበፊቱ ክብራቸው የሚበልጥ ክብር አግኝተዋል። የሚበልጥ ታሪክ ሠርተዋል። በማንነታቸው ላይም ሌላ ማንነት ደርበዋል። ማንነታቸውን ይዘው በክርስቶስ አንድ ሆነዋል። ኢትዮጵያም እንዲሁ ናት። በኢትዮጵያ በረት ውስጥ ያሉት ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች ሁሉ ኢትዮጵያዊነት የሚለውን የአንድነት ክብር ደርበዋል። ይህ ክብር በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ላለፉት፣ ኢትዮጵያንም ለመሠረቱት ብሔሮችና ብሔረሰቦች ብቻ የሚሰጥ ክብር ነው። በነበራቸው ማንነት ላይ የሚደርቡት ማንነት፤ በነበራቸውም ክብር ላይ የሚደርቡት የላቀ ክብር ነው።

ኢትዮጵያ እንደ ቤተልሔሟ በረት መለያየት፣ መከፋፈል፣ መጠላላትና መቀያየም የሚጠፋባት፣ ሕዝቦቿ አንድ ሆነው ታሪክ የሚሠሩባት ናት። ይህን አንድነት ለመበተንና አዲስ ጠላትነትን ለመትከል የሚጥሩ የሄሮድስ ቢጤዎች መኖራቸው አይቀሬ ነው። የበረቷ ብርሃን ያስጨንቃቸዋል። የበረቷ ክብር ያስፈራቸዋል። የበረቷ አንድነት ይቆረቁራቸዋል፤ የበረቷ ፍቅር ሰላም ይነሣቸዋል።

ይሄን ልዩ ፍቅር፣ ይሄንን አንድነት፣ ይሄንን ሰላምና ፍቅር ለመተናኮል ሄሮድሳውያን ሰይፋቸውን ያነሣሉ። ክርስቶስንም፣ ድንግል ማርያምንም፣ ዮሴፍንም፣ ሰሎሜንም፣ እረኞችንም፣ የጥበብ ሰዎችንም አያገኟቸውም። ሰይፋቸው የሚያርፈው ምንም በማያውቁ የቤተልሔም ሕጻናት ላይ ነው። ሐዲሳን ሄሮድሳውያንም በአካልና በወሬ የሚሠነዝሩት ሰይፍ የሚጎዳው በአካልና በአእምሮ ሕፃናት የሆኑትን ነው። የሚያልቁትና እያለቁ ያሉት ሕፃናቱ ናቸው። አድገን፣ ተምረን፣ ወላጆቻችንን እንረዳለን፤ ለሀገር ለወገን እንተርፋለን ብለው የሚጓጉት ሕፃናትና ወጣቶች ናቸው እየተጎዱ ያሉት፤ ሄሮድሳውያን ደግሞ ለልጆች አያዝኑም።

ሄሮድስ ምንም ያህል ሰይፍ ቢመዝዝ፤ ምንም ያህል ሕጻናትን ቢጎዳ፤ ምንም ያህል ለጊዜው ችግር ቢፈጥርም፤ የክርስቶስን ተልእኮና ጉዞ ግን አልገታውም። ሄሮድስ ክፉ ታሪኩን ትቶ ጠፋ። ክርስቶስ ግን የዓለም ብርሃን ነው። የቤተልሔሙ ብርሃን ለዓለም ተርፏል። የቤተልሔሙ ፍቅርና አንድነት ለዓለም ተርፏል። የቤተልሔሙ ሰላምና ይቅርታ ለዓለም ተርፏል። ሄሮድስ ግን የለም። ለዚህ ነው ሄሮድስነትና ከሄሮድስ ጋር መቆም ከጊዜያዊ ትርፍ ያለፈ ነገር አያስገኝም የምንለው፤ የበረቱ ዜጎች መሆን ጊዜያዊውን ፈተና የሚሻገር የላቀ ክብር አለው ብለን የምናምነው፤





በቤተልሔም የዛሬ ሁለት ሺሕ ዓመታት የተፈጸመውን አስደናቂ ታሪክ ለማሰብ ዛሬም በየዓመቱ ሚሊዮኖች ወደ ቤተልሔም ይጎርፋሉ። በኅብረ ብሔራዊነት ያገኘናቸውን ጸጋዎች ይዘን ኢትዮጵያዊ አንድነታችንን ካጸናን፤ ልዩነት መለያየት፣ አንድነት መጠፋፋት አለመሆኑን ከአስመሰከርን፣ ሄሮድሳውያንን ተሻግረን ለትውልድ የሚተርፍ ታሪክ እንሠራለን። ሚሊዮኖችም ይህንን ታሪክ ለማየት እንደ ቤተልሔም ወደ ኢትዮጵያችን የሚጎርፉበት ዘመን ሩቅ አይሆንም።

## መልካም የልደት (የገና) በዓል ይሁን!

# የጥምቀት በዓል መልእክት

ጥር 10/2012 ዓ.ም.

ኢየሱስ ክርስቶስ በፈለገ ዮርዳኖስ ከመጠመቁ በፊት የሰው ልጅ ውኃን የሚያውቀው በመዓትነቱና በእንቅፋትነቱ ነበር። በኖኅ ዘመን የሰው ልጅ የጠፋው በውኃ ነው። እስራኤላውያን ከግብጽ ወጥተው ወደ ከነዓን ሲጓዙ መንገድ የዘጋባቸው የኤርትራ ባሕር ነበር። ኢያሪኮን ተሻግረው ወደ ምድረ ርስት ሲገቡ የዘጋባቸው የዮርዳኖስ ወንዝ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ በማዕከለ ዮርዳኖስ ሲቆም ግን ለመዓት የነበረው ውኃ ለበረከት ሆነ። ይሄው ዛሬም በየዓመቱ ወደ ውኃ ወርደን የጥምቀትን በዓል እናከብራለን።

በዓለም ላይ አዲስ ሀብት ይፈጠራል ብለን መጠበቅ የለብንም። ለችግር፣ ለመከራና ለመዓት ሲውሉ የነበሩ ነገሮችን ነው ወደ በረከት መቀየር ያለብን፤ የሰው ልጅ በጥንተ ጠላቱ ምክንያት በጥፋቱና በስንፍናው ውኃን የመዓት ማዝነቢያ አድርጎት ነበር። ክርስቶስ ያንኑ ውኃ ለበረከት እንዲሆን አድርጎ ለውጦታል።

በሀገራችን በጠላት ግፊት ለመዓት የዋሉና ለበረከት ልንቀይራቸው የሚገቡን ብዙ ሀብቶች አሉን። ለምሳሌ፤ ብዙኅነታችንን ብንወስድ የመለያያና የመከፋፈያ





ምክንያት እየሆነብን ነው። ከአወቅንበት ግን ብዙኅነታችንን ለበረከት ማድረግ እንችላለን። ብዙኅነት ማለት ብዙ ዕሴት፣ ብዙ ጸጋ፣ ብዙ ሀብት፣ ብዙ ቅርስ፣ ብዙ ታሪክ፣ ብዙ ቋንቋ፣ ብዙ ባህል ማለት ነው። የሌላው ዓለም ሰዎች ይህን እኛ ያለንን ብዙ ሀብት ፍለጋ ዓለምን ይዞራሉ። እኛ ግን በሀገራችን ውስጥ ዓለምን የሚያስደንቅ ብዙኅነት አለን። አጠቃቀማችንን በጥበብ ብናደርገው ኢትዮጵያችን የሰው ልጅ ሀብቶች መናኸሪያ ናት።

ክርስቶስ ውኃን የቀደሰው ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ነው። ወደ ውኃው ሄዶ ነው። ማዕከለ ባሕር ቆሞ ነው። በውኃው ተጠምቆ ነው። እኛም መከተል ያለብን ይሄንን ነው። ራሳችንን ከሰቀልንበት ማውረድ፤ አንዳችን ወደ ሌላችን መሄድ፤ በሌላው መካከል መገኘት። ሌላውን የራሳችን ማድረግ፤ አንዳችን ከሌላችን መማር፤ በረከት የምናገኘው ከዳር ቆመን አይደለም። መሐል ገብተን እንጂ፤ ከሩቅ ሆነን አይደለም። ወደዚያው ተጉዘን እንጂ፤ እላይ ነን ብለን አይደለም። ወደ ሕዝቡ ወረድ ብለን እንጂ፡፡

ለመሆኑ፤ ሰፈሮቻችን፣ ክልሎቻችን፣ የአስተዳደር ወሰኖቻችን የጉዳት ምክንያት እንዲሆኑ ለምን እንፈቅድላቸዋለን? ለምን የበረከት ምክንያት አናደርጋቸውም? ለምን የግጭትና የመለያየት መንሥኤ ይሆኑብናል? ለምን የእኔ የእኔ እንባባልባቸዋለን? ለምን የመጋደያ ዐውዶች እናደርጋቸዋለን? ኢትዮጵያ የሁላችን መሆኗን ብናምን፤ በወሰኖቻችንን ላይ ሰፋፊ ገበያዎችን ብንዘረጋ፤ አንዱን ክልል ከሌላው የሚያገናኙ አካባቢዎችን በጋራ ብናለማ፤ አንዳችን ወደ ሌላችን ሰፈር ሄደን አብረን የመኖር ነባር ዕሴታችን ብናጠናክር፤ የሁላችን የሆነውን ሜዳ ለጋራ እርሻ፣ ወንዙን ለጋራ መዋኛ፣ ተራራውን ለጋራ መዝናኛ፣ ጫካውን ለጋራ መናፈሻ ብናውለው መዓቱን በረከት አደረግነው ማለት ነው። የሚያጣላን ሀብቱ አይደለም። አስተሳሰባችን እንጂ፤ አእምሯችን ውስጥ የገነባነውን ግድግዳ ካፈረስነው መሬት ላይ ያለው አጥር ገድቦ አይገድበንም። በአእምሯችን ያስቀመጥነው ክልል ካልሆነ በቀር መሬት ላይ

ያለው መንደር በፍቅር ከኖርንበት ጠብቦ አይጠበንም።

በታሪኮቻችንና በቅርሶቻችን፣ በጀግኖቻችንና በታሪካዊ ኩነቶቻችን ለምን እንጣላለን? እነዚህን ነገሮች የመዓት ማውረጃ ለምን እናደርጋቸዋለን? ለምን ወደ በረከት አንቀይራቸውም? ክፉውንም ደጉንም ታሪክ እንቀበለው፤ ያለፈውን በይቅርታ እንዝጋው፤ ታሪካዊ ቦታዎቻችንን የቱሪስት መስሕቦች እናድርጋቸው፤ ጀግኖቻችንን ለሚያከብሯቸው እንተውላቸው። የግድ ሁላችንም ካልተስማማንባቸው ብለን አንቆራቆስባቸው፤ ታሪካዊ ሁነቶችን አዳዲስ ዕሴቶች ጨምረን እንዘክራቸው፤ ያልተሟሉ ታሪኮቻችንን ጥናትና ምርምር አድርገን እናሟላቸው፤ እያፈረስን መሥራቱን ትተን እያሟላን እንሂድ፤ ያን ጊዜ ለመዓት እየዋሉ ያሉት ታሪካዊ ሀብቶቻችን የበረከት ምንጮች ይሆናሉ።

አደጉ የምንላቸው ሕዝቦች ሁሉ ያደጉት መዓቱን ወደበረከት መቀየር በመቻላቸው ነው። የበለጸጉ ሕዝቦች የብልጽግናቸው ምስጢር ሌላ ሳይሆን ችግርን ወደ ዕድል የመቀየር ችሎታቸው ነው፡፡ እነዚህ ሕዝቦች በረዶውና ሙቀቱ ያስቸገራቸው፤ ረኃቡና ወረርሽኙ ያስመረራቸው፤ ጦርነትና ስደት ያሰቃያቸው ነበሩ። ችሎታቸውን በመጠቀም የሚያስመርረውን የአየር ንብረት፣ ፈታኙን መልከአ ምድርና አስቸጋሪውን ተፈጥሮ ወደ በረከት ቀይረው ዛሬ ምቹ ሀገር ገንብተዋል፡፡ ያለችግር መፍትሔ፣ ያለፈተና ጥንካሬ፣ ያለጨለማ ብርሃን አይኖርም፡፡ የሳይንስና የቴክኖሎጂ ውጤቶችን ያሳደገው፣ ዘመናዊነትን ያመጣውና ሥልጣኔን የወለደው ችግርና ፈተና ነው። ሰዎች በብልሃት ከያዙት ከመዓት ውስጥ በረከት የሚሆን ነገር ማውጣት ይችላሉ።

“ሺህ ጊዜ ጨለማን መውቀስ ብርሃንን አያመጣም” እንደሚባለው ባለንበት ተተክለን መዓቱን ብንረግመው በረከት አይሆንም። ከቁልሉ ላይ እንውረድ፤ ከከፍታው ዝቅ እንበል፤ ወደ ውኃው እንሂድ፤ በውኃው መካከልም እንቁም፤





ራሳችንን እላይ ሰቅለን ከተደላደልን የሚመጣ ለውጥ የለም። ሌላው ወደእኛ እንዲመጣ ብቻ ከተመኘን የሚመጣ ለውጥ የለም። “ውጡ” ማለት ትተን እኛ ራሳችን እንውረድ፤ “ኑ” ማለ ትተን እንሂድ፤ ከዳር መሆን ትተን መሐል እንግባ፤ ያን ጊዜ የምንፈልገው በረከት ይሆናል።

የሰው ልጅ ሊያየው ሲመኘው የኖረው ምስጢር በጥምቀት የተገለጠው በዚህ ምክንያት ነው፡፡ ከላይ በመውረድ፣ ወደ ውሃውም በመሄድ፣ በውሃው ውስጥም በመግባት፤ ኤፒፋንያ (መገለጥ) የተባለውም ለዚህ ነው። አብ በደመና፤ መንፈስ ቅዱስ በርግብ አምሳል፣ ወልድ በዮርዳኖስ አስደናቂው ምስጢር የተገለጠው በዚህ ነው።

አንድ የምንሆንበት፣ የምንሠለጥንበት፣ የምንበለጽግበት፣ የምንዘምንበት፣ የምንፋቀርበት ምስጢር እንዲገለጥልን፤ ኑ ሁላችንም ከላይ እንውረድ፤ የችግርና የፈተና ምንጭ በመሰለን ነገር መካከል እንገኝ፤ ከሩቅ መመልከታችን አቁመን መካከል ላይ እንቁም። በቋንቋው፣ በባህሉ፣ በበዓሉ፣ በታሪኩ፣ በወጉ መካከል እንሁን። በጥምቀት በዓል ሕዝቡ ሁሉ ቤቱን ትቶ፤ ሠፈሩን ትቶ፤ ጎጡን ትቶ ሁሉን ወደሚያካትተው ባሕር ይወርዳል። ሁሉን ወደሚያካትተው ሜዳ ይሰባሰባል። ኑ እኛም ምሽጎቻችንን ትተን ሁላችንም ወደምንገኛኝበት ወደ ሰፊው ሜዳ እንሂድ። የራሳችን የምለው ሁሉ ይዘን፤ ከሌላው ጋር አብረን ለመሆን ወደሰፊ ሜዳ እንሂድ።

በጥምቀት ጊዜ ሁሉም ያለውን ይዞ፣ በየወጉ ለብሶ፣ በየቋንቋው እየተናገረ፣ በየባህሉ እየጨፈረ በአንድ የጥምቀት ሜዳ ይገናኛል። ኢትዮጵያ ዓይነተ ብዙ፣ ጸጋ ብዙ፣ ሀብተ ብዙ፣ ባህለ ብዙ መሆኗን ይመሰክራል። ሁሉም ይወርዳል፤ አንዱ በሌላው ሙዚቃ ይዋባል፤ አንዱ በሌላው ቋንቋ ያወጋል፤ አንዱ በሌላው ልብስ ያጌጣል፤ አንዱ የሌላውን ባህል ይወርሳል። ጠላታችን ለመዓት ሊያደርግብን የነበረውን ነገር ሕዝባችን ለምሕረት ያደርገዋል። የሚያዋጣንም ይኸ ነው።

**መልካም የከተራና የጥምቀት በዓል ይሁንልን!**

**ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት**
**ታፍራና ተከብራ ለዘላለም ትኑር!**

**ፈጣሪ ሀገራችንና ሕዝቦቿን ይባርክ!**

**አመሠግናለሁ!**



የካናዳው ጠቅላይ ሚኒስትር ጀስቲን ትሩዶ ጉብኝት

# ከመጋቢት እስከ መጋቢት

## መግለጫዎች እና መልእክቶች
## እንግሊዘኛ

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት



# Message to the people and Government of Eritrea on the occasion of Independence Day

June 19, 2019

**I would like to convey my congratulations to the people and Government of Eritrea on the occasion of the 28th Anniversary of Independence Day.**

On behalf of the people of Ethiopia and on my own behalf, I wish to express my conviction that the reestablishment of mutual trust between Ethiopia and Eritrea will continue

to further deepen the ties between our two countries and that of brothers and sisters across borders that have regained the impetus to build their relations.

I also wish to express Ethiopia's readiness to remain committed to jointly addressing all outstanding issues that we face and to strengthen bilateral relations in all aspects for the mutual benefit of our two countries.

**May peace and prosperity prevail for the people of Eritrea.**





# Message for Christmas

January 6, 2020

**Wishing you a joyous celebration of the birth of our Lord and Saviour, Jesus Christ.**

The celebration of the birth of Jesus Christ is a holiday of unity which marks dissolution of separation and enmity. It is a celebration that marks the unification of humans and God, heaven and earth, soul and body, humans and angles. Hence, we should celebrate this holiday by eliminating separation and divisions. Natural distinctions do not divide people since they are the beauty marks granted to them from the Creator. Diversity in sex, colour, nationality, language, thinking, perspective and more are our treasures that testify the wisdom of the almighty.

Nature exists in harmony enveloped within diversity. Its diverse components cannot stand in separation from the others. Harmonious interaction is what continues the existence of creation. Nature understands the golden

balance between unity and diversity. Christmas is a holiday which reminds us of this golden balance.

Through the birth of Christ, man and God, shepherd and king, men and women, child and elder, lion and calf connected in a manger. Their meeting in the manger is based on forgiveness and love. Enmity was destroyed, division was abolished, accusation was eliminated, vengeance was erased in that meeting. Since they connected in that manger in unity, they made history happen, they were glorified and became partakers of eternal glory.

Ethiopia is our manger of pride. Diverse communities, thoughts, religions, cultures, histories, languages and knowledge have made Ethiopia their common abode. All nation nationalities residing in Ethiopia's manger are adorned with the glory of being Ethiopian.

Being Ethiopian, just like the manger in Bethlehem, is where division, separation and enmity lose ground. There are always those like Herod who would try to destroy Ethiopia's unity and attempt to build enmity. They are terrified with the light in the manger, frightened with its glory, discomforted by its unity and troubled by its love and peace.

Those belonging to Herod raise their swords to challenge this unique love, unity, and peace. They will not have





the chance to meet Christ, the virgin Mary, Salome, the shepherds or the wise men. Their swords rest on the innocent children of Bethlehem.

Millions of pilgrims make their way to Bethlehem to celebrate the wonderful miracle that happened two thousand years ago. When we carry with us the treasures of our diversity and solidify our unity as Ethiopians; and we testify that differences are not divisions and that unity does not amount to assimilation, only then can we move past the Herods of our time to make history that anchors the generations to come. It will not be long for millions to journey to Ethiopia, as they do to Bethlehem, to witness this monumental history.

**Merry Christmas to all!**


የቦረና ማኅበረሰብ ተወካዮች ውይይት

# ከመጋቢት እስከ መጋቢት

## መግለጫዎች እና መልእክቶች

## አፋን ኦሮሞ

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት

የካቲት
፳፻፲፫



# Ergaa Ayaana Irreechaa

Onkoloolessa 3 bara 2019

## Irrechi SonawwanSirna Gadaa Keessaa Mallattoo Nageenyaaa fi Tokkummaati

**Irreechi nageenya, jaalala, araaraa, fi tokkummaatiif.**

Kabajamaa fi hammataa uummata Oromoo! Hunda dura bega guyyaa kabaja ayyaana guddaa galateeffannaa, jaalalaa, qulaqullummaa, nageenyaa, dhifaamaa, araaraa fi aa ntummaan namoomaa itti lallabamuu fi dhugoomu kanaan nagaangeessan, bega gammaddan.

**Sirni Gadaa qabeenya guduunfataa uummata Oromooti**

Qabeenya dibii madda siyaasaa fi bulchiinsa Oromoo jaarraawwanii kan ta'e sirni Gadaa Oromootiin sirna akka barii birraati miidhagee achii as be'ee dha. Sonawwan

sirna Gadaa keessaa tokko kan ta'e ayyaanni irreechas ukkaamsaa buttaafatee, akka ilillii birraatti daraaruun isaa ibsituuu dandamannaa fi bu'aa wareegama qabsoo dhalootaati.

## Irrechi ayyaana galateeffannaa fi kadhannaati

Uummanni Oromoo Waaqa waa hunda uume, Waaqa ardii fi samii, lagaa fi galaana, halkanii fi guyyaa, ifaa fi dukkana, du'aa fi jireenya, ganna, roobaa fi obonboleettii, akkasumas biqilaa, horii fi nama uume, Waaqa abbaa hundumaaf sirna galata itti galchuu fi ulfina itti kennuu dha.

Uummanni Oromoo qabeenyaa fi eebba, nageenyaa fi gammachuu, fayyaa fi umurii, jaalalaa fi ulfina, ifaa fi abdii argateef, baraa baratti, tibba tokko irraa kan biraatti nagaan ce'uu isaaatiif irreeffatee Waaqa galateeffata. Irreechi birraa riqicha gannaa fi bonaa, waqtii ayyaaneffannaa fi aarra-falfannaa ta'e kun, uummata Oromoo biratti tibba araaraa fi utubaa jaalalaati. Umaa fi uumamni ni dinqifatama.

Waqtiin irreecha birraa kun bacaiin gannaafi dukkanni roobaa darbee, wayita birranbari'u, kan facaafatandaraaree ija godhatee, lagni guute hir'atee yeroo lafti qooru, ollaan walitti bahee ifa birraa wayita simatuu fi dhangaa gammachuu waliin sooratu, Waaqa kanaan isa gahe galateeffatee, gammachuu isaa ibsata."ganna bacaqii dabartanii, baga booqa birraa geessan!"jechuunis ergaa gammachuu waliif dabarsa.

## Irreechi ayyaana harriiroo fi nagayaati

Irreechi Oromoo biratti ayyaana hariiroonuumaa fi uumammaa ittiin ibsamu dha. Uumaan nama, bineensa, biqiloota, beey'ilada, lageenii fi gaarota uumauun wal danda'anii akka jiraataniif sirna hariiroo uume ni dinqifatamal; ni eebbifama; ni galateeffama. Lubbu-qabeeyaiif soorata, lubbu- dhabeeyyiif sirni labata isaanii akka addaan hin cinneef icciitii addaatiinaala waan mijeesseef uumaan ni jajama. Oromoon duudhaa uumaa nageenyaafi tasgabbii qaba. Obbolummaa,jaalalaa fi tokummaa labsa.

## Irreechi guyaa waadaa/irbuuti

Uummatni Oromoo dhiiraa- dhalaan, umurii, ilaalcha siyaasaa fi amantaan otoo addaan hin daanga'inii fi wal hin qoodin waltajjii aadaa fi seenaaisaa, tokkumaa fi obbolummaa isaa ittiin ibsatu, ittiin haaromfatuu fi ittiin cimsatuu dha.

Gama kanaann hambaan aadaa kiliyaa ( intangible) mallattoo eenyummaa saba tokkoo ta'uusaa fi eenyummaan kun itti fufiinsa qabaatee dhalootaa- dhalootatti akka ce'u kangargaaru ta'uu irreechi raga ifatti mirkaneessuu dha. Kanaafuu, Oromoof ibsituu eenyummaa fi guyyaa gammachuu ta'ee bara-baraankabajama jiraata.

## Tumaan irrechaa jajjabaa, sirni isaas cimaa dha

Oromoonn dhufaa-darbaa du'aa fi jireenyaa (ganni bahee bonni mare dhufuu, dukkani darbee ifatti naanna'ee dhufuusa) "Mareewoo, mareewoo " jechaa hojii dinqii Waaqaa galateeffate. Seerri uumaa kun otoo hindabinmersaa isaaa eegatee akka itti fufu galateeffachuu fi kadhachuuf kabajma dinqiin kun hundaa'eera. Irreessa qabatee irree waliif ta'uu ibsata. Wal bira dhaabbatee bara darbuu fi rakkoo injifachuufis human gabbifata. Kanaafuu, duudhaankun malattoo tokkummaa fi waliin jireenyaatis.

## Irreechi irree fi mallatoo sabboonummaa oromooti

Dukkana cunqursaa umurii dheeraa lakkoofsise keessatti kan hin badnee fi hin moofomne, sammuu fi miira dhalootaa keessatti kan hin dagatmnee fi hin kulloome ta'ee jaarraawwaniif kan ture dha.

Irreechi eenyummaa sabummaa fi sabboonummaa Ofomoo irratti waan hodhameef humni kamuu dhaabuu hindandeenye. Duudhaa hammattummaa fi waliin jireenyaa ummattummaa Oromootiif dilbii qaneenyaa ta'ee itti fufa. Sabboonummaa Orommootiif dirriba ta'ee fullaa'a. kanaafuu, miidhaginni ayyaana irreechaa kan har'aa fi ammaa qofa otoo hin taane, dhalootaa dhalootatti kan ce,u dha.





## Irreechi mallattoo dhufaa- darbaa dhalootaati

Falaasamni sirna Gadaa akka hambaa addunyaatti galmaa'ee jiru, sirna dimokiraasii umurii irraa-jala irratti hundaa'e of-keessaa qaba. Hangafti quxisuu gahoomisuun, quxisuun immoo hangafa kabajuudhaan dhalootaa dhalootatti darbaa har'a kan gahe sirni irreechaa, sima ta'uurra darbee madda bulchinsa amayyaa ta'ee jira. Kanaanis duudhaa ilma namaa kabajuu fi ofitti qabu addunyaaf gumaacheera.

Ayyaanni irreechaa bara kanaa, falaasama sirna Gadaa keessatti hammattoo dimokiraasii fi aantummaa dhala mamaaf qabnu kan ittiin ibsinu, nageenyaa fi badhaadhummaa biyyaa fi ummataa kan ittiin labsinuu fi dilbii duudhaa keenyaa addunyaatti kan ittin mul'ifnuu dha.

## Irreechi calaqqee Oromummaa keessaa miidhagaa fi hirmaachisaa dha

Oromummaan hirmaachisu mmaa dha, aadaa waliin mari'achuu, waliigaluu fi mala hoggansaa sirna Gadaa irraa arganneen kaayyoo misooma saffisiisuu dhaloonni itti wareegame dhugoomsuuf hojjechutu nurraa eegama. Har'airreechi ayyaanaa fi sirna saba tokkoo ta'uu bira darbee, mallattoo hariiroo fi waliin miidhaginaa ta'aa jira. Ummattootni biroon sonawwan sirna Gadaa itti

dhiyeenyaan hordofanii fi faayidaa isaa hubatan waliin kabajuu eegalanii jiru. Kun ammo carraa guddaa biyya hunda keenyaaaf taatuittiin uumnu keessaa tokko ta'ee, abbaa sirna kanaa kan ta'e ummata Oromootiif infifanno guddaa dha. Seenaa fi duudhaa ummattoota biro xiinxalee waliin jireenya isaatiif itti fayyadamuufis carraa biro kanuumu dha.

## Oromummaan har'a irra dhaabbatanii egeree ijaaruu dha

Wal-harkaa fuudhiinnsi baallii Gadaa Meelbaa hanga Michilleetti jiru madda muuxannoo har'aa irra dhaabbatnii bor ilaaluu fi egeree ijaaruuti. Iccitiin duudhaa nageenuummaa Oromoos kanarraa madda. Aangoof jedhee wal hin jifatu. Wal-shakkii fi hamii hin fedhu, hin jaal'atus. Marsaan Gadaa tokko xumuramee gara marsaa birootti wayita ce'u, wal-hubannaa fi wal – dhageettiidhaan murteessa. Sirnaan hoggamamee wal-harkaa fuudhiinsa aangoo raawwata. Adeemsa kanaan amanamummaa isaas mirkaneeffata. Her'as ta'u kan nu baasuu fi rakkoo keenaaf furmaata ta'u, duudhaa Oromummaatti deebi'uudhaan sirna ammayyaa waliin wal-simsiifnee itti fayyada muu qofaa dha.

## Irreechi qulqullina

"Qufaa'aa hanna dhaquun hin hin danda'amu!" akkuma jedhamu, Oromummaa keessatti haaloo qabatanii waaqa kadhachuun hin ta'u, fudhatamas hin qabu. Oromoon galata galchuu dura gochaa qajeelummaa fi qalbii qululluuf durda kenna. Oromoon qalbii qulqullun waaqa isaa kadhatu isa kufe lafaa kaasa, jibba irra jaalala dursa. Lmalli isaas malaa fi kabaja irratti kan hundaa'ee dha

## Oromoon wal-dhabdee kamiyyuu gorsaa fi mariin furuu filata

Oromoon yoo garaa hammaate yookaan jibbee yoo garaa kutate abaaree balleessa; muka jiidhaa gogsa. Uoo fedhee fi jaal'ate, balleessaa yoo irratti arges ni gorsa. Har'as akkuma kaleessaa dhaloota abdiin guutameee dha. Waan yaadee fi kaayyeeffate mikeeffachuuf dhaloota miira ni danda'amaatiin hojjechaa jiruu dha. Wantoota adda tulluutti dura dhaabbatan hedduuf harka kan hin kennannee fi kan hin jibeenfannee dha. Boqonnaa qabsoo irra geenye kanattis garaa dhiifamaa fi qalbii guutuudhaan wal-tumsuu fi imala qabsoo keenyaa ceesifachuun abshaalummaa guddadha.

## Irreechi nageenya

Nageenyi keenya harka keenya keessa jira. Nageenya mirkneeffachuun carraa egeree keenya murteeffachuuf har'a hojjechuu qabna. Duudhaalee keenya fayyadamnee nageenyi amansiisaan akka uumanu gochuun ofis biyyas ijaaruu qabna. Yoo kena gone, guddummaaa ummatummaa fi duudhaa keenyaa ni mirkaneessina.

Yaada mo'ataa fi tarkaanfataa biyya bira darbee addunyaa amansiisu maddisiisuundantaa keenya guutummaatti kabachiisuun akka danda'amu shakkiin hin jiru.

### Irreechi falaasama Gadaa, dudhaalee fi shfuu isaa ijaarsa biyyaaf kanitti oolchinu dha

Irreechi amantaa, umurii fi ilaalchi hundumtuu garaa-garummaa tokko malee kan itti hirmaatan waltajjii heedduminaa fi tokkumaati. Ayyaanicha irratti adda-addummaanakka miidhaginaa fi ciminaatti fudhatamee tokkumaan Oromoo (Oromummaan) ni faartana, ni dinqisiifatama, ni leellifaama, ni Ijaarama, ni haaromfama, ni cima.waadaan/irbuun tokkummaa, jaalalaa, obbolummaa, wal-danda'uu ni seeneffama, ni haaromfama. Tokkumman caalmaa qabu ni uumama, baraa-barattis ni ce'a. amala addaa irreechi qabu fudhannee Itoophiyaa hunduma keenyaaf taatu ijaaruut heddumina sabaa fi sab-lammootaa fayyadamuu qabna, sab-daneessummaa milkeessina.

### Irreechi ayyaana abdii fi ce'umsaati

Aadaa keenya danuu keessaa kanneen walitti dhufeenyaa fi obbolummaa cimsan adda baasnee kabajuun tokkummaa fi ijaarsa biyyaaf faayidaa gudaa qaba. Kanaafuu, uummattootni itoophiyaa roga biyyattii hundaan jiratan waggoottan itti aanan keessatti irreecha akka waliin irreeffannu dhaamsa koon dabarsa.





### Xumura irratti irreechi mallattoo Oromummaa keenyaati

Ilmaan Oromoo gola Oromiyaa mara irraa jaarsa, jaartii, xiqqaa fi guddaa,akkasumas gandaa fi amantiin osoo adda hin bahin taatee midhaagaa fi hawataa ta'e tana hafuura tokkuummaa fi gamataa jalalaan waliin baanee ardaalee irreechaa hundaa irratti waliin irreeffachuun, ayyaanni irreechaamallattoo tokkummaa fi calaqqee eenyummaa Oromoo ta'uu isaa yeroo kamiyyuu caalaa akka mirkanaa'u taasisuu keessatti hirmaannaa naamusaa fi ilaa fi ilaameen qajeelfame gochuu keessaniif galata guddaan isiniif dhiyeessaa. Garafuula duraattis dirree kamiyyuu keessatti tokkummaa keenya caalaatti akka jabeeffannuuf waamicha Oromummaa koo isiniif dhiyeessuun barbaada.

Waaqa rooba hamaa fi dukkana gannaa nu ceesiseef galatni haa ga'u; irreechi sirna kennaa birraa waliin itti dhamdhamnu, kan gara injifannoo haarawaatti ce'uuf waadaa keenya itti haaromsinu, jaalalaa fi hammataa ta'uudhaanjibbiinsa kan itti mo'annu nuuf haa ta'u

## Galatoomaa!

**Itoophiyaan tattaafii ijoollee isheetiin oodamtee fi kabajamtee bara baraan haa jiraattu.**

**Uummaan Itoophiyaa fi ijoollee ishee haa eebbisu.**

# Ergaa Ayyaana Qillee

Amajjii 6 bara 2019

**Baga guyyaa dhaloota gooftaa keenya Yesuus Kiristoos, ayyaana Qilleen nagaan isin gahe**

Ayyaanni guyyaa dhaloota Yesuus Kiristoos kan addaan bahuun itti bade, wal-qoodinsi kan itti dhabamsiifame, ayyaana tokkummaati. Ayyaanni kun namaa fi waaqni, lafaa fi samiin, lubbuu fi foon, namaa fi ergamaan, kan tokko itti ta'ani dha. Ayyaana kana kan kabajnus wal-qoqqoodinsaa fi addaan bahiinsa balleessuun ta'uu qaba. Namoota gidduutti garaagarummaan uumamaa, garaagarummaan koorniyaa, garaagarummaan bifaa, garaagarummaan sabummaa, garaagarummaan afaanii, garaagarummaan yaadaa fi garaagarummaan ilaalchaa hojii uumaa fi uumamaa kennaa addaa ta'uu isaa kan nuuf mirkaneessani dha. Uumaan kan jireenya itti-fufaa godhe uume walitti hidhamiinsa jiruu fi jireenyaani dha. Uumamni daneessummaan garaagarummaa biliyoonotaan lakka'amu keessa jiraatti. Garaagarummaan kanneen garuu, kopha kophaa isaanii dhaabbachuu hin danda'an, kaan waliin walitti dhufeenya ijaarratanii jiraatu malee. Kophummaa fi gos-tokkummaan kennaa uumamaa keenya balleesa. Walitti dhufeenyi daneesummaa keessummeessu ammoo waliin jireenya itti-fufsiisa. Uumamni giddu-galeessummaan garaagarummaa fi tokkummaa gidduu miidhagina jiru ni beekti. Utubaan jiraachuus kanuma.

Uumamni addaan baatee qabduun akka wal-hin balleessineef, tokkummaan madaallii uumama ishee ni tiksa. Uumamni gos-tokkummmaan akka wal-hin harkifnee fi wal-hin liqimsineef addummaan ishee gidduu jiru ishee baraara. Addummaan ishee akka tokkummaa ishee hin diigneef, tokkummaan ishees akka addummaa ishee hin dhuunfanneef giddu- galeessummaa madaallii uumamaan jiraachifti. Ayyaanni Qillees madaallii giddu-galeessaa ajaa'ibaa ta'e kana kan ittiin yaadannu dha.

Kabaja ayyaana kanaan, namnii fi rabbi, bineeldotnii fi namni, tiksee fi mootiin, dubartootnii fi dhiirri, daa'imanii fi maanguddoon, mooraa horii tokkotti wal-arganii jiru. Mooraa kana keessatti wayita wal-arganis nagaa, dhiifamaa fi jaalala bu'uura godhataniitu. Diinummaan badee, wal-qooduun dhabamsiifamee, wal-himachuunis maqfamee, mufiinis haqameeti. Hundinuu mooraa sanatti tokko ta'anii waan wal-arganiif seenaa hojjetan. Balbalicharraas kabaja bara baraa qooddachuufis carraa argatan.

Itoophiyaan mooraa kabajaa keenya. Saboonni garaagaraa, yaadamoonni, amantiiwwan, aadaaleen, seenaawwan, afaanotni, beekumsi garaagaraa, kabaja caalmaaf jecha, mooraa keessatti wal-gahani dha. Tikseewwan, mootiiwwan, maanguddoonni, dubartoonni, gara mooraa erga dhufanii booda, kabaja isaanii duraa caalu kabaja argatanii jiru. Seenaa caalus hojjetanii jiru. Eenyummaa isaanii irratti eenyummaa biraa dabalatanii jiru.

Kennaawwan Itoophiyaa keessa jiran, saboonnii fi sab-lammoonni hundi Itoophiyummaa kan jedhu kabaja tokkummaan walitti dabaalamanii jiru. Kabajni kun seenaa Itoophiyaa keessa kan dabran, Itoophiyaas kan hundeessan sabaa fi sab-lammootaaf qofaa kabaja kennamu dha. Eenyummaa ofii qaban irratti eenyummaa biraa dabalanii kan fudhatan kabaja guddaa dha.

Itoophiyummaan akka mooraa loonii Beeteeliheemitti wal-qoodinsa, wal-jibbuu fi wal- mufachuun kan keessaa badu, uumamni ishee tokko ta'anii kan keessa jiraatani dha. Tokkummaa kana diiguu fi diinummaa haaraa dhaabuudhaaf kan ifaajan kanneen akka Heeroodis jiraachuun isaanii waan hin hafne dha. Ifni moorittii isaan dhiphisa. Kabajni moorittiis isaan sodaachisa. Tokkummaan moorittii isaan quuqa. Jaalallii fi nagaan moorittii isaan ifata. Jaalala addaa kana, tokkummaa kana, nagaa fi jaalala kana qocholuuf Heediroosonni seefii isaanii ol-kaasu. Kiristoosis, dubree Maaramiinis, Yooseefis, Saloomeenis, tikseewwanis namoota aartiis hin argani. Seefii isaanii dheereffatanis kan milkaa'uf warra omaa hin beekne daa'imman Beeteeliheem irratti dha. Haadisaanonnis, Heeroodisaanonnis seefiin oduudhaan facaasan kan miidhu qaamaa qalbiin warra kichuu ta'an daa'amman qofaa dha. Kan dhumanii fi warri dhumaa jiranis daa'immani dha. Guddannee, barannee, maatii keenya gargaarra, lammii fi biyyaaf gumaachina jedhanii kan hawwan daa'immanii fi dargaggoota kan miidhamaa jiran.

Heeroodis akka fedhetti seefii isaa luqqifatus, daa'amman hagam iyyuu miidhu, rakkoo hagamiis dhaqqabsiisu, ergamaa fi imala Yesuss garuu gufachiisuu hin dandeenye. Heeroodis seenaa isaa badaa dheessee sokke. Kiristoos garuu ifaa kaayyooti. Ifti Beeteeliheemis addunyaafuu dhaqqabee jira. Nagaa fi dhiifamni Beeteeliheem addunyaaf gahee jira. Heroodas garuu hin jiru. Kanaafi Heroodosii fi warra isa fakkaatan waliin dhaabbachuun bu'aa yeroo irra kan darbe, waan itti-fufaa hin argamsiisu kan jennu. Lammilee mooraa keessaa ta'uun qormaata yeroorra kan ceesisu kabaja guddaa qabaata jennee kan amannu.

Beeteeliheemitti waggoota kuma lama dura kan uumame seenaa ajaa'ibaa yaadachuun, ammas waggaa waggaan miliyoononni Beeteeliheemitti imalu. Miidhaginaafi kennaaa sab- daneessummaan arganne qabannee, tokkummaa Itoophiyummaa keenya yoo jabeessine, garaagarummaan addaan bahuu, tokkummaan

wal-balleessuu akka hin taane yoo mirkaneessine, Heeroodisootarra ceenee, seenaa dhalootaaf iyyuu hafu hojjenna. Miliyoononnis seenaa kana ilaaluuf barri itti gara Itoophiyyaatti girrisan fagoo hin ta'u.

**Ayyaana Qillee gaarii.**





የአክሱም ማኅበረሰብ ተወካዮች ውይይት

# ከመጋቢት እስከ መጋቢት

መግለጫዎች እና መልእክቶች

ትግርኛ

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት

የካቲት
፳፻፲፫



## መልእኽቲ መዓልቲ ሰምኣታት ትግራይ

14 ሰነ 2011

### ዝኽበርኩም ስድራ ስዉኣትን፤ ዝኽበርካ ህዝቢ ትግራይን

ህዝቢ ትግራይ ንመዋእላት ምስ ካልኦት ኣሕዋቱን ኣሓቱን ህዝብታት ኢትዮጵያ ብምኳን በቲ ሓደ ወገን መግዛእታዊ ሓድነትን ሉዑላውንትን ሀገሩ ኢትዮጵያ ንምዕቃብ፤ በቲ ካልእ ወገን ድማ ኣብ ፍትሓዊ ሓድነት ዝተመስረተት ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን፣ ኣብ ፍትሕን መሰል ዓርሰ ውሳነ ዝተመርኮሰ ሓደ ናይ ፖለቲካን ቁጠባን ማሕበረ ሰብ( ብሄረ መንግስት)ንምፍጣር ሰፍ ዘይብል መስዋእትን ዝከፈለ ህዝቢ እዩ። ሕዝቢ ትግራይ ምዕርይትን ሓቛፊትን ኢትዮጵያ ንምህናፅ ምስ ካልኦት ወገናቱ ብምኳን ኣብ ዝገበሮ ተጋድሎ መስዋእቲ ንዝኮኑ ቀያሕትን ፀለምትን ደቁ ዝዝክረላን ዘክብረላን ዕለት ሰነ 15 መሪፁ ከኽብር ጸኒሑ ኣሎ። ሰነ 15 ዝመረፀሉ ምክንያት ኣብዘ ዕለት እዚ ብርክት ዝበለ ሕዝቢ ከተማ ሓውዜንን ከባቢኣን ሃገር ኣማን እዩ ኢሉ ናብ ዕዳጋ ኣብ ዝውፈሩሉ ኣጋጣሚ በጸሓይ ቀትሪ በነፍርቲ ውግእ ተደብዲቡ ዘተጨፍጨፈላ ዕለት እያ። ሕዝቢ ትግራይ መዓልቲ ሰማእታት ምክባሩ ግቡን ንቡረን እዩ። እንተኮነ ግና መዓልቲ ሰማእታትና እንትነክብር ንድሕሪት ተመሊስና ክንቁዝምን ክንነብዕን ዘይኮነስ፣ ንዕላማ ስውኣት ከይረሳዕና ኣብ ጽኑዕ መትከልን

ፍቶትን ዝተመሰረተ ሓደን ዘይነቓንቕን ናይ ፖለቲካን ቁጠባን ማሕበረ ሰብ ብምህናፅ ንመሰዋእቶም ንምድባስ እዩ።

**ክብርን ሞገስን ንሰማእታትና!**
**ሰላምን ብልጽግናን ንህዝብና**